፲፭: ደ ኝም: የተናገረው: ነገር: ሳይፈጸም: እነሆ: ወጣች: ርብቃ: የበቱኤል: ልጅ: የሚልካ: ልጅ: እር ስዋም: የናሆር: ምስት: የአብርሃም: ወንድም። በ ጫንቃዋ: ላይ: ማድጋዋን: ተሸክማ።

፲፮: ብላቴናዪቱም: እጅግ: መልኧ: ያማረ: ቀን ጀ: ነበረች: ወንድ: የማያውቃት። ወደ: ምንጭም: ወረደች:ማድጋዋንም:መላች:ተመልሳም:ወጣች።

፲፯፡ ሎሌውም፡ ፈጥኖ፡ ተገናኛት፡አለም። አለም ኀሳለሁ፡ ከማድጋሽ፡ ጥቂት፡ ውኃ፡ አጠጭኝ።

፲፰፡ አለችውም፡ጠጣ፡ጌታዬ፡ሆይ። ፈጥናም፡ማድጋዋን፡ ከጫንቃዋ፡ በጀዋ፡ አውርዳ፡ አጠጣችው።

፲፱፡ አርሱንም፡ ካጠጣች፡ በኋላ፡ አለች። ለግመሎችኝ፡ ደግሞ፡ ውኃ፡ አቀዳለሁ፡ሁሉ፡እስኪጠጡ፡ ድረስ።

፳፡ ውኃውንም፡ ከማድጋዋ፡ በማጠጪው፡ ኀለበጠችው፡ ፈጥናም፡ ወደ፡ ጕድጓዷ፡ ደግሞ፡ ልትቀዳ፡ ሔዳች። ለግመሎችም፡ ሁሉ፡ ውኃ፡ ቀዳች።

፳፩፡ አርሱም፡ ተደንቅ፡ ዝም፡ ብሎም፡ ደመለከታት፡ ነበር። ያውቅ፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ መንገዷን፡ አቅንተለት፡ እንደሆን፡ ወይም፡ አይደለም።

፳፪፤ ግመሎችም፡ ከጠጡ፡ በኋላ፡ ያሰው፡ የውርቅ፡ ጕትቻ፡ አወጣ፡ ሚሳኑ፡ የሚትቀል፡ አኩሌታ፡ ሁለትም፡ የወርቅ፡ አምባር፡ ለጀችዋ፡ ያሥር፡ ሚት ቃል።

፳፫፡ አላትም። አንች፡ የማን፡ ልጅ፡ ነሽ። ንገሪኝ፡ አለምንግለሁ። ባባትሽ፡ ቤት፡ የምንወርድበት፡ ሰፋራ፡ ይገኖልን።

፳፬፡ አለችውም። እኔ፡ የበቱኤል፡ ልጅ፡ ነኝ፡ የሚልካ፡ ልጅ፡ ለናሆር፡ የወለደችው።

፳፭፡ አለችውም፡ በኛ፡ ዘንድ፡ አጅግ፡ ገላባ፡ አጅግ፡ አበቅም፡ አለ፡ ለማደርያም፡ ደግሞ፡ ሰ�ፋራ፡ አለነ።

፳፮፡ ያሰውም፡ ወደቅ፡ ለእግዚአብሔርም፡ ሰገደ።

፳፯፡ አለም፡ እግዚአብሔር፡ ደመሰገን፡ የጌታዬ፡ የአብርሃም፡ አምላክ፡ ምሕረቱን፡ ጽድቁንም፡ ከጌታዬ፡ ያልተወ። እኔ፡ በመንገድ፡ ሳለሁ፡ እግዚአብሔር፡ ወደ፡ ጌታዬ፡ ወንድሞች፡ ቤት፡ መራኝ።

፳፰፡ ብላቴናዪቱም፡ ፈጠነች፡ በናትዋም፡ ቤት፡ ያሉንን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ አዉወተች።

፳፱፡ ለርብቃም፡ ወንድም፡ ነበራት፡ ስሙን፡ ላባን፡ የሚሉት። ላባንም፡ ወደዚያ፡ ሰው፡ ወደ፡ ምንጩ፡ ሲሮጥ፡ ወጣ።

፴፡ ጕትቻውንና፡ አምባሩንም፡ በእቱ፡ እጅ፡ ባየ፡ ጊዜ፡ የርብቃንም፡ የእቱን፡ ነገር፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ እንደ ሀ፡ ሰትል፡ ያሰው፡እንደሀ፡ አለኝ። አርሱ፡ ወደዚያ፡ ሰው፡ መጣ፡ እሀሞም፡ በውኃው፡ ምንጭ፡ አጠገብ፡ ቁሞ፡ ነበር፡ ከግመሎቹ፡ ጋራ።

፴፩፡ አለውም። ግባ፡ አንት፡ የእግዚአብሔር፡ ቡሩክ። ስለ፡ ምን፡ አንተ፡ በሚሂ፡ ቁመኻል። እኔም፡ ቤት፡ አዘጋጅሁልኝ፡ ሰፈራም፡ ለግመሎችኝ።

፴፪፡ ያሰውም፡ ወደ፡ ቤት፡ ገባ፡ ግመሎችንም፡ አረገፈ። ገለባና፡ አበቅም፡ ለግመሎች፡ ሰጣቸው። ውኃም፡ አቀረበ፡ እግሩን፡ ያታጠብ፡ ዘንድ፡ ከርሱ፡ ጋራም፡ ያሉትን፡ ሰዎች፡ አግር።

፴፫፡ መብልም፡ አቀረበለት፡ አርሱም፡ አለ። አልበላም፡ ነገሬን፡ አስክነግር፡ ድረስ። አለውም፡ ተናገር።

፴፬፡ አርሱም፡ አለ። እኔ፡ የአብርሃም፡ ሎሌ፡ነኝ።

፴፭፡ እግዚአብሔርም፡ጌታዬን፡ እጅግ፡ባረከው፡· አበለጠውም። በግም፡ ላምም፡ ሰጠው፡ ብርም፡ ወርቅም፡ የወንድ፡ ባሮችም፡ የሴት፡ ባሮችም፡ ግመሎችም፡ አህዮችም።

፴፮፡ ሳራም፡ የጌታዬ፡ ምስት፡ ወንድ፡ ልጅ፡ ለጌታዬ፡ ወለደች፡ በርጅናዋ። ያለውንም፡ ሁሉ፡ ሰጠው።

፴፯፡ ጌታዬም፡ አማለኝ፡ እንደህ፡ ሲል። እኔ፡ ካለሁባቸው፡ ከከነዓን፡ ወገን፡ ልጀች፡ ለልጂ፡ ምስት፡ አትውሰድ።

፴፰፡ ነገር፡ ግን፡ ወደባቴ፡ ቤት፡ ወደ፡ ወገኔም፡ ሒድ፡ ለልጂም፡ ምስት፡ ውሰድለት።

፴፱፡ ጌታዬንም፡ አልሁት። ቤቲቱ፡ እንቢ፡ ብትል፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ትመጣ፡ ዘንድ፡ ምን፡ ልስራ።

፵፡ አርሱም፡ አለኝ። አግዚአብሔር፡ እኔ፡ በፊቱ፡ የምሔደው፡ መልክተኛውን፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ይልካል፡ መንገድኽንም፡ ያቀናል። ለልጂም፡ ምስት፡ ትወሰ ደለኽ፡ ከወገኖቼ፡ ካባቴም፡ ቤት።

፵፩፡ የዚያን፡ ጊዜ፡ ከመሐላዬ፡ ንጹሕ፡ ነኽ፡ ወደ፡ ዘመደቼ፡ ስትመጣ፡ አርሳቸውም፡ ባያሰጡኽ። የዚያን፡ ጊዜ፡ ከመሐላዬ፡ ንጹሕ፡ ትሆናለኽ።

፵፪፡ ዛሬም፡ ወደ፡ ውኃው፡ ምንጭ፡ መጣሁ፡ አልሁም። ጌታ፡ ሆይ፡ የጌታዬ፡ የአብርሃም፡ አምላክ፡ መንገዷን፡ እኔ፡ የምሔድባትን፡ ዛሬ፡ አንት፡ ብታቀናልኝ።

፵፫፡ እነሆ፡ እኔ፡ በውኃው፡ ምንጭ፡ ላይ፡ ቁሚያለሁ። ውኃ፡ ልትቀዳም፡ ለምትመጣው፡ ቀንጂ፡ ስላት። ጥቂት፡ ውኃ፡ ከማድጋሽ፡ አጠጭኝ።

፵፬፡ የምትለኝም፡ አንተም፡ ጠጣ፡ ደግሞም፡ ለግመሎችኝ፡ አቀዳለሁ። እግዚአብሔር፡ ለጌታዬ፡ ልጅ፡ ያዘጋጀት፡ ሴት፡ አርስዋ፡ ትሁን።

፵፭፡ እኔም፡ የልቤን፡ መናገር፡ ሳልፈጽም፡ እነሆ፡ ርብቃ፡ ወጣች፡ ማድጋዋን፡ በጫንቃዋ፡ ተሸክማ። ወደ፡ ምንጭም፡ ወረደች፡ ውኃም፡ ቀደች። አጠጭኝም፡ አለምንግለሁ፡ አልኋት።

፵፮፡ ፈጥናም፡ ማድጋዋን፡ ከጫንቃዋ፡ አወረደች፡ አንተ፡ ጠጣ፡ አሉትኝ፡ ግመሎችኝንም፡ ደግሞ፡ አጠጣለሁ። እኔም፡ ጠጣሁ፡ ግመሎችንም፡ ደግሞ፡ አጠጣች።

፵፯፡ ጠየቅኋትም፡ አልኋትም፡ አንች፡ የማን፡ ልጅ፡ ነሽ። አለችም። እኔ፡ የበቱኤል፡ ልጅ፡ ነኝ፡ የናሆር፡ ልጅ፡ ሚልካ፡የወለደችለት። አንጥልጥልም፡ ሰቀ ልሁላት፡ ለፈትዋ፡ ጌዋ፡ አምባርም፡ ለእጅዋ።

፵፰፡ በግምባሬም፡ ወደቅሁ፡ ለእግዚአብሔር ም፡ ሰገድሁ፡ እግዚአብሔርንም፡ የአብርሃም፡ የጌታዬን፡ አምላክ፡ አመሰገንሁ፡ በቀኖ፡ መንገድ፡ የመ

ራኻን። የጌታዬን: የወንድሙን: ልጅ: ለልጂ: አወሰድ: ዘንድ።

፴፱: አሁንም: ቸርነት: አውነትም: ትሰራ: አንደ ሆን: ከጌታዬ: ከአብርሃም: ጋራ: አስታውቁኝ። ከዚኝ: ሌላም: ትሹ: አንደ: ሆን: ንገሩኝ። ወደ: ቀኝ: ወ ደ: ግራም: አል: ዘንድ።

፴፪: ላባንና: በቱኤልም: መለሱ: አሉም። ነገሩ: ከ እግዚአብሔር: ዘንድ: ወጥተዋል። አንደቸንም: ክ ፋ: ቢሆን: በጎም: ቢሆን: አንናገር ኝ: ዘንድ: አንች ልም።

፴፫: እነኋት: ርብቃ: በፊትኝ: ናት። ደዘኘት: ሒ ድ። ለጌታ ኝም: ልጅ: ምስት: ትሁን: እግዚአብሔ ር: እንደሉ።

፴፬: የአብርሃምም: ሎሌ: ነገራቸውን: በሰማ: ጊ ዜ: ለእግዚአብሔር: ሰግደ: ወደ: ምድር: ወደቀ።

፴፫: ሎሌውም: የብርና: የወርቅ: አቃ: አወጣ: ል ብስም: ለርብቃም: ሰጣት: የከበረ: ሰጥወታም: ለ ወንጅምዋና: ለናትዋ: አቀረበ።

፴፱: እርሱም: በላ: ጠጣ: ከርሱ: ጋራም: ያሉት: ሰዎች: ከዚያም: አደረ። ማልደውም: ተነሡ። አላ ቸውም: ሰደደኝ: ወደ: ጌታዬ: አሔድ: ዘንድ።

፴፰: ወንድምዋና: እናትዋም: መለሱ: አሉም። በላቴናዊቱ: አንድ: ወይም: አሥር: ቀን: ሰንሺ: ከ ኛ: ዘንድ: ትቀመጥ: ከዚያም: በኋላ: ትሔጂለች።

፴፯: አላቸውም። ያ: አታድርጉኝ: እግዚአብሔር: መንገጂን: አቅንተልኛልና። ሰደደኝ: ወደ: ጌታዬ: አሔድ: ዘንድ።

፴፮: አሉም። ብለቴናዊቱን: እንጽራን: ካፈዋ: አንጠይቅ።

፴፭: ርብቃንም: ጸርተው: አልዋት: ትሔጂን: ከ ዚኝ: ሰው: ጋራ። አለችም: አሔጀለሁ።

፴፬: ርብቃንም: አታቸውን: ሰደድዋት: ሞግዚ ትዋንም: ከአብርሃም: ሎሌ: ከሰዉቹም: ጋራ።

፴፫: ርብቃንም: መረቋት: አልዋትም። አንች: አታ ችን: ለአልፋ: አእላፋት: ሁኝ። ዘርሽም: የጸላተቹን: ደጅ: ይውረስ።

፴፩: ርብቃም: ተነሣች: ቀንጀችዋም: በግመሎ ች: ላይ: ተቀመጡ: ያንም: ሰው: ተከተሉት። ሎሌ ውም: ርብቃን: ወሰደና: ሔደ።

፴፪: ይስሐቅም: ሰምዋን: የሕያው: የሚያይ: ከሚልዋት: ምንጭ: ተመለሰ። በአዜብ: ምድር: ተ ቀምጦ: ነበረና።

፴፫: ደስሐቅም: ወደ: ሜዳ: ወጥት: ነበር: በመ ሸ: ጊዜ: በልቡ: ሊያስብ። ዓይናቹንም: አነሣ: አነሆ ም: ግመሎች: ሲመጡ: አየ።

፴፬: ርብቃም: ዓይናችዋን: አነሣች: ይስሐቅንም: አየች። ከግመልም: ወረደች።

፴፭: ሎሌውንም: አለችው። ይኝ: ሰው: ማነው: በሜዳ: የሚመጣ: ሊገ ናኘነ። ሎሌውም: አላት: አ ርሱ: ጌታዬ: ነው። አርስዋም: መሸፈኝ: ወሰደ: ተከ ናነበች።

፴፯: ሎሌውም: ለይስሐቅ: ነገረው: ባደረገው: ነ ገር: ሁሉ።

፴፰: ይስሐቅም: ወደናቱ: ወደ: ሳራ: ድንኳን: አ ገባት። ርብቃንም: ወሰደት: ምሽትም: ሆነችለት: ወ ደደትም። ይስሐቅም: ከናቱ: ሞት: በኋላ: ተጸናና።

ምዕራፊ: ፸፭:

፩: አብርሃምም: ደግሞ: ምሽት: አገባ ሰምዋን: ቁጡራ: የሚልዋት።

፪: አርስዋም: ዘምራንን: ወለደችለት: ያቅሻንን ም: መደንንም: ሚድያምንም: የሽቦቅንም: ሹሐ ንም።

፫: የቅሻንም: ሣባንንና: ድዳንን: ወለደ። የድዳን ም: ልጆች: አሹሪም: ለጡሺምም: ላውሚምም።

፬: የሚድያምም: ልጆች: ዔፋ: ዔፈርም: ንኦክ ም: አቢደዕም: ኤልደዓም። አሌኝ: ሁሉ: የቁጡ ራ: ልጆች: ናቸው።

፭: አብርሃምም: የገዛውን: ሁሉ: ለይስሐቅ: ሰጠ።

፮: ለቁባቶችም: ልጆች: ለአብርሃም: የነበረ: አ ብርሃም: ለያንጂንጂ: ሰጥወታ: ሰጣቸው። ከልጂ ም: ከይስሐቅ: ፊት: ሰደደቸው: እርሱ: ገና: ሕያ ው: ሳለ: ወደ: ጸሓይ: መውጫ: ወደ: ምሥራቅ: አ ገር።

፯: አብርሃምም: የኖረበት: የዕድሜው: አመታ ት: አሌኝ: ናቸው። መቶ: ከሰብዓ: አምስት: አ መት።

፰: አብርሃምም: ደከመ: ሞተም: በመልካም: ሸምግለና። ሸመገለም: ብዙ: ዘመንም: ጠገበ: ወ ደ: ወገኖቹም: ተከማቸ።

፱: ይስሐቅን: እስማኤልም: ልጆቹ: ቀበሩት: በ መክፈላ: ዋሻ: በሂፊሮን: በዞሀር: ልጅ: በሄታዊው: ወጀድ: ባለችው: በመምሬ: ፊት: ለፊት።

፲: አብርሃም: ከሄት: ልጆች: በገዛው: ወጀድ። ከ ዚያ: ተቀበረ: አብርሃም: ሳራም: ምሽቱ።

፲፩: አብርሃምም: ከሞተ: በኋላ: እግዚአብሔ ር: ልጂን: ይስሐቅን: ባረከው። ይስሐቅም: ተቀም ጦ: ነበር: የሕያው: የሚያይ: ምንጭ: በሚባል: ሰ ፈራ።

፲፪: ያ ኝ: ነው: የእስማኤል: ትውልድ: የአብር ሃም: ልጅ: የምስሪቱ: የሳራ: ባርያ: አጋር: ለአብርሃ ም: የወለደችው።

፲፫: የእስማኤልም: የልጆቹ: ስም: እንደ ህ: ነው: በየስማቸው: በየትውልዳቸውም።

፲፬: የእስማኤልም: የበኩር: ልጅ: ነባዩት: ነው። ቄደርም: አድብኤልም: መብሣምም።

፲፭፡ መሽማዕም፡ ዲማም፡ መሣም፡ ሀደረ፡ ቲማ ም፡ የጡርም፡ ነፌሽም፡ ቂድማም።

፲፯፡ አሌኝ፡ የእስማኤል፡ ልጆች፡ ናቸው፡ ስማቸ ውም፡ ደኝ፡ ነው፡ ባባራቸው፡ በከተሞቻቸውም። አሠራ፡ ሁለት፡ አለቆች፡ ለየወገኖቻቸው።

፲፯፡ እስማኤልም፡ የተቀመጠበት፡ የዕድሜው፡ ዘመን፡ መተ፡ ሠላሳ፡ ሰባት፡ አመት፡ ነው። ደከመ፡ ሞተም፡ ወደ፡ ወገኖቹም፡ ተከማች።

፲፰፡ መኖርያቸውም፡ ከሀዊላ፡ እስከ፡ ሹር፡ ነበረ፡ በምስር፡ ፊት፡ ለፊት፡ ወደ፡ አሶር፡ በምትወስደው፡ መንገድ። እንደሀም፡ በወንድሞቹ፡ ሁሉ፡ ፊት፡ ተ ቀመጠ።

፲፱፡ ደኝም፡ የይስሐቅ፡ የአብርሃም፡ ልጅ፡ ትው ልድ፡ ነው። አብርሃም፡ ይስሐቅን፡ ወለደ።

፳፡ ይስሐቅም፡ አርባ፡ አመት፡ ሲሆነው፡ ርብቃን፡ አገባ፡ የሶርያዊውን፡ የበቱኤልን፡ ልጅ፡ በሁለቱ፡ ወን ዝ፡ መኻከል፡የሚኖረውን። የላባንን፡የሶርያዊውን፡ እት።

፳፩፡ ይስሐቅም፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ጸለየ፡ ስ ለ፡ ምሽቱ፡ መካን፡ ነበረችና። እግዚአብሔርም፡ ተ ለመነው፡ ርብቃም፡ ምሽት፡ ፀነሰች።

፳፪፡ ልጆችም፡ በሆድዋ፡ ይፋገጡ፡ ነበር። አለች ም እንደሀስ፡ ቢሆንልኝ፡ ለምን፡ እኔ፡ እንደሀ፡ ነበ ርሁ። ከእግዚአብሔርም፡ ትጠይቅ፡ ዘንድ፡ሔደች።

፳፫፡ እግዚአብሔርም፡ አላት። ሁለት፡ ወገኖች፡ በማሕፀንሽ፡ ናቸው፡ ሁለትም፡ ሕዝብ፡ ከሆድሽ፡ ይ ከፈላሉ። ሕዝብም፡ ከሕዝብ፡ ይበረታል፡ ታላቁም፡ ለታናሹ፡ ይገዛል።

፳፬፡ ዘመንዋ፡ ተፈጸመ፡ ትወልድ፡ ዘንድ። እነሆ ም፡ በሆድዋ፡ መንታ፡ ነበር።

፳፭፡ በፊትም፡ የወጣው፡ ቀይ፡ ነበረ፡ ሁለንትና ውም፡ ጸጕር፡ እንደ፡ ጸጕር፡ ልብስ፡ ነበር። ስሙም፡ ሏሳው፡ ተባለ።

፳፮፡ ከዚኽም፡ በኋላ፡ ወንድሙ፡ ወጣ፡ እጁን፡ የሏሳውን፡ ተረከዝ፡ ይዞ፡ ነበረ። ያዕቀብም፡ ብሎ፡ ጸራው። ለይስሐቅም፡ ሰድሳ፡ አመት፡ ሁኖት፡ ነበረ፡ በተወለደለት፡ ጊዜ።

፳፯፡ ብላቴኖችም፡ አደጉ። ሏሳውም፡ ማድን፡ የ ሚያውቅ፡ የበረሀ፡ ሰውም፡ ሆነ። ያዕቀብ፡ ግን፡ ጭ ምት፡ ሰው፡ ነበረ፡ በድንኳንም፡ ይቀመጥ፡ ነበር።

፳፰፡ ይስሐቅም፡ ሏሳውን፡ ይወድ፡ ነበረ። ካደነ ው፡ ይበላ፡ ነበርና። ርብቃ፡ ግን፡ ያዕቀብን፡ ትወድ፡ ነ በረች።

፳፱፡ ያዕቀብም፡ ወጥ፡ ሰራ። ሏሳውም፡ ከበረሀ፡ ደክሞ፡ ገባ።

፴፡ ሏሳውም፡ያዕቀብን፡አለው። ከቀዩ፡ ከዚኝ፡ ወጥ፡ አብላኝ። እኔ፡ እጅግ፡ ደክሚያለሁና። ሰለዚ ኝ፡ ስሙ፡ ኤደም፡ ተባለ።

፴፩፡ ያዕቀብም፡ አላው፡ ብኵርናኽን፡ ዛሬ፡ ሸጥ ልኝ።

፴፪፡ ሏሳውም፡ አለ፡ እነሆ፡ እኔ፡ ከሞትሁ፡ ደኝ ቺ፡ ብኵርና፡ ለምኔ፡ ናት።

፴፫፡ ያዕቀብም፡ አለው፡ ማልልኝ፡ ዛሬ። ማለለ ትም። ብኵርናውንም፡ ለያዕቀብ፡ ሸጠ።

፴፬፡ ያዕቀብም፡ ለሏሳው፡ እንጅራና፡ ምስር፡ ወ ጥ፡ ሰጠው። በላም፡ ጠጣም፡ ተነሣም፡ ሔደም። እ ንደሀም፡ ሏሳው፡ ብኵርናውን፡ ቸል፡ አላት።

ምዕራፍ፡ ፳፮፡

፩፡ በምድርም፡ ራብ፡ ሆነ፡ ቀድሞ፡ በአብርሃም፡ ዘመን፡ ከሆነው፡ ራብ፡ ሌላ። ይስሐቅም፡ ወደ፡ ፌል ስጥኤም፡ ንጉሥ፡ ወደ፡ አቢሜልክ፡ ሔደ፡ ወደ፡ ግ ራራ።

፪፡ እግዚአብሔርም፡ ታየው፡ አለውም። ወደ፡ ምስር፡ አትውረድ። እኔ፡ በምልኽ፡ ምድር፡ ተቀመ ጥ፡ እንጅ።

፫፡ በዚች፡ ምድር፡ ተቀመጥ፡ ካንት፡ ጋራም፡ እሆ ናለሁ፡ አባርክኽማለሁ። ደኝንችን፡ ምድር፡ ሁሉ፡ ላ ንተ፡ አሰጠለሁና፡ ለዘር፡ኽም፡ ለአብርሃምም፡ ላባ ትኽ፡ የማልሁትን፡ መሐላ፡ አፈጽማለሁ።

፬፡ ዘር፡ኽንም፡ አበዛለሁ፡ እንደ፡ ሰማይ፡ ከዋክብ ት፡ ደኝንችንም፡ ምድር፡ ሁሉ፡ ለዘር፡ኽ፡ አሰጣለሁ፡ የምድርም፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡ በዘር፡ኽ፡ ይባረካሉ።

፭፡ አብርሃም፡ ቃሌን፡ ሰምትዋልና፡ ያዘዝሁትን ም፡ ትእዛዜን፡ ጠብቋልና፡ ፍርዷንም፡ ሕጌንም።

፮፡ ይስሐቅም፡ በግራራ፡ ተቀመጠ።

፯፡ የዚያም፡ ስፈራ፡ ሰዎችም፡ ስለ፡ ምሽቱ፡ ጠየ ቁት፡ እርሱም፡ እቴ፡ ናት፡ አለ። ምሽቴ፡ናት፡ማለት፡ ፈርትዋልና። የዚኽ፡ ስፈራ፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ርብቃ፡ እ ንደያገሉኝ፡ ብሎ። እርስዋ፡ ውብ፡ ነበረችና።

፰፡ ብዙ፡ ቀንም፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ እርሱም፡ ከዚያ፡ ተ ቀምጦ፡ ሳለ፡ አቢሜልክ፡ የፌልስጥኤም፡ ንጉሥ፡ ጐ በ፡ በመስኮት፡ ሁኖ። ይስሐቅም፡ ርብቃን፡ ምሽቱ ን፡ ሲያፌት፡ አየ።

፱፡ አቢሜልክም፡ ይስሐቅን፡ ጸራ፡ አለውም። እ ነሆ፡ ምሽትኽ፡ እንደ፡ ሆነች፡ ታወቀች። እንጂትስ፡ እቴ፡ ናት፡ አልኽ። ይስሐቅም፡ አለው። በርስዋ፡ም ክንያት፡ እንደሚሞት፡ ብዬ።

፲፡ አቢሜልክም፡ አለ። ደኝ፡ ያደረግህብኑ፡ ምን ድር፡ ነው። ጥቂት፡ ቀረ፡ ከሕዝብም፡ አንድ፡ ሰው፡ ከምሽትኽ፡ ጋራ፡ ይተኛ፡ ነበር፡ ኃጢአትም፡ ታመጣ ብን፡ ነበር፡ኽ።

፲፩፡ አቢሜልክም፡ ሕዝቡን፡ ሁሉ፡ አዘዘ፡ እንደ ኽ፡ ሲል። ወደዚኽ፡ ሰው፡ ወደ፡ ምሽቱም፡ የደረሰ፡ ፍጹም፡ ሞት፡ ይመት።

፲፪፡ ይስሐቅም፡ በዚያች፡ ምድር፡ ዘር፡ ዘራ። በዚ

ያች፡ አመትም፡ መተ፡ አጽፈ፡ አገኘ፡ እግዚአብሔር፡ ባረከዋልና።

፲፫፡ ባለጠጋ፡ ሰውም፡ ሆነ፡ እጥመረም፡ ደበዛ፡ ነበር፡ እጅግ፡ እስኪበልጥ፡ ድረስ።

፲፬፡ የበግና፡ የላምም፡ ከብት፡ ሀነለት፡ እጅግም፡ ሎላልተች፡ ስለዚህም፡ የፈልስጥኤም፡ ሰዎች፡ ቀኑ በት።

፲፭፡ ያባቱም፡ ሎላልት፡ የማስዋትን፡ ጉድጓድ፡ ሁሉ፡ ባባቱ፡ በአብርሃም፡ ዘመን፡ የፈልስጥኤም፡ ሰ ዎች፡ ደፈኑ፡ አፈርም፡ መሉባት።

፲፮፡ አቢሜልክም፡ ይስሐቅን፡ አለው፡ ከኛ፡ ወጥ ተኽ፡ ሒድ። ከኛ፡ ይልቅ፡ እጅግ፡ በርትተኻልና።

፲፯፡ ይስሐቅም፡ ከዚያ፡ ወጥተ፡ ሔደ። ወደ፡ ግራ ራም፡ ወንዝ፡ ወረደ፡ ከዚያም፡ ተቀመጠ።

፲፰፡ ይስሐቅም፡ ባባቱ፡ በአብርሃም፡ ዘመን፡ የቆ ፈርዋትን፡ ጉድጓድ፡ ሁሉ፡ ደግሞ፡ አሰቀ፡ፈረ። አብ ርሃም፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ የፈልስጥኤም፡ ሰዎች፡ ደፈ ንዋት፡ ነበረና። አባቱም፡ በጸራት፡ ስም፡ ጸራት።

፲፱፡ የይስሐቅም፡ ባሮች፡ በቀላ፡ ምድር፡ ቁፈረ። ከዚያም፡ የሚፈላ፡ የውኃ፡ ምንጭ፡ አገኙ።

፳፡ የግራራም፡ አረኞች፡ ከይስሐቅ፡ አረኞች፡ ጋ ራ፡ ተከራከሩ፡ እንደህ፡ ሲሉ፡ ውኃው፡ የኛ፡ ነው። የዚያን፡ ጉድጓድም፡ ስም፡ ፀብ፡ አለው፡ ስለርሱ፡ ተጻልተውታልና።

፳፩፡ ሌላ፡ ጉድጓድም፡ ማሱ፡ ስለርስዋም፡ ደግ ሞ፡ ተጻሉ።

፳፪፡ ስምዋንም፡ ክርክር፡ አላት። ከዚያም፡ ተነ ሣ፡ ሌላም፡ ጉድጓድ፡ ማሰ፡ ስለርስዋም፡ አልተጻ ሉም። ስምዋንም፡ ሰፈት፡ብሎ፡ጸራት፡እንደህ፡ሲ ል። ዛሬ፡ እግዚአብሔር፡ አሰፈልነ፡ በምድርም፡ እ ንበዛለን።

፳፫፡ ከዚያም፡ ሰፍራ፡ ወደ፡ ቤርሰባዕ፡ ወጣ።

፳፬፡ በዚያችም፡ ሌሊት፡ እግዚአብሔር፡ ተገለጠ ለት፡ እንደህ፡ ሲል። እኔ፡ ያባትኽ፡ የአብርሃም፡ አ ምላክ። አትፈራ፡ እኔ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ነኝና። አባርክኽ ማለሁ፡ ዘርኽንም፡ አበዛለሁ፡ ስለ፡ አብርሃም፡ ስለ፡ ባርያዬ።

፳፭፡ ከዚያም፡ መሠውያ፡ ሰራ፡ የእግዚአብሔር ነም፡ ስም፡ ጸራ፡ ድንጊንም፡ ከዚያ፡ ተከለ። ከዚያ ም፡ የይስሐቅ፡ ሎላልተች፡ ጉድጓድ፡ ማሱ።

፳፮፡ አቢሜልክም፡ ወደርሱ፡ ሔደ፡ ከግራራ። አ ሁዛትም፡ ወደጀ፡ ፈኮልም፡ የሠራዊቱ፡ አለቃ።

፳፯፡ ይስሐቅም፡ አላቸው። ለምን፡ ወደኔ፡ መጣ ችሁ፡ ወደ፡ ጸላችሁኝ፡ ሰው፡ ከላንተም፡ ለያታችሁ፡ አወጣችሁኝ።

፳፰፡ አሉም። እግዚአብሔር፡ ካንተ፡ ጋራ፡ እንደ ሉ፡ በጠም፡ አየነ። ስለዚኽም፡ አልነ፡ በኛ፡ መኻከ ል፡ መሐላ፡ ይሁን። በኛና፡ ባንተ፡ መኻከል። ኪደን ም፡ ካንተ፡ ጋራ፡ እናድርግ፡

፳፱፡ አንተ፡ ክፈ፡ እንደትሰራብኔ፡ እኛ፡ አንተን፡ እንደልነካነህ፡ ነገር፡ ግን፡ በጉነት፡ ብቻ፡ አሳዋነህ፡ በደ ኅናም፡ ሰደድነኽ። አንተም፡ አሁን፡ ከእግዚአብሔ ር፡ ዘንድ፡ የተባረክኽ፡ ነኽ።

፴፡ ይስሐቅም፡ ምሳ፡ አደረገላቸው፡ በሉም፡ ጠ ጡም።

፴፩፡ ማልደውም፡ ተነሡ፡ እርሱ፡ በርሳቸውም፡ ተማማሉ። ይስሐቅም፡ ሰደደቸው፡ ከርሱም፡ ወጥ ተው፡ በደኅና፡ ሔደ።

፴፪፡ በዚያም፡ ቀን፡ የይስሐቅ፡ ባሮች፡ መጡ፡ ስ ለ፡ ቆፈርዋትም፡ ጉድጓድ፡ ነገሩት፡ አሉትም፡ ውኃ፡ አገኘን።

፴፫፡ መሐላም፡ ብሎ፡ ጸራት። ስለዚኽ፡ ያገሬቱ፡ ስም፡ ቤርሰባዕ፡ ነው፡ እርሱም፡ የመሐላ፡ ጉድጓድ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ።

፴፬፡ ኤሳው፡ ግን፡ አርባ፡ አመት፡ ሲሆነው፡ ምስ ት፡ አገባ፡ የሁቲትን፡ የኤታዊውን፡ የብኤሪን፡ ልጅ። ባስማትንም፡ የኤታዊውን፡ የኢሎንን፡ ልጅ።

፴፭፡ አሌኽንም፡ የይስሐቅንና፡ የርብቃን፡ ልብ፡ ያ ሳዘኑ፡ ነበረ።

ምዕራፍ፡ ፴፯፡

፩፡ ይስሐቅም፡ ሸመገለ፡ ዓይናቹም፡ ደከሙ፡ ማ የትም፡ ተሳነው። ኤሳውንም፡ ታላቁን፡ ልጂን፡ ጸራ፡ አለውም፡ ልጂ፡ ሆይ። እርሱም፡ አለ፡ እነሆኝ፡ እኔ።

፪፡ አለውም፡ እነሆ፡ እኔ፡ ፈጽሚ፡ አረጀሁ። የም ሞትበትን፡ ቀን፡ አላውቅም።

፫፡ አሁንም፡ ማያኖህን፡ ውሰድ፡ የፈላፀኽንን፡ አፎት፡ ቀስትኽንም፡ ወደ፡ ምድረ፡ በሂም፡ ውጣ፡ አ ድነኽም፡ አውረ፡ አምጣልኝ።

፬፡ የጸፈጠም፡ መብል፡ እኔ፡ እንደምወደው፡ አዘ ጋጅተህ፡ አምጣልኝ፡ እበላ፡ ዘንድ። ሰውነቴም፡ እን ድትባርክኽ፡ ሳልሞት።

፭፡ ርብቃም፡ ሰማች፡ ይስሐቅ፡ ለኤሳው፡ ለልጂ፡ ሲነግር። ኤሳውም፡ ወደ፡ ምድረ፡ በሂ፡ ሔደ፡ ሊያደ ን፡ የታደነውንም፡ ሊያመጣ።

፮፡ ርብቃም፡ ያዕቀብን፡ ልጅዋን፡ አለችው። እነ ሆ፡ አባትኽ፡ ለወንድምኽ፡ ለኤሳው፡ ሲነግረው፡ ሰ ማሁ፡ ሲለውም።

፯፡ አውረ፡ አድነኽ፡ አምጣልኝ፡ የምወደውን ም፡ መብል፡ አድርግልኝ። በልቼም፡ ልባርክኽ፡ በእግ ዚአብሔር፡ ፊት፡ ሳልሞት።

፰፡ አሁንም፡ ልጂ፡ ሆይ፡ እሺ፡ በለኝ፡ እኔ፡ በማዝ ኽ፡ ነገር።

፱፡ ወደ፡ መንጋ፡ ሒድ፡ የፈየልም፡ ሁለት፡ መልካ ም፡ ጥቦቶች፡ አምጣልኝ። እርሳቸውንም፡ ለባትኽ፡ መብል፡ አደርጋለሁ፡ እንደሚወደው።

፲፡ ላባትኽንም፡ ታገላለታለኽ፡ ይበላ፡ ይባርክኽ ም፡ ዘንድ፡ ሳይሞት።

፲፭፡ ያዕቀብም፡ ርብቃን፡ እናቱን፡ አላት። እነሆ፡ ዔሳው፡ ወንድሜ፡ ጸጕራም ሰው፡ ነው፡ እኔም፡ ለ ስላሳ፡ ነኝ።

፲፮፡ አባቴም፡ ምናልባት፡ ቢደሰኝ፡ እንደሚያላግ ድበት፡ እንደልሆን፡ በርሱ፡ ዘንድ። መርገምም፡ በላ ዬ፡ እመጣለሁ፡ በረከትም፡ አደደለም።

፲፫፡ እናቱም፡ አለችው፡ መርገመኝ፡ በኔ፡ ላይ፡ ደ ሁን፡ ልጄ፡ ሆይ። ነገር፡ ግን፡ ቃሌን፡ ብቻ፡ ሰማ፡ ሒደ ኝም፡ ያልሁኝን፡ አምጣልኝ።

፲፬፡ ሒደም፡ አመጣ፡ለናቱም፡ ሰጣት። እናቱም፡ መብሉን፡ አዘጋጀች፡ አባቱ፡ የሚወደውን።

፲፭፡ ርብቃም፡ ከርሰዋ፡ ዘንድ፡ በቤት፡ የነበረችው ን፡ መልካሚቱን፡ የታላቁን፡ ልጅዋን፡ የዔሳውን፡ ል ብስ፡ አመጣች፡ ያዕቀብንም፡ ታናሹን፡ ልጅዋን፡ አለ በሰችው።

፲፮፡ የጥቦቶቹንም፡ ለምድ፡ በጀቹ፡ ለስላስ፡ ባንገ ቱም፡ ላይ፡ ጠመጠመች።

፲፯፡ አንጅራን፡ የሰራችውንም፡ መብል፡ ለልጅዋ፡ ለያዕቀብ፡ በጂ፡ ሰጠችው።

፲፰፡ ወደባቱም፡ ገባ፡ አለም፡አባቴ፡ ሆይ። አለም፡ እኔ፡ እነሆኝ። ማነኝ፡አንተ፡ ልጂ፡ ሆይ።

፲፱፡ ያዕቀብም፡ አባቱን፡ አለ፡ እኔ፡ ዔሳው፡ የበኩ ር፡ልጅኝ፡ ነኝ። እንደዘዝኸኝ፡ አደረግሁ። ተነሣና፡ ተቀመጥ፡ አለምንኝለሁ፡ ካደንሁትም፡ ብላ፡ ሰው ነትኝ፡ እንድትባርከኝ፡ ዘንድ።

፳፡ ይስሐቅም፡ ልጂን፡ አለው። እንዲት፡ ፈጥነ ኝ፡ ደኽነን፡ አገኙኝ፡ ልጂ፡ ሆይ። አለም፡ እግዚአ ብሔር፡ አምላክኝ፡ ወደኔ፡ አስመጥተታልና።

፳፩፡ ይስሐቅም፡ ያዕቀብን፡ አለው። ወደዚኝ፡ ቅረብ፡ እደስኝ፡ ዘንድ፡ ልጂ፡ ሆይ። አንተ፡ ዔሳው፡ ልጂ፡ አንደ፡ ሆንኝ፡ ወይስ፡ አደደለኝም።

፳፪፡ ያዕቀብም፡ ወደ፡ ይስሐቅ፡ ወደባቱ፡ ቀረበ፡ ደሰሰውም፡ አለም። ድምፅ፡ የያዕቀብ፡ ድምፅ፡ ነ ው፡ እጀች፡ ግን፡ የዔሳው፡ እጀች፡ ናቸው።

፳፫፡ አላወቀውምም፡ እጀች፡ ጸጕር፡ የበዛባቸ ው፡ ነበረና፡ እንደ፡ ወንድሙ፡ እንደ፡ ዔሳው፡ እጀ ች። ባረከውም።

፳፬፡ አለውም፡ አንተን፡ ነኝ፡ ልጂ፡ ዔሳው። አለ ም፡ እኔ፡ ነኝ።

፳፭፡ አለውም። አቅርብልኝ፡ ከልጂም፡ አደን፡ ል በላ፡ ነፍሴ፡ ትበርክኝ፡ ዘንድ። አቀረበለትም፡ በላ ም። የወደን፡ ጀጅም፡ አመጣለት፡ጠጣም።

፳፮፡ ይስሐቅም፡ አባቱ፡ አለው፡ ወደኔ፡ ቅረብ፡ ሳ መኝም፡ ልጂ፡ ሆይ።

፳፯፡ ወደደቡም፡ ቀረበ፡ ሳመውም። የልብሱን ም፡ ሽታ፡ አሸተተ፡ ባረከውም፡ አለም። እነሆ፡ የል ጂ፡ ሽታ፡ እንደርግ፡ ሽታ፡ ነው፡ እግዚአብሔር፡ የባ ረከው።

፳፰፡ እግዚአብሔርም፡ ከሰማይ፡ ጠል፡ ደስጥ ኝ፡ ከምድርም፡ ሰብ። የሰንደንም፡ ብዛት፡ የወይ ንንም።

፳፱፡ አሕዛብ፡ ደገዙልኝ፡ ወገኖችም፡ ይሰገደል ኝ። የወንድሞችኝ፡ ጌታ፡ ሁን፡ የናትኝም፡ ልጅች፡ ይሰገደልኝ። የሚረግመኝ፡ አርሱ፡ ርጉም፡ ነው፡ የ ሚባርክኝም፡ ቡሩክ፡ ነው።

፴፡ ይስሐቅም፡ ያዕቀብን፡ ባርኮ፡ ከፈጸመ፡ በኋ ላ፡ ያዕቀብም፡ አሁን፡ ካባቱ፡ ከይስሐቅ፡ ፊት፡ ከወ ጣ፡ በኋላ፡ የዚያን፡ ጊዜ፡ ዔሳው፡ ከማደኑ፡ መጥተ ገባ።

፴፩፡ አርሱም፡ ደግሞ፡ ካደነው፡ መብል፡ አዘጋጀ፡ ላባቱም፡ ደዘለት፡ መጣ። አባቱንም፡አለው። አባቴ፡ ይነሣ፡ ከልጂም፡ አደን፡ ይብላ፡ ሰውነትኝ፡ ትባርከ ኝ፡ ዘንድ።

፴፪፡ ይስሐቅም፡ አባቱ፡ አለው፡ አንተ፡ ማነኝ። አርሱም፡ አለ፡ እኔ፡ ዔሳው፡ ነኝ፡ የበኽር፡ ልጅኝ።

፴፫፡ ይስሐቅም፡ አጅግ፡ ፈርተ፡ ተንቀጠቀጠ፡ እ ለም። ማነው፡ አደኙ፡ ደደነልኝ፡ ወደነሰ፡ አገብተ፡ ከ ሁሉ፡ ደበላኝ፡ አንተ፡ ሳትመጣ፡ የባረክሁትስ። ዮተ ባረከም፡ ሆኖ፡ ደኖራል።

፴፬፡ ዔሳውም፡ የይስሐቅን፡ ደባቱን፡ ነገር፡ በሰ ማ፡ ጊዜ፡ ታላቅ፡ አጅግም፡ መራራ፡ ጩኸት፡ ጮኸ። አባቱንም፡ አለው። እኔንም፡ ደግሞ፡ ባርከኝ፡ አባቴ፡ ሆይ።

፴፭፡ አለም፡ ወንድምኽ፡ በተንኰል፡ መጥተ፡ በ ረከትኽን፡ ወሰደ።

፴፮፡ ዔሳውም፡ አለ። በውነት፡ ስሙ፡ ደዕቀብ፡ ተባለ፡ ሁለተግዜ፡ ሸንግሎኖልና። በኵሪነቴን፡ ከወሰ ደ፡ በኋላ፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ በረከቴን፡ ወሰደ። አለም፡ ከ ተ፡ ለኔ፡ በረከት፡ አላስቀረኽልኝምን።

፴፯፡ ይስሐቅም፡ መለሰ፡ ለዔሳውም፡ አለ። እነ ሆ፡ ጌታኽ፡ አደረግሁት፡ ወንድሞቹንም፡ ሁሉ፡ ለር ሱ፡ ባሮች፡ ደሆኑ፡ ዘንድ፡ ሰጠሁት፡ በሸንደም፡ በወ ደንፅም፡ አበረታሁት። ላንተም፡ ምን፡ ላድርግልኝ፡ ልጂ፡ ሆይ።

፴፰፡ ዔሳውም፡ አባቱን፡አለው። አንዲት፡ በረከ ት፡ ብቻን፡ ናት፡ ያለችኝ፡ አባቴ፡ ሆይ። እኔንም፡ ደግ ሞ፡ ባርከኝ፡ አባቴ፡ ሆይ። ዔሳውም፡ ድምፁን፡ አን ሠተ፡ አለቀሰ።

፴፱፡ ይስሐቅም፡ አባቱ፡ መለሰ፡ አለውም። እነ ሆ፡ መኖርያኝ፡ በምድር፡ ሰባት፡ ይሆናል፡ ከሰማደ ም፡ ጠል፡ ከላይ።

፵፡ በሰይፍኽም፡ትመገባለኽ፡ለወንድምኽም፡ ትገዛለኽ። ከዚያም፡ በኋላ፡ ስትቃወመው፡ ቀምበ ሩን፡ ሰብረኽ፡ ካንገትኽ፡ ትጥላለኽ።

፵፩፡ ዔሳውም፡ በያዕቀብ፡ ቂም፡ ያዘበት፡ አባቱ፡ ስለ፡ ባረከው፡ በረከት፡ ዔሳውም፡ በልቡ፡ አለ። የል ቅሶ፡ ቀን፡ ስላባቴ፡ ቀርብዋል፡ ያዕቀብንም፡ ወንድ ሜን፡ እገላለሁ።

፴፱፤ ይኽም፡ የዔሳው፡ የታላቁ፡ ልጅዋ፡ ነበር፡ ለ ርብቃ፡ ደረሰላት። ያዕቀብንም፡ ታናሹን፡ ልጅዋን፡ አ ስጠርታ፡ አሰመጣችው፡ አለችውም። እነሆ፡ ዔሳው፡ ወንድምኽ፡ ተበቀሎሃል፡ ሊገልኽ።

፵፫፤ አሁንም፡ ልጄ፡ ሆይ፡ ቃሌን፡ ስማ። ተነሣና፡ ወደ፡ ወንድሜ፡ ወደ፡ ላባን፡ ሒድ፡ ወደ፡ ካራን።

፵፬፤ ከዚያም፡ አያሌ፡ ቀን፡ ተቀመጥ፡ የወንድ ምኽ፡ ሞጣ፡ እስኪመለስ፡ ድረስ።

፵፭፤ የወንድምኽ፡ ሞጣ፡ ካንት፡ እስኪመለስ፡ ድረስ፡ ያደረግኽበቱንም፡ እስኪረሳ፡ ድረስ። ከዚያ ም፡ ልኬ፡ አስመጣኻለሁ። ባንድ፡ ቀን፡ ሁለታችሁ ን፡ አንደላጣ።

፵፮፤ ርብቃም፡ ደስሐቅን፡ አለችው። ልቤ፡ በሕ ይወቴ፡ ደከመ፡ ስለ፡ ሄት፡ ሴቶች፡ ልጆች፡ አንደለዚ ኽ፡ አንደገሪቱ፡ ልጆች፡ ካሉ። በሕይወት፡ መኖር፡ ለ ምኔ፡ ነው።

ምዕራፍ፡ ፳፰፡

፩፤ ደስሐቅም፡ ያዕቀብን፡ ጸራው፡ ባረከውም፡ አንደህ፡ ሲልም፡ አዘዘው። ከከነዓናውያን፡ ልጆች፡ ምስት፡ አታግባ።

፪፤ ተነሣና፡ ሒድ፡ ወደ፡ ሁለቱ፡ ወንዝ፡ መኻከል፡ ወደ፡ በቱኤል፡ ቤት፡ ወደያቶኽ፡ አባት። ከዚያም፡ ተጋባ፡ ከላባን፡ ልጆች፡ ከያትኽ፡ ወንድም።

፫፤ አምላክም፡ ሁሉን፡ የሚችል፡ ደባርክኽ፡ ያፈ ራኽም፡ ያብዛኽም፡ ለብዙ፡ ሕዝቦች፡ ጉባዔ፡ ትሆ ን፡ ዘንድ።

፬፤ የአብርሃምንም፡ በረከት፡ ደሰጥኽ፡ ላንተ፡ ለ ዘርኽም፡ ካንተ፡ ጋራ። ስደተኛ፡ ሁነኽ፡ ተቀምጠኽ ባት፡ ያለችውን፡ ምድር፡ ትወርሰ፡ ዘንድ፡ እግዚአብ ሔርም፡ ለአብርሃም፡ የሰጣትን።

፭፤ ደስሐቅም፡ ያዕቀብን፡ ሰደደው፡ ወደ፡ ሁለቱ፡ ወንዝም፡ መኻከል። እርሱም፡ ሔደ፡ ወደ፡ ላባን፡ የ ሶርያዊ፡ የበቱኤል፡ ልጅ፡ የርብቃ፡ ወንድም፡ የያዕቀ ብን፡ የዔሳው፡ እናት።

፮፤ ዔሳውም፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ደስሐቅ፡ ያዕቀብን፡ አን ደ፡ ባረከ፡ ወደ፡ ሁለት፡ ወንዝም፡ መኻከል፡ እንደ፡ ሰደደው፡ ወደ፡ ሶርያ፡ አገር፡ ከዚያ፡ ምስት፡ ያገባ፡ ዘ ንድ። በባረከውም፡ ጊዜ፡ እንደዘዘው፡ አንደህ፡ ሲ ል፡ ከከነዓን፡ ወገን፡ ልጆች፡ ምስት፡ አታግባ።

፯፤ ያዕቀብም፡ ያባቱንና፡ የናቱን፡ ነገር፡ እንደ፡ ሰ ማ፡ ወደ፡ ሁለቱ፡ ወንዝም፡ መኻከል፡ እንደ፡ ሔደ።

፰፤ ዔሳውም፡ ባየ፡ ጊዜ፡ የከነዓናውያን፡ ልጆች፡ ባ ባቱ፡ በደስሐቅ፡ ዘንድ፡ የተጸሉ፡ እንደ፡ ሆኑ።

፱፤ ዔሳው፡ ወደ፡ አስማኤል፡ ሔደ፡ መህላትን ም፡ አገባ፡ የአስማኤልን፡ ልጅ፡ የአብርሃምን፡ የል ጀጌ፡ ልጅ፡ የነባዮትን፡ እት፡ ምስት፡ ትሆነው፡ ዘን ድ፡ ካሉት፡ ከሴቶች፡ ጋራ።

፲፤ ያዕቀብም፡ ከቤርሳባዕ፡ ወጣ፡ ወደ፡ ካራንም፡ ሔደ።

፲፩፤ ወደንድ፡ ሰፈራም፡ መጣ፡ ከዚያም፡ አደረ። ፀሐይ፡ ገብታ፡ ነበራችና። ከዚያም፡ ሰፈራ፡ ደንጎች፡ ወሰደ፡ ከራሱ፡ በታችም፡ ተንተርሶ፡ በዚያው፡ ሰፈ ራ፡ ተኛ።

፲፪፤ ሕልምም፡ አየ፡ እነሆም፡ መሰላል፡ በምድር፡ ላይ፡ ተተክሎ፡ራሱም፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ደርሶ፡እነሆም፡ የእግዚአብሔር፡ መልክተኖች፡ ደወጡ፡ ደወርዱበ ትም፡ ነበር።

፲፫፤ እነሆም፡ እግዚአብሔር፡ በላዩ፡ ቁሞበት፡ ነ በር፡ አለም። እኔ፡ እግዚአብሔር፡ የአብርሃም፡ ያባ ትኽ፡ አምላክ፡ ነኝ፡ የደሰሐቅም፡ አምላክ። ደኽች ን፡ አንተ፡ ተኝተኽባት፡ ያለኽተን፡ ምድር፡ ላንተ፡ አ ሰጣለሁ፡ ለዘርኽም።

፲፬፤ ዘርኽም፡ እንደ፡ ምድር፡ አሻዋ፡ ደሆናል። ት ሰፈማለኽ፡ እስከ፡ ምዕራብ፡ እስከ፡ ምሥራቅም፡ እስከ፡ ሰሜን፡ እስከ፡ ደቡብም። የምድርም፡ አ ሕዛብ፡ ሁሉ፡ ባንተ፡ ደባረካሉ፡ በዘርኽም።

፲፭፤ እነሆም፡ እኔ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ነኝ፡ በምትሔድባ ትም፡ መንገድ፡ ሁሉ፡ እጠብቅኻለሁ፡ ወደዚችም፡ ምድር፡ እመልስኻለሁ፡ የነገርሁኽንም፡ ሁሉ፡ እስ ካደርግልኽ፡ ድረስ፡ አልተውኽም።

፲፮፤ ያዕቀብም፡ ከንቅልፈ፡ ነቃ፡ አለም። በውነት፡ እግዚአብሔር፡ ከዚኽ፡ ነው፡ እኔ፡ አላውቅም፡ ነ በርሁ።

፲፯፤ ፈራም፡ አለም። ምን፡ ያስፈራ፡ ደኽ፡ ስፈራ፡ ደኽ፡ ምንድር፡ ነው፡ የእግዚአብሔር፡ ቤት፡ እንጅ። ደኽም፡ የሰማያ፡ ደጅ፡ ነው።

፲፰፤ ያዕቀብም፡ ማልደ፡ ተነሣ፡ ተንተርሶት፡ የነበ ረውንም፡ ደንጊያ፡ ወሰደ፡ ለዓምድ፡ አቆመውም፡ ዘይ ትም፡ በላዩ፡ አፈሰሰበት።

፲፱፤ ያዕቀብም፡ ደነኝ፡ ሰፈራ፡ ቤቴል፡ ብሎ፡ ጸራ ው። አስቀድሞ፡ ግን፡ የዚያች፡ አገር፡ ሰም፡ ሉዝ፡ ነበረ።

፳፤ ያዕቀብም፡ ስለት፡ ተሳለ፡ እንደህ፡ ሲል። እግ ዚአብሔር፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ቢሆን፡ በዚችም፡ በምሔድባ ት፡ መንገድ፡ ቢጠብቀኝ። የምበላውንም፡ እንድራ፡ የምለብሰውንም፡ ልብስ፡ ቢሰጠኝ።

፳፩፤ ወደባቴ፡ ቤትም፡ በጤና፡ ብመለስ። እግዚ አብሔር፡ አምላክ፡ ደሆንልኛል።

፳፪፤ ደኽም፡ ደንገደ፡ ለዓምድ፡ የተከልሁትን፡ የ እግዚአብሔር፡ ቤት፡ ደሆናል። ከሰጠኽኝም፡ ሁሉ፡ ላንተ፡ ካሥር፡ አንድ፡ አሰጥኻለሁ።

ምዕራፍ፡ ፴፩፡

፩፤ ያዕቀብም፡እግሬን፡አነሣ፡ ወደ፡ ምሥራቅም፡ ልጆች፡ ምድር፡ ሔደ።

፪፤ አየም፡ እነሆም፡ ጉድጓድ፡ በምድረ፡ ስደ፡ እነ ሆም፡ በዚያ፡ ሶስት፡ የበግ፡ ዘመንጎች፡ እርፈውበት፡

ነበር፡ከዚያ፡ጕድጓድ፡ በጎችን፡ ደጠጡ፡ ነበሩና፡ በጕድጓዱም፡ አፏ፡ ታላቅ፡ ደንጊያ፡ ነበረበት።

፫፡ መንጎችም፡ ሁሉ፡ ከዚያ፡ በተከማቹ፡ ጊዜ፡ ደንጊያውን፡ ከጕድጓዱ፡ አፏ፡ ደገለብጡት፡ ነበረ፡ በጎችንም፡ ያጠጡ፡ ነበር። ደንጊያውንም፡ ወደ፡ ስፍራው፡ መልሰው፡ ወደ፡ ጕድጓድ፡ አፏ፡ ደገለብጡት፡ ነበር።

፬፡ ያዕቀብም፡ ጠባቆችን፡ አላቸው። አላንት፡ የ ወንደት፡ ናችሁ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ። አሉትም፡ እኖ፡ ከካራን፡ ነን።

፭፡ አላቸውም። ላባንን፡ ታውቃላችሁን፡ የናሆር ን፡ ልጅ። አሉም፡ እናውቀዋለን።

፮፡ አላቸውም፡ እርሱ፡ ደኅና፡ ነውን። አሉትም፡ አወን፡ ደኅና፡ ነው። እነኋትም፡ ራሔል፡ ልጁ፡ ከበጎች፡ ጋራ፡ መጥታለች።

፯፡ ያዕቀብም፡ አላቸው፡ ቀኑ፡ ገና፡ አለባችሁ። በ ጎች፡ የሚከማቹበትም፡ ጊዜ፡ አልደረሰም። በጎችን፡ አጠጡና፡ ሒደችሁ፡ አሰማሩ።

፰፡ አርሳቸውም፡ አሉ። አንችልም፡ መንጎች፡ ሁ ሉ፡ ካልተከማቹ፡ ደንጊያውንም፡ ከጕድጓዱ፡ አፏ፡ ካልፈነቅልነ፡ከዚያ፡ወደ፡ያም፡በጎችን፡እናጠጣለን።

፱፡ አርሱም፡ ሲነገራቸው፡ እነኋት፡ ራሔል፡ የላባ ን፡ ልጅ፡ መጣች፡ ካባትዋ፡ በጎች፡ ጋራ። አርስዋ፡ ት ጠብቃቸው፡ ነበረችና።

፲፡ ያዕቀብም፡ ራሔልን፡ ባየ፡ ጊዜ፡ የናቱን፡ የወን ድምዋን፡ ልጅ፡ ያጎቱንም፡ የላባንን፡ በጎች። ያዕቀ ብ፡ ቀረበ፡ ደንጊያውንም፡ ከጕድጓዱ፡ አፏ፡ ፈነቀለ፡ የላባንንም፡ ያጎቱን፡ በጎች፡ አጠጣ።

፲፩፡ ያዕቀብም፡ ራሔልን፡ ተገናኛት፡ ቃሉንም፡ ከ ፏ፡ አድርጎ፡ አለቀሰ።

፲፪፡ ያዕቀብም፡ ራሔልን፡ አስታወቃት፡ ያባትዋ፡ ወንድም፡ እንደ፡ ሆነ፡ የርብቃም፡ ልጅ። ፈጥናም፡ ሔደች፡ ላባትዋም፡ ነገረችው።

፲፫፡ ላባንም፡ የያዕቀብን፡ የቱን፡ ልጅ፡ ወረ፡ በሰ ማ፡ ጊዜ፡ ፈጥኖ፡ ወደርሱ፡ ሔደ፡ አቅፏም፡ ሳመው፡ ወደ፡ ቤቱም፡ አገባው፡ ያነጋገ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለላባን፡ ነገረው።

፲፬፡ ላባንም፡ አለው፡ በውነት፡ አንተ፡ አጥንቴ፡ ሥጋዬም፡ ነኽ። አንድ፡ ወርም፡ የሚያህል፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ተቀመጠ።

፲፭ ላባንም፡ ያዕቀብን፡ አለው፡ ወንድሜ፡ ስለ፡ ሆንኽን፡ በከንቱ፡ ታገለግለኛለኽ። ንገረኝ፡ ዋጋኽ፡ ምንድር፡ ነው።

፲፮፡ ለላባንም፡ ሁለት፡ ሴቶች፡ ልጆች፡ ነበሩት። የ ታላቂቱ፡ ስም፡ ልያ፡ የታናሺቱም፡ ስም፡ ራሔል።

፲፯፡ የልያም፡ ዓይን፡ ልም፡ ነበረ። ራሔል፡ ግን፡ ላ ይን፡ መልካም፡ ነበረች፡ ፈትዋም፡ የተዋበ፡ ነበረ።

፲፰፡ ያዕቀብም፡ ራሔልን፡ ወደደ፡ አለም። ሰባት፡ አመት፡ እገዛኻለሁ፡ ስለ፡ ራሔል፡ ስለ፡ ታናሺቱ፡ ልጅኽ።

፲፱፡ ላባንም፡ አለው። ላንተ፡ አሰጣት፡ ዘንድ፡ ይ ሻላል፡ ለሌላ፡ ሰው፡ ክሰጣት። ከኔ፡ ጋራ፡ ተቀመጥ።

፳፡ ያዕቀብም፡ ስለ፡ ራሔል፡ ሰባት፡ አመት፡ ተገ ዛ። በርሱም፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ጥቂት፡ ቀን፡ ሆነበት፡ እ ጅግ፡ ይወደት፡ ነበርና።

፳፩፡ ያዕቀብም፡ ላባንን፡ አለው። ምሽቴን፡ ስጠ ኝ፡ እገባባት፡ ዘንድ። ቀኑ፡ ተፈጽምዋልና።

፳፪፡ ላባንም፡ የዚያን፡ ስፍራ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ሰበሰ በ፡ ሰርግም፡ አደረገ።

፳፫፡ በመሸም፡ ጊዜ፡ ልጂን፡ ልያን፡ ወሰደ፡ ለያዕ ቀብም፡ አገባለት። ወደርስዋም፡ ገባ።

፳፬፡ ላባንም፡ ዘልፋን፡ ባርያዪቱን፡ ለልያ፡ ለልጂ፡ ሰጠ፡ ባርያ፡ ትሆናት፡ ዘንድ።

፳፭፡ በነገውም፡ እነሆ፡ ልያ፡ ሁና፡ ተገኘች። ላባን ንም፡ አለው፡ ይኽ፡ ያደረግኽብኝ፡ ነገር፡ ምንድር፡ ነ ው። ስለ፡ ራሔል፡ የተገዛሁልኽ፡ አደደለምን፡ እን ደት፡ አታለልኽኝ።

፳፮፡ ላባንም፡አለ። ባገራችን፡ ወግ፡ የለም፡ ታናሺ ቱን፡ አንሰጥ፡ ዘንድ፡ ታላቂቱ፡ ሳለች።

፳፯፡ ይኽነን፡ ሰባት፡ ፈጽም፡ እርስዋንም፡ ደግ ሞ፡ እሰጥኻለሁ። ሰባት፡ አመት፡ ሌላ፡ ደግሞ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ስለምትሰራው፡ ፈንታ።

፳፰፡ ያዕቀብም፡ እንደ፡ ሀ፡ አደረገ፡ ይኽነንም፡ ሰ ባቱን፡ አመት፡ ፈጸመ። ራሔልንም፡ ልጁን፡ ሰጠው፡ ለርሱ፡ ምሽት፡ ትሆን፡ ዘንድ።

፳፱፡ ላባንም፡ በላሃን፡ ባርያዪቱን፡ ለራሔል፡ ለል ጂ፡ ሰጣት፡ ባርያ፡ ትሆናት፡ ዘንድ።

፴፡ ወደ፡ ራሔልም፡ ደግሞ፡ ገባ። ደግሞም፡ ራሔ ልን፡ ከልያ፡ ይልቅ፡ ወደደት። ተገዛውም፡ ሰባት፡ አ መት፡ ሌላ።

፴፩፡ እግዚአብሔርም፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ልያ፡ የተጸላ ች፡ እንደ፡ ሆነች፡ ማሕፀንዋን፡ ከፈተላት። ራሔል፡ ግን፡ መካን፡ ነበረች።

፴፪፡ ልያም፡ ፀነሰች፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች፡ ስ ሙንም፡ ሮቤል፡ ብላ፡ ጸራችው። እንደሀ፡ ብላለች ና። እግዚአብሔር፡ መከራዬን፡ አየ፡ ከዚኽም፡ ወ ደሀ፡ ባሌ፡ ደወደኛል።

፴፫፡ ደግሞም፡ ፀነሰች፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች፡ አለችም። እኔ፡ እንደ፡ ተጸላሁ፡ እግዚአብሔር፡ ሰ ማ፡ ደኽንም፡ ደገመኝ። ስሙንም፡ ስምዖን፡ብላ፡ ጸራችው።

፴፬፡ ደግማ ፡ ፀነሰች፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች፡ አለችም፡ አሁን፡ ባሌ፡ ወደኔ፡ ደጠጋል። ሶስት፡ ወን ድ፡ ልጆች፡ ወልጂለታለሁና። ስለዚኽ፡ ስሙን፡ ሌ ዊ፡ ብላ፡ ጸራችው።

፴፭፡ ደግማም፡ ፀነሰች፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች፡ አለችም። ዛሬ፡ እግዚአብሔርን፡ አመሰግናለሁ፡ ስ

ለዚኽ፡ ሰሙን፡ ደሁያ፡ ብላ፡ ጸራችው፡ ከመውለድ ም፡ ተቊረጠች።

ምዕራፍ፡ ፴፡

፩፡ ራሔልም፡ አየች፡ ለያዕቀብ፡ ልጆች፡ አንደት ወልድ፡ ራሔልም፡ በትዋ፡ ቀናችባት። ያዕቀብንም፡ አለችው። ልጆች፡ ሰጠኝ፡ ያለዚያም፡ አሞታለሁ።

፪፡ ያዕቀብም፡ ራሔልን፡ ተቊጣት፡ አላትም። በ ውኑ፡ እኔ፡ በእግዚአብሔር፡ ስፍራ፡ ነኝ፡ የሆድን፡ ፍ ረ፡ በነሣሽ።

፫፡ አለችም። እነኋት፡ ባርያዬ፡ በላሃ፡ ድረስባት፡ በኔ፡ ፈንታም፡ ትውለድ፡ ከርሰዋም፡ ልጆች፡ ይሁኑል ኝ፡ ለኔ፡ ደግሞ።

፬፡ በላሃንም፡ ባርያዪቱን፡ ምስት፡ ሰጠችው፡ ያዕ ቀብም፡ ደረሰባት።

፭፡ በላሃም፡ ፀነሰች፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ለያዕቀብ፡ ወለደች።

፮፡ ራሔልም፡ አለች። እግዚአብሔር፡ ፈረደልኝ፡ ቃሌንም፡ ደግሞ፡ ሰማ፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ሰጠኝ፡ ስለ ዚኽ፡ ስሙን፡ ዲን፡ ብላ፡ ጸራችው።

፯፡ በላሃም፡ የራሔል፡ ባርያ፡ ደግማ፡ ፀነሰች፡ ሁለ ተኛ፡ ልጅም፡ ለያዕቀብ፡ ወለደች።

፰፡ ራሔልም፡ አለች። የእግዚአብሔርን፡ መታገ ል፡ ከቱ፡ ጋራ፡ ታገልሁ፡ አሸነፉሁም። ስሙንም፡ ንፍ ታሌም፡ ብላ፡ ጸራችው።

፱፡ ልያም፡ ከመውለድ፡ እንደ፡ ተቊረጠች፡ ባየ ች፡ ጊዜ፡ ዘልፋን፡ ባርያዋን፡ ወሰደት፡ ለያዕቀብም፡ ሰጠችው፡ ምስት፡ ትሆነው፡ ዘንድ።

፲፡ ዘልፋም፡ የልያ፡ ባርያ፡ ፀነሰች፡ ለያዕቀብም፡ ወንድ፡ ልጅ፡ ወለደች።

፲፩፡ ልያም፡ በደኅና፡ ገባ፡ አለችው፡ ስሙንም፡ ጋ ድ፡ ብላ፡ ጸራችው።

፲፪፡ ዘልፋም፡ የልያ፡ ባርያ፡ ሁለተኛ፡ ልጅ፡ ለያዕ ቀብ፡ ወለደች።

፲፫፡ ልያም፡ አለች። ምስጋና፡ ሆነችልኝ፡ ሴቶች፡ ያ መሰግኑኛልና፡ ስሙንም፡ አሴር፡ ብላ፡ ጸራችው።

፲፬፡ ሮቤልም፡ ወጣ፡ ስንዴ፡ በሚያጭዱበት፡ ወ ራት፡ በርሻም፡ አገኮደ፡ አገኘ፡ ወደ፡ ልያም፡ ወደያ ቱ፡ ደዛት፡ መጣ። ራሔልም፡ ልያን፡ አለቻት፡ ከልጅ ሽ፡ አገኮደ፡ ስጭኝ።

፲፭፡ አርስቀም፡ አለቻት። በውኑ፡ ባሌን፡ የወሰድ ሽብኝ፡ ጥቂት፡ ነገር፡ ነውን፡ አሁን፡ ደግሞ፡ የልጄን፡ አገኮደ፡ ትወሰጅ፡ ዘንድ። ራሔልም፡ አለች። ሰለዚ ኽ፡ ካንች፡ ጋራ፡ ይተኛ፡ በዚች፡ ሌሊት፡ ሰለ፡ ልጅሽ፡ አገኮደ።

፲፮፡ ያዕቀብም፡ ሲመሽ፡ ከሜደ፡ በተመለሰ፡ ጊዜ፡ ልያ፡ ልትቀበለው፡ ወጣች፡ አለችውም። ወደኔ፡ ትገ ባለኽ፡ በልጄ፡ አገኮደ፡ ገዝቼኻለሁና። በዚያችም፡ ሌት፡ ከርሰዋ፡ ጋራ፡ ተኛ።

፲፯፡ እግዚአብሔርም፡ የልያን፡ ጸሎት፡ ሰማ። ፀ ነሰችም፡ ለያዕቀብም፡ አምስተኛ፡ ልጅ፡ ወለደች።

፲፰፡ ልያም፡ አለች። እግዚአብሔር፡ ዋጋዬን፡ ሰጠ ኝ፡ ባርያዬን፡ ለባሌ፡ ስለ፡ ሰጠሁ። ስሙንም፡ ይሳኮ ር፡ ብላ፡ ጸራችው።

፲፱፡ ልያም፡ ደግሞ፡ ፀነሰች፡ ለያዕቀብም፡ ስድስ ተኛ፡ ልጅ፡ ወለደች።

፳፡ ልያም፡ አለች፡ እግዚአብሔር፡ መልካም፡ ስ ጦወታ፡ ሰጠኝ። በዚኽ፡ ጊዜ፡ ባሌ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ይሆናል ፡ ስድስት፡ ልጆች፡ ወልጄለታለሁና። ስሙንም፡ ዛብ ሎን፡ ብላ፡ ጸራችው።

፳፩፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ ሴት፡ልጅ፡ወለደች፡ ስምዋ ንም፡ ዲና፡ አለቻት።

፳፪፡ እግዚአብሔርም፡ ረሔልን፡ አሰበ። እግዚአ ብሔርም፡ ተለመናት፡ ማሕፀንዋንም፡ ከፈተ።

፳፫፡ ፀነሰችም፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች፡ አለች ም። እግዚአብሔር፡ ስድቤን፡ አሰወገደ።

፳፬፡ ስሙንም፡ ዮሴፍ፡ ብላ፡ ጸራችው፡ እንደሀ፡ ስትል። እግዚአብሔር፡ ሁለተኛ፡ልጅ፡ይጨምርልኝ።

፳፭፡ ራሔልም፡ ዮሴፍን፡ ከወለደች፡ በኋላ፡ ያዕ ቀብም፡ ላባንን፡ ፖለው። ስደደኝ፡ ወደገዳ፡ ወደ፡ ም ድሬም፡ እመለስ፡ ዘንድ።

፳፮፡ ምስቶቼንና፡ ልጆቼን፡ ስለርሳቸው፡ የተገዛ ሁልኝን፡ መገዛት፡ ታውቃለኽና።

፳፯፡ ላባንም፡ አለው። ባንተ፡ ዘንድ፡ ሞገስ፡ ላግ ኝ። እግዚአብሔር፡ ባንተኩል፡ እንደ፡ ባረከኝ፡ አይ ቻለሁና።

፳፰፡ አለም። ዋጋኽን፡ ምረጥ፡ እርሱንም፡ እሰ ጥኻለሁ።

፳፱፡ እርሱም፡ አለው። አንተ፡ ያገለገልሁኽን፡ ታ ውቃለኽ፡ ከብትኽንም፡ ከኔ፡ ጋራ፡ የነበረውን።

፴፡ እኔ፡ ወደንተ፡ ሳልመጣ፡ ከብትኽን፡ ጥቂት፡ ነ በረኖ። ዛሬም፡ እጅግ፡ በዛ፡ እግዚአብሔርም፡ ባረከ ኽ፡ ወደንተ፡ በመግባቴ። አሁንም፡ እኔ፡ ደግሞ፡ ቤ ቴ፡ የሚሻውን፡ ነገር፡ መቼ፡ አሰባለሁ።

፴፩፡ እርሱም፡ አለ፡ የምሰጥኽው፡ ምንድር፡ ነ ው። ያዕቀብም፡ አለው፡ አንጀት፡ አትሰጠኝም። ደ ኽነን፡ ነገር፡ ብታደርግልኝ፡ በግኽን፡ ተመልሼ፡ አጠ ብቃለሁ።

፴፪ ዛሬ፡ በኽብትኽ፡ ሁሉ፡ አልፈለሁ፡ በዚያም፡ ከበግ፡ ጥቦቶች፡ ነጭጣ፡ ነጠብጣብም፡ ያለበቱን፡ በ ግ፡ ሁሉ፡ ጥቁርንም፡ በግ፡ ሁሉ፡ ከፍያሎችም፡ ነጭ ጣና፡ ነጠብጣብ፡ያለበቱን፡ አለያለሁ፡ እርሳቸውም፡ ደመወዜ፡ ይሁኑ።

፴፫፡ ነገም፡ እውነቴ፡ ደመሰክርልኛል፡ ደመወዜ፡ በፊትኽ፡ በመጣ፡ ጊዜ። በፍያሎች፡ ነጭጣና፡ ነጠብ ጣብ፡የሌለበት፡ ከበግ፡ ጥቦቶችም፡ ጥቁር፡ ያልሁ፡ እ ርሱ፡ በጂ፡ የተሰረቀ፡ ይሁንብኝ።

፴፱፡ ላገንም፡ አለ፡ አዋን። ደኽ፡ ደሁን፡ እንደ፡ ነገርኽ።

፴፭፡ በዚያም፡ ቀን፡ ከሎሮንቦች፡ ዝንጕርጕሬን፡ ሁሉ፡ ለያ፡ ነጠብጣብም፡ ያለበትን፡ ነጭማና፡ ነጠብ ጣብም፡ ያላጣትን፡ ሁሉ፡ ከፈየሎች፡ ነጭ፡ ያላጣትን፡ ሁሉ። ጥቁረንም፡ ሁሉ፡ ከበግ፡ ጥቦቶች። በልጆቹም፡ እጅ፡ ሰጣቸው።

፴፮፡ የሶስት፡ ቀን፡ መንገድ፡ ያኽልም፡ አራቃቸው፡ በርሱና፡ በያዕቀብ፡ መኻከል። ያዕቀብም፡ የቀሬትን፡ የላባንን፡ መንጎች፡ ይጠብቅ፡ ነበር።

፴፯፡ ያዕቀብም፡ እርጥብ፡ በትር፡ ወሰደ፡ ከለው ዝ፡ ሁር፡ ከሚሉትም፡ እንጨት፡ ከደልብም፡ ነጭ ም፡ አድርጎ፡ ላበው፡ ለመለሙም፡ ተገለጦ።

፴፰፡ የተላጠውም፡ በትር፡ ጥቁርና፡ ነጭ፡ ሁና፡ ታ የ። የላጠውንም፡ በትር፡ በውኃው፡ ማጠጫ፡ ተከ ለው፡ በበጎች፡ ፊት፡ ሊጠጡ፡ በመጡ፡ ጊዜ። ሊጠ ጡም፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ ይጐመጇ፡ ነበር።

፴፱፡ ሴቶች፡ በጎችም፡ ከመጐመጇታቸው፡ የተነ ሣ፡ በትረን፡ ሲያዩ፡ ነጭማ፡ ያለበትን፡ ይወልዷሉ፡ ነ ጠብጣብም፡ መልኩም፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነውን።

፵፡ ያዕቀብም፡ ጥቦቶቹን፡ ለየ፡ በጎቹንም፡ ወደ፡ ዘንጕርጕሬ፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ጥቁረም፡ ሁሉ፡ በላባን፡ በጎ ች፡ ፊት፡ ለፈቱ፡ አኖረ። መንጎቹንም፡ ለብቻቸው፡ አቆማቸው፡ ወደ፡ ላገንም፡ ከብት፡ አልጨመራቸ ውም።

፵፩፡ የበረቱም፡ በጎች፡ በጐመጇ፡ ጊዜ፡ ያዕቀብ ም፡ በትረን፡ በበጎች፡ ፊት፡ አደረገ፡ በውኃው፡ ማጠ ጫ። በጎች፡ በበትረ፡ ፊት፡ እንጂ፡ አመጇ።

፵፪፡ በደከሙ፡ በጎቹም፡ ፊት፡ በትረን፡ አያደርገ ውም፡ ነበር። የደከሙም፡ ለላባን፡ ሆኑ፡ የበረቱም፡ ለያዕቀብ።

፵፫፡ ያሰውም፡ እጅግ፡ ባለጠጋ፡ ሆነ። ብዙም፡ ከ ብት፡ ሆነለት፡ ሴቶችም፡ ወንጀቸም፡ ባሮች፡ ግመሎ ችም፡ አህዮችም።

ምዕራፍ፡ ፴፩፡

፩፡ ያዕቀብም፡ የላባን፡ ልጆች፡ያሉትን፡ነገር፡ሰማ። ያዕቀብ፡ ያባታችኑን፡ ከብት፡ ሁሉ፡ ወሰደ፡ ካባታችን ም፡ ከብት፡ ይኽነን፡ ክብር፡ ሁሉ፡ አገኘ።

፪፡ ያዕቀብም፡ የላባንን፡ ፊት፡ አየ፡ እነሆም፡ ከር ሱ፡ ጋራ፡ አልሆነም። እንደ፡ ትላንት፡ ከዘያም፡ አስቀ ድሞ።

፫፡ እግዚአብሔርም፡ ያዕቀብን፡ አለው። ወደባ ተኽን፡ ምድር፡ ተመለስ፡ ወደ፡ ትውልድ ኽም፡ ካን ተ፡ ጋራም፡ እሆናለሁ።

፬፡ ያዕቀብም፡ ላከ፡ ራሔልንና፡ ልያንም፡ ወደ፡ሜ ዳ፡ ጸራ፡ ወደ፡ በጎች፡ ሰፈራ።

፭፡ አላቸውም። እኔ፡ አያለሁ፡ ያባታችሁ፡ ፊት፡ ክኔ፡ ጋራ፡ እንደ፡ልሆነ፡ እንደ፡ ትላንትና፡ ከትላንትና ም፡ አስቀድሞ፡ እንደ፡ ነበረ። ነገር፡ ግን፡ ያባቴ፡ አም ላክ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ነው።

፮፡ አላንተም፡ ታውቃላችሁ፡ እኔ፡ በፈጽም፡ ጕል በቴ፡ ላባታችሁ፡ እንደ፡ ተገዛሁ።

፯፡ አባታችሁም፡ ተተነኰለብኝ፡ ዋጋዬንም፡ ለወ ጠብኝ፡ አሥር፡ ጊዜ። እግዚአብሔርም፡ እኔን፡ አሳ ልፎ፡ አልሰጠውም፡ ክፋ፡ ያደርግብኝ፡ ዘንድ።

፰፡ እርሱ፡ እንደህ፡ ባለ፡ ጊዜ፡ ነጭማ፡ ያለበት፡ ዋ ጋኽ፡ ደሁን። በጎቹ፡ ሁሉ፡ ነጭማ፡ ያለበት፡ ወለዷ። እንደህም፡ ቢል፡ መልካቸው፡ የተላለፈው፡ ዋጋኽ፡ ደሁን። በጎች፡ ሁሉ፡ መልካቸው፡ የተላለፈ፡ወለዷ።

፱፡ እግዚአብሔርም፡ ያባታችሁን፡ ከብት፡ ነሥቶ፡ ለኔ፡ ሰጠኝ።

፲፡ በጎችም፡ በሚፀንሱበት፡ ጊዜ፡ ዓይኔን፡ አንሣ ቼ፡ በሕልም፡ አየሁ፡ እነሆም፡ አውራ፡ ፈየሎች፡ አ ውራ፡ በጎችም፡ በነጠብጣ፡ ላይ፡ ደሰረ፡ ነበረ፡ ነጭማ፡ ያለባቸው፡ ነበረ፡ መልካቸውም፡ የተላለፈው፡ ነጠ ብጣብም፡ ያለባቸው።

፲፩፡ የእግዚአብሔር፡ መልክተኛም፡ በሕልሜ፡ አ ለኝ፡ ያዕቀብ፡ ሆይ። እኔም፡ አልሁ፡ እነሆኝ፡ እኔ።

፲፪፡ እርሱም፡ አለኝ። ዓይንኽን፡ አንሣ፡ አውራ፡ ፈየሎችንና፡ አውራ፡ በጎችንም፡ እይ፡ በእንስት፡ በ ጎችና፡ በእንስት፡ ፈየሎች፡ ላይ፡ የሚሰረትን። ሁሉ፡ ነጭማ፡ ያለባቸው፡ ናቸውና፡ ነጠብጣብም፡ መልካ ቸውም፡ የተላለፈ። ላባን፡ ያሚያደርግብኽን፡ሁሉ፡ አይቻለሁና።

፲፫፡ እኔ፡ የቤቴል፡ አምላክ፡ ነኝ፡ የደገኒያ፡ዓምድ፡ ከዚያ፡ ለቀባኽው፡ ከዚያም፡ ስለት፡ ለተሳልኽል ኝ። አሁንም፡ ተነሣና፡ ከዚኽ፡ ምድር፡ ውጣ፡ ወደ፡ ተወለድኽባትም፡ ምድር፡ ተመለስ።

፲፬፡ ራሔልና፡ ልያም፡ መለሱ፡ እሉትም፡ በውኑ፡ ፈንታ፡ ቀርተልናል፡ ወይስ፡ እርስት፡ ባባታችን፡ ቤት።

፲፭፡ በርሱ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ መጻተኖች፡ ተቊጥረን፡ የእመን። ሸጦናልና፡ ደግሞም፡ ብራትነን፡ በልተታ ልና።

፲፮፡ ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ካባታችን፡ የወሰደ ው፡ ከብት፡ ሁሉ፡ እርሱ፡ ለኛ፡ ነው፡ ለልጆቻችንም። አሁንም፡ እግዚአብሔር፡ ያዘዘኽን፡ሁሉ፡ አድርግ።

፲፯፡ ያዕቀብም፡ ተነሣ፡ ልጆቹንና፡ ምስቶቹን፡ በግ መል፡ ላይ፡ አስቀመጠ።

፲፰፡ መንጎቹንም፡ ሁሉ፡ ወሰደ፡ የገዛውንም፡ከብ ት፡ ሁሉ፡ በሁለቱ፡ ወንዝ፡ መኻከል፡ ያከማቸውን፡ ከብት። ወደ፡ ይስሐቅ፡ ወደባቱ፡ ደሔድ፡ ዘንድ፡ ወ ደ፡ ከነዓን፡ ምድር።

፲፱፡ ላገንም፡ ሒደ፡ ነበረ፡ የበጎቹን፡ ጸጕር፡ ያሰሸ ለት፡ ዘንድ፡ ራሔልም፡ ያባትዋን፡ ጣዖታት፡ ሰረ ቀች።

፳፡ ያዕቀብም፡ ከላባን፡ ካረማዊው፡ ነኳኄ፡ ሠ ወረ፡ እንደ፡ ኰበለለም፡ አላሰታወቀውም።

፴፭፡ እርሱም፡ ኰበለለ፡ ለርሱም፡ ያለው፡ ሁሉ። ተነሣም፡ ወንዙንም፡ ተሻገረ፡ ወደ፡ ገለዓድ፡ ተራራ ም፡ ፈቱን፡ አቀና።

፴፪፡ ላባንም፡ ሰማ፡ በሶስተኛው፡ ቀን፡ ያዕቀብ፡ እንደ፡ ኰበለለ።

፴፫፡ ወንድሞቹንም፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ወሰደ፡ያሰባት፡ ቀን፡ መንገድ፡ የሚያኽልም፡ ተከተለው። በገለዓ ድ፡ ተራራም፡ ደረሰበት።

፴፬፡ እግዚአብሔርም፡ ወደ፡ ላባን፡ ወደረማዊ ው፡ በሕልም፡ መጣ፡ በሌት፡ እንደህ፡ ሲለው። ተጠ ንቀቅ፡ ያዕቀብን፡ትናገረው፡ዘንድ፡በሚያሰኽፈው።

፴፰፡ ላባንም፡ በያዕቀብ፡ ደረሰበት፡ ያዕቀብም፡ ድንኳኑን፡ በተራራ፡ ተክሎ፡ ነበር። ላባንም፡ ከወን ድሞቹ፡ ጋራ፡ በገለዓድ፡ ተራራ፡ ድንኳኑን፡ ተከለ።

፴፯፡ ላባንም፡ ያዕቀብን፡ አለው። ለምን፡ እንደ ህ፡ አደረግኽ፡ ደህነን፡ ነገር፡ ከኔ፡ ሠውረኽ። ልጆቼን ሰ፡ ነጂነትው፡ በሰይፍ፡ እንደ፡ ተማረኩ።

፴፯፡ ለምንሰ፡ በስውር፡ ኰበለልኽ፡ ሳታስታውቀ ኝ። አልነገርኽኝምም፡ በደስታና፡ በዘፈን፡ አሰድኽ፡ ዘንድ፡ በከበሮም፡ በመሰንቆም።

፴፰፡ ወንደሶንም፡ ሴቶችንም፡ ልጆቼን፡ እነናኝ፡ ዘንድ፡ አልተውኽኝም። ደህነን፡ በሰንፈና፡ አደረ ግኽ።

፴፱፡ ክፈ፡ አደርግባችሁ፡ ዘንድ፡ ኃይልም፡ አለኝ። ነገር፡ ግን፡ ያባታችሁ፡ አምላክ፡ ትላንት፡ ተናገረኝ፡ እ ንደህ፡ ሲል። ተጠንቀቅ፡ ያዕቀብን፡ ትናገር፡ ዘንድ፡ በሚያሰከፈው፡ ነገር።

፵፡ አሁንም፡ ሔድኽ፡ ያባትኽን፡ ቤት፡ ስለ፡ ናፈ ቅኽ። ነገር፡ ግን፡ አምላኮቼን፡ ለምን፡ ሰረቅኽ።

፵፩፡ ያዕቀብም፡ መለሰ፡ ላባንንም፡ አለው። ስለ፡ ፈራሁ፡ ደህነን፡ አደረግሁ። ልጆችኽን፡ ከኔ፡ እንደት ወሰድ፡ ብዙ።

፵፪፡ አምላኮችኽን፡ ግን፡ በርሱ፡ ዘንድ፡ ያገኘኽ በት፡አርሰ፡ ይመት። በወንድሞቻችን፡ ፊት፡ ፈልግ፡ በኔ፡ ዘንድም፡ የተገኘውን፡ ከብትኽን፡ ሁሉ፡ ላንተ፡ ውሰደው። ያዕቀብም፡ አያውቅም፡ ነበር፡ ራሔል፡ ያባትዋን፡ አምላኮች፡ እንደ፡ ሰረቀች።

፵፫፡ ላባንም፡ ወደ፡ ያዕቀብ፡ ድንኳን፡ ገባ፡ ወደ፡ ልያም፡ ድንኳን፡ ገባ፡ ወደ፡ ሁለቱ፡ ባሮች፡ ድንኳን፡ አላገኘውም።ከልያም፡ ድንኳን፡ ወጥቶ፡ ወደ፡ ራ ሔል፡ ድንኳን፡ ገባ።

፵፬፡ ራሔልም፡ ጣዖታቱን፡ ወሰደች፡ ከግመሉ፡ ኮ ረቻ፡ በታች፡ ሸሽጋት፡ በላዩም፡ ተቀመጠችበት። ላባ ንም፡ ድንኳኑን፡ ሁሉ፡ ፈለገ፡እንደችም፡አላገኘም።

፵፭፡ አባቱንም፡ አለችው፡ ጌታዬ፡ አደቀጣብኝ፡ በፊትኽ፡ መቀም፡ አደቻለሻምና። በሴቶች፡ የሚደ ርስ፡ ደርሶብኛልና። እርሱም፡ ፈለገ፡ ጣዖታቱንም፡አ ላገኘም።

፵፮፡ ያዕቀብም፡ ተቈጣ፡ ላባንንም፡ ተጻላው። ያዕቀብም፡ መለሰ፡ ላባንንም፡ አለው። ምንድር፡ ነ ው፡ ኃጢአቴ፡ የበደልሁኽሰ፡ ምንድር፡ ነው፡ ፈለጋዬ ን፡ የተከተልኽኝ።

፵፯፡ አሁንም፡ እቃዬን፡ ሁሉ፡ በረበርኽ፡ ከቤት ኽሰ፡ አቃ፡ ሁሉ፡ ምን፡ አገኘኽ። ከዚኽ፡አድርገው፡ በወንድሞቼና፡ በወንድሞችኽ፡ ፊት፡ በኛም፡ በሁ ለታችን፡ መኽከል፡ ይፈረዱ።

፵፰፡ ህያ፡ አመት፡ ምሉ፡ እኔ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ነበር ሁ፡ በጎችኽ፡ ፍየሎችኽም፡ አልመከኑም፡ የመንጋ ኽንም፡ ደንግሎች፡ አልበላሁም።

፵፱፡ አርዌ፡ የሰበረውን፡ አላመጣልኽም፡ ነበር ሁ። እኔ፡ ሰለርሱ፡ እከፈልኽ፡ ነበርሁ። በቀን፡ የተሰ ረቀውን፡ በሌት፡ የተሰረቀውንም፡ ከጂ፡ ትሻው፡ነበ ርኽ።

፶፡ ትኩሳት፡ በቀን፡ ብርድም፡ በሌት፡ ፈጀኝ። እ ንቅልፌም፡ ካይኔ፡ ሸሸ።

፶፩፡ እንደሁ፡ ህያ፡ አመት፡ ካንተ፡ ጋራ፡በቤትኽ፡ ነበርሁ። አሥራ፡ አራት፡ አመት፡ ሰለ፡ ልጆችኽ፡ ተገ ዛሁልኽ፡ ሰድሰት፡ አመትም፡ ሰለ፡ በጎችኽ። ደመ ወዜንም፡ አሠር፡ ጊዜ፡ ለወጥኸው።

፶፪፡ ያባቴ፡ የአብርሃም፡ አምላክሰ፡ የደሰሐቅ ም፡ ፈርሃት፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ባይሆን፡ ዛሬ፡ ባይ፡ አጂን፡ ታ ወጣኝ፡ ነበር። እግዚአብሔር፡ መከራዬን፡ የጂቼ ንም፡ ድካም፡ አይተ፡ ትላንት፡ ገሠጸኽ።

፶፫፡ ላባንም፡ መለሰ፡ ያዕቀብንም፡ አለው። ልጂ ኽ፡ ልጂቼ፡ ናቸው፡ ሕፃናቱም፡ ሕፃናተቼ፡ ናቸው። በጎችም፡ በጎቼ፡ ናቸው፡ የምታየውም፡ ሁሉ፡ የኔ፡ ነ ው። ዛሬም፡በለዚኽ፡በልጂቼ፡በወለድዋቸውም፡በ ልጂታቸው፡ ምን፡ አደርግ፡ ዘንድ፡ ይቻለኛል።

፶፬፡ አሁንም፡ ና፡ ቃል፡ ኪደን፡ እንጋባ፡ እኔና፡ አ ንተ። ምስክር፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ በኔና፡ ባንተ፡ መኻ ከል።

፶፭፡ ያዕቀብም፡ ደንኒያ፡ ወሰደና፡ ለዓምድም፡ አቆመው።

፶፮፡ ያዕቀብም፡ ወንድሞቹን፡ አላቸው፡ደንኳች፡ አምጡ። ደንኳችም፡ ሰበሰቡ፡ መደብም፡ አደረጉ፡ ከ ዚያም፡ በመደብ፡ ላይ፡ በሉ።

፶፯፡ ላባንም፡ አላት፡ ደጋር፡ ሠሐዲታ። ያዕቀብ ም፡ አላት፡ ገለዓድ።

፶፰፡ ላባንም፡ አለ። ደኽች፡ መደብ፡ ዛሬ፡ ባንት ና፡ በኔ፡ መኻከል፡ ምስክር፡ ናት። ስለዚኽ፡ስምዋን፡ ገለዓድ፡ ጸራው፡ ሚጽጽም፡ (መጠበቅያ)።

፶፱፡ እንደህ፡ ብልዋልና፡ እግዚአብር፡ በኛ፡ መኻ ከል፡ ደደና፡ ደፈረድ፡ እርሱ፡ በርሳችን፡ በተለያየ፡ ጊዜ።

፶፡ ልጂቼን፡ ብትንቃቸው፡ ወይም፡ በላያቸው፡ ም ስቶች፡ ብታገባባቸው፡ ሰው፡ ከኛ፡ ጋራ፡ የለም። እነ ሆ፡ እግዚአብሔር፡ በኔና፡ ባንተ፡ መኻከል፡ ምስክር፡ ነው።

፶፭፡ ላባንም፡ ያዕቀብን፡ አለው። እነሆ፡ ይኽች፡ መደብ፡ እነሆም፡ ድኽ፡ ያቀምሁት፡ ዓምድ፡ በኔና፡ ባንተ፡ መ᎓ኻከል።

፶፪፡ ይኽች፡ መደብ፡ ምስክር፡ ናት፡ ይኽም፡ ደንጊያ፡ ይመሰክራል፡ እኔ፡ ወደንተ፡ ይኽቺን፡ መደብ፡ እንደላልፍ፡ አንተም፡ ይኽቺን፡ መደብና፡ ይህንን፡ ደንጊያ፡ ወደኔ፡ እንደታልፈው፡ ለክፋት።

፶፫፡ የአብርሃም፡ አምላክ፡ የናሆርም፡ አምላክ፡ ያባታቸው፡ አምላክ፡ በኛ፡ መ᎓ኻከል፡ ይፈረድ። ያዕቀብም፡ ማለ፡ ባባቱ፡ በይስሐቅ፡ ፈርሳት።

፶፬፡ ያዕቀብም፡ በተራራው፡ መሥዋዕት፡ ሠዋ፡ ወንድሞቹንም፡ ጸራ፡ እንጅራ፡ ደበሉ፡ ዘንድ። እን ጅራም፡ በሉ፡ በተራራውም፡ አደረ።

፶፭፡ ላባንም፡ ማልደ፡ ተነሣ፡ ወንደቾንና፡ ሴቶች ን፡ ልጆቹን፡ ተነናኘ፡ መረቃቸውም። ላባንም፡ ተመ ልሶ፡ ወደ፡ ሰፈራው፡ ሔደ።

ምዕራፍ፡ ፴፪፡

፩፡ ያዕቀብም፡ መንገዲን፡ ሔደ፡ የእግዚአብሔ ርም፡ መልክተኖች፡ ተገናኙት።

፪፡ ያዕቀብም፡ ባያቸው፡ ጊዜ፡ አለ። አሌ᎓ኽ፡ የእ ግዚአብሔር፡ ጭፍሮች፡ ናቸው። የዚያንም፡ ሰፈራ፡ ሰም፡ መ᎓ኸ᎓ያም፡ (ሁለት፡ሠራዊት)፡ ብሎ፡ጸራው።

፫፡ ያዕቀብም፡ ወደ፡ ወንድሙ፡ ወደ፡ ሴሳው፡ መ ልክተኖች፡ ላከ፡ በፈቱ፡ ወደ፡ ሳሢር፡ ምድር፡ወደ፡ ኤ ደም፡ አገር።።

፬፡ እንደህም፡ ሲል፡ አዘዛቸው። ለጌታዩ፡ ለሴሳ ው፡ ንገሩት፡ ይኽ፡ ነው፡ ያዕቀብ፡ ባርያኽ፡ የሚለ ው። ከላባን፡ ዘንድ፡ ተቀመጥሁ፡ አስከ፡ ዛሬ፡ድረስ፡ ዘገየሁ።

፭፡ ላሞችም፡ ሆኑልኝ፡ አህዮችም፡ በጎችም፡ ወ ንደች፡ ባሮችም፡ ሴቶችም፡ ባሮች። አሁንም፡ ላክሁ፡ ጌታዩን፡ ልንገር፡ ባንተ፡ ፊት፡ ሞገስ፡ አገኝ፡ ዘንድ።

፮፡ መልክተኖችም፡ ወደ፡ ያዕቀብ፡ ተመለሱ፡ እን ጂህ፡ ሲሉ። ወደ፡ ወንድም᎓ኽ፡ ወደ፡ ሴሳው፡ ሔድነ፡ አርሱም፡ ደገሙ፡ ሊያገኝኽ፡ ይመጣል፡ ከርሱም፡ ጋ ራ፡ አራት፡ መቶ፡ ሰዉች።

፯፡ ያዕቀብም፡ እጅግ፡ ፈራ፡ በልቡም፡ ተጨነቀ። ከርሱ፡ ጋራ፡ ያሉትንም፡ ሰዉች፡ ከፈፈላቸው፡ መን ጎችንም፡ ላሞችንም፡ ግመሎችንም፡ በሁለት፡ ወ ገን።

፰፡ አለም። ሴሳው፡ መጥቶ፡ አንጂን፡ ወገን፡ የመ ታ፡ አንደ፡ ሆን፡ የቀረው፡ ወገን፡ ያመልጣል።

፱፡ ያዕቀብም፡ አለ። ያባቴ፡ የአብርሃም፡ አምላ ክ፡ ሆይ፡ የይስሐቅም፡ ያባቴ፡ አምለክ። ጌታ፡ ሆይ፡ ወደ፡ ምድር᎓ኽ፡ ተመለስ፡ ያል᎓ኽኝ፡ ወደ፡ ተወለድ ᎓ኽበትም፡ ሰፈራ፡ በጐነትም፡ አደርግልሃለሁ።

፲፡ ምሕረት᎓ኽ፡ አውነት᎓ኽም፡ ሁሉ፡ ለባርያ᎓ኽ፡ የሰራ᎓ኸው፡ የማደገባኝ፡ ነኝ። በትረን፡ ይዤ፡ ይኽ ን፡ ዮርደያስን፡ ተሻገርሁና፡ አሁንም፡ ለሁለት፡ ጭፍ ሮች፡ ሆንሁ።

፲፩፡ ከወንድሜ፡ እጅ፡ ከሴሳው፡ እጅ፡ አድነኝ፡ አ ለምን᎓ኻለሁ። እኔ፡ ከርሱ፡ እፈራለሁና፡ መጥተ፡ እ ንደደመታኝ፡ እናቲቱንም፡ ከልጆች፡ ጋራ።

፲፪፡ አንተም፡ አል᎓ኽ፡ መልካም፡ አደርግል᎓ኻለሁ፡ ዘርኽንም፡ እንደ፡ ባሕር፡ አሻዋ፡ አደርጋለሁ፡ ከብ ዛት፡ የተነሣ፡ እንደማይቆጠር።

፲፫፡ በዚያችም፡ ሌሊት፡ ከዚያው፡ አደረ። ከያዘ ውም፡ ሁሉ፡ ለወንድሙ፡ ለሴሳው፡ በረከት፡ወሰደ።

፲፬፡ ሁለት፡ መቶ፡ እናት፡ ፎየል፡ ሀያም፡ ሞርንቢ። ሁለት፡ መቶ፡ እናት፡ በግ፡ ሀያም፡ ያገላሉ።

፲፭፡ ሠላሳ፡ የሚያጠቡ፡ ግመሎች፡ ከልጆቻቸው፡ ጋራ። አርባ፡ ላም፡ አሠርም፡ በረ። ሀያ፡ አንስት፡ አ ህያ፡ አሠርም፡ ግልገል።

፲፮፡ በባሮቹም፡ እጅ፡ በአ᎓ያመንጋው፡ ከፈፈሎ፡ አደረጋቸው። ባሮቹንም፡ አለ፡ በፊቴ፡ አለፈ፡ በመን ጋውና፡ በመንጋውም፡መ᎓ኻከል፡አሰፈታችሁ፡ሒደ።

፲፯፡ የፊተኛውንም፡ አዘዘ፡ እንደህ፡ ሲል። ሴሳ ው፡ ወንድሜ፡ ቢያገኝኽ፡ ቢጠይቅ᎓ኽም፡ አንት፡ የ ማነኽ፡ ብሎ፡ ወዴትስ፡ ትሔደለኽ፡ ወይስ፡ የማን፡ ነው፡ ይኽ፡ በፊትኽ፡ ያለው።

፲፰፡ በለው። የባርያ᎓ኽ፡ የያዕቀብ፡ ነው፡ ለጌታዩ ም፡ ለሴሳው፡ በረከት፡ ሰደደው። አነሆም፡ እርሱ፡ ደግሞ፡ በኋላችን፡ ነው።

፲፱፡ እንደሁም፡ ሁለተኛውን፡ አዘዘ፡ ሶስተኛው ንም፡ ከመንጎችም፡ በኋላ፡ የሚሔዷትን፡ ሁሉ፡ እ ንደህ፡ ሲል። ይኽን፡ ነገር፡ ለሴሳው፡ ንገሩት፡ ባገኛ ችሁት፡ ጊዜ።

፳፡ ደግማችሁም፡ በሉት። እነሆ፡ ያዕቀብ፡ ባርያ ኽ፡ ተከትሎናል። በፊቴ፡ በሚሔደው፡ መማለጀ፡ አታረቀዋለሁ፡ ብልዋልና። ከዚ᎓ኽም፡በኋላ፡ ፊቱን፡ አየዋለሁ። ምናልባት፡ የራራልኝ፡ እንደሆን።

፳፩፡ በረከቱም፡ አሰቀድሞ፡ ሔደ፡ አርሱም፡ በዚ ያች፡ ሌት፡ በጋዝ፡ አደረ።

፳፪፡ በዚያችም፡ ተነሣ፡ ሁለቱንም፡ ምስቶቹን፡ ሁለቱንም፡ ባሮቹን፡ አሥራ፡ አንጂንም፡ ልጆቹን፡ ወሰደ፡ የያቦቅንም፡ ወንዝ፡ ተሻገረ።

፳፫፡ ወሰደቸውም፡ ወንዙንም፡ አሻገራቸው፡ ከ ብቱንም፡ ሁሉ፡ አሻገረ።

፳፬፡ ያዕቀብም፡ ግን፡ ለብቻው፡ ቀረ። አንድ፡ ሰ ውም፡ ይታገለው፡ ነበረ፡ አስኪጸባ፡ ድረስ።

፳፭፡ አንደላሸነፈውም፡ ባዮ፡ ጊዜ፡ የጭኑን፡ ጅማ ት፡ ደሰሰው። የያዕቀብም፡ የጭኑ፡ ጅማት፡ ፈዘዘ፡ ሲታገለው።

፳፮፡ አሉውም። ልቀቀኝ፡ሊጸባ፡አቀላልትዋልና። አለውም፡ አለቅ᎓ኝም፡ ወደም፡ ባር᎓ኸኝ።

፳፯፡ አለውም፡ ስም᎓ኽ፡ ማነው። አለውም፡ ያዕ ቀብ።

፴፫፡ አለውም፡ ስምኽ፡ ደግሞ፡ ያዕቆብ፡ አይባል፡ እሥራኤል፡ ይባል፡ እንጅ። ከእግዚአብሔር፡ጋራ፡ ከሰውም፡ በርትተኻልና፡ አሸንፈኻልማልና።

፴፬፡ ያዕቆብም፡ ጠየቀው፡ አለም፡ አስታውቀኝ፡ ስምኽ፡ ማነው። አለውም፡ ስሜን፡ ለምን፡ ትጠይቃለኽ። በዚያም፡ ሰፈራ፡ ባረከው።

፴፡ ያዕቆብም፡ የዚያን፡ ቦታ፡ ሰም፡ ጵኒኤል፡ ብሎ፡ ጸራው፡ እንጂኽ፡ ሲል። እግዚአብሔርን፡ ፊት፡ ለፊት፡ አየሁ፡ ሰውነቴም፡ ድና፡ ቀረኽ።

፴፩፡ ፀሓይም፡ ወፃችበት፡ ጵኒኤልን፡ ሲያልፍ፡ አርሱም፡ በጭኑ፡ ያነክስ፡ ነበር።

፴፪፡ ሰለዚኽ፡ የእሥራኤል፡ ልጆች፡ በወርቹ፡ ያለውን፡ ጅማት፡ አይበሉም፡ አሰከ፡ ዛሬ፡ ድረስ። የያዕቆብን፡ ጭን፡ ደሶ፡ ይመቱን፡ አፈዝዘታልና።

ምዕራፍ፡ ፴፫፡

፩፡ ያዕቆብም፡ ዓይኑን፡ አነሣ፡ አነሆም፡ ዔሳው፡ አየ፡ ሲመጠ፡ ከርሱም፡ ጋራ፡ አራት፡ መቶ፡ ሰዉች። ልጆቹንም፡ ከፈሎ፡ ከልያ፡ ከራሔልም፡ ከሁለትም፡ ባሮች፡ ጋራ፡ አደረጋቸው።

፪፡ ባሮችንና፡ ልጆቻቸውንም፡ በፊት፡ አደረገ፡ ልያንና፡ ልጆችዋንም፡ በኋለኛው፡ ሰፈራ፡ ራሔልንና፡ ዮሴፍንም፡ ከሁሉ፡ በኋላ።

፫፡ አርሱም፡ በፊት፡ ሆነ፡ ሰግደም፡ ሰባት፡ ጊዜ፡ በምድር፡ ወደቀ፡ ወደ፡ ወንድሙ፡ አሰኪደርሰ።

፬፡ ዔሳውም፡ ሊገናኘው፡ ሮጠ፡ አቀፈውም፡ ዓን ገቱም፡ ላይ፡ ወደቀና፡ ሳመው። አለቀሱም።

፭፡ አይኑንም፡ አነሡና፡ ሴቶችን፡ አየ፡ ሕፃናቶችንም። አለም፡ አሌኽ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ያሉ፡ምንድር፡ ናቸው። አርሱም፡ አለ፡ አሌኽ፡ ሕፃናት፡ ናቸው፡ አግዚአብሔር፡ ለኔ፡ ለበርያኽ፡ የሰጠኝ።

፮፡ ባሮችም፡ ቀረቡ፡ አርሳቸው፡ ልጆቻቸውም፡ ሰገዷም።

፯፡ ልያም፡ ደግሞ፡ ቀረበች፡ ከልጆችዋ፡ ጋራ፡ ሰገዷም። በመጨረሻም፡ ዮሴፍና፡ ራሔልም፡ ቀረቡ፡ ሰገዷም።

፰፡ አለም። በቪህ፡ በተገናኘሁት፡ ጊዝ፡ ምን፡ አስብሳል። አለም፡ ሞገስ፡ አገኝ፡ ዘንድ፡ በጌታዬ፡ ፊት።

፱፡ ዔሳውም፡ አለ፡ ኸኔ፡ ዘንድ፡ እጅግ፡ ነው፡ ወንድሜ፡ ሆይ። ኸብትኽ፡ ላንተ፡ ይሁን።

፲፡ ያዕቆብም፡ አለ፡ አይሆንም። ነገር፡ ግን፡ በፊትኽ፡ ሞገስ፡ አግኝቼ፡ እንደ፡ ሆንሁ፡ በረኸቴን፡ ከጂ፡ ተቀበል። ፊትኽን፡ አይቻለሁና፡ የእግዚአብሔርን፡ ፊት፡ እንደሚያይ፡ በኞርነትም፡ ተቀበልኽኝ።

፲፩፡ ይ ኽኞቴንም፡ ያመጣሁልኽን፡ በረኸቴን፡ ተቀበል፡ እግዚአብሔር፡ በመሕረቱ፡ ሰጥተኞልና፡ አጅግ ም፡ለኔ፡ነው። የግድም፡ አለው፡ አስኪቀበል፡ ድረስ።

፲፪፡ አርሱም። አለው። ተነሥና፡ እንሒድ፡እኔም፡ በፊትኽ፡ አሔዳለሁ።

፲፫፡ አለውም፡ አንተ፡ ታውቃለኽ፡ ጌታዬ፡ ሆይ፡ ሕፃናት፡ ጨቅላ፡ ልጆች፡ እንደሆኑ፡ በጎችም፡ ላሞችም፡ ያጠባሉ። ሰዉችም፡ በመንገድ፡ አስቸኩለው፡ የኔድዋቸው፡ እንደሆን፡ ባንድ፡ ቀን፡ እንስሶች፡ ሁሉ፡ ይሞታሉ።

፲፬፡ ጌታዬ፡ በባርያው፡ ፊት፡ ይለፍ፡ እኔም፡ ኢያዘገምሁ፡ እከተላለሁ፡ እንደ፡ እንስሶች፡ ሕፃናትም፡ እርምጁ፡ መጠን፡ ወደ፡ ጌታዬ፡ እስክመጣ፡ ድረስ፡ እሰከ፡ ሳዒር።

፲፭፡ ዔሳውም፡ አለ። ከኔ፡ ጋራ፡ ካሉ፡ ከሰዉች፡ ከፊዱ፡ ልተውልኽ። አለም፡ ያስ፡ ለምንድር፡ ነው። በጌታዬ፡ ዘንድ፡ ሞገስ፡ ላግኝ።

፲፮፡ ዔሳውም፡ በዚያ፡ ቀን፡ ወደ፡ ሳዒር፡ መንገዱን፡ ተመለሰ።

፲፯፡ ያዕቆብም፡ ወደ፡ ሳኩት፡ መጣ፡ ከዚያም፡ ቤት፡ አቀመ፡ ለንሰሶቹም፡ ደሶች፡ አደረገ። ሰለዚኽ፡ የዚያን፡ ቦታ፡ ሰም፡ ሳኩት፡ ብሎ፡ ጸራው።

፲፰፡ ያዕቆብም፡ በደህንነት፡ ወደ፡ ሴኬም፡ ከተማ፡ መጣ፡ በከነዓን፡ ምድር፡ ወደለቸው፡ ከሶርያ፡ ወንዝ፡ መኘከል፡ ሲመለስ፡ በከተማዪቱም፡ ፊት፡ ሰፈረ።

፲፱፡ ድንጊንም፡ ተክሎበት፡ የነበረውን፡ የአርሻውን፡ ክፈል፡ ከሴኬም፡ አባት፡ ከሀሙር፡ ልጆች፡ በመቶ፡ በግ፡ ገዛው።

፳፡ ከዚያም፡ መሠውያ፡ አቀመ፡ የእሥራኤል ም፡ ብርቱ፡ አምላክ፡ ብሎ፡ ጸራ።

ምዕራፍ፡ ፴፬፡

፩፡ ዲናም፡ የልያ፡ ልጅ፡ ለያዕቆብ፡ የወለደቸ፡ የዚያን፡ አገር፡ ልጆች፡ ታይ፡ ዘንድ፡ ወጣች።

፪፡ ሴኬምም፡ የሀሞር፡ የሀዊው፡ ልጅ፡ የምድሩ፡ አለቃ፡ አያት። ወሰደቸም፡ ከርሰዋም፡ጋራ፡ ተኛ፡ አስነወራትም።

፫፡ ነፍሱም፡ በደ.ና፡ በያዕቀብ፡ ልጅ፡ ተጣበቀች። ብላቴናዪቱንም፡ወደደች፡ ልብዋንም፡ደሰ፡ በሚያሰኝ፡ቃል፡ ነገር፡ ተናገራት።

፬፡ ሴኬምም፡ ሀሙርን፡ አባቱን፡ አለው። ደኝ ቺን፡ ብላቴና፡ ምስት፡ አድርግልኝ።

፭፡ ያዕቀብም፡ ሰማ፡ ደ.ናን፡ ልጅዋን፡ አንደስነወራት። ልጆቹም፡ በምድረ፡ በደ፡ ነበሩ፡ ከከብቶቹ ው፡ ጋራ። ያዕቀብም፡ ዝማለ፡ አሰኪመጡ፡ ድረስ።

፮፡ ሀሙርም፡ የሴኬም፡ አባት፡ ወደ፡ ያዕቀብ፡ ወጣ፡ ይነግረው፡ ዘንድ።

፯፡ የያዕቀብም፡ ልጆች፡ ከምድረ፡ በደ፡ መጡ። ደኝነን፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ አርሳቸው፡ አዘኑ፡ አጅግም፡ ተቀጡ፡ በአሥራኤል፡ ስንፍና፡ በማድረጉ፡ የያዕቀብንም፡ ልጅ፡ በመተኛቱ፡ አንደህ፡ አደደረግምና።

፰፡ ሀሙርም፡ ነገራቸው፡ እንደህ፡ ሲል። ሴኬም፡

ልጁ፥ ነፍሱ፡ በልጅቅሁ፡ ተጣብቃለችና፡ ሰጡት፡ ም ሽት፡ ትሁነው።

፱፡ እርሱ፡ በርሳችን፡ እንዛመድ፡ አማቾችም፡ እን ሁን፡ ልጆቻችሁን፡ ሰጡ፡ ለላንተም፡ ልጆቻችንን፡ ው ሰጁ።

፲፡ ከኛም፡ ጋራ፡ ተቀመጡ፡ ምድሪም፡ በፊታች ሁ፡ ትሆናለች። ተቀመጡባት፡ ሸጡ፡ ለውጠ ፡ግ ዙባትም።

፲፩፡ ሴኬምም፡ አባትዋንና፡ወንድሞችዋን፡አሉ። በፊታችሁ፡ ሞገስ፡ ላግኝ፡ ያላችሁኝን፡ ሁሉም፡ እሰ ጣለሁ።

፲፪፡ ማጪዋን፡ እጅግ፡ አብዙ፡ እጅ፡ መንሻም፡ ያ ላችሁትንም፡ ሁሉ፡ እሰጣለሁ። ያኽቺን፡ ብላቴና፡ ፋን፡ አጋቡኝ።

፲፫፡ የያዕቀብም፡ ልጆች፡ ለሴኬምና፡ ለሀሙር፡ ላ ባቱ፡ በተንኰል፡ መለሱ፡ ገሠጹትም፡ ያ,ናን፡ እታች ውን፡ ስላረከሰ።

፲፬፡ አልዋጥውም። ያኽነን፡ ነገር፡ እናደርግ፡ ዘን ድ፡ አደጋለንም፡ እታችነን፡ ላልተገዘረ፡ ሰው፡ እንሰ ጥ፡ ዘንድ። ያኽ፡ ነውር፡ ያሆንብናልና።

፲፭፡ በዚኽ፡ ብቻ፡ እሺ፡ እንላችኋለን፡ እንደኛ፡ ብ ትሆኑ፡ ወንደቻችሁንም፡ ሁሉ፡ ብትገዝረ።

፲፮፡ ልጆቻችንንም፡ እንሰጣችኋለን፡ ከልጆቻችሁ ም፡ ሴቶች፡ እንወሰደለን። በላንትም፡ መኻከል፡ እ ንቀመጣለን፡ አንድ፡ ወገንም፡ እንሆነለን።

፲፯፡ እኛን፡ ባትሰሙ፡ ግን፡ ትገዘሩ፡ ዘንድ፡ ልጆች ነን፡ ያዘን፡ እንሔደለን።

፲፰፡ ነገራቸውም፡ መልካም፡ ሆነ፡ በሀሙር፡ ዘን ድ፡ በሴኬም፡ ዘንድ፡ በሀሙር፥ልጅ።

፲፱፡ ብላቴናውም፡ አልዘገየም፡ ያሉትን፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ የያዕቀብን፡ ልጅ፡ እጅግ፡ ወድዋልና። ባባቱ፡ ቤትም፡ ካሉት፡ ሁሉ፡ እርሱ፡ ከበረ።

፳፡ ሀሙርና፡ ሴኬምም፡ ልጂ፡ ወደገራቸው፡ ደ ጅ፡ መጡ፡ ላገራቸው፡ ሰዎችም፡ ነገረ፡ እንደሀ ሲሉ።

፳፩፡ እሌኽ፡ ሰዎች፡ የሰላም፡ ሰዎች፡ ናቸው፡ ከ ኛ፡ ጋራ። በምድራችን፡ ይቀመጡ፡ ዘንድ፡ እንተዋቸ ው፡ ይሸጡ፡ ይለውጡባትም፡ ዘንድ። ምድሪቱም፡ እንሆ፡ ሰፊ፡ ናት፡ በፊታቸው። ልጆቻቸውን፡ እናገባ ለን፡ ልጆቻችንንም፡ ለርሳቸው፡ እንሰጣለን።

፳፪፡ ነገር፡ ግን፡ ባንድ፡ ነገር፡ ብቻ፡ እሌኽ፡ ሰዎች፡ እሺ፡ ይሉናል፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ይቀመጡ፡ ዘንድ፡ እንድ፡ ወገን፡ እንሆን፡ ዘንድ። ወንደቻችንን፡ ሁሉ፡ ብንገገዝ ር፡ እርሳቸው፡ እንደ፡ ተገዘሩ።

፳፫፡ ከብታቸው፡ ያለቸውም፡ ሁሉ፡ እንሰሶቻቸ ውም፡ ሁሉ፡ ለኛ፡ አደሆኑምን። በዚኽ፡ ነገር፡ ብቻ፡ እሺ፡ ያልናቸው፡ እንደሆን፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ይቀመጣሉ።

፳፬፡ ካገሩም፡ ደጅ፡ የሚወጡ፡ ሁሉ፡ ሀሙርንና፡ ሴኬምን፡ ልጂን፡ አሺ፡ አሉ። ከርሳቸውም፡ ወንደ ች፡ ሁሉ፡ ተገዘሩ፡ ካገሩ፡ ደጅ፡ የሚወጡ፡ ሁሉ።

፳፭፡ ሶስተኛ፡ ቀንም፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ እጅግ፡ ሲቀሰ ልባቸው፡ የያዕቀብ፡ ልጆች፡ ስምዖንና፡ ሌዊ፡ የጂና፡ ወንድሞች፡ ኢየራሳቸው፡ ሰይፈቸውን፡ ያዙ፡ ወደገ ርም፡ ገቡ፡ ሳሂፈሩ፡ ወንጂንም፡ ሁሉ፡ ገደሉ።

፳፮፡ ሀሙርንም፡ ሴኬምንም፡ ልጂን፡ በሰሂፍ፡ ገ ደሉ። ደ,ንም፡ አታቸውን፡ ከሴኬም፡ ቤት፡ወሰደ፡ ወጡም።

፳፯፡ የያዕቀብ፡ ልጆች፡ ወደ፡ ሞቱት፡ ገቡ፡ አገር ም፡ በዘበዙ፡ አታቸውን፡ ስላረከሱባቸው።

፳፰፡ በጎቸውንም፡ ላማቸውንም፡ አህያቸውን ም፡ ባገር፡ ያለውንም፡ በሜዳ፡ ያለውንም፡ ወሰደ።

፳፱፡ ከብታቸውንም፡ ሁሉ፡ ሕሃናቸቸውንም፡ ሁሉ፡ ቤተቻቸውንም፡ ማረኩ፡ በቤት፡ ያለውንም፡ ሁሉ፡ ዘረፉ።

፴፡ ያዕቀብም፡ ስምዖንንና፡ ሌዊን፡ አለ። እኔን፡ አስጨነቃችሁኝ፡ የኮጸላሁ፡ ታደርጉኝ፡ ዘንድ፡ በከነዓ ናውያንና፡ በፈረዛዊያን፡ ዘንድ፡ በዚች፡ አገር፡ በሚኖ ሩ። እኔም፡ በቍጥር፡ ጥቂት፡ ነኝ፡ እርሳቸውም፡ ይሰ በሰቡብኛል፡ ይመቱኝማል፡ እጠፈማለሁ፡ እኔ፡ ከቤ ቴ፡ ጋራ።

፴፩፡ እርሳቸውም፡ አሉ፡ በእታችን፡ እንደ፡ በጋለ ሞታ፡ ይደረግን።

ምዕራፍ፡ ፴፭፡

፩፡ እግዚአብሔርም፡ ያዕቀብን፡ አለው። ተነሣና፡ ወደ፡ ቤቴል፡ ውጣ፡ ከዚያም፡ ተቀመጥ። ከዚያም፡ ለእግዚአብሔር፡ መሠውያ፡ ትከል፡ አንተ፡ ከኳሳ ው፡ ከወንድምኽ፡ ፊት፡ ሰትኰበልል፡ ለተገለጠ ልኽ።

፪፡ ያዕቀብም፡ ቤተ፡ ሰቡን፡ አለ፡ ከርሱ፡ ጋራም፡ ያ ሉትን፡ ሁሉ፡ ሌሎችን፡ አማልክት፡ ከመኻከላችሁ፡ አሸወግዲ፡ ንጹሓንም፡ ሁኑ፡ ልብሳችሁንም፡ ለ ውጡ።

፫፡ እንነሣና፡ ወደ፡ ቤቴልም፡ እንውጣ። ከዚያ ም፡ ለእግዚአብሔር፡ መሠውያ፡ እደርጋለሁ፡ በመከ ራዬ፡ ጊዜ፡ ለሰማኝ፡ በሔድሁበትም፡ መንገድ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ለነበረው።

፬፡ አንግደችንም፡ አማልክት፡ ሁሉ፡ ለያዕቀብ፡ ሰጡት፡ በጂቸው፡ የነበረትን። በጂርዋቸውም፡ የነበ ረትን፡ ጕትቾች። የዕቀብም፡ በሴኬም፡ አጠገብ፡ ካ ለቸው፡ ዛፍ፡ በታች፡ ቀበራቸው።

፭፡ ተነሡተውም፡ ሔዱ፡ የእግዚአብሔርም፡ ፍር ሃት፡ በዙርያቸው፡ ባለ፡ አገር፡ ሁሉ፡ ወደቀ፡ የያዕቀብ ንም፡ ልጆች፡ ለማሳደድ፡ አልተከተልዋቸውም።

፮፡ ያዕቀብም፡ በከነዓን፡ ምድር፡ ወደላቸው፡ ወ ደ፡ ሉዝ፡ መጣ፡ እርስዋም፡ ቤቴል፡ ናት። እርሱ፡ ከር ሱ፡ ጋራም፡ የነበረት፡ ሰዎች፡ ሁሉ።

፮: ከዚሂም: መወውሂ: ሰፊ። የዘሊሂንም: ቦት: ስም: ኤል: ቤቱል ፡የቤቱል፡አምላክነ ፡ብሎ። ጸፊው። ከዘሊሂ: እግዚአብሔር: ተገልጦለታልና: እርሱ: ከወ ንድሙ: ፈት: በሸሸበት: ጊዜ።

፯: ሂቦራም: የርብቃ: ሞግጊት: ሞተች: ከቤቱል ም: በዛፊ: በታች: ተቀበረች: ስሙም: የልቅሶ: ዛፊ: ተብሎ። ተጸፊ።

፰: እግዚአብሔርም: ለሂዕቀብ: ሂግሞ: ተገለጠ ለት: ከሶርሂ: ወንዝ: ከተመለሰ: በኋላ። ባረከውም።

፱: እግዚአብሔርም: አለው። ስም ኽን: እንጊሂህ: ሂዕቀብ: ተብሎ። ኢሂጸፊ: ስም ኽን: እሠራኤል: ሂ ባል: እኽጅ። ስሙንም: እሠራኤል: ጸፊው።

፲፰: እግዚአብሔርም: አለው: እኔ: እግዚአብሔ ር: ሁሉን: የምሂገዝ። ለምልም: ብዛም። ሕዝብ: የ አሕዛብም: ብዛት: ኻንተ: ሂሆናሉ: ነገሥታትም: ከ ወገብ ኽን: ሂወጣሉ።

፲፱: ለአብርሃምኑ: ለሂስሐቅም: የሰጠኋትን: ም ድር: ላንተ: አሰጣለሁ። ኻንተ: በኋላም: ለዘርኽ: ም ድሪቱን: አሰጣለሁ።

፲፫: እግዚአብሔርም: ከርሱ: ወደ: ላይ: ወጣ: ከ ተናገረበት: ቦታ።

፲፱: ሂዕቀብም: ሓምኦ: ተከለ: እግዚአብሔር: ከርሱ: ጋፊ: በተነገረው: ቦታ: የደንጊሂ: ሓምኦ። የ ወጠጥም: መሠዋዕት: በርሱ: አሂረገ: ዘሂትም: አ ፈሰሰበት።

፲፱: ሂዕቀብም: ሂነን: ቦታ: እግዚአብሔር: ከር ሱ: ጋፊ: የተነገረበቱን: ቤቴል: ብሎ: ጸፊው።

፲፯: ከቤቴልም: ተነሡ: ወደ: ኤፍራታም: ሊሂር ሱ: ጥቂት: ሲቀራቸው: ፊሐል: ወለዂት: ምጥም: ጸነሳት: በመውለዂዋ።

፲፱: ሂውም: በመውለዂዋ: ባስጨነቃት: ጊዜ: አ ዋላጂቱ: አለቻት: አሂዘቪኢትፈፊ። ሂኽ: ደግሞ: ወንድ: ልጂ: ላንች: ነውና።

፲፰: ነፍሲዋም: በምትወጣበት: ጊዜ: እርስዋም: ስትሞት: ስሙን: ብንኦኒ: ብሉ: ጸፊች። አባቱ: ግን: ብንሂያሚን: አለው።

፲፱: ፊሐልም: ሞተች። ወደ: ኤፍራታ: በምት ወስሂው: መንገድም: ተቀበረች። እርሰዋ: ቤተል ሔም: ናት።

፳፣ ሂዕቀብም: በመቃብርዋ: ላይ: የደንጊሂ: ሓ ምድ: አቆመ። ሂኽም: የፊሐል: የመቃብርዋ: ሓ ምድ: ነው: እሰከ: ዛፊ።

፳፩: እሠራኤልም: ከዚሂ: ተነሣ: ድንኳኑንም: ተከለ: ከመንጎች: ግምብ: በስተ: ወሂያ።

፳፪: እሠራኤልም: በዚሂች: አገር: በተቀመጠ: ጊዜ: ሮቤል: ሔዲን: በላሃን: ያባቱን: የጭን: ገረድ: ተገኙ፤ችት። እሠራኤልም: ሰማ። የሂዕቀብም: ልጂ ች: አሠራ: ሁለት: ናቸው።

፳፫: የልሂ: ልጂች። የሂዕቀብ: መጂመርሂ: ልጅ: ሮቤል። ሰምዖንም: ሌዊም: ሂሁዲም: ሂሳኮርም: ዛብሎንም።

፳፬: የራሔል: ልጂች: ዮሴፍን: ብንሂሚን።

፳፭: የበላሃም: ልጂች: የራሔል: ባርሂ :ሂንን: ዳ ቪታሌም።

፳፮: የዘለፋም: ልጂች: የልሂ: ባርሂ: ጋድን: አሴ ር። አሌኽ: የሂዕቀብ: ልጂች: ናቸው: በሶርሂ: ወን ዝ: መኽነከል: የተወለዲለት።

፳፯: ሂዕቀብም: ወደ: ሂስሐቅ: ወሂባቱ: መጣ: ወደ: መምረ: የአርባዕ: ከተማ: አርስዋም: ኬብሮ ን: ናት። አብርሃምና: ሂስሐቅ: እንግጂች: ሆነው: ወደ: ተቀመጡባት።

፳፰: የሂስሐቅም: ዕድሜ: መቶ: ሰማኒሂ: አመ ት: ሆነ።

፳፱: ሂስሐቅም: ሂከመ: ሞተም: ወደ: ወገኖቹ ም: ተከማቸ: ሸምግሎ: ዕድሜም: ጠግቦ። ሏሳው ን: ሂዕቀብም: ልጂቹ: ቀበሩት።

ምዕራፊ: ሠሄ:

፩: ሂኽም: የሏሳው: ትውልድ: ነው። እርሱም: ኤሂያሙ።

፪: ሏሳው: ምስቶች: አገባ: ከከነዓን: ልጂች። ሓ ሂን: የሏቱን: የአሂሉንን: ልጂ: አሕሊማንም: የ ሓናን: ልጂ: የሀዊዩን: የዘብሎንን: ልጂ።

፫: ባስማትንም: የእስማኤልን: ልጂ: የነባዩት ን: እት።

፬: ሏሂም:ለሏሳው:ኤሊፈዝን: ወለዲች: ባስማ ትም: ፊጥኤልን: ወለዲች።

፭: አሕሊማማም: ሂሉሰን: ወለዲች: የዕላሁነ ም: ቀፊሀንም። አሌኽ: የሏሳው: ልጂች: ናቸው: በከነዓን: አገር: የተወለዲለት።

፮: ሏሳውም: ምስቶቹን: ወሰሂ: ወንዲችንም: ልጂቹን: ሴቶችንም:ልጂቹን:ቤቱ: ሰቦቹንም: ሁሉ: ከብቱንም: ሁሉ: እንሰቦቹንም: ሁሉ: በከነዓንም: አገር: የገዛውን: ሁሉ: ወደ: ሌላም: አገር: ሔዲ: ከ ሂዕቀብ: ከወንድሙ: ፊት።

፯: ከብታቸው: እጂግ: በዝትዋልና: ባንድም: ሂ ቀመጡ: ዘንድ: አልቻሉም:የተቀመጡባትም:የእ ንግድነታቸው: ምድር: ታንሣቸው: ዘንድ: አልቻለች ም: ከነበራቸው: ከብት: የተነሣ።

፰: ሏሳውም: በሳሒር: ተራራ: ተቀመጠ። እርሱ ም: ሏሳው: ኤሂያም:ነው።

፱: ሂኽም: የሏሳው: ትውልድ: ነው: የኤሂያም: አባት: በሳሒር: ተራራ።

፲: የሏሳው: ልጂች: ስም: ሂኽ: ነው። ኤሊፈዝ: የአሂ: ልጂ: የሏሳው: ምስቶች: ፊጥኤልም: የባስማ ት: ልጂ: የሏሳው: ምስቶች።

፲፩: የኤሊፈዝም: ልጂች: አሌኽ: ናቸው: ቲማ ን: ኦምርም: ሰፊም: ገሂትምዓም: ቀንገዘም።

፲፪፡ ተመናዕም፡ የኤሊፈዝ፡ የሴሳው፡ ልጅ፡ የሞኝ፡ ገረድ፡ ነበረች፡ አማሌቅንም፡ ለኤሊፈዝ፡ ወለደ ችው፡ አሌ ንም፡ ሄሴሳው፡ ምስት፡ የአደ፡ልጆች፡ ናቸው።

፲፫፡ አሌ ንም፡ የራጉኤል፡ ልጆች፡ ናቸው። ናህት፡ ዛራህም፡ ሣማም፡ ሚዛም። አሌ ንን፡ የባስማት፡ የ ሴሳው፡ ምስት፡ ልጆች፡ ናቸው።

፲፬፡ አሌ ንም፡ የአሕሊማ፡ ልጆች፡ ናቸው፡ የአ ናን፡ ልጅ፡ የዘብዖን፡ ልጅ፡ የሴሳው፡ ምስት፡ ለሴሳው ም፡ ደሁስን፡ ወለደች፡ የዕላምንም፡ ቀራህንም።

፲፭፡ አሌ ን፡ የሴሳው፡ ልጆች፡ አለቅች፡ ናቸው። የኤሊፈዝ፡ ልጆች፡ የሴሳው፡ የበክር፡ ልጅ። ቲማን፡ አለቃ። ኦምር፡ አለቃ። ስፎ፡ አለቃ። ቀንዝ፡ አለቀ።

፲፮፡ ቀራህ፡ አለቃ። ገሳትም፡ አለቃ። አማሌቅ፡ አለቃ። አሌ ን። የኤሊፈዝ፡ አለቀች፡ ናቸው፡ በኤደ ም፡ ምድር። አሌ ን። የአደ፡ ልጆች፡ ናቸው።

፲፯፡ አሌ ንም፡ የራጉኤል፡ ልጆች፡ ናቸው፡ የሴሳ ው፡ ልጅ። ናህት፡ አለቃ። ዜራህ፡ አለቃ። ሣማ፡ አለ ቃ። ሚዘ፡ አለቃ። አሌ ን። የራጉኤል፡ አለቀች፡ በኤ ደም፡ ምድር። አሌ ን። የባስማት፡ ልጆች፡ ናቸው፡ የ ሴሳው፡ ምስት።

፲፰፡ አሌ ንም፡ የአሕሊማ፡ ልጆች፡ ናቸው፡ የሴ ሳው፡ ምስት። ሄሁስ፡ አለቃ። የዕላም፡ አለቃ። ቀራ ህ፡ አለቃ። አሌ ን። የአሕሊማ፡ የአና፡ ልጅ፡ የሴሳ ው፡ ምስት፡ አለቀች፡ ናቸው።

፲፱፡ አሌ ን። የሴሳው፡ ልጆች፡ ናቸው፡ አሌ ንም፡ አለቀቻቸው። እርሱም፡ ኤደም፡ ነው።

፳፡ አሌ ን። የሆሪው፡ የሳሂር፡ ልጆች፡ ናቸው፡ በዚ ያች፡ አገር፡ የተቀመጡ። ሎጣን፡ ሾባልም፡ ዘብዓን ም፡ ዓናም።

፳፩፡ ደሾንም፡ ኤጽርም፡ ደሻንም። አሌ ን። የሆ ሪው፡ የሳሂር፡ ልጆች፡ አለቀች፡ ናቸው፡ በኤደም፡ አገር።

፳፪፡ የሎጣንም፡ ልጆች፡ ሆሪ፡ ሒማምም። የሎ ጣንም፡ እት፡ ተመናዕ።

፳፫፡ የሾባልም፡ ልጆች፡ አሌ ን፡ ናቸው። ዓልዋን፡ መንኻትም፡ ሂባልም፡ ሸፂም፡ አውናምም።

፳፬፡ አሌ ንም፡ የዘብዖን፡ ልጆች፡ ናቸው። አያ፡ዓ ናም። ደ ንም፡ ዓና፡ ማዋቶች፡ ያኅኑ፡ ነው፡ በምድረ፡ በደ፡ ያባቱን፡ የዘብዖንን፡ አህሖች፡ ሲብብቅ።

፳፭፡ አሌ ንም፡ የዓና፡ ልጆች፡ ደሾን። አሕሊማ ማም፡ የዓና፡ ሴት፡ ልጅ።

፳፮፡ የደ ሻንም፡ ልጆች፡ አሌ ን፡ ናቸው። ሔም ደን፡ አሸባንም፡ የትራንም፡ ከራንም።

፳፯፡ አሌ ን፡ የኤጽር፡ ልጆች፡ ናቸው። በለሐን፡ ዘሰዋንም፡ ሁቃንም።

፳፰፡ አሌ ን፡ የደ ሻን፡ ልጆች፡ ናቸው። ሁዝ፡ አራ ንም።

፳፱፡ አሌ ን፡ የሆሪያን፡ አለቀች፡ ናቸው። ሎጣን፡ አለቃ። ሾባል፡ አለቃ። ዘብዖን፡ አለቃ። ዓና፡ አለቃ።

፴፡ ደ ሾን፡ አለቃ። ኤጽር፡ አለቃ። ደ ሻን፡ አለቃ። አሌ ን። የሆሪያን፡ አለቀች፡ ናቸው። በሳሂር፡ አገር፡ አለቀች፡ የሆኑ።

፴፩፡ አሌ ንም፡ ነገሥታት፡ በኤደም፡ አገር፡ የነገ ሡ፡ ናቸው፡ በእሥራኤል፡ ልጆች፡ ንጉሥ፡ ሳይነግሥ።

፴፪፡ በኤደምም፡ በለዓ፡ ነገሠ፡ የባሁር፡ ልጅ። ያ ገሪም፡ ስም፡ ደንዛባ፡ ናት።

፴፫፡ በለዓም፡ ሞተ፡ በስፍራውም፡ ዮባብ፡ ነገሠ፡ የዘራህ፡ ልጅ፡ ከባስራ።

፴፬፡ ዮባብም፡ ሞተ፡ በስፍራውም፡ ሁሻም፡ ነገ ሠ፡ ከቴማኒ፡ አገር።

፴፭፡ ሁሻምም፡ ሞተ፡ በስፍራውም፡ ሐሂድ፡ የ ባሂድ፡ ልጅ፡ ነገሠ፡ የሞዓድያንን፡ ሰዋት፡ የመታ፡ በሞ አብ፡ ሚሂ። ያገሪም፡ ስም፡ ዓዊት።

፴፮፡ ሐሂድም፡ ሞተ፡ በስፍራውም፡ ሠምላ፡ ነገ ሠ፡ ከመሥረቃ።

፴፯፡ ሠምላም፡ ሞተ፡ በስፍራውም፡ ሻውል፡ ነገ ሠ፡ በወንዝ፡ አጠገብ፡ ካለችው፡ ከረሆቦት።

፴፰፡ ሻውልም፡ ሞተ፡ በስፍራውም፡ በዓልሐናን፡ ነገሠ፡ የአክቦር፡ ልጅ።

፴፱፡ በዓልሐናንም፡ የአክቦር፡ ልጅ፡ ሞተ፡ በስፍ ራውም፡ ሐሂር፡ ነገሠ። ያገሪም፡ ስም፡ ፈሁ። የዖቦ ቱም፡ ስም፡ መሒጣብኤል፡ የመጥረድ፡ ልጅ፡ የሜ ዛሐብ፡ ልጅ።

፵፡ የሴሳውም፡ ያለቀች፡ ስም፡ ደ ን፡ ነው፡ በወገ ናቸው፡ በስፍራቸውም፡ በስማቸውም። ተመናዕ፡ አለቃ። ዓልዋ፡ አለቃ። የቴት፡ አለቃ።

፵፩፡ አሕሊማ፡ አለቃ። ኤላ፡ አለቃ። ፊኖን፡ አ ለቃ።

፵፪፡ ቀንዝ፡ አለቃ። ቲማን፡ አለቃ። ሚብዛል፡ አለቃ።

፵፫፡ መግዲኤል፡ አለቃ። ዒራም፡ አለቃ። አሌ ን፡ የኤደም፡ አለቀች፡ ናቸው። አንቲ፡ መኖር፡ቸው፡ በግዛታቸው፡ ምድር። ሴሳውም፡ እርሱ፡ የኤደማ ውያን፡ አባት፡ ነው።

ምዕራፍ፡ ፴፯፡

፩፡ ያዕቀብም፡ አባቱ፡ በኗቴኛ፡ በነበረባት፡ ምድር፡ ተቀመጠ፡ በከነዓን፡ ምድር።

፪፡ የያዕቀብም፡ ትውልዷ፡ ይኸ፡ ነው። ዮሴፍ፡ ያ ሠራ፡ ሰባት፡ አመት፡ ልጅ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ በግ፡ ይጠብቅ፡ ነበረ፡ ከወንድሞቹ፡ ጋራ። እርሱም፡ ታናሽ፡ ሳለ፡ ካባ ቱ፡ ምስቶች፡ ከበለዛሃ፡ ከዘልፋ፡ ልጆች፡ ጋራ፡ ነበረ። ዮሴፍም፡ ላባቱ፡ የክፋታቸውን፡ ወረ፡ አመጣለት።

፫፡ እሥራኤልም፡ ዮሴፍን፡ ያወድ፡ ነበረ፡ ከልጆ ቹ፡ ሁሉ፡ ይልቅ። የሸመገልኖው፡ ልጅ፡ ነበረና። ያጌጸ ትም፡ ቀሚስ፡ አደረገለት።

፬፡ ወንድሞቹም፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ አባቱ፡ ከልጆቹ፡ ሁሉ፡

አብልጦ፡እንጂ ወደው፡ጾሉት። የማያችሉም፡ሆኑ፡ በሰላም፡ሄደገሊት፡ዘንድ።

፭ ዮሴፍም፡ ሕልም፡ አለመ፡ ለወንድሞቹም፡ ነገራቸው። ደልቁንም፡ ደግሞ፡ ጾሉት።

፮ አላቸውም። ይኽንን፡ ሕልም፡ ስሙ፡ እኔ፡ ያ ለምሀትን።

፯ እነሆ፡ እኛ፡ በርግ፡ መኻከል፡ነበረን፡ ነጂ፡ ስናሠ ር። እነሆም፡ የኔ፡ ነጂ፡ ቀጥ፡ ብላ፡ ቀመች፡ ነድቀችሁ ም፡ እነሆ፡ ከባ፡ ለነጂዡ፡ ሰገጀች።

፰ ወንድሞቹም፡ አሉት። ንጉሥ፡ ትሆንብን፡ ዘ ንድ፡ ደሆነልን፡ ወደሰ፡ትገዛሄ፡ ዘንድ፡ ደሆነልን። ደግ ሞም፡ ደልቁን፡ ጾሉት፡ ሰለ፡ ሕልሙ፡ ሰለ፡ ነገረም።

፱ ደግሞም፡ ሌላ፡ሕልም፡ አየ፡ ለወንድሞቹም፡ ነገራቸው፡ አለም። እነሆ፡ ሁለተኛ፡ ሕልም፡ አየሁ። ፀሓደን፡ ጨረቃ፡ አሠራ፡ እንድም፡ ከዋክብት፡ ሲሰ ግዲልኝ።

፲ ላባቱና፡ ለወንድሞቹም፡ ነገራቸው። አባቱም፡ ተቀጣው፡ አለውም፡ ምንድር፡ ነው፡ ደኽነ፡ ሃየ ው፡ ሕልም። ምን፡ አልባት፡ እኔና፡ እናት ኽ፡ ወንድ ሞችኽም፡ መጥተን፡ እንሰግድልኽ፡ ደሆን፡ በም ድር፡ላይ።

፲፩ ወንድሞቹም፡ ቀኑበት። አባቱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ደጠብቀው፡ነበር።

፲፪ ወንድሞቹም፡ ሔዲ፡ ያባታቸውን፡ በግ፡ ደጠ ብቂ፡ ዘንድ፡ በሴኬም።

፲፫ አሠራኤልም፡ ዮሴፍን፡ አለው። ወንድሞ ችኽ፡ በሴኬም፡ በግ፡ አደጠብቁምን። ና፡ ወደርሳቸ ው፡ አልክኽ፡ ዘንድ። አርሱም፡አለው፡ እነሆኝ።

፲፬ አለውም። ሒድና፡ እደ፡ ወንድሞችኽና፡ በ ጎች፡ ደሃና፡ እንደሆኑ፡ ወሬያቸውንም፡ መልስልኝ። ከኬብሮንም፡ቀላ፡ሰደደው፡ወደ፡ሴኬምም። መጣ።

፲፭ አንድ፡ሰውም፡ አገኘው፡ እነሆም፡ ብምድረ፡ በደ፡ ጠፍተ፡ ነበር። ጠየቀውም፡ ምን፡ ትፈልጋለኽ፡ ብሎ።

፲፮ አርሱም፡ አለ። ወንድሞቼን፡ አፈልጋለሁ። ወዲት፡ ደጠብቃሉ፡ንገረኝ።

፲፯ ደሰውም፡ አለው። ከዚኽ፡ ሰፍራ፡ ተነሡ፡ወ ደ፡ ደታንም፡ እንሔደለን፡ ሲሉ፡ ሰማኋቸው። ዮሴ ፍም፡ የወንድሞቹን፡ ፈለጋ፡ ደዘ፡ ሔደ፡ በደታንም፡ አገኛቸው።

፲፰ አርሳቸውም፡ከረቅ፡አዩት፡ወደርሳቸውም፡ ሳደቀርብ፡ በርሱ፡ላይ፡ ተማከረ፡ ደገሉት፡ ዘንድ።

፲፱ እንዲም፡ ለወንድሙ፡ አለው። እነሆ፡ ባለ፡ ሕልሙ፡ ደኽነው፡ መጣ።

፳ አሁንም፡ ኑና፡ እንግደለው፡ ከለዛኽም፡ ጉድ ጊደት፡ ወደኀደቸው፡ እንጣለው። ክፈ፡ አርዌም፡ በ ላው፡ እንላለን፡ ከሕልሞቹም፡ የሚሆነውን፡ እና ያለነ።

፳፩ ሮቤልም፡ ደኽነን፡ ሰማ፡ ከጀቸውም፡ አደነ ው፡ አለም፡ ነፍሰ፡ አንግደል።

፳፪ ሮቤልም፡ አላቸው፡ ደም፡ አታፍሰሱ። በዚ ኽነት፡በምድረ፡ በደ፡ ባለቸው፡ ጉድጊድ፡ ጣሉት፡ እ ጀቸሁንም፡ አዘርጉበት። ደኽነንም፡ ማለት፡ ከጀቸ ው፡ ሊደድነው፡ነው፡ወደባቱ፡ ደመልሰው፡ዘንድ።

፳፫ ዮሴፈም፡ ወደ፡ ወንድሞቹ፡በደረሰ፡ጊዜ፡ቀ ሚሱን፡ ገፈፈት፡ ደችን፡ ዝንጉሪቱን፡ ቀሚስ፡ ደለብ ሳት፡ የነበረውን።

፳፬ ወሰጂትም፡ በጉድጊድም፡ ጣሉት። ጉድጊ ዲም፡ የደረቀ፡ነበረ፡ ውኃ፡ የሌለበት።

፳፭ እንጅራዴ፡ ሊበሉ፡ተቀመጡ፡ ዓይናቸውን ም፡ አነሡ፡ አዩም፡ እነሆም፡ የእስማኤላውያን፡ ቅ ፍለት፡ ከገለዓድ፡ የመጣ። ግመሎቻቸውም፡ ሸቱ፡ ተጭነው፡ነበረ፡ አምበርም፡ ከርቤም፡ ወደ፡ ምስር፡ ሃወርጂት፡ዘንድ።

፳፮ ይሁዳም፡ ወንድሞቹን፡ አላቸው። ጥቅማ ችን፡ምንድር፡ነው፡ ወንድማችነን፡ ገድለን፡ ደሙን፡ ብንሸሸግ።

፳፯ ኑ፡ ለእስማኤላውያን፡ እንሸጠው፡ እጀችን ንም፡ በርሱ፡ ላይ፡ አትሁን። ወንድማችን፡ነውና፡ ሠ ጋችንም። ወንድሞቹም፡ የርሱን፡ነገር፡ ሰሙት።

፳፰ ነጋደችም፡ የሚድያን፡ ሰዎች፡ አለፈ። ዮሴ ፍንም፡ አነሡ፡ ከጉድጊድም፡ አወጡት። ለእስማ ኤላውያንም፡ነጋደች፡ዮሴፍን፡ሸጡት፡ በ፳ብያ፡ብር፡ አርሳቸውም፡ዮሴፍን፡ ወደ፡ ምስር፡ አመጡት።

፳፱ ሮቤልም፡ወደ፡ ጉድጊጂ፡ተመለሰ፡ እነሆም፡ ዮሴፍ፡ በጉድጊጂ፡ የለም። ልብሱንም፡ ቀደደ።

፴ ወደ፡ ወንድሞቹም፡ ተመለሰ፡ አለም፡ ብላቴ ናው፡ የለም። እንጊያሀ፡እኔ፡ ወጂት፡ አሔጂለሁ።

፴፩ የዮሴፍንም፡ ቀሚስ፡ ወሰጂ፡ የፍየልም፡ ጥ ቦት፡ አረጂ፡ ቀሚሱንም፡ በጀም፡ ቀቡት።

፴፪ ዝንጉሪቱንም፡ ቀሚሱን፡ ሰደጂ፡ ወደባታቸ ውም፡ አገቡት፡ አሉትም፡ ደኽን፡ አገኘነ። እሰኪ፡እ የው፡ ደኽ፡ የልጅኽ፡ ቀሚስ፡ ነውን፡ ወደሰ፡ አደ ደለም።

፴፫ አርሱም፡ አወቀው፡ አለም፡ አርሱ፡ የልጂ፡ ቀሚስ፡ነው። ክፈ፡ አርዌ፡ በላው። ዮሴፈ፡ ሳደተረ ተር፡ አልቀረም።

፴፬ ደዕቀብም፡ ልብሱን፡ ቀደደ፡ በወገቡም፡ ማ ቅ፡ ለበሰ። ለልጂም፡ አጅግ፡ ቀን፡ አለቀሰ።

፴፭ ወንደች፡ ልጅቱም፡ ሁሉ፡ ሴተችም፡ ሁሉ፡ ተ ነሡ፡ ደጸናኑት፡ ዘንድ። ደጸናም፡ ዘንድ፡ እንቢደለ፡ እንደህ፡ ኢደለ። ወደ፡ ልጂ፡ወደ፡ መታን፡ ስፈራ(ዒ ኦል)፡ አዝ፫፡ እወርዲለሁ። አባቱም፡ ስለርሱ፡ ኢደለ ቀሰ፡ተቀመጠ።

፴፮ የምድያን፡ ሰዎች፡ ግን፡ ዮሴፍን፡ በምስር፡ ለ ጰጢፈር፡ሸጡት፡የፈርዖን፡ ባለምዋል፡ የዘበኖችም፡ አለቃ።

ምዕራፍ፡ ሠጅ፡

፩፡ በዚኢውም፡ ወራት፡ ሂሁሂ፡ ከወንድሞቹ፡ ተለይተ፡ ወረሂ፡ ወደ፡ሀኢለማዊም፡ ሰው፡ገባ፡ ስሙን፡ ሊራ፡ ዮሚሉት።

፪፡ ከዚኢም፡ ሂሁሂ፡ የከነዓናዊ፡ ሰው፡ ስሙን፡ ሸኬ፡ የሚሉት፡ ሴት፡ ልጅ፡ አየ፡ ወሰጂትም፡ ደረሰባ ትም።

፫፡ አረገዘችም፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች። ስሙን ም፡ ኤር፡ ብሎ፡ ጸራው።

፬፡ ደግሞም፡ ፀነሰች፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች። ስ ሙንም፡ ኦና፡ ብላ፡ ጸራችው።

፭፡ ደግሞም፡ ሶስተኛ፡ ልጅ፡ ወለደች፡ ስሙንም፡ ሼላ፡ ብላ፡ ጸራችው፡ አርሱንም፡ በወለደች፡ ጊዜ፡ በክ ዚብ፡ አገር፡ ነበረ።

፮፡ ሂሁሂም፡ የበክር፡ ልጂ፡ ኔ፡ ኤርን፡ ምሽት፡ አጋባ ው፡ ስምዋን፡ ታማር፡ የሚልዋት።

፯፡ ኤር፡ም፡ የሂሁሂ፡ የበክር፡ ልጅ፡ ክፈ፡ ነበረ፡ በእ ግዚአብሔር፡ ፊት። እግዚአብሔርም፡ ገደለው።

፰፡ ሂሁሂም፡ ኦና፡ንን፡ አለው፡ የወንድም፡ኽን፡ ም ሽት፡ አግባ፡ ድረስባትም፡ ለወንድም፡ኽም፡ የሚገባ ውን፡ ፈጸምላት፡ ለርሱም፡ዘር፡ አቁም።

፱ኑ ኦና፡ም፡ አወቀ፡ዘፈ፡ ለርሱ፡ እንደሂሆን፡ወደ፡ ወንድሙ፡ ምሽት፡ በገባ፡ጊዜ፡ በምድር፡ አፈሰሶ፡ ያ ጠፈው፡ ነበረ፡ ለወንድሙ፡ዘር፡ እንደሂሰኖ።

፲፡ ሂኽነነም፡ ማድረጉ፡ ክፈ፡ሆነበት፡ በእግዚአብ ሔር፡ ዘንድ፡ እርሱንም፡ ደግሞ፡ ገደለው።

፲፩፡ ሂሁሂም፡ ታማርን፡ የልጂ፡ ም ሽት፡ አላት። መበለት፡ ሁነሽ፡ ተቀመጭ፡ ባባትሽ፡ ቤት፡ ሼላ፡ ልጂ፡ እስኪያድግ፡ ድረስ። እርሱ፡ ደግሞ፡እንደ፡ ወንድሞ ቹ፡እንደሂሞት፡ብልዋልና። ታማርም፡ ሒደ፡ ባባት ዋ፡ቤት፡ ተቀመጠች።

፲፪፡ ከብዙ፡ ዘመንም፡ በኋላ፡ዮሹዓ፡ልጅ፡ ሞተች፡ ዮሂሁሂ፡ ም ሽት። ሂሁሂም፡በተጸናን፡ ጊዜ፡ የበጎቹን፡ ጸጉር፡ ወደሚቆርጡ፡ ሰዎች፡ ወደ፡ ቲምናት፡ ወጣ፡ እርሱ፡ ሂራም፡ ወደጂ፡ የሀሂለሚው።

፲፫፡ ለታማርም፡ ነገሮች፡ እንደህ፡ ሲሉ። እነሆ፡ አማትሽ፡ ወደ፡ ቲምናት፡ ደወጣል፡ የበጎቹን፡ ጸጉር፡ ሂቆርጥ፡ ዘንድ።

፲፬፡ ታማርም፡ የመበለትነትዋን፡ ልብስ፡ ጣለች፡ መጐናጸፊያም፡ ወሰጂት፡ ተጐናጸፈችም፡ ወደ፡ ቲ ምናትም፡ በሞትወሰጂው፡ መንገድ፡ ደር፡ ተቀመጠ ች፡በሳያይም፡ ደጅ። ሼላ፡እንደጂ፡ አደታለችን፡ ም ሽትም፡ አልሰጠችው።

፲፭፡ ሂሁሂም፡ ባሂት፡ ጊዜ፡ ገለሞታ፡ መሰለችው፡ ፊትዋን፡ ተሸፈኖ፡ ነበረችና።

፲፮፡ ወደርሰዋሃ፡ አገደ፡ አላትም፡ ተዘኝኖ፡ ወ ደንች፡ ልግ። ሶልጂ፡ ምሽት፡ እንደሆነች፡ አላወቀ ምና። እርስዋም፡ አለችው፡ ምን፡ ትሰጠኛለኽ፡ትገ ባብኝ፡ዘንድ።

፲፯፡ እርሱም፡ አላት። እኔ፡ የፈየል፡ ጥቦት፡ ከመን ጋዙ፡ እሰድልሻለሁ። እርስዋም፡ አለችው፡ መያዣ፡ ስጠኝ፡ እስክትሰድልኝ፡ ድረስ።

፲፰፡ አለም፡ ምን፡ መያዣ፡ ልስጥሽ። እርስዋም፡ አለች። ቀለበትኽን፡ አምባርኽንም፡ በትር፡ኽንም፡ በጅ፡ኽ፡ የምቲዛትን። ሰጣትም፡ወደርሰዋም፡ ደረሰ፡ ከርሱም፡ አረገዘች።

፲፱፡ ተነሠታም፡ ሔደች፡ መጐናጸፊያዋንም፡አወ ለቀች፡ የመበለትነትዋንም፡ልብስ፡ ለበሰች።

፳፡ ሂሁሂም፡ የፈየሉን፡ ጥቦት፡ ሰደደ፡በሂለሚ ው፡በወደጂ፡ አጅ፡ ከቤቲቱ፡ አጅ፡ መያዣውን፡ ሊ ወሰድ። እርስዋንም፡ አላገኛትም።

፳፩፡ የዚያንም፡ ሰፈራ፡ ሰዎች፡ ጠየቁ፡ እንደህ፡ ሲሉ። ወደት፡ ናት፡ በመንገድ፡ ደር፡ በሳያም፡ ተቀ ምጣ፡ የነበረችው፡ ገለሞታ። አሉትም፡ ከዚኢ፡ኽ፡ ገለ ሞታ፡ አልነበረችም።

፳፪፡ ወደ፡ ሂሁሂም፡ ተመለሰ፡ አለውም፡ አላገኘ ኋትም። ደግሞም፡ የዚያ፡ ሰፈራ፡ ሰዎች፡ አሉ፡ ከት፡ ከዚ፡ኽ፡ ገለሞታ፡ ተቀምጣ፡ አልነበረችም።

፳፫፡ ሂሁሂም፡ አለ፡ ትውሰደው፡ ገንዘብ፡ ሂሁነላ ት። እኛ፡ ዋዛ፡ እንደንሆን። እነሆ፡ እኔ፡ ደኽቺን፡ ጥ ቦት፡ ሰደድሁላት፡ አንተም፡አላገኘኸትም።

፳፬፡ ከሶስት፡ ወርም፡ በኋላ፡ ለሂሁሂ፡ ነገረት፡ እ ንደህ፡ ሲሉ። ታማር፡ የልጅኽ፡ ም ሽት፡ ገለሞተች፡ ደግሞም፡ በግልሙትና፡ እነሆ፡ አረገዘች። ሂሁሂም፡ አለ፡አውጥዋትና፡ በሳት፡ ትቃጠል።

፳፭፡ እርሳቸውም፡ ሲያወጥዋት፡ ወደማትዋ፡ ሰ ደደች፡ እንደህ፡ ሰትል። ለባለዚኽ፡ ሰው፡ እኔ፡ አረገ ዝሁ። አለትም፡ እወቅ፡ የማነው፡ ሂኽ፡ ቀለበት፡ አ ምባሪስ፡ ዘንጉሰ።

፳፮፡ ሂሁሂም፡ አወቃት፡ አለም። እርስዋ፡ አውነ ተኛ፡ ሆነች፡ ከኔ፡ ደልቅ፡ለሼላ፡ለልጂ፡ስላልሰጠኋት።

፳፯፡ ከዚሂ፡ በኋላም፡ አላወቃትም። የመውለድ ዋም፡ ጊዜ፡ ሲደርስ፡ እነሆ፡ መንታ፡በሆድዋ፡ነበረ።

፳፰፡ በመውለድዋም፡ ጊዜ፡ አንጂ፡ አጂን፡ አወ ጣ። አዋላጂቱም፡ ቀደ፡ ፈትል፡ ወሰደ፡ በጂ፡ አሠረ ች፡ እንደህ፡ ሰትል፡ ሂኽ፡ በፊት፡ ወጣ።

፳፱፡ እርሱም፡ እጂን፡ ሲያገባ፡ እነሆ፡ ወንድሙ፡ ወጣ። እርስዋም፡ አለች፡ አንተ፡ ለምን፡ትቀጂለኽ። ሂኽ፡ ቅድ፡ በላጂኽ፡እሁን። ስሙም፡ ፈረስ፡ተባለ።

፴፡ ከዚህ፡ በኋላም፡ ወንድሙ፡ ወጣ፡ በጂ፡ ቀደ፡ ፈትል፡ የነበረበት። ስሙም፡ ዛራህ፡ ተባለ።

ምዕራፍ፡ ሠዘ፡

፩፡ ዮሴፍ፡ግን፡ ወደ፡ ምስር፡ ወረደ። ጰጢፋርም፡ ገዛው፡ የፈርዖን፡ ባለመዋል፡ ቢትወደጂ፡ የምስር፡ ሰ ው፡ ከእስማኤላውያን፡ እጅ፡ ወሂዚህ፡ ካወረዲት።

፪ እግዚአብሔርም: ከዮሴፍ: ጋራ: ነበረ: ስራው ም: ሁሉ: የቀናለት: ሰው: ነበር። በጌታው: ቤትም: በምስሪው: ነበር።

፫ ጌታውም: አየ: እግዚአብሔር: ከርሱ: ጋራ: አ ንሂለ: የሚሄደርገውንም: ሁሉ: እግዚአብሔር: በ እጁ: ያሰላው: ነበረ።

፬ ዮሴፍም: በጌታው: ዘንድ: ሞገስ: አገኘ: ያገ ለግለውም: ነበር። በቤቱም: ላይ: አሰቀመጠው: የ ሚገዛውንም: ሁሉ: በእጁ: ሰጠው።

፭ በቤቱም: ላይ: ካሰቀመጠው: በኋላ: በገዛው ም: ሁሉ: ላይ: ከዚሂ: ዘመን: ጀምሮ: እግዚአብሔ ር: የምሰሪውን: ቤት: ስለ: ዮሴፍ: ባረከው። የለግ ዚአብሔርም: በረከት: በከብቱ: ሁሉ: ነበር: በቤት ም: በሚሂም።

፮ ከብቱንም: ሁሉ: በዮሴፍ: እጅ: አሳልፎ: ሰጠ ው: ከከብቱም: የሚሂውቀው: አልነበረም: ከሚ በላው: እንጅራ። በቀር። ዮሴፍም: መልኩ: ያማረ: ነ በረ: ፊቱም: የተዋበ: ነበር።

፯ ከዚኽነም: በኋላ: የጌታው: ምስት: ሳሂንዋ ን: በዮሴፍ: ላይ: ጣለችበት: አለችውም: ከኔ: ጋራ: ተኛ።

፰ እርሱም: እመቢሂለ: ለጌታውም: ምስት: አ ላት። እነሆ: ጌታዬ: በቤቱ: ከኔ: ጋራ: ያለውን: ከብ ት: አሂውቅም: ያለውንም: ሁሉ: በእጁ: ሰጠኝ።

፱ በዚች: ቤት: ከኔ: የሚበልጥ: ሰው: የለም: ያ ልሰጠኝም: ነገር: የለም: ካንት: በቀር። ምስቱ: ነሽ ና። እንሂት: ያ ኽነን: እሂግ: ኽፉ: ነገር: አደርጋለሁ: በ እግዚአብሔርስ: ፊት: ኃጢአት: አሰራለሁ።

፲ ሂሀንን: ነገር: ለዮሴፍ: ዕለት: ዕለት: ትነግረው: ነበረች። እርሱም: አልሰማትም: ከርስዋ: ጋራ: ሂተ ኛ: ዘንድ: ከርስዋም: ጋራ: ሂሀን: ዘንድ።

፲፩ ከብዙም: ቀን: አንድ: ቀን: ዮሴፍ: ወደ: ቤ ት: ገባ: ተግራጉን: ሃደርግ: ዘንድ: ከቤቱም: ሰዎች: ማንም: ከዚሂ: በቤት: አልነበረም።

፲፪ ልብሱንም: ተጠጣምጣ: ሃዘች: አለችውም: ከኔ: ጋራ: ተኛ። እርሱም: ልብሱን: በእጁዋ: ተወላት: ሸሸም: ወደ: ሚሂም: ወጣ።

፲፫ ልብሱንም: በእጁዋ: አንድ: ተወ: ባዮች: ጊዜ: ሸሸተም: አንድ: ወጣ።

፲፬ የቤትዋን: ሰዎች: ወደርሰዋ: ጸራች: አለቻቸ ውም: እዩ: ዕብራዲ: ሰው: አግብተብኃለና: ሊጫወ ትብኔ: ወደኔ: ገባ: አብሮኝ: ሊተኛ: እኔም: ድምፄን ም: ከፍ: አድርጌ: ጮኽሁ።

፲፭ ድምፄንም: ከፍ: አድርጌ: አንድ: ጮኽሁ: ቢሰማ: ልብሱን: በኔ: ዘንድ: ጥሎልኝ: ሸሽ: ወደ: ሚ ሂም: ወጣ።

፲፮ ልብሱንም: ከርስዋ: ዘንድ: አኖረች: ጌታው: ወደ: ቤቱ: እስኪገባ: ድረስ።

፲፯ ሂሀንን: ነገር: ነገረችው: እንዲህ: ሰትል። ያገባ ኽልን: ዕብራዲው: ባርሂ: ወደኔ: ገባ: ሊጫወትብኝ።

፲፰ እኔም: ድምፄን: ከፍ: አድርጌ: ሰጮኽ: ልብ ሱን: በእጁ: ተወውና: ወደ: ሚሂ: ሸሸ።

፲፱ ጌታውም: የምስቱን: ነገር: በሰማ: ጊዜ: የነገ ሬችውን: እንዲህ: አደረገች: ባርሂኽ: ብላ: እጅግ: ተቀጣ።

፳ የዮሴፍም: ጌታ: ወሰደው: በግዞትም: አገባ ው: የንጉሡ: እሥሮች: ወደሚታሠሩበት: ሰፈራ። ከ ዚሂም: በግዞት: ነበረ።

፳፩ እግዚአብሔርም: ከዮሴፍ: ጋራ: ነበር: ም ሕረትም: አደረገለት። ሞገስም: ሰጠው: በግዞቱ: አ ለቃ: ፊት።

፳፪ የግዞቱም: አለቃ: በግዞት: ያሉትን: እሥሮ ች: ሁሉ: ብዮሴፍ: እጅ: አሳልፎ: ሰጣቸው። ከዚሂ ም: ያደረጉት: ነገር: ሁሉ: እርሱ: የሚያደርገው: ነበር።

፳፫ የግዞቱም: አለቃ: በእጁ: ያለውን: ነገር: ከ ት: አላሰበም: እግዚአብሔር: ከርሱ: ጋራ: ስላለ። የ ሚያደረገውንም: ሁሉ: እግዚአብሔር: ያቀናለት: ነበር።

ምዕራፍ: ፵:

፩ ከዚኽነም: ነገር: በኋላ: የምስር: ንጉሥ: ጸጅ: አሳላፊ: የንጅራ: አበዛው: ክፉ: ሰሩ: በጌታቸው: በምስር: ንጉሥ: ላይ።

፪ ፈርዖንም: በሁለቱ: አለቀቹ: ላይ: ተቀጣ: በ ጸጅ: አሳላፊውና: በንጅራ: አበዛው።

፫ አሰጠበቃቸውም: በዘበኞች: አለቃ: ቤት: በግ ዞት: ቤት: ዮሴፍ: ታሠር: ወደለበቱ: ሰፈራ።

፬ ግለቃውም: ለዮሴፍ: አሳልፎ: ሰጣቸው: ያገ ለግላቸውም: ነበር። በግዞትም: አያሌ: ቀን: ተቀ መጡ።

፭ ሁለቱም: ሕልም: አዩ: ኢያራሳቸው: ባንድ: ሌት: ሕልሙን: አዮ። ኢያራሳቸውና: እንደ: ሕልሙ: ትርጓሜ: የምስር: ንጉሥ: ጸጅ: አሳላፊና: የእንጅ ራ: አበዛው: በግዞት: ታሠረው: የነበረት።

፮ ዮሴፍም: ማልደ: ወደርሳቸው: ገባ: እነሆም: አዝነው: አያቸው።

፯ የፈርዖንንም: አለቀች: ጠቦቀ: ከርሱ: ጋራ: በ ግዞት: የነበረትን: በጌታው: ቤት: እንደሂ: ሲል: ስ ለ: ምን: ፊታችሁ: ዛሬ: ጠውርዋል።

፰ አሉትም: ሕልም: አዮ: የሚተረጕመውም: አጣ። ዮሴፍም: አላቸው: በውኑ: ትርጓሜ: ለእግ ዚአብሔር: አደደለምን። የዖትሁትን: ንገረኝ።

፱ ጸጅ: አሳላፊውም: ሕልሙን: ለዮሴፍ: ነገረ ው: አለም። በሕልሜ: የወደን: ዛፍ: አየሁ: በፊቴ: ሁኖ።

፲ በዛፉቱም: ሶስት: ሐረግ: አለባት: አርስዋም: ቀጠልን: አበባ: አውጥታ: ነበረች: ዘለላም: አንጠል ጥላ: ነበረች: የዘለላዋም: ቤረ: በሰሉ: ነበር።

፲፭፥ የፈርዖንም፡ ጽዋ፡ በጀ፡ ነበር። ፍሬውንም፡ ወሰጀ፡ በፈርዖን፡ ጽዋ፡ ጠመቅሁት፡ ጽዋውንም፡ ለ ፈርዖን፡ በጀ፡ሰጠሁት።

፲፱፥ ዮሴፍም፡ አለው። ትርጒሜው፡ ደ ኽ፡ ነው። ሶስቱ፡ ሐረግ፡ ሶስት፡ ቀን፡ ነው።

፲፫፥ ከሶስት፡ ቀንም፡ በኋላ፡ ፈርዖን፡ ራስ ኽን፡ ከ ፍ፡ያደርጋል፡ ወደ፡ ቀድመውም፡ ኩመት ኽ፡ ደመል ስ ኻል። የፈርዖንንም፡ ጽዋ፡ በጀ፡ ትሰጣለ ኽ፡ እን ደ፡ ቀደመው፡ ሥርዓት፡ ጸጅ፡ አሳላፊው፡ በነበር ኽ፡ ጊዜ።

፲፬፥ ነገር፡ ግን፡ እኔን፡ አስበኝ፡ በጎ፡ ነገ፡ ባኘ ኽ፡ ጊ ዜ፡ ምሕረትም፡ አድርግልኝ። በፈርዖን፡ ፊት፡ ታስበ ኝ፡ ዘንድ፡ ከዚ ኽ፡ነም፡ ቤት፡ ታወጣኝ፡ ዘንድ።

፲፭፥ እኔ፡ ከዕብራውያን፡ አገር፡ ተሰርቂያለሁና። ከዚ ኽ፡ነም፡ ደግሞ፡ እንጀኽ፡ አልሰራሁም፡ በግዞት፡ ያኖረኝ፡ዘንድ።

፲፮፥ አንጅራ፡ አበዛውም፡ አየ፡ ሕልሙን፡ መልካ ም፡ እንደፈታው፡ ዮሴፍንም፡ አለው። እኔም፡ ደግ ሞ፡ በሕልሜ፡ ነበርሁ፡ እነሆም፡ ሶስት፡ ሞሰብ፡ ነጭ፡ እንጅራ፡ በራሴ፡ላይ፡ነበር።

፲፯፥ በላይኛውም፡ ሞሰብ፡ ፈርዖን፡ ከሚበላው፡ ከጋጋሮች፡ ሰራ፡ ሁሉ፡ ነበረበት። ወፎችም፡ ከርሱ፡ ደ በሉ፡ነበረ፡ በራሴ፡ላይ፡ካለው፡ ሞሰብ።

፲፰፥ ዮሴፍም፡ መለሰ፡ አለውም፡ ትርጒሜው፡ ደ ኽ፡ነው። ሶስቱ፡ ሞሰብ፡ ሶስት፡ ቀን፡ ነው።

፲፱፥ ከሶስት፡ ቀንም፡ በኋላ፡ ፈርዖን፡ ራስ ኽን፡ ካ ኻተ፡ደወሰደዋል፡በኀጩት፡ላይም፡ ደሰቅል ኻል። ሥ ፎችም፡ሥጋ ኽን፡ ካኻተ፡ ደበሉታል።

፳፫፥ በሶስተኛውም፡ ቀን፡ ፈርዖን፡ የተወለደበት፡ ቀን፡ነበረ፡ ምሳም፡ አደረገ፡ለብላቴኖቹ፡ሁሉ። ጸጅ፡ አሳላፊውንና፡ የአበዘችንም፡ አለቃ፡ አሰበ፡በሎላ ቱ፡መ ኽነከል።

፳፭፥ ጸጅ፡ አሳላፊውንም፡ ወደ፡ስፈራው፡መለሰ ው። በፈርዖን፡ እጅም፡ ጽዋሁን፡ሰጠ።

፳፪፥ የአበዘችንም፡ አለቅ፡ በንጩት፡ ላይ፡ ሰቀለ ው። ዮሴፍ፡ እንደ፡ ተረጐመላቸው።

፳፫፥ ጸጅ፡ አሳላፊው፡ ግን፡ ዮሴፍን፡ አላሰበው ም፡ረሳው፡እንጅ።

ምዕራፍ፡ ፵፩፥

፩፥ ከሁለት፡ አመትም፡በኋላ፡ ፈርዖን፡ ሕልም፡ አ የ፡ እነሆም፡በወንዝ፡ ደር፡ ቁሞ፡ነበረ።

፪፥ እነሆም፡ ሰባት፡ ላሞች፡ ከወንዙ፡ ወጡ፡ መል ካቸው፡ ያማረ፡ሥጋቸውም፡ የሠነደነ። በመስክም፡ ደሰማሩ፡ነበር፡በውኃው፡ደር።

፫፥ እነሆም፡ ሰባት፡ ላሞች፡ ሌሎች፡ከርሳቸው፡በ ኋላ፡ከወንዝ፡ ወጡ፡ መልካቸውም፡ የከፋ፡ ሥጋቸ ውም፡የከሳ። በለዚያም፡ ላሞች፡ አጠገብ፡ደቀሙ፡ ነበር፡በወንዝ፡ደር።

፬፥ ባያንም፡ የከፋት፡ላሞች፡ ሠጋቸውም፡ የከሰ፡ ሰባቱን፡ በመልካቸው፡ ያማረታን፡ ደንደያችን፡ ላሞ ች፡ ዋጥዋቸው። ፈርዖንም፡ነቃ።

፭፥ ደግሞም፡ ተኛ፡ ሁለተኛ፡ ሕልምም፡ አየ። እነ ሆም፡ ባንድ፡ አገደ፡ ሰባት፡ እሸቶች፡ ወጡ፡ የደነደኑ፡ ያማረ።

፮፥ እነሆም፡ ሰባት፡ እሸቶች፡ የቀጠኑ፡ ከርሳቸው፡ በኋላ፡ ወጡ፡ ትኩሰ፡ነፈሰ፡ የመታቸው።

፯፥ የረቀቁትም፡ እሸቶች፡ ሰባቱን፡ መልካሞችን፡ እሸቶች፡ የመሉትን፡ ዋጥዋቸው። ፈርዖንም፡ነቃ፡እ ነሆም፡ሕልም፡ ሆነ።

፰፥ በአባም፡ ጊዜ፡ ሰውነቱ፡ታወከችበት፡ ወደ፡ ኩ ከብ፡ ቀጣሮች፡ሁሉ፡ ወደ፡ ምስርም፡ አዋቀች፡ ሁሉ፡ ላከ፡ ወደርሱም፡ ጸሬቸው። ፈርዖንም፡ሕልሙን፡ነ ገራቸው። ለፈርዖንም፡የሚፈታለት፡አልተገኘም።

፱፥ የዚያን፡ጊዜ፡ ጸጅ፡ አሳላፊው፡ ፈርዖንን፡ተናገ ረው፡እንደህ፡ቢል። እኔ፡ኃጢአቴን፡ዛሬ፡አስባለሁ።

፲፡ ፈርዖን፡ ባርቹን፡ ተቀጣ፡ እኔንም፡ በግለቃው፡ ቤት፡ ግዞት፡ ጣለኝ።

፲፩፥ እኔንና፡ አንጅራውን፡ አዛዝ። ባንዲት፡ ሌት ም፡ እኔና፡ እርሱ፡ ሕልም፡ አየነ፡ ከኛ፡ ኢያንዳንዳች ን፡ ሕልሙን፡ አየ፡ እንደ፡ ፍቹ።

፲፪፥ ከዚያም፡ አንድ፡ የዕብራውያን፡ ብላቴና፡ ከ ኛ፡ ጋራ፡ነበረ፡ የግለቃው፡ ባርያ። ሕልማችንም፡ነገር ነው፡ እርሱም፡ ፈታልነ። ለያንዳንዱ፡ እንደ፡ሕልሙ፡ ፈታ።

፱፡ የፈተኖውም፡ዕፃ፡ ከአሣፍ፡ ወገን፡ ለነበረው፡ ለዮሴፍ፡ ወጣ፡ ሁለተኛውም፡ ለጌዲልያ፡እርሱ፡ልጆ ቹም፡ ወንድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፡ ሶስተኛው፡ ለዘኩር፡ ልጆቹና፡ ወንድሞቹም፡አ ሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፩፡ አራተኛው፡ ለዞጽሪ፡ ልጆቹና፡ ወንድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፪፡ አምስተኛው፡ ለነታንሃ፡ ልጆቹና፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፫፡ ሰድስተኛው ፡ ለቡቂሂ ፡ ልጆችና ፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፬፡ ሰባተኛው፡ ለሂዘርኤል፡ልጆቹና፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፭፡ ስምንተኛው፡ላሂሻዕሃ፡ ልጆቹና፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፮፡ ዘጠነኛው ፡ ለማታንሃ ፡ ልጆቹና ፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፯፡ አሠረኛው ፡ ለሺምኢ ፡ ልጆቹና ፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፰፡ አሠራ፡ አንሂኛው፡ለዓዘርኤል፡ልጆቹና፡ ወን ድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፲፱፡ አሠራ፡ ሁለተኛው፡ለሀሸብሃ፡ልጆቹና፡ወንድ ሞቹም፡አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፡ አሠራ፡ ሶስተኛው፡ ለሹባኤል፡ ልጆቹና፡ወንድ ሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፩፡ አሠራ፡ አራተኛው ፡ ለማቲትሂ፡ ልጆቹና፡ ወ ንድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ነበረ።

፳፪፡ አሠራ፡ አምስተኛው ፡ ለሂሪሞት፡ ልጆቹና፡ ወንድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፫፡ አሠራ፡ሰድስተኛው፡ ለሀናንሃ፡ ልጆቹና፡ወን ድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፬፡ አሠራ ፡ ሰባተኛው ፡ ለዮሠበቃሣ፡ ልጆቹና፡ ወንድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፭፡ አሠራ፡ ስምንተኛው ፡ ለሀናኒ፡ ልጆቹና፡ ወን ድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፮፡ አሠራ፡ ዘጠኛው፡ ለመሎቲ፡ ልጆቹና፡ወንድ ሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፯፡ ኘሂያኛው ፡ ለኤልያታ ፡ ልጆቹና ፡ ወንድሞቹ ም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፰፡ ኘሂያ፡አንሂኛው፡ለሆቲር፡ ልጆቹና፡ ወንድሞ ቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፳፱፡ ኘሂያ፡ ሁለተኛው፡ ለጊደልቲ፡ ልጆቹና፡ ወንድ ሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፴፡ ኘሂያ፡ ሶስተኛው ፡ ለመሀዚአት ፡ ልጆቹና፡ ወን ድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

፴፩፡ ኘሂያ፡ አራተኛው ፡ ለሮመምቲኤዝር፡ ልጆቹ ና፡ ወንድሞቹም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ነበረ።

ምዕራፍ፡ ፮፯፡

፩፡ በረኞችም፡ እንደዚህ፡ ትከፈሉ። ከቀረህ፡ ወገ ን፡ መቨለምያ፡ ነበረ፡ የቀረ፡ ልጁ ፡ ከአሣፍ፡ ልጆች።

፪፡ የመሸለምያም፡ ልጆች፡መጀመርያው፡ዘካርያ ስ፡ ሁለተኛው፡ ደዲዓኤል፡ ሶስተኛው፡ ዘበድያ፡አራ ተኛው፡ የትኒኤል።

፫፡ አምስተኛው ፡ ዒላም፡ ሰድስተኛው፡ ይሆሐና ን፡ ሰባትኛው፡ ኤልይሆኤናሂ።

፱፡ የሠቤድኤደም፡ ልጆች፡ መጀመርያው፡ ሽማዕያ፡ ሁለተኛው፡ ይሆዛባድ፡ ሶስተኛው፡ ዮአሕ፡አራተኛው፡ ሣካር፡ አምስተኛው፡ ናትናኤል።

፭፡ ስድስተኛው፡ ዓሚኤል፡ ሰባተኛው፡ ይሳኮር፡ ስምንተኛው፡ ፈሁሌታይ፡ እግዚአብሔር፡ ባርኮታልና።

፮፡ ለሸማዕያም፡ ለልጁ፡ ልጆች፡ ተወለዱ፡ ባባታቸው፡ ቤት፡ የሠለጠኑ፡ እጅግም፡ ኃያላን፡ ነበሩና።

፯፡ የሸማዕያም፡ልጆች፡ ዖትኒ፡ረፋኤልም፡ ዖቤድ ም፡ ኤልዛባድም፡ ወንድሞቹም፡ አጅግ ፡ ጨካኖች፡ ሰዎች፡ ነበሩ፡ አሊሑና፡ ሰመኽያ።

፰፡ አሌ ኽ፡ሁሉ፡ከዖቤድኤደም፡ ልጆች፡ ነበሩ፡አ ርሳቸውና፡ ልጆቻቸው፡ በማገልገል፡ኃያላንና፡ጨካኖ ች፡ ሰዎች፡ ስድሳ፡ ሁለት፡ ከዖቤድኤደም።

፱፡ የመሸለምያም፡ ልጆች፡ወንድሞቹም፡አጅግ፡ ጨካኖች፡ አሥራ፡ ስምንት፡ነበረ።

፲፡ የሆሣም፡ ልጆች፡ አርሱም፡ ከመራሪ፡ልጆች፡አ ለቃው፡ ሠምሪ፡ ነበር። በኩር፡ ልጅ፡ አልነበረምና፡ አ ባቱ፡ አለቃ፡ አደረገው፡ አንጅ።

፲፩፡ ሁለተኛው፡ ሒልቅያ፡ ሶስተኛው፡ጠበልያ፡ አ ራተኛው፡ ዘካርያስ። ይሆሣም፡ ልጆች፡ ሁሉ፡ ወንድ ሞቹም፡ አሥራ፡ ሶስት፡ ነበረ።

፲፪፡ አሌ ኽ፡ በረኞች፡ የጠባቂች፡ አለቆች፡ ሁነው፡ አንሂ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ተከፈሉ ፡ በእግዚአብሔር፡ ቤት፡ ያገለግሉ፡ዘንድ።

፲፫፡ ዕፃውንም፡ ለታናሾችና፡ለታላላቆች፡ አስተካክ ለው፡ ጣሉ፡ በወገኑ፡ቸው፡ በሂጂ ፡ ሁሉ ፡ ያገለግሉ፡ ዘንድ።

፲፬፡ ለሸለምያም፡በምሥራቅ፡ዕፃ፡ወደቀ፡ ለልጂ ም፡ ለዘካርያስ፡ ለምክር፡ አዋቂው፡ሰው፡ አጅግም፡ ለሚያስተውለው፡ ዕፃ፡ ጣሉ፡ ዕፃውም፡በመስዕ፡ወ ደቀ።

፲፭፡ ለዖቤድኤደም፡በዓዙብ፡ ወደቀ፡ለልጂቹም፡ በመከማቻው፡ ቤት፡ አጠገብ፡ ነበረ።

፲፮፡ ለሡፊምና፡ለሆሣም፡ወደ፡ምዕራብ፡ወደቀ፡ ወደ፡ አቀበቱም፡ መንገድ፡ ወደሚወሰደው፡ ደጅ።

፲፯፡ ወደ፡ ምሥራቅ ፡ ስድስት ፡ ሌዋውያን፡ ነበረ፡ ወደ፡መሰዕም፡ አራት፡ ዕለት፡ዕለት፡ ወደ፡ዓዜብም፡ አራት፡ ዕለት፡ ዕለት፡ መዝማቻም ፡ ወደሚሆንበት፡ ሁለት፡ሁለት።

፲፰፡ በአየራሹ፡ ዓምደኞ፡ በምዕራብ፡ ትሂዩ፡ አራ ት፡ በመንገኑ ፡ ሁለቱም፡ በአደራሹ፡ ዓምደኞ፡ነበረ።

፲፱፡ የበረኞችም፡ የቀረሀና፡ የመራሪ ፡ ልጆች፡ ክፍ ል፡ ደህ፡ ነበር።

፳፡ ከሌዋውያንም፡አሂያ፡በእግዚአብሔር፡ቤት፡ ሣፅን፡ ላይ፡ ነበረ፡ በተቀደሰውም፡ ዕቃ፡ ሣፅን፡ላይ።

፳፩፡ የለዕደን፡ ልጆች። የጌርሾኒው፡የለዕደን፡ልጆ ች። የለዕደንም፡ የጌርሾኒው፡ ወገን፡ አለቆች፡ አሂኤ ሊ፡ነበረ።

፳፪፡ የደሂኤሊ፡ ልጆች፡ዜታም፡ ዮኤልም፡ወንድ ሙ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ክብት፡ ላይ፡ የነበረት።

፳፫፡ ከሳመራም፡ወገን፡ ከደጅሐርም፡ ወገን፡ከሌ ብሮንም፡ ከሁዚኤልም፡ አሌ ኽ ፡ የነበረት ፡ ናቸው።

፳፬፡ በኩብቱ፡ ላይ፡ የሚያዝ፡ ሸቡኤል፡ ነበረ፡ የጌ ርሾም፡ ልጅ፡ የሙሴ፡ ልጅ።

፳፭፡ ወንድሞቹም ፡ ከኤሊዔዝር፡ ወገን፡ ረ ኻብ ያ፡ ልጂ ፡ ይሻዕያ፡ልጂ ፡ ዮራም፡ ልጂ ፡ ዚክሪ፡ ልጂ ፡ሸ ሎሚት፡ ልጂ።

፳፮፡ ይህም፡ ሸሎሚት ፡ ወንድሞቹ፡ ነጉሡ፡ደዊ ት፡ በቀደሰው፡ ቅድሳት፡ ክብት፡ ላይ፡ ተሹመው፡ ነበ ረ፡ የወገኖችም ፡ አለቆች ፡ የሽ ኽና፡ የመተም፡ አለቀ ች፡ የጭፍራም፡ አለቆች፡ በቀደሱት፡ ሁሉ፡ ላይ።

፳፯፡ ከሰልፋና፡ ከምርኮ፡ ክብቱን ፡ ቀደሱት፡ የአ ግዚአብሔርን፡ መቅደስና፡ ዕቃውን፡ ለማበጀት።

፳፰፡ ተመልካቹም ፡ ሳሙኤል፡ የቀደሰው፡ ሁሉ፡ ሳኦልም፡ የቂሥ፡ ልጅ፡ አብኔርም፡ የኔር፡ ልጅ፡ ዮአብ ም፡ የጽሪያ፡ ልጅ፡ የተቀደሰውም ፡ ክብት፡ ሁሉ፡በሸ ሎሚትና፡በወንድሞቹ፡ እጅ፡ ነበረ።

፳፱፡ ከይጽሐርም፡ ልጆች ፡ ክነንያና፡ ልጆቹ፡ በሚ ደ፡ ስራ፡ ሁሉ፡ በእሥራኤል፡ላይ፡ነበረ፡ሹማምትም፡ ፈራጆችም፡ ሆኑ።

፴፡ ከሄብርንም፡ ልጆች ፡ ሀሽብያ፡ ወንድሞቹም፡ እጅግ፡ ኃያላን፡ ሰዎች ፡ ሽ ኽ፡ ከሰባት፡ መቶ፡ ነበረ፡ በ እሥራኤል፡ ላይ፡ የተሾመ፡ በዮርደናስ፡ ማደ፡ በምዕ ራብ፡ ትደዩ፡በእግዚአብሔር፡ሰራ፡ ሁሉ፡በንጉሡም፡ ማገልገያ።

፴፩፡ ከሄብርንም፡ወገን፡ ደሪያ፡የሄብርን፡ልጆች፡ አለቃ ፡ ነበር ፡ አንደባቶቹ፡ ዘመደኞ። ደዊት፡ በነገሠ፡ ባርባ፡አመት ፡ ይሸዋቸው፡ ነበረ፡ከርሳቸውም፡ በጊል ዓድ፡ በየዕዜር፡ አጅግ፡ ጽኑዓን፡ ሰዎች፡ ተገኙ።

፴፪፡ ወንድሞቹም፡ ኃይል፡ያላቸውም፡ ሰዎች፡ሁ ለት፡ ሽ ኽ፡ ከሰባት፡ መቶ ፡ ነበረ ፡ የወገን፡ አለቆች፡ ን ጉሡም፡ ደዊት፡ በሮቤልና ፡ በጋድ፡ ላይ፡ በምናሴም፡ ነገድ፡ አኩሌታ ፡ ላይ፡ አደረጋቸው ፡ ለእግዚአብሔር ና፡ ለንጉሠ፡ ማገልገል፡ ሁሉ።

ምዕራፍ፡ ፳፯፡

፩፡ የአሠራኤልም፡ ልጆች፡ አንሂ፡ ቍጥራቸው፡ያ ባቶች፡ አለቆች ፡ የሽ ኽና ፡ የመቶ ፡ አለቆች፡ ንጉሡን ም፡ የሚያገለግሉ፡ በክፍላቸው፡ በወር፡ በወር፡ የሚ ገቡ፡የሚወጡም፡ባመቱ፡ወር፡ሁሉ፡በየክፍሉ፡ ኽነ፡ አራት ፡ ሽ ኽ፡ነበረ።

፪፡ በመጀመርያው ፡ ወር ፡ የሾብዓም ፡ የዘብጂኤ ል፡ ልጅ፡ በፈተኖው፡ክፍል፡ ተሹሞ፡ ነበረ፡ የሠራዊቱ ም፡ ክፍል፡ ኽነ፡ አራት፡ ሽ ኽ፡ ነበር።

፫፡ አርሱም፡ ከፈረሶ፡ ወገን ፡ የጭፍራውም፡ አለ ቀች፡ ሁሉ፡ አለቃ፡ በመጀመርያው፡ ወር፡ ነበረ።

፬፡ በሁለተኛውም ፡ ወር ፡ ሠራዊት፡ ላይ፡ የአሆሂ

ው፡ ደኗይ፡ ነበረ፡ ከርሱም፡በኋላ፡ ሚቅሎት፡ አለቃ፡ ነበር፡ የሠራዊቱም፡ ክፍል፡ ኽያ፡ አራት፡ ሽኽ፡ ነበር።

፭፡ የሶስተኛውም፡ሠራዊት፡ አለቃ፡በየሶስተኛው፡ ወር፡ ብናያ፡ ነበር ፡ የካህኑ፡ የዮኗይ፡ ልጅ፡ የሠራዊቱም፡ ክፍል፡ ኽያ፡ አራት፡ ሽኽ።

፮፡ ደህም፡ብናያ፡ እጅግ፡ብርቱ፡ነበር፡በሠላሳው፡ መኻከል፡ ከሠላሳውም፡ በላይ፡ በሠራዊቱም፡ላይ፡ ልጁ፡ ኳሚዛባድ፡ ተሹሞ፡ነበረ።

፯፡ አራተኛው፡ አለቃ፡ባራተኛው፡ ወር፡ አሣሤል፡ የዮአብ፡ ወንድም፡ ነበረ ፡ ከርሱም፡ በኋላ፡ ልጁ ፡ ዘበድያ፡ በሠራዊቱም፡ ኽያ፡ አራት፡ ሽኽ።

፰፡ አምስተኛው ፡ ባምስተኛው፡ ወር፡ ሠምሁት፡ የደዝረሒው፡አለቃ፡ ነበረ፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡አራት፡ ሽኽ።

፱፡ ስድስተኛው ፡ ባምስተኛው፡ ወር፡ ዒራ፡ የተቀዒው፡ የዒቄስ፡ ልጅ፡ነበረ፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡አራት፡ ሽኽ።

፲፡ ሰባተኛው፡በሰባተኛው ፡ ወር፡ ሔሌጽ፡ የፈሎኒው፡ነበረ፡ ከኤፍረም፡ ልጆች፡ሠራዊቱም፡ ኽያ፡ አራት፡ሽኽ።

፲፩፡ ስምንተኛው ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ የሁሻቲው፡ዒብካይ፡ ነበረ፡ ከዘርሒ፡ ወገን፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡አራት፡ ሽኽ።

፲፪፡ ዘጠነኛው፡ በዘጠነኛው፡ ወር፡ የሳንተቲው፡ አቢዔዝር፡ ነበረ፡ ከብንያም፡ ወገን፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡ አራት፡ ሽኽ።

፲፫፡ አሠረኛው፡ባሠረኛው፡ወር፡ የነጦፋቲው፡መሐራይ፡ ነበረ፡ ከዘርሒ፡ ወገን፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡አራት፡ ሽኽ።

፲፬፡ አሠራ፡ አንደኛው ፡ ባሠራ ፡ አንደኛው፡ ወር፡ ብናያ፡ የፊራቶኒው፡ ነበረ፡ከኤፍረም፡ልጆች፡ ወገን፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡ አራት፡ሽኽ።

፲፭፡ አሠራ፡ ሁለተኛው፡ባሠራ፡ሁለተኛው፡ ወር፡ የነጦፋቲው፡ ሕልደይ፡ ነበረ ፡ ከዐትኒኤል፡ ወገን፡ ሠራዊቱም፡ ኽያ፡ አራት፡ ሽኽ።

፲፮፡ በእሠራኤልም፡ነገድ፡ ሁሉ፡ ላይ፡ አሌኽ፡ነበረ። ኤሊዔዝር፡ የዚክሪ ፡ ልጅ ፡ በሮቤል፡ ወገን፡ ላይ፡ አለቃ፡ነበረ። በስምዖን፡ ወገን፡ ላይ፡ ሸፈጥያ፡ የመዓካ፡ልጅ።

፲፯፡ በሌዋውያን፡ ላይ፡ሀሸብያ፡የቁሙኤል፡ልጅ። በሐሮን፡ ወገን፡ ላይ፡ ጻደቅ።

፲፰፡ በይሁዳ፡ ላይ፡ ኤሊሑ፡ከኀደዊት፡ወንድሞች፡ በይሳኮር፡ ላይ፡ ዖምሪ፡ የሚካኤል፡ ልጅ።

፲፱፡ በዛብሎን፡ ላይ ፡ ይሽማዕያ፡ የዖበድያ፡ ልጅ። በንፍታሌም፡ ላይ፡ ይሪሞት፡ የዓዝሪኤል፡ ልጅ።

፳፡ በኤፍረም፡ ልጆች፡ ላይ፡ ሆሼዓ፡ የዓዘዝያ፡ልጅ። በምናሴ፡ነገድ፡ እኩሌታ፡ ላይ፡ ዮኤል፡ የጴዳያ፡ ልጅ።

፳፩፡ በምናሴ፡ነገድ፡ እኩሌታ፡ ላይ፡ በጊልዓድ፡ኢዶ፡ የዘካርያስ፡ ልጅ። በብንያም፡ ላይ ፡ የዐዚኤል፡ የአብኔር፡ ልጅ።

፳፪፡ በደን፡ ላይ፡ ዓዘርኤል፡የደርሳም፡ልጅ። እሌኽ፡ የእሠራኤል፡ ነገድ፡ አለቆች፡ ናቸው።

፳፫፡ ዳዊትም፡ ከኻያ፡ አመት፡ ጀምሮ፡ ከዚያ፡ በታች ፡ ሆሉትን ፡ አልቊጠረም ፡ እንደ፡ ሰማያ፡ ከዋክብት፡እሠራኤልን፡እንደያበዛ፡ እግዚአብሔር፡ ብል ዋልና።

፳፬፡ ዮአብ፡ የጽረያ፡ ልጅ፡ ግን፡ ደቊጥራቸው፡ጀመረ፡ ነገር፡ ግን፡ አልፈጸመም፡ ስለዚኽም፡ በእሠራኤል፡ ላይ፡ ቍጣ፡ ወረደ፡ የተቊጠረችም፡ ቍጥር፡በ ንጉሡ፡ በዳዊት፡ ደብዳቤ፡ አልተጻፈም።

፳፭፡ በንጉሡም፡ ኩብት፡ላይ፡ዓዝማዳዊት፡ የዓዲኤል፡ ልጅ፡ ተሹሞ፡ ነበረ፡ በርሻና፡ በከተሞች፡ በመንደርና፡ በግመብ፡ ባለው፡ ኩብት ፡ ዮናታን፡ የሁዚያ፡ ልጅ፡ ተሹሞ፡ ነበረ።

፳፮፡ በርሻ፡ ላይም፡ ምድረንም፡ በሚያርሱ፡ላይ፡ ዔዝራ፡ የኽሉብ፡ ልጅ፡ ነበረ።

፳፯፡ በወይኑም፡ አታክልት ፡ ላይ፡ ሺምዒ፡የራማቲው፡ነበረ፡በወይን፡ ጸጀም፡ቤት፡ላይ፡የሺፊሚው፡ዛብዲ።

፳፰፡ በቊላም፡ባለው፡ በወይራውና፡ በሾላው፡ ላይ፡ የግደሪው፡ በዓልሐናን፡ ነበረ፡ በዘይቱም፡ ቤት፡ላይ፡ ዮአሽ።

፳፱፡ በሻሮንም፡ ይሰማሩ፡በነበረት፡ኩብቶች፡ላይ፡ የሻሮኒው፡ ሺጥራ፡ ተሹሞ፡ ነበረ፡ በቀላ፡በነበረውም፡ ላም፡ ላይ፡ ሻፋጥ፡ የዓድላይ፡ልጅ።

፴፡ በግመሉም፡ ላይ፡ ዖቢል፡ የኢሰማኤላዊው፡ባህቦትም፡ ላይ፡ የሜሮኖቲው፡ ይሕድያ።

፴፩፡ በበጎችም፡ ላይ፡ የሀጋሪው፡ ያዚዝ። እሌኽ፡ ሁሉ፡በንጉሡ፡ በዳዊት፡ ኩብት፡ ላይ፡አለቆች፡ ነበረ።

፴፪፡ ዮናታንም፡ የኢዊት፡ አጐት፡መካሪ፡አሰተዋይ፡ አዋቂ፡ ሰው፡ነበር፡ ደሂኤልም፡ የሐክሞኒ፡ ልጅ፡ ከንጉሡ፡ ልጆች፡ ጋራ፡ ነበረ።

፴፫፡ አሒጦፈልም፡ የንጉሡ፡ መካሪ፡ነበር፡ ሑሣ ደም፡ የአርኪው፡ የንጉሡ፡ ወዳጅ፡ነበረ።

፴፬፡ ከአሒጦፈልም፡ በኋላ፡ የበናያ፡ ልጅና፡ አብያታር፡ነበረ። ዮአብም ፡ የንጉሡ ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ፡ ነበር።

ምዕራፍ፡ ፳፰፡

፩፡ ዳዊትም፡ የእሠራኤልን ፡ አለቆች፡ ሁሉ፡ የነገዶንም፡ አለቆች፡ ንጉሡንም፡ከሚያገለግሉት፡ከጭፍሮች፡ በላይ፡ ያሉትን፡ የሻለቆችንም፡ የመቶ፡ አለቆችንም፡ በንጉሡ፡ ኩብትና፡ በግዛቱም፡ላይ፡ የተሾሙትን፡ ልጆቹንም፡ ባለምዋሉቹንም፡ ኃያላኑንም፡ ጨካኖቹንም ፡ ሁሉ፡ ወደ፡ የሩሳሌም፡ ሰበሰበ።

፪፡ ዳዊትም፡ ንጉሡ፡በእግሩ ፡ ቀመ፡ አለም። ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ሕዝቤ፡ ሆይ፡ስሙኝ። ለእግዚአብሔ

ር፡ ለቃል፡ ኪሂኑ፡ ታቦትና፡ ላመላካቸን፡የግፈ፡ጪማ፡ የዕረፍት፡ ቤት፡ ለመሰበራት፡ አሰብሁ፡ ሁሉንም፡ ለስ ራ፡ አዘጋጀሁ።

፫፡ እግዚአብሔርም፡ አለኝ። ለስሚ፡ ቤት፡ አትስ ራ፡ የሰልፍ፡ ሰው፡ ነኽና፡ ደምመ፡ አፈሰስኻልና።

፬፡ ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡የአሥራኤል፡ አምላ ክ፡ ካባቴ፡ ቤት፡ ሁሉ፡ መረጠኝ፡ በአሥራኤል፡ ላይ፡ ለዘላለም፡ ንጉሥ፡ እሆን፡ ዘንድ። ሂሁኢን፡ መርጥዋ ልና፡ አለቀ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ደግሞም፡ ከአሀሂኢ፡ ቤት፡ ያባቴን፡ ቤት፡ መረጠ፡ ካባቴም፡ ቤት፡ በአሥራኤል፡ ሁሉ፡ ላይ፡ ንጉሥ፡ ለመሆን፡ እኔን፡ ደመርጠኝ፡ ዘን ድ፡ ወደደ።

፭፡ ደግሞም፡ ከልጆቹ፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔር፡ ብ ዙ፡ ልጆች፡ ሰጥቶኛልና፡ ልጄን፡ ሰሎሞንን፡መረጠ፡በ እግዚአብሔር፡ መንግሥት፡ ዙፋን፡ ላይ፡ ይቀመጥ፡ ዘንድ፡ በአሥራኤል፡ ላይ።

፮፡ አለኝም። ልጅኽ፡ሰሎሞን፡ቤቴንና፡አደባባዮ ቼን፡ ይሰራል፡ ለኔ፡ ልጅ፡ ይሆነኝ፡ ዘንድ፡ መርጨዋለ ሁና፡እኔም፡ አባት፡ እሆነዋለሁ።

፯፡ መንግሥቱንም፡ ለዘላለም፡ እጸናለሁ፡ ትእዛ ዜንና፡ ፍርዴን፡ በማድረግ፡ ቢጸና፡ እንደ፡ ዛሬ።

፰፡ አሁንም፡ በእሥራኤል፡ሁሉና፡በእግዚአብሔ ር፡ ጉባኤ፡ ዓይን፡ ፊት፡ በአምላካችንም፡ ጆሮ፡ ፊት፡ የአምላካችንን፡ የእግዚአብሔር፡ ትእዛዝ፡ ሁሉ፡ ጠ ብቁ፡ አሽዋትም፡ መልካሚቱን፡ ምድር፡ ትገዙ፡ ዘን ድ፡ ከላንተ፡ በኋላ፡ ለልጆቻችሁ፡ ለዘላለም፡እንድታ ወርሱዋት።

፱፡ አንተም፡ልጄ፡ሆይ፡ ሰሎሞን፡ያባትኽን፡ አም ላክ፡አወቅ፡ በፈጹምም፡ ልብ፡ በምትወድም፡ ነፍስ፡ ተገዛው፡ እግዚአብሔር፡ ልብን፡ ሁሉ፡ ያመረምራል ና፡ አሳብንም፡ ሁሉ፡ ያውቃልና። ብትፈልገው፡ ታገኛ ዋለህ፡ ብትጥለውም፡ ለዘላለም፡ ይጥልኻል።

፲፡ አሁንም፡እነሆ፡ቤት፡ መቅደስን፡ ትሰራ፡ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ መረጠኽ፡ ጽኑም፡ ፈጽመውም።

፲፩፡ ደዊትም፡ ለልጁ፡ ለሰሎሞን፡ የሰቀላውንና፡ የቤተኞቹን፡ የአቃ፡ ቤተኞቹን፡ የሂደቡን፡ጕርጆች፡የው ሠጡን፡ጕርሂችና፡ሶስርሥቱን፡ቤት፡ምሳሌ፡ሰጠው።

፲፪፡ ደግሞም፡ ለእግዚአብሔር፡ ቤት፡ አደባባዮች ን፡ በዙርያው፡ ለነበረቱ፡ ጕርጆች፡ ለእግዚአብሔር፡ ከብትና፡ ለተቀደሰው፡ ሁሉ፡ ከብት፡ አቃ፡ ቤተኞ፡ በ መንፈስም፡ ላሰበው፡ ሁሉ፡ ምሳሌ፡ ሰጠው።

፲፫፡ የካህናትንና፡ የሌዋውያንን፡ ክፍል፡ የእግዚ አብሔርን፡ ቤት፡ ሰራ፡ ሁሉን፡የቃውን፡ ሁሉ፡ምሳሌ፡ ለእግዚአብሔር፡ ቤት፡ ሰራ፡ ሰጠው።

፲፬፡ ሰለ፡ ማገልገሂው፡ አቃ፡ ሁሉ፡ከወርቅ፡ሰለ ሚሂረገው፡ እንሂ፡ሚዛኑ፡ ወርቅ፡ ለብረም፡ አቃ፡ሁ ሉ፡ እንሂ፡ ሚዛኑ፡ ብር፡ ሰጠ።

፲፭፡ ሰለ፡ወርቁ፡መቅረዝና፡ ሰለ፡ ማብርያው፡የተ መዘዙ፡ ወርቅ፡ ሰጠ፡በመቅረዙና፡በማብርያው፡ልክ። እንደዚሁም፡ ሰለ፡ ብረ፡ መቅረዝ፡ ሰለ፡ መቅረዙና፡ ሰለ፡ ማብርያው፡ በልክ፡ የተመዘዙ፡ ብር፡ ሰጠ፡እንደ፡ መቅረዙ፡ ሁሉ፡ ሰራ።

፲፯፡ ሰለሚታየው፡ እንጅራ፡ ማዕድ፡ ወርቅ፡ ሰጠ፡ ለማዕደ፡ሁሉ፡እንሂ፡ሚዛኑ፡ እንደሁም፡ ብር፡ሰጠ፡ ሰለ፡ ብረ፡ ማዕድ።

፲፯፡ ሰለ፡ ቮኮቹና፡ ሰለ፡ ሂኮች፡ ሰለ፡ መንቀሎች ም፡ ሁሉ፡ ምዝምዝ፡ ወርቅ፡ ሰጠ፡ ሰለ፡ ወርቁም፡ ጽ ዋች፡ ሁሉ፡ እንሂ፡ ሚዛኑ፡ ወርቅ፡ ሰጠ። እንደሁም፡ ሰለ፡ ብረ፡ ጽዋች፡ ሁሉ፡ እንሂ፡ሚዛኑ፡ብር፡ ሰጠ።

፲፰፡ አጣንም፡ለሚታጠንበት፡መሠውያ፡ክንፈቸ ውንም፡ ለዘረጉት ፡ የአግዚአብሔርን ፡ የቃል፡ ኪሂኑ ን፡ ታቦት፡ ለሚሰውረት ፡ ለኪሩቤል ፡ ሠረገላ ፡ ምሳ ሌ፡ እንሂ፡ ሚዛኑ፡ጽረ፡ወርቅ፡ ሰጠ።

፲፱፡ አለም። ሁሉ፡ በእግዚአብሔር፡እጅ፡ተጽፎ፡ መጣልኝ፡ የምሳሌውን፡ ሰራ። ሁሉ፡ አውቅ፡ዘንድ።

፳፡ ደዊትም፡ ልጁን፡ ሰሎሞንን፡ አለው። ጽኑ፡በ ርታ፡ አድርግም፡ አትፍራም፡ አትደንግጥም። እግዚ አብሔር፡ አምላኬ፡ ካንተ፡ጋራ፡ ሂሆናልና፡ አይተው ኽም፡ምና፡ አይጥልኽም፡ምና፡ የእግዚአብሔርን፡ የ ቤቱን፡ማገልገሂ፡ ሰራ፡ ሁሉ፡ እሰክትጨርስ፡ ድረስ።

፳፩፡ እነሆም፡የካህናቱና፡የሌዋውያን፡ከፈሎች፡ ለእግዚአብሔር፡ ቤት፡ ማገልገል፡ ሁሉ፡ይቀማሉ፡ብ ልሀተኛውም፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በነፍሱ፡ ፈቃድ፡ በስራው፡ ሁሉ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ይሆናል ፡ አለቀችና፡ ሕዝቡም፡ ሁ ሉ፡ ሰራህን፡ ሁሉ፡ ያደርጉ፡ዘንድ፡ ተዘጋጅተዋል።

ምዕራፍ፡ ፳፱፡

፩፡ ደዊትም፡ ለማኅበረ፡ ሁሉ፡ እንደሀ፡ ሲል፡ ተና ገረ። ልጄን፡ ሰሎሞንን ፡ ብቻውን ፡ እግዚአብሔር፡ መረጠ፡ እርሱም፡ ገና፡ ለጋ፡ ብላቴና ፡ ነው፡ ሰራው፡ ግ ን፡ ታላቅ፡ ነው፡ ግምቡ፡ ለሰው፡አደደለምና፡ለእግዚ አብሔር፡ ነው፡ እንጅ።

፪፡ እኔም፡ እንደ፡ ጕልበቴ፡ ላመላኬ፡ቤት፡ አዘጋጀ ሁ፡ ወርቁን፡ ለወርቁ፡ እቃ፡ ሁሉ፡ ብረንም፡ ለብረ፡ እ ቃ፡ ናሱንም፡ ለናሱ፡ እቃ ፡ ብረቱንም፡ ለብረቱ፡ እቃ፡ እንጨቱንም፡ ለንጨቱ፡ እቃ፡ የያቁቱን፡ ደንጊያና፡ የ ሚለበጠውን፡ ደንጊያ፡ብልጭልጭ፡ የሚለውንና፡ል ዩ፡ ልዩ፡ መልክ፡ ያለውን፡ ደንጊያ ፡ የከበረውንም፡ ደ ንጊያ፡ ሁሉ፡ እንደሁም፡ አጅግ፡ አብዙ፡ በረድ።

፫፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ያመላኬን፡ ቤት፡ ወድጀለሁ ና፡ ላመላኬ፡ ቤት፡ ከከብቴ፡ ወርቅና፡ ብር፡ ሰጠሁ፡ ላ ምላኬ፡ መቅደስ፡ ካዘጋጀሁት፡ ሁሉ፡ ሌላ።

፬፡ ሶስት፡ ሽኽ፡ መክሊት፡ ወርቅ፡ከኦፊር፡ ወርቅ፡ ሰባት፡ ሽኽም፡ መክሊት፡ አጅግ፡ ማለፊያ፡ ብር፡የቤ ተቹን፡ናሰ፡ ለመለበጥ።

፭፡ ወርቅ ፡ የሚሂሻውን ፡ ከወርቅ፡ ብር፡ የሚያሻ ውንም፡ ከብር፡በሰሮች ፡ እጅ፡ ለስራ ፡ ይሆን፡ ዘንድ።

በፈቃደ፡ እጁን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ የሚመለ፡ ማነው።

፭፡ የወገኑም፡ አለቀትና ፡ የአሠራኤል፡ ነገድ፡ ታላ ላቀት፡ ደግሞም፡ የሻለቀትና ፡ የመተ፡ አለቀት፡ የንጉ ሡ፡ አገልጋዮችም፡ አለቀት፡ በፈቃደቸው፡ ሰጡ።

፮፡ የእግዚአብሔርንም፡ቤት፡ ለመሰራት፡ አምስ ት፡ ሽ ህ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ አሥር ፡ ሽ ህም፡ ወቄት፡ ሰጡ፡ አሠራ፡ ሽ ህም፡ መክሊት ፡ ብር ፡ አሠራ። ስም ንት፡ ሽ ህም፡ መክሊት፡ናስ፡መተ፡ሽ ህም፡መክሊት፡ ብረት።

፰፡ ከርሶ፡ ዘንድም፡ ዕንቊ፡ የተገኘ፡ሁሉ፡ለእግዚ አብሔር፡ መቅደስ፡ አቃ፡ ቤት ፡ በጌርሾኒው፡ በይሔኤ ል፡ እጅ፡ ሰጠ።

፱፡ ሕዝቡም፡ በፈቃደቸው፡ ሰለ፡ ሰጡ፡ደስ፡አላቸ ው፡ ከለልባቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በውድ፡ አቅርበ ዋልና፡ ደግሞም፡ ንጉሡ፡ ደዊት፡ ታላቅ ፡ ደስታ፡ ደስ፡ አለው።

፲፡ ደዊትም፡በጉባኤው፡ሁሉ፡ ፊት፡ እግዚአብሔ ርን፡ አመሰገነ፡ አለም። አቤቱ፡የአሠራኤል፡ የባታች ን፡ አምላክ፡ አንተ፡ከዘላለም፡ እስከ፡ዘላለም፡ተመ ሰገን።

፲፩፡ አቤቱ፡ ታላቅነት፡ ችሎትና፡ ክብር፡ ኃይልና፡ም ሰጋናም፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ላንተ፡ ነው። መንግሥቱም፡ ላንተ፡ ነው፡ አቤቱ፡ አንተ፡ራስ፡ ነህና፡በሁሉ፡ ላይ፡ ከፍ፡ ከፌ፡ ትላለ ኽ።

፲፪፡ ባለጠግነትና፡ ክብር፡ ካንተ፡ ነው፡ ሁሉንም፡አ ንተ፡ ትገዛለ ኽ፡ ኃይልና ፡ ችሎትም፡ በጅ ኽ፡ ነው፡ ሁ ሉንም፡ታላቅና፡በርቱ፡ለማድረግ፡በጅ ኽ፡ነው።

፲፫፡ አሁንም፡ ላንተ ፡ እንገዛለን ፡ አምላካችን፡ ሆ ድ፡ ክቡረንም፡ስም ኽን፡ እናመሰግናለን።

፲፬፡ እኔ፡ ማነኝ፡ወገኖቼስ፡ ምንድር፡ናቸው፡ደህን፡ ሁሉ፡ በፈቃደኽን ፡ እናቀርብልህ ፡ ዘንድ፡ የሚቻለ፡። ሁሉ፡ ካንተ፡ነውና፡ከጅ ኽንም፡ የተቀበልነውን፡እናቀ ርብልኻለን።

፲፭፡ እኛ፡በፊ ት ኽ፡ ስደተኖች፡ነን፡ መጻተኖችም፡ እንደባተቻችን፡ ሁሉ፡ዘመናችንም፡ በምድር፡ ላይ፡እ ንደ፡ ጽላ፡ታልፈለች፡ እትጸናምም።

፲፮፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ ፡ አምላካችን፡ ለቅዱስ፡ ስምኽ፡ ቤት፡ እንሰራ ፡ ዘንድ ፡ ደህ፡ ያዘጋጀኸው፡ ባለ ጠግነት፡ ሁሉ፡ እርሱ ፡ ከጅ ኽ፡ ነው ፡ ሁሉም ፡ ላንተ፡ ነው።

፲፯፡ እኔ፡ አውቃለሁ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ልብን፡ እን ድትመረምር ፡ ቅንነትንም ፡ እንድትወድ ፡ ስለዚ ኽ ም፡ እኔ፡ በልቤ፡ ቅንነት ፡ በፈቃደ፡ደህን፡ ሁሉ፡ አቀረ ብሁል ኽ፡ አሁንም፡ደህ፡ ከዚ ኽ፡ ያለው፡ ሕዝብ ኽ፡ በፈቃደ፡ ሲያቀርብል ኽ፡ በደስታ፡ አየሁ።

፲፰፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ፡የአብርሃም፡የይስሐቅ፡ የያዕቀብም፡ ያባቶቻችን፡ አምላክ ፡ ደህን ፡ በሕዝብ ኽ፡ ልብ፡ ያለውን፡ አሳብ ፡ ለዘላለም ፡ ጠብቅ፡ ልባቸ ውንም፡ ባንተ፡ አጽና።

፲፱፡ ለልጀም፡ ለሰሎሞን ፡ ፍጹም፡ ልብ፡ ስጠው፡ ትእዛዝ ኽን፡ ምስክር ኽንና፡ ሕግ ኽን፡ ደጠብቅ፡ዘን ድ፡ ሁሉንም፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ እኔ፡ም፡ያዘጋጀሁለትን፡ ግምብ፡ ይሰራ፡ ዘንድ።

፳፡ ደዊትም፡ ማኅበረ ን፡ ሁሉ፡አለ። እግዚአብሔ ርን፡አምላካ ችሁን፡አመስግኑ። ማኅበረ ም፡ ሁሉ፡ አ ግዚአብሔርን ፡ ያባቶቻቸውን ፡ አምላክ፡ አመሰገኑ። ወደቁም፡ ለእግዚአብሔርም፡ሰገዱ ፡ ደግሞም፡ ለን ጉሡ።

፳፩፡ ለእግዚአብሔርም፡ መሥዋዕት፡ሠው፡የሚ ቃጠልም፡ ቍርባን ፡ አቀረቡ ፡ በነገውም ፡ ሽ ህ፡ በረ፡ ሽ ህም፡ ደንግሌ፡ ሽ ህም፡ጥቦት፡ከመጠጡ፡መሥዋ ዕት፡ ጋራ፡ መሠዋዕትም ፡ ሰለ ፡ እሠራኤል፡ ሁሉ፡ አ ብዝተው፡ አቀረቡ።

፳፪፡ በዚያም፡ቀን፡ በሉ፡ ጠጡም፡በእግዚአብሔ ር፡ ፊት፡ በታላቅ፡ ደስታ፡ ሰሎሞንንም፡ የደዊትን፡ ል ጅ፡ ሁለተኛ፡ አነገሡት፡ ለእግዚአብሔርም ፡ አለቃ፡ አድርገው፡ ቀቡት፡ ጻደቅንም፡ ካህን።

፳፫፡ ሰሎሞንም፡ በእግዚአብሔር፡ዙፋን፡ ላይ፡ን ጉሥ፡ ሁኖ፡ ተቀመጠ፡ በደዊት ፡ ባባቱ፡ ፈንታ፡ መልካ ምም፡ አደረገ፡ አሠራኤልም፡ ሁሉ፡ ታዘዙለት።

፳፬፡ ደግሞም፡ አለቆቹና ፡ ኃያላኑ ፡ ሁሉ፡ የደዊት ም፡ የንጉሡ፡ ልጆች፡ሁሉ፡አጅ፡ ሰጡት፡ ለንጉሡም፡ ለሰሎሞን፡ ተገዙ።

፳፭፡ እግዚአብሔርንም ፡ ሰሎሞንን፡ በአሠራኤ ል፡ ሁሉ፡ ፊት፡ እጅግ፡ አገነነው ፡ ከርሱ፡ በፊትም፡ ለነ በረ፡ት፡ ለአሠራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ያልሆነውን ፡ የመን ግሥት፡ ክብር፡ ሰጠው።

፳፮፡ ደዊትም፡የእሤይ፡ልጅ፡ በአሠራኤል፡ሁሉ፡ ላይ፡ ነገሠ።

፳፯፡ በአሠራኤል፡ ላይም፡ የነገሠበት ፡ ዘመን፡ አ ርባ፡ አመት ፡ ነበር። ሰባት ፡ አመት ፡ በኬብሮን፡ ነገሠ፡ ሠላሳ፡ ሶስትም፡ አመት፡ በዮሩሳሌም።

፳፰፡ በመልካምም፡ ሽምግልና፡ ሞተ፡ ዕድሚ፡ ጠ ግቦ፡ ባለጠግነትና፡ ክብርም፡ በርሱም፡ ፈንታ፡ ልጁ፡ሰ ሎሞን፡ ነገሠ።

፳፱፡ የደዊትም፡ስራ፡የፌተኛውና፡ የኋለኛው፡አ ነሆ፡ በተመልካቹም፡በሳሙኤል፡ታሪክ፡መጽሐፌ፡በ ነቢዩም፡ በናታን፡ ታሪክ፡ መጽሐፌ፡ በተመልካቹም፡ ሀጋድ ፡ ታሪክ፡ መጽሐፌ፡ ተጽፌዋል።

፴፡ ደግሞም፡የመንግሥቱ፡ስራና፡ጭከናው፡ሁሉ፡ ያለፈውም፡ ዘመኑ፡ ሁሉ፡በእሠራኤለና፡ ባገር፡ መን ግሥታት፡ ሁሉ፡ ተጽፌዋል።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ፡ ካልኣ።

ምዕራፍ ፡ ፩

፩ ፡ ሰሎሞንም ፡ የሂዋት ፡ ልጅ ፡ በመንግሥቱ ፡ በረታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አምላኩ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ ላይም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው።

፪ ፡ ሰሎሞንም ፡ ከእሥራኤል ፡ ሁሉ ፡ ከሻለቆቹና ፡ ከመኰ ፡ አለቆቹ ፡ ከፈራጂቹና ፡ ከእሥራኤል ፡ ሁሉ ፡ መሳፍንት ፡ ከአባቶችም ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ተናገረ።

፫ ፡ ሰሎሞንና ፡ ማኅበረ ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጊቤዖን ፡ ከፍታ ፡ ሔደ ፡ ሙሴ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባርያ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሠራት ፡ የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ድንኳን ፡ ከዚያ ፡ ነበረና።

፬ ፡ ሂዋት ፡ ግን ፡ ከኪርያት ፡ ሂዐሪም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ወደዘጋጀለት ፡ ቦታ ፡ አምጥቶት ፡ ነበር ፡ በዖሪሳሌም ፡ ድንኳን ፡ ተክሎለት ፡ ነበርና።

፭ ፡ የናስም ፡ መሠውያ ፡ ባስልኤል ፡ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ የሁር ፡ ልጅ ፡ የሠራው ፡ ከዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡ አቁሞት ፡ ነበር ፡ ሰሎሞንና ፡ ማኅበረ ፡ ሁሉ ፡ ሄዱት ፡ ነበረ።

፮ ፡ ሰሎሞንም ፡ ወደ ፡ ናሱ ፡ መሠውያ ፡ ወጣ ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ሺ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ።

፯ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በዚያች ፡ ሌት ፡ ለሰሎሞን ፡ እንጂህ ፡ ሲል ፡ ተገለጠ ፡ እሰጥኻ ፡ ዘንድ ፡ የምትወጂውን ፡ ለምን።

፰ ፡ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ። ካባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ምሕረት ፡ አንተ ፡ አደረግኽ ፡ በር ሱም ፡ ፈንታ ፡ አነገሠኽኝ።

፱ ፡ አሁንም ፡ አቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምለክ ፡ ሆ ያ ፡ ላባቴ ፡ ለዳዊት ፡ ተሰፋ ፡ የሰጠኸው ፡ ነገር ፡ ይጠረ ፡ ቍጥሬ ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ትቢያ ፡ የሆንህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አንግሠኸኛልና።

፲ ፡ አሁንም ፡ ጥበብና ፡ ማስተዋል ፡ ስጠኝ ፡ በዚኽ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ እገባ ፡ አወጣም ፡ ዘንድ። ያለ ፡ በማያ ኽል ፡ በዚኽ ፡ በታላቁ ፡ ሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ያፈርድ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ አለና።

፲፩ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፡ አለው ። ልብ ኽ ፡ ይህን ፡ ወድዋልና ፡ ባለጠግነትንና ፡ ንብረትን ፡ ክብር ንና ፡ የጦላቶችኽን ፡ ነፍስ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ አልሻኽ ም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥበብን ፡ ማስተዋል ፡ ለመን ፡ ኽ ፡ ነገሥ ፡ አድርጌ ፡ ባስነሣህኽ ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ትች ል ፡ ዘንድ።

፲፪ ፡ አሁንም ፡ ጥበብንና ፡ ማስተዋልን ፡ ሰጠሁኽ ፡ ባለጠግነትንና ፡ ንብረትንና ፡ ክብርን ፡ ከነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ በኋላኽም ፡ ከሚነሡት ፡ አንድ ፡ ሰንኳ ፡ የማይመስልኽ ፡ አንሂሂናር።

፲፫ ፡ ሰሎሞንም ፡ ከጊቤዖን ፡ ከኮረብታ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ድንኳን ፡ ከኢኑ ፡ ሂንኳን ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ዖሪሳሌም ፡ ተመለሰ ፡ በእሥራኤልም ፡ ላይ ፡ ነገሠ።

፲፬ ፡ ሰሎሞንም ፡ ሠረገሎችንና ፡ ፈረሰኞችን ፡ ሰበሰ በ ፡ ሸ ኽ ፡ ሻራት ፡ ሠላት ፡ ሠረገል ፡ አሠራ ፡ ሁለትም ፡ ሺ ኽ ፡ ፈረስ ፡ ሆነለት ፡ በሠረገሎቹም ፡ ከተሞች ፡ አኖራቸ ው ፡ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ በዖሪሳሌም።

፲፭ ፡ ንጉሡም ፡ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ በዖሪሳሌም ፡ እን ሂ ፡ ሂንጊ ፡ አደረገው ፡ ዝግሮስንም ፡ እንሂ ፡ ሾላውን ፡ በቍላ ፡ እንሂ ለው ፡ አበዛው።

፲፮ ፡ ፈረሰም ፡ ለሰሎሞን ፡ ከሙሶር ፡ ሂወጣለት ፡ ነበ ር። የንዙ ፡ ሂማ ፡ ነጋዶች ፡ በዋጋ ፡ ገዝተው ፡ እንሂ ፡ እ ንሂ ፡ ገዛ ፡ ፈረስ ፡ ሂመጡ ለት ፡ ነበረ።

፲፯ ፡ ሠረገላውንም ፡ በሺህሶት ፡ ሰኖ ፡ ሚትቃል ፡ በ ር ፡ ከሙሶር ፡ ሂወጡ ፡ ነበረ ፡ ፈረሱንም ፡ በመኖ ፡ አም ሳ። እንሂህም ፡ ለሔታውያንና ፡ ለሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ፈረሱን ፡ በእጂቸው ፡ ሂወጡ ፡ ነበረ።

ምዕራፍ ፡ ፪

፩ ፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤትን ፡ ለ ራሱ ፡ ቤተ ፡ ንጉሡ ፡ ሂሰራ ፡ ዘንድ ፡ አሰበ።

፪ ፡ ሰሎሞንም ፡ ሰብዓ ፡ ሸ ኽ ፡ ተሸካሚዎች ፡ ሞጠረ ፡ ሰማንሂ ፡ ሸ ኽ ፡ ም ፡ በተራራ ፡ ሂንሂ ፡ የሚወቅሩ ፡ ከርሳ ቸው ፡ በላሂም ፡ የሚሂዙ ፡ ሶስት ፡ ሸ ኽ ፡ ከሰሂስት ፡ መ ቶ ፡ ነበረ።

፫ ፡ ሰሎሞንም ፡ እንሂህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ ሑራም ፡ ወደ ፡ ቢሮስ ፡ ንጉሡ ፡ ላከ ፡ ካባቱ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ እንሂደረግ ኽ ፡ ዞቂድሮስ ፡ እንጨት ፡ ም ፡ እንሂ ፡ ሰሂድ ኽ ፡ ለት ፡ የሚ ቀመጥበት ፡ ቤት ፡ ሂሰራ ፡ ዘንድ ፡ እንሂህ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አድርግ።

፬ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላምላኬ ፡ ስም ፡ ቤ ት ፡ እሰራ ፡ ዘንድ ፡ አሰብሁ ፡ እቀድሰው ፡ ም ፡ ዘንድ ፡ በፊ ቱ ፡ እጣን ፡ ለማጠን ፡ ሸቱም ፡ ለማጢስ ፡ ዘወትርም ፡ የሚተኂ ፡ እንሂራ ፡ ለማቅረብ ፡ በጾዋትና ፡ በማታም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ለዐሠዋት ፡ በሰንበትም ፡ በ ሠረገም ፡ ትውልድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ም ፡ በእሥራኣ ኝ ፡ በላላ ፡ ለዘላለም ፡ ለእሥራኤል ፡ እንሂ ፡ ታዘ ዘው።

፭ ፡ እሰራውም ፡ ዘንድ ፡ የማሰበው ፡ ቤት ፡ ታላቅ ፡ ነ ው ፡ አምላኣኖች ፡ ከአማልክት ፡ ሁሉ ፡ በላሂ ፡ ታላቅ ፡ ስ ለ ፡ ሆነ።

፮፡ ነገር፡ግን፡ለርሱ፡ቤት፡ሂሰራ፡ዘነጽ፡ማን፡ሂቅላ ል፡ሰማሂ፡ ከሰማሂትም፡ በላሂ፡ ሂለው፡ ሰማሂ፡ ሂነ ሣው፡ዘነጽ፡ ሖማሂቅል። እኔ፡ማነኝ፡ለርሱ፡ ቤት፡እ ሰራ፡ዘነጽ፡ ሖማሂቅል። ነገር፡ግን፡ብፅ፡በፈተ፡ሀጣነ፡ለ ማጠን፡ነው።

፯፡ አሀንም፡ ኣዋቂ፡ሰው፡ሰሂድልኝ፡ወርቁንና፡ብ ረን፡ መልካም፡እድርጎ፡ሖሚሰራ፡ናሱን፡ብረቱን፡ቀዘ ን፡ ነጨነ፡ ሰማሂዊነ፡ ሐር፡ የቅርጹንም፡ ስራ፡ ሖሚ ሂው፡ቅ፡ከኔ፡ዘንድ፡በሂሀሂነ፡በየረሳሌም፡ካሉት፡ሰ ራተኖች፡ሂዊት፡አባቱ፡ንዘጋጂቸው፡ጋራ።ሖሚሰራ።

፰፡ ሂግሞም፡ከሊባኖስ፡ዋዘግ፡የዕድነ፡ሖስንሂል፡ እንጨት፡ ሰሂድልኝ። ባሮቸኝ፡ ከሊባኖስ፡ እንጨት፡ መሞኦሊጥ፡እንሂ ሂው፡ቅ፡እኔ፡ አውቃለሁና፡ እነሆም፡ ባሮቼ፡ከባሮችኽ፡ጋራ።ሂሆነሉ።

፱፡ እጂግ፡እንጨትም፡ ሂዘጋጂልኝ፡ ዘንድ፡ ልሰራ ው፡ሖማስበው።ቤት፡እጂግ፡ታላቅና፡ድንቅነውና።

፲፡ እኔም፡ እነሆ፡ ለሎላልተኽ፡ ለሰራተኞች፡ እን ጨት፡ ለሚቀ።ርጡት፡ ኽሂ፡ ሸኽ፡ሸክም።ስንጂ፡እሰ ጣለሁ፡ ኽሂ፡ ሸ ኽም፡ ማድጋ፡ የወደኔ፡ ኦጅ፡ ኽሂ፡ሸ ኽም።ማድጋ።ዘሂት።

፲፩፡ ሑራምም፡ የጢሮስ፡ ንጉሥ፡ እንሂህ፡ ሲል፡ለ ሰሎሞን፡መልክት፡ ሰደደ፡ እግዚአብሔር፡ ሕዝቡን፡ ወድዋልና፡ሰለዚኽ፡እንተን፡በርሱ፡ላይ፡እነገሠህ።

፲፪፡ ሑራምም፡ደግሞ፡ አለ። እግዚአብሔር፡የእ ሠራኤል፡ አመላክ፡ ሰማያንና፡ ምድርን፡የፈጠረ፡ለ ንጉሡም፡ ለሂዊት፡ ብልሀተኛ፡ አዋቂና፡ አስተዋይ፡ ልጅ፡ የሰጠ፡ ቡሪክ፡ነው፡ ለእግዚአብሔር፡ቤት፡ ደሰ ራ፡ዘነጽ፡ለራሱም፡ቤተ።ንጉሥ።

፲፫፡ አሀንም፡ አስተዋይና፡እጅግ፡አዋቂ፡ሰው፡ሑ ራም፡አቢ፡የሖሌትን፡ሰሂድሁል ኽ።

፲፬፡ የሴት፡ ልጅ፡ ከደን፡ ልጂት፡ ወገን፡ አባቱም፡ከ ጢሮስ፡ነው፡ ወርቅና፡ብርም፡ደሰራ፡ዘነጽ፡ያውቃል፡ ናስና፡ብረትም፡ደንጊያም፡ እንጨትም፡ ቀይና፡ ሰማ ሂዊ፡ሐርም፡ ሖለፈሂ፡ ጥጥና፡ ወርቀ፡ ዘቦም፡ የሚያ ሻውንም፡ ስራ፡ ሁሉ፡ሂቀርጽ፡ዘንድ፡ያውቃል፡ከሰራ ተኖችኽ፡ጋራ፡ከጌታዬም፡ ከሂዊት፡ ካባትኽ፡ ሰራተ ኞች፡ጋራ።

፲፭፡ አሁንም፡ጌታዬ፡ሆይ፡ ያልኽውን፡ ስንሂውን ና፡ንብሰጎ፡ዘሂቱንና፡ ኣጂኁን፡ለባሮችኽ፡ሰሂደ።

፲፮፡ እኛም፡ከሊባኖስ፡እንጨቱን፡እንቆርጣለን፡ አንተ፡ እንሂ፡ ወደጅኽ፡ በባሕርም፡ ላይ፡ አሳብረን፡ አሠረን፡ እስከ፡ ያፋ፡ እንሰሂዋለን፡ አንተም፡ ወደ ሂሩሳሌም፡ተወጣዋለኽ።

፲፯፡ ሰሎሞንም፡ በእሠራኤል፡ ምድር፡ የሚኖሩ ትን፡ ሰሂተኖች፡ሁሉ፡ቊጠረ፡ሂዊት፡አባት፡ከቀ።ጠረ ው፡ቊ።ጥር፡በኋላ፡መቶ፡አምሳ፡ ሶሰት፡ ሸ ኽ፡ ከሰጅሰ ት፡ሰመቶ።ተገኘ።

፲፰፡ ከርሳቸውም፡ ሰብዓ፡ ሸ ኽ፡ ሸክሙን፡ የሚሸ ከሙ፡ ሰማንሂ፡ በተራራ፡ ደንጊሂ፡ የሚወቅረ፡አደረ ገ፡ ሶሰት፡ ሸ ኽ፡ ከሰጅሰት፡ መተማ፡ በሕዝቡ፡ ሰራ፡ላ ደ፡የተ።ሙ።

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ ሰሎሞንም፡ የእግዚአብሔርን፡ ቤት፡ መሰራ ት፡ሂመረ፡ በየረሳሌም፡ ለሂዊት፡ ላባቱ፡ በተገለጠበ ት፡በሞሪሂ፡ተራራ፡ሂዊት፡ባዘጋጂው፡ ሰፍራ፡ በየቡሳ ዊው፡ በኦርናን፡ አውድማ።

፪፡ በነገሠም፡ባራተኛው፡አመት፡በሁለተኛው፡ወ ር፡ሰራ።ጀመረ።

፫፡ ሰሎሞንም፡የእግዚአብሔርን፡ ቤት፡ሂሰራ።ዘ ንድ፡ የጣለው፡ መሠረት፡ ሂህ፡ ነው። በመጀመርያ ው፡ልክ፡ርዝመቱ፡ ሰሂሳ፡ክንድ፡ ወርሂም፡ ኽሂ፡ክ ንድ።

፬፡ በፊቱም፡ የነበረው፡ ሰቀላ፡ ርዝመቱ፡በቤቱ፡ወ ርድ፡ልክ፡ ኽሂ፡ክንድ፡ ነበረ፡ቁመቱም፡መቶ፡ ኽሂ፡ክ ንድ፡ሰሰገ።ውሥጥም፡በአ።ወርቅ።ለበጠው።

፭፡ ሂግሞም፡ታላቁን፡ ቤት፡በጽድ።እንጨት፡ከሂ ነው፡ ኦ።ም፡ ወርቅ፡አሳሰት።ለበጠው።ሰሌንም፡ቀረ ጸበት፡ እንሂ፡ ሰንሰለትም፡ እርሱ፡ በርሱ፡ አሰተቀ ቅፂ።

፮፡ ቤቱንም፡እጂግ፡ባማረ፡ ደንጊሂ፡ጠፈጠፈው፡ በብዙ።ጌጽ። ወርቁም፡የጸርዋሂም፡ወርቅ፡ነበረ።

፯፡ ቤቱንም፡ እንጨቱንም፡ መድረኩንም፡ናሱን ም፡ሳነቃውንም፡ በወርቅ፡ ለበጠው፡ በነሱም፡ ላይ፡ ኪሩቤል፡ቀረጸ።

፰፡ ሂግሞም፡የቅጂሳንን፡ ቅድሰት፡ ቤት፡ አደረገ፡ ርዝመቱ፡ እንሂ፡ ቤቱ፡ ወርድ፡ ኽሂ፡ ክንድ፡ እንሂሁ ም፡ወርሂ፡ ኽሂ፡ክንድ።በጽ።ወርቅም።ስድሰት።መ ተ።መክሊት።በሚሆን፡ለበጠው።

፱፡ የችንካር።ቱም፡ ሚዛን፡ አምሳ፡ ሚትቃል፡ ወር ቅ፡ነበረ። የሂርቡንም።ጕር።ጅች።በወርቅ።ለበጠው።

፲፡ ደግሞም፡ በቅጂሳን፡ ቅድሰት፡ ቤት፡ ኪሩቤል ን፡አደረገ፡በቅርጽ።ሰራ።በወርቅም።ለበጣቸው።

፲፩፡ የኪሩቤልም፡ክንፋ፡ ኽሂ፡ክንድ።ተዘርግተ።ነበ ረ። ሃንጂም፡ ክንፋ፡ አምስት። ክንድ፡ ነበር፡ የቤቱን ም፡ናሰ።የነካ፡ነበር። ሁለተኛውም፡ ክንፋ፡ አምስት። ክንድ፡ነበር፡የሁለተኛውንም፡ኪሩ።ብን፡ክንፋ፡ የነካ፡ ነበር።

፲፪፡ እንጂሁም፡የሁለተኛው።ኪሩ።ብ፡ክንፋ፡አም ስት። ክንድ፡ ነበር፡በርሱም።ናሱን፡የነካ፡ነበር።ሁለተኛ ውም፡ ክንፋ፡ አምስት። ክንድ፡ ነበር፡ በርሱም፡የሌላ ውን፡ኪሩ።ብ፡ክንፋ፡የነካ፡ነበር።

፲፫፡ የኪሩቤልም፡ክንፋ፡ ኽሂ፡ክንድ።የተዘረጋ።ነበ ር፡ አርባቸውም። በእግራቸው፡ ቁመው።ነበረ።ፊታቸ ውም፡ወደ።ቤት።ውሥጥ።ሂሂ።ነበር።

፲፬፡ ሂግሞም፡ ከሰማሂዊነ፡ ከቀሂ፡ ከነጭና፡ ከብ ዟ።ሐር።መጋረ።ሰራ።ኪሩቤልንም።በለፈበት።

፲፭፡ ባቡቱም፡ ፊት፡ ሁለት።አምሂት።አሂረገ።ርዝ

መታቸውም፡ሠላሳ፡አምስት፡ክንድ፡ክባሳቸውም፡በላያቸው፡አምስት፡ክንድ።

፲፮፡ በመቅደሱም፡እንደ፡ሰንሰለት፡ያለ፡አደረገ፡በአምጀቅም፡ራስ፡አደረው፡ደግሞም፡መቶ፡ፈማን፡በሰንሰለቱ፡መኻከል፡አደረገ።

፲፯፡ አምጀቁንም፡በመቅደሱ፡ፊት፡አቅማሾው፡አንዱን፡በቀኝ፡ሁለተኛውንም፡በግራ። በቀኝ፡ያለውንም፡ያኪን፡ብሎ፡ጸራው፡በግራ፡ያለውንም፡ቦዓዝ።

ምዕራፍ፡ ፬፡

፩፡ ደግሞም፡የናሰ፡መሠውያ፡ሰራ፡ርዝመቱ፡ኻያ፡ክንድ፡ወርዷም፡ኻያ፡ክንድ፡ቁመቱም፡አሥር፡ክንድ።

፪፡ የፈሰሰም፡ባሕር፡እደረገ፡የዙርያውም፡ክበብ፡ከሂር፡እስከ፡ሂር፡አሥር፡ክንድ፡ነበር። ቁመቱም፡አምስት፡ክንድ፡በዙርያውም፡ሠላሳ፡ክንድ፡ገመድ፡ያዞር፡ነበረ።

፫፡ በከንፈሩም፡ታች፡በረ፡የሚመስል፡ነበረበት፡በዙርያው፡ባሥሩ፡ክንድ። ባሕሩንም፡ከበውት፡ነበሩ። በሮቹም፡በሁለት፡ተራ፡ሁነው፡ከባሕሩ፡ጋራ፡ባንድ፡የፈሰሱ፡ነበር።

፬፡ ባሕረም፡ባሥራ፡ሁለት፡በረ፡ላይ፡ተቀምጦ፡ነበር፡ሶስቱ፡ወደ፡መስዕ፡ሶስቱም፡ወደ፡ምዕራብ፡ሶስቱም፡ወደ፡ዓዜብ፡ሶስቱም፡ወደ፡ምሥራቅ፡ያዩ፡ነበር። ባሕረም፡በላያቸው፡ተቀምጦ፡ነበር፡የበረው ም፡ሁሉ፡ጀርባ፡ከባሕረ፡በታች፡በስነ፡ውሥጥ፡ነበረ።

፭፡ ወፈረም፡ስንዝር፡ነበር፡ከንፈረም፡እንደ፡ጽዋ፡ከንፈር፡ነበር፡እንደ፡ፈነደ፡አበባ፡ነበር፡ሶስት፡ሽህ ም፡ማድጋ፡ያኸ፡ነበረ።

፮፡ ደግሞም፡አሠር፡ደካ፡ሰራ፡ከርሳቸውም፡አ ምስቱን፡በቀኝ፡አምስቱንም፡በግራ፡አደረገ፡ለሚቃጠለው፡ ቍርባን፡የሚቀርበው፡ነገር፡ሁሉ፡ያታጠብባ ቸው፡ዘንድ፡በባሕረ፡ግን፡ብቻ፡ካህናት፡ያታጠቡ፡ነበረ።

፯፡ የወርቅም፡አሠር፡መቅረዝ፡እንደ፡አገባቡ፡ል ክ፡ሰርተ፡አምስቱን፡በቀኝ፡አምስቱንም፡በግራ፡አድ ርጎ፡በመቅደሱ፡አኖረው።

፰፡ አሠርም፡ማዕድ፡አደረገ፡በመቅደሱም፡አም ስቱን፡በቀኝ፡አምስቱንም፡በግራ፡አኖረው። መቶ ም፡የወርቅ፡ጽዋ፡አደረገ።

፱፡ ደግሞም፡ለካህናቱ፡አደባባይ፡አደረገ፡ለሕዝ ቡም፡ሁሉ፡ታላቅ፡አደባባይ፡ለርሳቸውም፡ሳንቃቸ፡ አደረገ፡በናሰም፡ለበጣቸው።

፲፡ ባሕረንም፡በስተቀኝ፡በምሥራቅ፡ትይዩ፡በስ ከ፡ሊባ፡እኩል፡አደረገው።

፲፩፡ ሑራምም፡ምቾቶች፡መጫሪዎችን፡ጽንሖች፡ሰራ። ሑራምም፡ስራውን፡ሁሉ፡ለንጉሡ፡ለሰሎሞ ን፡በእግዚአብሔር፡ቤት፡ይሰራው፡የነበረውን፡ሁሉ፡ ጨረሰ።

፲፪፡ ሁለቱን፡አምኢትን፡ገንቦ፡የሚመስሉትን፡ክ ባሳቸውን፡በአምኢቱ፡ራስ፡ላይ፡የነበረቱንን፡ሁለቱ ን፡ሳያነ፡ርግቦች፡ገንቦ፡የሚመስሉትን፡የአምኢቱን፡ ክባሶች፡የሚከድኑትን፡ሰራ።

፲፫፡ አራት፡መቶም፡ፈማኖች፡በሁለቱ፡ሳያነ፡ርግቦ ች፡ላይ፡ሰራ፡ባንኢም፡ሳያነ፡ርግብ፡ላይ፡ሁለት፡የፈ ማን፡ተርታ፡አደረገ፡ገንቦ፡የሚመስሉትን፡የአምኢ ቱን፡ክባሶች፡ደከድኑ፡ዘንድ፡አደረገ።

፲፬፡ ደግሞም፡ደገፎች፡ሰራ፡ደቦቶንም፡በደገፈ ው፡ላይ፡አኖራቸው።

፲፭፡ አንድ፡ባሕርም፡አሠራ፡ሁለትም፡በረ፡በ ታቹ።

፲፮፡ ምንቸቶችንና፡መጫሪዎችን፡ቦቦችንና፡የቀረ ውንም፡አቃ፡ሁሉ፡ሑራም፡አቢ፡ለንጉሡ፡ለሰሎሞ ን፡ለእግዚአብሔር፡ቤት፡ከናሪ፡ነሰ፡ሰራ።

፲፯፡ ንጉሡም፡በዮርደናስ፡ወጂህ፡ማጂ፡አሰፈሰ ሰው፡በወፈራም፡ምድር፡በሡኾትና፡በጸረዷታ፡መ ኻከል።

፲፰፡ ሰሎሞንም፡ይህነን፡አቃ፡ሁሉ፡እጅግ፡አብዝ ት፡ሰራ፡የናስ፡ሚዛን፡አይመረመርም፡ነበርና።

፲፱፡ ሰሎሞንም፡ለእግዚአብሔር፡ቤት፡የሚያሻ ውን፡አቃ፡ሁሉ፡ሰራ፡የወርቁንም፡መሠውያና፡ሰደቀ ቹን፡ በላያቸውም፡ የሚታየው፡ እንጅራ፡ ነበረባቸ ው።

፳፡ ደግሞም፡መቅረዞች፡ከማብሪያቸው፡ጋራ፡በ ራእዩ፡ስፍራ፡ፊት፡እነደ፡ሥርዓቱ፡ያበረ፡ዘንድ፡ከ ምዝምዝ፡ወርቅ፡ሰራቸው።

፳፩፡ አበቦቹ፡ ማብሪዞቹና፡ መኰስተሪዮቹ፡ ወር ቀቅ፡ነበረ፡ከምዝምዝ፡ወርቅ።

፳፪፡ ካሮቹና፡መርጨቹ፡መንኮቹና፡ጽዮቹ፡ከምዝ ምዝ፡ወርቅ፡ ነበረ። የውሠጡም፡ የመቅደሱ፡ ሳን ቃ፡ለቅዱሳን፡ ቅድስት፡የነበረውና፡የሚሂው፡መቅደ ስ፡ሳንቀቅ፡ከወርቅ፡ነበረ።

ምዕራፍ፡ ፭፡

፩፡ ሰሎሞንም፡ለእግዚአብሔር፡ቤት፡ያሰራው፡ የነበረው፡ሰራ፡ሁሉ፡ተጨረሰ። ሰሎሞንም፡አባቱ፡ዳ ዊት፡የቀደሰውን፡ብረንና፡ ወርቁን፡ አቃውንም፡ሁ ሉ፡ አመጥተ፡ በእግዚአብሔር፡ ቤት፡ አቃ፡ ቤት፡ አኖ ረው።

፪፡ የዚያን፡ ጌዜ፡ ሰሎሞን፡ የእሥራኤልን፡ ሸማ ግሎች፡ የነገጆቹን፡ ሁሉ፡ አለቀችና፡የእሥራኤል፡ልጆ ች፡ያባቶች፡ አለቀች፡ሁሉ፡ወደ፡የሩሳሌም፡ብበሰበ፡የ እግዚአብሔርን፡የቃል፡ ኪደኑን፡ ታቦት፡ ከጂዊት፡ከ ተማ፡ያመጡ፡ዘንድ፡አርስዋም፡ጽዮንን፡ናት።

፫፡ እንጂሁም፡የእሥራኤል፡ሰዋች፡ሁሉ፡በሰባተ ኛው፡ወር፡በዓል፡ወደ፡ንጉሡ፡ተሰበሰቡ።

፬፡ የእሥራኤልም፡ ሸማግሎች፡ ሁሉ፡መጡ፡ሌዋ ውያንም፡ታቦቲቱን፡ተሸከሙ።

፳፩፡ ታቦቲቱንም፡ አኅብዋት፡ ድንኳኒቱንና፡ በድንኳኒቱ፡የነበረውንም፡የመቅደሱን፡ አቃ፡ ሁሉ፡ ካህናቱና፡ሌዋውያን፡አገቡ።

፳፪፡ ንጉሡ፡ ሰሎሞንና፡ የእሥራኤል፡ ማኅበር፡ ሁሉ፡ከርሱ፡ጋራ፡ በታቦቲቱ፡ ፊት፡ የተሰበሰቡት፡ግን፡ከብዛቱ፡ የተነሣ፡ሰፈርን፡ ቊጥር፡የሌለው፡በግና፡በሬ፡ ያቀርቡ፡ነበረ።

፳፫፡ ካህናቱም፡የእግዚአብሔርን፡የቃል፡ኪዳኑን፡ ታቦት፡ ወደ፡ መቅደሱ፡ ራእይ፡ ወደ፡ ቅድሳን፡ ቅድሰት፡ከኪሩቤል፡ክንፍ፡በታች፡አኖሩት።

፳፬፡ ታቦቱም፡ በተቀመጠበት፡ ሰፈራ፡ ላይ፡ኪሩቤል፡ክንፎቻቸውን፡ዘርግተው፡ ነበረ። ኪሩቤልም፡ ታቦቱንና፡መሎጊያውን፡በላይ፡ከድነውት፡ነበረ።

፳፭፡ መሎጊያቹንም፡ አውጥተዋቸው፡ ነበረ፡ የመሎጊያቹም፡ ጫፍ፡ ከታቦቱ፡ ጥቂት፡ዘልቀ፡በራእዩ፡ሰፈራ፡ፊት፡ይታይ፡ነበረ። ነገር፡ ግን፡ በስከሚደ፡ አይታይም፡ነበር። ታቦቱም፡ከዚያ፡አለ፡አስከ፡ዛሬ።

፲፱፡ በታቦቱም፡ ከምስር፡ በወጡ፡ ጊዜና፡ እግዚአብሔር፡ ከእሥራኤል፡ልጆች፡ ጋራ፡ ኪደን፡ ባደረገ፡ጊዜ፡ ሙሴ፡ በኮሪብ፡ባሥራቸው፡ከሁለቱ፡ጽላቶች፡በቀር፡ አንጂች፡አልነበረም።

፲፭፡ ካህናቱም፡ ከመቅደስ፡ በወጡ፡ ጊዜ፡ ከዚያ፡ የተገኙት፡ ካህናት፡ ሁሉ፡ ተቀድሰው፡ ነበሩና፡በዚያ፡ ዘመን፡ በርሳቸው፡ መ ኻከል፡ የማገልገል፡ ሥርዓት፡ አልተከፈለም።

፲፪፡ ከሌዊም፡ ወገን፡የነበሩት፡መዘምራን፡ከአሣፍ፡ከሔማንና፡ ከዮዲቱን፡ አጅ፡ በታች፡የነበሩት፡ልጆቻቸውና፡ ወንድሞቻቸው፡ የተልባግር፡ለብሰው፡ጽናጽል፡በገናና፡ መሰንቆ፡በመሠውያ፡አጠገብ፡ቁመው፡ በምሥራቅ፡ አኩል፡ ይመቱ፡ ነበሩ። ከርሳቸውም፡ ጋራ፡መቶ፡ ኻያ፡ካህናት፡መለከት፡ይነፉ፡ነበሩ።

፲፫፡ ሁሉም፡ ባንድ፡ ያመሰግኑ፡ነበረ፡በመለከትና፡ በዜማም፡ እግዚአብሔርን፡ በማመሰገን፡ ባንድ፡ ድምፅ፡ያሰሙ፡ ዘንድ፡በመለከትና፡በጽናጽል፡በተለያየም፡በምስጋና፡ አቃ፡ ሁሉ፡ ድምፃቸውን፡ ወደ፡ላይ፡ ኸፍ፡ አደርገው፡ አንደሀ፡ ሲሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ማመሰገን፡በጀመረ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔርን፡ አመሰግኑ፡ መልካም፡ ነውና፡ ምሕረቱም፡ ለዘላለም፡ነውና፡የእግዚአብሔርን፡ቤት፡ደመና፡ይመላው፡ነበረ።

፲፱፡ ካህናቱም፡ ከደመናው፡ የተነሣ፡ መቆም፡ ማገልገል፡ አልተቻላቸውም፡ የእግዚአብሔር፡ ብርሃን፡የእግዚአብሔርን፡ቤት፡መልቶት፡ነበረና።

ምዕራፍ፡ ፯፡

፩፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ ሰሎሞን፡ አለ፡ እግዚአብሔር፡በጽጋግ፡ይቀመጥ፡ዘንድ፡ተናገረ።

፪፡ እኔም፡ ቤት፡ ሰራሁልኝ፡ ትቀመጥበት፡ ዘንድ፡ መቀመጪም፡ለዘላለም፡ትኖርበት፡ዘንድ።

፫፡ ንጉሡም፡ፊቱን፡ መልሶ፡ የእሥራኤልን፡ ማኅበር፡ ሁሉ፡ባረከ። የእሥራኤልም፡ ማኅበር፡ ሁሉ፡ ቁመ፡ነበር።

፬፡ አለም፡ እግዚአብሔር፡የእሥራኤል፡ አምላክ፡ደመሰገን፡ለደዊት፡ላጣቴ፡ አንደህ፡ሲል፡ባፏ፡የተናገረውን፡በጂ፡የፈጸመ።

፭፡ ሕዝቤን፡ከምስር፡ ምድር፡ ካወጣሁ፡ ጀምሮ፡ ከእሥራኤል፡ ነገድ፡ ሁሉ፡ ከተማ፡ ቤት፡ ደሰራ፡ ስሜ፡ከዚያ፡ደኖር፡ዘንድ፡አልመረጥሁም፡ለእሥራኤልም፡ ለወገኔ፡ አለቃ፡ የሚሆን፡ ሰው፡ አልመረጥሁም።

፮፡ ነገር፡ግን፡ ስሜ፡ ደኖርባት፡ዘንድ፡የረሳሌምን፡ መረጥሁ፡ደዊትም፡በወገኔ፡ በእሥራኤል፡ ላደ፡ ደነገሠ፡ዘንድ፡መረጥሁ።

፯፡ ደዊትም፡ አባቴ፡ለእሥራኤል፡አምላክ፡ለእግዚአብሔር፡ስም፡ቤት፡ለመስራት፡በልቡ፡ወደደ።

፰፡ እግዚአብሔርም፡ ደዊትን፡ አባቴን፡ አለው። ለስሜ፡ ቤት፡ ትሰራ፡ዘንድ፡በልብኽ፡አስበኻልና፡መልካም፡አደረግኽ፡ደህ፡ከልብኽ፡ሰለ፡ሆነ።

፱፡ ነገር፡ግን፡ አንተ፡ ቤቱን፡አትሰራ፡ልጅኽ፡ከወገብኽ፡የሚወጣው፡አርሱ፡ለስሜ፡ቤት፡ደሰራ።

፲፡ እግዚአብሔርም፡ የተናገረውን፡ ነገር፡ ፈጸመ፡ አኔም፡ በደዊት፡ ባባቴ፡ ፈንታ፡እግዚአብሔር፡እንደ፡ ተናገረው፡ ተነሣሁ፡ በእሥራኤልም፡ ዙፋን፡ ተቀመጥሁ፡ ለእግዚአብሔርም፡ ለእሥራኤል፡ አምላክ፡ ስም፡ቤት፡ሰራሁ።

፲፩፡ ከእሥራኤልም፡ ጋራ፡ ያደረገው፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ኪደን፡ያለበትን፡ታቦት፡አኖርሁበት።

፲፪፡ በእግዚአብሔርም፡መሠውያ፡ፊትየ፡በእሥራኤል፡ማኅበር፡ሁሉ፡ታየ፡ቁመ፡እጂን፡ዘረጋ።

፲፫፡ ሰሎሞን፡የናስ፡ደገፋ፡ሰርተ፡ ነበርና፡ ባደባባዩ፡ መ ኻከል፡ተከለው፡ርዝመቱ፡አምስት፡ክንድ፡ነበር፡ ወርደም፡ አምስት፡ ክንድ፡ ቁመቱም፡ሶስት፡ክንድ፡ ነበር፡ በላዩም፡ ቀመ፡ በእሥራኤልም፡ወገን፡ሁሉ፡ፊት፡ በጉልበቱ፡ ተንበረከከ፡ አጂንም፡ ወደ፡ሰማይ፡ዘርግቶ፡አለ።

፲፬፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ፡ የእሥራኤል፡ አምላክ፡ በሰማይና፡ በምድር፡ አንተን፡ የሚመስል፡ አምላክ፡ የለም፡አንተ፡ነኽ፡ቃል፡ኪዳንና፡ ምሕረት፡ ከለልባቸው፡ ሁሉ፡ በፊትኽ፡ ለሚሔዱት፡ ለባሮቾኽ፡ የምትጠብቅ፡

፲፭፡ አንተ፡ ነኽ፡ ለደዊት፡ ላጣቴ፡ የተናገረኽውን፡ ሁሉ፡የሰጠኽው፡ባፏኽም፡ተሰፈ፡ያስደረግህለትን፡ ዛሬ፡እንደ፡ተገለጠ፡በጅኽ፡ፈጸምኽው።

፲፮፡ አሁንም፡እግዚአብሔር፡ ሆይ፡ የእሥራኤል፡ አምላክ፡ ለባርያኽ፡ለደዊት፡ላጣቴ፡እንደህ፡ብለኽ፡ የተናገርኽውን፡ ፈጽም። በፊቴ፡ በእሥራኤል፡ዙፋን፡ ላይ፡ የሚቀመጥ፡ ሰው፡ ካንተ፡ አይታጣም፡ብቻ፡ ልጆችኽ፡ መንገዲቸውን፡ ቢጠብቁ፡ በሕጌም፡ ቢሔዱ፡አንተ፡በፊቴ፡እንደ፡ሔድኽ።

፲፭፡ እሥራኤልም፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ፡የእሥራኤል፡ አምላክ፡ ሊቀዊት፡ ለባርያኽ፡ የተናገርኸው፡ነገር፡ ይጽና።

፲፮፡ በውኑ፡ እግዚአብሔር፡ከሰው፡ጋራ፡በምድር፡ላይ፡ ይቀመጣልን። እነሆ፡ ሰማይ፡ የሰማያትም፡ ሰማይ፡እይችልኽም፡ይልቁንስ፡ ይህ፡ እኔ፡ የሰራሁት፡ ቤት፡እያየኸ፡አንር፡ትነዋ።

፲፱፡ ነገር፡ግን፡እግዚአብሔር፡አምላኬ፡ሆይ፡ወደ፡ ባርያኽ፡ጸሎትኖ፡ልመና፡ ፈትኽን፡ መልስ፡ ባርያኽ፡ በፊትኽ፡ የሚያደረገውን፡ ጩኸትና፡ ልመና፡ ትሰማ፡ዘንድ።

፳፡ በዚህ፡ ቤት፡ ላይ፡ ዓይንኽን፡ ትከፈት፡ዘንድ፡ በቀንና፡በሌት፡ስም፡ኽን፡ታኖርበት፡ዘንድ፡ተሰፈ፡በሰ ጠኽው፡ ስፍራ፡ ላይ፡ ባርያኽም፡በዚህ፡ስፍራ፡የሚ ጸልየውን፡ጸሎት፡ትሰማ፡ዘንድ።

፳፩፡ ቦባርያኽንና፡ የሕዝብኽንም፡ የእሥራኤል ን፡በዚህ፡ ስፍራ፡ የሚጸልዩትን፡ ልመና፡ አድምፅ፡ ከ ሰማያ፡ ከመኖርያኽ፡ሰማ፡ሰምተኽም፡ይቅር፡በል።

፳፪፡ ማንም፡ ባልንጀራውን፡ ቢበድል፡ እርሱም፡ ቢያምለው፡ መሐላውም፡በመሠውያኽ፡ፊት፡በዚ ኽ፡ቤት፡ቢመጣ፡

፳፫፡ አንተ፡ ከሰማያ፡ሰማ፡ቦባሮችኽንም፡ፍርድ፡ አድርግ፡ የኃጢአተኛውንም፡ መንገድ፡ በራሱ፡ ላይ፡ መልሰ፡ ለጸድቁም፡ እንደ፡ ድድቁ፡ ዋጋውን፡ ሰጥተ ኽ፡አጽድቀው።

፳፬፡ ሕዝብኽም፡ እሥራኤል፡ አንተን፡በድለው፡ ከጸላቶቻቸው፡ ፊት፡ ድል፡ተመትተው፡ቢሸሹ፡ተመ ልሰውም፡ ኀጢሐ፡ ቢገቡ፡ ሰምህንም፡ ቢለምኑ፡ በዚ ህም፡ቤት፡በፊትኽ፡ቢጸልዩ።

፳፭፡ አንተ፡ ከሰማይ፡ ሰማ፡ የእሥራኤልንም፡ የ ሕዝብህን፡ ኃጢአት፡ ይቅር፡ በል፡ ለርሳቸውና፡ ላባት ቻቸውም፡ወደ፡ሰጠኻት፡ምድር፡መልሳቸው።

፳፮፡ ሰማይ፡ ቢዘጋ፡ ስለ፡ ሕዝቡ፡ኃጢአትም፡ዝና ም፡ ባይዘንም፡ በዚህም፡ ስፍራ፡ ቢለምኑ፡ኽ፡ለስም ኽም፡ አላበይነም፡ ቢሉ፡ ከኃጢአታቸውም፡ ቢመለ ሱ፡አንተ፡አዋርጀኻቸዋልና።

፳፯፡ አንተ፡ ከሰማይ፡ ሰማ፡ የእሥራኤልንም፡ የ ሕዝብኽንና፡ቦባሮችህን፡ኃጢአት፡ ይቅር፡ በል፡የሚ ሔዱባትንም፡ መልካም፡ መንገድ፡አሰተምራቸው፡ ሕዝብኽም፡ ይወርስዋት፡ ዘንድ፡ ለሰጠኻቸው፡ም ድር፡ዝናም፡ሰጥ።

፳፰፡ በምድር፡ ላይ፡ራብ፡ ቸነፈር፡ቢሆን፡በአህል ም፡ ላይ፡ ዋግ፡ጎመንም፡አንበጣ፡ኩብኩባ፡አላቶ ቻቸውም፡ ባገራቸው፡ የከተማቸውን፡ ደጅ፡ ቢያሰ ጨንቁ፡ ማናቸውም፡መቅሠፍትና፡ ማናቸው፡ደዌ፡ ሁሉ፡ቢሆን።

፳፱፡ ጸሎትና፡ልመና፡ ሁሉ፡ አንድ፡ ሰው፡ ወይም፡ እሥራኤል፡ሕዝብኽ፡ ሁሉ፡ መቅሠፍቱንና፡ደዌው ን፡አውቀ፡ቢጸልይ፡በዚኽም፡ቤት፡እጀን፡ቢዘረጋ።

፴፡ አንተ፡ ከሰማይ፡ ከመኖርያኽ፡ ሰማው፡ይቅር ም፡ በለው፡ ለሁሉም፡ እንደ፡ መንገዱ፡ ልቡን፡ አንደ ምታውቀው፡ መጠን፡ ስጠው፡ የሰውን፡ልጆች፡ልብ፡ አንተ፡ብቻ፡ታውቃለኽና።

፴፩፡ ይፈሩኽ፡ ዘንድ፡ ዘንድ፡ በመንገድኽም፡ይሔዱ፡ዘ ንድ፡ ላባቶቻችን፡ በሰጠኻት፡ በምድር፡ ፊት፡ ላይ፡በ ሕይወታቸው፡ዘመን፡ሁሉ።

፴፪፡ ስለ፡ትኖም፡ ከሕዝብኽ፡ ከእሥራኤል፡ ያል ሆነ፡ ከሩቅ፡ ምድር፡ቢመጣ፡ስለ፡ታላቁ፡ስምኽ፡ስለ፡ ብርቱ፡ እጅኽም፡ ስለ፡ ተዘረጋውም፡ ክንድኽ፡መጥ ተው፡ቢኽ፡ቤት፡ቢጸልይ።

፴፫፡ አንተ፡ ከሰማይ፡ ከማደርያኽ፡ ሰማው፡ ስለ ተጠራውም፡የለመነኽን፡ነገር፡ሁሉ፡አድርግ። የምድር፡ አሕዛብ፡ሁሉ፡ ስምኽን፡ ያውቁ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ሕዝ ብኽም፡ እንደ፡ እሥራኤል፡ ይፈሩኽ፡ ዘንድ፡ በዚህ ም፡ እኔ፡ በሰራሁት፡ ቤት፡ ስም፡ኽ፡እንደ፡ተጸራ፡ያው ቁ፡ዘንድ።

፴፬፡ ሕዝብኽ፡ ወደ፡ ሰልፍ፡ ቢወጡ፡ በጸላቶቻ ቸው፡ ላይ፡ በምትልካቸው፡ መንገድ፡ ሁነው፡ ወደ፡ ዚች፡ እንተ፡ ወደ፡ መረጽኻት፡ አገር፡ ወደንተ፡ ቢጸ ልዩ፡ ለስምኽም፡ እኔ፡ ወደ፡ ሰራሁት፡ ቤት።

፴፭፡ አንተ፡ ልመናቸውንና፡ ጸሎታቸውን፡ ከሰ ማይ፡ ሰማ፡ ፍረድላቸውም።

፴፮፡ አንተንም፡ ቢበድሉ፡ የማይበድል፡ ሰው፡ የ ለምና፡ ብትቀጣቸውም፡ ለጸላቶቻቸውም፡ አሳል ፈኽ፡ ብትሰጣቸው፡ ወደ፡ ራቅ፡ አገርም፡ ቢማርኳ ቸው፡ ወይም፡ ወደ፡ቅርብ።

፴፯፡ በተማረኩባትም፡ ምድር፡ ከለልባቸው፡ ቢ መለሱ፡ ኀስሐም፡ ቢገቡ፡ በተማረኩባትም፡ ምድር፡ አንተን፡ ቢለምኑ። እንደህ፡ ሲሉ፡ ኃጢአት፡ ሰራነ፡ በደልንም፡ ግፍም፡ አደረግነ።

፴፰፡ ከለልባቻውና፡ ከለነፍሳቸውም፡ ወደንተ፡ ቢመለሱ፡ በተነደባት፡ በምርኮቸው፡ ምድርም፡ ሁ ነው፡ ላባቶቻቸው፡ ወደ፡ ሰጠኻት፡ ምድርና፡ አንተ፡ ወደ፡ መረጥኻት፡ አገር፡ ለስምኽም፡ እኔ፡ ወደ፡ ሰ ራሁት፡ ቤት፡ ቢጸልዩ።

፴፱፡ አንተ፡ ከሰማይ፡ ከማደርያኽ፡ ልመናቸው ንና፡ ጸሎታቸውን፡ ሰማ፡ ፍረድላቸውም፡ አንተን ም፡ ለበደለኽ፡ ለሕዝብኽ፡ ኃጢአቱን፡ ተውለት።

፵፡ አሁንም፡ አምላኬ፡ ሆይ፡ በዚኽ፡ ስፍራ፡ ወ ደሚሆነው፡ ጸሎት፡ ዓይኖችኽ፡ የተከፈቱ፡ ጀሮች ኽም፡ የሚሆደምፁ፡ አንደሆኑ፡ አለምንኽለሁ።

፵፩፡ አሁንም፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ሆይ፡ ወ ደ፡ ዕረፍትኽ፡ ተነሣ፡ አንተና፡ የኃይልህ፡ ታቦት፡ ካ ህናትኽም፡ አቤቱ፡ አምላክ፡ ሆይ፡ ደኅንነት፡ ይልበ ሱ፡ ጻደቃንኽም፡ በበረከት፡ ደስ፡ ይበላቸው።

፵፪፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ሆይ፡ የመሢሕኽ ን፡ ፊት፡ አትመልስ፡ ለባርያኽም፡ ለደዊት፡ ያደረግ ሀለትን፡ ቸርነት፡ አስብ።

ምዕራፍ፡ ፯፡

፩፡ ሰሎሞንም፡ ጸሎቱን፡ በፈጸመ፡ ጊዜ፡ እሳት፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ የሚቃጠለውን፡ ቍርባንን፡ የአር ያን፡ መሥዋዕቱን፡ በላ፡ የእግዚአብሔርም፡ ክብር፡ በቤቱ፡ ሞላ።

፪፡ ካህናቱም፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ መቅደስ፡መ ግባት፡ አልቻሉም፤ የእግዚአብሔርን፡ ክብር፡ የእግ ዚአብሔርን፡ ቤት፡ መልቶት፡ ነበረና።

፫፡ የእሥራኤልም፡ ልጆች፡ ሁሉ፡ እሳቱ፡ ሲወር ድ፡ ያዩ፡ ነበሩ፡ የእግዚአብሔርም፡ ክብር፡ በቤቱ፡ ላ ይ። በድንጊያም፡ በተጠፈጠፈው፡ አደባባይ፡ ላይ፡ ሰ ግደው፡ ወደቁ፡ እግዚአብሔርንም፡ አመሰገኑ፡ እር ሱ፡ ቸር፡ እንጂሆነ፡ ቸርነቱም፡ ለዘላለም፡ እንጂሆነ።

፬፡ ንጉሡና፡ ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ በእግዚአብሔር፡ፊ ት፡ የእርድ፡ መሥዋዕት፡ ያቀርቡ፡ ነበሩ።

፭፡ ንጉሡም፡ ሰሎሞን፡ ኻያ፡ ሁለት፡ ሽኽ፡ በሬ፡ ሠዋ፡ ከበግም፡ መቶ፡ ኻያ፡ ሽኽ። የእግዚአብሔር ንም፡ ቤት፡ ንጉሡና፡ ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ቀደሱት።

፮፡ ካህናቱም፡ በየሥራታቸው፡ ቁመው፡ ነበሩ፡ ሌ ዋውያንም፡ የእግዚአብሔርን፡ የማሳሌቱን፡ እቃ፡ ንጉሡ፡ ዳዊት፡ ያደረገውን፡ ይዘው፡ እግዚአብሔ ርን፡ ለማመስገን፡ ምሕረቱ፡ ለዘላለም፡ ነውና፡ ዳዊ ት፡ በጀቸው፡ ባመሰገኑ፡ ጊዜ። ደግሞም፡ ካህናት፡ በ ፊታቸው፡ በመለከት፡ ያመሰግኑ፡ ነበሩ፡ እሥራኤል ም፡ ሁሉ፡ ቁመው፡ ነበሩ።

፯፡ ሰሎሞንም፡በእግዚአብሔር፡ መቅደስ፡ ፊት፡ የነበረውን፡ የአደባባዩን፡ ውሰጥ፡ ቀደሰ፡ ከዚያ፡ የ ሚቃጠል፡ ቍርባንና፡ የደኅንነት፡ የሰብ፡ መሥዋዕ ት፡ አቅርብዋልና፡ ሰሎሞን፡ የሰራው፡ የናስ፡ መሠ ውይ፡ የሚቃጠለውን፡ መሥዋዕትና፡ የእህሉን፡ ቍ ርባን፡ ስቡንም፡ ያነሣ፡ ዘንድ፡ አልቻለምና።

፰፡ ሰሎሞንም፡ በዚያን፡ ወራት፡ ሳባት፡ ቀን፡ በዓ ል፡ አደረገ፡ አሥራኤልም፡ ሁሉ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ አጅግ፡ ታላቅ፡ ጉባኤ፡ ከሀማት፡ መግቢያ፡ ጀምሮ፡ አስከ፡ ም ስር፡ ወንዝ፡ ድረስ።

፱፡ በስምንተኛውም፡ ቀን፡ የጉባኤ፡ በዓል፡ አደረ ጉ። ሰባት፡ ቀን፡ መሠውያውን፡ ቀድሰዋልና፡ ሰባት፡ ቀን፡ በዓል፡ አደረጉ።

፲፡ ከሰባተኛውም፡ ወር፡ በኻያ፡ ሶስተኛው፡ ቀን፡ ሕዝቡን፡ ኢየድንጊያቸው፡ አሰናበተ፡ እግዚአብሔ ር፡ ለዳዊትና፡ ለሰሎሞን፡ ለእሥራኤልም፡ ለወገኑ፡ ሰላደረገው፡ ቸርነት፡ ደስ፡ ብልዋቸው፡ ተጸናንተው፡ ሔዱ።

፲፩፡ ሰሎሞንም፡ የእግዚአብሔርን፡ ቤትና፡ የንጉ ሡን፡ ቤት፡ ጨረሰ፡ ይሰራውም፡ ዘንድ፡ በልቡ፡ ያሰ በውን፡ ሁሉ፡ በእግዚአብሔር፡ ቤትና፡ በቤቱ፡ ፈጸ መ።

፲፪፡ እግዚአብሔርም፡ ለሰሎሞን፡ በሌት፡ ተገለ በለት፡ አለውም። ጸሎትኽን፡ ሰማሁ፡ ይህንም፡ ሰ ፋራ፡ ለቍርባን፡ ቤት፡ መረጥሁ።

፲፫፡ ሰማያት፡ ብዘን፡ ዝዙምም፡ ባሪወርድ፡ አንበ ጣንም፡ ምድሪቱን፡ ያበላ፡ ዘንድ፡ ባዘው፡ ወይም፡በ ሕዝቤ፡ ላይ፡ ቸነፈር፡ ብልክ።

፲፬፡ በርሱም፡ ስሜ፡ የተጸራበት፡ ሕዝቤ፡ ወደኔ፡ ቢመለስ፡ አኔን፡ ሲለምን፡ ፊቴንም፡ ሲሻ፡ ከክፋ፡መ ነገሂም፡ ቢመለስ፡ ከሰማይ፡ እሰማዋለሁ፡ ኃጢአ ታቸውንም፡ ይቅር፡ አላለሁ፡ ምድራቸውንም፡ እፈ ውሳለሁ።

፲፭፡ አሁንም፡ በዚኽ፡ ሰፈራ፡ ለሚጸልይ፡ ሣሪያ ቼ፡ የተከፈቱ፡ ጀሮቼም፡ የሚሂደምሁ፡ ይሆናሉ።

፲፮፡ አሁንም፡ ይህን፡ ቦታ፡ መርጨዋለሁ፡ ቀድሼ ዋለሁም፡ ስሜ፡ ለዘላለም፡ ይኖርበት፡ ዘንድ፡ ሣሂኔ ና፡ ልቤም፡ ለዘላለም፡ በርሱ፡ ይጸናል።

፲፯፡ ደግሞም፡ አንተ፡ በፊቴ፡ ብትሔድ፡ ደዊት፡ አባትኽ፡ እንደ፡ ሔደ፡ እንደዘዝሁኽም፡ ሁሉ፡ ብታ ደርግ፡ ሕጌንና፡ ፍርደኝንም፡ ብትጠብቅ።

፲፰፡ እኔ፡የመንግሥትኽን፡ ዙፋን፡ አጸናለሁ፡ ላባ ትኽ፡ ለደዊት፡ እንደህ፡ ብዬ፡ ተስፋ፡ አንደ፡ ሰጠሁ ት። ከዘርኽ፡ በእሥራኤል፡ አለቃ፡ የሚሆን፡ ሰው፡ አደቀረጥም።

፲፱፡ ፈቀቅም፡ ብትሉ፡ እኔም፡ ለናንተ፡ የሰጠኋች ሁን፡ ሕጌንና፡ ትእዛዜን፡ ብትጥሉ፡ ብትሔዱም፡ ሌ ሎችንም፡ አማልክት፡ ብታመልኩ፡ ብትሰግዱላቸ ውም።

፳፡ ከሰጠኋቸው፡ ምድሬ፡ እነቅላቸዋለሁ፡ ደህ ንም፡ ቤት፡ ለስሜ፡ የቀደስሁትን፡ ከፊቴ፡ አውጥቼ፡ እጥላለሁ፡ በአሕዛብም፡ ሁሉ፡ ዘንድ፡ ለምሳሌና፡ለ ዋዛ፡ አደርገዋለሁ።

፳፩፡ ደህም፡ ረጅም፡ የሆነው፡ ቤት፡ መንገድ፡ ለ ሚያልፈ፡ ሰዋች፡ ሁሉ፡ ምሳሌ፡ ይሆናል፡ ደሂነቁማ ል፡ እንደህም፡ ይላሉ። ስለ፡ ምን፡ እግዚአብሔር፡ በ ዚች፡ ምድር፡ በዚህም፡ ቤት፡ እንደህ፡ አደረገ።

፳፪፡ ደግሞም፡ እንደህ፡ ሲሉ፡ ይመልሳሉ። ከም ስር፡ ያወጣቸውን፡ ያነተቻቸውን፡ አምላክ፡ እግዚ አብሔርን፡ ትተዋልና፡ ሌሎችንም፡ አማልክት፡ ተከ ትለዋልና፡ አምልከዋልምና፡ ሰግደውላቸዋልምና። ስለዚኽ፡ ደህን፡ ክፈ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ አመጣባቸው።

ምዕራፍ፡ ፰፡

፩፡ ሰሎሞንም፡ የእግዚአብሔርን፡ ቤትና፡ቤቱን፡ ከሰራ፡ በኋላ፡ ኻያ፡ አመት፡ በተፈጸመ፡ ጊዜ።

፪፡ ሑራም፡ ለሰሎሞን፡ የሰጠውን፡ ከተሞች፡ ሰ ሎሞን፡ አአና፡ የእሥራኤልንም፡ ልጆች፡ አሰቀመ ጠባቸው።

፫፡ ሰሎሞንም፡ ወደ፡ ሀማት፡ ጾባ፡ ሔደ፡ በረታባ ትም።

፱፡ በምድረ፡ በደም፡ ተድሞርን፡ ሰራ፡ በሀማት ም፡ የሰራቸውን፡ የእቃ፡ ቤቱን፡ ከተሞች፡ ሁሉ።

፭፡ የላይኛውን፡ ቤትሖሮንና፡ የታችኛውን፡ ቤት ሖሮን፡ ሰራ፡ ቅጥር፡ ሳንቃ፡ ሞጎፈ፡ ያለባትን፡ የጸና ትውን፡ አገር፡ አነጸ።

፮፡ በዓለትንና፡ ለሰሎሞን፡ የነበረትን፡ የእቃ፡ ቤ ት፡ ከተሞች፡ ሁሉ፡ የሠረገሎችንና፡ የፈረሰኞችንም፡ ከተሞች፡ ሰሎሞንም፡ ለመስራት፡ የሻውን፡ ሁሉ፡ በየሪሳሌምና፡ በሊባኖስ፡ ከመንግሥቱም፡ በታች፡ በ ነበረው፡ ምድር፡ ሁሉ፡ አነጸ።

፯፡ ከእሥራኤልም፡ ወገን፡ ያልሆኑ፡ አሕዛብ፡ ሁ ሉ፡ ከሄታውያን፡ የቀረ፡ ከአሞራውያንም፡ ከፈረዛ ውያንም፡ ከሀዋደያንም፡ ከየቡሳውያንም።

፰፡ ከልጆቻቸው፡ በምድር፡ በኋላቸው፡ ከቀረት፡ የእሥራኤል፡ ልጆች፡ ካልነደልዋቸው፡ አርሶቸውን፡ ሰሎሞን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ገባሮችና፡ ዜጎች፡ አደ ረጋቸው።

፱፡ ከእሥራኤልም፡ ልጆች፡ ሰሎሞን፡ የንጉሡን፡ ስራ፡ ለመስራት፡ ሎላልት፡ አላደረገም፡ ተዋጎችና፡ ሹማምት፡ የሠረገሎቹና፡ የፈረሰኞችም፡ አለቀች፡ነ በረሱ።

፲፡ የንጉሡም፡ የሰሎሞን፡ አይነተኞች፡ አለቀች፡ በሕዝቡ፡ ላይ፡ የሠለጠኑ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ካምሳ፡ ነ በረ።

፲፩፡ ሰሎሞንም፡ የፈርዖንን፡ ልጅ፡ ከደዊት፡ ከተ ማ፡ ወደ፡ ሰራላት፡ ቤት፡ አወጣት፡ ምስቴ፡ በደዊት፡ በእሥራኤል፡ ንጉሥ፡ ቤት፡ አትቀመጥ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ታቦት፡ የገባበት፡ ስፍራ፡ ቅደስ፡ ነውና፡ ሲል።

፲፪፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ ሰሎሞን፡ ለእግዚአብሔር፡ የሚቃጠል፡ ቊርባን፡ አቀረበ፡ በሰቀላው፡ ፊት፡ ለእ ግዚአብሔር፡ በሰራው፡ መሠውያ፡ ላይ።

፲፫፡ ሁለግዜ፡ ያቀርብበት፡ ነበረ፡ ሙሴ፡ እንደዘዘ፡ በሰንበትና፡ በጨረቃ፡ ትውልድ፡ በበዓላቱም፡ ቀን፡ ባመት፡ ሶስት፡ ጊዜ፡ እርሱም፡ በበዓለ፡ ናእት፡ በበዓ ለ፡ ሰዊትና፡ በበዓለ፡ መጸለት።

፲፬፡ ደግሞም፡ ካህናቱን፡ እንደ፡ አባቱ፡ እንደ፡ ደ ዊት፡ሠርዓት፡ እንደ፡ከፈላቸው፡በያገልግሎታቸው፡ አቀመ፡ ሌዋውያንም፡ እንደ፡ ሥርዓታቸው፡ ያመሰ ግኑ፡ ዘንድ፡ በካህናቱም፡ ፊት፡ እንደ፡ ቀኑ፡ሥርዓት፡ ያገለግሉ፡ ዘንድ፡ በረኞችም፡ በክፍላቸው፡ በደጅና፡ ደጅ፡ ደዊት፡ የእግዚአብሔር፡ሰው፡ እንደህ፡ አዝዋ ልና።

፲፭፡ የንጉሡም፡ ስለ፡ ካህናትና፡ ስለ፡ ሌዋውያን፡ ስለ፡ነገረ፡ ሁሉና፡ ስለ፡ አቃው፡ ጥበቃ፡ ባዘዘው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከተ፡ የሚተላለፍ፡ አልነበረም።

፲፮፡ የሰሎሞንም፡ ስራ፡ ሁሉ፡ የተዘጋጀ፡ ነበረ፡ የእ ግዚአብሔርን፡ ቤት፡ መሠረት፡ ከጣለ፡ ጀምሮ፡ እስ ኪጨርሰው፡ ድረስ። የእግዚአብሔርም፡ ቤት፡ በጣ ም፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ።

፲፯፡ የዚያን፡ ጊዜ፡ሰሎሞን፡ ወደ፡ ዓጽዮን፡ጋብር፡ ሔደ፡ ወደ፡ ኤሎትም፡ በኤደምያስ፡ ምድር፡ ሳለ ው፡ በባሕረ፡ አጠገብ።

፲፰፡ ሑራምም፡ በባሮቹ፡ እጅ፡ መርከቦችና፡የባሕ ረን፡ጠባይ፡ የሚያውቁ፡መርከበኞች፡ ሰደደለት። ከ ሰሎሞንም፡ ባሮች፡ጋራ፡ወደ፡ኦፊር፡ሔደ፡ ከዚያም፡ አራት፡ መቶ፡ አምሳ፡ መክሊት፡ ወርቅ፡ አነሡ፡ ወደ፡ ንጉሡም፡ ወደ፡ ሰሎሞን፡ ደዘው፡ መጡ።

ምዕራፍ፡ ፪፡

፩፡ የሳባም፡ ነግሥት፡ የሰሎሞንን፡ ወሬ፡በሰማች፡ ጊዜ፡ በእንቊ፡ሞልሽ፡ ትፈትነው፡ዘንድ፡ ከታላቅ፡ጉዞ ና፡ ሸቱና፡ብዙ፡ወርቅ፡የከበረም፡ዕንቊ፡ከተሸከሙ፡ ግመሎች፡ ጋራ፡ ወደ፡ የሩሳሌም፡ መጣች። ወደ፡ ሰሎ ሞንም፡ በደረሰች፡ ጊዜ፡ በልብዋ፡ያለውን፡ሁሉ፡ ነገረ ችው።

፪፡ ሰሎሞንም፡ የጠየቀችውን፡ ሁሉ፡ ተረጐመላ ት፡ ለሰሎሞንም፡ ከጠየቀችው፡ ሁሉ፡ የተሰወረው፡ ነገር፡ አልነበረም።

፫፡ የሳባም፡ ነግሥት፡ የሰሎሞንን፡ ጥበብ፡ ካዮች፡ በኋላ፡ የሰራውንም፡ ቤት።

፬፡ ደግሞም፡ የማዕጀን፡ መብል፡ የባሮቹንም፡ አ ቀማመጥ፡ የሎላልቱንም፡ ሠርዓት፡ አለባበሳቸውን ም፡ ጽጅ፡ አሳላፎቹንም፡ ልብሳቸውንም፡ ወደ፡ እግ ዚአብሔር፡ ቤት፡ ይወጣበት፡ የነበረውን፡ መውጪ፡ ባዮች፡ ጊዜ፡ ከመደነቅ፡ የተነሣ፡ መንፈስ፡ አልቀረላ ትም።

፭፡ ንጉሡንም፡ አለችው። በምድሬ፡ ሳለሁ፡ ስለ፡ ስራኽና፡ ስለ፡ ጥበብህ፡ የሰማሁት፡ ነገር፡ እውነት፡ ነው።

፮፡ የነገሩኝንም፡ አላመንሁም፡እኔ፡ እስክመጣ፡ ዓይኔ፡ እስኪያይ፡ ድረስ፡ እነሆም፡ የታላቁን፡ ጥበብ ኽን፡ እኩሌታ፡ አልነገረኝም፡ እነሆም፡ ጥበብህ፡ከተ ወራው፡ ይልቅ፡ በልጦ፡ አገኘሁት።

፯፡ ሰዎችኽ፡ ምስጉኖች፡ ናቸው፡ ባሮችኽም፡ በዘ መኑ፡ ሁሉ፡ በፊትኽ፡ የሚቀሙትና፡ ጥበብኽን፡ የ ሚሰሙት፡ መስጉኖች፡ ናቸው።

፰፡ እግዚአብሔር፡ አምላክኽ፡ የተባረከ፡ ይሁን፡ በዙፋኑ፡ ያነግሠህ፡ዘንድ፡የወደደ፡ ለእግዚአብሔር፡ ላምላክኽ፡ ንጉሥ፡ እንድትሆን። አምላክኽ፡ እሥ ራኤልን፡ ወድዋልና፡ ስለዚኽ፡ በላዩ፡ ንጉሥ፡ አደረገ ኽ፡ ፈርድና፡ ቅን፡ ታደርግ፡ ዘንድ።

፱፡ ደግሞም፡ ለንጉሡ፡ መቶ፡ ኽያ፡ መክሊት፡ ወ ርቅ፡ ሰጠችው፡ እጅግም፡ ብዙ፡ ሸቱ፡ የከበረም፡ ብ ዙ፡ ዕንቊ። ለሰሎሞንም፡ ለንጉሡ፡ የሳባ፡ ንግሥት፡ እንደ፡ ሰጠችው፡ ሸቱ፡ ያለ፡ አልነበረም።

፲፡ ደግሞም፡ የሑራም፡ ባሮች፡ ከሰሎሞን፡ ባሮች፡ ጋራ፡ ከኦፊር፡ ወርቅን፡የሰንደል፡እንጨት፡እጅግም፡ የከበረ፡ ዕንቊ፡ አመጡ።

፲፭፡ ንጉሡም፡ከሰንደሉ፡ እንጨት፡ ወደ፡ እግዚአ ብሔር፡ ቤትና፡ ወደ፡ ንጉሡ ፡ ቤት፡ መውጫ፡ መውረጃ፡ አደረገ፡ ለመዘምራኑም ፡ መሰንቆና ፡ በገና። ይህን፡ የሚመስል፡ እንጨትም ፡ በይሁዳ፡ ምድር፡ ከተ፡ አልታየም።

፲፮፡ ንጉሡም፡ሰሎሞን፡ ለሳባ፡ንግሥት፡ የሻችውን፡ የለመነችውን፡ ሁሉ፡ ሰጣት፡ ደግሞም፡ እርስዋ፡ ከሰጠችው፡ የሚበልጥ። ከሎላልትዋም፡ ጋራ፡ ተመለሰች፡ ወደገርዋም፡ ሔደች።

፲፫፡ ለሰሎሞንም፡ባመት፡ባመት፡የሚገባው፡የወርቁ፡ ሚዛን፡ ስድስት፡ መቶ ፡ ከሰድሳ፡ ስድስት፡ መክሊት፡ ወርቅ፡ነበረ።

፲፬፡ ሸቀጡችና፡ ነጋዴች፡ከሚያደርሱት፡ ሌላ። የዓረብ፡ ነገሥታትና፡የምድር፡ ከማመትም፡ለሰሎሞን፡ ወርቅና፡ብር፡ ያመጡ፡ነበረ።

፲፭፡ ንጉሡም፡ ሰሎሞን፡ ሁለት ፡ መቶ፡ ቅጥቅጥ፡ የወርቅ፡ ጋሻ፡ አደረገ፡ ኢያንደንጂም ፡ ጋሻ፡ ስድስት፡ መቶ፡ ሚትቃል፡ ወርቅ፡ ነበረ።

፲፮፡ ሶስት፡ መቶም፡ ሾለላ፡ ጋሻ፡ ኢያንደንጂም፡ ጋሻ፡ ሶስት፡ መቶ ፡ ሚትቃል ፡ ወርቅ፡ ነበረ። ንጉሡም፡ በሊባኖስ፡ ዱር፡ በተሰራው፡ አደራሽ፡ አኖረው።

፲፯፡ ደግሞም፡ ንጉሡ፡ታላቅ፡የዘሀን፡ ጥርስ፡ ዙፋን፡ አደረገ፡ በጽረ፡ወርቅም፡ አለበሰው።

፲፰፡ ስድስት፡ እርከንና፡ አንድ ፡ የወርቅ፡ የግረ፡ ድጊም፡ ከዙፋኑ፡ ጋራ፡የተጋጠሙ፡ ነበረ። በዙፋኑም፡ በዚህና፡ በዚያ፡ ሁለት፡ ደገፍች፡ ነበረ። በደገፍቹም፡ አጠገብ፡ ሁለት፡ አንበሶች፡ ቁመው፡ ነበረ።

፲፱፡ አሥራ፡ ሁለትም፡አንበሶች፡ በስድስቱ፡ እርከኖች፡በዚኽና፡በዚያ፡ቁመው፡ነበረ። በመንግሥታት፡ ሁሉ፡ እንደርሱ፡ ያለ፡ ዙፋን፡ አልተደረገም።

፳፡ ንጉሡም፡ ሰሎሞን፡የሚጠጣበት፡ እቃ፡ሁሉ፡ የወርቅ፡ ነበር፡ ከሊባኖስም፡ ዱር፡ በተሰራው፡ ቤት፡የ ነበረው፡ እቃ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ከጽረ፡ ወርቅ፡ ነበረ፡ በሰሎሞን፡ ወራት፡ብር፡ ከተ ፡ ጉደይ፡ አልነበረምና።

፳፩፡ የንጉሡ ፡ መርከቦች ፡ከሑራም፡ ባሮች፡ ጋራ፡ ወደ፡ ተርሲስ፡ ይሔዱ፡ ነበሩና ፡ ከዚያም ፡ በየሶስት፡ አመት፡ አንደግዜ፡ ብርና፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ነበረ፡ ያዘሀን፡ ጥርስና፡ ዝንጀሮ፡ ሶሪትም፡ (ጠዋዊስም)።

፳፪፡ ሰሎሞንም፡ ከምድር፡ነገሥታት፡ሁሉ፡ በባለ ጠግነትና፡ በክብር፡ በለጠ።

፳፫፡ የምድርም፡ነገሥታት፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔር፡ ለልቡ፡የሰጠውን ፡ ጥበብ ፡ ይሰሙ፡ ዘንድ፡ የሰሎሞንን፡ ፊት፡ ይመኙ፡ ነበረ።

፳፬፡ ባመት፡ባመትም፡ እጅ፡ መንሻ፡ያመጡለት፡ ነበር፡ የብርና፡ የወርቅ፡ እቃ ፡ ግምጃም ፡ ጋሻ፡ ጦርም፡ ሸቱም፡ ፈረስና፡ በቅሎም።

፳፭፡ ለሰሎሞንም፡አራት፡ሽኽ፡ ጋጥ፡ የሠረገላ፡ፈረስ፡ ነበረው፡ አሥራ፡ሁለቱ፡ሽኽም፡ ፈረሰኖች፡በሠረገላችም፡ከተሞች፡ አኖራቸው፡ በየረሳሌምም፡ከንጉሡ፡ ጋራ።

፳፮፡ በነገሥታትም፡ ሁሉ፡ ላይ፡ ከኤፍራጥስ፡ ወንዝ፡ ጀምሮ፡እስከ፡ ፈልስጥኤም፡ ምድርና፡ እስከ፡ግብስርም፡ ደርቻ፡ ድረስ፡ ነገሣ፡ ነበረ።

፳፯፡ ንጉሡም፡ ብሩን፡ በየረሳሌም ፡ አንድ፡ደንጊያ፡ አደረገው፡ የዘግባውንም፡ አንጨት፡ በቁላ ፡ አንደሚበቅል፡ ሾላ፡ አበዛው።

፳፰፡ ለሰሎሞንም፡ ፈረስ ፡ ከምስርና፡ከአገር፡ ሁሉ፡ ይወጣለት፡ ነበር።

፳፱፡ የሰሎሞንም ፡የቀረው፡ስራ፡የፊተኛውና፡የኋለኛው፡ በነቢይ፡ በናታን ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ፡ የተጻፈ፡ አይደለውምን፡ በሲሎኒውም ፡ በአሂያ፡ የትንቢት፡ መጽሐፍ፡በዶይም፡በተመልካቹ፡ራእይ፡በናባጥ፡ ልጅ፡ በዮርብዓም፡ ላይ፡ባየው፡ መጽሐፍ።

፴፡ ሰሎሞንም፡ በየረሳሌም፡በእሥራኤል፡ሁሉ፡ ላይ፡ አርባ፡ አመት፡ ነገሠ።

፴፩፡ ሰሎሞንም፡ ካባቶቹ፡ ጋራ ፡ አንቀለፈ፡ ባባቱም፡ በዳዊት፡ ከተማ፡ ቀበረት፡በርሱ፡ፈንታም፡ልጁ፡ ሮብዓም፡ ነገሠ።

ምዕራፍ፡ ፲፡

፩፡ ሮብዓምም፡ ወደ፡ ሴኬም፡ ሔደ፡ እሥራኤል፡ሁሉ፡ ያነግሡት፡ ዘንድ፡ ወደ፡ሴኬም፡ መጥተው፡ ነበሩና።

፪፡ የሮብዓምም፡የናባጥ፡ልጅ፡ በምስር፡የነበረው፡ በሰማ፡ጊዜ፡ ከሰሎሞን፡ ፊት፡ ወደዚያ፡ ሸሽቶ፡ነበርና፡ የዚያን፡ጊዜውን፡ከምስር፡ተመለሰ።

፫፡ ልከውም ፡ ጸረት። የሮብዓምም ፡ ከእሥራኤል፡ ሁሉ፡ ጋራ፡መጣ፡ ለሮብዓምም፡ እንደ፡ሲሉ፡ ነገሩት።

፬፡ አባትኽ፡ ቀምበራችነን፡ አከበደ፡ አንተም፡አባትኽ፡ካሸከመነው፡ከጽኑው፡አገልግሎት፡ከከበደው፡ ቀምበር፡ ዋቂት ፡ አቅልልን ፡ እኛም፡ እንገዛልኻለን።

፭፡ እርሱም፡ከሶስት፡ቀን፡በኋላ፡ወደኔ፡ተመለሱ፡ አላቸው፡ ሕዝቡም፡ ሔደ።

፮፡ ንጉሡም፡ሮብዓም፡ባባቱ፡በሰሎሞን፡ፊት፡ በሕይወቱ፡ ሳለ፡ይቆሙ፡የነበረትን ፡ ሸማግሌች፡ አንድህ፡ ሲል፡ ተማከረ። ምን፡ ትመክረኛላችሁ ፡ ለዚኽ፡ ሕዝብ፡ እመልስለት፡ ዘንድ።

፯፡ እርሳቸውም ፡ አሉት። እሌህን ፡ ሕዝብ፡ ደስ፡ ብታሰኛቸው፡ በገራ ፡ ነገርም ፡ ብትናገራቸው ፡ በዘመኑ፡ ሁሉ፡ባሮች፡ ይሆኑኻል።

፰፡ እርሱ፡ ግን፡ የሸማግሌችን፡ምክር፡ትተ፡ከርሱ፡ ጋራ ፡ ያደጉትንና ፡ በፊቱ ፡ የሚቀሙትን፡ አሸከርች፡ ተማከረ።

፱፡ አላቸውም፡ ምን፡ ትመክራላችሁ፡ ለዚኽ፡ሕ

ዝብ፡አባትኽ፡የጨነብነን፡ቀምበር፡ጥቂት፡አቅልል፡የሚለኻ፡አመልስ፡ዘንድ።

I፡ እኩያተቹም፡ከርሱ፡ጋራ፡ያደጉቱ፡መለስለት፡አሉትም። አባትኽ፡ያከበደብነን፡ቀምበር፡አንተ፡አቅልልን፡ላሉኽ፡ሕዝብ፡መልስላቸው፡እንደሀም፡በላቸው። ታናሽ፡ጻቴ፡ካባቴ፡ወንብ፡ደደነድናል።

I፭፡ አባቴ፡የከበደ፡ቀምበር፡ጨነባችሁ፡እኔም፡ከዚያ፡የከበደ፡እጨምርባችኋለሁ። አባቴ፡በኮርባጅ፡ገረፈችሁ፡እኔ፡ግን፡በጊንጥ፡እገርፈችኋለሁ።

I፱፡ የሮብዓምና፡ሕዝቡም፡ሁሉ፡በሶስተኛው፡ቀን፡ወደ፡ረ፞ኾብዓም፡መጡ፡ንጉሡ፡እንደሀ፡ሲል፡እንደዘዛቸው፡በሶስተኛው፡ቀን፡ወደኔ፡ተመለሱ።

I፫፡ ንጉሡም፡በጽኑ፡ነገር፡መለሰላቸው፡ንጉሡም፡ረ፞ኾብዓም፡የሸማግሎችን፡ምክር፡ተወ።

I፬፡ እንጂ፡ሕፃናቱም፡ምክር፡መለሰላቸው፡አላቸውም፡አባቴ፡የከበደ፡ቀምበር፡ጨነባችሁ፡እኔ፡ግን፡ከዚያ፡አብልጦ፡የከበደ፡እጨምርባችኋለሁ። አባቴ፡በኮርባጅ፡ገረፈችሁ፡እኔ፡ግን፡በጊንጥ፡እገርፈችኋለሁ።

I፭፡ ንጉሡም፡የሕዝቡን፡ነገር፡አልሰማም፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የተመደበ፡ነበርና፡እግዚአብሔር፡በሲሎያዊው፡በአሂያ፡እጅ፡ለናባጥ፡ልጅ፡ለዮሮብዓም፡የተናገረውን፡ነገር፡ይፈጽም፡ዘንድ።

I፮፡ እሥራኤልም፡ሁሉ፡ንጉሡ፡እንደሰማቸው፡ባዩ፡ጊዜ፡ሕዝቡ፡ለንጉሡ፡መለሱለት፡እንደሀም፡አሉ። ከጀሴት፡ጋራ፡ምን፡ክፍል፡አለን፡ርስት፡ከእሤይ፡ልጅ፡ጋራ፡የለነም። እሥራኤል፡ሆይ፡ወደ፡ድንኳንኽ፡ተመለስ። አሁንም፡አንተ፡ጀሴት፡ሆይ፡ቤትኽን፡ጠብቅ ። እሥራኤልም፡ሁሉ፡ኢየድንኳኑ፡ሔደ።

I፯፡ በደሁያ፡ከተሞች፡በተቀመጡት፡በእሥራኤል፡ልጆች፡ላይ፡ግን፡ረ፞ኾብዓም፡ነገሠ።

I፰፡ ንጉሡም፡ረ፞ኾብዓም፡ግብር፡አስገባሪው፡ሐዶራምን፡ሰደደ፡የእሥራኤልም፡ልጆች፡ወገሩት፡ሞተም። ንጉሡም፡ረ፞ኾብዓም፡ፈጥኖ፡ወደ፡ሠረገላው፡ተቀምጦ፡ወደ፡የሩሳሌምም፡ሸሸ።

I፱፡ እሥራኤልም፡አስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡ከጀሴት፡ቤት፡ሸፍተ፡ተለየ።

ምዕራፍ፡ ፲፩፡

፩፡ ረ፞ኾብዓምም፡ወደ፡የሩሳሌም፡ሒደ፡የይሁዳንና፡የብንያምን፡ቤት፡ሰበሰበ፡መቶ፡ሰማንያ፡ሽኽ፡የተመረጠ፡አርበኛ፡እሥራኤልን፡ይወጋ፡ዘንድ፡መንግሥቱንም፡ወደ፡ረ፞ኾብዓም፡ይመልስ፡ዘንድ።

፪፡ የእግዚአብሔርም፡ነገር፡ወደ፡ሻማዕያ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ሰው፡እንደሀ፡ሲል፡ሆነ።

፫፡ ለረ፞ኾብዓም፡ለሰሎሞን፡ልጅ፡ለይሁዳ፡ንጉሡ፡ንገረው፡በይሁዳና፡በብንያምም፡ላሉት፡ለእሥራኤል፡ሁሉ፡እንደነገሙ፡በላቸው።

፬፡ እግዚአብሔር፡የሚለው፡ይህ፡ነው። አትውጡ፡ወንድሞቻችሁንም፡አትዋጉ። ከላንት፡ሰው፡ሁሉ፡ወደ፡ቤቱ፡ይመለስ፡ይህ፡ነገር፡ከኔ፡ሁንዋልና። የእግዚአብሔርንም፡ነገር፡በሰሙ፡ጌዜ፡ተመለሱ፡ከየሮብዓምም፡ጋራ፡ለመዋጋት፡አልሔዷም።

፭፡ ረ፞ኾብዓምም፡በየረሳሌም፡ተቀመጠ፡በይሁያም፡ቅጥር፡ያለባቸው፡ከተሞች፡ሰራ።

፮፡ ቤተልሔምንም ፡ሰራ ፡ ዔታምንም ፡ተቀዓንም።

፯፡ ቤትጹርንም፡ሦኮንም፡ዓጺላምንም።

፰፡ ጋትንም፡ማረሻንም፡ዚፍንም።

፱፡ አደራያምንም፡ላኪሽንም፡ዓዘቂንም።

I፡ ኦርዓንሃህ፡አየሎንንም፡ኬብሮንንም፡በይሁያና፡በብንያምም፡እጅግ፡የጸኑትን፡ከተሞች።

I፩፡ ምሸጎቹንም፡አጸና፡አለቀችም፡አረባቸውም፡ምግቡን፡ዘይትና፡ጸጅም፡አከማቸው።

I፪፡ ደግሞም፡በኢያንጂንጂ፡ከተማ፡ሁሉ፡ሶለላ፡ጋሻና፡ሰላጢን፡አኖረ፡እጅግም ፡ተጠንቅቀ፡አጸናቸው፡በይሁያና፡በብንያምም፡ላይ፡ነገሠ።

I፫፡ ካህናትና፡ሌዋውያንም፡በእሥራኤል፡ሁሉ፡የተገኙት፡ካገራቸው፡ሁሉ፡ወደርሱ፡መጡ።

I፬፡ ሌዋውያን፡ርስታቸውንና፡ጕልታቸውን፡ትተው፡ወደ፡ይሁያና፡ወደ፡የሩሳሌምም፡አለፈ፡የርብዓምና፡ልጆቹ፡አርቀዋቸው፡ነበረና፡የእግዚአብሔር፡ካህናት፡እንደይሆኑ።

I፭፡ አርሱ፡ግን፡ለኮረፏታው፡ካህናት፡አስነሣ፡ለሰይጣናትና፡ለሰራቸው፡አንቦሶች።

I፮፡ ደግሞም፡ከእሥራኤል፡ነገድ፡ሁሉ፡እግዚአብሔርን፡የእሥራኤልን፡አምላክ፡ለመለመን፡ልባቸውን፡የሰጡ፡ሁሉ፡አርሳቸውን፡ተከትለው፡ወደ፡የሩሳሌም፡መጡ፡ለእግዚአብሔር፡ላባቶቻቸው፡አምላክ፡መሥዋዕታቸውን፡ያቀርቡ፡ዘንድ።

I፯፡የይሁያንም፡መንግሥት፡አበረቱ፡ረ፞ኾብዓምንም፡የሰሎሞንን፡ልጅ፡ሮሰት፡አመት፡አጸኑት፡በሂዊትና፡በሰሎሞን፡መንገድ ፡ሶስት ፡አመት ፡ሒደዋልና።

I፰፡ ረ፞ኾብዓምም፡መህላቱን፡የይሪሞትን፡ልጅ፡የሂዋትን፡የልጂን፡ልጅ፡አገባ፡ደግሞም፡አቢሐይልን፡የኤልያብን፡ልጅ፡የአዜን፡የልጅ፡ልጅ።

I፱፡ ወንጀች፡ልጀችም፡ወለደችለት ፡ይዑሽን፡ሸመሪያንም፡ዘሐምጊም።

፳፡ ከርሰዋም፡በኋላ ፡መዓካን ፡አገባ፡የአብሸሎምን፡ልጅ፡አቢያንም ፡ወለደችለት ፡ዓታይንም፡ዚዛንም፡ሸሎሚትንም።

፳፩፡ ረ፞ኾብዓምም ፡ከምሸቶቹና ፡ከቁባቶቹ፡ሁሉ፡ይልቅ፡መዓካን ፡የአብሸሎምን ፡ልጅ፡ ወደደ፡አሥራ፡ስምንት ፡ምሸቶችና ፡ስድሳ ፡ቁባቶች፡ነበሩት ፡ኻያ ፡ስምንት ፡ወንጀች ፡ልጀችና፡ስድሳ፡ቤቶች፡ልጀች፡ወለደ።

፲፮፡ ፈ፦ንብዓምም፡ አቢያን፡ የመሀካን፡ ልጅ፡ በ ወንድሞቹ፡በላይ፡አለቃ፡አድርጎ፡ አቀመው። ንጉሥ፡ ያደርገው፡ ዘንድ፡ አስብዋልና።

፲፯፡ ብልሀተኞም፡ ሆነ፡ልጆቹንም፡ሁሉ፡ በይሁዳ፡ ግዛት፡ ሁሉ፡ ከፈላቸው። በብንያምም፡ በጸኑትም፡ ከተሞች፡ ሁሉ፡ ብዙ፡ ምግብም፡ ሰጣቸው። አጅግ፡ ሴተኞም፡ ፈቀደላቸው።

ምዕራፍ፡ ፲፪፡

፩፡ ፈ፦ንብዓምም፡ መንግሥቱን፡ ባጸናና፡ ባበረታ፡ ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን፡ ሕግ፡ተወ፡ አሠራኤልም፡ ሁሉ፡ ከርሱ፡ ጋራ።

፪፡ ፈ፦ንብዓም፡ በነገሠ፡ባምስት፡አመት፡ዚ፡ዛቅ፡ የምስር፡ ንጉሥ፡ ወደ፡ የፈሳሌም፡ወጣ፡እግዚአብሔ ርን፡ በድለዋልና።

፫፡ ሸኽ፡ ከሁለት፡ መተም፡ ሠረገላ፡ ይዞ፡ መጣ፡ስ ድሳ፡ ሸኽም፡ፈረሰኛ። ከምሰርም፡ ከርሱ፡ጋራ፡ ለመ ጣው፡ ሕዝብ፡ቍጥር፡አልነበረውም፡ አርሱም፡ ከሊ ቢያ፡ከሡቂምም፡ ከኢትዮጵያም።

፬፡ በደሁያም፡ የጸኑትን፡ ከተሞች፡ ወሰደ፡ ወደ፡ የፈሳሌምም፡ መጣ።

፭፡ ነቢዩም፡ ሸማዕያ፡ ወደ፡ ፈ፦ንብዓምና፡ ከሢ ዛቅ፡ ፊት፡ ሸሸተው፡ በየፈሳሌም፡ ወደ፡ ተከማቹት፡ ወደ፡ይሁዳ፡ አለቀች፡ገባ፡አላቸውም። እግዚአብሔ ር፡ የሚለው፡ ይህ፡ነው፡ አላንተ፡ ጣላቸሁኝ፡አኔም፡ በሢዛቅ፡ አጅ፡ ጣልኋችሁ።

፮፡ ንጉሡና፡ የአሠራኤልም፡ አለቀች፡ ተዋረደ፡ አሉም፡ እግዚአብሔር፡ ጻድቅ፡ነው።

፯፡ እግዚአብሔርም፡አርሳቸው፡ አንደ፡ተዋረደ፡ ባየ፡ጊዜ፡ የእግዚአብሔር፡ነገር፡አንደህ፡ሲል፡ለሸማ ዕያ፡ ሆነ ። ተዋርደዋልና፡ አላጠፋቸውም ፡ ጥቂት፡ አረያቸዋለሁ፡ አንጅ፡ ቍጣዩ፡ በየፈሳሌም፡ ላይ፡ በ ሢዛቅ፡ አጅ፡ አንደይፈስ።

፰፡ ነገር፡ ግን፡ ይገዙለታል፡ለኔ፡ በመገዛትና፡ለምድ ር፡ነገሥታት፡ በመገዛት፡ መኽከል፡ ያለውን፡ ልዩነት፡ ያውቁ፡ዘንድ።

፱፡ ሢዛቅም፡ የምስር ፡ ንጉሥ፡ ወደ፡ የፈሳሌም፡ መጣ፡የእግዚአብሔርን፡ ቤትና፡የንጉሡንም፡ ቤት፡ አቃ፡ ወሰደ፡ ሁሉንም፡ በዘበዘ፡ ሰሎሞንም፡የሰራው ን፡ የወርቁን፡ ጋሻ፡ ወሰደ።

፲፡ ንጉሡም፡ፈ፦ንብዓም፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ የናስ፡ ጋ ሻ፡ አደረገ፡ ለጋሻ፡ ጀግሮችም፡ አለቀች፡ የንጉሡን፡ ቤ ት፡ ደጅ፡ ይጠብቁ፡ ለነበረት፡ አሳለፎ፡ ሰጣቸው።

፲፩፡ ንጉሡም፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በገባ፡ ጊዜ፡ መጥተው፡ ጋሻውን፡ደሸከሙ፡ ነበረ፡ ደግሞም፡ መልሰው፡ በጠባቂች፡ ቤት፡ ያኖረት፡ ነበር።

፲፪፡ አርሱም፡ ሰውነቱን፡ ሰለ ፡ አዋረደ ፡ የእግዚአ ብሔር፡ ቍጣ፡ ፈጽሞ፡ አንደያጠፋው፡ ከርሱ፡ተመ ለሰ፡ በይሁያም፡ ደግሞ፡ ጥቂት፡ በጉነት፡ ነበረ።

፲፫፡ ንጉሡም፡ፈ፦ንብዓም፡በየፈሳሌም፡ በረታ፡ነገ ሠም። መንግሥትም ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ያርባ፡ አንድ፡ አመት፡ ኮልማሳ፡ ነበረ፡ በየፈሳሌምም፡ አሠራ፡ ሰባ ት፡ አመት፡ ነገሠ፡ ስሙን ፡ ከዚያ ፡ ያኖር ፡ ዘንድ፡ ከአ ሠራኤል፡ነገድ፡ ሁሉ፡ አግዚአብሔር፡ በመረጣት፡ አ ገር። የናቱም፡ ስም፡ ናዕማ፡ ነበረ ፡ አርስዋም፡ አሞና ዊት።

፲፬፡ ክፈ፡ ነገርም፡ ሰራ ፡ እግዚአብሔርን፡ ደሻ፡ ዘን ድ፡ልቡን፡ አላዘጋጀም፡ ነበረና።

፲፭፡ የፈ፦ንብዓምም፡ ሰራ፡ የፊተኞቹና፡ የኋለኛ ቹ፡ አርስዋ፡በነቢዩ፡ በሸማዕያ፡ መጽሐፍ፡ በተመ ልካቹ፡ በዒዶ፡ መጽሐፍ፡ የተጻፈች፡አደደለችምን። ፈ፦ንብዓምና፡ሮብዓም፡ግን፡በዘመናቸው፡ ሁሉ፡ አ ርሱ፡በርሳቸው፡ ደዋኑ፡ነበር።

፲፮፡ ፈ፦ንብዓምም፡ ካባተቹ፡ ንራ ፡ አንቀላፈ፡በደ ዊትም፡ ከተማ፡ ተቀበረ፡ በርሱም፡ ፈንታ፡ አበ ያ፡ል ጀ፡ነገሠ።

ምዕራፍ፡ ፲፫፡

፩፡ የሮብዓምም፡ በነገሠ፡ ባሥራ፡ ስምንተኞው፡አ መት፡ አቢያ፡ በይሁዲ፡ ላይ፡ ነገሠ።

፪፡፡ በየፈሳሌምም፡ሶስት፡አመት፡ነገሠ፡ የናቱም፡ ስም፡ ሚካያ፡ ነበረ፡ አርስዋም፡ ሠኡሪኤል፡ ልጅ፡ከጊ ቤዓ። በአቢያና ፡ በየሮብዓምም ፡ መኽከል ፡ ሰልፍ፡ ነበረ።

፫፡ አቢያም፡ ወደ፡ ሰልፍ፡ ወጣ፡ ሰዎቹም፡ አጅግ፡ ሰልፈኞች፡ ነበረ፡ የተመረጡም ፡ አራት፡ መቶ፡ ሸኽ፡ የሮብዓመም፡ በርሱ፡ ላደ ፡ ተሰለፈ፡ ሰምንት፡ መቶ፡ ሸኽ፡ሰዎች፡ ሁኖ ፡ አርሳቸውም ፡ የተመረጡ፡ ነበሩ፡ በሰልፍም፡ አጅግ፡ የበረቱ።

፬፡ አቢያም፡ በኤፍረም፡ ተራራ፡ ባለው፡በጸማራ ይም፡ ተራራ፡ ቀመ፡ አለም። ሰማ፡ የሮብዓም፡ ሆይ፡ አላንተም፡ አሠራኤል፡ ሁላችሁ።

፭፡ በውኑ፡አታውቁምን፡አግዚአብሔር፡የአሠራ ኤል፡አምላክ፡መንግሥትን፡ ለደዊት፡ በአሠራኤል፡ ላይ፡ ለዘላለም፡ ለርሱና ፡ ለልጆቹ፡ በጨው ፡ መሐላ፡ አንደ፡ ሰጠ።

፮፡ የሮብዓም፡ ግን፡ የናባጥ፡ ልጅ፡ የደዊት፡ ልጅ፡የ ሰሎሞን፡ ባርያ፡ ተነሣ፡በጌታውም፡ ላመፀ።

፯፡ ምናምንቶች፡ ሰዎችና፡ የሰይጣን፡ልጆችም፡ወደ ርሱ፡ ተሰበሰቡ፡በረ፡ኘ፡ፈ፦ንብዓምም፡በሰሎሞን፡ልጅ፡በ ረቱበት፡ ፈ፦ንብዓምም ፡ ሕፃን ፡ ልቡም ፡ ፈሪ ፡ ነበረ፡ ደቋቋማቸውም፡ ዘንድ፡ አልቻለም።

፰፡ አሁንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት፡ በደ ዊት፡ ልጆች፡አጅ፡ የሚያስገዛትን፡መቋቋም፡ አንጂ ቻላችሁ፡ ታሰባላችሁ ፡ አላንተም ፡ አጅግ ፡ ታላቅ፡ ሕ ዝብ፡ ናችሁ፡ የወርቅም፡ አንቦሶች፡ የሮብዓም፡ያደረ ግላችሁ፡አማልክት፡ አልዋችሁ።

፱፡ የሐሮንንም፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ካህና

ትና፡ሌዋውያን፡ አላሳደደችሁምን፡ እነሂ፡ ምድር ም፡አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ለላንተ፡ ካህናት፡አደረጋችሁ። የ መጣ፡ ሁሉ፡ ለላንተ፡ ካህናት፡ የደረጋችሁ። የመጣ፡ ሁሉ፡እጂንም፡ የቀደሰ፡በወደፈን፡ወይም፡ በሰባት፡ ደንግሌ፡ ለለዚያ፡ አማልክት፡ ላልሆኑት፡ካህን፡ ይሆ ናል።

፲፡ ለኛ፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ነው፡ አምላካችን፡ እ ኛ፡ የማንተወው፡ ካህናቱም፡ የአግዚአብሔር፡አገል ጋዮች፡ የሐሮን፡ ልጆች፡ ናቸው፡ ሌዋውያንም፡ በሥር ዓታቸው፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ናቸው።

፲፩፡ ለእግዚአብሔርም፡ የሚቃጠል፡ ቍርባን፡ ጽ ዋትና፡ ማታ፡ ያቀርባሉ፡ ያማረውንም፡ እጣን፡ የሚ ታየውንም፡ እንጅራ፡ በጽረይቱ፡ ማዕድ፡ የወርቂቱ ንም፡ መቅረዝ፡ማብርያዋንም፡ ማታ፡ ማታ፡ ትበራ፡ ዘንድ፡ ያዘጋጀሉ። እኛ፡ ያመላካችነን፡ ትእዛዝ፡ እን ጠብቃለን፡ አላንተ፡ ግን፡ ተዋችሁት።

፲፪፡ እነሆም፡ በጭፍሮቻችን፡ እግዚአብሔር፡ አለ ቃ፡ነው፡ መለከትም፡ የሚነፋ፡ ካህናቱ፡ ናቸው፡በላ ንተ፡ ላደም፡ ይጮኻሉ። አላንት፡ የእሥራኤል፡ልጆ ች፡ እግዚአብሔርን፡ ያባቶቻቸሁን፡ አምላክ፡ አትዋ ጉ፡ ይህ፡ነገር፡ አደበጀችሁምና።

፲፫፡ የሮብዓም፡ ግን፡በስከ፡ኋላቸው፡ በጀርባቸው፡ ደመጣባቸው፡ ዘንድ፡ ደጀን፡ አዞረባቸው፡ እንጂሁ ም፡ በደሁድ፡ ፌት፡ ነበረ፡ደጀኑም፡በኋላቸው፡ከብዋ ቸው፡ነበር።

፲፬፡ ደሁድም፡ በፌቱና፡ በኋላው፡ ሰልፈን፡ ባዮ፡ጊ ዜ፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ጮኸ፡ ካህናቱም፡መለከት፡ ነፉ።

፲፭፡ የደሁደም፡ ሰዉች፡ ጮኹ፡ የደሁደም፡ ሰዉ ች፡በጮኹ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ የሮብዓምንና፡ አ ሠራኤልን፡ ሁሉ፡ በደሁደና፡ በአቢያ፡ ፌት፡ መታ ቸው።

፲፮፡ የእሥራኤልም፡ ልጆች፡ ከደሁድ፡ ሸሹ፡ እግዚ አብሔርም፡ በጀቸው፡ ጣላቸው።

፲፯፡ አቢያም፡ ከሕዝቡ፡ ጋራ፡ ታላቅ፡አመታት፡መ ታቸው፡ ከእሥራኤልም፡ አምስት፡ መቶ፡ ሽኽ፡ የተ መረጡ፡ ሰዉች፡ ተውግተው፡ ወደቁ።

፲፰፡ በዚያም፡ ዘመን፡ የእሥራኤል፡ ልጆች፡ተዋረ ዱ፡ የደሁደም፡ ልጆች፡ በእግዚአብሔር፡ ባባቶቻቸ ው፡ አምላክ፡ ታምነዋልና፡ አጀግ፡ ጐለመሱ።

፲፱፡ አቢያም፡ የሮብዓምን፡አሳደደው፡ከተሞቹን ም፡ ቤትኤል፡ መንደሮችዋንም፡ ደሻናንም፡ መንደ ሮችዋንም፡ ሄፈሮንንም፡ መንደሮችዋንም፡ ወሰደ።

፳፡ የሮብዓምም፡ ከዘደ፡ ኃይላ፡ በአቢያ፡ ዘመን፡ ደቀም፡ ዘንድ፡አልቻለም፡እግዚአብሔርም፡ ቀሠፈ ው፡ ሞተም።

፳፩፡ አቢያም፡ ጸና፡ አሠራ፡ አራትም፡ ምሽቶች፡ አገባ፡ ኽነ፡ ሁለትም፡ ወንደች፡ ልጆች፡ ወለደ፡ አሠ ራ፡ ስድስትም፡ ሴቶች፡ ልጆች።

፳፪፡ የአቢያም፡ የቀረው፡ ታሪኩ፡ መንገዲና፡ነገሩ ም፡በነቢዩ፡በሢደ፡መጽሐፈ፡ተጽፈዋል።

ምዕራፍ፡ ፲፬፡

፩፡ አቢያም፡ ካባቶቹ፡ ጋራ፡ አንቀላፈ፡ በደዊትም፡ ከተማ፡ ቀበረት። በርሱም፡ ፈንታ፡ አሣ፡ ልጂ፡ ነገሠ፡ በዘመኑም፡ምድር፡ አሠር፡ አመት፡ዐረፈች።

፪፡ አሣም፡ በእግዚአብሔር፡ ባምላኩ፡ፌት፡መል ካም፡ቅን፡ ነገር፡ አደረገ።

፫፡ የንግደቹንም፡ አማልክት፡ መሠውደያና፡ ኮረፌ ቶች፡ ሓምደቹንም፡ሰበረ፡ ዛፈንም፡ ቍረጠ።

፬፡ ደሁደንም፡ እግዚአብሔርን፡ ያባቶቹን፡ አም ላክ፡ ደሻ፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ ሕጉንና፡ ትእዛዙንም፡ያደር ግ፡ ዘንድ።

፭፡ ከደሁደም፡ አገር፡ ሁሉ፡ መሠውደውንና፡ የፀ ሐደቱን፡ ሓምደች፡ አራቀ፡ መንግሥቱም፡ በፌቱ፡ ጸ ጥ፡ አለች።

፮፡ በደሁደም፡ የጸኑ፡ ከተሞች፡ ሰራ፡ አገረ፡ ጸጥ፡ ብሎ፡ነበርና፡ በዚያም፡ ዘመን፡ እግዚአብሔር፡ዕረፌ ት፡ ሰለ፡ሰጠው፡ ፀብ፡ አልነበርምና።

፯፡ ደሁደንም፡ አለው። እነዚህን፡ ከተሞች፡ እን ሰራቸው፡ በቅጥርም፡እንክበባቸው፡በግምብም፡እና ጽናቸው፡ በሳንቃና፡በቀጭልፌም፡ አገረ፡ ሁሉ፡ ያባቶቻ ችነን፡ አምላክ፡ሰለ፡ፈለግነ፡ከሰልፌ፡ጸጥ፡ብለዋልና። እኛ፡ፈለግነው፡እርሱም፡በዙርያችን፡ዕረፌት፡ሰጠነ። እርሳቸውም፡ ሰረ፡ የሰረትንም፡ በሰላም፡ ፈጽሙ።

፰፡ ለአሣም፡ ጋሻና፡ ጦር፡ የሚሸከም፡ ከደሁድ፡ሶ ስት፡ መቶ፡ ሽኽ፡ ወራዊት፡ ነበር፡ ከብንያምም፡ ጋሻ፡ የሚሸከሙ፡ ፌላሳም፡ የሚወረውሩ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ከሰማንያ፡ ሽኽ፡ ነበረ፡ ሁሉም፡ አጀግ፡ ኃያላን፡ ሰዉ ች፡ ነበረ።

፱፡ ሴራህም፡የኢትዮጵያው፡ወጣሳቸው፡ በሽኽ፡ ጊዜ፡ሽኽ፡ ወራዊት፡ በሶስት፡ መቶም፡ ሣረገላ፡ወደ፡ መረሻም፡ መጣ።

፲፡ አሣም፡ ሊገናኘው፡ወጣ፡በመረሻም፡ አቅራቢ ያ፡ ባለው፡ በሰፈታ፡ ደሐ፡ ለሰልፌ፡ ተሰረ።

፲፩፡ አሣም፡ እግዚአብሔርን፡ አምላኩን፡ ጸራ፡አ ለም፡ አቤቱ፡ ሆደ፡ ኃደለኛውንና፡ ደኅማዉን፡ ለመ ርደት፡ ባንተ፡ዘንድ፡ ልዩነት፡ የለውም። አቤቱ፡ ሆደ፡ አምላካችን፡አርደነ፡ባንተ፡ ታምነናልና፡በስምኽም፡ በዚህ፡ ታላክ፡ ብዙት፡ ላደ፡ መጣነ። አቤቱ፡ ሆደ፡ አን ተ፡ ነኽ፡ አምላካችን፡ ሰውም፡ አደችልኽም።

፲፪፡ አንደሁም፡እግዚአብሔር፡ኢትዮጵደውንን፡ መታ፡በአሣና፡ በደሁደ፡ ፌትም፡ ኢትዮጵደውደን፡ ሸሹ።

፲፫፡ አሣና፡ ከርሱ፡ጋራም፡የነበረት፡ሕዝብ፡እስከ፡ ግራር፡ ድረስ፡ አሳደደቸው፡ ኢትዮጵደውንም፡ ማስ ተንፈስ፡ አስኪሳናቸው፡ ድረስ፡ ወደቁ፡በእግዚአብ

ሔርና፡በሠራዊቱ፡ፈት ፡ተሰባብርዋለና፡ከርሳቸውም፡እጅግ፡ብዙ፡ምርኮ፡ወሰደ።

፲፱፡ በግራር፡ዙርያ፡ያለውንም፡አገር፡ሁሉ፡መቱ፡ታላቅ፡ድንጋጼ፡በሁሉ፡ላይ፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ወድቀባቸው፡ነበርና ፡ከተሞቹንም ፡ሁሉ፡ዘረፉ፡እጅግ፡ብዙ፡ምርኮ፡በውሥጣቸው፡ነበርና።

፲፭፡ የከብቶቹና፡በረት፡አፈረሱ፡ከበጎችና፡ከግመሎችም፡ብዙ፡ምርኮ፡ወሰደ፡ወደ፡የሩሳሌምም፡ተመለሱ።

ምዕራፍ፡ ፲፭፡

፩፡ የእግዚአብሔርም ፡መንፈስ ፡በዓዘርያ፡በዖደድ፡ልጅ፡ላይ፡ሆነ።

፪፡ አሣንም፡ሊገናኘው ፡ወጣ ፡አለውም። አሣ፡ሆይ ፡ስማኝ። አንተም ፡ይሁዳ ፡ብንያምም ፡ሁሉ ሁ። እግዚአብሔር፡ከላንት ፡ጋራ፡ነው፡አላንተ፡ከርሱ፡ጋራ፡ሁኖ፡ኋልና። የሻችሁትም፡አጓደሆን፡ታገኙ ታላችሁ፡ብትጥሉትም፡ይጥላችኋል።

፫፡ አሥራኤልም፡ብዙ፡ዘመን፡ያለ፡አውነተኛ፡አምላክ፡ያለ ፡አስተማሪም ፡ካህን፡ያለ፡ሕግም፡ይሆራሉ።

፬፡ በመከራቸውም፡ጊዜ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ወደ፡አሥራኤል፡አምላክ፡ተመልሰው፡ይለምኑታል። እርሱም፡ይገኘላቸዋል።

፭፡ በዚያም፡ዘመን፡ለሚወጣውና፡ለሚገባው፡ሰላም፡አይሆንለትም፡ነገር፡ግን፡በምድር፡በሚኖሩት፡ሁሉ፡ላይ፡ታላቅ፡ፍርሃት፡ይሆናል።

፮፡ ወገንም፡ወገኑን፡ይወጋል፡አገርም፡አገሩን፡አግዚአብሔር፡በመከራ፡ሁሉ፡ያስጨንቃቸዋልና።

፯፡ አላንተ፡ግን፡ጽኑ፡እጆችሁም ፡አይላላ፡ለስራችሁ፡ፋደ፡ይሆናችኋልና።

፰፡ አሣም፡ይህንን፡ነገር፡የዓዘርያንና፡የነቢዩን፡የዖደድን፡ልጅ፡ትንቢት፡በሰማ፡ጊዜ፡በረታ፡ጣዖታቱንም፡አስወገደ፡ከብንያምና፡ከይሁዳ፡ምድር፡ሁሉ፡በኤፍሬምም፡ተራራ፡ከያዘው፡አገር፡ሁሉ፡የእግዚአብሔርንም፡መሠውያ፡በአግዚአብሔር፡ቤት፡ሰቀላ፡ፊት፡የነበረውን፡አደሰ።

፱፡ ይሁዳንና፡ብንያምንም፡ሁሉ፡ወደርሳቸው፡ከኤፍሬም፡ከምናሴና፡ከስምዖን፡የተሰደዱትን፡ሰበሰበ። ከእሥራኤል፡ብዙ፡ሰዎች ፡እግዚአብሔር፡አምላኩ፡ከርሱ፡ጋራ፡እንደ፡ሆነ፡ባዩ፡ጊዜ፡ወደርሱ፡ተጠግተዋልና።

፲፡ አሣም፡በነገሠ፡ባሥራ፡አምስተኛው፡አመት፡በሶስተኛው፡ጥር፡ዮኟ፡የሩሳሌም፡ተሰበሰቡ።

፲፩፡ በዚያን፡ጊዜም፡ከወሰዷት፡ምርኮ፡ሰባት፡መቶ፡በሬና፡ሰባት፡ሽኽ፡ደንግሌ፡ለእግዚአብሔር፡አቀረቡ።

፲፪፡ እግዚአብሔርንም፡ያባቶቻቸውን፡አምላክ፡ከለልባቸውና፡ከለነፍሳቸው፡ይለምኑ፡ዘንድ፡ቃል፡ኪዳን፡አደረጉ።

፲፫፡ አሉም። እግዚአብሔርን፡የአሥራኤልን፡አምላክ፡የማይለምን፡ሁሉ፡ከታላቁ፡እስከ፡ታናሹ፡ድረስ፡ከወንድ፡እስከ፡ሴት፡ድረስ፡ይሙት።

፲፬፡ ለእግዚአብሔርም፡በታላቅ፡ቃልና፡በልልታም፡በመለከትና፡በእንቢልታ፡ማሉ።

፲፭፡ በይሁዳም፡የነበረት፡ሁሉ፡ዘመሐላው፡ደስ፡አላቸው፡ከለልባቸው፡ምለዋልና፡በፈጹምም፡ሕሊናቸው፡ሸተውታልና፡አገኙትም፡እግዚአብሔርም፡በዙርያቸው፡ዕረፍት፡ሰጣቸው።

፲፮፡ ደግሞም፡አሣ፡ንጉሡ፡መየኽን፡እናቱን፡የጣዖት፡ምሳሌ፡ስላደረገች፡ከወደዘርኒትዋ፡አዋረደት። አሣም፡ምሳሌውን፡ፈጨው፡አደቀቀውም፡በቄድሮንም፡ወንዝ፡አጠጉብ፡አቃጠለው።

፲፯፡ ነገር፡ግን፡በኮረፍታው፡ላይ፡የነበረው፡መሠውያ፡ከእሥራኤል፡አልፈቀም፡ደረ፡ግን፡የአሣ፡ልብ፡በዘመኑ፡ሁሉ፡ፈጹም፡ነበረ።

፲፰፡ አርሱ፡የተሳለውንና፡አባቱ፡የተሳለውንም፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ቤት፡አመጣ፡ወርቁንና፡ብረን፡ልዩ፡ልዩውንም፡አቃ።

፲፱፡ በአሣም፡መንግሥት፡አስከ፡ሠላሳ፡አምስተኛው፡አመት፡ድረስ፡ፀብ፡አልሆነም።

ምዕራፍ፡ ፲፮፡

፩፡ በአሣም፡መንግሥት፡በሠላሳ፡ስድስተኛው፡አመት፡ባሢሣ፡የእሥራኤልን፡ንጉሥ፡ወደ፡ይሁዳ፡ወጣ፡ራማትንም፡በቅኖር፡ከበበ፡ማናቸው፡ወደ፡አሣ፡ወደ፡ይሁዳ፡ንጉሥ፡መግባት፡መውጣት፡እንዳይችል።

፪፡ አሣም፡ከእግዚአብሔር፡ቤት፡አቃ፡ቤትና፡ከንጉሡ፡ቤት፡ወርቅና፡ብር፡አወጣ፡በደማስቀም፡ወደ፡ተቀመጠው፡ወደ፡ሶርያ፡ንጉሥ፡ወደ፡ቤንሐደድ፡እንደሀ፡ሲል፡ሰደደ።

፫፡ በኔና፡ባንተ፡ባባቴና፡ባባትኽ፡መኻከልም፡ቃል፡ኪደን፡አለ። እነሆ፡ብርና፡ወርቅ፡ሰደድሁልኽ፡ባንተና፡በባኢሣ፡በእሥራኤል፡ንጉሥ፡ያለውን፡ቃል፡ኪደን፡ከኔ፡ይርቅ፡ዘንድ፡እንድታፈርስ።

፬፡ ቤንሐደድም፡ለንጉሡ፡ለአሣ፡አሺ፡ብሎ፡በእሥራኤል፡ከተሞች፡ላይ፡የሠራዊቱን፡አለቆች፡ሰደደ፡ኢዮንንም፡መቱ፡ደንንም፡አቤልማይምን፡ሰንቅ፡የነበረባቸውንም፡የንፋታሌምን፡ከተሞች፡ሁሉ።

፭፡ ባኢሣም፡ያነን፡በሰማ፡ጊዜ፡ራማትን፡መስራት፡ተወ፡ከስራውም፡ተጊጉሉ።

፮፡ ንጉሡም፡አሣ፡ይሁዳን፡ሁሉ፡ወሰደ፡ባኢሣም፡ራማትን፡ደሰራበት፡የነበረውን፡እንጨቱና፡ደንጊያ፡አነሣ፡ጌበዓንና፡ሚጽፋንም፡አጸናባት።

፯፡ በዚያም፡ዘመን፡ነቢዩ፡ሃናኒ፡ወደ፡ይሁዳ፡ንጉሥ፡ወደ፡አሣ፡መጣ፡አለውም። በሶርያ፡ንጉሥ፡ታምነኻልና፡በእግዚአብሔርም፡ባመላክኽ፡አልታ

መንኽምና፡ ዮሶርያ፡ ኄንሥ፡ ጭፈራ፡ ከጅኽ፡ አመ ለጠ።

፲፰ ኢትዮጵያውያንና፡ ሊቢያውያን፡ ደልቅ፡ በፈ ረሰና፡ በሠረገላ፡ ቍጥራቸው፡ የበዛ፡ አልነበረምን፡ በ እግዚአብሔር፡ ግን፡ ስለ፡ ታመንህ፡ በጅኽ፡ ጣላ ቸው።

፲፱ ልቡ፡ ወደርሱ፡ ፈጹም፡ የሆነውን፡ ሁሉ፡ ያጸና፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር፡ ዓይኖች፡ በምድሪ፡ ሁሉ፡ ይ ዞራሉና። አሁንም፡ በስንፍና፡ አደረግኽ፡ ስለዚህ ም፡ ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ ሰልፍ፡ ይነሣብኻል።

፲፱ አሣም፡ በተመልካቹ፡ ላይ፡ ተቈጥቶ፡ በግንድ፡ አሠረው፡ ስለዚኽ፡ እጅግ፡ ተጐዋጥቶ፡ ነበርና፡ በዚያ፡ ወራትም፡ ከሕዝቡ፡ አያሌ፡ ሰዎች፡ አሰጨነቀ።

፲፩ የአሣም፡ ስራ፡ የፈተኖቹ፡ የኋለኞቹ፡ እነሆ፡ በይሁዳና፡ በእሥራኤል፡ ነገሥታት፡ መጽሐፍ፡ ተጽፈዋል።

፲፪ አሣም፡ በነገሠ፡ በሠላሳ፡ ዘጠነኛው፡ አመት፡ እግሩን፡ በጽኑ፡ ደዌ፡ ታመመ፡ በታመመም፡ ጊዜ፡ ደ ግሞ፡ እግዚአብሔርን፡ አልፈለገም፡ ነገር፡ ግን፡ በባለ፡ መድኃኒቶች፡ ታመነ።

፲፫ አሣም፡ ካባቶቹ፡ ጋራ፡ አንቀላፈ፡ በነገሠም፡ ባርባ፡ አንደኛው፡ አመት፡ ሞተ።

፲፬ ለርሱም፡ በቍፈረው፡ መቃብር፡ በደዊት፡ ከ ተማ፡ ቀበሩት፡ ልዩ፡ ለዩ፡ መልካም፡ ሽቱ፡ በተቀባ፡ አ ልጋ፡ ላይም፡ አኖሩት፡ እጅግ፡ ታላቅ፡ ማቃጠልም፡ አ ቃጠሉለት።

ምዕራፍ፡ ፲፯፡

፩ ዮሣፈጥም፡ ልጁ፡ በርሱ፡ ፈንታ፡ ነገሠ፡ በእሥ ራኤልም፡ ላይ፡ በረታ።

፪ በቅጽሮም፡ በተከበቡት፡ በይሁዳ፡ ከተሞች፡ሁ ሉ፡ ወታደር፡ አኖረባቸው፡ በይሁዳ፡ ምድርና፡ አባቱ ም፡ አሣ፡ በወሰደቸው፡ በኤፍሬም፡ ከተሞችም፡ጠ ባቂች፡ አስቀመጠ።

፫ እግዚአብሔርም፡ ከዮሣፈጥ፡ ጋራ፡ ነበረ፡ በፊ ተኛዪቱ፡ ባባቱ፡ በደዊት፡ መንገድ፡ ሒድዋልና፡ በዓ ሊምንም፡ አልፈለገምና።

፬ ነገር፡ ግን፡ ባባቱ፡ አምላክ፡ ታመነ፡ በትእዛዙ ም፡ ሔደ፡ እንጂ፡ እሥራኤል፡ ስራም፡ አልሰራም።

፭ እግዚአብሔርም፡ መንግሥትን፡ በጂ፡ አጸና፡ ይሁዳም፡ ሁሉ፡ እጅ፡ መንሻ፡ ለዮሣፈጥ፡ ሰጠ፡ እጅ ግ፡ ብዙ፡ ባለጠግነትና፡ ክብርም፡ ሆነለት።

፮ ልቡም፡በእግዚአብሔር፡ መንገድ፡ ጸና፡ ደግሞ ም፡ኮረፈታውንና፡አፀደን፡ከይሁዳ፡አስወግደ።

፯ በነገሠም፡ በሶስተኛው፡ አመት፡ ካለቀቹ፡ብን ሐደልን፡ ሶበድያን፡ዘካርያስን፡ናትናኤልን፡ሚካ ያንም፡በይሁዳ፡ምድር፡ያስተምሩ፡ዘንድ፡ሰደደ።

፰ ከርሳቸውም፡ ጋራ፡ሌዋውያንን፡ሸማዕያንና፡ነ ታንያን፡ ዘበድያንና፡ ዓሣሄልን፡ሸሚራሞትንና፡ይሆ ናታንን፡ አዶኒያንና፡ ጦቢያን፡ ጦብአዶኒያንን፡ ከርሳ ቸውም፡ጋራ፡ሁለቱን፡ካህናት፡ኤሊሻማና፡ይሆራም ን፡ሰደደ።

፱ በይሁዳም፡ ያስተምሩ፡ ነበር፡ የእግዚአብሔር ንም፡ የሕጉን፡መጽሐፍ፡ ይዘው፡ ሔዱ፡ በይሁዳም፡ ከተሞች፡ሁሉ፡ዞረ፡ሕዝቡንም፡ያስተምሩ፡ነበር።

፲ በይሁዳም፡ ዙርያ፡ በነበሩት፡ መንግሥታት፡ ሁ ሉ፡የእግዚአብሔር፡ፍርሃት፡ነበረ፡ዮሣፈጥንም፡አል ተዋጉትም።

፲፩ ደግሞም፡ ፈልስጥኤማውያን፡ለዮሣፈጥ፡እ ጅ፡መንሻ፡ያመጡለት፡ነበሩ፡አንድ፡ጭነትም፡የብር፡ ግብር። ዓረቦችም፡ ከመንጎቻቸው፡ ሺ፯ መቶ፡እንደሁም፡ከፍ የሉ፡ሰባት፡ሺ፯ ከሰባት፡መቶ፡አውራፈየሎች።

፲፪ ዮሣፈጥም፡ ኢየበረታ፡ ሔደ፡ ፈጽሞም፡ታላ ቅ፡ሆነ፡በይሁዳም፡የግመብ፡ቤቶችና፡የእህል፡መሰብ ሰቢዮች፡ከተሞች፡ሰራ።

፲፫ በይሁዳም፡ አገር፡ እጅግ፡ ሰንቅ፡ አዘጋጀ፡የሚ ዋጉ፡ሰዎችና፡ጨካኞችም፡በዖሳሌም፡ነበረ።

፲፬ ቍጥራቸውም፡ ይህ፡ ነው፡ እንደባቶቻቸው፡ ቤት። የሻለቆቹ፡በይሁዳ፡ዓድና፡መስፍን፡ከርሱም፡ ጋራ፡ሶስት፡መቶ፡ሺ፯ ጨካኞች፡ሰዎች።

፲፭ ከርሱም፡ በኋላ፡ ዮሐናን፡ አለቃ፡ከርሱም፡ጋ ራ፡ሁለት፡መቶ፡ሰማንያ፡ሺ፯

፲፮ ደግሞም፡ ከዚኽ፡በኋላ፡ዓማሰያ፡የዚክሪ፡ል ጅ፡በፈቃዱ፡ሰውነቱን፡ለእግዚአብሔር፡የቀደሰው፡ ከርሱም፡ጋራ፡ሁለት፡መቶ፡ሺ፯ ኃያላን፡ሰዎች።

፲፯ ከብንያምም፡ኤልያዳ፡አጅግ፡ ጨካኝ፡ ሰው፡ ከርሱም፡ ጋራ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ሺ፯ ሰዎች፡ ቀስተኖ፡ጋ ሻ፡የሚይዙ።

፲፰ ከርሱም፡ በኋላ፡ ዮዛባድ፡ ከርሱም፡ጋራ፡ሁለ ት፡መቶ፡ሰማንያ፡ሺ፯ ለሰልፍ፡የተዘጋጁ።

፲፱ አሌኽም፡ ለንጉሡ፡ያገለግሉ፡ነበረ፡ ከለዚያ፡ በይሁዳ፡ሁሉ፡ከተሞች፡በቅጽር፡በመሸጉት፡ኅያሬዎ ው፡ሌላ።

ምዕራፍ፡ ፲፰፡

፩ ዮሣፈጥም፡ ባለ፡ ጠጋ፡ነበረ፡አጅግም፡የከበረ። ለአሐብም፡አማች፡ሆነ።

፪ ከጥቂት፡ዘመንም፡ በኋላ፡ ወደ፡አሐብ፡ወደ፡ሰ ማርያ፡ ወረደ፡ አሐብም፡ብዙ፡ደንግሎችን፡ብዙ፡በሮ ች፡ አረደለት፡ ከርሱ፡ ጋራም፡ለነበረ፡ሕዝብ፡ከርሱ ም፡ጋራ፡ ወደ፡ ራሞት፡ ጊልዓድ፡ ይወጣ፡ዘንድ፡ አባበ ለው።

፫ አሐብም፡ የእሥራኤል፡ ንጉሥ፡ዮሣፈጥን፡ የ ይሁዳን፡ንጉሥ፡ አለው። ከኔ፡ጋራ፡ ወደ፡ ራሞት፡ ጊል ዓድ፡ ትወጣለኽን። መለሰለትም፡ አለውም። እኔ፡ እንደኀተ፡ነኝ፡ ሕዝቤም፡ እንደ፡ ሕዝብኽ፡ነው፡ እኔ ም፡ካንተ፡ጋራ፡ወደ፡ሰልፍ፡እወጣለሁ።

፱፡ ዮሣፈጥም፡ የእሥራኤልን፡ ንጉሥ፡ አለው።
እስከ፡ዛሬ፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ጠይቅ።
፳ የእሥራኤልም፡ ንጉሥ፡ ከነቢያት፡ አራት፡ መ
ቶ፡ሰዉቅ፡ ሰበሰበ፡ አላቸውም። ሬሞት፡ ጊልዓድን፡
ለመውጋት፡ እንሔድ፡ ዘንድ፡ ይሆንልናልን፡ወይስ፡ል
ቅር። እርሳቸውም፡ ውጣ፡ እግዚአብሔርም፡ በንጉ
ሡ፡እጅ፡ይጥላታል፡አሉት።
፮ ዮሣፈጥም፡ አለ። ያሳመሳ፡ የእግዚአብሔር፡
ነቢይ፡አንጠይቀው፡ዘንድ፡ከዚህ፡አይገኝምን።
፯ የእሥራኤልም፡ ንጉሥ፡ ዮሣፈጥን፡ አለው።
ከዚኝ፡አንድ፡ሰው፡አለ፡በርሱም፡እግዚአብሔርን፡
እንጠይቅ፡ ዘንድ፡ ይቻለናል፡ነገር፡ግን፡አጸላዋለሁ፡በ
ዘመኑ። ሁሉ፡ከክፈ፡በቀር፡መልካም፡አይገርልኝም
ን፡ አርሱም፡ ሚክያ፡ የዬምላ፡ ልጅ፡ ነው። ዮሣፈጥ
ም፡አለ፡ንጉሡ፡እንደህ፡አይበል።
፰ የእሥራኤልም፡ ንጉሥ፡ ከባለሙዋሎች፡ አን
ዷንጻራ፡ አለውም። ሚክያን፡የዬምላን፡ልጅ፡ፈጥ
ነኝ፡ድራው።
፱ የእሥራኤል፡ ንጉሠን፡ ዮሣፈጥ፡ የይሁኗ፡ንጉ
ሡ፡ግን፡ሁለቱ፡ የመንግሡት፡ ልብስ፡ ለብሰው፡ በየዙ
ፋናቸው፡ ላይ፡ ሁነው፡ ባይባባይ፡በሰማርያ፡ደጅ፡አጠ
ገብ፡ ተቀምጠው፡ ነበረ። ነቢያቱም፡ ሁሉ፡ በፊታቸ
ው፡ትንቢት፡ይናገሩ፡ነበረ።
፲ ጼድቅያስም፡ የከነዓና፡ ልጅ፡ የብረት፡ቀንድ፡አ
ደረገ፡አለም። እግዚአብሔር፡ የሚለው፡ ይህ፡ነው።
በዚኝ፡ሶርያን፡ እስክታጠፋቸው፡ ድረስ፡ ትወጋቸዋ
ለህ።
፲፩ እንደሁሙ፡ ነቢያት፡ ሁሉ፡ ደናግሩ፡ነበረ፡ወደ፡
ሬሞት፡ጊልዓድ፡ ውጣ፡ደቀኖ ካልም፡ ኢያሉ፡ እግዚ
አብሔርም፡በንጉሡ፡እጅ፡ይጥላታል።
፲፪ ሚክያን፡ደጻራ፡ዘንድ፡የሔደው፡መልክተኛ፡
ግን፡አለው። የነቢያት፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ባንድ፡ አፏ፡ ለንጉ
ሡ፡ መልካም፡ ደናገሩል፡ አሁንም፡አለመንኝለሁ፡ነ
ገርኝ፡ አንደ፡ ነገራቸው፡ ይሁን፡የሚያምረውንም፡ነ
ገር፡ተናገር።
፲፫ ሚክያም፡ አለው። ሕያው፡ እግዚአብሔር
ን፡አምላኬ፡የነገረኝን፡እንድናገር።
፲፬ ወደ፡ንጉሡም፡መጣ፡ንጉሡም፡አለው። ሚ
ክያ፡ሆይ፡ሬሞት፡ጊልዓድን፡ለመውጋት፡እንሔድ፡ዘ
ንድ፡ ይሆናልን፡ ወይስ፡ ልቅር። እርሱም፡ አለ። ው
ጡ፡ይቀናቸኋልም፡በጀችሁም፡ይጣላሉ።
፲፭ ንጉሡም፡አለው። ከውነት፡ ሌላ፡እንደትነግ
ረኝ፡ ስንት፡ ጊዜ፡ በእግዚአብሔር፡ ስም፡ አምልኝ
ለሁ።
፲፮ አለውም። እኔ፡አየሁ፡እሥራኤል፡ሁሉ፡ጠባ
ቂ፡እንደሌለው፡ በግ፡ በተራራ፡ ተበትኖ። እግዚአብ
ሔርም፡ አለ። ለኣዚኝ፡ ዔታ፡ የላቸውም፡ ሁሉም፡
ኢየቤቱ፡በደኅና፡ይመለስ።
፲፯ የእሥራኤልም፡ ንጉሥ፡ዮሣፈጥን፡ አለው።
አላልሁኽምን፡ ከክፈ፡በቀር፡ ደህ፡መልካም፡እንደ
ይገርልኝ።
፲፰ እርሱም፡ደግሞ፡ አለ። የእግዚአብሔርን፡ነ
ገር፡ ሰሙ፡ እኔ፡ እግዚአብሔርን፡ በዙፋኑ፡ላይ፡ ተቀ
ምጦ፡አየሁ፡የሰማይም፡ሠራዊት፡ ሁሉ፡ በቀኙና፡ በ
ግራው፡ቁመው።
፲፱ እግዚአብሔርም፡አለ። አሔብን፡የእሥራኤ
ልን፡ንጉሥ፡ ማን፡ ያስተዋል፡ እንደ፡ወጣ፡ ወደ፡ ሬሞ
ት፡ ጊልዓድም፡ ሒደ፡ አደጋ፡ እንደ፡ኖል። ከርሳቸው
ም፡እንደ፡እንደህ፡መለሰ፡ሌላውም፡እንደ፡ያ።
፳ መንፈስም፡ወጣ፡በእግዚአብሔርም፡ፊት፡ቀ
መ፡አለም። እኔ፡አስተዋለሁ። እግዚአብሔርም፡አ
ለው፡በምን።
፳፩ አለውም። እወጣለሁ፡በነቢያቱም፡ሁሉ፡አ
ፏ፡አሰተኛ፡መንፈስ፡አሆናለሁ። እግዚአብሔርም፡
አለው፡ አንተ፡ታስተዋላኝ፡ትበረታበትማለኝ፡ው
ጣና፡እንደህ፡አድርግ።
፳፪ አሁንም፡ እነሆ፡እግዚአብሔር፡በለዚኝ፡በነ
ቢያተኝ፡ሁሉ፡አፏ፡ያሰት፡ መንፈስ፡ ሰጠ፡እግዚአብ
ሔርም፡ባንተ፡ላይ፡ክፈ፡ተናግሮብኻል።
፳፫ ጼድቅያስም፡የከነዓና፡ልጅ፡ ቀረበ፡ ሚክያን
ም፡ ፊቱን፡ ጸፈው፡ አለውም። የእግዚአብሔር፡ መ
ንፈስ፡ በወደት፡ መንነጂ፡ ከኔ፡ አልፏ፡ ላንተ፡ ተናነ
ረኝ።
፳፬ ሚክያም፡አለው። እነሆ፡በዚያ፡ቀን፡ልትሸ
ሸግ፡ከማጀት፡ወደ፡ማጀት፡በገባኝ፡ጊዜ፡ታያለኝ።
፳፭፡የእሥራኤልም፡ንጉሡ፡እንደህ፡ሲል፡አዘዘ።
ሚክያን፡አንሡት፡ ወደ፡ ክተማውም፡ አለቀ፡ ወደ፡
አሞን፡ውሰጂት፡ወደ፡ ዮአስም፡ወደ፡ ንጉሡ፡ ልጅ።
፳፮ በልዋቸውም፡ ንጉሡ፡ የሚለው፡ ይህ፡ነው፡
ደህን፡ በግዞት፡ አኑረት፡በደኅናም፡አስክመለስ፡ድረ
ስ፡ የመከራ፡ እንጅራ፡ መግቡት፡የመከራም፡ውኃ፡አ
ጠጡት።
፳፯ ሚክያም፡አለ። አንተ፡ በደኅና፡ብትመለስ፡
እግዚአብሔር፡ በኔ፡ አልተናገረም። አለም፡ አለንተ፡
ሕዝብ፡ሁላቸሁ፡ስሙ።
፳፰ የእሥራኤል፡ ንጉሥና፡ ዮሣፈጥም፡ የይሁ
ኗ፡ንጉሥ፡ወደ፡ሬሞት፡ጊልዓድ፡ወጡ።
፳፱ የእሥራኤልም፡ ንጉሥ፡ዮሣፈጥን፡አለው።
እኔ፡ልብሴን፡አለውጣለሁ፡እንደሁም፡ ወደ፡ ሰልፏ፡
አሔደለሁ፡ አንተ፡ ግን፡ ልብሰ ኽን፡ ልበስ። የእሥራ
ኤልም፡ ንጉሥ፡ ልብሱን፡ለወጠ፡ወደ፡ሰልፏም፡ገቡ።
፴ የሶርያ፡ንጉሥ፡ግን፡ የሠረገሎቹን፡ አለቆች፡አ
ንደህ፡ሲል፡አዘዘ። ከእሥራኤል፡ ንጉሥ፡ በቀር፡ ታላ
ቅ፡ሆነ፡ታናሽ፡ሆነ፡አትውጉ።
፴፩ እንደሁም፡ የሠረገሎቹ፡ አለቀች፡ ዮሣፈጥ
ን፡ባዩ፡ጊዜ፡ደህ፡የእሥራኤል፡ንጉሥ፡ነው፡ብለው፡ሊ
ወጉት፡ከበቡት። ዮሣፈጥም፡ ጮኸ፡ እግዚአብሔር
ም፡ረደው፡ከርሱም፡መለሳቸው።

፴፪፡ የሠረገላቱም፡ አለቆች፡ የእሥራኤል፡ ንጉሥ፡እንደልሆነ፡ባዞ፡ጊዜ፡ከርሱ፡ተመለሱ።

፴፫፡ አንድ፡ሰውም፡በየዋህነቱ፡ፈላፃ፡ወረወረ፡የ እሥራኤልንም፡ ንጉሥ፡ በልብደ፡ መጋጠሚያ፡ ወጋ ው። የሠረገላውንም፡ መሪ፡ ተወግቻለሁና፡ እጅኽ ን፡መልሰህ፡ከሰልፍ፡አውጣኝ፡አለው።

፴፬፡ የዚያም፡ ቀን፡ ሰልፍ፡ አጥብቀ፡ ጽኑ፡ ነበር፡የ እሥራኤልም፡ ንጉሥ፡ እስከ፡ ማታ፡ድረስ፡በሶርያ፡ሰ ዎች፡ትደዩ፡ፀሐይም፡በገባች፡ጊዜ፡ሞተ።

ምዕራፍ፡ ፲፱፡

፩፡ ዮሣፈጥም፡ የይሁዳ፡ንጉሥ፡ወደ፡ቤቱ፡ወደ፡የ ሩሳሌም፡በሰላና፡ተመለሰ።

፪፡ ተመልካቹም፡ዬሑ፡ የሐናኒ፡ልጅ፡ ሊገናኘው፡ ወጣ፡አለውም። አንተ፡ለከሐደውን፡ታግዛለኽ፡አ ግዚአብሔርንም፡ የሚጸሉትን፡ ትወዳለኽ። ስለ ዚህም፡ ቍጣ፡ ባንተ፡ ላይ፡ ነው፡ ከእግዚአብሔር፡ ፊት።

፫፡ ነገር፡ግን፡መልካም፡ነገር፡ ተገኝብኽ፡ ከይሁዳ፡ ምድር፡ጣዖታትን፡አርቀኽልና፡ እግዚአብሔርንም፡ ትለምን፡ዘንድ፡ልብኽን፡አዘጋጅተኻልና።

፬፡ ዮሣፈጥም፡ በየሩሳሌም፡ ተቀመጠ። ደግሞ ም፡ወደ፡ሕዝብ፡ወጣ፡ከቤርሰባ፡ጀምሮ፡አስከ፡ኤፍ ሬም፡ ተራራ፡ ድረስ፡ ወደባላቸቹዋቸውም፡ አመላክ፡ ወ ደ፡እግዚአብሔር፡መለሳቸው።

፭፡ በም፡ድርም፡ ፈራጀች፡ አኖረ፡ በተመሸጉት፡በደ ሁዳ፡ከተሞች፡በኢያንደንደ፡ከተማ።

፮፡ ፈራጀቹንም፡ እንደህ፡ሲል፡አዘዘ። የምታደር ጉትን፡ተመልከቱ፡ለሰው፡ አትፈርዷምና፡ ለእግዚአ ብሔር፡ እንጅ፡ አርሱም፡ በፈርድ፡ ነገር፡ከላንተ፡ጋራ፡ ነው።

፯፡ አሁንም፡ የእግዚአብሔር፡ ፍርሃት፡ከላንተ፡ጋ ራ፡ደሁን፡ሁሉንም፡ተጠንቅቅቅሁ፡ አድርጉ። ባምላ ካችን፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡በደልና፡ ለሰው፡ ፊት፡ ማድላትና፡መመሳሰጀ፡መውሰድ፡የለምና።

ስ። እነሆ፡ ይጸልያልና። *ም፡ ፷፭፡ ፴፱፡፡

፲፪ በራእይም፡ አንድ፡ ሰው፡ አየ፡ ስሙን ፡ ሐናን
ያ፡የሚሉት፡ ሲገባ፡እጁንም፡በላዩ፡ ሲጭንበት፡ያደ፡
ዘንድ።

፲፫ ሐናንያም፡መለሰ፡ አለም። አቤቱ፡ ከብዙ፡ ሰ
ዎች፡የዚህን፡ሰው፡ነገር፡ፈጽሟ፡ ሰማሁ፡ስንት፡ክፈ፡
እንደደረገ፡ በቅዲሳንህ፡ በየሩሳሌም።

፲፬ ከዚህም፡ ከካህናት፡ አለቀች፡ ሥልጣን፡ አለ
ው፡ ስምህን፡ የሚጸሩን፡ ሁሉ፡ ያሥር፡ዘንድ።

፭ ቀሮ፡ ፭፡ ፪፡፡

፲፭ ጌታም፡ አለው። ሒድ፡ደህ፡ ለኔ፡ የተመረጠ፡
እቃ፡ነውና፡ ስሜን፡ደሽከም፡ዘንድ፡በአሕዛብ፡ፊት፡
*በነገሥታትም፡ በእሥራኤል፡ ልጀችም።

*ም፡ ፷፭፡ ፲፫፡፡ ሮሚ፡ ፭፡ ፭፡፡

፲፮ እኔም፡ስለ፡ስሜ፡ የሚቀበለውን፡ መከራ፡ አ
ስታውቀዋለሁ። ቍ፡ ፷፫፡፡ ፪፡ ቀሮ፡ ፲፭፡ ፷፫፡፡

፲፯ ሐናንያም፡ሔደ፡ወደ፡ቤትም፡ገባ፡እጁንም፡
ጫነበት፡ አለም። ወንድሜ፡ ሆይ፡ ሳውል። ጌታ፡ ወደ
ንተ፡ላከኝ።የሱስ፡በመንገድ፡የታየ'ኸው፡ ስትመጣ።
ታደ፡ዘንድ፡ መንፈስ፡ ቅዲስም፡ ደመላብህ፡ ዘንድ።

፲፰ የዚያን፡ ጊዜም፡ ካይኑ፡ ወደቀ፡ እንደ፡ ቅርፍ
ት፡ ያለ። አየም፡ ተነሠተም ፡ ተጠመቀ።

፲፱ መብልም፡ በተቀበለ፡ ጊዜ፡በረታ። ሳውልም፡
በደማስቀ፡ካሉ፡ከደቀ፡መዛሙርት፡ጋራ፡ባንድ፡ ሆነ፡
ጥቂት፡ ቀን።

፳ የዚያን፡ ጊዜውም፡ በክርስቶስ፡ አስተማረ፡በ
መስኪደች፡አርሱ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ እንደ፡ ሆነ።

፳፩ የሰሙትም፡ሁሉ፡ተደነቁ፡አሉም።ይህ፡በየ
ሩሳሌም፡ይህንን፡ስም፡የሚጸረጉን፡ ሁሉ፡ ያጠፋ፡አደ
ደለምን። ስለዚህም፡ ወደዚህ፡ ሰጣ፡አሥሮ፡ ወደ፡
ካህናት፡ አለቀች፡ ሊወስደቸው። *ቍ፡ ፭፡ ፲፱፡፡

ም፡ ፷፡ ፭፡፡ ፷፯፤ ፲፡፡

፳፪፡፡ ሳውልም ፡ ኃይል ፡ ይጨመርለት ፡ ነበረ፡ በደ
ማስቀ፡ የተቀመጡትንም፡ አደሁድ፡ ያውክ፡ ነበረ።
ደህ፡ ክርስቶስ፡ አንደ፡ ሆነ፡ ሲገልጠላቸው።

ም፡ ፲፰፡ ፷፰፡፡

፳፫፡ ብዙ፡ ቀንም፡ ከሆነ፡ በኋላ፡ አደሁድ ፡ አንድ፡
ሁነው፡ ተማከሩ፡ ደገሉት፡ ዘንድ።

፳፬፤ ሳውልም፡ አንደ፡ተማከሩበት፡ አወቀ። ደጀ
ትንም፡ ደጠብቁ፡ ነበሩ፡ በሌት፡ በቀንም፡ ደገሉት፡ ዘ
ንድ።

፳፭፡ ደቀ፡መዛሙርት፡ግን፡ በሌት፡ ወሰዷት፡ በቅ
ጥርም፡ ላደ፡ በንቅብ፡ አወረዷት።

፪ ቀሮ፡ ፲፩፡ ፴፱፤ ፴፫፡፡

፳፮ ሳውልም፡ ወደ፡ የሩሳሌም፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ከ
ደቀ፡ መዛሙርት፡ ጋራ፡ ባንድ፡ ደሆን፡ ዘንድ፡ ወደደ።
ሁሉም፡ ፈሩት፡ ባደማኑት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር፡ አንደ፡
ሆነ። ገላት፡ ፩፡ ፲፯፡፡

፳፯ በርናባስ፡ግን፡ ወሰደው፡ወደ፡ ሐዋርያትም፡
አገባው፡ አጨወታቸውም፡ ጌታን፡ በመንገድ ፡ እንደ
የው፡እንደ፡ ተናገረውም። በደማስቀም፡ አንደ፡ ተጋ
ደለ፡ በየሱስ፡ ስም። ቍ፡ ፮፡፡

፳፰ ከርሳቸውም፡ጋራ፡ ተቀመጠ፡ ሲገባ፡ ሲወጣ
ም ፡ በየሩሳሌም፡ በየሱስም፡ በጌታ፡ ስም፡ ሲጋደል።

፳፱ ለአይሁድም፡ ደናገር፡ነበረ፡ ከፅርዕ፡ አገር፡ ለ
ሚሆኑ፡ደከራከራቸውም፡ነበር። አርሳቸው፡ ግን፡ሊ
ገሉት፡ ወደደ።

፴ ወንድሞችም፡ደህንን፡ባወቁ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቂሣ
ርያ፡ ወሰዷት፡ ወደ፡ *ጠርሴስም፡ ሰደደቷት።

*ም፡ ፲፩፡ ፷፭፡፡

፴፩ ቤተ፡ክርስቲያኒቱ፡ሁሉ፡ግን፡ በይሁዲ፡ የነበረ

ችው፡በገሊላም፡ በሰማርያም፡ በደሀና፡ ነበረች። ተሰ
ርታ፡በእግዚአብሔር፡ፈርሃትም፡ጸንታ። በምንፈሰ፡
ቅዱሰም፡ጸጋ፡በዙ።

፴፱፡ ጴጥሮሰም፡ በዮስፎራው፡ ሲዞር፡ በሊደ፡ ወደ
ሚኖሩ፡ ቅዱሳን፡ ወረደ።

፵፡ ከዚያም፡አንድ፡ ሰው፡ ሰሙን፡ ኤንያ፡ የሚ
ሉት፡ አገኘ። ባልጋ፡ ላደ፡ ወድቀ፡ ከሰሞንት፡ አመት፡
ጀምሮ፡ መፀጉዕም፡ ነበረ።

፵፩፡ ጴጥሮሰም፡አለው። ኤንያ፡ ሆይ፡ የሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ይፈውስህ።ተነሣ፣ለራስህም፡አንጽፏ። የዚያ
ን፡ ጊዜውም፡ ተነሣ።

፵፪፡ በሊደም፡ የሚኖሩ፡ ሁሉ፡ በሰሮናም፡ አዩት፡
ወደ፡ እግዚአብሔርም፡ ተመለሱ።

፵፫፡ በኢዮጴም፡አንድ፡ት፡ረድ፡ነበረች፡ሰምዋን፡
ጣቢታ፡ የሚልዋት ። ሰምዋም፡ ደተረጉማል ፡ ምሀ
ቋ፡ተብሎ።ይህቺም፡ መልካም፡ ነገር፡ መልተባት፡ነበ
ር፡*ምጽዋትም፡ታደርግ፡ነበረች። *ዘዳ፡ ፲፭፡ ፩፡፡

፵፬፡ በዚያቺም፡ ወራት፡ ታመመች ፡ ሞተችም።
አፀብዋትም፡ በደርብ፡ ላይም፡ አደረጊት።

፵፭፡ ሊደም፡ ለኢዮጴ፡ ቅርብ፡ ናትና፡ ደቀ፡ መዛ
ሙርት፡ ጴጥሮስ፡ ከዚያ፡ እንደ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ሁለ
ት፡ሰዎች፡ወደርሱ፡ ላኩ፡ ደለምኑት፡ ዘንድ፡ እምቢ፡
እንደደል፡ ወደርሳቸው፡ ከመምጣት።

፵፩፡ ጴጥሮስም ፡ ተነሣ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ መ
ጣ። ወደርሳቸውም፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ደርብ፡ አወ
ጡት። በፊቱም፡ቀሙ፡ ባልቴቶት፡ ሁሉ፡ ኢያለቀሱ፡
ቀሚሶችንም፡ልብሶችንም፡ ኢያሳዩት፡ ምደቋ፡ ታደ
ርገው፡የነበረችውን፡ ከርሳቸው፡ ጋራ። ሳለች።

፵፡ ጴጥሮስም፡ሁሉን፡ወደ፡ሜደ፡አወጣ፡ በተንበ
ረከከም፡ ጊዜ፡ ጸለየ፡ ወደ፡ በድንም፡ ተመለስ ፡ አለ
ም። ጣቢታ፡ ሆይ፡*ተነሺ። አርስዋም፡ ዓይንዋን፡ገለ
ጠች፡ጴጥሮስንም፡ባየች፡ ጊዜ፡ ተቀመጠች።

*ማር፡ ፭፡ ፴፭፡፡ ሉቃ፡ ፯፡ ፲፱፡፡

፵፩፡ እጅንም፡ሰጣት፡አስነሣትም፡ቅዱሳንንም፡
ባልቴቶችንም፡ ጸራ፡ ደሀየም፡ ሁና፡ በፊታቸው፡ አቀ
ማት።

፵፪፡ ደህም፡ ወረ፡ የታወቀ፡ ሆነ፡ በኢዮጴ፡ ሁሉ።
*ብዙም፡ ሰዎች፡ በጌታ፡ አመኑ።

*ዮሐ፡ ፲፡ ፴፡፡ ፲፡ ፵፪፡፡

፵፫፡ አያሌ፡ቀንም፡በኢዮጴ፡ተቀመጠ፡ወደንድ፡
ሰው፡ ሰምዖን፡የሚባል፡ቀርበት፡ ፈቂ። ም፡ ፲፡ ፮፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፡

፩፡ በቂሣርያም፡ አንድ፡ሰው፡ነበረ፡ ስሙን፡ ቀርኔ
ሌዎስ፡ የሚሉት፡ *የመተ፡ አለቃ፡ ለጭፈራ፡ ኢጣሊ
ቂ፡ለሚልዋት። *ማቴ፡ ፳፡ ፭፡፡

፪፡ መልካም፡ የሚሰራ፡እግዚአብሔርንም፡የሚ
ፈራ፡ ከቤቱ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ጋራ።እጅግም፡ ምጽዋት፡

*ለሕዝብ፡ያደረገ፡ ወደ፡ እግዚአብሔርም፡ሁልግዜ፡
የለመነ። *ዲን፡ ፬፡ ፴፬፡፡

፫፡ እርሱም፡በግልጥ፡ በቀኑ፡ በዘጠኝ፡ ሰዓት፡የእግ
ዚአብሔርን፡መልአክ፡በራእይ፡አየ፡ወደርሱ፡ ሲገባ፡
ሲለውም። ቀርኔሌዎስ፡ ሆይ።

፬፡ እርሱም ፡ በተመለከተው ፡ ጊዜ፡ ፈራ። አለው
ም።ምንድር፡ነገር፡ ነው፡ጌታ፡ሆይ። መልአኩም፡ አለ
ው። ጸሎትህ፡ምጽዋትህም፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡
ለመታሰብ፡ ወጣ።

፭፡ አሁንም፡ ሰዎች፡ ላክ፡ ወደ፡ ኢዮጴ፡ ሲመንን
ም፡ጴጥሮስ፡ የሚባለው፡ አሰመጣ።

፮፡ እርሱም፡አንግድነት፡ መጥተዋል፡ ወደንድ፡ሰ
ው፡ ሲሞን፡*ቀርበት፡ ፈቂ፡ ወደሚሉት። ቤቱም፡ በ
ባሕር፡ አጠገብ ። እርሱ ፡ ደነግርሃል፡ ተታደርገው፡ ዘን
ድ፡የሚገባህን፡ነገር። *ም፡ ፬፡ ፵፫፡፡ ተም፡ ፪፡ ፲፬፡፡

፯፡ መላኩም፡ ቀርኔሌዎስን፡ የነገረው፡ በሔደ፡ ጊ
ዜ፡ ሁለቱን፡ ሎላልቱን፡ ጸራ፡ ዘወትርም፡ ከማይለዩ
ት፡ ከጭፈርቹ፡ አንዷን፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ
ን፡ወታደር።

፰፡ ነገረንም ፡ ሁሉ ፡ አጫወታቸው ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ
ም፡ሰደደቸው።

፱፡ በነገው፡ም፡እርሳቸው፡በመንገድ፡ሲሔዱ፡ወደ
ገርም፡በቀረቡ፡ጊዜ፡ ጴጥሮስ፡ወደ፡ ሰገነት፡ ወጣ፡ ደጸ
ልይ፡ዘንድ፡ በሰድሰት፡ ሰዓት።

፲፡ ተራበም፡ ሊበላም፡ ወደደ። ሰዉቅም፡ መብል፡
ሲያበጁ ፡ራእደ፡ ወደቀበት።

፲፩፡ ሰማዮችም ፡ ተከፈተው ፡ አየ ፡ መጉያጸፈያ
ም፡ሲወርድ፡ አንደ ፡ ታላቅ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ምድርም፡
ደርሶ፡*ባራት፡ ወገን፡ታሥር። *ም፡ ፲፩፡ ፭።
ሉቃ፡ ፲፫፡ ፳፱።

፲፪፡ የምድርም፡ እንስሳ፡ ሁሉ፡ ነበረበት፡ አራዊት
ም፡ የሚንቀሳቀስም፡ የሰማደም፡ ወፍች።

፲፫፡ ድምጽም፡ወደርሱ፡ መጣ፡ኣንደህ፡ ሲል። ተነ
ሣ፡ ጴጥሮስ፡ ሆደ፡ አርደህ፡ ብላ።

፲፬፡ ጴጥሮስም ፡ አለ ። አደሆንም ፡ ከተ ፡ አቤቱ።
*ርኩስ ፡ የሚያስጸደፈም ፡ በልቼ ፡ ከተ ፡ አላውቅ
ምና። *ሕዝ፡ ፬፡ ፲፬፡፡ ዘሌዋ፡ ፲፩፡ ፯፡ ፲፫፡ ፳፫፡፡

፲፭፡ ድምጽም፡ ደግሞ፡ ሁለተኛ፡ ወደርሱ፡ መጣ፡
አንደህ፡ሲል።እግዚአብሔር፡*ያነጻውን፡አንተ፡አታ
ርክሰው። *ማቴ፡ ፲፭፡ ፲፩፡፡

፲፮፡ ደህም፡ሆነ፡ሶስትግዜ። አቃውም፡ ከዚያ፡ ወ
ደያ፡ ወደ፡ ሰማያ፡ ተመለሰ።

፲፯፡ ጴጥሮስም፡ በልቡ፡ ሲቸገር፡ያየው፡ ራእይ፡ም
ንድር፡ነው፡ብሎ። አነኒቸው፡ ሰዎች፡ቀርኔሌዎስ፡ የላ
ካቸው ፡ የሲሞንን ፡ ቤት፡ ደጠይቁ፡ በደጀም፡ ቁመ
ው፡ነበረ።

፲፰፡ ጸረም፡ ደጠይቁ፡ዘንድ፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስ፡ የ
ሚባላው፡ ከዚያ፡ እንግድነት፡ መጥተ፡ እንደ፡ ሆነ፡ብ
ለው።

፲፱፡ ጴጥሮስም፡ሲያስብ፡ባየው፡ራእይ፡መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አለው። እነሆ፡ ሶስት፡ ሰዎች፡ ይሹሃል።

፳፡ ነገር፡ግን፡ተነሣና፡ ውረድ፡ ከርሳቸው ጋራ፡ ሒድ፡በሁለት፡ልብም፡አትሁን። እኔ፡ልኪያቸዋለሁና።

፳፩፡ ጴጥሮስም፡ ከቀርኔሌዎስ፡ ወደ፡ተላኩት፡ ሰዎች፡በወረደ፡ ጊዜ፡አለ። እነሆ እኔ፡ነኝ፡ የምትሹኝ። ምን፡ ምክንያት፡ነው፡ የመጣችሁበት።

፳፪፡ አርሳቸውም፡አሉ። ቀርኔሌዎስ፡ የመቶ፡አለቃ፡ ጻድቅ፡ ሰው፡ እግዚአ፡ሔርንም ፡ የሚፈራ፡ የተመሰከረለትም፡ በአይሁድ፡ ወገን፡ ሁሉ። ቅዱስ፡ መልአክ፡ታየው፡ወደ፡ቤቱም፡ያመጣህ፡ ዘንድ፡አለው፡ ካንተም፡ ነገር፡ ይሰማ፡ ዘንድ።

፳፫፡ ጸራቸውም፡እንግድነትም፡ተቀበላቸው። በ ነጋውም፡ጴጥሮስ፡ከርሳቸው፡ጋራ፡ ወጣ፡ ሰዎችም፡ በ ኢዮጴ፡ ካሉ፡ ወንድሞች፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ሔደ።

፳፬፡ በነገውም፡ ወደ፡ ቄሣርያ ፡ ገቡ ። ቀርኔሌዎስ ም፡ዘመዶቹን፡ የቀረቡትንም፡ ወዳጆቹን፡ ጸርቱ፡ ደ ጠብቃቸው፡ ነበር።

፳፭፡ ጴጥሮስም፡ በገባ፡ጊዜ፡ ቀርኔሌዎስ፡ ተቀበለ ው፡በግረም፡ ወደቀ፡ ሰገደለትም።

፳፮፡ ጴጥሮስ፡ግን፡ አስነሣው፡ እንጂህ፡ ሲል ። ተነ ሣ፡እኔ፡ ደግሞ፡ሰው፡ ነኝና። ም፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

ራእ፡ ፲፱፡ ፲፡፡

፳፯፡ ከርሱ፡ጋራ፡ኢየተናገረ፡ም፡ገባ፡ አጅግ፡ሰዎች ም፡አገኘ፡ ከርሱ፡ዘንድ፡ተከማችተው።

፳፰፡ አላቸውም ። አላንት፡ ታውቃላችሁ ፡ ለይሁ ዴ፡ሰው፡እንደይገባ፡ደገናኝና፡ደገባ፡ዘንድ፡ወደ፡ሌላ፡ ወገን። ነገር፡ግን፡ እግዚአብሔር፡ አሳየኝ፡ ከሰው፡ ማ ነንም፡ አንደልል፡ ርኩስ፡ ወይ፡ የሚያስጸይፈ፡ነው።

፳፱፡ ስለዚህም፡ሳልጠራጠር፡ መጣሁ፡ብጠፈኝ። አሁንም፡እጠይቃችኋለሁ፡ለም፡ ምክንያት፡ አመ ጣችሁኝ።

፴፡ ቀርኔሌዎስም፡ አለ። ካራት፡ቀን፡ ጀምረ፡እስ ከዚች፡ሰዓት፡ድረስ፡ጾመኛ፡ነበርሁ። ስጸልይም፡ በቤ ቴ፡በዘጠኝ፡ ሰዓት፡እነሆ፡ አንድ፡ ሰው፡ በፊቴ፡ ቀመ፡ ነጭ፡ ልብስ፡ለብሶ።

፴፩፡ አለም። ቀርኔሌዎስ፡ ሆይ፡ ጸሎትህ፡ ተሰማ ችልህ፡ምጽዋትህም፡ታሰበችልህ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት።

፴፪፡ አሁንም፡ወደ፡ኢዮጴ፡ላክ፡ሲሞንንም፡ጴጥ ሮስ፡የሚባለውን፡አስመጣ። አርሱ፡እንግድነት፡ተቀ ምጥዋል፡በቀርበት፡ፈቂው፡ በሲሞን፡ቤት፡ በባሕር፡ አጠገብ። እርሱም ፡ መጥቶ፡ ነገር፡ ይነግርሃል።

፴፫፡ የዚያን፡ጊዜም፡ላክሁብህ።አንተም፡መልካ ም፡ሰራ፡ሰራህ፡በመምጣትህ። አሁንም፡እነሆ፡እኛ፡ ሁላችን፡ ከዚህ፡ አለን፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ እንሰ ማ፡ዘንድ፡አንተ፡ የታዘዝህበትን፡ ሁሉ፡ ከእግዚአብ ሔር፡ ዘንድ።

፴፬፡ ጴጥሮስም፡አፈን፡ ከፈተ፡ አለም። በውነት፡ አስተዋልሁ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው፡ ፊት፡ አንደያ ደላ። ፩፡ ሰሙኤ፡ ፲፭፡ ፯፡፡ ሮሀ፡ ፱፡ ፲፩፡፡

፴፭፡ ነገር፡ግን፡ በሕዝብ፡ሁሉ፡ የሚፈራው፡ ቅን፡ ነገርም፡ የሚያደርግ፡ አርሱ፡ በርሱ፡ዘንድ፡ የተቀበለ፡ ነው። ዮሐ፡ ፲፡ ፲፯፡፡

፴፮፡ ወደ፡ እሥራኤል፡ልጆች፡ የላከውን፡ነገር፡ የ ምስራች፡ ሲነግራቸው ፡በኢየሱስ፡ ክርስተ ስ፡አርሱ፡ *የሁሉ፡ ጌታ፡ነው። *ማቴ ፳፰፡ ፲፰፡፡

፴፯፡ ደህን፡ነገር፡አላንት፡ታውቃላችሁ፡ በይሁዳ፡ ሁሉ፡የሆነውን፡ከገሊላ፡ጀምሮ፡ ዮሐንስ፡ ካስተማረ በት፡ጥምቀት፡ በኋላ። ማቴ፡ ፬፡ ፲፪፡፡

፴፰፡ ስለ፡የሱስ፡ስለ፡ናዝሬቱ፡እግዚአብሔር፡ በ መንፈስ፡ቅዱስ፡በኃይልም፡ቀብተታልና።የመጣ፡መ ልካምም፡ ያደረገ፡ ሰይጣን፡ ያሸነፈቸውንም ፡ ሁሉ፡ የፈወሰ። እግዚአብሔር፡ከርሱ፡ጋራ፡ ነበርና።

ኢሳ፡ ፷፩፡ ፩፡፡

፴፱፡ እኛም፡ምስክሮች፡ ነን፡ ባደረገው፡ነገር፡ሁሉ፡ በይሁዳ፡ሉገር፡በየረሳሌምም።ይህን፡የገደሉት፡ በን ጨት፡ ላይ፡ ሰቅለው።

፵፡ ደህነን፡እግዚአብሔር፡ አስነሣው፡ በሶስተኛ፡ ቀን፡ ሰጠውም፡ ደገለጥ፡ ዘንድ።

፵፩፡ ለሕዝብ፡ሁሉ፡አደደለም፡ለምስክሮች፡እን ጅ፡ እግዚአብሔር፡ አሰቀድሞ፡ ለመረጣቸው። እኛ ም፡ነን፡ከርሱ፡ጋራ፡ የበላነ፡ የጠጣነም፡ ከሙታን፡ ከተ ነሣ፡ በኋላ። ዮሐ፡ ፲፱፡ ፳፱፡፡ ፲፭፡ ፳፯፡፡

፵፪፡ ለሕዝብም ፡ እያስተምር ፡ እንመሰክርም፡ ዘንድ፡እዘዘነ፡ ደህ፡እንደ፡ሆነ፡እግዚአብሔር፡ የመረ ጠው፡ በሕያዋንና፡ በሙታን፡ *ይፈርድ፡ ዘንድ።

*ም፡ ፲፯፡ ፴፭፡፡

፵፫፡ ለርሱም ፡ ደመሰክራሉ ፡ *ነቢያት፡ ሁሉ፡ በር ሱ፡የሚያምን፡ሁሉ፡የኃጢአተን፡ስርየት፡እንጂ ወስ ድ፡በስሙ። *ኢሳ፡ ፶፫፡ ፭፡ ፮፡፡ ኤር፡ ፴፩፡ ፴፬፡፡ ሕዝ፡ ፴፮፡ ፲፭፡ ፱፡ ፴፱፡፡ ሆሴ፡ ፲፫፡ ፲፬፡፡ ሚክ፡ ፯፡ ፲፰፡፡

፵፬፡ ጴጥሮስም ፡ ደህነን ፡ ነገር፡ ሲናገር ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ነገሩን፡ በሰሙት፡ ሁሉ፡ ላይ፡ ወረደ።

፵፭፡ ከግዝረት፡ ወገንም፡ የሚሆኑ፡ ከጴጥሮስ፡ ጋ ራ፡የመጡ፡ም፡አምኖን፡ ሁሉ፡ ደነገጡ፡ የ መንፈስ፡ ቅ ዱስ፡ጸጋ፡ በአሕዛብ፡ ላይ፡ ደግሞ፡ ስለ፡ ፈሰሰ።

፵፮፡ በሌላ፡ *ቋንቋ፡ ሲናገሩ፡ ሰምተዋቸዋልና፡ እ ግዚአብሔርንም ፡ ሲያከብሩ። *ም፡ ፱፡ ፱፡፡ ማር፡ ፲፮፡ ፲፯፡፡

፵፯፡ የዚያን፡ጊዜም፡ መለሰ፡ጴጥሮስ፡ አለም። በ ውኑ፡ማንም፡ ውኃ፡ደከለክላልን፡ አሌሁ፡ እንደይጠ መቁ። መንፈስ፡ቅዱስን፡ የወሰደ፡ እኛ፡ ደግሞ፡ እን ደ፡ወሰድነ።

፵፰፡ በጌታ ፡ ሰምዶ ፡ ደጠመቁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸ ው። የዚያን፡ጊዜ፡ *ለመኑት፡ ከርሳቸው፡ ዘንድ፡ አያ ሌ፡ቀን፡ ይቀመጥ፡ ዘንድ። *ዮሐ፡ ፬፡ ፴፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፩፡

፩፡ ሐዋርያትም፡በሄሮድ፡የነበረ፡ወንድሞችም፡ሰሙ፡አሕዛብ፡ደግሞ፡የእግዚአብሔርን፡ነገር፡እን ደ፡ተቀበሉ።

፪፡ ጴጥሮስም፡ወደ፡የሩሳሌም፡በወጣ፡ጊዜ፡*የግ ዝረት፡ሰዎች፡ተጣሉት፡እንጂህ፡ሲሉ። *ም ፲፡ ፵፰።

፫፡ ወደልተገዘረ፡ሰዎች፡ገባህ፡ከርሳቸውም፡ጋራ፡ በላህ።

ገላት፡ ፪፡ ፲፪።

፬፡ ጴጥሮስም፡ ወረውን፡ ሁሉ፡ ተከታትሎ፡ ያጨ ውታቸው፡ ጀመረ፡እንጂህም፡ አለ።

ም፡ ፲፡ ፲፡፡

፭፡ እኔ፡ በኢዮጴ፡ አገር፡ ነበርሁ ፡ ሰጸልይ፡ በራእይ ም፡እየሁ፡ታላቅ፡ልብስ፡ከሰማይ፡ እንጂ፡ ወረደ፡ እን ጂ፡ ታላቅ፡ መጕናጸፊያ፡ ባራት፡ወገን፡ ታሥሮ፡ ወደኔ፡ መጣ።

፮፡ አስተውዬም፡ በተመለከትሁ፡ ጊዜ፡ የምድር፡ እንስሳ፡አየሁ፡ አራዊትም፡ ተንቀሳቃሽም፡ የሰማይ ም፡ ወፎች።

፯፡ የሚለኝንም ፡ ድምጽ፡ ሰማሁ። ተነሣ፡ ጴጥሮ ስ፡ ሆይ፡ አረድና፡ብላ።

፰፡ አልሁም። አይሆንም፡ከተ፡አቤቱ። እንጂች፡ር ኩስ፡የሚያስጸይፈም፡ወደፈ፡ንብተ፡አላውቅምና።

፱፡ ድምጽም፡ከሰማይ፡ደግሞ፡ሁለተኛ፡መለሰል ኝ፡አለኝም። እግዚአብሔር፡ ያነጻውን፡ አንተ፡ አታር ክሰው።

፲፡ ይህም፡ሶስት፡ጊዜ፡ሆነ።ከዚያ፡ በኋላም፡ ሁሉ፡ ወደ፡ሰማይ፡ተሳበ።

፲፩፡ እነሆም፡በዚያች፡ሰዓት፡ሶስት፡ሰዎች፡ቀሙ፡ እኔ ፡ ባለሁበት ፡ ቤት ። ከቂሣርያ ፡ ወደኔ ፡ ተልከው።

፲፪፡ መንፈስ፡ቅዱስም፡አለኝ፡ ከርሳቸው፡ጋራ፡ እ ሔድ፡ዘንድ፡በመንም፡ ሳልጠራጠር። ከኔም፡ጋራ፡መ ጡ፡አሌህ፡ሰድሰቱ፡ ወንድማማች። ወደዚያ፡ ሰው፡ ቤትም፡ ገባነ።

፲፫፡ ነገረነም፡ መ፡አኸን፡እንደየ፡ በቤቱ፡ ቁሞ፡ሲ ለውም። ሰዎች፡ወደ፡ኢዮጴ፡ላክ፡ ሲመንንም፡ ጴጥ ሮስ፡የሚባለውን፡ አስመጣ።

፲፬፡ እርሱ፡ ይነግርሃል፡እንተ፡ የምትድንበትን፡ ነገ ር፡ የቤትህም፡ ሰዎች፡ ሁሉ።

ም፡ ፲፡ ፮።

፲፭፡ ለሠናዋ፡ህ፡ በጀመርሁ፡ ጊዜ፡መንፈስ፡ ቅዱ ስ፡ ወረደባቸው፡ በኛ፡ አሰቀድሞ፡ እንደ፡ ወረደ።

ም፡ ፪፡ ፬።

፲፮፡ የጌታንም፡ነገር፡ አሰብሁ፡ እንዲት፡ እንደለ። ዮሐንስ፡በውኃ፡ አጠመቀ፡እላንት፡ ግን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ትጠመቃላችሁ።

ም፡ ፭፡ ፭፡፡ ማቴ፡ ፫፡ ፲፩።

፲፯፡ እግዚአብሔርም፡ የጸጋን፡ እንድነት፡ከሰጣቸ ው፡ለኛ፡ እንደ፡ ሰጠ፡ በጌታ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ባመ ንሁ፡ጊዜ።እኔ፡ማነኝ፡ እግዚአብሔርን፡ ለመከልከል፡ እችል፡ዘንድ።

፲፰፡ ይህንም፡ በሰሙ ፡ጊዜ፡ ዝማሉ ፡ እግዚአብ ሔርንም፡ አመሰገኑ፡ እንደህ፡ሲሉ።እንጂህም፡እ ግዚአብሔር፡ ለአሕዛብ፡ ንስሐ፡ ሰጣቸው፡ ደድኑ፡ዘ ንድ።

፲፱፡ የተበተኑት፡ግን፡ በእስጢፋኖስ፡ ላይ፡ በተደረ ገው፡መከራ፡ወደ፡ፊንቄ፡ መጡ፡ ወደ፡ቀጵሮስም፡ወ ደ፡አንጾክያም፡ ማነንም፡ነገሬን፡ አያስተምሩም፡ነበ ሩ፡ ለአይሁድ፡ ብቻ፡እንጅ።

ም፡ ፰፡—፱፡፡

፳፡ ሌሎችም፡ ከርሳቸው፡ ሰዎች፡ ከቀጵርስ፡ ወገ ን፡ነበሩ፡ከቂሬኔም። እርሳቸውም፡ ወደ፡አንጾክያ፡በ ገቡ፡ጊዜ፡ አረማውያንን፡ አስተማሩ፡ የጌታን፡ የየሱ ስን፡ የምስራች፡ ሲነግርዋቸው።

፳፩፡ የእግዚአብሔር፡እጅም፡ከርሳቸው፡ጋራ፡ነበ ር። ሰዎችም፡ቍጥራቸው፡ እጅግ፡ የሚሆን፡ ወደ፡ጌ ታ፡ተመለሰ።

ም፡ ፱፡ ፴፯፡፡

፳፪፡ ወረደቸውም፡ በየሩሳሌም፡ባለው፡ ቤተ፡ክ ርስቲያን፡ጀሮ፡ ተሰማ፡ በርናባስንም፡ ሰደደት፡ ወደ፡ አንጾክያ፡ ይሔድ፡ ዘንድ።

፳፫፡ በመጣም፡ጊዜ፡ የእግዚአብሔርንም፡ ጸጋ፡ባ የ፡ጊዜ፡ደስ፡አለው፡ ሁሉንም፡አጸናቸው፡ በጌታ፡ደና ረ፡ዘንድ፡ በጸና፡ በልባቸው፡ ፈቃድ።

ም፡ ፲፫፡ ፴፫፡—፴፱፡፡

፳፬፡ጻድቅ፡ሰው፡ነበረና፡መንፈስ፡ቅዱስም፡*የመ ላበት፡ ሃይማኖትም ። እጅግ ፡ †ሰዎችም ፡ ለጌታ፡ ተ ጨመረ።

*ም፡ ፮፡ ፭፡፡ †ም፡ ፭፡ ፲፱፡፡

፳፭፡ በርናባስም፡ወደ፡ ጠርሲስ፡ ወጣ፡ *ሳውልን፡ ሊሻ።ባገኘውም፡ጊዜ፡ወደ፡አንጾክያ፡ ይዞት፡ መጣ።

*ም፡ ፱፡ ፴፡፡

፳፮፡ አንድ፡ አመትም፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ተሰበ ሰቡ፡ እጅግ፡ ሰዎችም፡ አሰተማረ ። *በአንጾክያም፡ አሰቀድሞ ፡ ደቀ፡ መዛሙርት ፡ ክርስቲያን ፡ ተባሉ።

*ገላት፡ ፪፡ ፲፩፡፡

፳፯፡ በዚችም፡ ወራት፡ *ነቢያት፡ ከየሩሳሌም፡ ወ ደ፡ አንጾክያ፡ ወረዱ።

*ም፡ ፲፫፡ ፩፡፡ ፲፭፡ ፴፱፡፡

፳፰፡ ከርሳቸውም፡አንዷ፡ተነሣ፡ስሙን፡አጋቦስ፡ የሚሉት፡በመንፈስ፡ ቅዱስም፡ተናገረ፡ታላቅ፡ራብ፡ አንድሆን፡በዓለም፡ ሁሉ። እርሱም፡ የሆነ፡ በአቅሉ ዲዎስ፡ ቁዛር፡ ዘመን።

ም፡ ፴፩፡ ፲፡፡

፳፱፡ ደቀ፡መዛሙርትም፡ *ፈቀዷ፡ከርሳቸው፡አ ያንደንዷ፡ አንድ፡ ከብቱ፡ መጠን፡ ማገልገል፡ ይሰዷ፡ ዘንድ፡ በይሁዳ፡ላሉት፡ ወንድሞች።

*ገላት፡ ፪፡ ፲፡፡

፴፡ ይህንንም፡አደረጉ፡ወደ፡ሽማግሌዎችም፡ ሰደዷ ት፡ *በበርናባስና፡ በሳውል፡ እጅ።

*ም፡ ፲፪፡ ፴፭፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፪፡

፩፡ በዚያም፡ዘመን፡ *ሄሮድስ፡ ንጉሥ፡እጁን፡ባያ ሌ፡ሰዎች፡ ላይ፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡ ጨነ፡ መከራ፡ሊያ ሰያቸው።

*ም፡ ፱፡ ፫፡፡

፪፡ ያዕቆብንም ፡ የዮሐንስን፡ ወንድም ፡ በሰይፍ፡ ገደለው።

፫፡ ያም፡አደሁድን፡ደሰ፡እንደሰኛቸው፡ባዮ፡ጊዜ፡ ጨመረበት፡ ጴጥሮስን፡ ላደዝ፡ ደግሞ። የፈሲካም፡ በዓል፡ ወራት፡ነበረ።

፬፡ በያዘውም፡ጊዜ፡ *በግዞት፡አሰቀመጠው፡ ላራ ት፡ሙፍሮችም፡ አሳልፎ፡ ሰጠው፡ ይጠብቁት፡ ዘንድ፡ ከፈሲካ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሕዝብ፡ ያወጣው ፡ ዘንድ፡ ፈ ቀደ። *ም፡ ፲፯፡ ፷፱፡፡

፭፡ ጴጥሮስም፡ በግዞት፡ ይጠበቅ፡ ነበረ፡ ደሮ ፡ ግን፡ ጸሎት፡ ሁለዛ፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ወደ፡ እግዚአብ ሔር፡ ይሆን፡ ነበረ፡ ሰለርሱ።

፮፡ ሄሮድስም፡ ወደርሳቸው፡ ያወጣው፡ ዘንድ፡ በ ወደደ፡ጊዜ፡ በዚያ፡ሌሊት፡ጴጥሮስ፡ተኝቶ፡ ነበር፡ በሁ ለት፡ወታደር፡መካከል፡ በሁለት፡ ሰንሰለት፡ ታሥሮ። ጠባቆችም ፡ በደጇ ፡ ፊት፡ የግዞቱን፡ ቤት፡ ይጠብቁ፡ ነበር።

፯፡ እነሆም፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ወደርሱ፡ ቀመ፡ብርሃንም፡በቤቱ፡በራ። የጴጥሮስንም፡ ጎን፡ መ ታው፡ አስነሣውም፡ እንደህ፡ ሲል ። ፈጥነህ ፡ ተነሣ። ሰንሰለትኞም፡ ከጀ ፡ ወደቁ። ም፡ ፭፡ ፲፬፡፡

፰፡ መልአኩም፡አለው።ታጠቅ፡ጪማህንም፡ልበ ስ።እንደሁም፡አደረገ። አለውም። ልብስን፡ ልበስና፡ ተከተለኝ።

፱፡ ጴጥሮስም ፡ ተከትሎት፡ ወጣ፡ በመልአኩም፡ የሚደረገው፡ ነገር፡ አውነት፡ እንደ፡ ሆነ፡ አላወቀም፡ ራእይ፡ የሚያደ፡ ይመስለው፡ ነበረ፡ እንጇ።

፲፡ የመጀመርያውንም ፡ ሁለተኞውንም ፡ ዘብ፡ ባ ለፈ፡ ጊዜ፡ ወደገር፡ ወደሚወሰደው፡ ወደ ፡ ብረቱ፡ ደ ጅ፡ ደረሱ፡ ቦገዛጇ ፡ የተከፈተላቸው ። በወጡም፡አ ንደገም፡ መንገድ፡በሔደ፡ ጊዜ፡ የዚያን፡ ጊዜ፡ መል አኩ፡ ከርሱ፡ ራቀ።

፲፩፡ ጴጥሮስም፡ወደ፡ልቡ፡ ተመለሰ፡ አለም። አሁ ን፡ በውነት፡ አወቅሁ፡ እግዚአብሔር፡ መልአኩን፡አ ንደ፡ ላከ፡ ከሄሮድስም፡ እጅ፡የአደሁድ፡ወገንም፡ ካ ሰቡት፡ ሁሉ፡ አንደደነኝ።

፲፪፡ እውነት፡አንደ፡ ሆነም፡ ባወቀ፡ ጊዜ፡ ማርቀስ፡ ወደሚባለው፡ወደ፡*ዮሐንስ፡እናት፡ወደ፡ማርያም፡ ቤት፡መጣ፡እጇግ፡ሰዎች፡ ተከማችተውበት፡ ከነበረ ት፡ ሰፈራ፡ ሲጸልዩ። *ም፡ ፲ፉ፡ ፲፯፡፡

፲፫፡ ጴጥሮስም፡ የቤቱን፡ደጇ፡ በመታ፡ጊዜ፡ ሸንደ ት፡ብላቴና፡ መጣች፡ ስምዋን፡ ሮዳ፡ የሚልዋት፡ ትሰ ማ፡ዘንድ።

፲፬፡ የጴጥሮስንም፡ድምጽ፡ባወቀች፡ጊዜ፡ከደስታ ዋ፡ የተነሣ፡ አልከፈተችም፡ ተቀደደመች፡ አንጇ፡ የ ምስራቹም፡ነገረች፡ ጴጥሮስ፡ በደጇ፡ ቁሞ፡ አንደለ።

፲፭፡ አርሳቸው፡ግን፡ አልዋት። ታብደለች።አርስዋ ም፡ነገርዋን፡በውነት፡አጸናች።አርሱ፡ አንደ፡ሆነ። አር ሳቸውም፡ አሉ ። *መልአኩ፡ ይሆናል።

*ሉቃ፡ ፷፱፡ ፸፯፡፡

፲፮፡ ጴጥሮስ፡ ግን ፡ ደጇን፡ ሲመታ ፡ ዘገዮ። በከፈቱ ም፡ ባዩትም፡ ጊዜ፡ አደነቁ።

፲፯፡ አርሱ፡ግን፡በጇ ፡ጠቀሳቸው፡ዝም፡አንደሉ። አጫወታቸውም፡ አንደት፡ አግዚአብሔር፡ ከግዞት፡ አንደወጣው፡አለም።ያህንን፡ ለያዕቀብ፡ ንገሪ፡ ለወ ንድሞችም። ወጥተም፡ ወደ፡ ሌላ፡ሰፈራ፡ ሔደ።

፲፰፡ ማልደም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ ፈጇት፡ ሆነ፡ በጭፈራ ው፡ መካከል፡ ጥቂት፡ አደደለውም፡ አንደህ፡ ሲሉ። አንጇ፡ ጴጥሮስን፡ ምናገኘው። ም፡ ፭፡ ፷፭፡ ፷፪፡፡

፲፱፡ ሄሮድስም ፡ ባስፈለገው፡ ጊዜ፡ ባያገኘውም፡ ጠባቆቾን፡ መረመረ፡ ሊገልዋቸውም፡ አዘዘ።ከደሁ ደ ፡ አገርም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ወረደ ፡ ከዚያም ፡ ተቀ መጠ።

፳፡ ሄሮድስም፡በጢሮስና፡በሲደና፡ ሰዎች፡ተቆጥ ተ፡ነበረ። አርሳቸው፡ ግን፡ባንድ፡ወደርሱ፡ መጡ፡ብላ ስጦስንም፡በንጉሠ ፡ ግዛት፡ የተቦመውን ፡ አሺ፡ባሰ ኙት፡ጊዜ፡ዕርቅ፡ፈለጉ።*ያገራቸው፡አህል፡ከንጉሡ፡ ግዛት፡ነበርና። *ፅ፡ ነገሠ፡ ፭፡ ፱፡ ፲፩፡፡ ሕዝ፡ ፳፯፡ ፲፯፡፡

፳፩፡ በተቀረጠመ፡ቀን፡ሄርሂድስ፡ የንጉሠ፡ልብስ፡ ለበሰ ፡ በዙፋንም፡ ተቀመጠ፡ የግልጽም፡ ነገር፡ ተናገ ራቸው።

፳፪፡ ሕዝቡም፡ጮሁ።የአምላክ፡ቃል፡ነው፡የሰው ም፡ቃል፡ አደደለም። ሕዝ፡ ፳፰፡ ፪፡፡

፳፫፡ የዚያን፡ ጊዜም ፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ቀሠፈው፡ለእግዚአብሔር፡ *ምስጋና፡ ስላልሰጠ። ት ልም፡ ፈላበትና፡ ሞተ። *ኢ፡ ፭፡ ፮፡፡

፳፬፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ግን፡ ያድግ፡ ያበዛም፡ ነበረ። ም፡ ፮፡ ፯፡፡ ኢሳ፡ ፶፭፡ ፲፩፡፡

፳፭፡ በርያባስና፡ሳውል፡ግን፡ ከዮሩሳሌም፡ ተመለ ሱ ፡ መልእክታቸውን ፡ *በፈጸሙ ፡ ጊዜ ። ከርሳቸው ም፡ጋራ፡ ዮሐንስን፡ ወሰዱ፡ ተማርቀስ፡ የተባለውን። *ም፡ ፲፭፡ ፷፱፡፡ †ቀ፡ ፲፪፡፡ ም፡ ፲፭፡ ፸፯፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፫፡

፩፡ በአንጾክያም ፡ ባሉች፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ *ነቢያ ትና፡መምህራን፡ነበሩ፡ ከርሳቸውም፡ በርናባስ፡ ስም ዖንም፡ ኒጌር፡ የሚባለው። ሉክዮስም፡ የቀሬናው። ማናሄንም፡ከሄሮድስ፡ጓራተኞው፡ አለቃ፡ጋራ፡ ያደገ ው።ሳውልም። *ም፡ ፲፩፡ ፷፯፡፡ ፷፩፡ ፲፡፡

፪፡ አርሳቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሲያገለግሉ፡ ሲጾሙም፡መንፈስ፡ቅዷስ፡አለ። *በርያባስንና፡ ሳው ልን፡ ለዮልኝ፡ ለጸራኋቸው፡ ስራ። *ም፡ ፱፡ ፲፭፡፡

፫፡ የዚያን ፡ ጊዜም፡ *ጾመ፡ ጸለዩም ። እጇቸውን ም፡ ተበጫኑባቸው፡ ጊዜ፡ ሰደድዋቸው።

*ም፡ ፲፱፡ ፷፫፡፡ †ም፡ ፮፡ ፯፡፡

፬፡ እሌህም፡ ከመንፈስ፡ ቅዷስ፡በተላኩ፡ ጊዜ፡ወ ደ፡ሴሌውቅያ፡ መጡ፡ ከዚያም፡ወደ፡ ቀጵርስ፡ በመ ርከብ፡ ሰረፉ።

፭፡ ወደ፡ሰላሚስም፡በደረሱ፡ጊዜ፡በእግዚአብሔ

ር፡ ነገር፡ አስተማረ፡ በአይሁድ፡ መስጊደች ።*ዮሐን በም፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ነበረ፡ ሲያገለግላቸው።

*ም፡ ፲፪፡፡ ፲፪፡ ፹፭፡፡

፮፡ ደሴቱንም ፡ ሁሉ፡ በዞረ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ጳፎስ፡ መ ጡ ። ከዚያም፡ አስማተኛ፡ ሰው፡ አሰኮሽም፡ ነቢይ፡ አገኙ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ ሰሙን ፡ ባርዮሱስ ፡ የሚ ሉት።

፯፡ ከሰርጊዎስ፡ ጳውሎስ ፡ ከሸሙ፡ ባስተዋይ፡ ሰ ው፡ ጋራ፡ የነበረ ። ይህ፡ በርናባስንና፡ ሳውልን፡ አስመ ጣ፡ የእግዚአብሔርንም፡ ነገር፡ ሊሰማ ፡ ለመፍ።

፰፡ ኤላማስም፡አስማተኛው፡ ሰሙ፡እንደሁ፡ይ ተረጕማልና፡ ተቋቋማቸው፡ ሸሙን፡ ከሃይማኖቱ፡ ሊመልሰ፡ ቢሻ። ፱፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፷፡፡

፱፡ ሳውል፡ግን፡ደግሞ፡ ጳውሎስ፡ የተባለው፡ መን ፈሰ ፡ ቅዱስን ፡ መላ ፡ ሳይኑንም ፡ ተክሎ ፡ ተመለከ ተው።

፲፡ አለም።አንተ፡ ሸንገላ፡ የመላበት፡ ተንኰልም፡ ሁሉ፡ የሰይጣን፡ ልጅ፡ የጽድቅም፡ ሁሉ፡ ጸላት። አት ተውምን፡የእግዚአብሔርን፡ መንገድ፡ የቀናችውን፡ ጠማማ፡ ማድረግ።

፲፩፡ አሁንም፡እነሆ፡ የእግዚአብሔር፡እጅ፡ባንተ፡ ላይ፡ነው። ዕውርም፡ ሁን፡ ፀሓይም፡አትይ፡ አስከ፡ጊ ዜው ። የዚያን፡ ጊዜም፡ ጭጋግ፡ ወደቀችበት፡ ጨለማ ም። ይዞርም፡ ጀመረ፡ የሚመረታትንም፡ ለመፍ።

፲፪፡ የዚያን፡ጊዜም፡ ሸሙ፡ የተደረገውን፡ ተአምሯት፡ ባየ፡ ጊዜ፡ አመነ፡ ተገርሞ፡ ከእግዚአብሔር፡ ት ምህርት፡ የተነሣ።

፲፫፡ ጳውሎስ፡ግን፡ ከርሱም፡ጋራ፡ የነበሩት፡ ከጳፎ ስ፡ በሔደ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ጰርጊያ፡መጡ፡ በጰምፊልያ፡ያ ለችው ። ዮሐንስ፡ ግን፡ ተለያቸው፡ *ወደ፡ የሩሳሌም ም፡ ተመለሰ።

*ም፡ ፲፭፡፡ ፴፰፡፡

፲፬፡ አርሳቸውም፡ከጰርጊያ፡ አለፈ፡ ወደ፡ አንጾክ ያም፡የጲሲድያ፡ወደምትሆን፡አገር፡መጡ።ወደ፡መ ሰኒድም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ፡ ቅደሚ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ።

፲፭፡ ኦሪትም፡ ነቢያትም ፡ ከተነበቡ፡ በኋላ ፡ የመ ስኒዲ፡ አለቀች ፡ ወደርሳቸው ፡ ሊኩ፡ እንደህ፡ ሲሉ። እላንት ፡ ሰዎች፡ ወንድሞች፡ የትምህርት፡ ነገር፡ እን ደላችሁ፡ ለሕዝቡ፡ ይነገር፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ተናገሩ።

፲፮፡ ጳውሎስም፡ተነሣ፡ በጀ.ም፡ ጠቀሳቸው፡ አለ ም። አላንት፡ ሰዎች፡ የእሥራኤል፡ ወገን፡ አግዚአብ ሔርንም፡ የምትፈሩ፡ ስሙ።

፲፯፡ የዚህ፡ የእሥራኤል፡ወገን፡ አምላክ፡ አባቶቻ ችነን፡መረጠ፡*ሕዝቡንም፡በተሰደደባት፡ በምሥር፡ አገር፡ተከፈ፡ከፍ፡አደረገው፡ከርስቦም፡አወጣቸው፡ በታላቅ ፡ ክንድ። *ኢሳ፡ ፩፡ ፰፡፡

†ዘፀአ፡ ፲፪፡ ፴፯፡ ፵፭፡፡

፲፰፡ አርባ፡አመትም፡ ምሉ፡ በምድረ፡ በያ፡ መገባ ቸው። ዘፀአ፡ ፲፮፡ ፴፭፡፡ ዘኁል፡ ፲፬፡ ፴፱፡፡ ዘደግ፡ ፩፡ ፴፭፡፡

፲፱፡ *ሰባት፡ አሕዛብም ፡ በከነዓን ፡ አገር፡ ካጠፈ፦ በኋላ ፡ ምድራቸውን ፡ ተበፃ፡ አካፈላቸው።

*ዘደግ፡ ፯፡ ፩፡፡ †ኢያ፡ ፲፫፡ ፪፡፦

፳፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ፈራጆች ፡ ሰጣቸው፡ አራት፡ ዓሥ፡ካምሳ፡አመት፡የሚያህል፡አስከ፡ነቢዩ፡አስከ፡ ሳሙኤል፡ዘመን፡ድረስ። መሳ፡ ፪፡ ፲፮፡፡ ፫፡ ፴፡፡

፳፩፡ ከዚያም፡በኋላ፡ንጉሥ፡ለመኑ፡እግዚአብሔ ርም ፡ሳኦልን፡ ሰጣቸው ፡ የቂስን ፡ ልጅ ፡ ከብንያም፡ ወገን፡ የሚሆንን፡ ሰው፡ አርባ፡ አመት።

፩፡ ሳሙኤል፡ ፲፡ ፳፩፡፦

፳፪፡ አርሱንም ፡ ካሻረው ፡ በኋላ፡ ንጉሥ፡ አስነሣ ላቸው፡*ደዊትን፡ የመሰከረለትን፡ ያለውንም። ደዊ ትን፡የእሤይን፡ልጅ፡አገኘሁ፡እንደ፡ልቤ፡ያለ፡ ሰው፡ ፈቃደኝ፡ሁሉ፡ የሚያደርግ።

*፩፡ ሳሙኤል፡ ፲፫፡ ፲፪፡ ፲፫፡፦

፳፫፡ እግዚአብሔርም፡ከዚህ፡ *ዘር፡ እንደ፡ መሐ ላው፡ ለእሥራኤል፡ የሱስን ፡ አስነሣ፡ መድኃኒት፡ እ ድርጎ። *ኢሳ፡ ፲፩፡ ፩፡፦

፳፬፤ ዮሐንስም፡ አስቀድሞ፡ የሙሰራች፡ ተናገረ፡ በመምጣቱ፡ፊት፡*በንስሐ፡ጥምቀት፡ለእሥራኤል፡ ወገን፡ ሁሉ። *ማቴ፡ ፫፡ ፩፡፦

፳፭፡ ዮሐንስም፡ ሩጫውን፡ በፈጸመ፡ ጊዜ፡ አለ። ምንድር፡ ነው ፡ የመሰላችሁ፡ እኔ፡ እንደ፡ ሆንሁ ። ያ፡ እኔ፡እደይለሁም።ነገር፡ግን፡እነሆ፡ ከኔ፡በኋ.ኋ፡ይመጣ ል፡ የማይገባኝ፡ የግሩን፡ ጫማ፡ እፈታ፡ ዘንድ።

ዮሐ፡ ፩፡ ፳፯፡፡ ማር፡ ፩፡ ፯፡፡ ሉቃ፡ ፫፡ ፲፮፡፦

፳፮፡ አላንት ፡ ወንድማማች ፡ ሰዋች ። የአብርሃ ም፡ ዘር፡ልጆች፡ ከለንትም፡ እግዚአብሔርን፡ የምት ፈሩ፡ ሁሉ። ለላንት፡ ተላከ፡ የዚህ፡ መድኃኒት፡ ነገር። ቊ፡ ፴፯፡፦

፳፯፡ በየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ፡ ሰዋች፡ ግን፡ አለቀቻ ቸውም፡ ይህን ፡ *ባያውቁ ፡ የነቢያትንም ፡ ድምጽ፡ ቅደሚ ፡ ቅደሚ፡ የሚነበበውን፡ ፈጸሙት ፡ በፈረዱ በት፡ ጊዜ። *ዮሐ፡ ፲፮፡ ፫፡፦

፳፰፤ ለሞትም፡የምታደርስ፡እንዲት፡ ስንኳ፡ ም ክንያት፡ባያገኙበት፡ ወደ፡ ጲላጦስ፡ *ለመኑ፡ ይገድሉ ው፡ ዘንድ። *ማቴ፡ ፳፯፡ ፳፪፡ ፳፫፡፦

፳፱፡ ሰለርሱ፡ የተጻፈውንም ፡ ሁሉ ፡ በፈጸሙ፡ ጊ ዜ፡ *ከንጨት፡አወረዷት፡ በመቃብርም፡ ጨመሯት። *ማቴ፡ ፳፯፡ ፶፱፡፦

፴፡ እግዚአብሔር፡ ግን፡ ከሙታን፡ አስነሣው።

ም፡ ፫፡ ፲፭፡፦

፴፩፡ ብዙ፡ቀንም፡ ተግለጠ፡ከገሊላ፡ ወደ፡ የሩሳሌ ም፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ለወጡ። እርሳቸውም፡ ምስክሮች፡ ናቸው፡ በሕዝብ፡ ዘንድ። ም፡ ፭፡ ፫፡፡

፴፪፡ እኛም፡የምሰራች፡እንዛግራችኋለን፡ላባቶቻ ችን፡በሆነው፡ተስፋ። ቊ፡ ፲፫፡፡

፴፫፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ለኛ ፡ ለልጆቻቸው፡ ፈጽሞታልና፡ የሱስን፡ ባስነሣ፡ጊዜ።እንደ፡ ተጻፈ፡ ደ

ግሙ፡በሁለተኛው፡መዝሙር፡እንደሂህ፡ሲል።*አንተ፡ልጄ፡ነህ፡እኔ፡ዛሬ፡ወለድሁህ። *መዝ፡ ፪፡ ፯።

ወፀ፡ እርሱም፡ከሙታን፡አስነሥተታልና፡ወደ፡ጥፋትም፡አደመለስምና፡ደግሞ፡እንደሁ፡አለ።*የጀዊትን፡የታመነቅውን፡ጸጋ፡እሰጣችኋለሁ።

*ኢሳ፡ ፶፭።

ወፈ፡ ስለዚህም፡በሌላው፡ሰፍራ፡ደግሞ፡ይላል። ወደጅህን፡አተውም፡ጥፋት፡ያይ፡ዘንድ።

መዝ፡ ፲፮፡ ፲።

ወፈ፡ ደዊትም፡የእግዚአብሔርን፡ፈቃድ፡በዘመኑ፡ካገለገለ፡በኋላ፡አንቀላፈ፡ወደባቶቹም፡ሔደ፡ጥፋትም፡አየ። ም፡ ፪፡ ኽ፬።

ወፈ፡ ደህ፡ግን፡እግዚአብሔር፡ያስነሣው፡ጥፋት፡አላየም።

ወፈ፡ አሁንም፡በላንት፡ዘንድ፡ የታወቀ፡ይሁን፡አላንት፡ ሰዋች፡ ወንጅማማች ፡በዚህ ፡እንደ፡ነርላች ሁ፡የኃጢአት፡ስርየት።

ወፀ፡ ከኃጢአትም ፡ሁሉ፡ በሙሴ ፡አሪት ፡ከርስዋ ፡ትነጹ፡ዘንድ፡ የማትችሉ።ም በዚ ፡ ፡ የሚያፅኃን፡ሁሉ፡ደነጻል። ሮሜ፡ ፲፣ ፱።

ፘ፡ አሁንም፡ተጠንቀቁ፡እንደይመጣባችሁ፡*በነቢያት፡ የተባለው። *አንባ፡ ፩፡ ፭።

ፘፀ፡ እዩ፡አላንት፡ቸልተኖች፡ተደነቁም፡ ጥፈም። እኔ፡ በዘመናችሁ፡ ሰራ፡ አሰራለሁና፡ የማታምኑትን፡ ማንም፡ ቅሉ፡ ቢነግራችሁ።

ፘፀ፡ አርሳቸውም፡ከአደሁድ፡መሰኒድ፡ሲወጡ፡ለመንቀቸው፡አሕዛብ፡በሚመጣው፡ ቅደሚ፡ ደሀነኝ፡ነገር፡ ደነግርዋቸው፡ ዘንድ።

ፘር፡ ጉባዔውም፡ በተፈታ፡ ጊዜ፡ ከአደሁድ፡ አጅግ፡ ሰዋች፡ ሰደተኖችም፡ ለእግዚአብሔር፡ የሚገዙ፡ ጳውሎስንና፡ በርናባስን፡ ተከተሉ። የነገርዋቸው፡ አሺ፡ደሰኝዋቸውም፡ በእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ ይጸኑ፡ ዘንድ። *ም፡ ፲፭፡ ፭፫።

ፘፀ፡ በሁለተኛውም፡ቅደሚ፡ ተሰበሰቡ፡ ያገረ፡ሰዋች፡ ሁሉ፡የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡ ደሰሙ ፡ ዘንድ።

ፘፈ፡ አደሁድም፡ የተሰበሰቡትን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ፡ ቅናት፡ መላባቸው ። የጳውሎስንም፡ ነገር፡ አፈረሱ፡ ኢየ ተቃወሙ፡ ኢየተሳደቡም። ቊ፡ ፶፡ ም፡ ፲፱፡ ፪።

ፘፗ፡ ጳውሎስና፡በርናባስም፡አጽንተው፡ ተናገሩ፡ አሉም።*አስቀድመን፡የእግዚአብሔርን፡ነገር፡ለላንት፡እንነግር፡ ዘንድ፡ደገባል። ነገር፡ግን፡ብትገፏት፡ በነፍሳችሁም፡ብትፈርዷ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ እንደደገብችሁ፡ እነሆ፡ ወደ፡ አሕዛብ፡ እንመለሳለን።

*ም፡ ፫፡ ፶፭። ማቴ፡ ፲፡ ፭፡

ፘፗ፡ እግዚአብሔር፡ እንደሁ፡እዞናልና፡እንደህ፡ሲል። *ለአሕዛብን፡ብርሃን፡ አደረግሁህ፡መድኃኒት፡ ትሆን፡ ዘንድ፡ እስከ፡ ምድር፡ ደርቻ፡ ድረስ።

*ኢሳ፡ ፵፱፡ ፮።

ፘፚ፡ አሕዛብም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ደሳላቸው፡ የእግዚአብሔርንም፡ ነገር፡ አመሰገኑ። ለዘላለም፡ ሕይወ ትም፡ *የተዘጋጁ፡ሁሉ፡ አመኑ። *ሮሜ፡ ፰፡ ፳፱።

ፘፚ፡ የእግዚአብሔርም፡ ነገር፡ በዚያች፡ አገር፡ ሁሉ፡ ወጣ።

፱፡ አደሁድ፡ግን፡የሚገዙትን፡ የሚከብሩትንም፡ ሴቶች፡ አወኩ፡ ያገሩንም፡ አለቀች። ስደትም፡ አስነሡ፡ በጳውሎስና፡ በበርናባስ፡ ላይ፡ ካገራቸውም፡ አወጥዶቸው።

፱፩፡ አርሳቸው፡ ግን፡ የግራቸውን፡ ትቢያ፡ አረገፈ ባቸው፡ ወደ፡ ኢቆንዩምም፡ መጡ። ም፡ ፲፫፡ ፯። ማቴ፡ ፲፡ ፲፬።

፱፪፡ ደቀ፡ መዛሙርትም፡ ደስታን፡ መንፈስ፡ ቅ ደስንም፡ መሉ።

ምዕራፍ፡ ፲፬፡

፩፡ በኢቆኒዩምም፡ ሆነ፡ ወደ፡ አደሀ ድ፡ መስኒድ፡ ደግሞ፡ ገቡ፡ እንደሁ፡ም፡ ተናገረ፡ ብዙ፡ ሰዋች፡ አስ ኪያምኑ፡ ድረስ፡ ከአደሁድ፡ ከአረማውያንም።

፪፡ ያላመኑ፡ አደሁድ፡ ግን፡ የአሕዛብን፡ ልብ፡ አሰነሡ፡ አስበፈፃሙ፡ ዘወንጅሞች፡ላደ። ም፡ ፲፫፡ ፶፭።

፫፡ እርሳቸው፡ ግን፡ ከዚያ፡ረጅም፡ዘመን፡ ተቀመጡ፡ በእግዚአብሔር፡ ሲጋደሉ፡ ለጸጋው፡ ነገር፡ የመሰከረ፡ ተአመራትም፡ ድንቅም፡ በጀቸው፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ የሰጠ። ም፡ ፲፬፡ ፲፭። ዕብ፡ ፪፡ ፬።

፬፡ ያገሩም፡ ሰዋች፡ተከፈሉ። እኩሌቶቹም፡ ከአደሁድ፡ ሆኑ፡ እኩሌቶቹም፡ ከሐዋርያት፡ ጋራ።

፭፡ የአሕዛብና፡ የአደሁድም፡ መነሣት፡ ብሆነ፡ ፫ዜ፡ ካለቅቻቸው፡ ጋራ፡ ያ'ሥሰቀ'ልዋቸው፡ደወግርዋቸውም፡ዘንድ። ቊ፡ ፲፬፡ ፪፡፡ ፭፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፩።

፮፡ ያነን፡ ባወቁ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ሊቃኦኒያ፡ አገር፡ ኩበ ለሉ፡ ወደ፡ ልስዋራ፡ ወደ፡ ደርቤም፡ ባጠነብዋም፡ ወ ደለቸው፡ አገር።

፯፡ ከዚያም፡ የመሰራች፡ ደነገረ፡ ነበር።

ም፡ ፲፭፡ ፲፱፡ ፳፫።

፳፡ ባልስዋራም፡አንድ፡ ሰው፡ ነበር፡ ለግረ፡ ኃይል፡ የሌለው፡ ተቀምጦ። አንካሳ፡ ከናቱ፡ማሕፀን፡ይ፫ም ሮ፡ ከተም፡ አደሔድም፡ ነበር። ም፡ ፫፡ ፭።

፱፡ ደህ፡ሰማ፡ ጳውሎስ፡ሲናገር። እርሱም፡ ዓይኑን፡ ተክሎ፡ በተመለከተው፡ባየም፡ጊዜ፡ *ዛደማናት እንደለው፡ ደድን፡ ዘንድ። ማቴ፡ ፱፡ ፳፰።

፲፡ በታላቅ፡ ቃል፡ አለው። በግርህ፡ቀንተህ፡ ቁም። ተነሠተም፡ ሔደ።

፲፩፡ አሕዛብም፡ ጳውሎስ፡ ያደረገውን፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ ድምጻቸውን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አደረጉ፡ በሊቃኦኒያ፡ ቋንቋ፡ ሲሉ። አማልክት፡ ሰዋች፡ መሰሉ፡ ወደኛም፡ ወረዱ። ም፡ ፲፰፡ ፯።

፲፪፡ በርናባስንም፡ ድያ፡ አሉት፡ ጳውሎስንም፡ ሄርሜን። እርሱ፡ ነውና፡ ነገሩን፡ የሰራ።

፲፫፡ የድያ፡ ካህን፡ ግን፡ ባገራቸው፡ ፈት፡ የነበረ፡ በ
ሮችና፡ አክሊሎች፡ ወደ፡ ደጅ፡ አመጣ፡ ሊሠዋላቸው
ም፡ ወደደ፡ ከሰዎች፡ ጋራ።
፲፬፡ ሐዋርያትም፡ ጳውሎስና፡ በርናባስ፡ ይህነን፡
በሰሙ፡ ጊዜ፡ ልብሳቸውን፡ ቀደደ፤ ወደ፡ ሕዝቡም፡
ቀልጥፈው፡ ሮጡ።
፲፭፡ ኢየጹሁ፡ ኢያሉም። አላጎት፡ሰዎች፡ለምን፡
ይህነን፡ ትሰራላችሁ። እኛም፡ እንደላንተ፡ ሰዎች፡
ነኑ፡ በድካም፡ የተካከልናችሁ። እናስተምራችሁማ
ለን፡ ትመለሱ፡ ዘንድ፡ ከዚህ፡ ከንቱ፡ ወደ፡ ሕያው፡
እግዚአብሔር፡ ሰማያን፡ ምድርንም፡ ባሕርንም፡ ሁ
ለምንም፡ ሁሉ፡ በርሳቸውም፡ ያለውን፡ የፈጠረ።
ም፡ ፲፡ ፷፮፡፡
፲፮፡ ባለፈው፡ ትውልድ፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ የተው፡
በመንገዳቸው፡ ይሔዱ፡ ዘንድ።። ም፡ ፲፯፡ ፴፡፡
፲፯፡ ምንሰ፡እርሱ፡ራሱን፡ያለ፡ ምስክር፡ያልተው፡
ለ፫፡ በጎ፡ ሲያደርግ፡ ከሰማይም፡ ዝናመ፡ ሲሰጠ፡
ፍሬ፡ የሚሆንበትንም፡ ጊዜ። ልባችነንም፡ መብልና፡
ደስታ፡ ሲመላው። መዝ፡ ፻፵፯፡ ፰፡፡ ኤር፡ ፭፡ ፷፬፡፡
፲፰፡ ይህነንም፡ ብለው፡ የግድ፡ አሕዛብን፡ አስተ
ውዋቸው፡ እንደይወዱላቸው።
፲፱፡ አደሁድ፡ ግን፡ ከአንጾክያ፡ ከኢቆኒደምም፡
መጡ፡ አሕዛብንም፡ አሺ፡ አሰኝዋቸው፡ ጳውሎስን
ም፡ *ወገሩት፡ ካገር፡ ወደ፡ሚደም፡ ጉተቱት፡ የሞተ
ም፡ መሰላቸው።። *፪፡ ቀሮ፡ ፲፭፡ ፷፭፡፡
፪፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፩፡፡
፳፡ ደቀ፡ መዛሙርት፡ ግን፡ ከበውት፡ ሳሉ፡ ተነሡ
ት፡ ወደገር፡ ገባ፡ በነገውም፡ ወደ፡ ደርቤ፡ ወጣ፡ ከበር
ናባስ፡ ጋራ።
፳፩፡ በዚያችም፡ አገር፡ ባስተማረ፡ ጊዜ፡ አጅግ፡
ሰዎችም፡ደቀ፡ መዛሙርት፡ ባደረጉ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ልስ
ጥራ፡ ተመለሱ፡ ወደ፡ አቂኒደምም፡ ወደ፡ አንጾክ
ያም።
፳፪፡ የደቀ፡ መዛሙርትንም፡ ልብ፡ ያጸኑ፡ ይለም
ንዋቸውም፡ ነበረ፡ በሃያማኖት፡ ይጸኑ፡ ዘንድ፡አንደ
ህ፡ ሲሉ። በብዙ፡ መከራ፡ ይገባናል፡ ወደ፡ እግዚአብ
ሔር፡ መንግሥት፡ እንገባ፡ ዘንድ።። ም፡ ፲፭፡ ፷፫፡፡
፭፡ ተሰ፡ ፫፡ ፫፡፡
፳፫፡ ሽማግሌችም፡መረጡ፡ ለርሳቸው፡ በኢየማ
ንበረ። ሁሉ። በጾምም፡ ጸለዩላቸው፡ ለእግዚአብሔ
ርም፡ ላመኑበት፡ አደራ፡ ሰጥዋቸው።። ም፡ ፲፫፡ ፫፡፡
፳፬፡ በጲሲድያም፡ በዙረ፡ ጊዜ፡ከዚያ፡ ወደ፡ ጳም
ፊልያ፡ መጡ።
፳፭፡ በጰርጊያም፡ የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡ ከተና
ገረ፡ በኋላ፡ ወደ፡ አጠልያ፡ ወረዱ።
፳፮፡ ከዚያም፡ ወደ፡ አንጾክያ፡ በባሕር፡ ሰረፉ።
ለእግዚአብሔርን፡ ጸጋ፡ አስቀድሞ፡ አደራ፡ ወደ፡ ተ
ሰጡበት፡ ሰፈራ፡ ለፈጸሙት፡ ሰራ።። ም፡ ፲፫፡ ፭፡ ፱፡፡
፳፯፡ በመጡም፡ ጊዜ፡ የቤተ፡ ክርስቲያንንም፡ ሰ
ዋች፡ ሁሉ፡ በሰበሰቡ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ከርሳቸ
ው፡ ጋራ፡ ያደረገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ነገረ፡ ለአሕዛብም፡
የሃይማኖትም፡*ደጅ፡አንደ፡ከፈተ። *፭፡ቀሮ፡፲፭፡፱፡፡
፳፰፡ ከዚያም፡ አያሌ፡ ቀን፡ ተቀመጡ፡ ከደቀ፡
መዛሙርት፡ ጋራ።

ምዕራፍ፡ ፲፭፡

፩፡ ሰዎችም፡ ከአይሁዲ፡ መጡ፡ ወንድሞችንም፡
አስተማሩ፡ እንደህ፡ ሲሉ። እንደ፡ ሙሴ፡ ሥርዓት፡
ካልተዘራችሁ፡ አትችሉም፡ ትድኑ፡ ዘንድ።
ገለት፡ ፭፡ ፱፡፡
፪፡ ጽልም፡ ክርክርም፡ ለጳውሎስና፡ ለበርናባስ፡
ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ጥቂት፡ ያደደለ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ጳውሎ
ስና፡ በርናባስ፡ ከርሳቸውም፡ ሌሎች፡ ሰዎች፡ ወደ፡
የሩሳሌም፡ ይሔዱ፡ ዘንድ፡ አዘዙ፡ ወደ፡ ሐዋርያት፡
ወደ፡ ሽማግሌችም፡ስለዚህ፡ ክርክር። ም፡ ፲፭፡ ፱፡፡
ገላት፡ ፪፡ ፩፡፡
፫፡ እርሳቸውም፡ ከጉባዔው፡ተሸኝተው፡ ወደ፡ ፈ
ንቂ፡ ወደ፡ ሰማርያም፡ ሔዱ፡ የአሕዛብንም፡ መመ
ለስ፡ ይነገርዋቸው፡ነበረ፡ ታላቅ፡ ደስታም፡አደረጉ፡ ለ
ወንድሞች፡ ሁሉ።
፬፡ ወደ፡ የሩሳሌምም፡ በደረሱ፡ጊዜ፡ ተቀበልዋቸ
ው፡ ቤተ፡ ክርስቲያኑ፡ ሁሉ፡ ሐዋርያትም፡ ሽማግሌ
ችም።እግዚአብሔርም፡ባደረገው፡ሁሉ፡ከርሳቸው፡
ጋራ፡ አጨወትዋቸው።። ም፡ ፲፱፡ ፷፮፡፡
፭፡ ሰዎችም፡ተነሡ፡ ከፈሪሳውያን፡ወገን፡ያመኑ፡
እንደህ፡ ሲሉ። ይገባል፡ ትገዝርዋቸው፡ ዘንድ፡ ታዝ
ዋቸውም፡ ዘንድ፡ የሙሴን፡ ሕግ፡ እንደ፫ብቁ።
፮፡ ሐዋርያትም፡ ሽማግሌችም፡ ተሰበሰቡ፡ ይህነ
ን፡ ነገር፡ ያዩ፡ ዘንድ።
፯፡ አጅግም፡ ክርክር፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ጴጥሮስ፡ ተነሣ፡
አላቸውም። አላጎት፡ ወንድሞች፡ ሰዎች። አላጎት፡
ታውቃላችሁ፡ ባለፈው፡ዘመን፡እግዚአብሔር፡ ከኛ፡
እንደ፡ መረጠ፡ አሕዛብ፡ ካፈ፡ የወንጌል፡ ነገር፡ ይሰ
ሙ፡ ዘንድ፡ ያመኑም፡ ዘንድ።። ም፡ ፲፭፡ ፲፭፡፡
፰፡ ልብንም፡ የሚያውቅ፡ አመላክ፡ መሰከረላቸ
ው፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡በሰጣቸው፡ ጊዜ፡ ለኛ፡እንደ፡
ሰጠን፡ ደግሞ።
፱፡ በርሳቸውና፡ በኛም፡ መካከል፡ አንደች፡ አልለ
የም፡ ልባቸውንም፡ በሃያማኖት፡ አነጻው።
ም፡ ፲፡ ፴፱፡፡
፲፡ አሁንም፡ ለምን፡ እግዚአብሔርን፡ ትፈታተና
ላችሁ፡ ቀምበርስ፡ ትጭናላችሁ፡በደቀ፡ መዛሙርት፡
ጫንቃ፡ ላይ፡ አባተቻችን፡ እኛም፡ እንሸከመው፡ ዘን
ድ፡ ያልቻልነ።። ገላት፡ ፫፡ ፲፡፡ ፭፡ ፭።
፲፩፡ ነገር፡ ግን፡ በጌታ፡ በዮሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጸጋ፡ እን
ድን፡ዘንድ፡እናምናለን፡እንደለዚያ። ገላት፡ ፪፡ ፲፮።
ኤፈ፡ ፪፡ ፱፡—፲፡፡
፲፪፡ ሰዎችም፡ ሁሉ፡ ዝም፡ አሉ፡ጳውሎስና፡ በርና

ግስም፡ተአምራትን፡ ሲያጪውቱ፡ሰሙ፡ድንቁንም፡ እግዚአብሔር፡ በጀቸው፡ በአሕዛብ፡ ያደረገውን።

፲፫፡ እርሳቸውም፡ ዝም፡ ካሉ፡ በኋላ፡ መለሰ፡ያዕቆብ፡ እንደህ፡ ሲል። አላንት፡ ሰዉች፡ ወንድሞች፡ ስሙኝ።

ም፡ ፳፭፡ ፲፰፡፡

፲፬፡ ስምዖን፡ ተናግሮዋልና፡እግዚአብሔር፡ አበቀድሞ፡ እንደት፡ እንደ፡ ጐበኘ፡ ከአሕዛብ፡ ወገን፡ ይወስድ፡ዘንድ፡ ለስሙ።

፲፭፡ ይህም፡ ለነቢያት፡ ቃል፡ ይሰማማል፡ እንደ፡ ተጻፈ።

፲፮፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ እመለሳለሁ፡ የፈዊትንም፡ ጎጇ፡ የወደቀውን፡ አሰራለሁ፡ የፈረሰውንም፡ ተመልሼ፡አጸናለሁ፡አቀመዋለሁም። ዓሞ፡ ፱፡ ፲፩፡ ፲፪፡፡

፲፯፡ የቀሩቱ፡ ሰዉች፡ እግዚአብሔርን፡ ይፈልጉ፡ዘንድ፡ አሕዛብም፡ሁሉ፡ስሜ፡ በርሳቸው፡የተጸራው። ይህን፡ ሁሉ፡ የሚያደርግ፡ እግዚአብሔር፡ አለ።

፲፰፡ ለእግዚአብሔር፡ ስራው፡ሁሉ፡የታወቀ፡ነው፡ ከጥንት፡ ጀምሮ።

፲፱፡ ስለዚህም፡ እኔ፡ አፈርደለሁ፡ ከአሕዛብ፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ የተመለሱትን፡ እንደታድክሙ።

፳፡ ነገር፡ግን፡እንላክባቸው፡ከጣዖታት፡ ርኩሰቱ፡ ደርቁ፡ዘንድ፡ ከዝሙትም፡ ከታነቀም፡ *ከደምም።

*ዘፍጥ፡ ፱፡ ፬፡፡ ዘሌዋ፡ ፫፡ ፲፯፡፡

፳፩፡ ለሙሴ፡ ከቀደመው፡ ትውልድ፡ ጀምሮ፡ ሰዉች፡ ነበረትና፡ ቅደሚ፡ ቅደሚ፡ ባነረ፡ ሁሉ፡በየመስ ጊደ፡ የሚያነቡት። ም፡ ፲፫፡ ፲፭፡፡

፳፪፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ ሐዋርያት፡ ሽማግሌዎችም፡ ከቤተ፡ ክርስቲያኑ፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ አዩ፡ በጎ፡ እንደሆን፡ ከርሳቸው፡ ሰዉችን፡ ይመርጡ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ አንጾክያም፡ ይሰደ፡ ዘንድ፡ ከጳውሎስና፡ ከበርናባስ፡ ጋራ። እርሳቸውም፡ ይሁዳ፡ በርሰባስ፡የተባለው፡ሲላስም፡ ከወንድሞች፡ መሮች፡ የነበሩ።

፳፫፡ በጀቸውም፡ይህን፡ነገር፡ ጻፉ። ከሐዋርያት፡ ከሽማግሌችም፡ ከወንድሞችም፡ ወደ፡ወንድሞች፡ ከአሕዛብ፡ ወገን፡ በአንጾክያ፡ በሻምም፡ በቂልቂያም፡ ይሰ፡ይበላችሁ።

፳፬፡ ከኛ፡ ሰዉች፡ *ወዋተው፡ እንደወጂችሁ፡ ልባችሁንም፡ በነገሯው፡ እንደ፡ ገለበጡት፡ ሰምተናልና። እንደህ፡ ሲሉ። ትገዘሩ፡ ዘንድ፡ ኦሪትንም፡ ትጠብቁ፡ ዘንድ፡ ደገባችኋል። እኛ፡ ያላዘዝናቸውን።

*ም፡ ፭፡ ፲፡፡ ገላት፡ ፪፡ ፬፡፡

፳፭፡ አየነ፡ ባንድ፡ በተሰበሰብነ፡ ጊዜ፡ ሰዉች፡ እነ መርጥ፡ ዘንድ፡ ወደላንት፡የምንሰደቸው፡ከወደጀቻችን፡ ከበርናባስና፡ ከጳውሎስ፡ ጋራ።

፳፮፡ ነፍሳቸውን፡ የለወጡ፡ ሰዉች፡ ስለ፡ ጌታችን፡ ስለ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም።

፳፯፡ ይሁዳንና፡ ሲላስንም፡ ላክነ፡ እርሳቸውም፡ ደግሞ፡ ባፈቸው፡ ይህን፡ ነገር፡ ይነግርቸኋል።

፳፰፡ መንፈስ፡ቅዲስ፡አይትዋልና፡ እኛም፡ አይተናልና፡ ትርፍ፡ ሸክም፡አንደንጭንባችሁ፡ከዚህ፡ከሚ ገባችሁ፡ ሕግ፡ በቀር።

፳፱፡ ለጣዖት፡ ከተሠዋ፡ መበል፡ ትርቁ፡ዘንድ፡ ከ ደምም፡ ከታነቀም፡ ከዝሙትም። ከዚህ፡ ራሳቸሁ ን፡ ከጠበቃችሁ፡መልካም፡ታደርጋላችሁ። ጤና፡ ይስ ጣችሁ።

፴፡ እርሳቸውም፡ በተሰናበቱ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ አንጾክ ያ፡ መጡ። ሕዝቡንም፡ ሁሉ፡ ሰብስበው፡መልእክቱ ን፡ ሰጥዋቸው።

፴፩፡ *ባነበቡትም፡ ጊዜ፡ ደሳላቸው፡ ልባቸውም፡ ጸና። *ም፡ ፲፫፡ ፵፮፡፡

፴፪፡ ይሁዳና፡ ሲላስ፡ ግን፡ *ነቢያት፡ ነበረና፡ ወንድሞችን፡ በጅግ፡ ነገር፡ ደስ፡ አሰኝዋቸው፡ አጸንዋቸውም። *ም፡ ፲፭፡ ፵፯፡፡ ፲፫፡ ፭፡፡

፴፫፡ ከርሳቸውም፡ ዘንድ፡ አያሌ፡ ቀን፡ በተቀመጡ፡ ጊዜ፡ ከወንድሞች፡ ወደ፡ ሐዋርያት፡ በደህና፡ ተሰናብተው፡ ሔደ።

፴፬፡ ሲላስ፡ ግን፡ ወደደ፡ ከዚያ፡ ይቀመጥ፡ዘንድ።

፴፭፡ ጳውሎስና፡ ባርናባስም፡ በአንጾክያ፡ ተቀመጡ፡ ያስተምረ፡ም፡ የመስራችም፡ ደነግረ፡ ነበረ፡ በአ ግዚአብሔር፡ ነገር፡ ከሌሎች፡ ደግሞ፡ ከብዙ፡ ሰዉች፡ ጋራ።

፴፮፡ ከብዙ፡ ቀንም፡ በኋላ፡ ጳውሎስ፡ በርናባስን፡ አለው፡ ና፡ እንመለስ፡ ወንድሞቻችነን፡ እንጉብኛቸው፡ የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡ባስተማርነባት፡አገር፡ ሁሉ፡ እንደት፡ ናቸው። ፭፡ ተሰ፡ ፫፡ ፭፡፡

፴፯፡ ባርናባስን፡ ወደደ፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ዮሐንስን፡ ደወሰድ፡ ዘንድ፡ ማርቀስ፡ የተባለውን።

ም፡ ፲፪፡ ፲፪፡ ፭፭፡፡

፴፰፡ ጳውሎስ፡ ግን፡ አልወደደም፡ደህነን፡ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ሊወሰድ፡ ከርሳቸውም፡ ከጳምፊልያ፡ የተ ለየውን፡ ከርሳቸውም፡ ጋራ፡ ወደ፡ ስራ፡ ያልመጣውን። ም፡ ፲፫፡ ፲፫፡፡

፴፱፡ በመካከላቸውም፡ መከፈፋት፡ ሆነ፡ እስኪ ለያዩ፡ ድረስ። በርናባስም፡ ማርቀስን፡ ወሰደ፡በመር ከብም፡ ሰረረ፡ ወደ፡ ቀጵሮስም፡ ሔደ።

፵፡ ጳውሎስ፡ ግን፡ ሲላስን፡ መረጠ፡ ወጣም፡ ለኤ ዝአብሔር፡ ጸጋ፡ ተማጓፅ፡በወንድሞች፡ ጸሎት።

፵፩፡ በሶርያም፡ በቂልቂያም፡ ዞረ፡ አብያት፡ ክር ስቲያናትንም፡ አጸና።

ምዕራፍ፡ ፲፮፡

፩፡ ወደ፡ ደርቤና፡ ወደ፡ ልሥጥራም፡ ደረሰ። እነሆ ም፡ ከዚያ፡ አንድ፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ ነበረ፡ ስሙም፡ *ጢሞቴዎስ። ያመነቸም፡ የአይሁዲዊት፡ ሴት፡ ልጅ፡ ነበር፡ አባቱ፡ ግን፡ አረማዊ። *ም፡ ፲፯፡ ፲፬፡፡ ፲፱፡ ፶፪፡፡

፪፡ በጎም፡ የተመሰከረለት፡ ነበረ፡ በልስጥራ፡ና፡ በ ኢቆኒዶም፡ ከሚኖረ፡ ወንድሞች። ም፡ ፮፡ ፫፡፡

፫፡ ይህነን፡ ወደደ፡ ጳውሎስ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ይወጣ፡

ዘንድ፡ ወሰደውም፡ ገዘረውም፡ በዚያ፡ ሰፈራ፡ ሰለ፡ ነበረ፡ አይሁድ። ሁሉ፡ አባቱን፡ አውቁት፡ ነበረን፡ አ
ረማዊ፡ እንደ፡ ሆነ። ፪፡ ጢሞ፡ ፭፡ ፭፡፡

፬፡ አገረንም፡ ሁሉ፡ ሲዞረ፡ አሳልፈው፡ ሰጥዋቸ
ው፡ ከሐዋርያት፡ ከሽማግሌዎችም፡ በየረሳሌም፡ ከ
ሚኖሩ፡ *የታዘዘውን፡ ትእዛዝ፡ ይጠብቁ፡ ዘንድ።
ም፡ ፲፯፡ ፳፡—፳፱፡፡

፭፡ አብያተ፡ ክርስቲያናትም፡ ሁሉ፡ በሳይማኖት፡
ጸንተው፡ ይኖሩ፡ ነበር፡ በቍጥርም፡ ይበዙ፡ ነበር፡ ዕለ
ት፡ ዕለት።

፮፡ ወደ፡ አፈሪኒያም፡ ወደ፡ ገላትያም፡ ካለፈ፡ በ
ኋላ፡ ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ ተከለከሉ፡ ነገር፡ እንደደኑ
ሩ፡ በእስያ። ም፡ ፲፮፡ ፮፡፡

፯፡ ወደ፡ ሚስያም፡ መጡ፡ በቢቲንያም፡ይሔዱ፡ ዘንድ፡ ወደደ፡ መንፈስ፡ ግን፡ አልተዋቸውም።

፰፡ ከሚስያም፡ ባለፉ፡ ጊዜ፡ወደ፡ትሮአስ፡መጡ።

፱፡ ለጳውሎስም፡ በሌት፡ ራእይ፡ ታየው። አንድ፡ የመቄዶንያ፡ ሰው፡ ቁሞ፡ ይለምነው፡ነበረ፡አንደህ፡ ሲል። ወደ፡ መቄዶንያ፡ አለፍን፡ እርደነ።

፲፡ ራእይም፡ ባየ፡ ጊዜ፡ የዚያን፡ ጊዜውን፡ ወደ፡ መቄዶንያ፡ እንሔድ፡ ዘንድ፡ ፈቀድነ፡ፈርድናልና፡ እ
ግዚአብሔር፡ እንደ፡ ጸራነ፡ ልናሰተምራቸው።

፲፩፡ ከትሮአስም፡በወጣነ፡ጊዜ፡መንገደኞነን፡ወደ፡ ሳሞትራኬ፡ አቀናነ። በነገውም፡ ወደ፡ ኔያጶሊስ፡ ሔ
ድነ።

፲፪፡ ከዚያም፡ ወደ፡ ፊልጵስዩስ፡ እርስዋም፡ የመ
ቄዶንያ፡ ግዛት፡ መጀመርያ፡ የምትሆን፡ የኮሎንያ
ም። በዚቺም፡ አገር፡ አያሌ፡ ቀን፡ ተቀመጥነ።

፲፫፡ ቅዳሜ፡ ቀንም፡ ካነር፡ ወደ፡ ሜዳ፡ ወጣነ፡ ወ
ደ፡ ወንዙ፡ ጸሎት፡ ይደረግበት፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ለመደ
ው፡ ሰፈራ። በተቀመጥነም፡ ጊዜ፡ ለተሰበሰቡት፡ ሴ
ቶች፡ ተናገርነ።

፲፬፡ አንዲት፡ሴትም፡ ሰምዋን፡ ሊዲያ፡ የሚልዋ
ት፡ ቀይ፡ ሐር፡ የምትሸጥ፡ ከቲያቲራ፡ አገር፡ ለአግዚ
አብሔር፡ የምትገዛ፡ ትሰማ፡ነበረች። እግዚአብሔር
ም፡ ልብዋን፡ ከፈተላት፡ ከጳውሎስ፡ ወደ፡ተባለው፡
ነገር፡ ታደምጽ፡ ዘንድ። ዮሐ፡ ፮፡ ፶፬፡፡

፲፭፡ እርሰዋም፡ በተጠመቀች፡ ጊዜ፡ የቤትዋም፡ ሰዎች፡ ለመነችነ፡ እንደህ፡ ስትል። ደታወቃችሁስ፡ እንደ፡ ሆን፡ እኔ፡በጌታ፡ እንደመንሁ፡ ወደ፡ ቤቴ፡ግቡ
ና፡ ተቀመጡ። የግድም፡ አለችነ።

፲፮፡ እንደህም፡ ሆነ፡እኛ፡ ወደ፡ ጸሎት፡ ስንሔድ፡ አንዲት፡ ቀንደ፡ ተቀበለችነ፡ የምዋርተኝነትም፡ መ
ንፈስ፡ነበረባት። በጠንቋይነትዋም፡ ለጌተችዋ፡ እጅ
ግ፡ ጥቅም፡ ትጠቅም፡ ነበረች። ም፡ ፲፭፡ ፳፱፡፡

፲፯፡ ይህች፡ ጳውሎስን፡ ተከተለች፡እኛንም። እን
ደህ፡ ስትልም፡ ጮኸች። አሌህ፡ ሰዎች፡ የልዑል፡ አ
ምላክ፡ ባሮች፡ ናቸው። እርሳቸውም፡ የመድኃኒት፡
መንገድ፡ ያስተምርዋችኋል። ማር፡ ፭፡ ፳፱፡፡

፲፰፡ ይህንንም፡ እጅግ፡ ቀን፡ አደረገች። ደህየ፡ ጳ
ውሎስን፡ አሳዘነው፡ ተመለሰም፡ ለዚያ፡ ጋኔንም፡ አ
ለ። አዝዛለሁ፡ በዮሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሰም፡ ከርስዋ፡ ት
ወጣ፡ዘንድ።በዚያውም፡ጊዜ፡ወጣ። ማቴ፡ ፲፯፡ ፲፯፡፡

፲፱፡ ጌተችዋም፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ የመጠቀማቸው፡ ተስ
ፋ፡ እንደ፡ ተቍረጠ፡ ጳውሎስንና፡ ሲላስን፡ ያዝዋቸ
ው፡ በገቢያም፡ ወደላቀች፡ ጐተትዋቸው።

፳፡ ወደ፡ አገርም፡ ሸማምተ፡ባመጥዋቸው፡ጊዜ፡ አሉ። አሌህ፡ ሰዋች፡ አገራችነን፡ እጅግ፡ አወኩ፡ አር
ሳቸውም፡ አይሁድ፡ ናቸው። ም፡ ፲፯፡ ፮፡፡

፳፩፡እንቀበለውም፡እናደርገውም፡ዘንድ፡የማይ
ገባነን፡ሕግ፡ያስተምራሉ። እኛ፡ የርም፡ ሰዋች፡ነንና።

፳፪፡ ሕዝቡም፡ ተነሣባቸው፡ሸማምተም፡ልብሳ
ቸውን፡ ቀደዷ፡በሽመልም፡ *ይመትዋቸው፡ ዘንድ፡ አዘዙ። *፪፡ ቀሮ፡ ፲፩፡ ፳፭፡፡ ፊል፡ ፭፡ ፴፡፡
፭፡ ተሰ፡ ፪፡ ፪፡፡

፳፫፡ በብዙ፡ መምታትም፡በገረፋዋቸው፡ጊዜ፡ ወ
ደ፡ ግዞት፡ ቤት፡ ጣልዋቸው፡ ግዞት፡ ጠባቂውንም፡ አዘዙት፡ ተጠንቅቀ፡ይጠብቃቸው፡ዘንድ።

፳፬፡ አርሱም፡ ደህነን፡ ትእዛዝ፡ በተቀበለ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ውስጡ፡ግዞት፡ አዘጋቸው፡ እግራቸውንም፡ በ
መጠርቀቂያ፡ ጠረቀቃቸው።

፳፭፡ በመንፈቀ፡ሌሊትም፡ጳውሎስና፡ ሲላስ፡ *ይ
ጸልዩ፡ እግዚአብሔርንም፡ ያመሰግኑ፡ ነበረ። እሥሮ
ችም፡ይሰማዋቸው፡ ነበረ። *ም፡ ፬፡ ፴፭፡፡ ፭፡ ፶፭፡፡

፳፮፡ ድንገትም፡ ታላቅ፡መናወጥ፡ ሆነ፡የግዞቱ፡ መ
ሠረት፡እስኪናወጥ፡ ድረስ። የዚያን፡ጊዜም፡ ደጀች፡
ሁሉ፡ ተከፈቱ። እሥራትም፡ ለታሠሩት፡ ሁሉ፡ ተፈ
ታላቸው።

፳፯፡ ግዞት፡ ጠባቂውም፡ ከእንቅልፈ፡ በነቃ፡ጊዜ፡ የግዞቱንም፡ ደጀ፡ ሁሉ፡ ተከፍተ፡ባየ፡ ጊዜ፡ሰይፈን፡
መዘዘ፡ ራሱን፡ ደገደል፡ ዘንድ፡ የታሠረ፡ቱ፡ የኰበለ
ሉ፡ መሰሎት።

፳፰፡ ጳውሎስ፡ ግን፡ በታላቅ፡ ቃል፡ ጮኸበት፡ እን
ደህ፡ ሲል። በራስህ፡ ክፈ፡ ነገር፡ አታደርግ። እኛ፡ ሁላ
ችን፡ ከዚህ፡ ነንና።

፳፱፡ መብራትም፡ፈለገ፡ ተነሣም፡ኢየተንቀጠቀ
ጠም፡ ገባ፡ ለጳውሎስና፡ ለሲላስም፡ ሰግደ፡ ወደቀ።

፴፡ ወደ፡ ሚደም፡ አወጣቸው፡ አለም። ጌተቼ፡
ሆይ፡ ምን፡ ይገባኛል፡ *አደርገው፡ ዘንድ፡ እንድድን።
ም፡ ፪፡ ፴፯፡፡ *ሉቃ፡ ፫፡ ፲፡፡

፴፩፡ እርሳቸውም፡አሉት። በጌታ፡ በየሱስ፡ ክርስ
ቶስ፡ *አመን፡ አንተም፡ ትድናለህ፡ ቤትህም፡ ሁሉ።
*ዮሐ፡ ፫፡ ፲፮፡፡

፴፪፡ የጌታንም፡ ነገር፡ አጪወቱት፡ በቤቱ፡ ላሉት
ም፡ ሰዎች፡ ሁሉ።

፴፫፡ በዚያን፡ ጊዜም፡ በሌት፡ ወሰደቸው፡ ቍሰላ
ቸውንም፡አጠባቸው። የዚያን፡ጊዜውንም፡ተጠመ
ቀ፡ አርሱ፡ የቤቱም፡ ሰዎች፡ ሁሉ።

፴፱፡ ወደ: ቤቱም: አወጣቸው: ማዕድም: አቀረ
በላቸው: ደሳለውም: አርሱ:የቤቱም: ሰዎች:ሁሉ:
በእግዚአብሔር: ስላመኑ።

፴፰፡ ማልደም:በሆነ:ጊዜ:ሹማምት:አሣሮችን:
ሰደዱ: እንደህ: ሲሉ: አሊያን: ሰዎች: ፍታ።

፴፯፡ ግዞት: ጠባቂውም: ለጳውሎስ: የምስራች:
ነገረው: በዚህ: ነገር። ሹማምት: ላኩ: ትወጡ: ዘንድ። አሁንም: ውጡ: በደህየም: ሒዲ።

፴፮፡ ጳውሎስ: ግን: አላቸው። በግልጽ: መቱን: ያ
ለ: ፍርድ: እኛ: *የርም: ሰዎች: ሰንሆን: በግዞትም:
ጨመሩን። አሁንም: በሥውር: ያወጡናልን። አደሆ
ንም። እርሳቸው: መጥተው: ያውጡን: እንጅ።

ም: ፳፱፡ ፴፭፡፡

፴፮፡ አሣሮችም: ደህነን:ነገር:ለሹማምት:ነገሩ።
የርም: ሰዎች: እንደ: ሆኑም:በሰሙ: ጊዜ: ፈሩ።

፴፱፡ ወደርሳቸውም: መጡ:ተናገርዋቸውም: አ
ወጥዋቸውም: ከከተማም: ደወጡ: ዘንድ: *ለመ
ንዋቸው። *ማቴ፡ ፰፡ ፴፱፡፡

፴፯፡ ከግዞትም: ከወጡ: በኋላ: ወደ:ሊድያ: ገቡ።
ወንድሞችንም: ባዩ: ጊዜ: አጸንዋቸው: ወጡም።

ምዕራፌ: ፲፮:

፩፡ ወደ: አምፊጶሊስም: ወደ:አጶሎንያም: ካለ
ፉ:በኋላ: ወደ: ተሰሎንቄ: መጡ: የአይሁድ: መስ
ጊድ: ወደለባት። ፩፡ተሰ፡ ፪፡ ፪፡፡

፪፡ ጳውሎስም: እንደ: ለመደው: ወደርሳቸው:
ገባ: ሶስት: ሰንበትም: የመጽሐፈን: ደነግራቸው:
ነበር።

፫፡ ኢየከፈተ: ኢየገለጸም: ለክርስቶስ:እንደተገ
ባው: ሕማማት: ደቀበል: ዘንድ: ከሙታንም: ደነ
ሣ: ዘንድ። እንደህም: ሲል። ደህ: ክርስቶስ:የሶስ:
ነው: እኔ: እርሱን:የማስተምራችሁ።

ሉቃ: ፳፬: ፳፯: ፵፮፡፡

፬፡ ከርሳቸውም: ሰዋች: አመኑ: ከጳውሎስና: ከ
ሲላስም: ጋራ: ሆኑ። ከአረማውያንም: እግዚአብ
ሔርን: ከሚፈሩ: ሰዋች: እጅግ: ብዙ። ከሴቶችም:
ከታላላቆች: ጥቂት: ደደደሉ።

፭፡ የማያምኑ: አደሁድ: ግን: ክፈ: ሰዋች: ከገቢ
ያ: ደሰበሰቡባቸው: ነበረ: አገረንም: አወኩ: በያሶ
ንም: ቤት: ቀመሙ: ሲቧቸው: ወደ: ሕዝብ: ደወስ
ድዋቸው: ዘንድ።

፮፡ ባለገኝዋቸውም: ጊዜ: ያሶንን: ከወንድሞች
ም: አንደንደን: ወደገፈ: አለቀች: ጉተቱ: እንደህ:
ሲሉም: ጮሁ። እለዚህ: ዓለሙን: ያወኩ: ደግሞ:
ከዚህ: መጡ። ም: ፲፯፡ ፳፫፡፡ ፩፡ ነገሥ: ፲፰፡ ፲፯፡፡

፯፡ ያሶንም:ተቀበላቸው። አሌህም: ሁሉ:የቄሣ
ርን: ትእዛዝ: የሚጣላ: ደደርጋሉ: እንደህ: ሲሉ።
ሌላ: ንጉሥ: አለ: የሶስ: የሚሉት። ሉቃ: ፳፫፡ ፪፡፡

፰፡ ሕዝብንም: ያገፈንም: አለቀች: አስታወኩ:
ደህነን: ነገር: በሰሙ: ጊዜ።

፱፡ ከያሶንም: ከቀረትም:ዋስ:ተቀበሉ: ለቀቅዋ
ቸውም።

፲፡ ወንድሞችም: የዚያን: ጊዜ: ጳውሎስንና:ሲላ
ስን: ወደ: ቤሮያ: አገር: በሌት: ሰደድዋቸው። ወደር
ስዋም: በመጡ: ጊዜ:ወደ: አደሁድ: መስጊድ:ገቡ።

፲፩፡ እርሳቸውም:የከበረ: ነበረ: በተሰሎንቄ: ከ
ሚያሩት: ደልቅ። ነገሩን: በፈጹም: ልባቸው: ተቀ
ብለዋልና። ሁለግዜም: መጻሕፍትን: *ደመረምረ:
ነበረ: ደህ:ነገር:እንደህ:እንደሆነ። *ኢሳ:፴፱፤ ፲፯፡፡
ሉቃ:፲፯፡ ፴፬፡፡ ዮሐ: ፭፡ ፴፱፡፡

፲፪፡ ከርሳቸውም:ብዙ: ሰዋች: አመኑ። ከዮናው
ያንም: አጅግ: ከተመረጡም: ሴቶች: ወንደችም:
ጥቂት: ያደደሉ።

፲፫፡ አደሁድም: በተሰሎንቄ:ያሉት:ባወቁ:ጊዜ:
ጳውሎስ:የእግዚአብሔርን:ነገር:በቤሮያ: ያስተም
ር: እንደ:ነበረ: ወደዚያ: ደግሞ: መጡ:ሰዋችንም·
አናወጡ። ፭፡ ተሰ: ፪፡ ፲፱፡፡

፲፬፡ በዚያን: ጊዜም:ወንድሞች: ጳውሎስን: ሰደ
ዱ: ወደ: ባሕር: ደሔድ:ዘንድ። ሲላስና: *ጢሞቴዎ
ስ:ግን: ከዚያው: ተቀመጡ። *ም: ፲፮፡ ፭፡፡

፲፭፡ ጳውሎስንም:የወሰዱት:ወደ: አቴና:ደዘው
ት: ሔዱ። ከርሱም: መልክት: በወሰዱ: ጊዜ: ወደ:
ሲላስና: ወደ: ጢሞቴዎስ: ፈጥነው: ወደርሱ: ደሔ
ዱ:ዘንድ:ወጡ።

፲፮፡ ጳውሎስ:ግን: በአቴና: ሲጠበቃቸው: ሰው
ነቱ: ታወከበት: በራሱ: አገሪቱ: ብዙ: ጣዖት: ስታመ
ልክ: እንደ: ነበረች: አደትዋልና።

፲፯፡ በጉባዔም: አደሁድን: ያስተምር: ነበረ: እግ
ዚአብሔርንም: የሚፈሩትን። በገቢያም: ሁለግዜ:
የሚያገኛቸውን።

፲፰፡ ከኤጲቁሮስም: ከአስጦኢኮችም: ፈሎሶፎ
ች: ወገን: ደጋደሉት:ነበረ። ም፣ደሻል. ደህ: *ነገር:
ዘራ: ደል: ዘንድ። ሌሎችም: አሉ። ባሂሶች: አማል
ክት:ስም:ያስተምረናል። በየሱስ:በትንሣኤውም:
ያስተምራቸው:ነበርና። *ዕ፡ ቀሮ: ፱፡ ፲፱፡፡

፲፱፡ ያዙትም: ወደ: አርዮስ: ፈሳስም: ወሰዱት:
እንደህ: ሲሉ። ደህነን: አዲስ: ትምህርት: የምትና
ገርበትን: እናውቅ: ዘንድ: ደቻለናልን።

፳፡ ባዲስ:ነገር: ጀርዋችነን: ታደክመሃልና። እኛ
ም:እንወደለን:እናውቅ: ዘንድ: ደህ: ነገር: ምንድ
ር:ነው።

፳፩፡ አቴናዉች:በዚያም:የነበረ:እንግደች: ጊዜያ
ቸውን: በሌላ: ነገር:እያሳልፈም:ነበሩና:አዲስ:ነገር:
ከመናገርና: ከመስማት: በቀር።

፳፪፡ ጳውሎስም: በአርዮስ: ፈሳስ: መሳከል: ቀ
መ: አለም። እላንት: የአቴና: ሰዎች: አያችኋለሁ:
በስራችሁ:ሁሉ:ጣዖታትን: ማምለክ:እንድታበዙ።

፳፫፡ እኔ፡ ሳልፈ፡ የምታመልኩትን፡ አይቻለሁና፡ መሠዊያም፡ አገኘሁ፡በርሱ፡ የተጻፈ፡ የሚል። ለማ ይታወቅ፡ አምላክ። ይህም፡ የምታመልኩት፡የማታ ውቁትም፡ ይህን፡ እኔ፡ አነግራችኋለሁ።

፳፬፡ ዓለሙን፡ የፈጠረ፡አምላክ፡ በርሰዋ፡ያለው ንም፡ ሁሉ። እርሱ፡ የሰማይና፡ የምድር፡ ጌታ፡ነውና፡ አደያርም፡ እጅ፡ በሰራው፡ መቅደስ። ም፡፯፡ ፴፰፡፡

፳፭፡ የሰው፡እጅም፡ አያገለግለውም፡ *ማነንም፡ አያሻም። እርሱ፡ለሁሉ፡ ሕይወትና፡ትንፈሽ፡ ይሰጣ ልና፡ ያላቸውንም፡ነገር፡ሁሉ። *መዝ፡ ፱፡ ፶፡፡

፳፮፡ እርሱም፡ ካንድ፡ ደም፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ ፈ ጠረ፡ በምድር፡ ፊት፡ ሁሉ፡ ላይ፡ ይኖሩ፡ ዘንድ። ዘመ ኑንም፡ ለርሳቸው፡ ሠራ፡ ከጥንት፡ ፲ምሮ፡ ሰፈራቸ ውንም፡ *ይኖሩበት፡ዘንድ። *ዘያግ፡ ፴፪፡ ፷፡፡

፳፯፡ እግዚአብሔርን፡ አንዲሹ፡ አንዲፈልጉም፡ ምናልባት፡ ያገኙት፡ አንደ፡ሆን። ነገር፡ግን፡ ከኛ፡ ከሁ ላችን፡ የራቀ፡ አይደለም።

፳፰፡ እኛ፡ በርሱ፡ አንኖራለንና፡ አንንቀሳቀሳለን ም፡ አንባኾለንም። ከላንት፡አዋቀች፡ የቅኔ፡ አድራሳ ች፡ ደግሞ፡ አንደተናገሩ። እኛ፡ ዘመደቹ፡ነንና።

፳፱፡ የአግዚአብሔር፡ ዘመደች፡ከሆነ፡አደገባም፡ እንል፡ ዘንድ፡ ወርቅም፡ ሆነ፡ ብርና፡ ደንጊያ፡ ሆነ፡ በሰ ው፡ ብልሣት፡ ባሳቡም፡ የተቀረጸ፡ የተጸረበም፡ ሰራ፡ ሆነ፡ ይህ፡ አምላክን፡ ይመስላል። *ዘፍጥ፡ ፭፡ ፲፯፡፡ ኢሳ፡ ፵፡ ፲፰፡፡

፴፡ ያነንም፡ የድንቍርናውን፡ *ወራት፡ አግዚአብ ሔር፡ አሳለፈው። አሁን፡ ግን፡ሰውን፡ ሁሉ፡በየቦታቸ ው፡ ተአዘዘ፡ ንሰሐ፡ ይገቡ፡ ዘንድ። *ም፡ ፲፱፡ ፲፯፡፡ ተሉቃ፡ ፳፬፡ ፵፯፡፡

፴፩፡ በዓለሙ፡የሚፈርድበትን፡ ቀን፡ አቁምዋል ና፡ በቅን፡ ፈርድ፡ በዚያ፡ ሰው፡ እጅ፡ በመረጠው። ስ ለዚህም፡ የታመነ፡ ምስክር፡ለሁሉ፡ሰጠው፡እርሱን፡ በማስነሣቱ፡ ከሙታን። ሮሚ፡ ፲፡ ፱፱፡፡

፴፪፡ በሙታንም፡መነሣት፡በሰሙ፡ጊዜ፡እኩሌታ ቸው፡ *አፈዙ፡ እኩሌታቸውም፡ አሉ። ይህነንም፡ ደግሞ፡ እንሰማሃለን። *፭፡ ቀሮ፡ ፭፡ ፵፫፡፡

፴፫፡ እንደሁም፡ወጣ፡ጳውሎስ፡በመካከላቸው።

፴፬፡ ከሰዎች፡ ግን፡ተከፈለው፡ከርሱ፡ጋራ፡አንድ፡ ሆኑ፡ አመኑም። ከርሳቸውም፡ አንዲ፡ ዲዮናስዮስ፡ ነበር፡የአርዮስ፡ ፈጎስ፡ፈራጅ። አንዲት፡ ሴትም፡ስ ምዋን፡ደማሪስ፡የሚልዋት። ሌሎችም፡ከርሳቸው፡ ጋራ።

ምዕራፍ፡ ፲፰፡

፩፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ጳውሎስ፡ ከአቴና፡ወጣ፡ወደ፡ ቀሮንቶስም፡ መጣ።

፪፡ ከዚያም፡ አንድ፡ አይሁዳዊ፡ አገኖ፡ ስሙም፡ አኪላስ፡ አገራም፡ ጶንጦስ፡የሚሆን። አርሱም፡ከጥ ቂት፡ወራት፡ በፊት፡ ከኢጣልያ፡ መጣ፡ ከጵርስኪላ፡ ከምስቹ፡ ጋራ። አቅሉዲዮስ፡ አዞ፡ ነበርና፡ አይሁድ፡ ከሮሜ፡ ይወጡ፡ ዘንድ። ሮሚ፡ ፲፮፡ ፫፡፡

፫፡ ከርሳቸውም፡ ጋራ፡ ተቀመጠ፡ *ይሰራም፡ነበር፡ ከሰራቸው፡ ወገን፡ ነበረና። ሰራቸውም፡ ድንኳን፡ መ ስፈት፡ ነበረ። *፩፡ ቀሮ፡ ፱፡ ፲፪፡፡

፬፡ ቅደሚ፡ ቅደሚም፡ በመሰኒድ፡ ይናገር፡ ነበር፡ አይሁድንም፡ አረማውያንንም፡ አሺ፡ ያሰኝ፡ ነበረ።

፭፡ *ሲላስና፡ ጢሞቴዎስም፡ ከመቄደንያ፡ በመ ጡ፡ ጊዜ፡ ጳውሎስ፡ በመንፈስ፡ በረታ፡ ለአይሁድ፡ መሰከረ፡ የሱስ፡ ክርክቶስ፡ አንደ፡ ሆነ።

*ም፡ ፲፯፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

፮፡ እርሳቸው፡ግን፡በተቋቋሙ፡በተሳደቡም፡ጊዜ፡ ልብሱን፡ *አረገፈ፡አላቸውም።ደማቾሁ፡በራሳቸሁ፡ ይሁን። እኔ፡ ንጹህ፡ ነኝ። ከንጊይህ፡ ወደህ፡ ወደ፡ አ ሕዛብ፡ አሔደለሁ። *ም፡ ፲፫፡ ፶፭፡፡ ፳፡ ፳፯፡፡

፯፡ ከዚያም፡ ወጥቶ፡ ወደንጅ፡ ሰው፡ ቤት፡ ገባ፡ ሰ ሙ፡ ዮስጦስ፡ለአግዚአብሔር፡የሚገዛ። ቤቱም፡ ወ ደ፡ መሰኒድ፡ የቀረበ፡ነበር።

፰፡ ክሪስጰስም፡ የመሰኒደ፡ አለቃ፡ በጌታ፡ አመነ፡ ከቤቱ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ጋራ።ብዙም፡ሰዎች፡ከቀሮንቶስ፡ ወገን፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ አመኑ፡ ተጠመቁም።

፱፡ ጌታም፡ በሌት፡ በራእይ፡ ጳውሎስን፡ አለው። አትፈራ፡ ነገር፡ ግን፡ ተናገር፡ ዝምም፡ አትበል።

፩፡ ቀሮ፡ ፪፡ ፫፡፡

፲፡ እኔ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ነኝና። ማንም፡ አይነካህም፡ ክፈ፡ ሊያደርግብህ። በዚህ፡ አገር፡ ተአጅግ፡ ወገን፡ አ ለኝና። *ኤር፡ ፩፡ ፰፡፡ ተሆሴ፡ ፪፡ ፲፫፡፡ ዮሐ፡ ፲፡ ፲፮፡፡

፲፩፡ በቀርንቶስም፡ አመት፡ ከስድስት፡ ወር፡ ተቀ መጠ፡ የአግዚአብሔርን፡ ነገር፡ ሲያስተምር፡ በመካ ከላቸው።

፲፪፡ ጋሊዮንም፡ በአካይያ፡ ላይ፡ በተሾመ፡ጊዜ፡ አ ይሁድ፡ ተባብረው፡ በጳውሎስ፡ ተነሡበት፡ ወደ፡ መ ቀመጫውም፡ አመጡት።

፲፫፡ አንደህ፡ ሲሉ። ይህ፡ ሰዎችን፡ ያባብላል፡ አግ ዚአብሔርን፡ ያመልኩ፡ ዘንድ፡ በሕግ፡ ላይ።

፲፬፡ ጳውሎስም፡ አፈኝ፡ ደገልጽ፡ ዘንድ፡ በወደደ፡ ጊዜ፡ጋሊዮን፡ አይሁድን፡ አላቸው። በደል፡ ቢሆን፡ ወ ይም፡ ሌላ፡ ክፈ፡ ነገር፡ አላንት፡ አይሁድ፡ መልካም፡ ነበረ፡ አሰማችሁ፡ ዘንድ። ም፡ ፳፭፡ ፲፩፡—፲፰፡፡

፲፭፡ ነገር፡ግን፡መጣበት፡ከሆነ፡ሰለ፡ነገር፡ ሰለ፡ ሰም ም፡ ሰለ፡ሕጋችሁም፡ አላንት፡ *አወቁ።እኔ፡ አልወድ ም፡ በዚህ፡ነገር፡ ፈራጅ፡ አሆን፡ ዘንድ።

*ማቴ፡ ፳፯፡ ፲፱፡፡ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፴፩፡፡

፲፮፡ ከዚያ፡ ወደ፡ያም፡ ከወንበረ፡ ፈት ፡ አስወጣ ቸው።

፲፯፡ ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ *ሶስቴንስን፡ያዙት፡የመሰኒ ደን፡ አለቃ፡ በወንበረ፡ ፈትም፡ መቱት። ጋልዮንም፡ በዚህ፡ነገር፡ሁሉ፡አንደ፡ት፡አላለም። *፭ቀሮ፡ ፭፡ ፭፡፡

፲፰፡ ጳውሎስ፡ግን፡ደግሞ፡አጅግ፡ቀን፡ተቀመጠ።

ከዚያም፡ በኋላ፡ ወንድሞችን፡ተሰናበተና፡ወደ፡ ሶር ያ፡ሔደ። ከርሱም፡ጋራ፡ጵርስኪላስ፡ አኪላስም፡ *ፊ ሱን፡ በተላጨ፡ ጊዜ፡ በክንክሬያ ። ስለት፡ ነበረበትና።

*ም፡ ፳፭፡ ፳፱፡፡ ዘኁል፡ ፮፡ ፱፡ ፲፰፡፡

፲፱፡ ወደ፡ ኤፌሶንም ፡ ደረሰ ፡ እሊያንም ፡ ከዚያ ው፡ተዋቸው። እርሱ፡ ግን፡ወደ፡ መስኪድ፡ ገባ፡ ለአይ ሁድም፡ ተናገረ።

፳፡ እርሳቸውም፡ በለመኑት፡ ጊዜ፡እጅግ፡ ቀን፡ከ ርሳቸው፡ ዘንድ፡ እንዲ ቀመጥ፡ ልመናቸውን ፡ አልሰ ማም።

፳፩፡ ተሰናበታቸው፡ እንጅ፡ እንደ ህ፡ ሲል። ከተ፡ ደገባቸል፡የሚመጣውን፡በሣል፡ *በየሩሳሌም፡አደር ግ፡ዘንድ። ነገር፡ግን፡ ወደላንት፡ እመለሳለሁ፡ በእግዚ አብሔር፡ ፈቃድ። ከኤፌሶንም፡ ወጣ።

*ል፡ ቀሮ፡ ፱፡ ፲፬፡፡ ዕብ፡ ፮፡ ፫፡፡ ያዕ፡ ፱፡ ፲፭፡፡

፳፪፡ ወደ፡ ቄሣርያ ፡ በመጣ፡ጊዜ፡ ከዚያ፡ ወጣ፡ ለ ቤተ፡ክርስቲያንም፡ ሰላም፡ ሰጠ፡ ወደ፡ አንጾክያም፡ ወረደ።

፳፫፡ ከዚያም፡አያሌ፡ ቀን፡ከተቀመጠ፡ በኋላ፡ወ ጣ፡በገላትያና፡ በፍሪጊያም፡ አገር፡ ሁሉ፡ አለፈ፡ደቀ፡ መዛሙርትንም፡ ሁሉ፡አጸና።

፳፬፡ አንድም፡አይሁዲ፡ነበረ፡ ስሙን፡ አጵሎስ፡ የሚሉት፡አገሬም፡አስክንድርያ። ተናጋሪ፡ ሰው። መ ጽሐፍ፡ለመተርጕምም፡ብርቱ፡ነበረ። ፭፡ቀር፡ር፡፯፡፡

፳፭፡ ይህ፡በእግዚአብሔር፡መንገድ፡ የተማረ፡ነበ ር፡በመንፈስም፡የሚቃጠል፡ነበረ። በጌታም፡ነገር፡ ይ ናገር፡ ያስተምርም፡ነበረ። የዮሐንስን፡ም ጥመቀት፡ ብቻ፡ ያውቅ፡ ነበረ።

፳፮፡ ይህም፡ በመጀኪድ፡ ነገሩን፡ ይገልጥ፡ ጀመረ። አኪላስና፡ጵርስኪላም፡ በሰሙት፡ ጊዜ፡ ወሰዲት፡ የ እግዚአብሔርንም ፡ መንገድ ፡ አስታወቁት ፡ እጅግ፡ ፈጹም፡ ማስታወቅ።

፳፯፡ እርሱም፡ ወደ፡አካይያ፡ ማለፍ፡ በወደደ፡ ጊ ዜ፡ወንድሞች፡ ወደ፡ደቀ፡ መዛሙርት፡ስለርሱ፡ ጻፈ፡ ለመንዎቸውም ፡ ደቀበሉት ፡ ዘንድ ። ወደርሳቸው ም፡በመጣ፡ ጊዜ፡ እጅግ፡ ጠቀመ፡ በጸጋ፡ ላመኑት፡ ሰ ዎች።

፳፰፡ አይሁድን፡ በሁሉ፡ ፈት፡ ይገሠጽ፡ ነበርና፡ ጽ ኑ፡ተግሣጽ፡ከመጽሐፍ፡ኢየገለጠ፡ የሱስ፡ክርስቶስ፡ አንደ፡ሆነ።

ም፡ ፲፡ ፳፪፡፡ ፲፯፡ ፫፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፱፡

፩፡ አጵሎስም፡ በቀርንቶስ፡ ሳለ፡ ጳውሎስ ፡ የዚያ ን፡አገር፡ላይ፡ ላዶን፡ ደዞር፡ ነበር፡ወደ፡*ኤፌሶንም፡መ ጣ፡ደቀ፡መዛሙርትም፡አገኘ። *ም፡ ፲፰፡ ፲፱፡ ፳፭፡፡

፪፡ አላቸውም።*መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተቀበላችሁ ን፡ባመናችሁ፡ጊዜ።እርሳቸው፡ግን፡ አሉት። መቀበል ስ፡ ደቅርያ፡ ተመንፈስ፡ቅዱስ፡ እንደሉ፡ ስንኂ፡ አልሰ ማነም።

*ም፡ ፲፡፵፯፡፡ ፕሮሐ፡ ፯፡ ፴፱፡፡

፫፡ አላቸውም።በምን፡ተጠመቃችሁ።እርሳቸው ም፡ አሉ። በዮሐንስ፡ ጥምቀት።

፬፡ ጳውሎስም፡አለ።*ዮሐንስስ፡በንስሐ፡ጥምቀ ት፡እጠመቀ፡ለሕዝብ፡እንደህ፡ ሲል፡ ያምኑ፡ዘንድ፡ ከርሱ፡ በኋላ፡ በሚመጣው። ያውም፡ በክርስቶስ፡ የ ሱስ።

*ማቴ፡ ፫፡ ፲፩፡፡

፭፡ ደህንም ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ተጠመቁ ፡ በጌታ ፡ በየ ሱስ።

፮፡ ጳውሎስም፡ እጂን፡ በጫነባቸው፡ ጊዜ፡ መንፈ ስ፡ቅዱስ፡ ወረደላቸው። ባዲስ፡ቋንቋም፡ ተናገሩ፡ ት ንቢትም፡ ተናገሩ። ም፡ ፳፡ ፲፯፡፡ ፲፡ ፴፱፡ ፵፱፡፡

፯፡ ሰዉችም፡አሠራ፡ሁለት፡ያህል፡ ነበሩ።

፰፡ ወደ፡ መስኪድም፡ በገባ፡ ጊዜ፡ በግልጥ፡ ይናገር፡ ነበር፡ ሶስት፡ ወርም፡ የሚያህል ፡ ተቀመጠ፡ ሲያስተ ምር፡ሲረዳቸውም፡ ስለ፡እግዚአብሔር፡ ስለ፡ መንግ ሥቱ፡ነገር።

፱፡ ሰዉችም፡ ከርሳቸው ፡ *እምቢ፡ ቢሉ ፡ ባያመኑ ም፡ መንገዲንም፡ ተቢሰድቡ፡ በጉባኤው፡ ፊት። ከር ሳቸው፡ራቀ፡ደቀ፡መዛሙርትንም፡ ከርሳቸው፡ ለየ፡ ሁለግዜም ፡ደነባር፡ ነበረ፡ ባንድ፡ ሰው፡ ቤት፡ ስሙን፡ ጢራኑስ ፡ የሚሉት ፡ እርሱም፡ መምህር፡ የሚሆን።

*ዘ፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፭፡፡ ተም፡ ፫፡ ፱፡፡

፲፡ ይህም፡ ሆነ፡ ሁለት ፡ አመት፡ በእስያ ፡ የተቀመ ጡት፡ሁሉ፡የጌታን፡ የየሱስን፡ ነገር፡ አሰኪሰሙ፡ ድረ ስ። እርሳቸውም፡ አይሁድ፡ አረማውያንም።

፲፩፡ እግዚአብሔርም፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ታላቅ፡ ተአምራ ት፡ያደርግ፡ ነበረ፡ በጳውሎስ፡ እጅ። ም፡ ፲፱፡ ፫፡፡

፲፪፡ ከሰውነቱ፡ መጠምጠሚያውን ፡ ሌላ ፡ ልብስ ም፡ አስኪወስዲ፡ ድረስ፡ በድውያንም፡ ላይ፡ አስኪ ቱት፡ ድረስ ። ከርሳቸውም ፡ ደቂያቸው ፡ ደወጣ፡ ነበረ ።ደግሞም፡ አጋንንት፡ ክፉ፡ ክፈ፡ የሆኑ፡ ከርሳቸ ው፡ ደወጡ፡ ነበሩ። ም፡ ፭፡ ፲፭፡፡

፲፫፡ ከአይሁድም ፡ ሰዉች፡ መጡ፡ አስማት፡ ኢያ ደረጉ፡ የሚዞረ። የጌታንም፡ የየሱስን ፡ ስም፡ ደጸረ፡ ጀመረ፡ክፉ፡ ክፈ፡ አጋንንት፡ ባሉባቸው፡ ላይ። እንደ ህ፡ሲሉ።እኛ፡ምላችኋለን፡ በየሱስ፡ ጳውሎስ፡ በሚያ ስተምርበት። ሉቃ፡ ፱፡ ፶፬፡፡

፲፬፡ እንደህም፡ ያደረጉት፡ ሰዉች፡ የአስቄዋ፡ የአ ይሁዲዊ፡ የካህናቱ፡አለቃ፡ ልጆች፡ነበረ፡ ሞጥራቸው ም፡ ሰባት፡ ነበር።

፲፭፡ ክፈውም፡ጋኔን፡መለሰ፡እኝይህም፡አለ።የሱ ስንስ፡ አውቀዋለሁ ፡ ጳውሎስንም፡ ተረድቸዋለሁ፡ ነገር፡ ግን፡ አላንት፡ አለማን፡ናችሁ።

፲፮፡ ያ፡ሰውም፡ክፈ፡ጋኔን፡ያለበቱ፡ሮጠባቸው፡ገዛ ቸውም፡አስነፈቸውም። ከዚያ፡ቤት፡ ራቁታቸውን፡ ተሙለው ፡ አስኪሸሹ፡ ድረስ።

፲፯፡ ይህም፡በኤፌሶን፡በሚኖረ፡በአይሁድና፡በአ ረማውያን፡ ሁሉ፡ ዘንድ፡ ታወቀ፡ በሁሉም፡ ላይ፡ ፈር

ሳት፡ ወደቀባቸው፡ የጌታም፡ የየሱስ፡ ሳም፡ ታላቅ፡ ሆነ።
ም፡ ፳፡ ፳፡ ፲፩።

፲፰፡ ካመኑትም፡ እጅግ፡ ሰዎች፡ ደመጡ፡ ነበር፡ ኃጢአታቸውን፡ ኢያስታውቁ፡ ያደረጉትንም፡ ሊያተ ናገሩ።

፲፱፡ እጅግም፡ ሰዎች፡ አስማት፡ ያደረጉ፡ መጽሐ ፈቸውን፡ አከማቹ፡ በሰው፡ ሁሉ፡ ፊትም፡ አቃጠሉ ት። ዋጋውንም፡ ቍጠረ፡ አገኙትም፡ አምሳ፡ ሽህ፡ ብር።

፳፡ እንደሁ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ በኃይል፡ ያድ ግ፡ደጸየም፡ነበር።
ም፡ ፯፡ ፮።

፳፩፡ ደህም፡ነገር፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡ጳውሎስ፡ በመ ነፈስ፡አሰበ፡ወደ፡መቄዶንያና፡ወደ፡አካይያ፡ካለፈ፡ በኋላ፡ወደ፡የሩሳሌም፡ደሔድ፡ዘንድ፡እንደሀ፡ሲል። ወደዚያም፡ ከሄረሰሁ፡ በኋላ፡ ደግሞ፡ *ሮሜን፡ አደ፡ ዘንድ፡ደገባቸል።
*ም፡ ፳፫፡ ፲፭።

፳፪፡ ከሚያገለግሉትም፡ ሁለት፡ሰዎች፡ ወደ፡ መ ቄዶንያ፡ላከ።እርሳቸውም፡ *ጢሞቴዎሰና፡ ተኤራስ ጦስ።እርሱ፡ ግን፡በእስያ፡ አያሌ፡ ቀን፡ ተቀመጠ።
*ም፡ ፲፯፡ ፲፱።

፳፫፡ በዚያም፡ ወራት፡ ሁከት፡ ሆነ፡ ጥቂት፡ ያደደ ለ፡ስለዚህ፡ መንገድ።
ቍ፡ ፱።
፪፡ ቀር፡ ፭፡ ፳።

፳፬፡ አንድ፡ሰው፡ነበርና፡ስሙን፡ድሜጥሮስ፡የሚ ሉት፡ብር፡ሰሪ።የብርም፡ታናሽ፡ መቅደስ፡ ለአርጤም ስ፡ይሰራ፡ነበረ፡አንጥረኞችንም፡ *አጅግ፡ደረባ፡ነበር።
*ም፡ ፲፯፡ ፲፯፡

፳፭፡ አርሱም፡ ደህንን፡ስራ፡ የሚሰሪን፡ ሁሉ፡ ሰበ ሰበ፡አላቸውም።አላንት፡ሰዎች፡ ታውቃላችሁ፡ ጥቅ ማችን፡ ከዚህ፡ ስራ፡ እንደ፡ ሆነ።

፳፮፡ አደታችኋልም፡ ሰማታችኋልም፡ በኤፌሶን፡ ብቻ፡አደሄለም፡በአስያ፡ ሁሉ፡ አንጅ። ደህ፡ ጳውሎ ስ፡ አጅግ፡ ሰዎች፡ አንደ፡ ረደ፡ አንደ፡ መለሰም፡ አን ደህ፡ ሲል። አሌህ፡ በጅ፡ የተሰራ፡ አማልክት፡ አደደ ሉም።

፳፯፡ ደህም፡ ብቻ፡ የሚደስጨንቀን፡ አደደለም፡ ስራችን፡ የተናቀ፡ እንደ፡ ሆነ። የታላቂቱ፡ የአርጤም ስ፡ መቅደስ፡ ምናምን፡ ደሆነል፡ አንጅ። ታላቅነትዋ ም፡ ደገባ፡ ደቀራፉ፡ አስያ፡ሁሉ፡ ዓለሙም፡ የሚያ መልካት።

፳፰፡ ደህንም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ቍጣ፡ መለባቸው፡ ሡሁም፡ እንደህ፡ ሲሉ። ታላቅ፡ ናት፡ የኤፊሶን፡ አር ጤምስ።

፳፱፡ አገረም፡ ሁሉ፡ ተሸበረ፡ ሁሉም፡ ወደ፡ ጨወ ታ፡ ስፍራ፡ ፈጥነው፡ መጡ። ጋይዮንንና፡ አርስጠርኮ ሰንም፡የመቄዶንያን፡ሰዎች፡ የጳውሎስን፡ ባልንጀሮ ች፡ነጥቀው፡ከርሳቸው፡ጋራ፡ወሰደ።
፱፡ ቀር፡ ፭፡ ፳።

፴፡ ጳውሎስ፡ግን፡ ወደ፡ ሕዝቡ፡ ደገባ፡ ዘንድ፡ በወ ደደ፡ ጊዜ፡ ደቀ፡ መዘሙርት፡ አልተውትም።

፴፩፡ ሌሎቹም፡ከእስያ፡አለቀች፡ ወደጀቹ፡ላኩበ ት፡ሲለምኑ፡ወደ፡ጨወታ፡ ስፍረ፡መሔድ፡እንደደደ ፈር።

፴፪፡ ሌሎችም፡በሌላ፡ነገር፡ደጮሁ፡ነበረ፡ጉባኤው ም፡ ደንግጠው፡ ነበረ፡ የሚበልጡትም፡ አላወቁም፡ ስለ፡ምን፡ ተሰበሰቡ።

፴፫፡ ከሕዝቡም፡እስክንድሮስን፡ አወጡት፡ አደ ሁድ፡ በፊት፡ ሲያቀመት።እስክንድሮስ፡ ግን፡በጀ፡ ጠቀሰ፡ ለሕዝብ፡ ደናገር፡ ዘንድ፡ ወደ።

፴፬፡ ባወቁም፡ጊዜ፡አደሁደዊ፡ አንደ፡ሆነ፡ ከሰዉ ች፡ጩኸት፡ሆነ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ ደሆን፡ ኢየሡሁ፡ እን ደህ፡ ሲሉ። ታላቅ፡ ናት፡ አርጤምስ፡ የኤፈሶኒቱ።

፴፭፡ የአገር፡ ጻፌ፡ ግን፡ ሰዉችን፡ ዝም፡ አሰኛቸ ው፡ እንደህ፡ ሲል። አላንት፡ የኤፈሶን፡ ሰዉች ፡ ማነ ው፡የማያውቅ፡ሰው፡የኤፈሶን፡ ሰዉች፡አገር፡ ታላቂ ቱን፡ አርጤምስን፡ እንድታመልክ፡ ጣዖትዋንም፡ ከ ሰማደ፡ የወረደውን።

፴፮፡ ደህም፡ የማደከረከረበት፡ነገር፡ነውና፡ሰለዚ ህ፡ዝም፡ ትሉ፡ዘንድ፡ ደገባችኋል፡ ምንም፡ በችኩላ፡ ሳታድርጉ።

፴፯፡ አሌህን፡ ሰዉች፡ አመዋታችኋልና፡ የመቅደ ሳችሁን፡ አቃ ፡ ያልሰረቁ፡ አመላካችሁንም፡ ያልሰ ደቡ።

፴፰፡ ድሜጥሮስና፡ ከርሱ ፡ ጋራ፡ ያሉ፡ ሰራተኖች፡ ግን፡ በማንም፡ላደ፡ነገር፡ እንደላቸው፡ እነሆ፡ ፈርድ፡ አለ፡አለቀችም፡አሉ።እርሱ፡ በርሳቸው፡ ደከራከረ።

፴፱፡ ሌላ፡ነገር፡ግን፡ ትሹ፡ እንደ፡ ሆን፡ በጉባኤው፡ ደፈታል፡ እንደ፡ ሕግ፡ በሚሰበሰቡት።

፵፡ ፈርሳት፡ነውና፡እኖ፡ዛሬ፡ በሆነ፡ነገር፡ስለ፡ ዓመ ፃ፡እንከሰስ፡ዘንድ፡ ምክንያትም፡ አልተገኘም፡ እን መልስበት ፡ የምንችል ፡ ስለዚህ ፡ መራወጥ ። ደህን ም፡ብሎ፡ ሕዝቡን፡ ሰደደ።

ምዕራፍ፡ ፳፡

፩፡ ሁከቱም፡ ጸጥ፡ካለ፡በኋላ፡ ጳውሎስ፡ ደቀ፡ መ ዛሙርትን፡ጸራ። ከተሳለማቸውም፡ *በኋላ፡ወደ፡መ ቄዶንያ፡ ደሔድ፡ ዘንድ፡ ወጣ።
*፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፫።

፪፡ ደነንም፡ስፍራ፡ በዞረ፡ጊዜ፡በብዙ፡ ነገርም፡ ባጸ ናቸው፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ዕርዕ፡ መጣ።

፫፡ ከዚያም፡ሶስት፡ወር፡ ከተቀመጠ፡ በኋላ፡ከፈ፡ ምክርም፡ከአደሁድ፡በርሱ፡ላደ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ሶ ርያ፡ ለመሔድ፡ አሰቦ፡ሳለ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ፡ ደመለ ሰ፡ዘንድ፡ ፈቃደ፡ን፡ አቀመ።

፬፡ ከርሱም፡ጋራ፡ወጣ፡ሶሲጳዋሮስ፡ የጲሮስ፡ልጅ፡ *ከቤሮያ ። ከተሰሎንቄ፡ ወገንም፡ †አርስጠርኮስ፡ ሳ ኩንደሰም፡ጋይዮስም፡ ጢሞቴዎሰም፡ ከደርቤ፡ ወገ ን፡ የሚሆን ። ከእስያ፡ ወገን ፡ ግን፡ ጢኪዎስ ፡ ጠሮፊ ሞስም።
*ም፡ ፲፮፡ ፲፡ †ም፡ ፲፱፡ ፳፱።

፭፡ አሌህ፡አልፈው፡በጥሮአስ፡ቀዳነ።ም፡ ፲፮፡ ፮።

፮፡ እኖ፡ግን፡ከፈልጵዶስ፡ በባሕር፡ ሔድነ፡ከፊሲ

ካ፡ወራት፡በኋላ፡ወደ፡ጥሮአስም፡መጣ፥ከርሳቸው፡ዘንድ፡ሰባት፡ ቀን፡ ወደ፡ ተቀመጥነበት።

፯፡ ከሰንበታቱም ፡ *በመጀመርያው ፡ ቀን ፡ ደቀ፡ መዛሙርት ፡ ተከማችተው ፡ ሳሉ ፡ †እንጀራ፡ ይቀራ ፡ ሰ፡ ዘንድ፡ ጳውሎስ፡ ደሰብኅቸው ፡ ነበር ። በነገው ፡ የ ሚወጣ፡ነበርና።። ነገረንም፡አረዘመ፡እስከ፡መንፈቀ፡ ሌሊት። *፩፡ ቀር፡ ፲፯፡ ፪።። †ም፡ ፪፡ ሟ፪።። ሟ፯።።

፰፡ በነበርነበትም፡ቤተ፡ ንጉሥ፡እጅግ፡ መብራት፡ ነበረ።

፱፡ አንድ፡ ብላቴናም፡ ነበረ፡ ሰሙን፡ አውጢኮስ፡ የሚሉት፡ በመስኮት ፡ ተቀምጦ ። ታላቅ ፡ እንቅልፍ ም፡ ወሰደው ፡ ጳውሎስ፡ እጅግ፡ ነገር፡ ሲያስረዝም። እንቅልፍም፡ በበረታበት፡ ጊዜ፡ ከሶስተኛው፡ ደርብ፡ ወደ፡ታች፡ወደቀ፡ ሙተም፡ በርሱ፡ አነሡት።

፲፡ ጳውሎስም፡ወረደ፡ በላዩም፡ *ወደቀበት፡ አቀ ፈውም፡ አለም። አደንግጹ። ነፍሱ፡ አለችና።

*፩፡ ነገሥ፡ ፲፯፡ ፳፩።።

፲፩፡ ደግሞም፡ወጣ፡ እንጀራም፡ ቈረሰና፡ በላ፡ እ ጅግም፡ነገራቸው፡ እስኪጠጣ። እንደሀም፡ ወጣ።

፲፪፡ ብላቴናውንም፡ደህና፡ ሁና፡ወሰደት። ጥቂት፡ ደደደለ፡ ደስታም፡ ደሳላቸው።

፲፫፡ እኛ፡ ግን፡ ወደ፡ መርከብ፡ መጣ ፡ ወደ፡ አሶስ ም፡ ሰረርነ። ከዚያም፡ ጳውሎሰን፡ እንወሰደው። ዘን ድ፡አሰብነ። እንጂሁ፡ነግርነ፡ነበርና፡በግሬ፡ደሔድ፡ዘን ድ፡ አስቦ።

፲፬፡ በአሶስም ፡ ባገኘነው ፡ ጊዜ፡ ወሰድነው፡ ወደ፡ ሚጢሊኒም፡ ደዘነው፡ መጣ።

፲፭፡ ከዚያም፡ በባሕር ፡ ሰረርነ ፡ በሚመጣውም፡ ቀን፡በኪዶስ፡ፊት፡መልሕቅ፡ጣልነ። በነገውም፡ ወደ፡ ሳሞስ፡መጣ፡ በትሮጊሊዮም፡ተቀመጥነ፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ወደ፡ ሚሌጦስ፡ ደረስነ።

፲፮፡ ጳውሌስ፡ከኤፌሶን፡ ርቀ፡ያልፍ፡ ዘንድ፡ ወድ ዋልና፡እጅግ፡ዘመን፡እንደደቀመጥ፡በእስያ። ደፈጥ ን፡ነበርና፡ ቢቻለው፡ የጰንጠቀስጤን፡ ቀን፡ በየሩሳሌ ም፡ ደውል፡ ዘንድ። ም፡ ፲፰፡ ፳፭።። ፳፭፡ ፱፡ ፲፪።።

፲፯፡ ከሚሌጦስም፡ወደ፡ኤፌሶን፡ ላከ፡ የቤተ፡ ክ ርስቲያኒቱንም ፡ ሸማግሌችን።

፲፰፡ ወደርሱም፡በመጡ፡ጊዜ፡እላቸው። እላንት፡ ታውቃላችሁ፡ወደ፡እስያ፡ ከገባሁበት፡ከመጀመርያ፡ ቀን፡ ጀምረ፡ እንጂት፡ ነበርሁ፡ ከላንት፡ ጋራ፡ ዘመን፡ ሁሉ። ም፡ ፲፰፡ ፲፱።። ፲፱፡ ፲።።

፲፱፡ እግዚአብሔርን፡አገለግል፡ ነበርሁና፡በትሕት ና፡ሁሉ፡በብዙ፡እንብም፡በደረሰብኝም፡ፈተና፡በአደ ሁድ፡ መሸጉኖ። ቀ፡ ፫።።

፳፡ ከሚጠቅማላችሁም ፡ ነገ፡ አንደት፡ አላስቀ ረሁም፡ አነግራችሁ ፡ አስተምራችሁም፡ ነበርሁ፡ አን ጅ፡በጉባዔም፡ ሰቤትም።

፳፩፡ ስመሰክር፡ ለአደሁድ፡ ለአረማውያንም፡ወ ደ፡እግዚአብሔር ፡ በመመለስ ፡ በጌታችንም ፡ በየሱ ስ፡ክርስተስ፡ በማመን።

፳፪፡ አሁንም፡እኔ፡በመንፈስ፡ቅዷስ፡ ታሠረ፡እነ ሆ፡ወደ፡የሩሳሌም፡ አሔዷለሁ፡ በርስዋ፡ ምን፡ የሚ ሆንብኝን፡ ሳላውቅ። ም፡ ፲፰፡ ፳፩።። ፲፱፡ ፳፩።።

፳፫፡ መንፈስ፡ቅዷስ፡ግን፡ባገሬ፡ሁሉ፡ ደመሰክርል ኛል፡እንጂህ፡ ሲል። እሥራትና፡ መከራ፡ ደቀ፡ይሃልል። ም፡ ፱፡ ፲፮።። ፳፭፡ ፱፡ ፲፭።።

፳፬፡ ደር፡ግን፡ ደህን፡ ምክንያት፡ አድርጌ፡ አልቀ ኖረውም።ነፍሴም፡ ደግሞ፡ በኔ፡ ዘንድ፡ እንድትከበ ር፡አላሰብም፡ሩጫዬን፡አስክፈጽም፡ድረስ፡በደስታ፡ መልእክቴንም፡ከጌታ፡ከየሱስ፡ የተቀበልኋትን፡በአ ግዚአብሔር ፡ጸጋ ፡ወንጌልን ፡ እመሰክር ፡ ዘንድ።

ም፡ ፳፭፡ ፲፫።።

፳፭፡ አሁንም፡እነሆ፡ እኔ፡አውቃለሁ፡ ሁላችሁ፡ደ ግሞ፡ፊቴን፡እንደታዩ።አላንት፡የዘርኋችሁ፡ የእግዚ አብሔርን፡ መንግሥት፡ ሳስተምራችሁ።

፳፮፡ ስለዚህም፡ እኔ ፡ እመሰክርላችኋለሁ ፡ በዚ ህ፡ ቀን፡ ንጹህ፡ እንደ፡ ሆንሁ፡ ከሁላችሁ፡ደም።

ም፡ ፲፰፡ ፯።።

፳፯፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምክር ፡ ሁሉ ፡ አላንትን፡ ከማስተማር፡ አልተውሁምና።

፳፰፡ አሁንም፡ለራሳችሁ፡ተጠንቀቁ፡ለመንጋው ም፡ሁሉ፡ መንፈስ፡ ቅዷስ፡ በርሱ፡ላይ፡ ጠባቆች፡ አድ ርጎ፡የሾማችሁ፡የእግዚአብሔርን፡ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ትጠብቁ፡ዘንድ፡ አርሱ፡ በደሙ፡ የዋጀችን።

፩፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፲፮።። ፩፡ጴጥ፡ ፭፡ ፪።።

፳፱፡ ደህን፡እኔ፡አውቃለሁና፡ ከሔድሁ፡ በኋላ፡የ ሚያጠቁ፡ *ጅቦች፡ እንጂ ገቡባችሁ፡ ለመንጎች፡የማ ያዝኑ። *ማቴ፡ ፯፡ ፲፭።።

፴፡ ከበውሠጣችሁም፡የሚነሡ፡ሰዎች፡ አሉ፡ጠ ማማ፡ ነገር፡የሚያገረ፡ደቀ፡መዘሙርትን፡ ወደ፡ ኋላ ቸው፡ይሰቡ፡ ዘንድ።

፴፩፡ ስለዚህም፡ ንቁ፡ አስባችሁ፡ እንደልተውሁ፡ ሶሰት፡አመት፡ሌትና፡ቀን፡እላንትን፡በንብ፡ ከማስተ ማር፡ ካላንት፡ ኢያንደንደችሁ።

፴፪፡ አሁንም፡ ውንድሞቼ፡ ለእግዚአብሔር፡ አ ደራ፡ሰዋቻችኋለሁ፡ለጸጋውም፡ነገር፡ ያሰራችሁ፡ ዘን ድ፡የሚችል፡ርስትም፡ይሰጣችሁ፡ ዘንድ፡ ከቅዷሳን፡ ሁሉ፡ጋራ።

፴፫፡ ወርቅ፡ግን፡ብርም፡ሆነ፡ልብሰም፡ ሆነ፡ ከማን ም፡ አልሻሁም። ማቴ፡ ፲፡ ፮።። ፩፡ ቀር፡ ፱፡ ፲፩።። ፩፡ ሳሙኤ፡ ፲፪፡ ፫።።

፴፬፡ አላንትም ፡ ታውቃላችሁ፡ አሌሀ፡ እጅቼ፡ ለ ምሻው፡ነገር፡ከኔ፡ ጋራ፡ ላሉትም፡ እንደገለገሉ።

ም፡ ፲፰፡ ፫።። ፩፡ ቀር፡ ፱፡ ፲፪።። ፩፡ ተሰ፡ ፪፡ ሀ።።

፴፭፡ ሁሉንም፡ገለጥሁላችሁ።። እንደሁ፡እንጂ ገባ ችሁ፡ ትሰራ፡ ዘንድ፡ ለደካሞችም፡ ረዷት፡ ትሰጡ፡ዘ ንድ፡ የጌታን፡ የየሱስን፡ ቃል፡ አስባችሁ ። እርሱ፡ ብል

ዋልና። ከሚወስድ፡ ይልቅ፡ለሚሰጥ፡ ምስጋና፡ ይገባ ዋል።

፴፯፤ ይህንንም፡ ባለ፡ጊዜ፡ በጕልበቱ፡ ተንበረከከ፡ ከሁሉ፡ ጋራ፡ *ጸለየም። *ም፡ ፳፩፡ ፭፡፡

፴፯፤ ከሁሉም፡እጅግ፡ ልቅሶ፡ ሆነ፡ በጳውሎስም፡ አንገት፡ላይ፡ወድቀው፡ይሰሙት፡ ነበረ።

፴፰፤ ይልቁን፡ አዝነው፡ ባለው ፡ነገር ፡ እንኊይህ፡ ደግሞ፡ ፈቴን፡ አታዩም። አሰከ፡ መርከብም፡ ድረስ፡ ሸኙት።

ምዕራፍ፡ ፳፩፤

፩፤ ከርሳቸውም፡ከተለዩ፡በኋላ፡ እኛ፡ ሰረርነ፡ መንገድችንም፡አቅንተን፡ወደ፡ቆስ፡መጣ፡ በነገውም፡ ወደ፡ ሮሄስ፡ ከዚያም፡ ወደ፡ ጳጥራ።

፪፤ ወደ ፡ ፊንቄም፡ የሚያልፈ፡ መርከብ ፡ አገኘን፡ በርሱም፡ተቀመጥነና፡ ሔድነ።

፫፤ ቀጵርስም፡ ባየ፡ ጊዜ፡ በግራችን ፡ ተውነት፡ ወ ደ፡ ሶርያም፡ ሔድነ፡ ወደ፡ ጢሮስም፡ መጣ ። ከዚያ፡ መርከብ፡ ሸክሙን፡ የሚገለብጥ፡ ነበረና።

፬፤ ደቀ፡መዛሙርትንም፡ባገኘን፡ጊዜ፡ ከርሳቸው፡ ዘንድ፡ተቀመጥነ፡ሰባት፡ቀን።እርሳቸውም፡በመንፈ ስ፡ጳውሎስን፡አሉት፡ወደ፡የሩሳሌም፡እንኊይወጣ።

ቍ፡ ፲፭፤ ፲፪፡፡ ም፡ ፳፫ ፳፫፡፡

፭፤ ጊዜያችንንም፡ ፈጽመን፡ በተቀመጥነ፡ ጊዜ፡ ወ ጣነ፡ሔድነም። እርሳቸውም፡ሁሉ፡ ሸኙን፡ ከሴትቻቸ ው፡ ከልጆቻቸውም፡ ጋራ ፡ አስካገሬ ፡ ሜዿ ፡ ድረስ። ተንበረከክነም፡ በባሕር፡ ደር፡ ጸለይነም።

ም፡ ፳፫ ፳፯፡፡

፮፤ እርሱ፡በርሳችንም፡ተሰነባበትነ፡ወደ፡ መርከብ ም፡ ሰረርነ። አሌያም፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ ተመለሰ።

፯፤ እኛ፡ግን፡ከጢርስ፡ተነሥተን፡ባሳሕጊን፡ መንገ ድ፡በፈጸምነ፡ጊዜ፡ ወደ፡ ጵቶልማይስ፡ ወጣነ። ወንድ ሞችንም፡ እንኊት፡ ናቸሁ፡ አልነ ፡ከርሳቸውም፡ ዘን ድ፡ አንድ፡ ቀን፡ ተቀመጥነ።

፰፤ በነገውም፡ ወጥተነ፡ ወደ፡ቄሣርያ፡ መጣነ፡ ወ ደ፡ ወንጌላዊውም፡ ወደ፡ ፊልጶስ፡ ቤት፡ ገባነ። እርሱ ም፡ ከሰባቱ፡ አንድ፡ የሚሆን ። ወደርሱም ፡ ተቀመ ጥነ። ም፡ ፰፡ ፴፡፡

፱፤ ለዚህም፡ አራት፡ ሴቶች፡ ልጆች፡ ደናግል፡ ነቢ ት፡ትንቢት፡ የሚናገሩ። ም፡ ፱፡ ፲፯፡፡

፲፤ ከዚያም፡ እጅግ፡ ቀን፡ በተቀመጥነ፡ጊዜ፡ ከአይ ሁያ፡ አገር፡ ነቢይ፡ ሰው፡ወረደ፡ሰሙን፡ *አጋቦስ፡የሚ ሉት። *ም፡ ፲፩፡ ፳፰፡፡

፲፩፤ ወደኛም፡ መጣ፡የጳውሎስንም፡ መቀነት፡ ወ ሰደ፡ አጂንና፡እግሩንም፡አሠረበት፡አለም። ደሀነን፡ ነገር፡ ደላል፡ መንፈሰ፡ ቅዱስ። የዚህን፡ መቀነት፡ ባለ ቤት፡ ሰው፡ እንደሁ፡ አደሁድ፡ ያሥረታል፡ በየሩሳሌ ም፡ ለአሕዛብም፡ እጅ፡ አሳልፎ፡ ደሰጡታል።

ም፡ ፳፡ ፳፫፡፡

፲፪፤ ደህንንም፡ ነገር፡ በሰማነ፡ ጊዜ፡ እኛ፡ ያገሩም፡ ሰዎች፡ ለመነው፡ ወደ፡ የሩሳሌም፡ እንኊይወጣ።

ም፡ ፲፯፡ ፳፪፡፡

፲፫፤ ጳውሎስም፡ መለሰ፡ አለም። ምን፡ ታደርጋላ ችሁ፡ ለምንስ፡ ታለቅሳላችሁ፡ ልቤንም፡ ትሰብሪታላ ችሁ። እኔ፡የጨከንሁ፡ነኝና፡ ለሠራት፡ብቻ፡ አይደለ ም፡ ለሞትም፡ እንጂ፡ በየሩሳሌም፡ ሰለ፡ ጌታ፡ ሰለ፡ የሱስ፡ ስም። ም፡ ፳፡ ፳፱፡፡

፲፱፤ ባይታዘዘነም፡ ዝማልነ፡ እንኊህ፡ ሰንል። የጌ ታ፡ ፈቃድ፡ ትሁን።

፲፭፤ ከዚያችም፡ ቀን፡ በኋላ፡ የተዘጋጀነ፡ ወደ፡ የሩ ሳሌምም፡ ወጣነ።

፲፮፤ ከኖም፡ ጋራ፡ ደግሞ፡ ሰዎች፡ ከደቀ፡ መዛሙሙ ርት፡ ወገን፡ ከቄሣርያ፡ መጡ፡ አንድም፡ ሰው፡ ከነር ሳቸው፡ ጋራ፡ አመጡ፡ምናሶንን፡ የቀድሮያናሱን፡ የሽ መገለ፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ ከርሱ፡ ዘንድ፡ ያደርነ።

፲፯፤ ወደ፡ የሩሳሌምም፡ በደረስነ፡ ጊዜ፡ ወንድሞ ች፡ በደስታ፡ ተቀበሉነ።

፲፰፤ በነገውም፡ ጳውሎስ፡ከኛ፡ጋራ፡ ወደ፡ ያዕቆብ፡ ገባ፡ ሽማግሌችም፡ ሁሉ፡ ከዚያ፡ነበረ።

ም፡ ፲፭፡ ፲፫፡፡ ገላት፡ ፩፡ ፲፱፡፡

፲፱፤ በተገኛቸውም፡ ጊዜ፡ አጨወታቸው፡ ኢያን ድንኊቱ፡ እግዚአብሔር፡ ካደረጋት፡ ሰራ፡ በአሕዛብ፡ መካከል፡ በማገልገሉ።

፳፤ እርሳቸውም፡ ይህነን፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡እግዚአብ ሔርን፡አመሰገኑ።አሉትም።ታያለህ፡ወንድም፡ሆይ፡ ስንት፡ አእላፋት፡ናቸው፡ ከአይሁድ፡ያመኑ፡ እርሳቸ ውም፡ ሁሉ፡ ለኦሪት፡ የሚቀኑ፡ናቸው። ም፡ ፲፭፡ ፭፡፡

፳፭፤ ስላንተም፡ ሰምተዋል።በአሕዛብ፡ መካከል፡ ያሉትን፡ አይሁድን፡ ሁሉ።እንድታስተምር፡ከሙሴ፡ ሠርዓት፡ ይርቁ፡ ዘንድ፡ እንኊህ፡ ኢያልህ። ልጆቻቸ ውን፡ እንኊይገዝሩ፡ በሕግም፡ እንኊይሔዱ።

ም፡ ፲፯፡ ፫፡፡ ሮሜ፡ ፫፡ ፱፡፡

፳፱፤ እንኊህስ፡ምን፡ይሁን። የግድ፡ሕዝብ፡ሳሂ ሰበሰቡ፡ አይቀሩም። አንተ፡ እንኊ፡ መጣህ፡ ይሰማ ሉና።

፴፫፡አሁንም፡ይህነን፡የምንልህን፡አድርግ።ከኛ፡ዘን ድ፡አራት፡ሰዎች፡አሉ።በራሳቸው፡ስለት፡ያለባቸው።

፳፬፤ አሌህንም፡ ውሰድና፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ንጻ ገንዘብን፡ ስትሰጣቸው፡ራሳቸውን፡እንኊላጩ። እን ደህም፡ የሆነ፡ እንኊ፡ ሆን፡ ሁሉ፡ ያውቃሉ፡ ሰላንተ፡ የመጣላቸው፡ ወሬ፡ ሁሉ፡ አሰት፡ እንኊ፡ ሆነ፡ አንተ፡ እንኊ፡ ተሰማማህ፡ እንጂ፡ ሐግንም፡ ጠባቂ፡ እንኊ ሆንህ። ም፡ ፲፰፡ ፲፰፡፡

፳፭፤ ስላመኑት፡ አሕዛብ፡ ግን፡ እኛ፡ ላክነላቸው፡ አዘዝናቸውም፡ እንኊህ፡ ያሉ፡ነገር፡ እንኊይጠብቁ፡ ሰውነታቸውን፡ከመጠበቅ፡ በቀር፡ለጣዖት፡ ከታረደ ው፡ ከደምም፡ ከታነቀውም፡ ከዝሙትም።

ም፡ ፲፭፡ ፳፡ ፳፱፡፡

፳፯፡ የዚያን፡ጊዜም፡ጳውሎስ፡ ሰዎችን፡ ወሰደ፡ በነገውም፡ ነጻ፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ወደ፡ መቅደስም፡ ገባ፡ኢያወራ፡የመንጻቱን፡ ቀን፡ ፯ ጫ ሚ፡ ስለ፡ ሁሉ፡ ኢያንዳንዳቸው፡ *መሠዋዕት፡ እስኪ ሠው፡ድረስ።
*ዘኁል፡ ፮፡ ፲፫፡፡

፳፯፡ ሰባቱ፡ቀንም፡ ደፈጸመ፡ ዘንድ፡ በቀረበ፡ጊዜ፡ ከእስያ፡ የመጡ፡ አይሁድ፡ በመቅደስ፡ አዩት፡ሰዎች ንም፡ ሁሉ፡ አወኩ፡ አያቸውንም፡ ጣሉበት።

፳፰፡ ኢየሡሱ፡ እንደሀም፡ኢያሉ። አላንት፡ሰዎች፡ የእሥራኤል፡ ወገን፡ አርደ፡ነ። ደህ፡ ነው፡ ሁሉን፡ የሚያስተምር፡ ሰው፡በየስፈራው፡ሕዝባችነን፡የሚ ጣላ፡ትምህርት፡አሪትንም፡ደህንም፡ስፈራ።ቦኦው ደንንም፡ ደግሞ፡ ወደ፡ መቅደስ፡ አገባ፡ ደህንም፡የተ ቀደሰ፡ስፈራ፡አረከሰው። ም፡፮፡፲፱፡፡ ሕዝ፡ ፵፬፡፯፡፡

፳፱፡ አሰቀድመው፡ *ጥሮፈሞስን፡የኤፌሶኑን፡ባ ገር፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ አደተው፡ነበረ፡ን፡ጳውሎስም፡ ወደ፡ መቅደስ፡ ያገባው፡ መሰላቸው። *ም፡ ፳፡ ፱፡፡

፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፮፡፡

፴፡ ምሉው፡ አገር፡ ሁሉም፡ ታወከ፡ የሕዝብም፡ ሁሉ፡ መሬወጥ፡ሆነ። ጳውሎስንም፡ ያዙት፡ከመቅደ ስ፡ ወደ፡ ሚደም፡ አወጡት፡ የዚያን፡ ጊዜውም፡ደ ጀ.፡ ሁሉ፡ ተዘጋ።

፴፩፡ አርሶተውም፡ ሊገሉት፡ ሲቸ፡ ወደ፡የሻለቃ ው፡ በጭፈራ፡ ላደ፡ የተሾመ፡ወረ፡ደረሰ፡የፈ ሳሌም፡ ፈጽማ፡ አንደ፡ ታወከች።

፴፪፡ አርሶተም፡ በዚያው፡ጊዜ፡ ጭፈራ፡የመቶ፡አለ ቀችም፡ ወሰደ፡ ሲሮጥም፡ ደረሰባቸው። አርሳቸው፡ ግን፡ የሻለቃውን፡ ጭፈሮችንም፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ ጳውሎስ ን፡ ከመምታት፡ ተውት።

፴፫፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ የሻለቃው፡ ወደደሱ፡ ቀረበ፡ ያዘውም፡ በሁላት፡ ሰንሰለትም፡ ይታሠር፡ ዘንድ፡ አ ዘዘ፡ጠየቀም፡ ማን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ምንስ፡ አደረገ።
ም፡ ፳፡ ፳፫፡፡

፴፬፡ ከሕዝቡም፡ አንዱ፡ ደህን፡ሌላውም፡ ደነን፡ ነገር፡ ጮኸ። አርግጡን፡ ማወቅ፡ ባደቻለው፡ ስለ፡ ጩ ኸቱ፡ ብዛት፡ ወደደሬሽ፡ ደወሰደት፡ ዘንድ፡ አዘዘ።

፴፭፡ ወደ፡ መውጪውም፡በደረሰ፡ ጊዜ፡ጭፈሮች፡ አንደ፡ ተሸከሙት፡ ሆነ፡ ስለ፡ ሕዝቡ፡ ጭንቀት።

፴፮፡ የሕዝብ፡ብዛት፡ ደከተሉት፡ ነበርና፡ ኢየጨ ሁ፡አንደህም፡ ኢያሉ። አስነሣው።

፴፯፡ ወደደሬሽም፡ ሲወሰደት፡ጳውሎስ፡የሻለቃ ውን፡ አለው። ትፈቅድልኛለህን፡ አንድ፡ ነገር፡ብነግር ህ። አርሱም፡ አለ። የፅርዕ፡ ቋንቋ፡ ታውቃለህን።

፴፰፡ አንተ፡ የመሠር፡ ሰው፡ አደደለህምን፡ ከዚ ህ፡ ዘመን፡ አሰቀድመህ፡ ሁከት፡ ያደርገህ፡ ወደ፡ ም ድረ፡ በደስ፡ አራት፡ ሽህ፡ በተንኩል፡ ገሂዮችን፡ ያወ ጣህ።

፴፱፡ ጳውሎስም፡ አለ። እኔስ፡ አይሁዲ፡ ሰው፡ ነኝ፡ አገረ፡ም፡ *ጠርሴስ፡ ነው፡ የከበረ፡ ከተማ፡ የሚ ሆን፡በቂልቅያ፡ ምድር።አለምንላለሁ፡ አንድትታወ ኝ፡ ለሕዝቡ፡ አነግር፡ ዘንድ።
*ም፡ ፱፡ ፲፭፡፡

፴፡ በተወለትም፡ጊዜ፡ጳውሎስ፡በመድረኩ፡ላደ፡ ቀመ፡ ሕዝቡንም፡ በጀ.፡ ጠቀሰ። አጅግም፡ ጸጥታ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡በዕብራይስጥ፡ቋንቋ፡ ነገራቸው፡አንደህ፡ ሲል።
ም፡ ፲፪፡ ፲፯፡፡ ፲፫፡ ፲፯፡፡ ፲፱፡ ፴፫፡፡

ምዕራፍ፡ ፳፪፡

፩፡ አላንት፡ሰዎች፡ወንድሞች፡አባቶችም፡ነገሬን፡ ስመ፡ ዛሬ፡ ለላንት፡ ስለ፡ ሰውነቴ፡ የምነግራችሁን።
ም፡ ፯፡ ፪፡፡ ፲፫፡ ፳፯፡፡

፪፡ በሰሙም፡ጊዜ፡ በዕብራይስጥ፡ ቋንቋ፡ አንደነ ግራቸው፡ ጸጥታ፡ አበዙ። እርሱም፡ አለ።
ም፡ ፳፩፡ ፴፡፡

፫፡ እኔ፡ አደሁይዊ፡ ሰው፡ ነኝ፡ በጠርሴስ፡ አገር፡ በ ቂልቅያ፡ ምድር፡ የተወለድሁ፡ በዚቺም፡ አገር፡ ደደ ግሁ፡ ከገማልዬል፡ አግር፡በታች። ባባቶችን፡ሕግ፡ በጣ ም፡ ተምረ፡ ለአግዚአብሔር፡ ቅናተኛ፡ ሆንሁ፡ አን ደላንተ፡ አንደ፡ ሁላችሁ፡ ዛሬ።
ም፡ ፳፫ ፴፱፡፡

ም፡ ፱፡ ፭—፲፱፡፡ ፳፯፡ ፱፡—፲፳፡፡

፬፡ በዚህ፡መንገድም፡የሚሔዲን፡ሰዎች፡እስከ፡ ሞት፡ ድረስ፡ አስጨነቅሁ፡ አሠርሁም፡ ወደ፡ ግዞት ም፡ አመጣሁ፡ ወንደችንም፡ ሴቶችንም።
ም፡ ፰፡ ፫፡፡

፭፡ አንደ፡መሰክርልኝ፡ ደግሞ፡ የካህናቱ፡ አለቃ፡ ሽማግሌችም፡ ሁሉ። ከርሳቸው፡ ወደ፡ ወንድሞች፡ መልእክት፡ ተቀበልሁ፡ ወደ፡ ደማስቀም፡ ሔድሁ፡ ከዚያ፡ ያሉትን፡ አሠሬ፡ ወደ፡ የፈሳሌም፡ ላመጣ፡ ደሣቀዮ፡ ዘንድ።

፮፡ ስሔድም፡ ወደ፡ ደማስቀም፡*ስቀርብ፡ በቀት ር፡ ጊዜ፡ ድንገት፡ ታላቅ፡ ብርሃን፡ በዙርያዬ፡ በራ።
*ም፡ ፱፡ ፫—፲፯፡፡ ፭፡ ቀሮ፡ ፲፭፡ ፳፡፡

፯፡ በምድርም፡ ላደ፡ ወደቅሁ፡ አንደህ፡ የሚለኝ ንም፡ ድምጽ፡ ሰማሁ። ሳውል፡ ሳውል፡ ለምን፡ ታሳ ደኛለህ።
ም፡ ፳፯፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

፰፡ አኔም፡ መለስሁ፡ አልሁም፡ አንተ፡ማነህ፡አቤ ቱ። አለኝም። አኔ፡ ነኝ፡ የሱስ፡ የናዝሬቱ፡ አንተ፡ የ ምታሳደኛ።

፱፡ *ከኔ፡ ጋራ፡ የነበሬት፡ ግን፡ ብርሃኑን፡ አዩ፡ እጅግ ም፡ ፈሩ። የሚናገረኝን፡ ድምጽ፡ ግን፡ አልሰሙም።
*ም፡ ፱፡ ፯፡፡

፲፡ አልሁም። ምን፡ልስራ፡ አቤቱ። ጌታም፡ አለኝ። *ተነሠተህ፡ወደ፡ ደማስቀ፡ ሒድ። ከዚያም፡ ላንተ፡ ደባላል፡ የተሠራልህን፡ ሁሉ፡ ታደርገው፡ ዘንድ።
*ም፡ ፱፡ ፮፡፡

፲፩፡ ማየትም፡ አጥቼ፡ ከዚያ፡ ብርሃን፡ ብልጭታ፡ የተነሣ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ የነበሬ፡ ሰዎች፡ ሲመሬኝ፡ ወደ፡ ደ ማስቀ፡ መጣሁ።

፲፪፡ አንድ፡ ሰውም፡ ስሙን፡ ሐናንያ፡ የሚሉት፡

እግዚአብሔርን፡የሚፈራ፡ አንድ፡ ሕጉ፡ ከአይሁድ ም፡ከዚያ፡ የሚኖረ፡ መልካም፡ የተመሰከረለት።

፲፫፡ አርሱ፡ወደኔ፡መጣ፡በፌቴም፡ቀመሰ፡አለኝም። ወንድሜ፡ ሆይ፡ ሳውል፡ አደ። አኔም፡ በዚያች፡ ጊዜ፡ ወደርሱ፡ አየሁ።

፲፬፡ አርሱም፡ አለ። ያባቶቻችን፡ አመላክ፡ አስቀ ድሞ፡ *መረጠህ፡ ፈቃዷን፡ ታውቅ፡ ዘንድ፡ ጻድቁን ም፡ ታደ፡ ዘንድ፡ ካፈም፡ ድምጽ፡ ትሰማ፡ ዘንድ።

*ም፡ ፬፡ ፲፭።

፲፭፡ በሰውም፡ሁሉ፡ ፊት፡ ምስክር፡ ትሆንለታለ ህ፡ ባየኸው፡ በሰማኸውም፡ ሰራ። ሁሉ።

፲፮፡ አሁንስ፡ ምን፡ ትዘገያለህ። ተነሣና፡ ተጠመ ቅ፡ኃጢአትህንም፡ ታጸብ፡ የጌታን፡ ስም፡ ሰትጸራ።

፲፯፡ ሆነም፡ ወደ፡ የረሳሌም፡ *በተመለስሁ፡ ጊዜ፡ በመቅደስም፡ በጸለይሁ፡ ጊዜ፡ በራእደ፡ ተነኖቁ።

*ም፡ ፱፡ ፳፯።

፲፰፡ አርሱን፡ አየሁ፡ የሚለኝን። ከየረሳሌም፡ ተ ሌ፡ ውጣ፡ ለኔ፡ የምትመሰክረውን፡ አደቀበሉህ ምና።

፲፱፡ አኔም፡ አልሁ። አቤቱ፡ አርሳቸው፡ ያውቃሉ፡ በመስኪጂ፡ ሁሉ፡ አኔ፡ አመታ፡ አሠርም፡ አንደ፡ ነበ ርሁ፡ ባንተ፡ የሚያምኑን።

ቊ፡ ፱።

፳፡ የሰማዕትህም፡ የእስጢፋኖስ፡ ደም፡በፈሰሰ፡ ጊዜ፡ አኔ፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ቁሜ፡ ደስታዱን፡ በሞቱ፡ አየሁ፡ የገደሉትንም፡ ልብስ፡ *አጠብቅ፡ ነበርሁ።

*ም፡ ፯፡ ፶፯።፡ ፷፡ ፭።

፳፩፡ አለኝም። ሒድ፡ አኔ፡ አልክህለሁና፡ ሩቅ፡ አ ገር፡ ወደ፡ አሕዛብ።

ም፡ ፱፡ ፲፭።፡ ፲፫፡ ፪።

፳፪፡ አርሱንም፡ ሰሙት፡ አስከዚህ፡ ቃል፡ ድረስ። ድምጻቸውንም፡ አነሡ፡ ተባብረው፡ አንደህ፡ ሲሉ። አንደህ፡ ያለውን፡ ከምድር፡ አስነሣው። አደገባው ምና፡ ደኖር፡ ዘንድ።

ም፡ ፮፭፡ ፴፯።፡

፳፫፡ አርሳቸውም፡ ሲጮሁ፡ ልብሳቸውንም፡ ሲጥ ሉ፡ ትቢያም፡ ወደ፡ ነፈሰ፡ ሲበትኑ።

፳፬፡ የሻለቃው፡ አዘዘ፡ ወደደራቪ፡ ደወስደት፡ ዘ ንድ፡ በመግረፊያም፡ አንደ መረምረት፡ ያውቅ፡ዘን ድ፡ በምን፡ ምክንያት፡ አንደህ፡ ደጨሁበታል።

፳፭፡ ለመግረፍም፡ የፈጥኝ፡ ባሠረት፡ ጊዜ፡ ጳው ሎስ፡ ለመቶው፡ አለቃ፡ለማበገረፍ፡ቁሞ፡ ለነበረው፡ አለ። *ይገባች፡ኋልን፡ የርምን፡ ሰው፡ ትገርፈ፡ ዘንድ፡ ያልተፈረደበትን።

*ም፡ ፲፭፡ ፴፯።፡ ፳፫፡ ፳፯።፡

፳፮፡ የመቶው፡ አለቃም፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ መጣ፡ ለሻ ለቃውም፡ ነገረው፡ አንደህ፡ ሲል። ምን፡ ትሻለህ፡ ታ ደርግ፡ ዘንድ። ደህ፡ ሰው፡ ሮማዊ፡ ነውና።

፳፯፡ የሻለቃውም፡ ወደርሱ፡ ቀረበ፡ አለውም። ን ገረኝ፡ አንተ፡ ሮማዊ፡ አንደ፡ ሆንህ። አርሱም፡ አለ። አዎን።

፳፰፡ የሻለቃውም፡ መለሰ፡ አለም። አኔ፡ በብዙ፡ ከብት፡ ደህነን፡ የርምን፡ የባላባትነት፡ ሥልጣን፡ ገዛ ሁት። ጳውሎስም፡ አለ። አኔ፡ ግን፡ በርስዋ፡ ተወለ ድሁ።

፳፱፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ ከርሱ፡ ራቁ፡ ደመቱት። የነበ ሩት። የሻለቃውም፡ ደግሞ፡ ፈራ፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ ሮማ ዊ፡ አንደ፡ ሆነ፡ ስላሠረውም።

፴፡ በነገውም፡የሰራውን፡ ነገር፡ አስረግጦ፡ ሊያው ቅ፡ በወደደ፡ ጊዜ፡ ሰለ፡ ምንስ፡ ከአይሁድ፡ አንደ፡ ተ ከሰሰ፡አርሱን፡ ከሠራቱ፡ ፈታው፡ የካህናቱ፡ያለቅች ም፡ ከጉባኤው፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ ደመጡ፡ ዘንድ፡ አዘዘ። ጳውሎስንም፡ አስወርደ፡ በፈታቸው፡አቀመው።

ምዕራፍ፡ ፳፫፡

፩፡ ጳውሎስም፡ ጉባኤውን፡ አጽንተ፡ ኢያየ፡አለ። አላንት፡ ወንድማማች፡ ሰዎች፡ አኔ፡ *በመልካም፡ ሕሊና፡ ሁሉ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ናርሁ፡ አስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ።

*ም፡ ፳፬፡ ፲፯።

፪፡ ሐናንያ፡ የካህናቱ፡ አለቃ፡ግን፡በፊቱ፡ቁመው፡ የነበረትን፡ አዘዘ፡ አፏን፡ ደመቱት፡ ዘንድ።

፫፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ ጳውሎስ፡ አለው። እግዚአ ብሔር፡ ደመጣሃል፡ አንተ፡ የተለሰንህ፡ ግድግጁ። አ ንተ፡ተቀምጠህን፡ በሥርዓት፡ትፈርድብኛለህ፡ያለ፡ ሥርዓትስ፡ታዛለህ፡ አመታ፡ ዘንድ።

፬፡ የቆሙት፡ ግን፡አሉ። የአግዚአብሔርን፡ ካህና ት፡ አለቃንን፡ ትሰድባለህ።

፭፡ ጳውሎስም፡ አለ። አላወቅሁም፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ የካህናት፡ አለቃ፡ አንደ፡ ሆነ። *ተጽፏልናና፡ የ ሕዝብህን፡ አለቃ፡ አትሰድብ፡ ተብሎ።

*ዘፀአ፡ ፳፪፡ ፳፰።፡ ፪፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፲።፡

፮፡ ጳውሎስም፡ ባወቀ፡ ጊዜ፡ አኩሌታቸው፡ ሰጲ ቃውያን፡አኩሌታቸውም፡ ፈሪሳውያን፡አንደ፡ ሆኑ፡ በሸንጎው፡ መካከል፡ ጮኸ፡አንደህ፡ ሲል። አላንት፡ ወንድማማች፡ሰዎች። አኔ፡*ፈሪሳዊ፡ልጅ፡ነኝ። ሰለ፡ ተሰፋው፡ ሰለ፡ ሙታንም፡ ትንሣኤ፡ በኔ፡ ደፈረድብ ኛል።

*ም፡ ፳፮፡ ፭።፡

፯፡ ደህነንም፡ ባለ፡ ጊዜ፡ መለየት፡ ሆነ፡ በፈሪሳው ያንና፡ በሰጲቃውያን፡ መካከል፡ ጉባኤውም፡ ተከ ፈለ።

፰፡ *ሰጲቃውያን፡ ደላሉና፡ ትንሣኤ፡ የለም፡ መ ልአክም፡ መንፈስም። ፈሪሳውያን፡ ግን፡ በዚህ፡ ሁ ሉ፡ ያምናሉ።

*ማቴ፡ ፳፪፡ ፳፫።፡

፱፡ ታላቅም፡ ጩኸት፡ ሆነ። የፈሪሳውያንም፡ ወገ ን፡ ጻፎች፡ ተነሡ፡ በለርሱም፡ ተጣሉ፡አንደህ፡ ሲሉ። በዚህ፡ ሰው፡ *ክፋ፡ ነገር፡ አናገኝም። መንፈስ፡ ነግሮ ት፡ አንደሆን፡ አንጅ። ወደም፡ መልአክ፡ ተአግዚአብ ሔርን፡ አንጣላ።

*ም፡ ፷፭፡ ፷፭።፡ ተተም፡ ፭፡ ፴፬።፡

፲፡ አጅግም፡ መለየት፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ የሻለቃው፡ ፈ ራ፡ ጳውሎስን፡ በመካከላችው፡አንደደነጥቁት። ጭ ፍራውንም፡ አዘዘ፡ ከመካከላቸው፡ጠልፈው፡ ደወ ስጂት፡ ዘንድ፡ ወደደራሹም፡ ያገቡት፡ ዘንድ።

ባ፡ ባደፈ፡ ልብስ።

፫፡ መልካምም፡ ልብስ፡ ወደ፡ ለበሰው፡ ብታዩ፡ እ
ንደ፡ህም፡ ትሉታላችሁ። አንተ፡ ከዚህ፡ በመልካም፡
ስፍራ፡ ተቀመጥ፡ ምስኪኑንም፡ ትሉታላችሁ። አን
ተ፡ ከዚያ፡ ቁም፡ ወይም፡ ወደ፡ ተቀመጥ፡ ከግሬ፡
ድጊ፡ በታች።

፬፡ እንጂደህ፡ያድልዉ፡ ነገር፡ ማድረጋችሁ፡ አደደ
ለምን። በክፋም፡ ሕሊና፡ አልፈረደችሁምን።

፭፡ ስሙ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ የተወደደችሁ። እግ
ዚአብሔር፡ የዚህን፡ ዓለም፡ ድኖች፡ *የመረጠ፡ አደ
ደለምን፡ በሃይማኖት፡ ባለጠጎች፡ ለወደጇቹም፡ ተስ
ፋ፡ ያደረገባትን፡መንግሥት፡ወራሾች፡ ይሆኑ፡ዘንድ።
*ል፡ ቀሮ፡ ፭፡ ፹፯፡፡ ዘፀአ፡ ፹፯፡፡

፮፡ አላንት፡ግን፡ድኃውን፡አቃለላችሁ።ባለጠጎች፡
የግድ፡ የሚልዋችሁ፡ አደደሉምን፡ አርሳቸውም፡ወ
ደ፡ ፍርድ፡ ሻንጎ፡ ደጉትዋችኋል።

፯፡ በሳንትም፡ የተጸራውን፡ የከበረውን፡ ስም፡ የ
ሚሰድቡ፡ አደደሉምን።

፰፡ የንጉሠን፡ሕግ፡ብትፈጽሙ፡*በመጽሐፍ፡ አን
ደ፡ተጻፈ፡ ባልንጀራህን፡ ወደድ፡ አንደ፡ ነፍስህ፡ መል
ካም፡ ታደርጋላችሁ። *ማር፡ ፲፪፡ ፴፭፡፡
ዘሌዋ፡ ፲፱፡ ፲፰፡፡

፱፡ ፈት፡አደታችሁ፡ግን፡ብታደሉ፡ኃጢአት፡ ታደር
ጋላችሁ፡ሕግም፡ ትዘልፈችኋለች፡ አንደ፡ ተላላፊች።
ዘደግ፡ ፩፡ ፲፯፡፡ ና፡ ፲፭፡ ፲፱፡፡

፲፡ ሕግን፡ሁሉ፡*የሚጠብቅ፡ባንደ፡ቱም፡የሚበድ
ል፡በሁሉ፡ የተላለፈ፡ ሁንዋልና። *ማቴ፡ ፭፡ ፲፱፡፡

፲፩፡ አታመንዝር፡ *ያለው፡ ደግሞን፡ አትግደል፡አ
ለ። አሁን፡ ግን፡ ባታመነዝርም፡ ከገደልህ፡ ፈጽመህ፡
ሕግን፡ተላለፍህ። *ዘዕአ፡ ፳፡ ፲፫፡ ፲፱፡፡

፲፪፡ አንደህ፡ ተናገረ፡ አንደህም፡ አድርጉ፡*በአር
ነት፡ሕግ፡የምትፈረጁ፡አንደላችሁ። *ም፡ ፭፡ ፹፭፡፡

፲፫፡ ምህረት፡ የሌለበት፡*ፍርድ፡ደሆነልና፡ምህረ
ት፡ ለማያደርግ። ምህረትም፡ በፍርድ፡ ላይ፡ ትመካ
ለች። *ማቴ፡ ፭፡ ፯፡፡ ና፡ ፲፰፡ ፱፡ ፲፭፡፡
ና፡ ፹፭፡ ፵፭፡ ፱፯፡፡

፲፬፡ ምን፡ ጥቅም፡ ነው፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ አንድ፡
ሰው፡ቢል፡ሃይማኖት፡አለኝ፡*ምግባርም፡ የለውም።
ሃይማኖቱ፡ታድነው፡ ትችላለችን። *ማቴ፡ ፯፡ ፹፯፡፡

፲፭፡ ወንድም፡ ወይም፡ እት፡ ዕራቁታቸውን፡ቢሆ
ኑ፡የዕለት፡ራታቸውንም፡ የሚሹ። ሉቃ፡ ፫፡ ፲፩፡፡

፲፮፡ አንጂም፡ ከላንት፡ ቢላቸው፡ በደህና፡ ሒዱ፡
ደሙቁት፡ዑገቡም። ሠጋቸው፡ግን፡ የሚሻውን፡አ
ሰጥዋቸውም።ምን፡ ደጠቅማል። ል፡ ዮሐ፡ ፫፡ ፲፯፡፡

፲፯፡ አንጂሁ፡ ሃይማኖትም፡ ምግባር፡ ከሌላት፡ አ
ርስዋ፡ የሞተች፡ናት፡ለብቻዋ፡ ስትሆን።

፲፰፡ ነገር፡ግን፡አንድ፡ ሰው፡ደላል። አንተ፡ ሃይማኖ
ት፡ አለህ፡ እኔም፡ ምግባር፡ አለኝ። አንተ፡ ሃይማኖት
ህን፡ ደለ፡ ምግባር፡ *አሳዦኝ፡ እኔም፡ ሃይማኖቴን፡ ከ
ምግባሬ፡አሳደሃለሁ። *ገላት፡ ፭፡ ፮፡፡

፲፱፡ አንተ፡ታምናለህ፡ እግዚአብሔር፡ አንድ፡ እን
ደሆነ፡ መልካም፡ ታደርጋለህ። ሰደጣናትም፡ ደግሞ፡
ያምናሉ፡ ደንቀጠቀጡማል።

፳፡ ነገር፡ግን፡ ትሻለህን፡ ታውቅ፡ ዘንድ፡አንተ፡ ከን
ቱ፡ሰው፡ሃይማኖት፡ ምግባር፡ የሌለባት፡ የሞተች፡ እ
ንደሆነች።

፳፩፡ አባታችን፡ አብርሃም፡ በምግባሩ፡ የጸደቀ፡አ
ደደለምን፡ልጂኁ፡ ደስሐቅን፡ ለመሥዋዕት፡ ባቀረበ
ው፡ጊዜ። ዘፍጥ፡ ፳፪፡ ፱፡ ፲፡ ፲፪፡፡

፳፪፡ ተመልከት፡ሃይማኖት፡ ከምግባሩ፡ ጋራ፡ እን
ደደረገች። ከምግባርም፡ የተነሣ፡ ሃይማኖት፡ ተፈጸ
መች።

፳፫፡ መጽሐፈም፡*ያለው፡ተፈጸመ። አብርሃም፡
በእግዚአብሔር፡ አመነ፡ ጽድቅም፡ ሁኖ፡ ተቊጠረለ
ት፡ የእግዚአብሔርም፡ †ወደጅ፡ተባለ።
*ዘፍጥ፡ ፲፭፡ ፮፡፡ †ኢሳ፡ ፵፩፡ ፳፡፡

፳፬፡ አሁንስ፡ አያችሁ፡ ሰው፡ በምግባሩ፡ እንጂጸ
ድቅ፡ በሃይማኖትም፡ብቻ፡ አደደለውም።

፳፭፡ እንጂሁም፡ *ረዓብ፡ ጋለሞታ፡ በምግባርዋ፡
የጸደቀች፡ አደደለችምን፡ ጕበኖችን፡ በተቀበለች፡ጊ
ዜ፡ በሌላ፡ መንገድም፡ ባወጣቻቸው፡ ጊዜ።
*ዕብ፡ ፲፩፡ ፴፩፡፡

፳፮፡ ነፍስ፡ የሌለችበት፡ ሥጋ፡ የሞተ፡ እንደ፡ ሆነ፡
እንደሁም፡ *ሃይማኖት፡ ደለ፡ ምግባር፡ የሞተች፡ ና
ትና። *ቆ፡ ፲፯፡፡

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ አጅግ፡መምህራን፡አትሁኑ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡
ታላቅ፡ ፍርድ፡ እንድንወሰድ፡ ታውቃላችሁና።

፪፡ አሾ፡ ሁላችን፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ እንበድላለንና። በነገ
ረ፡ የማያሰተ፡ደህ፡ ፈጹም፡ ሰው፡ ነው፡አርሱም፡ሠ
ጋውን፡ ሁሉ፡ ደገዛ፡ ዘንድ፡ ይቾላል።

፫፡ እነሆ፡*ልጋም፡እናደርጋለን፡ በፈረስ፡ አፍ፡ ትታ
ዘዝልኑ፡ ዘንድ፡ ሠገዋንም፡ ሁሉ፡ እንስበዋለን።
*መዝ፡ ፴፪፡ ፱፡፡

፬፡ ደግሞም፡ እነሆ፡ ታላላቅች፡ መርከቦች፡ ከጽና
ች፡ዓውሎ፡ነፈስ፡ተነድተው፡ በታናሽ፡እንዠት፡ደመ
ለሳሉ፡ የመርከብ፡ መሪ፡ፈቃድ፡ ወደሚወደው፡ ስፍ
ራ፡ሁሉ።

፭፡ እንጂሁም፡ መላስ፡ታናሽ፡ብልት፡ነው፡ታላላቅ
ም፡ ነገር፡ ደያገራል። እነሆ፡ እሳት፡ ጥቂት፡ ብትሆን፡
ምንድር፡ የሚያህልንስ፡ ታቃጥላለች።

፮፡ መላስም፡ እሳት፡ ነው፡ የዓለም፡ ግፍ፡ ሁሉ፡ የ
መላበት። እንጂሁ፡መላስ፡በብልታችን፡ተሰርትዋል፡
ሠጋንም፡ ሁሉ፡ *ያረክሳል፡ የፈጥረታችንንም፡ ረጪ፡
ያቃጥላል፡ ከገሃነም፡ ትሂለች።
*ማቴ፡ ፲፭፡ ፲፩—፲፱፡፡ ም፡ ፲፪፡ ፴፯፡ ፴፯፡፡

፯፡ የእንስሳ፡ባሕርያ፡ሁሉ፡ የአራዊትም፡ የአዕዋ
ፍም፡ የሚገቀሳቀስውም፡ በባሕርም፡ ያሉ፡ እንስሶ
ች፡ደለመደሉ፡ በሰው፡ ባሕርደም፡ ተለምደዋል።

፳፡ መላስን፡ግን፡ከሰው፡ ማንም፡ አደቾልም፡ ደገ ዛው፡ ዘንድ። ክፈ፡ ዓመፀኛም፡ ነውና፡ *የሞት፡ መር ዝ፡የመላበት። *መዝ፡ ፻፵፤ ፱፡፡

፱፡ በርሱ፡እግዚአብሔር፡ አብን፡ እናመሰግናለን። በርሱም፡ ሰውን፡ እንረግማለን፡ በእግዚአብሔር፡ አ ምሳል፡ የተፈጠረውን። ዘፍ.፥ ፭፡ ፶፯፡፡

፲፡ ካንድ፡ አፍ፡ ደወጣል፡ በረከትና፡ መርገምዋ። አደገባም፡ወንድሞቼ፡ሆይ፡ ደህ፡ነገር፡ እንደህ፡ ደሆ ን፡ ዘንድ።

፲፩፡ ወደስ፡ ካንድ፡ ምንጭ፡ የጨው፡ ውኃና፡ ጸፋ ጭ፡ውኃ፡ ደፈሳልን።

፲፪፡ ወደስ፡ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ በለስ፡ወደራ፡ታፈራ ለችን። ወደንም፡ በለስን። እንደሁም፡ አንድ፡ ምን ጭ፡ መራራ፡ ውኃ፡ የጸፈጠም፡ አደፈስም።

፲፫፡ ማነው፡ከላንት፡ *ጠቢብ፡አስተዋደም። ከመ ልካም፡አካሔዱ፡ ተሰራውን፡ ደገለጥ፡ በጥበብ፡ የው ሳት። *ኤፈ፡ ፭፡ ፲፭፡፡ ተም፡ ፪፡ ፲፮፡፡

፲፬፡ *ቅንዓት ፡ ግን፡ ቢኖርባችሁ ፡ መተማማትም፡ በልባችሁ፡ አትመኩ፡ በውነትም፡ ላደ፡ አትዋሹ።

*ኤፈ፡ ፱፡ ፴፭፡፡

፲፭፡ ደህች፡ ጥበብ፡ *ከላደ፡ የወረደች፡ አደደለች ም፡ነገር፡ግን፡ የምድር፡ናት፡ የሠጋም፡ ናት፡ የሰይጣን ም፡ናት። *ም፡ ፩፡ ፭፡ ፲፯፡፡

፲፮፡ ቅንዓትና፡መተማማት፡ ባለበት፡ ስፍራ፡ ከዚ ያ፡ አንድነት፡ የለምና፡ ክፈም፡ ስራ። ሁሉ፡ አለበት።

፲፯፡ ከሰማደ፡ ግን፡ የወረደች፡ ጥበብ፡ ታራቂ፡ አሰ ቀድሞ፡ ንጹሕ፡ ነው፡ ደግሞም፡ የዕርቅ፡ ወደጅ፡ ገር ም፡ እሺ፡ባደም፡ ምህረትና፡ መልካም፡ ፈረ፡ የመላ ባት፡ ደለ፡ ማድላትና፡ ደለ፡ ግብገዝነት።

፲፰፡ የጽድቅ፡ *ፈረ፡ግን፡ በሰላም፡ ትዘራለች፡ ሰላ ም፡ ለሚደደርጉ። *ኢሳ፡ ፴፪፡ ፲፯፡፡

ምዕራፍ፡ ፬፡

፩፡ ጽል፡ክርክርም፡ ከወደት፡ መጣችባችሁ። ከዚ ህ፡ አደደለችምን፡ በብልታችሁ፡ ከምትታወክ፡ ፈት ወታችሁ። ፭፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፲፩፡፡

፪፡ ትመኛላችሁ፡ለላንትም፡ አደሆንም። ትገድላ ላችሁ፡ ትቀኑማላችሁ፡ መውሰድም፡ አደሆንላችሁ ም። ትጻላላችሁ፡ ትዋጉማላችሁ። ምንም፡ የላችሁ ም፡ ስላለመናችሁ።

፫፡ *ትለምናላችሁ፡ አትቀበሉም፡ ለመልካም፡ አ ትለምኑምና፡ በፈትወታችሁ፡ ልትፈጂት፡ ነው፡ እ ንጂ። *መዝ፡ ፲፯፡ ፴፱፡፡

፬፡ አላንት፡ አመንዝሮች፡ አመንዝራዶቶችም፡ አ ታውቁምን፡ የሳለም፡ፈቅር፡ በእግዚአብሔር፡ ላደ፡ ጸላትነት፡ እንደ፡ ሆነች። የሳለም፡ ወደጅ፡ መሆን፡ የ ሚወድ፡ የእግዚአብሔር፡ ጸላት፡ ሁን፡ ተገኘ።

ሉቃ፡ ፮፡ ፳፭፡፡ ሮሜ፡ ፭፡ ፯፡፡ ፭፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፲፭፡፡

፭፡ ወደስ፡ ደመስላችኋልን፡ *መጽሐፍ፡ በከንቱ፡ የሚያገር። በች፡ ያደረብ፡ መንፈስ፡ በቅንዓት፡ ደወ ደል። *ገላት፡ ፭፡ ፲፯፡፡

፮፡ ነገር፡ግን፡ ጸጋውን፡ አብልጦ፡ ደሰጣል። ስለዚህ ም፡ ደላል ። *እግዚአብሔር፡ ልባቸውን፡ የሚያስታ ብዶን፡ ሰዎች፡ ደቃወማል፡ ለትሑታን፡ ግን፡ ጸጋ፡ ደሰ ጣል። *ኢዮብ፡ ፭፪፡ ፳፱፡፡ ማቴ፡ ፳፫፡ ፲፪፡፡

፯፡ አሁንም፡ለእግዚአብሔር፡ ተገዙ። ሰይጣንን፡ *ትቋቋሙ፡ ከላንትም፡ ደሸሻል። *ኤፈ፡ ፮፡ ፲፪፡፡

፰፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ *ቅረቡ፡ አርሱም፡ ወደላ ንት፡ደቀርባል።እጆችሁን፡ ተአንጹ፡አላንት፡ ኃጢአተ ኞች፡ልባችሁንም፡ አጽሩ፡ በሁለት፡ ልብ፡ የምትሆኑ።

*ዘካ፡ ፩፡ ፫፡፡ ተኢሳ፡ ፩፡ ፲፮፡፡

፱፡ ተቸገረ፡ አልቅሱም፡ እዘኑም። ሳቃቸሁ፡ ወደ፡ ልቅሶ፡ ደመለስ፡ ደስታችሁም፡ ወደ፡ ኃዘን።

፲፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ *ዝቅ፡ ዝቅ፡ በሉ፡ ከፍ፡ ከፍ ም፡ ደደርጋችኋል። *፩፡ ጴጥ፡ ፭፡ ፮፡፡

፲፩፡ አርሱ፡በርሳችሁ፡ *አትናገረ፡ አላንት፡ ወንድ ሞች። በወንድሙ፡ ላደ፡ የሚናገር፡ በወንድሙም፡ የሚፈርድ፡ ፈጽሞ፡ በሕግ፡ ላደ፡ደናገራል፡ በሕግም፡ ደፈርዷል። በሕግም፡ ከፈረድህ፡ አንተ፡ ሐግን፡ አድ ራጊ፡አደደለህም፡ ፈራጅ፡ አንጂ። *መዝ፡ ፲፭፡ ፫፡፡ ፭፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፭፡፡

፲፪፡ አንድ፡ነውና፡ የሕግ፡ አጋገና፡ ፈራጅ፡ ያድን፡ ዘ ንድ፡ደገልም፡ዘንድ፡ ችሎት፡ ያለው። *አንተ፡ ማነህ፡ በባልንጀራህ፡ተፈርድ፡ዘንድ። *ማቴ፡ ፯፡ ፭፡፡

፲፫፡ አሁንም፡ ሒዲ፡ አንደህ፡ *የሚሉትን፡ ሰዋ ች። ዛሬ፡ ወደም፡ነገ፡ ወደዚያች፡ አገር፡ አንሔደለን፡ ከዚያም፡ አመት፡ አናደርጋለን፡ አንነግድማለን፡ አና ተርፈማለን። *ምሳ፡ ፳፯፡ ፩፡፡

፲፬፡ አላንትም፡ *አታውቁም፡ ነገ፡ የሚሆነውን። ሕይወታችን፡ምንድር፡ ናት። እንደ፡ ጽጋግ፡ አደደለ ችምን፡ ጥቂት፡ ታደተ፡ የሚጠፈ። *ሉቃ፡ ፲፪፡ ፳፡፡

፲፭፡ በምትሉበት፡ ፈንታ። እግዚአብሔር፡ ቢፈቅ ደው፡ብንናርም፡ ደህንን፡ ወደም፡ ደነን፡አናደርጋለን። የሐዋ፡ ፲፰፡ ፳፩፡፡

፲፮፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዛረ ፡ በማሰባችሁ፡ ትመካላችሁ። አንደህ፡ ደለው፡ መመካት፡ ሁሉ፡ ክፈ፡ ነው።

፲፯፡ *መልካም፡ ነገርም፡ ማድረግ፡ የሚደወቅ፡ የ ማደደርገውም፡ ደም፡ ኃጢአት፡ ደሆንበታል።

*ሉቃ፡ ፲፪፡ ፵፯፡፡

ምዕራፍ፡ ፭፡

፩፡ አሁንም፡ ሒዲ፡ አላንት፡ *ባለጠጎች፡ አልቅሱ፡ ዋደም፡ በሉ፡ በሚመጣባችሁ፡ መከራ።

*ምሳ፡ ፲፩፡ ፳፰፡፡ ሉቃ፡ ፮፡ ፳፬፡፡

፪፡ *ባለጠግነታችሁ፡ ጠፈትዋልና፡ልብሳችሁንም፡ ብል፡ በልተታልና። *ማቴ፡ ፮፡ ፲፱፡፡

፫፡ ወርቃችሁ፡ብራችሁም፡ ዛገ፡ዝገቱም፡ምስክር፡ ደሆንባችኋል፡ ሥጋችሁንም፡ ደበላዋል፡ እንደሳት። ለኋለኛው፡ ቀን፡ መዝገብ፡ አከማቻችሁት።

፱፡ እነሆ፡ የሰራተኖች፡ ምድራችሁን፡ ያጨዱት፡ ዋጋ፡ አላጎት፡ ያቀማቸኋቸው፡ ደመሳል። ያጨዩች ም፡ድምጽ፡ወደ፡ የባለዮት፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ጀሮ፡ ደረሰ። ዘያግ፡ ፭፱፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

፭፡ በምድር፡ ላይ፡ ደሳላችሁ፡ በሴሰኝነት፡ ተቀመ ጣችሁ።ልባችሁን፡አደነደናችሁ፡በበዓል፡ ቀን፡እንደ፡ ሆነ። ሉቃ፡ ፲፯፡ ፲፱፡ ፭፳፡፡

፮፡ በጻድቁም፡ ፈረደችሁ፡ ገደላችሁትም፡ አልተ ጠናወታችሁምወም።

፯፡ አሁንም፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ *ታገሡ፡ እስከ፡ጌ ታ፡መገለጥ፡ድረስ። እነሆ፡ ገባረ፡ የከበረችቱን፡ ምድ ር፡ፈረ፡ደጅ፡ ደጸናል፡ ሲታገሥላት፡ የፊተኛውንና፡የ ኋለኛውን፡ ዝናም፡ እስክትወስድ፡ ድረስ።

*ሉቃ፡ ፳፭፡ ፲፱፡፡ ዕብ፡ ፲፡ ፴፯፡፡

፰፡ እላንትም፡ደግሞ፡ታገሡ፡ ልባችሁን፡ አጽኑ፡የ ጌታ፡መምጣት፡ ቀርብዋልና።

፱፡ እርሱ፡ በርሳችሁ፡ አትተዛዝኑ፡ ወንድሞቼ፡ሆ ይ፡ እንደትኩነኑ። እነሆ፡ *ፈራጅ፡ በደጅ፡ፊት፡ ቁም ዋልና። *ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፫፡፡

፲፡ ነቢያትን፡ በጌታ፡ ስም፡ የተናገረትን፡ ወንድሞ ቼ፡ ሆይ፡ የመከራንና፡ የትዕግሥትን፡ ምሳሌ፡ ተቀበ ሉ። እነሆ፡ የታገሡትን፡ እናመሰግናለን።

ማቴ፡ ፭፡ ፲፪፡፡

፲፩፡ የኢዮብን፡*ትዕግሥት፡ሰምታቸኋል፡የእግዚ አብሔርንም፡ ፍጻሜ፡አያችሁ፡ †እግዚአብሔር፡ ም ህረቱ፡ የበዛ፡ ነውና፡ የሚራራም።

*ኢዮብ፡ ፩፡ ፲፭፩፡ ፲፪፡፡ †መዝ፡ ፻፫፡ ፰፡፡

፲፪፡ ከሁሉ፡ ይልቅ፡ ግን፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ አትማ ሉ። በሰማይ፡ በምድርም፡ በሌላም፡ መሐላ። በነገራ ችሁ፡ ግን፡ አዎን፡ አዎን፡ ይሁን፡ አደይለም፡ አደይለ ም፡ከፈርድ፡ በታች፡ እንደትወድቁ።

ማቴ፡ ፭፡ ፴፬፡—፴፯፡፡

፲፫፡ ማንም፡ከላንት፡ *በመከራ፡ ቢሆን፡ ይጸልይ። ደስ፡ ቢለውም፡ †ይዘምር። *መዝ፡ ፶፡ ፲፭፡፡ †ቀለ፡ ፫፡ ፲፯፡፡

፲፬፡ ማንም፡ከላንት፡ ቢታመም፡ የቤተ፡ ክርስቲያ ንን፡ቀሳውስት፡ይጽራ፡ ይጸልዩለትም፡ *ዘይትም፡ይ ቅቡት፡በጌታ፡ስም።

*ማር፡ ፮፡ ፲፫፡፡

፲፭፡ የሳይማናትም፡ *ጸሎት፡ ድውዩን፡ ትፈውሳ ለች፡ ጌታም፡ ያስነሣዋል። ኃጢአትም፡ ሰርተ፡እንደ ሆነ፡ትሰረይለታለች።

*መዝ፡ ፴፡ ፫፡፡

፲፮፡ እርስ፡ በርሳችሁ፡ ተናዘዙ፡ በኃጢአታችሁ፡ አ ንደ፡ም፡ላንደ፡ ይጸልይለት፡ *እንድትፈወሱ። የጻድ ቅ፡ጸሎት፡ ታላቅ፡ ኃይል፡ ታደርጋለች።

*መዝ፡ ፪፻፵፭፡ ፲፰፡፡

፲፯፡ ኤልያስ፡ ሰው፡ ነበረ፡ እንደኛ፡በእኩል፡ ሕማ ማት፡ጸሎትም፡ጸለየ፡ ከሰማይ፡ ዝናም፡ እንደይዘን ም። በምድር፡ ላይም፡ *አልዘነመም፡ ሶስት፡ አመት፡ ከሰድስት፡ወር። *፩፡ ነገሥ፡ ፲፯፡ ፩፡፡ ሉቃ፡ ፬፡ ፳፭፡፡

፲፰፡ ደግሞም፡ ጸለየ፡ ሰማይም፡ ዝናም፡ ሰጠች፡ ምድሪቱም፡ፈረዋን፡አበቀለች። ፩፡ነገሥ፡ ፲፰፡ ፵፪፡፡

፲፱፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ከላንት፡ ማንም፡ ከውነት፡ መንገድ፡ቢስት፡የሚመልሰውም፡ቢኖር።

ገላት፡ ፮፡ ፩፡፡

፳፡ ያወቅ፡ ኃጢአተኛን፡ ከስሕተት፡ መንገድ፡ የ ሚመልስ፡ነፈስን፡ከሞት፡ የሚያድን፡ እንደሆነ፡ የኃ ጢአትንም፡ብዛት፡ ይሰውራል።

የሐዋርያ ፡ የጴጥሮስ ፡ መልእክት ፡ መጀመርያዪቱ።

ምዕራፍ፡ ፩፡

፩፡ ከጴጥሮስ፡ከየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሐዋርያ፡ ወደ፡ተ በተኑት፡ ስደተኖች፡ በጵንጦስ፡ አገር፡ በገላትያም፡ በ ቀጰደቅያም፡በእስያም፡ በቢቲንያም፡ የተቀመጡ።

ያዕ፡ ፩፡ ፩፡፡

፪፡ ቀደመው፡ *የተመረጡት፡ እንደ፡ እግዚአብ ሔር፡አብ፡እውቀት፡በመንፈስ፡ቅድስና፡ለመታዘዝ፡ ለየሱስ፡ክርስቶስም፡ለደሙ፡ መርጨት። ጸጋ፡ ምህረ ትም፡ ትብዛላችሁ። *ሮሜ፡ ፰፡ ፳፱፡፡

፫፡ እግዚአብሔር፡*ይመስገን፡የጌታችንም፡የየሱ ስ፡ክርስቶስ፡ አባት፡ በምህረቱ፡ብዛት፡ ደግሞ፡ የወለ ደን፡ወደ፡ ሕይወት፡ ተስፋ፡በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ትንሣ ኤ፡ ከሙታን። ፪፡ ቀሮ፡ ፩፡ ፫፡፡

፬፡ ወደማያረጅ፡ ወደማይጠፋም፡ *ወደማይለ ወጥም፡ርስት፡ በሰማይ፡ የተጠበቀላችሁን።

*ቀለ፡ ፩፡ ፲፪፡፡

፭፡ አላንት፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ *የተጠበቃች ሁ፡በሃይማኖት፡ ለመድኃኒት፡ በኋለኛው፡ ዘመን፡ ይ ገለጥ፡ዘንድ፡ለተዘጋጀው። *ዮሐ፡ ፲፡ ፳፰፡፡ ፲፯፡ ፲፩፡፡

፮፡ ዛሬ፡ በርሱ፡*ደስ፡ የሚላችሁ፡ ጥቂትም፡ ልባች ሁ፡ቢያዝን፡በተላለፈ፡ መከራ፡ †ስትፈተኑ፡ ለላንት፡ የሚገባ፡ቢሆን። *ሮሜ፡ ፭፡ ፪፡፡ ፪፡ ቀሮ፡ ፱፡ ፲፯፡፡ †ም፡ ፭፡ ፲፡፡

፯፡ የሳይማናታችሁ፡መፈተን፡ *ከሚጠፋ፡ወርቅ፡ የሚከብር፡ ምንስ፡ በእሳት፡ ቢጸራ፡ ደገኛ፡ ዘንድ፡ ለ ትምክሕት፡ ለምስጋናም፡ ለክብርም፡በየሱስ፡ ክርስ ቶስ፡ መገለጥ። *ም፡ ፲፯፡ ፫፡፡ መልክ፡ ፫፡ ፫፡፡

፷፡ *ያላያችሁት፡ የምትወዷትም፡ ዛፈም፡ አታዩ ትም፡ ነገር፡ ግን፡ አመናችሁበት፡ በብዙም፡ ደስታ፡ ደ ስ፡አላችሁ፡ በማይነገርበት፡ ደስታ፡ክብር፡የመላበት።

*ዮሐ፡ ፳፡ ፳፱፡፡ ፭፡ ቀሮ፡ ፭፡ ፺፡፡

፱፡ የሣይማናታችሁን፡ *ፈጸማ፡ በትወሰኗ፡የነፈሳ ችሁን፡ ደህንነት። *ሮሜ፡ ፮፡ ፳፪፡፡

፲፡ ስለዚህም፡መድኃኒት፡*ነቢያት፡ፈለጉ፡መረመ ረም፡ በዚች፡ ለላንት፡ በሆነችው፡ ጸጋ፡ ትንቢት፡ የተ ናገረ። *ሂን፡ ፱፡ ፳፫፡ ፳፱፡፡ ሉቃ፡ ፲፡ ፳፱፡፡

፲፩፡ ሲመረምረ፡ ምን፡ ወይም፡ ማናቸው፡ዘመን፡ የነበረባቸው፡ የክርስቶስ፡ መንፈስ፡ አንሂ፡ አመለከ ተ፡ ስለ፡ ክርስቶስ፡ *ሕማማት፡ ከዚያ፡ በኋላም፡ ስ ለሚመጣው፡ ክብሩ፡ ቀድሞ፡በመሰከረ፡ ጊዜ።

*መዝ፡ ፳፪፡ ፮፡፡ ኢሳ፡ ፶፫፡፡

፲፪፡ ይህም፡ ተገለጠላቸው፡ ለራሳቸው፡ ሊያገለግ ሉ፡ አይደለም፡ ለኛ፡አንጅ፡ያ፡ነገር፡ዛሬ፡ለላንት፡ የተ ወራ፡ ወንጌልን፡ ከሰበኩላችሁ፡ሰዋቅ፡በመንፈስ፡ ቅ ዱስ፡ ከሰማይ፡ በተላከው። ይህም፡ ነገር፡ *መላእክ ት፡የሚወዷ፡ ያዩት፡ ዘንድ። *ኤፈ፡ ፫፡ ፲፡፡

፲፫፡ ስለዚህም፡ የልባችሁን፡ ወገብ፡ *አጽኑ፡ ንቁ ም፡ ፈጽማችሁም፡ በዮሱስ፡ ክርስቶስ፡መገለጥ፡የም ትሰጣችሁን፡ ጸጋ፡ ተሰፋ፡ አድርጉ። *ኤፈ፡ ፫፡ ፲፡፡

፲፬፡ እንደሚያዘዙ፡ልጆች፡ በቀደመችውም፡ *ፍ ትወት፡ ያለውቀት፡ ባደረጋችኋት፡ አትምሰሉ።

*ሮሜ፡ ፲፪፡ ፪፡፡

፲፭፡ ነገር፡ ግን፡ አንደ፡ ጸራችሁ፡አንደ፡ቅዱሱ፡ አላ ንት፡ ደግሞ፡*ቅዱሳን፡ ሁኑ፡በአካሔዳችሁ፡ ሁሉ።

*ሉቃ፡ ፩፡ ፎ፭፡፡

፲፮፡ *ተጽፏልና። ቅዱሳን፡ ሁኑ፡ †እኔ፡ ቅዱስ፡ ነኝና። *ዘሌዋ፡ ፲፩፡ ፵፬፡፡ †መዝ፡ ፎ፩፡ ፶፪፡፡

፲፯፡ ያለ፡ *አድልዎም፡የሚፈርደውን፡ ለሁሉም፡ ኢያንደንደ፡ አንደ፡ ስራው፡ የሚሰጠውን፡ አባት፡ የምትሉት፡ብትሆኑ፡ ከዚህ፡አንግድነት፡በተቀመጣ ችሁበት፡ ዘመን፡ ሁሉ፡ በፈርሃት፡ ሒደ።

*የሐዋ፡ ፲፭፡ ፴፭፡፡

፲፰፡ ታውቃላችሁና፡በሚጠፋ፡ *በወርቅና፡ በብር፡ ከከንቱ፡ ስራችሁ፡ *አንደልደያችሁ፡ ካባቶቻችሁ፡ ከ ተቀበላችሁት። *ዕ፡ ቀሮ፡ ፮፡ ፮፡፡ ና፡ ፮፡ ፶፫፡፡

†ም፡ ፱፡ ፫፡፡

፲፱፡ ነገር፡ ግን፡ በከበረው፡ በበግ፡ ደም፡ ነውር፡ ርኩ ሰትም፡ የሌለበት፡ አርሱም፡ ክርስቶስ።

፳፡ ከዋንቱም፡ *የተመረጠ፡ ዓለም፡ ሳይፈጠር፡ በኋለኛው፡ ዘመን፡ ግን፡ ተገለጠ፡ ስለላንት።

*ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፭፡፡

፳፩፡ በርሱም፡ በእግዚአብሔር፡ *አመናችሁ፡ ከ ሙታን፡ ተባስነሣው፡ ክብርም፡ በሰጠው፡ ሃይማኖታ ችሁና፡ ተስፋችሁ፡ በእግዚአብሔር፡ ይሆን፡ ዘንድ።

*ዮሐ፡ ፲፬፡ ፮፡፡ †የሐዋ፡ ፫፡ ፲፭፡፡

፳፪፡ ነፈሳችሁንም፡ ካነጻችሁ፡ ለውነት፡ በመታዘ ዛችሁ፡ ወደ፡ ወንድሞች፡ ፈቅርም፡ ያለ፡ ሽንገላ፡ ከ መጣችሁ። እርሱ፡ በርሳችሁ፡ ተዋደዱ፡ በንጹሕ፡ ል ብ፡ በፈጹምም፡ ውድ።

፳፫፡ ከሚጠፈ፡ ዘር፡ አልተወለደችሁምና፡ ነገር፡ ግን፡ከማይጠፈ፡ ከዘላለሙ፡ ከሕያው፡ከአግዚአብ ሔር፡ ቃል፡ የተነሣ። ዮሐ፡ ፭፡ ፲፫፡፡ ያዕ፡ ፩፡ ፲፰፡፡

፳፬፡ ሰው፡ ሁሉ፡ አንደ፡ ሣዕር፡ ነውና። የሰውም፡ ክብር፡ ሁሉ፡ አንደ፡ ሣዕር፡ አበባ። ሣዕሩ፡ ደደርቃል፡ አበባውም፡ ደረግፈል። ኢሳ፡ ፵፡ ፮፡ ፯፡፡

ያዕ፡ ፩፡ ፲፡ ፲፩፡፡

፳፭፡ የአግዚአብሔር፡ቃል፡ግን፡ ለዘላለም፡ ይኖራ ል። በወንጌልም፡ የተሰበከላችሁ፡ ቃል፡ ይህ፡ነው።

ምዕራፍ፡ ፪፡

፩፡ አሁንም፡ ክፈ፡ነገርን፡ ሁሉ፡ *ጣሉ፡ ተንኰልን ም፡ ሁሉ፡ ግብዝነትንም፡ ቅናትንም፡ ሐሜትንም፡ ሁሉ። *ሮሜ፡ ፮፡ ፬፡፡ ና፡ ፲፪፡ ፀ፡፡ ፩፡ ቀሮ፡ ፲፬፡ ፷፡፡

፪፡ ዛሬም፡ እንደ፡ ተወለደ፡ *ሕፃናት፡ አእምሮ፡ ወደለውና፡ ወደውነተኛው፡የቃልን፡ወተት፡ †ናፈቁ፡ በርሱ፡ ታድጉ፡ዘንድ። *ዕብ፡ ፭፡ ፲፪፡ ፲፫፡፡ †ማቴ፡ ፲፰፡ ፫፡፡

፫፡ ቀምሳችሁ፡ እንደ፡ ሆናችሁ፡ ጌታ፡ ምህረተኛ፡ አንደሆነ። መዝ፡ ፴፬፡ ፱፡፡

፬፡ የቀረባችሁት፡ የሕይወት፡ ደንጊያ፡ በስውም፡ ዘንድ፡ የተናቀ፡ ነው፡ ግን፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የተመረጠና፡ የከበረ፡ነው። መዝ፡ ፻፲፰፡ ፳፪፡፡

፭፡ አላንትም፡ ደግሞ፡ የሕይወት፡ ደንጎች፡ ሆናች ሁ፡ ትሠረ፡ ዘንድ፡ መንፈሳውያን፡ *መቅደስ፡ ሁናች ሁ፡ የተቀደሳችሁ፡ †ካህናት፡ መንፈሳዊት፡ **መሥ ዋዕት፡ ታቀርቡ፡ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የተ ቀበሉች፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ። *ኤፈ፡ ፪፡ ፳፩፡፡

†ቀሮ፡ ፀ፡፡ **ሮሜ፡ ፲፪፡ ፩፡፡

፮፡ በመጽሐፈ፡ *ተጽፏልና። እነሆ፡ በፅዮን፡ የ ማዝን፡ ራስ፡ የተመረጠ፡ ደንጊያ፡ የከበረም፡ እናራ ለሁ፡ የሚያምንበትም፡ እያፈርም።

*ኢሳ፡ ፳፰፡ ፲፮፡፡

፯፡ ደህቺም፡ክብር፡ ለላንት፡ ናት፡ እላንት፡ ያመና ችሁበት፡ ለማያምኑበት፡ ግን፡ እናጆች፡ የናቁት፡ ደን ጊያ፡ እርሱ፡ የማዝን፡ ራስ፡ ሆነ። *ማቴ፡ ፳፩፡ ፵፪፡፡

፰፡ *የንቅፈትም፡ ደንጊያ፡ የመሰናከልም፡ ደሆን ባቸዋል፡ በቃል፡ ለሚሰናከሉ፡ ስላልታዘዙ። እርሳቸ ውም፡ለዚህ፡ተሰጡ። *ኢሳ፡ ፰፡ ፲፬፡፡ ሮሜ፡ ፱፡ ፴፫፡፡

፱፡ እላንት፡ ግን፡ የተመረጠ፡ *የመንግሥትና፡ የክ ህነትም፡ ወገን፡ ናችሁ። የተቀደሰች፡ ዘር። ለርስት፡ የተለየ፡ ሕዝብ። ከጨለማ፡ ወደማደነገር፡ወደ፡ ብር ሃኑ፡ የጸራችሁን፡ ስራ፡ ትገልጡ፡ ዘንድ።

*ዘፀአ፡ ፲፱፡ ፮፡፡ ራእ፡ ፩፡ ፮፡፡

፲፡ እላንት፡ *ከዋንቱ፡ ወገን፡ ያልነበራችሁ፡ አሁን፡ ግን፡ ፈጽማችሁ፡ ወገን፡ ሆናችሁ፡ ለእግዚአብሔር።

ደቅር፡ የተባላችሁም፡ አልነበራችሁም፡ ዛሬ፡ ግን፡ ደቅር፡ ተባላችሁ።

*ሆሴ፡ ፪፡ ፶፫፡፡ ሮሜ፡ ፱፡ ፷፭፡፡

፲፩፡ ወደጀቴ፡ ሆይ፡ *እንድ፡ እንግደች፡ እንደ፡ መንገድም፡ አላፊች፡እለምናችኋለሁ፡ነፍስን፡ ተከማት ዋጋ፡ ከሠጋዊት፡ መመኖት፡ **ትርቁ፡ ዘንድ።

*መዝ፡ ፴፱፡ ፲፫፡፡ ተምሳ፡ ፭፡ ፴፪፡፡ **ሮሜ፡ ፲፫፡ ፲፫፡፡

፲፪፡ አካሔዲችሁም፡በአሕዛብ፡ መካከል፡ አሳመሩ፡ በክፋ፡ የሚያገረባችሁ፡ *መልካሙን፡ሰራችሁን፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ በጥያቄ፡ ቀን፡ እግዚአብሔርን፡ያመሰግኑ፡ ዘንድ።

*ማቴ፡ ፭፡ ፲፮፡፡

፲፫፡ አሁንም፡ ለሰው፡ሠርዓት፡ ሁሉ፡ *ተገዙ፡ስለ፡ እግዚአብሔር፡ለንጉሠም፡ ቢሆን፡ በሁሉ፡ ላይ፡ ሁን ዋልና።

*ሮሜ፡ ፲፫፡ ፩፡ ፭፡፡ ቲቶ፡ ፫፡ ፩፡፡

፲፬፡ ለመኳንንትም፡ ቢሆን፡ ከርሱ፡ ተልከዋልና፡ በክፋ፡ አድራጎች፡ ላይ፡ መቅሠፈትን፡ ሊያመጡ፡ በበጎ፡ አድራጎች፡ ግን፡ ምስጋና።

፲፭፡ ይህች፡ የእግዚአብሔር፡ ፈቃድ፡ ናትና፡ በጎ፡ *በማድረግ፡ የሰነፎችን፡ ያለማወቅ፡ ዝም፡ ታሰኙ፡ ዘንድ።

*ም፡ ፫፡ ፲፮፡፡

፲፮፡ የሰው፡ *ልጆች፡ ሁናችሁ፡ የሰው፡ ልጅነታችሁም፡ ለክፋት፡ መሸፈኛ፡ አትሁን፡ እንጂ፡ እግዚአብሔር፡ ባሮች፡ እንጅ።

*ገላት፡ ፭፡ ፲፫፡፡

፲፯፡ ሁሉን፡ *አክብሩ። ወንድማችን፡ ውደዱ። እግዚአብሔርን፡ ፍሩ፡ ተንጉሠን፡ አክብሩ።

*ሮሜ፡ ፲፪፡ ፲፡፡ ተማቴ፡ ፮፪፡ ፮፭፡፡

፲፰፡ *ባሮች፡ ለጌተቻቸው፡ ደዝ፡በፈርሃት፡ሁሉ። ለመልካሞች፡ ብቻ፡ ለየዋዛም፡ አይደለም፡ ለጠማሞችም፡ እንጅ።

*ኤፌ፡ ፮፡ ፭፡፡ ቲቶ፡ ፪፡ ፱፡፡

፲፱፡ ይህች፡ ጸጋ፡ናትና፡ ማንም፡ ስለ፡ እግዚአብሔር፡ አዘንን፡ ቢታገሥ፡ ግፈ፡ ባገኘው፡ ጊዜ።

፳፡ ምን፡ ትምክሕት፡ አላችሁን፡ ኃጢአትን፡ ሰር ታችሁ፡ መከራ፡ ብትቀበሉና፡ ብትታገሡ። ነገር፡ ግን፡ *መልካም፡ አደርጋችሁ፡ መከራ፡ ብትቀበሉ፡ ብትታገሡም፡ ይህ፡ ጸጋ፡ ነው፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ።

*ም፡ ፫፡ ፲፱፡ ፲፯፡፡ ፱፡ ፲፱፡፡ ማቴ፡ ፭፡ ፲፡፡

፳፩፡ ለዚህ፡ ተጸርታችኋልና። ክርስቶስ፡ ደግሞ፡ ስለኛ፡ሕማም፡ ተቀብልዋልና፡ ለኛ፡ *ምሳሌን፡ትተ፡ ፈለጋውን፡ ትከተሉ፡ ዘንድ።

*ማቴ፡ ፲፮፡ ፳፬፡፡

፳፪፡ ኃጢአት፡ ያልሰራ፡ አሰትም፡ ባሏ፡ ያልተገኘ በት። ኢሳ፡ ፶፫፡ ፱፡፡ ዮሐ፡ ፯፡ ፸፮፡፡ ፪፡ ቀሮ፡ ፭፡ ፳፭፡፡

፳፫፡ ሲሰድቡትም፡ አልተሳደበም። መከራም፡ ሲያመጡበት፡ አልተቃየመም። እውነተኛውን፡ ፍርድ፡ ለሚፈርደው፡ አንጅ፡ ነፍሱን፡ ሰጠ።

ኢሳ፡ ፶፫፡ ፯፡፡

፳፬፡ እርሱ፡ *ኃጢአታችነን፡ በሥጋው፡ በንጡት፡ ላይ። ከኃጢአት፡*ወጥተን፡ለጽድቅ፡እንኖር፡ዘንድ። በቊሰሉ፡ የተፈወሳችሁ።

*፭፡ ዮሐ፡ ፫፡ ፭፡፡ ተሮሜ፡ ፮፡ ፲፭፡፡

፲፭፡ እንደ፡ *ጠፋ፡ በጎች፡ ነበራችሁና፡ ነገር፡ ግን፡ አሁን፡ ወደ፡ ነፍሳችሁ፡ ተአረያኖ፡ ጠባቂ፡ ተመለሳችሁ።

*ኢሳ፡ ፶፫፡ ፮፡፡ ሕዝ፡ ፴፬፡ ፭፡፡ ተዮሐ፡ ፫፡ ፲፪፡፡

ም፡ ፭፡ ፱፡፡

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ እንደሁም፡ አላጎት፡ ሴተች፡ ለባሎቻችሁ፡ ተገዙ። ከርሳቸው፡ ሰዎች፡ ቢያረፉ፡ ለነገር፡ የማይገዙ፡ ደረቡ፡ ዘንድ፡ ያለ፡ ነገር፡ በሴተቻቸው፡ አካሔድ።

ኤፈ፡ ፭፡ ፳፪፡፡

፪፡ የነጻችውን፡ አካሔዲችሁን፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ በፈር ሃት።

፫፡ አሊያ፡ ጌጻቸው፡ከአፈአ፡ ያይደለ፡ የራስ፡ ጸጕር፡ በመሰራት፡በወርቅም፡ ዝርግፈ፡በጌጽም፡ ልብስ።

ኢሳ፡ ፫፡ ፲፰፡፡ ፭፡ ጢሞ፡ ፪፡ ፱፡፡

፬፡ ነገር፡ ግን፡ በማጠፈ፡ በተሰወረች፡ በልብ፡ ሰውነት፡ በየዋህም፡ ነፍስ፡ ጸጥ፡ ባለ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ገናንነቱ፡ዮከበረ።

፭፡ ቀድሞ፡ እንደህ፡ነፈሳቸውን፡ ያስጌጹ፡ነበረና፡ የተቀደሱት፡ በእግዚአብሔር፡ የታመኑ፡ ሴተች፡ ለባሎቻቸውም፡ የተገዙ።

፮፡ ለአብርሃም፡ እንደ፡ ተገዛች፡ እንደ፡ሳራ፡ ጌታ ይም፡ ትለው፡ነበረች። እላጎት፡ ልጀችዋ፡ የሆናችሁ፡ መልካም፡ ስታደርጉ፡ ከፈርሃትም፡ ሁሉ፡ አንደች፡ ሳ ትፈሩ።

፯፡ አላጎትም፡ ወንደች፡ እንደሁ፡ በውቀት፡ ተቀመጡ፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ አውቃችሁም፡ የሴተች፡ ፈጥረት፡ ደካማ፡ እንደሆነ፡ አክብርዋቸው። ከላጎት ም፡ ጋራ፡ የሕይወት፡ ጸጋ፡ ደወርሳሉና፡ በነገረ፡ ሁሉ፡ ጸሎታችሁን፡ እንደትቀርጡ።

ኤፈ፡ ፭፡ ፳፭፡፡

፰፡ የዚህም፡ ፈጻሜ፡ ያንድ፡ ልብ፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡ ነው፡ ከሚያዝንም፡ ጋራ፡ የምታዝኑ። እንደ፡ ወንድ ሞችም፡ የምትወዷ። መሐሮችም። የተዋረደችሁ ም።

፱፡ በክፈም፡ክፈ፡አትመልሱ፡በስድብም፡ስድብ። ደህነን፡ ትታችሁ፡ ባርኩ፡ እንጅ። ለዚህ፡ እንደ፡ ተጸራችሁ፡ አውቃችኋልና፡ በረከትን፡ ትወርሱ፡ ዘንድ።

፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፲፭፡፡

፲፡ *ተጽፈዋልና። ሕይወትን፡ደወድ፡ ዘንድ፡ መልካምንም፡ ዘመን፡ደያ፡ ዘንድ፡ የሚሻ፡ ተመላሱን፡ ከ ክፈ፡ ደከልክል፡ ከንፈሮቹንም፡ሸንግላውን፡ እንደደ ናገረ።

*መዝ፡ ፴፬፡ ፲፫፡፡ ተያዕ፡ ፩፡ ፳፮፡፡

፲፩፡ ከክፈ፡ ደራቅ፡ መልካምም፡ ያድርግ። ሰላም ን፡ ደሻ፡ ደከተላትም።

፲፪፡ የእግዚአብሔር፡ ዓደያች፡ በጻድቃን፡ ላደ፡ ና ቸው፡ ደሮቹም፡ ልመናቸውን፡ ደሰማሉ። የእግዚአ ብሔር፡ ፊት፡ ግን፡ ክፈ፡ በሚያደርጉ፡ ላደ፡ ነው።

፲፫፡ ማነው፡ የሚጐደችሁ፡ የመልካም፡ ተከታዮ ች፡ ብትሆኑ።

መዝ፡ ፴፬፡ ፲፭፡፡ ፲፯፡ ፲፯፡፡

፲፱፡ ነገር፡ ግን፡ ስለ፡ *ጽድቅ፡ መከራ፡ ብትቀበሉ፡ ደግሞ፡ ብፁዓን፡ናችሁ። ከፍርሃታቸውም፡አትፍሩ፡ አትደንግጡም።
*ም፡ ፪፡ ፲፡—፲፭፡፡

፲፭፡ ነገር፡ ግን፡ ጌታን፡ እግዚአብሔርን፡ በልባችሁ፡ ቀድሱት። በጊዜውም፡ ሁሉ፡ የተዘጋጀችሁ፡ ሁኑ፡ ለሚጠይቃችሁ፡ ሁሉ፡ስላላችሁ፡ ተስፋ፡ ለመመለስ፡ በየውሳት፡ በፍርሃትም።

፲፮፡ በመልካም፡ ሕሊና፡ያፈፈ፡ዘንድ፡እንደ፡ክፋ፡ ሰዋች፡የሚናገሩባችሁ። መልካሙንም፡ አከሔያች ሁን፡ በክርስተስ፡ የሚያነውረ።

፲፯፡ መልካም፡ስታደርጉ፡ መከራ፡ትቀበሉ፡ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ ቢወደው። ክፈ፡ ስታደርጉ፡ መከራ፡ ከመቀበል፡ ይሻላልና።
ቍ፡ ፲፱፡፡

፲፰፡ ክርስተስ፡ ደግሞ፡ አንደግዜ፡ ስለ፡ ኃጢአት፡ አሞታልና፡ ጻድቁ፡ ስለ፡ ዓመፀኖች። እኛን፡ ወደ፡ እ ግዚአብሔር፡ ያቀርበን፡ ዘንድ። በሥጋም፡ ሞተ፡ በ መንፈስ፡ግን፡ ሕያው፡ ሆነ።
ም፡ ፪፡ ፳፭፡፡

፲፱፡ በርሱም፡ *በግዞት፡ ወደሉ፡ነፈሶች፡ ሒደ፡ሰበ ከላቸው።
*ም፡ ፱፡ ፮፡፡

፳፡ ቀድሞ፡ አምቢ፡ ብለው፡ ለነበረ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ምህረት፡ ረጅም፡ ዘመን፡በዘነፆች፡ጊዜ፡ በኖህ፡ ዘመን፡ አርሱ፡ መርከብን፡ ሲሰራ። ጥቂቶች፡ አርሳቸ ውም፡ ስምንት፡ሰዎች፡ በውኃ፡አልፈው፡ የደኑባት።
ዘፈ፡ ፯፡፲፯፡፡

፳፩፡ ለርሱም፡ ዛረ፡ ምሳሌ፡ ያለች፡ አርስዋም፡ *ጥምቀት፡ ታድነናለች። (ከሠን፡ አድፈን፡ ማፀብ፡አ ደደለም፡ የበሳ፡ ሕሊና፡ ልመና፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ እንጅ)። በየሱስ፡ክርስተስ፡ትንሣኤ።*ኤፈ፡፭፡፳፮፡፡

፳፪፡ አርሱ፡በእግዚአብሔር፡*ቀኝ፡ያለ፡ወደ፡ሰማ ይ፡ ወጥተ፡መላእክትም፡ አለቀችም፡መኳንንትም፡ ያዘዙለታል።
*ኤፈ፡፩፡፲፡፲፭፡፡

ምዕራፍ፡ ፱፡

፩፡ እንኒያህ፡ክርስተስ፡በሥጋው፡ ሕማም፡ስለኛ፡ ከተቀበለ፡ እንደሁ፡አላንት፡ ደግሞ፡ ይህነን፡ፈቃድ፡ እንደ፡ አቃ፡ ጦር፡ ልበዙ። በሥጋው፡መከራ፡ የተቀበ ለ፡ከኃጢአት፡ ወጥተዋልና።

፪፡ በሰው፡ መመኛት፡ ደግሞ፡ እንደደየር፡ በሥጋ፡ በሚቀርበት፡ ዘመን፡ ሁሉ፡ የእግዚአብሔርን፡ ፈቃ ድ፡ እንደ፡ያደርግ፡ እንጅ።

፫፡ ያለፈው፡ዘመን፡ *ይበቃናልና፡ የአሕዛብን፡ ፈ ቃድ፡ ያደረግነበት፡ በሴሰኝነት፡ ሒደን፡ ነህመመኛት ም፡ በስካርም፡ በመብልም፡ በዘፈንም፡ በርኩሰት ም፡በሚያስጸይፈም፡ በጣዖት፡ አምልኮት።
*ኤፈ፡ ፪፡ ፪፡ ፫፡፡ ቲት፡ ፫፡ ፫፡፡

፬፡ አሁንም፡ ለርሳቸው፡ ልዩ፡ ሆነችሁበት፡ ደህንነ ት፡ በሌለባት፡ባሰተኛዪቱም፡ ስራቸው፡ ስላልተከተ ላችኋቸው፡ ደሰይባችሁማል።

፭፡ አርሳቸውም፡ምላሽ፡ይሰጣሉ፡ በሕያዋንና፡ በ ሙታን፡ይፈርድ፡ዘንድ፡ላለው።፪፡ጢሞ፡፬፡፩—፰፡፡

፮፡ ስለዚህም፡ *ለሙታን፡ ደግሞ፡ በወንጌል፡ ተሰ በከ፡ እንደ፡ሰው፡ በሥጋ፡ እንደ፡ፈረድባቸው፡ በመን ፈስ፡ ግን፡ ለእግዚአብሔር፡ ሕያዋን፡እንደ፡ሆኑ።
*ም፡ ር፡ ፲፬፡

፯፡ የነገር፡ሁሉ፡ መጨረሻ፡ቀርብዋል። ስለዚህም፡ አስተውሉ፡ ለጸሎትም፡ ትጉ።
፩፡ ቀሮ፡ ፲፡ ፲፭፡፡

፰፡ ቦሉ፡ ፪፡ ፲፮፡፡

፰፡ ከሁሉም፡ በፊት፡ አርሱ፡ በርሳችሁ፡ የምትቃ ጠል፡ ፍቅር፡ ትኑርላችሁ። *ፍቅር፡ የኃጢአትን፡ ብዛ ት፡ ትሰውራለችና።
*ምሳ፡ ፲፡ ፲፪፡፡ ያዕ፡ ፭፡ ፹፡፡

፱፡ እንግዶችን፡ የምትወዷ፡ ሁኑ፡ አርሱ፡ በርሳች ሁ፡ ያለ፡ ማንጉራጕር።
ዕብ፡ ፲፫፡ ፪፡—፮፡፡

፲፡ ሁሉም፡ ኢያንደንዷ፡ በተቀበለው፡ ጸጋ፡ መጠ ን፡ ባልንጀራውን፡ያገልግለው። እንደ፡ እግዚአብሔ ር፡ እንደ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ጸጋው፡ ደህና፡ መጋቦች።

፲፩፡ የሚናገር፡ ቢሆን፡ እንደ፡ እግዚአብሔር፡ቃል፡ ይናገር። የሚያገለግል፡ እግዚአብሔር፡ኃይል፡እንደ፡ ሰጠው፡ ያገልገል፡ እግዚአብሔር፡ በሁሉ፡ ይመሰገን፡ ዘንድ፡ በየሱስ፡ ክርስተስን ምስጋና፡ ያለው፡ ችሎት ም፡ ለዘላለም። አሜን።
ሮሚ፡ ፲፪፡ ፮፡፡

፲፪፡ ወደጀቼ፡ ሆይ፡ የምትመጣባችሁን፡ መከራ፡ እንደ፡ እሳት፡ የምትሆንን፡ አታድንቁ፡ እንደ፡ልዩ፡ ስ ራ።
ም፡ ፩፡ ፮፡ ፲፡፡

፲፫፡ ነገር፡ግን፡በክርስተስ፡ሕማም፡አንድ፡በመሆና ችሁ፡ደስ፡ ይበላችሁ። ክብረ፡ በተገለጠ፡ጊዜ፡ አጅግ፡ ደስ፡ ይላችሁ፡ ዘንድ፡ደግሞ።
የሐዋ፡ ፭፡ ፶፭፡፡
ሮሚ፡ ፰፡ ፲፯፡፡ ያዕ፡ ፩፡ ፪፡፡

፲፬፡ ስለ፡ክርስተስ፡ስምም፡ቢላገድዋችሁ፡ብፁዓ ን፡ ናችሁ። ክብር፡ ያለበት፡ የእግዚአብሔር፡ መንፈ ስ፡ ያርፈባችኋልና፡ ከርሳቸው፡ ይሰደባል፡ በላንት፡ዘ ንድ፡ ግን፡ ይከብራል።
ም፡ ፪፡ ፹፡፡

፲፭፡ ነገር፡ ግን፡ ማንም፡ ከላንት፡ መከራ፡ የሚቀበ ል፡አይሁን፡አንድ፡ነፈስ፡ገደይ፡ እንደ፡ ሌባም፡ እንደ፡ ክፈ፡ ሰሪም፡ አንደ፡ ለገመኛም።

፲፮፡ ክርስቲያን፡ ግን፡ ስለ፡ ሆነ፡ቢሆን፡ አይፈር፦በ ዚህ፡ ስም፡ መክንያት፡ እግዚአብሔርን፡ *ያመሰግ ን፡አንጅ።
*ፊል፡ ፩፡ ፳፱፡፡

፲፯፡ ፍርድ፡ የሚጀመርበት፡ ጊዜ፡ አለና፡ በእግዚ አብሔር፡ ቤት። በኛም፡ የተጀመረብ፡ ከሆነ፡ የእግ ዚአብሔርን፡ ወንጌል፡ የሚክደ፡ ፍጻሜ፡ ምን፡ ይሆ ናል።
ኤር፡ ፳፭፡ ፳፱፡፡ ሕዝ፡ ፱፡ ፮፡፡

፲፰፡ ጻድቅም፡የግድ፡የሚድን፡ ከሆነ፡ ኃጢአተኛ፡ ዓመፀኛስ፡ በወዲት፡ ደገለጥ፡ ዘንድ፡ አለው።
ምሳ፡ ፲፩፡ ፴፩፡፡ ሉቃ፡ ፳፫፡ ፴፩፡፡

፲፱፡ ስለዚህም፡መከራ፡የሚቀበሉ፡ እንደ፡ እግዚ አብሔር፡ ፈቃድ፡ ነፍሳቸውን፡ ለእግዚአብሔር፡ አደ ራ፡ ይሰጡ፡ ለታመነ፡ ፈጣሪ፡ መልካም፡ በማድረግ።
መዝ፡ ፴፩፡ ፮፡፡

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ በላንት፡ ዘንድ፡ ያሉትን፡ በማማሎች፡ እለምና ችዋለሁ፡ እኔ፡*በማማሌ፡ እንደርሳቸው ም፡ ሕማም፡ የምመሰክር፡ እንድነትም፡ያለኝ፡ የሚ ገለጠውም፡ ተክብር። *፪፡ ሮሐ፡ ፩፡፡ ተርሚ፡ ፳፡ ፲፯፡፡

፪፡ በላንት፡ዘንድ፡ያለውን፡ የእግዚአብሔርን፡መ ንን፡ ትጠብቁና፡ ትጐበኝዋቸውም፡ ዘንድ፡ በግድ፡ አ ደደለም፡ በልብ፡ፈቃድ፡እንጅ። ረብ፡ ለማግኘት፡ አ ደደለም፡ በርኅራኄ፡ እንጅ። ዮሐ፡ ፳፩፡ ፲፭፡፡ የሐዋ፡ ፳፡ ፳፳፡፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፪፡፡

፫፡ እንደ፡ ጌተችም፡ *በእግዚአብሔር፡ ርስት፡ ላ ደ፡ አደደለም፡ ለመንጎች፡ ተምሳሌ፡ እንደሚሆኑ፡እ ንጅ። *፪፡ ቀር፡ ፩፡ ፳፱፡፡ ተቲተ፡ ፪፡ ፯፡፡

፬፡ የጠባቀችም፡ *አለቃ፡ በተገለጠ፡ ጊዜ፡ የማይ ጠፋውን፡ ተየክብርን፡ አክሊል፡ ትወስደላችሁ። *ዕብ፡ ፲፫፡ ፲፫፡፡ ተ፩፡ ቀር፡ ፱፡ ፲፭፡፡ ፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፲፡፡

፭፡ እንደሁም፡እላንት፡ንዐበዛዝት፡ለሽማግሌች፡ ተገዙ። *ሁላችሁም፡ እርሱ፡ በርሳችሁ፡ ተገዙ። ትሕ ትኖውንም፡ ልበሱ። ተእግዚአብሔር፡ ልባቸውን፡ የ ሚያስታብዩን፡ ደጣላልና፡ ለትሑታን፡ግን፡ ጸጋውን፡ ይሰጣል። *ኤፈ፡ ፭፡ ፳፩፡፡ ተማቴ፡ ፳፫፡ ፲፪፡፡ ያዕ፡ ፬፡ ፮፡፡

፮፡ እንኒደህ፡ዝቅ፡በሉ፡ ከጸናችው፡ ከእግዚአብ ሔር፡ እጅ፡ በታች፡ በጊዜው፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደርጋችሁ፡ ዘንድ። ኢዮብ፡ ፴፪፡ ፴፱፡፡ ያዕ፡ ፬፡ ፲፡፡

፯፡ ትጣዝያችሁንም፡ ሁሉ፡ በርሱ፡ ጣሉት፡እርሱ፡ ያስብላችኋልና። ማቴ፡ ፮፡ ፴፭፡፡ ፊል፡ ፬፡ ፮፡፡

፰፡ አቅሞውን፡ ጠብቁ፡ትጉም፡ ሰይጣን፡ ጸላታች ሁ፡እንደሚሠሁ፡አንበሳ፡ደዞራልና፡ የሚውጠውን፡ ሰው፡ ሸተ። ሉቃ፡ ፳፩፡ ፴፬፡፡ ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፮፡፡

፱፡ እርሱን፡ በሃይማኖት፡ ጸንታችሁ፡ ተቃወሙ ት። እንደህም፡ ያለ፡ መከራ፡ በዓለም፡ ባሉ፡ በወገኔ ሞቻችሁ፡ እንደፈጸም፡ እወቁ። ኤፈ፡ ፮፡ ፲፩፡፡

፲፡ የጸጋም፡ ሁሉ፡ አመላክ፡ እኛን፡ ወደ፡ ዘላለም፡ ክብሩ፡ በክርስተስ፡ የጠራ፡ የጸራ፡ ጥቂት፡ መከራ፡ ከ ተቀበላችሁ፡ በኋላ፡ እርሱ፡ ያበጀችኋል፡ ያጸናችኋል ም፡ ያበርታችኋልም፡ ይመሠርታችኋልም።

ም፡ ፭፡ ፯፡፡

፲፩፡ ለርሱ፡ ክብር፡ ችሎትም፡ ይሁን፡ ለዘላለም። አሜን።

፲፪፡ በስልዋናስ፡ እጅ፡ በታመነ፡ ወንድም፡ እኔ፡ እ ንደ፡ ቍጠርሁት፡ ጥቂት፡ ነገር፡ ጸፍሁላችሁ፡ ላጸናች ሁ፡ልመሰክርላችሁም፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር፡ እውነ ተኛ፡ ጸጋ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እላንት፡ የቀመችሁበት።

ዕብ፡ ፲፫፡ ፶፪፡፡

፲፫፡ እንደት፡ ናችሁ፡ ትላችኋላች፡ ከላንት፡ ጋራ፡ የ ተመረጸችው፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡በባቢሎን፡ያለችው፡ *ማርቀስም፡ ልጀ። የሐዋ፡ ፲፪፡ ፲፪፡ ፭፭፡፡ ፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፲፭፡፡

፲፬፡ እርሱ፡በርሳችሁ፡*ተሳለሙ፡በፍቅር፡ ሰላም። ለላንት፡ ሰላም፡ ይድረሰላችሁ፡ ለሁላችሁ፡ በክርስተ ስ፡የሱስ፡ላላችሁ።አሜን። *፭፡ ቀር፡ ፲፯፡ ፶፫፡፡

የሐዋርያ ፡ የጴጥሮስ ፡ መልእክት ፡ ሁለተኛዪቱ።

ምዕራፍ፡ ፩፡

፩፡ ከስምዖን፡ ጴጥሮስ፡ ከየሱስ፡ ክርስተስ፡ ባርያ፡ ከሐዋርያም፡ ተካክሎ፡ የከበራውን፡ ኃይማኖት፡ ከ ኛ፡ጋራ፡ ወደ፡ተቀበሉት፡ባመላካችን፡ ጽድቅ፡ በመድ ኃኒታችንም፡ በየሱስ፡ ክርስተስ።

፪፡ ጸጋ፡ ደህንነትም፡ ይብዛላችሁ፡ በእግዚአብሔ ር፡ እውቀት፡ በጌታችንም፡ በየሱስ፡ ክርስተስ።

፫፡ ያመላክነቱ፡ ኃይል፡ ለሕይወትና፡ ለመልካም፡ አምልኮ፡ የምንሻውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከሰጠ፡ እርሱን፡ በማወቅ፡ በክብሩና፡ በበጉነቱ፡ *የጸራ፡፡

*፭፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፱፡፡

፬፡ በዚህም፡ እጀግ፡ ታላቅ፡ ተስፋ፡ የከበረም፡ ተ ሰጠነ፡ የእመላካዊውን፡ባሕርይ፡ተካፈዮች፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡ ሸሽታችሁ፡ በዓለም፡ ካለው፡ ጥፋት፡ በሥጋ፡ ፍትወት።

፭፡ ስለዚህም፡ጥረትን፡ ሁሉ፡ አቅርባችሁ፡*በሃይ ማኖታችሁ፡ በጉነትን፡ ጨምረ። በበጉነትም፡ እውቀ ትን። ገላት፡ ፭፡ ፯፡ ፲፪፡፡

፮፡ በውቀትም፡መግትን፡መግዛት።በመግትንም፡ መግዛት፡ ትዕግሥትን። በትዕግሥትም፡ አምልኮን።

፯፡ በአምልኮም፡ወንድሞችን፡ መውደድን። ወን ድሞችንም፡በመውደድ፡ፍቅርን። ገላት፡ ፭፡ ፲፡፡

፰፡ ይህ፡በላንት፡ቢሆን፡ቢበዛም፡ ታካቾችና፡ ያለ፡ ፈረ፡አያደርጋችሁም፡ጌታችን፡ የሱስ፡ ክርስቶስን፡ በ ማወቅ።

፱፡ ይህም፡እንደሁ፡የሌለበት፡እርሱ፡ዕውር፡ነው፡ ጭፍንም፡ የቀደመውንም፡ ኃጢአቱን፡ ማንጻት፡ የ ረሳ። ፭፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፱፡ ፲፩፡፡

፲፡ ስለዚህም፡እላንት፡ወንድሞች፡ አብዝታችሁ፡ ተጠበቁ፡መጸራታችሁ፡ መመረጻችሁም፡ ትጸና፡ ዘን ድ። ይህን፡ ብታደርጉት፡ ከተ፡ አትሰናከሉም።

፲፩፡ እንደሁም፡በባለጠግነት፡ መግቢያው፡ደሰጣ ችኃል፡ወደ፡ ጌታችንና፡ወደ፡ መድኃኒታችን፡ወደ፡ የሱ ስ፡ ክርስተስ፡ ወደ፡ ዘላለሙ፡ መንግሥት።

፲፪፥ *ስለዚህም፡እኔ፡ቸል፡አልልም፡ ሁልግዜ፡ ሊያ
ሳስባችኋለሁ፡ ስለዚህች፡ ሁሉ፡ ምንስ፡ ብታውቋት፡
ደግሞ፡በሆነውም፡ እውነት፡ የጸናችሁ፡ ብትሆኑ።
*ሮሚ፡ ፲፭፥ ፲፬፥ ፲፭።

፲፫፥ እኔም፡ የሚገባኝ፡ ይመስለኛል፡ በዚህ፡ ማደ
ርያ፡ ባለሁበት፡ ዘመን፡ በማሳሰብ፡ ላስነሣችሁ።

፪፥ ቀር፡ ፭፥ ፩።

፲፬፥ አውቃለሁና፡ ከዚህ፡ማደርያ፡መለየቴ፡ *ፈጥ
ኖ፡አንዲሆን። ጌታችን፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ደግሞ፡ እን
ደ፡ገለጠልኝ። *ዮሐ፡ ፳፩፥ ፲፰፥ ፲፱።

፲፭፥ እኔም፡ አጣጣራለሁ፡ ይህችን፡ ነገር፡ሁልግዜ፡
የምታስቡ፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡ ከመውጣቴ፡ በኋላ።

፲፮፥ *ያሰትን፡ የበብ፡ነገር፡ተከትለንን። የጌታችን፡
የጦስ፡ ክርስቶስን፡ ኃይልና፡ መገለጥ፡ †አላስታወቅ
ናችሁምና፡ የርሱን፡ታላቅነት፡ አደተን፡ እንጅ።
*፩፥ ቀር፡ ፩፥ ፲፯። †፩፥ ቀር፡ ፪፥ ፱።

፲፯፥ ክብርና፡ምስጋና፡ ከእግዚአብሔር፡ አብ፡ ወሰ
ድዋልና፡ድምጽም፡አንደሁ፡ መጣለት፡ ከገዘነው፡ ክ
ብር፡ አንደህ፡ ሲል። *ደህ፡ ነው፡ልጀ፡ የተወደደው፡
ደስ፡የምልበት። ማቴ፡ ፫፥ ፲፯።። ያ፡ ፲፯፥ ፭።
ሉቃ፡ ፱፥ ፴፭።። ኤፈ፡ ፩፥ ፮።

፲፰፥ ደህነንም፡ድምጽ፡እኛ፡ሰማነው፡ከሰማይ፡የ
መጣለት፡እኛ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ሳለነ፡ በተቀደሰ፡ ተራራ።
ማቴ፡ ፲፯፥ ፭።

፲፱፥ ከኛ፡ጋራም፡እጅግ፡ የሚጸና፡ የትንቢት፡ ነገር፡
አለነ፡ በጎም፡ ታደርጋላችሁ፡ ብትመለከቱት፡ እንደ
*መብራት፡ በጨለማ፡ ሰፈራ፡ የሚያበራ፡ እስኪጸባ
ድረስ፡ የንጋትም፡ ኮከብ፡ በልባችሁ፡ እስኪወጣ፡ ድ
ረስ። *መዝ፡ ፻፲፱፡ ፻፷፡፡ ፪፡ ቀር፡ ፱፥ ፮።

፳፥ ደህነንም፡ አስቀድማችሁ፡ እወቁ፡ *የመጽሐ
ፍ፡ትንቢት፡ሁሉ፡ትርጓሜዋ፡ ከራስዋ፡ እንደደደለ።
*ሮሚ፡ ፲፪፥ ፮።። ፪፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፮።።

፳፩፥ ትንቢት፡ከተ፡ በሰው፡ ፈቃድ፡ አልመጣችም
ኖ፡ነገር፡ግን፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተመርተው፡ የእግዚ
አብሔር፡ቅዱሳን፡ ሰዎች፡ ተናገሩ።

ምዕራፍ ፪

፩፥ ነገር፡ግን፡ አስተኖች፡ነቢያት፡ በሕዝብ፡ ነበረ፡በ
ላንትም፡እንደሁ፡*አስተኖች፡መምህራን፡ይሆናሉ፡
የጥፋትን፡ ኀፋቄ፡ በስውር፡ የሚያገቡ፡ የ ዘቸውን
ም፡ጌታ፡ የሚክደ፡ ፈጥነውም፡ በራሳቸው፡ ላደ፡ ጥ
ፋት ፡ የሚደመጡ። *ማቴ፡ ፳፬፥ ፲፩።።
፩፥ ጢሞ፡ ፱፥ ፩።።

፪፥ *ብዙም፡ ሰዎች፡ ይከተልዋቸዋል፡ በርኩስነታ
ቸው፡ ከርሳቸውም፡ የተነሣ፡ የውነት፡ መንገድ፡ ይሰ
ደባል። *፪፥ ጢሞ፡ ፬፥ ፫፥ ፬።።

፫፥ ከብትንም፡በመውደድ፡በምናምንም፡ነገር፡ደ
ረቡባችኋል።አሌሁ፡ ፈርደታቸው፡ከብዙ፡ ዘመን፡ጀም
ሮ፡ የማይዘገይም፡ ጥፋታቸውም፡ አደተኛም።

፬፥ እግዚአብሔር፡ ያላዘነ፡ ከሆነ፡ ስለ፡ በደሉት፡
*መላእክት። ነገር፡ ግን፡ ወደ፡ ጨለማ፡ በታቸ፡ አወረ
ደቸው፡ በሰንሰለትም፡ ታሠረው፡ ለፍርድ፡ ሊጠበ
ቁ፡አሳልፎ፡ሰጣቸው። *ሄሁ፡ ቀ፡ ፮።።

፭፥ ለቀደመውም፡ ዓለም፡ አልራራለትም ፡ ስም
ንተኛውን፡ኖህን፡ጠበቀው፡አንጅ፡ የጽድቅን፡ አስተ
ማራ፡የጥፋትንም፡ ውኃ፡ አመጣ፡ በኃጢአተኖች፡ ዓ
ለም፡ላደ። ም፡ ፫፥ ፮።። ዘፈጥ፡ ፮፥ ፲፰።።

፮፥ *የሶደመንን፡የገሞራንም፡አገር፡ በአሳት፡ አቃ
ጥሎ፡ †ለጥፋት፡ ፈረደባት፡ ለሚመጡ ፡ ዓመጸኖች
ም፡ ምሳሌ፡ አደረጋት። *ዘፈጥ፡ ፲፱፥ ፳፬።።
†ዕብ፡ ፲፩፥ ፮።።

፯፥ ሎጥንም፡ጻድቁን፡ አደነው፡ ከክፈ፡ ስራቸው፡
ካካሔደቸውም፡ ርኩሰነት፡ አዝኖ፡ የነበረውን።

፰፥ በርሳቸው፡ መካከል፡ ጻድቁ፡ ተቀምጦ፡ ሳለ፡
በየቀኑ፡ጻድቅ፡ነፈሱን፡ በኃጢአት፡ነገር፡ *ያሳዝን፡ነበ
ረና፡ በማየትም፡ በመስማትም።
*መዝ፡ ፻፲፱፡ ፻፯፻።። ሕዝ፡ ፱፥ ፱።።

፱፥ እግዚአብሔር፡ ያውቃል፡ የሚያመልኩትን፡
ከመከራ፡ያድን፡ዘንድ፡ ኃጢአተኖችን፡ግን፡ ለፍርድ፡
ቀን፡ሊሣቀዩ፡ይጠብቃቸዋል። ፭፡ቀር፡ ፲፡ ፲፫።።
ራእ፡ ፫፡ ፲።

፲፡ ይልቁንም፡ ከሥጋ፡በኋላ፡ የሚሔዱ፡ በርኩሰነ
ት፡መመኖት። ጌትነትንም፡ ደንቃሉ። እርሳቸውም፡
ደፈሮች፡ ናቸው። ትቢተኖች። የሥልጣኑንም፡ ገንዘ
ት፡ቢሰድቡ፡ አደፈረም።

፲፩፥ መላእክትም፡ ከርሳቸው፡ በኃይል፡ በቸሎት
ም፡የሚበልጡ፡ የስድቡን፡ ፍርድ፡ አያመጡባቸው፡
በእግዚአብሔር፡ ፊት።

፲፪፥ አሌህ፡ ግን፡*አእምሮ፡ አንደሌላቸው፡ የፈጥ
ረታቸውንም፡ ዝንበላ፡ እንደሚከተሉና፡ ለመጸመ
ድና፡ለጥፋት፡አንደተፈጠረ፡አንበሶች፡ ናቸው፡ የማ
ያውቁትን፡ደሰድባሉ፡በጥፋታቸውም፡ ይጠፈሉ፡ የ
ኃጢአታቸውንም፡ዋጋ፡ ደወስደሉ። *ኤር፡ ፲፪፥ ፫።።
ደሁደ፡ ቀ፡ ፲።

፲፫፥ ደስታቸውን፡በቀን፡ መቀመጠል፡ ደቊኖፈታ
ል። እርሳቸውም፡ ርኩሶች፡ ነውረኖች። በመታለላቸ
ው፡ራሳቸውን፡ የሚያወፍረ፡ከላንት፡ጋራ፡ በተከማ
ቹ፡ጊዜ፡ በምሳ።

፲፬፥ ለርሳቸውም፡ ምንዝር፡ የመላበት፡ ዓይን፡ አ
ላቸው። ከኃጢአት፡ የማይጸግቡ፡ ናቸው፡ ያልጸኖች
ንም፡ነፈሰ፡ያታላሉ።ከብትን፡ በመውደድ፡ የለመደ፡
ልብ፡ አላቸው። የተረገሙ፡ ልጀች።

፲፭፥ የቀናውን፡ መንገድ፡ ትተው፡ ጠፈ። *የበለዓ
ምንም፡ የቦሶርን፡ልጅ፡መንገድ፡ ተከተሉ። ደህ፡ የግ
ፈ፡ዋጋ፡ የወደደ። *ዘኁል፡ ፳፪፥ ፯።። ራእ፡ ፪፡ ፲፬።።

፲፮፥ የጥማምኖቱንም፡ ዘለፈ፡ ተቀበለ፡ ከማትና
ገር፡ አህያ፡ በሰው፡ ቃል፡ የተናገረች፡ የነቢደንም፡ ስን
ፈና፡ የከለከለች። ዘኁል፡ ፳፪፥ ፳፰።።

፲፯፡ አሌህ፡ውኃ፡የሌለባቸው፡ ምንጮች፡ናቸው። ጽጋግም፡ኩርፈት፡የሚነደው። ጥቁር፡ጨለማ፡ ለዘላለም፡የተጠበቀላቸው።

፲፰፡ የተንበርጣጭና፡ የከንቱ፡ ነገር፡ ሲናገሩና፡ በሰ ህተት፡ከሚሔዱ፡በውነት፡ ያመለጡን፡ ሰዎች፡በሥ ጋ፡መመኖት፡ በሴሰኝነትም፡ ያባብላሉ።

፲፱፡ የሰው፡ ልጅነት፡ ተስፋ፡ ያደርጋሉ፡ አርሳቸው ም፡ የጥፋት፡ባሮች፡ናቸው። ሰው፡ከማንም፡ ቢሸነፍ፡ ለርሱ፡ አንደ፡ ባርያው፡ ደግሞ፡ ደገዛዋልና።

ዮሐ፡ ፰፡ ፴፬፡፡

፳፡ በጌታችንና፡ በመድኃኒታችን፡ በየሱስ፡ ክርስቶ ስ፡አውቀት፡ ከዓለም፡ርኩሰት፡ካመለጡ፡ በርስዋ፡ ደግሞ፡ ቢያዙና፡ቢገለበጡ፡*የኋለኛይቱ፡ ከፊተኛዪ ቱ፡የምትከፋ፡ ትሆንላቸዋለች። *ማቴ፡ ፲፪፡ ፴፩፡፡

፳፩፡ ይሻላቸው፡ ነበርና፡ የጽድቅን፡ መንገድ፡ ባያ ውቁ፡ኪያውቋት፡ ከተሰጠቻቸውም፡ ከተቀደሰች፡ ትእዛዝ፡*ኪወጡ። *ሉቃ፡ ፲፪፡ ፵፯፡ ፵፰፡፡

፳፪፡ እውነተኛ፡ ምሳሌም፡ ደመጣባቸዋል። *ው ሻ፡ወደ፡ ትፈቱ፡ተመለሰ። እርያም፡ታጽባ፡ ባዛባ፡ለ መንከባለል፡ተመለሰች። *ምሳ፡ ፳፮፡ ፲፩፡፡

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ ይህቺን፡ ሁለተኛ፡ መልእክት፡ ጻፍሁላችሁ፡ወ ደኛቹ፡ ሆይ፡ በርስዋ፡ ንጹሕ፡ ልባችሁን፡ የማነቃባት፡ በማሳሰብ። ም፡ ፭፡ ፲፫፡፡

፪፡ ከቅዱሳን፡ ነቢያት፡ ቀድሞ፡ የተባለውን፡ ነገር፡ ታስቡ፡ ዘንድ፡ የጌታችነንም፡ የዮሱስ፡ ክርስቶስን፡ ት እዛዝ፡ በኛ፡ በሐዋርያቱ፡ የተሰጠቻችሁን።

፫፡ አስቀድማችሁ፡ ግን፡ ይህን፡ እወቁ፡ በኋለኛ ው፡ዘመን፡ፈዘኖች፡ ይመጣሉና፡ በፈቃደኛቸው፡ የሚ ሔዱ፡ የሚሉም። ፭፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፭፡፡

፬፡ ወዴት፡ አለ፡ የመምጣቱ፡ ተስፈ። አባቶች፡ ከ ሞቱ፡በኋላ፡ ሁሉ፡እንደሀ፡ነው፡ ከቀደመ፡ ፍጥረት፡ ጀምሮ። ኢሳ፡ ፭፡ ፲፱፡፡ ሕዝ፡ ፲፪፡ ፷፪፡፡ ማቴ፡ ፷፬፡ ፸፭፡፡

፭፡ ይህን፡ አያውቁትምና፡ በራሳቸው፡ ፈቃድ፡ *ሰማይ፡ከጥንት፡እንደ፡ነበረ፡ ተምድርም፡ ከውኃ፡ በ ውኃም፡ጸንታ፡ በእግዚአብሔር፡ ቃል።

*ማቴ፡ ፷፬፡ ፴፮፡፡ ተዘፍጥ፡ ፩፡ ፪፡ ፯፡፡ መዝ፡ ፴፬፡ ፮፡፡

፮፡ በርስዋም፡በዚያን፡ጊዜ፡ የነበረው፡ ዓለም፡ ሠ ጠመ፡ጠፋም። ም፡ ፪፡ ፭፡፡ ዘፍጥ፡ ፯፡ ፯፩፡፡

፯፡ ዛሬም፡ የሚሆኑ፡ ሰማያት፡ ምድር፡ በዚች፡ ቃ ል፡ጸንተዋል፡ለሳት፡ ተጠብቀው፡እስከ፡ ፍርድ፡ ቀን፡ እስከ፡ ኃጢኣተኞችም፡ጥፋት፡ ቀን። ቍ፡ ፲፡፡

፰፡ ነገር፡ ግን፡ይህ፡ነገር፡ ከላንተ፡ አደሰወር፡ ወደ፱ ቹ፡ሆይ፡ አንደ፡ቀን፡ በአግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ አንደ፡ ሽህ፡አመት፡ ነውና፡ ሽህም፡ አመት፡ አንደንድ፡ ቀን።

መዝ፡ ፺፡ ፬፡፡

፱፡ *የአግዚአብሔር፡ተስፈ፡አደዘገደም፡ ሰዎች፡ ደዘገደል፡ አንደ፡መስላቸው፡ ነገር፡ ግን፡ አርሱ፡ ደታገ ሠልናል፡ ማንም፡ ቢጠፋ፡ አደወድምና፡ ሁሉም፡ ወ ደ፡ ተንስሐ፡ ደመጡ፡ ዘንድ፡ ደወደል፡ አንፎ።

*አንባ፡ ፪፡ ፫፡፡ ተ፭፡ ጢሞ፡ ፪፡ ፬፡፡

፲፡ የአግዚአብሔር፡*ቀን፡አንደ፡ሌባ፡ ደመጣልና፡ ተሰማያት፡ በታላቅ፡ መንቀቃት፡ የሚደልፈበት፡ የፈ ጥረትም፡ ሁሉ፡ሠር፡ በሳት፡ ደፈታል፡ ምድርም፡ በር ስዋም፡ያለ፡ሰራ፡ ሁሉ፡ የሚቃጠልበት።

፪፡ ተሳ፡ ፭፡ ፪፡ ፫፡፡ ተቀ፡ ፯፡፡ ማቴ፡ ፷፬፡ ፷፬፡፡ ራእ፡ ፳፡ ፲፭፡

፲፩፡ ደህም፡ ሁሉ፡ አንደህ፡ የሚፈታ፡ ሲሆን፡ እን ደ፡ምን፡ደገባቸኋል፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡ በተቀደሰች፡ አካ ሔድ፡ በመልካምም፡ አምልኮት።

፲፪፡ የአምላክን፡ ቀን፡ መምጣት፡ ስትጠብቁ፡ ወ ደርሱም፡ስትቸ ሉ።ስለርሱ፡ሰማዮች፡ተቃጥለው፡ ደፈታሉ፡የፈ ፡ ም፡ሠር፡ ደቀልጣል፡ በትኩሳት።

፲፫፡ እኛ፡ግን፡እንደ፡ ተሰፈው፡ *አደሱን፡ ሰማይ፡ አደ ሲቱንም፡ምድር፡ አንጠብቃለን፡ †ጽድቅ፡ የሚ ኖርባትን። *ኢሳ፡ ፷፭፡ ፲፯፡፡ ኖ፡ ፭፯፡ ፷፪፡፡ †ራእ፡ ፷፩፡ ፭፡ ፷፯፡፡

፲፬፡ ስለዚህም፡ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ደህን፡ ተሰፈ፡ ብታደርጉ፡ ተጣንቀቁ፡ ከርሱ፡ በሰላም፡ያለ፡ ነውር፡ያ ለ፡ ርኩሰትም፡ ትገኙ፡ ዘንድ።

፲፭፡ የጌታችነንም፡ *ትዕግሥት፡ መድኃኒት፡ ቀኖጠ ሩት፡ ጳውሎስ፡ ደግሞ፡ የተወደደው፡ ወንድማችን፡ በተሰጠችው፡ ብልሃት፡ አንደ፡ ጻፈላችሁ።

*ሮሜ፡ ፪፡ ፬፡፡

፲፮፡ አንደለችም፡ በመልእክቱ፡ ሁሉ፡ ስለዚህ፡ ነገ ር፡ሲናገርባት። መታወቋ፡ የጸና፡ነገር፡ ያለባት፡ የሚያ ጣምዋት፡ አሊያ፡ አውቀትና፡ ጽናት፡ የሌላቸው፡ ሌ ሎችን፡ መጻሕፈት፡ አንደ፡ያጣሙ፡ ደግሞ፡ ወደ፡ ጥ ፋታቸው።

፲፯፡ አላንት፡ግን፡ ወደ፱ቹ፡ ሆይ፡ ደህችን፡ ነገር፡ አ ስቀድማችሁ፡ አውቃችኋልና፡ *ተጠበቁ፡ በሰነፎች፡ ስሕተት፡ተወሰደችሁ፡ከጽናታችሁ፡ አንደትወድቁ።

*ማር፡ ፲፫፡ ፭፡ ፱፡፡ ፴፫፡፡

፲፰፡ ነገር፡ ግን፡ በጸጋ፡ ብዙ፡ በጌታችንም፡ በመድኃ ኒታችንም፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አውቀት። ለርሱ፡ ም ስጋና፡ ደሁን፡ዛሬ፡ አስከ፡ ዘላለምን፡ ቀን፡ ድረስ። አ ሜን።

የሐዋርያ : የዮሐንስ : መልእክት : መጀመርያዪቱ።

ምዕራፍ: ፩፡

፩፡ *ከመጀመርያ: ጀምሮ: የነበረ: የሰማነውም: ባይናችንም: ያየነው: የተመለከትነውም: ተእጃች ንም: የደሰሰችው: ስለ: ሕይወት: ቃል።

*ዮሐ: ፩፡፩፡፲፱፡፡ ተሉቃ: ፳፬፡፴፱፡፡

፪፡ *ሕይወትም: ተገለጸች: አየነም: እንመሰክር ማለን: በዘላለሙም: ሕይወት: እናስታውቃችኋለ ን: ተበአብ: ዘንድ: በነበረች: ለእኛም: በተገለጸች።

*ዮሐ: ፩፡ ፱፡፡ ተዮሐ: ፩፡ ፩፡፡

፫፡ ያየነውንም: የሰማነውም: እርስን: እናስታ ውቃችኋለን: ለላንት: ደግሞ: ከኛ: ጋራ: አንድነት: ትሆንላችሁ: ዘንድ: የኛ: አንድነት: ግን: ከአብ: ጋራ: ናት: ከልጁም: ከዮሱስ: ክርስቶስ: ጋራ።

፬፡ ደህችንም: ነገር: እንጽፈላችኋለን: *ደስታች ሁ: ትፈጽም: ዘንድ። *ዮሐ: ፲፭፡፲፩፡፡ ና: ፲፮፡ ፳፱፡፡

፭፡ ከርሱም: የሰማናት: የነገርናችኋትም: መልእ ክት: ደህች: ናት። *እግዚአብሔር: ብርሃን: አንድ: ሆነ: ከትም: ጨለማ: አንድ: ሌለበት። *መዝ: ፹፱፡ ፰፡፡ ዮሐ: ፳: ፲፪፡፡

፮፡ ከርሱ: ጋራ: አንድነት: አለነ: ብንል: በጨለማ: ብንመላለስ: እንዋሻለን: እውነትንም: አናደርግም። ም: ፪: ፱፡፡

፯፡ በብርሃን: ግን: ብንመላለስ: እርሱ: በብርሃን: እንደለ: ለኛ: አንድነት: አለነ: እርሱ: በርሳችን: የል ጁም: የየሱስ: ክርስቶስ: ደም: ከኃጢአት: ሁሉ: ያነ ጻናል።

፰፡ ኃጢአት: የለብነም: ብንል: እኛ: ራሳችነን: እና ስታለን: እውነትም: የለችነም።

፱፡ በኃጢአታችን: *ብንናዘዝ: እርሱ: ተየታመነና: ጻድቅ: ነው: ኃጢአታችነን: ይቅር: ይልን: ዘንድ: ከግፏ ም: ሁሉ: ያነጻን: ዘንድ። *ም: ፴፰: ፲፫፡፡ ተ፩: ተሳ: ፭: ፴፱፡፡

፲: ኃጢአት: አልሰራነም: ብንል: አሰተኛ: እናደር ገዋለን: ቃሉም: በኛ: የልነም።

ምዕረፍ: ፪፡

፩: ልጀቼ: ሆይ: ደህችን: ነገር: እጽፈላችኋለሁ: ኃ ጢአት: እንደሰረ። ከላንትም: ማንም: ኃጢአት: ቢ ሰራ: ከአብ: ዘንድ: *አማላጅ: አለነ: የሱስ: ክርስቶስ: ጻድቅ። *ሮሀሜ: ፰: ፴፬፡፡ ዕብ: ፯: ፳፭፡፡

፪፡ እርሱም: የኃጢአታችን: *መታረቅ: ነው: ግን: ስለ: ኃጢአታችን: ብቻ: አደደለም: ሰለ: ዓለም: ሁ ሉ: ኃጢአት: እንጅ። *ቀለ: ፩: ፳፡፡

፫፡ በዚህም: እናውቃለን: እንድናውቀው: ትእዛ ዙን: ብንጠብቅ።

፬፡ አውቀዋለሁ: *የሚል: ትእዛዙንም: የማደ ጠብቅ: እርሱ: አሰተኛ: ነው: እውነትም: የለበትም። *ም: ፩: ፯፡፡ ና: ፬: ፳፡፡

፭፡ ቃሉን: ግን: *የሚጠብቅ: በዚህ: የእግዚአብ ሔር: ፍቅር: በውነት: ተፈጸመች: በዚህም: እናውቃ ለን: እኛ: በርሱ: እንደለነ። *ዮሐ: ፲፬: ፳፩: ፳፫፡፡

፮፡ እኔ: በርሱ: *እናራለሁ: የሚል: ይሔድ: ዘንድ: ደገባዋል: እርሱ: እንደ: ሔደ። *ዮሐ: ፲፭: ፬: ፭፡፡

፯፡ ወንድመቼ: ሆይ: አደስ: ትእዛዝ: የምጽፈላ ችሁ: አደደለሁም: ነገር: ግን: አሮጌዪቱን: ትእዛዝ: ከጥንት: ከላንት: ጋራ: የነበረቸውን: አሮጌዪቱም: ትእዛዝ: እርስዋ: ናት: ከጥንቱ: የሰማቸሁት: ነገር።

፰፡ ደግሞ: አደስ: ትእዛዝ: እጽፈላችኋለሁ: ይ ህም: እውነት: ነው: በርሱ: በላንትም። *ጨለማ: አል ፏዋልና: የውነትም: ብርሃን: ከዚህ: ወደ: ሀ: ያበራል። *ሮሚ: ፲፫፡ ፲፪፡፡

፱፡ እኔ: በብርሃን: አለሁ: የሚል: ወንድሙንም: *የሚጸላ: እርሱ: እስከ: ዛረ: በጨለማ: ነው። *ም: ፫: ፲፭፡፡ ና: ፬: ፷፡፡

፲፡ *ወንድሙን: የሚወድ: እርሱ: በብርሃን: ደሃ ራል: ማሰነከልም: የለበትም። *ም: ፫: ፲፬፡፡

፲፩፡ ወንድሙን: ግን: የሚጸላ: እርሱ: በጨለማ: ነው: በጨለማም: ደመላለሳል: ዞሚሔድበትንም: አያውቅም: ጨለማ: ዓይኑን: አሳውሮታልና።

፲፪፡ እጽፈላችኋለሁ: አላንት: ልጀች: ኃጢአታች ሁ: *ተሰረዮችላችሁና: ስለ: ስሙ። *ሉቃ: ፳፬: ፵፯፡፡ የሐዋ: ፬: ፲፪፡፡

፲፫፡ እጽፈላችኋለሁ: አላንት: አባቶች: ከጥንት: የነበረውን: አውቃችኋልና። እጽፈላችኋለሁ: አላን ት: ጐበዛዝት: ክፈውን: አሸንፈችኋልና። እጽፈላች ኋለሁ: አላንት: ሕፃናት: አብን: አውቃችኋልና።

፲፬፡ ጻፏሁላችሁ: አላንት: አባቶች: ከጥንት: ጀም ሮ: የነበረውን: አውቃችኋልና። ጻፏሁላችሁ: አላን ት: ጐበዛዝት: አላንት: *በርትታችኋልና: የእግዚአብ ሔርም: ነገር: ጸንተባችኋል: ክፈውንም: ድል: ነሡታ ችኋል። *ኤፈ: ፮: ፲፡፡

፲፭፡ ዓለምን: አትውደዲ: በዓለምም: ያለውን። ዓለምን: በሚወድ: ሰው: የእግዚአብሔር: ፍቅር: የለበትም። ያዕ: ፬: ፬፡፡

፲፮፡ በዓለም: ያለው: ሁሉ: የሥጋ: መመኛት: የዓ ይንም: መመኛት: የሰውም: ትምክሕት። ደህም: ከአብ: አደደለም: ከዓለም: እንጅ።

፲፯፡ ዓለሙም፡ ያልፈፈ፡ ምኞቱም። የእግዚአብሔርን፡ ፈቃድ፡ ግን፡ የሚያደርግ፡ እርሱ፡ ለዘላለሙ፡ ይኖራል።

፲፰፡ ልጆቼ፡ ሆይ፡ ይህች፡ የኋለኛዪቱ፡ ጊዜ፡ ናት። እንደ፡ ሰማችሁም፡ *ሐሳዊ፡ መሢሕ፡ እንደ፡መጣ፡ አሁንም፡አሰተኞች፡ መሢሖች፡ እጅግ፡ ሆኑ። ከዚህም፡ የተነሣ፡ እናውቃለን፡ የኋለኛዪቱ፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ሆነች። *ማቴ፡ ፳፬፡ ፭፡ ፳፬፡፡

፲፱፡ ከኛ፡ *ወጡ፡ ነገር፡ግን፡ ከኛ፡ አልነበረም። ከኛ ስ፡ ሁነው፡ በነበረ፡ከኛ፡ጋራ፡ በጸኑ፡ነበር። ነገር፡ ግን፡ ወጡ፡ ይገለጡ፡ ዘንድ፡ ሁላቸው፡ ከኛ፡ እንደልሆኑ።

*የሐዋ፡ ፭፡ ፴፡፡ ፩፡ቀሮ፡ ፲፩፡ ፲፱፡፡

፳፡ እላንትም፡መቅባት፡ አላቸሁ፡ ከቅዷሱ፡ ሁሉንም፡ አውቃቸኋል። ቊ፡ ፳፯፡፡

፳፩፡ ወደላንት፡ አልጻፍሁም፡ እውነትን፡ ስላለወቃችሁ። ታውቁታላቸሁና፡ እንጅ፡ አሰትም፡ ሁሉ፡ ከውነት፡እንደደለሉ።

፳፪፡ ማነው፡ አሰተኛው፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ እንደ ሆነ፡ከሚክድ፡በቀር። ደህ፡ ነው፡ ሐሳዊ፡ መሢሕ፡ አብንም፡ ወልድን፡ የሚክድ።

፳፫፡ *ወልድን፡ የሚክድ፡ ሁሉ፡ አብ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ የለም። በወልድ፡ የሚያምን፡ አብም፡ ደግሞ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ነው። *ም፡ ፬፡ ፲፭፡፡

፳፬፡ እላንት፡ግን፡ከጥንቱ፡ የሰማችሁት፡ በላንት፡ ይጽና። ከጥንት፡ የሰማችሁት፡ በላንት፡ ቢጸና፡ እላንትም፡ ደግሞ፡ በአብና፡ በወልድ፡ ትጸናላችሁ።

፳፭፡ ደህም፡ተስፈው፡እርሱ፡ የሰጠነ፡ ነው፡ የዘላለም፡ሕይወት።

፳፮፡ ደህችን፡ ነገር፡ ጻፍሁላችሁ፡ ስለሚያስትዋችሁ።

፳፯፡ ከርሱ፡የወሰደቸኋትም፡*መቅባት፡ በለንት፡ ትጸናባችኋለች፡ማንም፡ ያስተምራችሁ፡ ዘንድ፡አት ሹም። እንደዚሁ፡ መቅባት፡ ያስተምራችኋል፡ እንጅ፡ ሰለ፡ ሁሉ። እርስም፡ እውነተኛ፡ ነው፡ አሰትም፡ አደደለም። እንደስተማራችሁም፡ ትጸኑበታል።

*ዮሐ፡ ፲፬፡ ፳፮፡፡ ፫፡፲፯፡ ፲፫፡፡

፳፰፡ አሁንም፡ልጆቼ፡ ሆይ፡ ጽኑበት፡እርሱ፡ በተገለጠ፡ጊዜ፡ድፍረት፡ይሆንልን፡ዘንድ፡ እኛም፡ ከፊቱ፡ አናፍርም፡ በመገለጡ። ም፡ ፫፡ ፳፭፡፡

፳፱፡ ጻድቅ፡ እንደሆነ፡ ካወቃችሁ፡ አወቁ፡ *ጽድቅ፡ የሚሰራ፡ ሁሉ፡ ከርሱ፡ የተወለደ፡ እንደሆነ።

*ም፡ ፫፡ ፯፡ ፲፡፡

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ አዩ፡እንዲት፡ያለውን፡ፍቅር፡ሰጠነ፡ አብ፡ *የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ እንባል፡ ዘንድ። ሰለዚህ፡ ዓለም፡ ተአያውቅነም፡ እርሱን፡ አላወቀምና።

*ዮሐ፡ ፭፡ ፲፱፡ ፲፫፡፡ ተዮሐ፡ ፲፯፡ ፫፡፡

፪፡ ወደ፱ቹ፡ ሆይ፡ አሁን፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ነን። *ገና፡ም፡ምን፡ እንሆናለን፡ አልተገለጠም፡ ነገር፡ግን፡ እርሱ፡ በተገለጠ፡ጊዜ፡ እንደርሱ፡ እንድን ሆን፡አወቅነ። እናየዋለንና፡ እርሱ፡ እንደለ።

*ሮሚ፡ ፰፡ ፲፯፡፡ ቀለ፡ ፫፡ ፱፡፡

፫፡ ደህችም፡ተስፈ፡ያለችው፡ሁሉ፡ራሱን፡ያነጻል፡ እርሱም፡ንጹሕ፡እንደ፡ሆነ።

፬፡ ኃጢአትን፡ የሚያደርግ፡ ሁሉ፡ ሕግንም፡ መተላለፍ፡ ያደርጋል። ኃጢአትም፡ እርሱ፡ ሕግን፡ መተላለፍ፡ ነው።

፭፡ እላንትም፡ ታውቃላችሁ፡ ያ፡ እንደ፡ ተገለጠ፡ ኃጢአታችነን፡ ሊያሰወግድ። ኃጢአትም፡ በርሱ፡ የለም። ኢሳ፡ ፶፫፡ ፱፡ ፭፡፡ ፩፡ጴጥ፡ ፪፡ ፳፬፡፡

፮፡ በርሱ፡ የሚኖር፡ሁሉ፡ ኃጢአት፡ አይሰራም። ኃጢአት፡ የሚሰራ፡ ሁሉ፡ አላየውም፡ አላወቀውምም። ሮሚ፡ ፮፡ ፲፱፡፡

፯፡ ልጆቼ፡ ሆይ፡ ማንም፡ አያስታችሁ። ጽድቅ፡ የሚያደርግ፡ ጻድቅ፡ነው፡ ያም፡ ጻድቅ፡ እንደ፡ ሆነ። ም፡ ፪፡ ፳፱፡፡

፰፡ ኃጢአትም፡ የሚያደርግ፡ እርሱ፡ ከሰይጣን፡ ነው፡ ሰይጣን፡ ከጥንት፡ ኃጢአትን፡ አድርጋልና። ስለ ዚህ፡ተገለጠ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ የሰይጣንን፡ ሰራ፡ ሊሽር። ዮሐ፡ ፰፡ ፵፬፡፡

፱፡ ከእግዚአብሔር፡ የሚወለድ፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡ አያደርግም። ዘሩ፡ጸንተበታልና፡ ኃጢአትም፡ደሰራ፡ ዘንድ፡ አይችልም። ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ ነውና። ቊ፡ ፱፡ ም፡ ፭፡ ፲፰፡፡

፲፡ በዚህ፡ይታወቃሉ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ የሰይጣንም፡ልጆች። ጽድቅ፡ የማያደርግ፡ ሁሉ፡ ከእግዚአብሔር፡ አደደለም፡ ወንድሙንም፡ የማይወድ፡ እንደሁ፡ ነው።

፲፩፡ ደህ፡ ነው፡ ከቀደመው፡ የሰማችሁት፡ ትእዛዝ፡እርሱ፡ በርሳችን፡እንዋደድ፡ዘንድ።

ዮሐ፡ ፲፫፡ ፴፬፡፡

፲፪፡ ከክፈ፡ እንደ፡ ሆነ፡እንደ፡ *ቃየል፡ አደደለም፡ ወንድሙንም፡ገደለው። ለምንስ፡ገደለው። ስራው፡ ክፈ፡ነበረ፡ የወንድሙ፡ ግን፡ መልካም፡ ነበር።

ዘፈጥ፡ ፬፡ ፰፡፡ ማቴ፡ ፳፫፡ ፴፭፡፡ ደሁደ፡ ቊ፡ ፲፭፡፡

፲፫፡ አታድንቁ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ዓለም፡ ቢጸላችሁ። ማቴ፡ ፭፡ ፲፩፡፡ ዮሐ፡ ፲፭፡ ፲፰፡ ፲፱፡፡

፲፬፡ እኛ፡ከሞት፡ወጥተን፡ ወደ፡ ሕይወት፡ እንደ፡ ደረስነ፡ *እናውቃለን። ወንድሞችን፡ እንወደለንና። ተወንድሙን፡ የማይወድ፡ በሞት፡ ይኖራል።

*ዮሐ፡ ፭፡ ፳፬፡፡ ም፡ ፱፡ ፲፩፡፡ ተዘሌዋ፡ ፱፡ ፲፯፡፡

፲፭፡ ወንድሙን፡የሚጸላ፡ሁሉ፡ነፍሰ፡ገደደ፡ነው። እላንትም፡ ታውቃላችሁ፡ነፍሰ፡ ገደደ፡ ሁሉ፡ የዘላለም፡ሕይወት፡ እንደሌለው። ማቴ፡ ፭፡ ፳፩፡ ፳፪፡፡

፲፮፡ በዚህ፡ ፍቅረን፡ አወቅነ፡ ስለኛ፡ ራሱን፡ ለውጦታልና። ለኛም፡ይገባል፡ራሳቸነን፡ስለ፡ ወንድሞች፡ እንለውጥ፡ዘንድ።

፲፯፡ የዚህ፡ዓለም፡ጥሪት፡ ያለው፡ ወንድሙንም፡ አንጀት፡ሲግ፡ የሚያየው፡ ርኅራኄውንም፡ የሚከለ ክልበት፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ እንዲት፡ ያኖርበ ታል።
ም፡ ፬፡ ፮፡፡

፲፰፡ ልጆቼ፡ ሆይ፡ አንውደድ፡ በቃል፡ በመላስም፡ በስሬዶ፡በውነት፡አንጂ። ያዕ፡ ፩፡ ፮፪፡፡ ዮ፡ ፪፡ ፲፭፡፡

፲፱፡ በዚህም፡ እናውቃለን፡ እኛ፡ ከውነት፡ እንደ ሆነ፡ በፊቱም፡ ልባችንን፡ እናሳርፈለን።

፳፡ ልባችን፡ ቢነቅፈን፡ እግዚአብሔር፡ ከልባችን፡ ይበልጣልና፡ ሁሉንም፡ ያውቃል።

፳፩፡ ወደጀቼ፡ ሆይ፡ልባችንስ፡ ባይነቅፈን፡ *ድፈረ ት፡አለነ፡ወደ፡ እግዚአብሔር።
*ም፡ ፪፡ ፮፳፡፡
ዮ፡ ፬፡ ፲፯፡፡ ሮሜ፡ ፭፡ ፩፡ ፪፡፡ ዕብ፡ ፬፡ ፲፯፡፡

፳፪፡ የምንለምነውንም፡ ሁሉ፡ ከርሱ፡ እንወሰደ ለን፡ ትእዛዙንም፡ እንጠብቃለንና፡ በፊቱም፡ ደስ፡ የሚያሰኘውን፡ነገር፡እናደርጋለንና። ማር፡ ፲፩፡ ፳፱፡፡

፳፫፡ *ትእዛዙም፡ ይህች፡ ናት፡ እናምን፡ ዘንድ፡በ ልጁ፡ በዮሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሰም፡ እርሱ፡ በርሳችንም፡ †እንዋደድ፡ዘንድ፡ትእዛዙን፡ እንደ፡ሰጠነ።
*ዮሐ፡ ፮፡ ፷፱፡፡ †ማር፡ ፲፪፡ ፴፭፡፡

፳፬፡ ትእዛዙንም፡*የሚጠብቅ፡ በርሱ፡ ይኖራል፡ እርሱም፡ ደግሞ፡ በርሱ፡ ይኖራል። በዚህም፡ እናው ቃለን፡ እርሱ፡ በኛ፡ እንደ፡ናር፡ለኛ፡ ከሰጠው፡ ከመን ፈሱ።
*ዮሐ፡ ፲፱፡ ፷፫፡፡

ምዕራፍ፡ ፬፡

፩፡ ወደጀቼ፡ ሆይ፡ መንፈስን፡ ሁሉ፡ አትመኑ። መ ናፍሰትን፡ ፈተኑ፡ እንጂ፡ ከእግዚአብሔር፡ እንደ፡ሆ ኑ።ብዙ፡ ያሰት፡ ነቢያት፡ ወደ፡ ዓለም፡ ወጥተዋልና።

፪፡ በዚህ፡የእግዚአብሔርን፡ መንፈስ፡ታውቃላች ሁ።የሚያምን፡መንፈስ፡ሁሉ፡የሱስ፡ክርስቶስ፡ በሥ ጋ፡ እንደ፡ መጣ፡ እርሱ፡ ከእግዚአብሔር፡ነው።
፩፡ቀር፡ ፲፪፡ ፫፡፡

፫፡ የማያምንም፡መንፈስ፡ሁሉ፡ የኩስ፡ክርስቶስ፡ በሥጋ፡ እንደ፡ መጣ፡እርሱ፡ ከእግዚአብሔር፡ አደደ ለውም። ይህም፡የሐሳዊ፡ መሢሕ፡ መንፈስ፡ ነው፡ እንደ መጣ፡ የሰማችሁት፡ አሁንም፡ እርሱ፡ በዓለ ም፡ነው።

፬፡ አላንት፡ከእግዚአብሔር፡ ናችሁ፡ ልጀቼ፡ ሆይ፡ አሸንፈችኋቸው፡ውሰማል፡ በላንት፡ ያለው፡ ይበልጣልና፡ በዓለም፡ዓለም፡ነው። ፪፡ ነገሥ፡ ፮፡ ፲፯፡፡ ፭፡ ዜና፡ ፴፪፡ ፯፡፡

፭፡ እርሳቸው፡ ከዓለም፡ ናቸው። ስለዚህ፡ ከዓለ ም፡ ይናገራሉ፡ ዓለምም፡ ይሰማቸዋል።
ዮሐ፡ ፫፡ ፴፭፡፡ ዮ፡ ፲፭፡ ፲፱፡፡

፮፡ እኛ፡ ከእግዚአብሔር፡ ነኝ። እግዚአብሔርን፡ የሚያውቅ፡ ይሰማናል። ከእግዚአብሔር፡ ያልሆነ፡ አይሰማንም። በዚህ፡ እናውቃለን፡ የውነቱን፡ መን ፈስና፡ የስሕተቱን፡መንፈስ።
ዮሐ፡ ፰፡ ፴፯፡፡

፯፡ ወደጀቼ፡ ሆይ፡ እርሱ፡ በርሳችን፡ እንዋደድ፡ ፍ ቅር፡ ከእግዚአብሔር፡ናትና። የሚወድም፡ ሁሉ፡ ከ እግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ ነው፡እግዚአብሔርንም፡ ያውቃል።

፰፡ የማይወድም፡ እግዚአብሔርን፡ አላወቀም። እግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ነውና።

፱፡ በዚህ፡ ተገለጠ፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ወደ ኛ፡ እግዚአብሔር፡ አንድ፡ ልጁን፡ ወደ፡ ዓለም፡ ልኳ ልና፡ በርሱ፡እንድንበት፡ዘንድ።
ዮሐ፡ ፫፡ ፲፮፡፡
ቲተ፡ ፪፡ ፲፩፡፡

፲፡ ፍቅርም፡በዚህ፡ናት። እኛ፡እግዚአብሔርን፡እ ንደ፡ ወደድነው፡ አደደለም፡ እርሱ፡ እንደ፡ ወደደ፡ አንጅ። ልጁንም፡ እንደ፡ ላከ፡ ማስተሰረያ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ስለ፡ ኃጢአታችን።
ሮሜ፡ ፭፡ ፲፡፡
፪፡ ቀር፡ ፭፡ ፲፱፡፡ ቀለ፡ ፩፡ ፮፡፡

፲፩፡ ወደጀቼ፡ ሆይ፡ እግዚአብሔር፡ እንደሀ፡ የወ ደደን፡ ከሆነ፡ ለኛም፡ እርሱ፡ በርሳችን፡ እንዋደድ፡ ዘ ንድ፡ ደገባናል።
ማቴ፡ ፲፰፡ ፴፫፡፡

፲፪፡ እግዚአብሔርን፡ ማንም፡ ከተ፡ አላየውም። እርሱ፡ በርሳችን፡ ብንዋደድ፡ እግዚአብሔር፡ ደናር ብናል። ፍቅረም፡ በኛ፡ የተፈጸመች፡ ናት።
*ዘፀአ፡ ፴፫፡ ፮፡፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፲፰፡፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፮፡ ፲፮፡፡

፲፫፡ በዚህ፡ እናውቃለን፡ እኛ፡ በርሱ፡ እንድንኖር፡ እርሱም፡ በኛ፡ ከመንፈሱ፡ ሰጥተናልና።

፲፬፡ እኛም፡አደተናል፡እንመሰክርማለን፡ አብ፡ል ጁን፡እንደ፡ላከ፡የዓለም፡መድኃኒት፡ ይሆን፡ ዘንድ።

፲፭፡ የሱስ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ እንደ፡ሆነ፡የሚ ያምን፡ እግዚአብሔር፡ ደናርበታል፡ እርሱም፡በእግ ዚአብሔር፡ ደናርበታል፡ እርሱም፡በእግዚአብሔር።
ም፡ ፭፡ ፭፡፡

፲፮፡ እግዚአብሔርም፡ ወደኛ፡ ያለችውን፡ ፍቅር፡ እኛ፡ አወቅነ፡ አመንነም። እግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ነው። በፍቅርም፡ የሚኖር፡ በእግዚአብሔር፡ ደናራ ል፡እግዚአብሔርም፡ በርሱ።

፲፯፡ በዚህ፡ ፍቅረ፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ተፈጸመች፡ ድፈረ ት፡ ትሆንልን፡ዘንድ፡ በፍርድ፡ቀን። እርሱ፡እንደሆነ፡ እንደሁም፡ እኛ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ነነ።
ም፡ ር፡ ፹፭፡፡

፲፰፡ በፍቅር፡ ፍርሃት፡ የለም። የተፈጸመች፡ ፍቅ ር፡ፍርሃትን፡ወደ፡ሚደ፡አውጥታ፡ትዋላለች፡እንጂ። በፍርሃት፡ ሠቃይ፡ነውና። የሚፈራም፡ በፍቅር፡ አል ተፈጸመም።

፲፱፡ እኛ፡ እንወደዋለን፡ እርሱ፡አስቀድሞ፡ወደና ልና።

፳፡ እግዚአብሔርን፡ እወደለሁ፡ ብሎ፡ ወንድሙ ን፡ የሚጸላ፡አሰተኛ፡ነው። ያየውን፡ ወንድሙን፡ ያ ልወደደ፡ ያላየውን፡እግዚአብሔርን፡ ደወድ፡ዘንድ፡ አንደት፡ ይችላልና።
*ም፡ ፪፡ ፱፡ ፲፭፡፡

፳፩፡ ደህችንም፡ ትእዛዝ፡ ከርሱ፡ ተቀበልነ። እግ ዚአብሔርን፡ የሚወድ፡ ወንድሙን፡ ደግሞ፡ እንደ ወድ።
ማር፡ ፲፪፡ ፴፩፡፡

ምዕራፍ፡ ፭፡

፩ ዐ የሚያምን፡ ሁሉ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ እንደ፡ሆነ፡ እርሱ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ ነው። ወላጁን ም፡ የሚወድ፡ ሁሉ፡ ከርሱ፡ የተወለደውን፡ ደግሞ፡ ይወደዋል። ዮሐ፡ ፩፡ ፲፪፡ ፲፫፡፡

፪ *በዚህ፡ እናውቃለን፡ እኛ፡ የእግዚአብሔርን፡ ልጆች፡ እንደ፡ ወደድነ፡ እግዚአብሔርን፡ ብንወድ፡ ትእዛዙንም፡ብንጠብቅ። *ም፡ ፫፡ ፲፬፡፡

፫ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ይህች፡ ናትና፡ *ትእዛ ዙን፡እንጠብቅ፡ዘንድ፡ ትእዛዙም፡ †የከበደች፡ አይ ደለችም። *ዮሐ፡ ፲፱፡ ፲፭፡ ፳፫፡ ፳፱፡፡ †ማቴ፡ ፲፩፡ ፴፡፡

፬ ከእግዚአብሔር፡ *የተወለደ፡ ሁሉ፡ ዓለምን፡ ያሸንፋልና። ዓለምንም፡ †የምናሸንፍበት፡ማሸነፊ፡ ሣይ ማናቸችን፡ ናት። *ዮሐ፡ ፭፡ ፲፫፡፡

†ዮሐ፡ ፲፮፡ ፴፫፡፡

፭ ማነው፡ *ዓለምን፡ የሚያሸንፈ፡ የሱስ፡ የእግ ዚአብሔር፡ ልጅ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከማያምን፡ እንጂ። *ም፡ ፱፡ ፱፡፡ ፭፡ ቀሮ፡ ፲፭፡ ፱፯፡፡

፮ ይህ፡ ነው፡ በውኃና፡ በደም፡ የመጣው፡ እርሱ ም፡ የሱስ፡ ክርስቶስ። *በውኃ፡ብቻ፡ አይደለውም፡ በውኃና፡ በደም፡ እንጂ። መንፈስም፡የሚመሰክር፡ ነው። መንፈስ፡ እርሱ፡ እውነት፡ ነውና።

†ዮሐ፡ ፲፱፡ ፴፱፡ ፴፭፡፡

፯ በሰማይ፡ የሚመሰክሩ፡ *ሶስት፡ ናቸውና፡ እር ሳቸውም፡አብ፡ ቃልም፡መንፈስ፡ቅዱስም። እሌህ፡ ሶስትም፡ አንድ፡ ናቸው። *ማቴ፡ ፳፰፡ ፲፱፡፡

፰ በምድርም፡ የሚመሰክሩ፡ሶስት፡ ናቸው፡ እር ሳቸውም፡ መንፈስ፡ ውኃም፡ ደምም። ሶስቱም፡ ባ ንድ፡ ይገድማሉ።

፱ የሰውን፡ምስክር፡ብንቀበል፡ የእግዚአብሔር፡ ምስክር፡ እጅግ፡ይበለጣል።ይህች፡የእግዚአብሔር፡ ምስክር፡ናትና፡ስለ፡ልጁ፡የመሰከረባት፡ ዮሐ፡፭፡ ፴፯፡፡

፲ በእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ የሚያምን፡ምስክር፡ በ ነፍሱ፡ አለው። ለእግዚአብሔር፡ የማያምን፡ አሰተ ኛ፡ አደረገው፡ እግዚአብሔር፡ ስለ፡ ልጁ፡ በመሰከረ ባት፡ ምስክር፡ አላመነምና። ሮሜ፡ ፫፡ ፲፯፡፡ ዮሐ፡ ፫፡ ፴፮፡፡

፲፩ ምስክሪቱም፡ይህች፡ ናት። እግዚአብሔር፡ የ ዘላለምን፡ ሕይወት፡ እንደ፡ ሰጠነ። ይህችም፡ ሕይ ት፡በልጁ፡ አለች። ዮሐ፡ ፭፡ ፱፡፡

፲፪ ወልድ፡ ያለው፡ሕይወት፡ አለችው። የእግዚ አብሔር፡ ልጅም፡ የሌለው፡ ሕይወት፡ የለችውም።

፲፫ ይህችን፡ ነገር፡ ጻፍሁላችሁ፡ አላንት፡ በእግዚ አብሔር፡ ልጅ፡ ስም፡ ያመናችሁ፡ ታውቁ፡ዘንድ፡ የዘ ላለመ፡ ሕይወት፡ እንደ፡ላችሁ።

፲፬ ይህችም፡ *ድፍረት፡ ናት፡ በኛ፡ ያለችው፡ ከር ሱ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ፈቃዷ፡ አንደ፡ችን፡ብንለምነው፡ አ ርሱ፡ሊሰማነ። *ም፡ ፭፡ ፲፬፡፡ ፫፡ ፲፭፡፡ ኤፈ፡ ፫፡ ፲፪፡፡ ዕብ፡ ፱፡ ፲፯፡፡

፲፭ ብናውቅም፡የለመነውን፡እንደ፡ሰማነ፡እናው ቃለን፡ ከርሱ፡ የለመንውን፡ ልመና፡ እንድንወስድ።

፲፮ ማንም፡ ወንድሙን፡ሞት፡የማይገባት፡ ኃጢ አት፡ ሲሰራ፡ ቢያየው፡ ይለምን፡ እግዚአብሔርም፡ ሕይወት፡ ይሰጠዋል። ሞት፡ የማይገባት፡ኃጢአት፡ ለሚሰረ። ሞት፡ የሚገባት፡ ኃጢአት፡ አለች። ስለ ርስዋ፡ የምል፡ አይደለሁም፡ለርሱ፡ይለምን፡ ዘንድ። ማቴ፡ ፲፪፡ ፴፩፡፡

፲፯ ግፍ፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡ ነው፡ ለሞትም፡ የማት ሆን፡ ኃጢአት፡ አለች።

፲፰ *እናውቃለን፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡ እንደ፡ይሰራ፡ከእግዚአብሔር፡የተወ ለደ፡ ራሱን፡ ይጠብቃል፡ አንጂ፡ ክፈም፡ አይነካው ም። *ም፡ ፫፡ ፱፡፡ ፪፡ ተሰ፡ ፫፡ ፫፡፡

፲፱ አኛም፡እናውቃለን፡ከእግዚአብሔር፡እንደ፡ ሁነ፡ዓለሙም፡ሁሉ፡በክፈ፡ተደዝዋል።ገላት፡ ፩፡ ፬፡፡

፳ እናውቃለን፡ ግን፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ እን ደ፡መጣ፡እውቀትንም፡ሰጠነ። አውነተኛው፡የሚሆ ነውን፡እናውቅ፡ዘንድ።አኛም፡በውነተኛው፡አነናራ ለን፡በልጁ፡በየቡስ፡ክርስቶስ።ይህ፡ነው፡ *አውነተኛ፡ አምላክ፡ የዘላለሙም፡ ሕይወት። *ዮሐ፡ ፲፯፡ ፫፡፡ ሮሚ፡ ፱፡ ፭፡፡ ፩ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፯፡፡ ዕብ፡ ፩፡ ፰፡፡

፳፩ ልጆቼ፡ ሆይ፡ ከጣዖታት፡ ተጠበቁ። አሜን። ዘፀአ፡ ፳፡ ፫፡፡ ፩ ቀሮ፡ ፲፡ ፲፱፡፡

የሐዋርያ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ ሁለተኛዪቱ።

፩ ከሸማሌው፡ ወደ፡ ተመረጠች፡ *እመቤትና፡ ልጆችዋ፡ እኔ፡ ተወደምወደዮው፡ በውነት። እኔም፡ ብቻ፡ አደደለሁም፡ አውነትን፡ የሚያውቁ፡ ሁሉ፡ እ ንጂ። *፩ ጴጥ፡ ፭፡ ፩፡፡ †፫፡ ዮሐ፡ ፩፡፡

፪ ስለ፡ አውነት፡ ስለሚጸና፡ ለዘላለሙም፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ይኖራል።

፫ ጸጋ፡ ምህረትም፡ ሰላምም፡ ከላንት፡ ጋራ። ይሆ ኑ፡ከእግዚአብሔር፡አብ። ከጌታችንም፡ ከየሱስ፡ ክ ርስቶስ፡ ከአብ፡ ልጅ፡ በውነት፡ በፍቅርም።

፬ እጅግ፡ ደሰለኝ፡ ከልጆችሽ፡ አግኝቻለሁና፡ በው ነት፡ የሚሔዱ፡ ከአብ፡ ትእዛዝ፡ አንደ፡ ወሰድናት።

፭ አሁንም፡ እኔ፡አለምንሻለሁ፡ አመቤቴ፡ ሆይ፡

አደሰ፡ ትእዛዝ፡እንደሚጽፈልሽ፡ አይደለም፡ ከጥንቱ፡ በኖ፡የነበረችውን፡ ትእዛዝ፡እንጅ። እርሱ፡ በር ሳችን፡ እንዋደድ፡ ዘንድ። ፭፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፯፡፡

፮፡ ፈቅርም፡ ይህች፡ ናት፡ በትእዛዙ፡ እንሔድ፡ ዘንድ። ይህች፡ ትእዛዝ፡ ናት፡ ከጥንት፡ እንደ፡ ሰማች ሁ፡ ትሔደባት፡ ዘንድ።

፯፡ ብዙ፡ አሳቾች፡ ወደ፡ ዓለም፡ ገብተዋልና፡ የማ ያምኑ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ በሥጋ፡ እንደ፡ መጣ። ይህ፡ ነው፡ አሳች፡ ሐሳዊም፡ መሢሕ።

፭፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፲፰፡፡ ና፡፬፡ ፭፡—፫፡፡

፰፡ ተጠበቁ፡ በራሳችሁ፡ ምግባራችነን፡ እንደያጠ ፋ፡ ፊጹምን፡ ዋጋ፡ እንድንወስድ፡ እንጅ።

ገላት፡ ፬፡ ፲፩፡፡

፱፡ የሚወጣ፡ ሁሉ፡ በክርስቶስ፡ ትምህርትም፡ የ ማይጸና፡ አምላክ፡ የለውም። በክርስቶስ፡ ትምህር ት፡የሚጸና፡ ለዚያ፡ አብ፡ ወልድ፡ አለው።

፭፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፳፪፡ ፳፫፡፡

፲፡ ማንም፡ ወደላንት፡ ቢመጣ፡ ይህነንም፡ ትምህ ርት፡ ባያመጣ፡ በቤታችሁ፡ አትቀበሉት፡ አትሳለሙ ት። ፪፡ ተሰ፡ ፫፡ ፮፡፡

፲፩፡ እርሱን፡ የሚሳለመው፡ በክፈ፡ ስራው፡ ደገኛ ኑዋልና።

፲፪፡ እጅግ፡ ነገር፡ አለኝ፡ የምጽፈላችሁ፡ ነገር፡ ግን፡ አልወደድሁም፡ በወረቀትና፡በቀለም፡አጽፈላችሁ፡ ዘንድ፡ ተስፈ፡አደረጋለሁ፡እንጅ፡ወደላንት፡ አመጻ፡ ዘንድ፡ አፈ፡ላፈም፡ እነግራችኋለሁ፡ደስታችሁ፡ ፈጹ ም፡ ይሆን፡ ዘንድ። ፫፡ ዮሐ። ቍ፡ ፲፫፡፡

፲፫፡ እንደት፡ነሽ፡ ይሉሻል፡የተመረጠችው፡የትሽ፡ ልጀች። አሜን።

የሐዋርያ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ ሶስትኛዪቱ ።

፩፡ ከሽማግሌው፡ ወደ፡ ጋይዮስ፡ወደ፡ ወደጅ፡እኔ፡ *የምወደው፡ በውነት። *፪፡ ዮሐ። ቍ፡ ፩፡፡

፪፡ ወደጂ፡ ሆይ፡ ከሁሉ፡ በፊት፡ ደህና፡ ባለ፡ ጤና ም፡ ትሆን፡ ዘንድ፡ እመኝልሃለሁ፡ ነፍስህ፡ ደህና፡ እ ንደ፡ ሆነች።

፫፡ እጅግ፡ ደስ፡ብሎኛልና፡ወንድሞች፡መጥተው፡ ስለ፡ እውነትህ፡ በመሰከሩ፡ ጊዜ፡ አንተ፡ በውነት፡ እ ንድትሔድ። ፪፡ ዮሐ፡ ፬፡፡

፬፡ ከዚህ፡የበለጠ፡ ደስታ፡የለኝም፡እሰማ፡ዘንድ፡ ልጀቼ፡በውነት፡ እንደሔዱ።

፭፡ ወደጂ፡ ሆይ፡ መልካም፡ ስራ፡ ነው፡የምትሰራ ው፡ ሁሉ፡ በወንድሞች፡ በስደተኞችም።

፮፡ ስለ፡ ፍቅርህ፡ የመሰከረ፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ፊት። መልካም፡ ትሰራለህ፡ በሰደድሳቸው፡ ጊዜ፡ ለ እግዚአብሔር፡ እንደ፡ገባ።

ቲቶ፡ ፫፡ ፲፫፡፡

፯፡ ስለ፡ ስሙ፡ ወጥተዋልና፡ ከአሕዛብም፡ አንደ ኞ፡ አልወሰደም። ማቴ፡ ፲፡ ፭፡፡ ፪፡ ቀሮ፡ ፱፡ ፲፪፡ ፲፭፡፡

፰፡ ለኞም፡ደገባናል፡እንደለዚህ፡ያሉትን፡እንቀበ ል፡ዘንድ፡ የሰራ፡ ባልንጀሮች፡ ከውነት፡ ጋራ፡ እንድን ሆን።

ዕብ፡ ፲፫፡ ፪፡፡

፱፡ ለቤተ፡ ክርስቲያን፡ ጻፊሁ፡ ነገር፡ ግን፡ ድዮትፌ ፍስ፡ በርሳቸው፡ ላይ፡ አለቅነት፡ የወደደ፡ አልተቀበ ለነም።

፲፡ ስለዚህም፡ በመጣሁ፡ ጊዜ፡ ባደረጋት፡ ስራ፡አሳ ስበዋለሁ፡ በክፈም፡ በኖ፡ ላይ፡ በሚናገርብኝ። በዚህ ም፡ ብቻ፡ አይበቃውም፡ ወንድሞችንም፡ አይቀበል ምና። ደቀበልዋቸው፡ ዘንድ፡ የሚወጂንም፡ አደተ ውም፡ ከቤተ፡ ክርስቲያንም፡ ያወጣቸዋል።

፲፩፡ ወደጅ፡ ሆይ፡ በክፈ፡ አትከተል፡ በመልካም፡ እንጅ። መልካም፡ የሚያደርግ፡ እርሱ፡ ከእግዚአብ ሔር፡ ነው። ክፈን፡ የሚያደርግ፡ እግዚአብሔርን፡ አ ላየውም። ፫፡ ዮሐ፡ ፫፡—፮፡፡

፲፪፡ ድሜጥሮስ፡ ከሁሉ፡ ተመሰክሮለታል፡ ከእው ነትም፡ ደግሞ። እኛም፡ደግሞ፡እንመሰክርለታለን፡ ምስክርነታችንም፡ *እውነት፡ እንደ፡ ሆነች፡ ታውቃላ ችሁ። *ዮሐ፡ ፲፱፡ ፴፭፡፡ ና፡ ፷፭፡ ፷፱፡፡

፲፫፡ እጅግ፡ ነገር፡ አለኝ፡ የምጽፈልህ፡ ነገር፡ ግን፡ አ ልሻሁም፡ በቀለምና፡ በብርዕ፡ አጽፈልህ፡ ዘንድ።

፪፡ ዮሐ፡ ቍ፡ ፲፪፡፡

፲፬፡ ፈጥኜ፡ አደህ፡ ዘንድ፡ ተስፈ፡አደርጋለሁ፡ እን ጅ፡ አፍ፡ላፈም፡ እንናገራለን።

፲፭፡ ሰላም፡ ላንት፡ይሁን። ወደጀቾችን፡ እንዲት፡ ነህ፡ ያሉሳል። አንተም፡ ወደጀችን፡ እንዲት፡ ናቸሁ፡ በል፡ስሙን፡ ጸርተህ፡ በያንዳንዷ።

የሐዋርያ : የደሁደ : መልእክት፡፡

፩ ከደሁደ፡ ከየሱስ፡ክርስቶስ፡ባርያ፡*ከያዕቀብ፡ ወንድም፡ በእግዚአብሔር፡ አብ፡ ወደ፡ተጸረት፡ በየ ሱስ፡ ክርስቶስም፡ ወደ፡ ተጠበቁ፡ወደ፡ ተቀደሱ፡፡

*ማቴ፡፲፫፡ ፶፭፡፡

፪ ምህረት፡ሰላምም፡ፈቅርም፡ ትብዛላችሁ፡፡

፫ ወደ፱ቴ፡ ለሁላችን፡ ሰላለ፡ ሰለ፡ ደህንነት፡እጽ ፍላችሁ፡ ዘንድ፡ አጅግ፡ ታጥረ፡ ሳለሁ፡ እንደ፲ድ፡ አየሁት፡ ጽፈ፡ አመክራችሁ፡ ዘንድ፡!ለቅደሳን፡ አን ድ፡ ጊዜ፡ ለተሰጠችው፡ *ሃደማናት፡ አንድትጋደሉ፡፡

*፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፰፡፡

፬ ሰዉች፡ ቀሰ፡ ብለው፡ ገብተዋልና፡ አሰቀድሞ፡ ለዚህ፡ ፍርድ፡ የተጻፈ። እርሳቸውም፡እግዚአብሔ ርን፡ *የማደፈረ፡ ደምላካችነንም፡ ጸጋ፡ በርኩሰት፡ የለወጡ፡ አንደ፲ንም፡ አምላካችነንና፡ ጌታችነን፡የሱ ሰ፡ክርስቶስ፡ የካደ፲ት። *ቲተ፡ ፩፡ ፲፭፡፡

፭ አሳስባችሁም፡ዘንድ፡ አወደለሁ፡ ምንሰ፡ አን ደግዜ፡ ደህነን፡ ብታውቁት፡ እግዚአብሔር፡ ሕዝቡ ን፡ ከግብጽ፡ ምድር፡ አንደደነ፡ ሁለተኛም፡ ያላመኑ ት፡ን፡ ፈጽሞ፡ አንደጠፈ።። ዘኁል፡ ፲፬፡ ፴፭፡፡ ፩፡ ቀሮ፡ ፲፡ ፭፡፡

፮ አለቅነታቸውንም፡ ያልጠበቁትን፡ ሰፈራቸው ንም፡ የተው፡ አንጅ፡ *መላእክት፡ በጨለማ፡ ውሥ ጥ፡ ጠበቃቸው፡ በዘላለም፡ አሥራት፡ አሰከ፡ ታላቁ፡ ቀን፡ ፍርድ።። *ዮሐ፡ ፰፡ ፶፬፡፡

፯ አንደ፡ሶደምና፡አንደ፡ገሞራ፡በዙርያቸውም፡ አንደ፡ነበረ፡አገሮች፡ዝሙት፡ያደረጉ፡አንደርሳቸው፡ ከሌላ፡ ሥጋም፡ በኋላ፡ የሔደ፲ ፡ አርሳቸውም፡ ምሳ ሌ፡ሆኑ፡ሲ ሣቀዩ፡ በዘላለም፡አሳት።።ዘፍጥ፡ ፲፱፡ ፳፬፡

፰ አንደሁም፡ ደግሞ፡ አለዚህ፡ ሕልማሞች፡ሥ ጋቸውን፡ደረክሳሉ፡ጌትነትንም፡ደቃላሉ፡ክብርንም፡ ደሰድባሉ።

፱ *ሚካኤል፡ ግን፡ የመላእክት፡ አለቃ፡ ከሰይጣ ን፡ ጋራ፡ በተከራከረ፲ጊዜ፡ ሰለ፡ ሙሴ፡ ሥጋ፡ ቢናገር።። በፈርደ፲ ደሰድበው፡ ዘንድ፡ አልደፈረም፡ ነገር፡ ግን፡ አለው፡ እግዚአብሔር፡ ተደቀጣህ።።

*ደን፡ ፲፪፡ ፭፡፡ †ዘካ፡ ፫፡ ፪፡፡

፲ አለዚህ፡ ግን፡ በማያውቁት፡ ነገር፡ደሳደባሉ፡ በ ባሕርደያም፡ የሚያውቁትን፡ ነገር፡ አእምሮ፡ አንደሌ ለበት፡ አንሰሳ፡ በርሱ፡ ደጠፈሉ።። ፪፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፲፪፡፡

፲፩ ወዮላቸው።። *በቃየል፡ መንገድ፡ ሒደዋልና፡ ሰለ፡ ዋጋም፡ ራሳቸውን፡ተለበለዓም፡ ስህተት፡አሳል ፈው፡ ሰጡ፡ **በዋፈም፡ ክሕደት፡ አለቁ።።

*ዘፍጥ፡ ፬፡ ፭፡፡ †ራእ፡ ፪፡ ፲፬፡፡ **ዘኁል፡ ፲፮፡ ፭፡፴፭፡፡

፲፪፡ እሌህ፡በፈቅር፡ ምሳችሁ፡ ነውር፡ ናቸው፡ ከላ ንት፡ ጋራ፡ ሲበሉ፡ ያለ፡ ፈርሃት፡ ራሳቸውን፡ ሲያሰማ ረ፡ ውኃ፡ አንደሌለባት፡ ደመና፡ ነፋስ፡ የምትነደው፡ አንደ፡ጸደደም፡ዛፎች፡ የማያፈረ።። ሁለተ፡ ጊዜም፡ የሞቱ፡ ከሥራቸውም፡ የተነቀሉ።።

፲፫፡ የሚተም፡ የባሕር፡ሞገድ፡ *ኃፈረቱን፡የሚያ ረፍርፍ፡ ያለ፡ ሠርሳት፡የሚዞረ፡ ከዋክብት፡ የዘላለ ምም፡ ጽኑ፡ ጨለማ፡ ተጠብቀላቸዋል።

*ኢሳ፡ ፶፯፡ ፳፡፡

፲፬፡ ከአደም፡ ሰባተኛው፡ *ሄኖክ፡ በለዚህ፡ ትንቢ ት፡ ተናግሮባቸዋል፡ እንደህ፡ ሲል።። እነሆ፡እግዚአብ ሔር፡ ደመጣል፡ ከአእላፋ፡ ቅደሳን፡ ጋራ።።

*ዘፍጥ፡ ፭፡ ፳፭፡፡

፲፭፡ በሁሉ፡ *ደፈርድ፡ ዘንድ፡ ዓመጸኖችንም፡ ሁ ሉ፡ ሰለ፡ ተጠራጠረበት፡ ጥረጣሪ፡ ሁሉ፡ ደነሠጽ፡ ዘ ንድ፡ ኃጢአትኖችም፡ መናፈቃን፡ በተናገረበት፡ጽኑ፡ ነገር፡ ሁሉ።። *ማቴ፡ ፮፭፡ ፴፭፡፡

፲፮፡ አሌህ፡ የሚያንጉረጉሩ፡ የሚነቀፈ፡ናቸው፡ በመመኛታቸው፡ የሚሔዱ።። አፈቸውም፡ በትዕቢ ት፡ ደናገራል።። ለሰው፡ ፊትም፡ ደደላሉ፡ ሊረቡ።።

፲፯፡ አላንት፡ ግን፡ ወደ፱ቴ፡ከጌታችን፡ ከየሱስ፡ ክ ርስቶስ፡ሐዋርያት፡ቀድሞ፡የተባለውን፡ነገር፡አስቡ።።

፲፰፡ ነገረዋችኋልና፡ አንደህ፡ ሲሉ።። *በኋለኛው፡ ዘመን፡ደመጣሉ፡ የሚያፈዙ፡ አንደ፡መመኛታቸው ም፡ በክሕደት፡ ይሔደሉ።። *፩፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፩፡፡ ፪፡ ጴጥ፡ ፫፡ ፫፡፡

፲፱፡ አርሳቸው፡የተለዩ፡ናቸው።። የሥጋ፡ወገን፡ መ ንፈስ፡ የሌለባቸው።። ፩፡ ቀሮ፡ ፪፡ ፲፬፡፡

፳፡ አላንት፡ ግን፡ ወደ፱ቴ፡ ሆይ፡አጅግ፡ በተቀደሰ ች፡ በዛደማናታችሁ፡ ተሠረ፲ ፡ በመንፈስ፡ ቅደስም፡ ጸልዩ።። ቀሉ፡ ፪፡ ፲፡፡ ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፲ሰ፡፡

፳፩፡ በእግዚአብሔርም፡ ፈቅር፡ ተጠበቁ፡ የጌታ ችነን፡ የየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ምህረት፡ ተስፈ፡ ስታደር ጉ፡ ለዘላለም፡ ሕደወት።።

፳፪፡ አኩሉንም፡ ማረ፲ ፡ ስትለያዩ።።

፳፫፡ አኩሉን፲ ፡ ግን፡ *በፈርሃት፡ አድንዋቸው፡ ከአ ሳት፡ ነበልባልም፡ ስትነየቋቸው፡ ደግሞም፡ ከሥጋ፡ የረከሰቺውን፡ ተልብስ፡ ሰትጠሉ።። *ያዕ፡ ፭፡ ፲፱፡ ፳፡፡ †ራኤ፡ ፫፡ ፱፡፡

፳፬፡ ደጠቅቃችሁ፡ ዘንድ፡ ግን፡ ለሚችለው፡ አን ደትወድቁ፡ በክብረ፲ ፊትም፡ ያቀማችሁ፡ ዘንድ፡ ያ ለ፡ ነውር፡ ደሰ፡ ብልዋችሁ።። ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፳፫፡፡ ፊል፡ ፩፡ ፲፡፡

፳፭፡ አርሱም፡ አንደ፡ እግዚአብሔር፡መድኃኒታ ችን።። ለርሱ፡ ምስጋና፡ ደሁን፡ ታላቅነትም፡ ግዛትም፡ ኃደልም፡ ዛረ፲ ፡ አስከ፡ ዘላለምም፡ ድረስ።። አሜን።። ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፯፡፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፯፡፡

የዮሐንስ ፡ ራእይ ።

ምዕራፍ ፭

፩ የዐሱስ፡ ክርስቶስ፡ ራእይ፡ እግዚአብሔር፡ የሰጠው፡ *ፈጥኖ፡ የሚሆነውን፡ ነገር፡ ለባሮቹ፡ ያገልጥ፡ ዘንድ፡ አመለከተተም፡ በመልኩ፡ እጅ፡ም፡ ወደ፡ ባርያው፡ ወደ፡ ዮሐንስ፡ ላካት። *ቊ፡ ፲፱።

ም፡ ፷፪፤ ፯፤ ፯።

፪ ለእግዚአብሔር፡ ቃል፡ *የመሰከረ፡ ለየሱስ፡ ክርስቶስም፡ ምስክር፡ ባየው፡ ሁሉ፡ ነገር።

*ቊ፡ ፱።፤ ም፡ ፯፤ ፱።።

፫ ምስጋና፡ ያገባዋል፡ ለሚያነብ፡ የዚህንም፡ ትንቢት፡ ነገር፡ ለሚሰሙ፡ በርሱ፡ የተጻፈውንም፡ ለሚጠብቁ። *ዘመን፡ ቀርብዋልና። *ም፡ ፷፪፤ ፯።።

ተም፡ ፷፪፤ ፲።

፬ ከዮሐንስ፡ በአስያ፡ ወደሉት፡ ወደ፡ሰባቱ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት። ለላንት፡አጋ፡ያሁንላቸሁ፡ሰላምም፡ *ከያለው፡ከነበረውም፡ ከሚመጣውም። በዙፋኑ፡ ፊት፡ ካሉም፡ *ከሰባቱ፡ መናፍስት።

*ዘፀአ፡ ር፡ ፲፱፤ ፲፭።። ዕብ፡ ፲ር፤ ፷።። ተም፡ ር፡ ፭።

ኢሳ፡ ፲፩፤ ፪።።

፭ ከዮሱስ፡ ክርስቶስም፡ ከታመነው፡ *ምስክር። የሙታን፡ ተበኩር፡ የምድር፡ ነገሥታትም፡ አለቃ። **ለወደደን፡ ከኃጢአታችንም፡ በደሙ፡ ††ላጸበን።

*ም፡ ር፡ ፲፱።። ዮሐ፡ ፲፮፡ ፴፯።። ተቊ፡ ፲፮።።

ቀለ፡ ፭፡ ፲፮።። **ም፡ ፲፱፡ ፲፯።። ††ም፡ ፯፡ ፲፱።።

ዕብ፡ ፱፡ ፲፱።።

፮ ነገሥታትና፡ ካህናት፡ *ያደረገን፡ ላባቱ፡ ለአግዚአብሔር። ††ለርሱ፡ ክብር፡ ይሁን፡ ችሎትም፡ ከዘላለም፡ አሰከ፡ ዘላለም። ድረስ፡ አሜን። *ም፡ ፭፡ ፲።።

፭፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፭—፱።።። ††ዘፀአ፡ ፲፱፡ ፮።።

፯ እነሆ፡ አርሱ፡ በደመና፡ ይመጣል፡ዓይንም፡ ሁሉ፡ *ታየዋለች፡የወጉትም፡ደግሞ፡የምድርም፡ነገድ፡ ሁሉ፡ ያለቅሱለታል። አዎን። አሜን።

*ዘካ፡ ፲፪፡ ፲።። ዮሐ፡ ፲፱፡ ፴፯።።

፰ እኔ፡ ነኝ፡ አልፈና፡ ዖሜጋ። መጀመርያ፡ መጨረሻም፡ እግዚአብሔር፡ ይላል፡ ያለ፡ የነበረም፡ የሚመጣም፡ ሁሉን፡ ቻይ። ም፡ ፷፪፡ ፲ር።። ኢሳ፡ ፵፭፡ ፱።።

ና፡ ፵፬፡ ፮።። ና፡ ፵፰። ፲፪።።

፱ እኔ፡ ዮሐንስ፡ ወንድማችሁ፡በኃዘንም፡ደግሞ፡ *ባልንጀራችሁ፡ በመንግሥትም፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ትዕግሥት፡ ጽጥም፡ በምትባል፡ ደሴት፡ ነበርሁ፡ ስለ፡ እግዚአብሔር፡ ቃል፡ ስለ፡ የሱስ፡ ክርስቶስም፡ ምስክር። *ርዕ፡ ፮፡ ፲፯።።

፲ በመንፈስም፡ ሆንሁ፡ በጌታ፡ ቀን። በኋላዬም፡ ታላቅ፡ ድምጽ፡ ሰማሁ፡ እንደ፡ መለከት፡ ያለ።

ቊ፡ ፲፭።።

፲፩ እንደሀ፡ ሲል። እኔ፡ ነኝ፡ አልፋ፡ ዖሜጋ፡ የፊ ተኛው፡ የኋለኛውም። የምታየውንም፡ በመጽሐፍ፡ ጻፈው፡ በአሰያ፡ ወደሉት፡ ሰባቱ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናትም፡ ስደደው። ወደ፡ ኤፌሶን። ወደ፡ ስሚር ናም። ወደ፡ ጴርጋሞስም። ወደ፡ ቲያቲራም። ወደ፡ ሰርዲስም። ወደ፡ፊላድልፊያም፡ ወደ፡ላደቅያም።

*ም፡ ፷፪፤ ፲ር።።

፲፪ የሚያገረኝንም፡ ድምጽ፡ አይ፡ ዘንድ፡ተመለስሁ። በተመለስሁም፡ ጊዜ፡ሰባት፡ የወርቅ፡ መቅረዞች፡ አየሁ።

፲ር፡ የሰባቱም፡ መቅረዝ፡ *መካከል፡ አንድ፡ ተየሰው፡ ልጅ፡ የሚመስል፡ ነበረ፡ ልብስ፡ ለብሶ፡ እስከግር ፡ በደረቱም፡ በወርቅ፡ መታጠቅያ፡ የታጠቀ።

*ም፡ ፪፡ ፭።። ተዲን፡ ፯፡ ፲ር።።

፲፬ ራሱ፡ ግን፡ጸጉሩም፡እንደ፡ *ነጭ፡የበግ፡ጸጉር፡ ነበር። እንደ፡ ባዘተ፡ የነጸ። ተኅይዖቹም፡ እንደ፡ እሳት፡ ነበልባል። *ዲን፡ ፯፡ ፪።። ተም፡ ፪፡ ፲፷።።

፲፭ እግሮቹም፡ እንደ፡ ሊባኖስ፡ *ብረት፡ በእቶን፡ እንደ፡ ጋሉ። ድምጹም፡ እንደ፡ ብዙ፡ ውኖች፡ ድምጽ። *ም፡ ፪፡ ፲፷።።

፲፮ በቀኝ፡ እጀ.ም፡ *ሰባት፡ ከዋክብት፡ ነበር። ካፊም፡ ደወጣ፡ነበረ፡ሁለት፡ ልሳን፡ ያለው፡ ተዮተሳለ፡ ሰደፍ፡ ፊቱም፡ ያበራል፡ እንደ፡ ጸሓይ፡ በኃይልዋ።

*ቊ፡ ፲።። ም፡ ፪፡ ፭።። ተም፡ ፪፡ ፲፪፡ ፲፯።። ና፡ ፲፪፡ ፲፭።።

፲፯ ባየሁትም፡ ጊዜ፡ በግሬ፡ ወደቅሁ፡ እንደ፡ ሞተ። በላዬም፡ ቀኝ፡ እጀ.ን፡ ጫነብኝ፡ እንደሀ፡ ሲል። አትፍራ፡ እኔ፡ ነኝ፡ የፊተኛው፡ የኋለኛውም።

ዲን፡ ፲፡ ፲፷።።

፲፰ ሕያውም፡ ሙቼም፡ ነበርሁ። እነሆም፡ ሕያው፡ ነኝ፡ ለዘላለሙ። አሜን። የሲኦልና፡ የሞት፡ መክፈቻም፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ነው።

ሮሚ፡ ፮፡ ፱።።

፲፱ ያየኸውን፡ *ጻፍ፡ የሚሆነውንም፡ከዚህም፡ *ከኋላ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ያለውን። *ም፡ ፲፱፡ ፲ር።።

ተም፡ ፱፡ ፭።።

፳ በቀኙ፡ ያየሳት፡ የሰባቱ፡ ከዋክብት፡ ምሥጢር፡ የሰባቱም፡ የወርቅ፡ መቅረዞች። ሰባቱ፡ ከዋክብት፡ የሰባቱም፡ የወርቅ፡ መቅረዞች። ሰባቱ፡ ከዋክብት፡ የሰባቱ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ መላእክት፡ ናቸው። ያየሳቸውም፡ ሰባቱ፡ መቅረዞች፡ ሰባት፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ናቸው።

መልክ፡ ፪፡ ፯።።

ምዕራፍ ፪

፩ ወደ፡ ኤፌሶን፡ቤተ፡ክርስቲያን፡መልእክ፡ጻፈ። እንደሀ፡ይላል፡በቀኙ፡ *ሰባት፡ ከዋክብት፡ የያዘው፡ በሰባቱ፡ በወርቅ፡ መቅረዞች፡ መካከል፡ የሚሔድ።

*ም፡ ፭፡ ፲ር።። ፲፯፡ ፷።።

፪፡ ስራህን፡ አወቅሁ፡ ድካምህንም፡ ትዕግሥትህ
ንም። ክፎችንም፡ ትታገሣቸው፡ዘንድ፡እንደትችል፡
*ፈትነሃቸዋልና፡ ሐዋርያት፡ ነኝ፡ የሚሉን፡ እንደሁ
ም፡ አይደሉም፡ አሰትቸችም፡ ሁነው፡ አገኘሃቸው።
*፩፡ዮሐ፡ ፬፡ ፪፡ ር፡፡

ር፡ ቻልህም፡ ትዕግሥትም፡አለህ።ስለ፡ስሜም፡ደ
ከምህ፡ አልሰለቸህምም። ገላት፡ ፮፡ ፱፡፡

፱፡ ብ፡ ፲፪፡ ፭፡ ፲፪፡ ፲፭።

፱፡ ነገር፡ ግን፡ ጥቂት፡አግኝቼብሃለሁ፡የቀደመጴቱ
ን፡ ፈቅርህን፡ ትተሃልና። ም፡ ር፡ ር፡ ፲፱፡፡

፭፡ አሁንም፡ ከወደቺት፡ወደቅህ፡አስብ፡ንስሐም፡
ግባ፡ የቀደመውንም፡ ስራ፡ ስራ። ያለዚያ፡ እኔ፡ ፈጥ
ኜ፡ አመጣብሃለሁ፡ መቅረዝህንም፡ ከስፈራዋ፡አስ
ወግደታለሁ፡ ነስሐ፡ ባትገባ።

፮፡ ነገር፡ ግን፡ ደህ፡ አለህ። እርሱም፡ *የኒቀላውያ
ንን፡ ስራ፡ †ጸልተሃልና፡ እኔ፡ ደግሞ፡ የምጸላትን።
*ቀ፡ ፲፭፡፡ †መዝ፡ ፻፱፱፡ ፻፭፡፡

፯፡ ጆሮ፡ ያለው፡ ደስማ፡ መንፈስ፡ ለአብያተ፡ክር
ስቲያነ ት፡የሚለውን። ድል፡ ለነሣው፡ እኔ፡ እሰጠዋ
ለሁ፡ ደበላ፡ዘንድ፡ በእግዚአብሔር፡ ገነት፡ ውሥጥ፡
ካለው፡ †ከሕይወት፡ ዛፍ። *ቀ፡ ፲፭፡ ፲፯፡ ፳፪፡፡
ም፡ ር፡ ፭፡ ፲፪፡ ፳፭፡፡ †ም፡ ፳፪፡ ፪፡፡ ዘፍጥ፡ ፪፡ ፱፡፡

፰፡ ለስሚርና፡ ቤተ፡ክርስቲያንም፡መልአክ፡ ጸፍ።
ይህ፡ነው፡የሚለው፡የፊተኛው፡ፎኋለኛውም። መ
ተ፡ የነበረው፡ ሕያውም፡ የሆነው። *ም፡ ፭፡ ፲፯፡፡
ና፡ ፳፪፡ ፲ር፡፡

፱፡ ስራህን፡ አውቃለሁ፡ አዘንህንም፡ ድኅነትህን
ም። (ነገር፡ግን፡ አንተ፡ *ባለጠጋ፡ ነህ፡) †አይሁድ፡ ነኝ፡
የሚሉትንም፡ ስድብ፡ አወቅሁ፡ አርሳቸውም፡ አይ
ደሉም፡**የሰይጣን፡ ማኅበር፡ ናቸው፡ አንጂ።
*ያዕ፡፪፡ ፭፡፡ ም፡ ር፡ ፭፡፡ **፪፡ ቀር፡ ፲፭፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

፲፡ ያገኝህ፡ዘንድ፡ ባለው፡ሁሉ፡ መከራ፡ አትፍራ።
እነሆ፡ ሰይጣን፡ ከላንት፡ ወገን፡በግዞት፡ያኖር፡ ዘንድ፡
ጊዜ፡ አለው፡ ትፈተኑ፡ ዘንድ። አዘንም፡ ይደርሰባች
ኋል፡ አሥር፡ ቀን፡ እስከ፡ ሞት፡ድረስ፡ የታመንህ፡ ሁ
ን። እኔም፡ የሕይወት፡ *አክሊል፡ እሰጥሃለሁ።
*ማቴ፡ ፲፡ ፳፮፡፡ ፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፳፡፡

፲፩፡ ጆሮ፡ ያለውን፡ይስማ፡መንፈስ፡ ለአብያተ፡ ክ
ርስቲያናት፡የሚለውን። ድል፡ የነሣ፡ ከሁለተኛዪቱ፡
ሞት፡ አይጐዳም። ም፡ ፳፡ ፲፬፡፡

፲፪፡ ለጴርጋሞስም፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ መልአክ፡ ጸ
ፍ፡ ሁለት፡ ልሳን፡ ያለው፡ የተሳለ፡ ሰይፍ፡ በጂ፡ ያለ
ው፡ የሚለው፡ ይህ፡ ነው። ም፡ ፭፡ ፲፯፡፡

፲ር፡ እኔ፡ስራህን፡ አውቃለሁ፡ወጂትስ፡ትና፡ለህ።
*የሰይጣን፡ ዙፋን፡ ወደለበት። አንትም፡ †ስሜን፡
ይዘሃል፡ ሃይማኖቴንም፡ አልካድህም፡ ደግሞም፡ የ
ታመነ፡ ምስክሬ፡ አንቲጳስ፡ በነበረባት፡ ቀን፡ በላንት፡
ዘንድ፡ የገደሉት፡ ሰይጣን፡ ባለበት፡ ዘንድ።
*ም፡ ፲ር፡ ፪፡፡ †ም፡ ር፡ ፳፡፡

፲፬፡ ነገር፡ ግን፡ ጥቂት፡ ለኔ፡ አለኝ፡በላይህ። ላንት፡
ከዚያ፡ ሰዎች፡ አሉ፡ልህ፡ *በበለዓም፡ ትምህርት፡ የ
ተያዙ፡ ባላቅን፡ ያስተምር፡የነበረ፡ በእሥራኤል፡ልጆ
ች፡ ፊት፡ መሰናከያ፡ለመጣል፡ለጣዖታት፡የታረደው
ን፡ ይበሉ፡ ዘንድ፡ ያመነዝሬም፡ ዘንድ።
*ዘኁል፡ ፴፩፡ ፲፮፡፡ ይሁዳ፡ ፲፩፡፡

፲፭፡ እንደሁም፡ ላንት፡ ሰዎች፡ አሉህ፡ በኒቀላው
ያን፡ ትምህርት፡ የተያዙ፡ እኔ፡ የምጸላው።
ቀ፡ ፯፡፡

፲፮፡ ንስሐ፡ ግባ። ያለዚያ፡ እኔ፡ ፈጥ፡ኜ፡ አመጣብ
ሃለሁ፡ ባፈ፡*ሰይፍም፡ አጣላቸዋለሁ።
*ም፡ ፭፡ ፲፮፡፡ ና፡ ፲፱፡ ፲፭፡ ፳፭፡፡

፲፯፡ ጆሮ፡ ያለው፡ ይሰማ፡ መንፈስ፡ ለአብያተ፡ ክ
ርስቲያናት፡ የሚለውን። ድል፡ ለነሣ፡ አሰጠዋለሁ፡
ከተሰወረው፡ መና፡ ይበላ፡ ዘንድ። ነጭ፡ ደንጊያም፡
አሰጠዋለሁ። በደንጊያውም፡ ላይ፡ አዲስ፡ ስም፡ ተ
ጽፈበታል፡ ማንም፡ የማያውቀው፡ ከተሰጠው፡ በ
ቀር። ም፡ ር፡ ፲፪፡፡

፲፰፡ለቲያቲራም፡ቤተ፡ክርስቲያን፡መልአክ፡ጸፍ።
ይህ፡ነው፡ የአግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ያለው። እንደ፡ አ
ሳት፡ ነበልባል፡ ያሉ፡ *ዓይኖች፡ ያሉት፡ እግሮቹም፡ እ
ንደ፡ ሊባኖስ፡ ብረት። *ም፡ ፭፡ ፲፱፡፡ ና፡ ፲፱፡ ፲፪፡፡

፲፱፡ ስራህን፡ አወቅሁ፡ ፈቅርህንም፡ መገዛትህን
ም፡ ሃይማኖትህንም፡ትዕግሥትህንም፡ማድረግህን
ም። የኋለኛዪቱም፡ ከፊተኛዪቱ፡ እንድትበልጥ።

፳፡ ነገር፡ ግን፡ ጥቂት፡ አግኝቼብሃለሁ። ያችን፡ ሴ
ት፡ *ኢሳቤልን፡ትተሃልና፡ነቢይት፡ነኝ፡የምትለውን።
ታስተምር፡ ዘንድ፡ ባሮቼንም፡ታስታቸው፡ ዘንድ፡እን
ደ፡ያመነዝሩ፡ለጣዖታትም፡ የታረደውን፡እንጂበሉ፡
ቀ፡ ፬፡፡ *፩፡ ነገሥ፡ ፲፮፡ ፴፩፡፡

፳፩፡ ጊዜም፡ ሰጠኋት፡ ንስሐ፡ ትገባበት፡ ዘንድ፡ አ
ልገባችም።

፳፪፡ እነሆ፡ እኔ፡ ባልጋ፡ ላይ፡ አጥላታለሁ፡ ከርሰዋ
ም፡ ጋራ፡ የሚያመነዝሩን፡ በታላቅ፡ አዘን፡ ከስራቸ
ው፡ ባይመለሱ።

፳፫፡ ልጆችዋንም፡በሞቱ፡ እገላለሁ። ቤተ፡ክርስ
ቲያኒቱም፡ሁሉ፡ ታውቃለች፡ እኔ፡ እንደ፡ሆነሁ፡ †ኩ
ላሊትንና፡ ልብን፡ የፃመመረምር። ከላንትም፡ ለሁላ
ችሁ፡ እንደ፡ ስራችሁ፡ እከፈላችኋለሁ።
*መዝ፡ ፯፡ ፲፡፡ ኤር፡ ፲፯፡ ፲፡፡

፳፬፡ ለላንት፡ ግን፡ እላለሁ፡ ለቀረትም፡ በቲያቲ
ራ፡ላሉት። ደህ፡ ትምህርት፡ ከርሳቸው፡ዘንድ፡ የሌ
ለውን፡ ሁሉ፡ የሰይጣንንም፡ ጥልቅ፡ የማያውቁን፡
ሁሉ። እርሳቸው፡ እንደ፡ናገሩ። ሌላ፡ የከበደ፡ነገር፡
አልጭንባችሁም።

፳፭፡ ነገር፡ ግን፡ ከላንት፡ጋራ፡ ባለው፡ ተያዙ፡እስክ
መጣ፡ ድረስ። ም፡ ር፡ ፲፭፡፡

፳፮፡ ድል፡ የነሣውም፡ስራዬንም፡ እስከ፡ ፈጻሚ፡
የሚጠብቅ፡ሠልጣን፡እሰጠዋለሁ፡በአሕዛብ፡ላይ።

፮፯፡ በብረት፡ በትር፡ ይጠብቃቸዋል፡ እንደ፡ ሸክላም፡ እቃ፡ ይቀጠቀጣሉ። ም፡ ፲፪፡ ፭፡፡

፮፰፡ እኔ፡ ደግሞ፡ ባባቴ፡ እንደ፡ ወሰድሁ። የንጋት ኝ፡ ኮከብ፡ አሰጠዋለሁ። መዝ፡ ፪፡ ፹፡፡

፮፱፡ ጆሮ፡ ያለው፡ ይስማ፡ መንፈስ፡ የአብያተ፡ ክርስቲያናት፡ የሚለውን። ም፡ ፫፡ ፯፡፡

ምዕራፍ፡ ፫፡

፩፡ በሰርዲስ፡ ላለችውም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ መልአክ፡ ጻፍ። ይህ፡ ነው፡ የሚለው፡ *ሰባቱ፡ የእግዚአብሔር፡ መናፍስት፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ያሉት፡ ተሰባትም፡ ከዋክብት። ስራህን፡ አወቅሁ፡ ስም፡አንደለህ፡ሕያው፡ እንደ፡ ሆንህ፡ አንተ፡ የሞትህ፡ ስትሆን።

*ም፡ ፭፡ ፯፡፡ †ም፡ ፩፡ ፲፯፡፡

፪፡ *የነቃህ፡ ሁን፡ ይሞቱ፡ ዘንድ፡ ያላቸውንም፡ የቀረችን፡ ተአጽና፡ ስራህን፡ መልታ፡ አላገኘሁምና፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት። *ቊ፡ ፲፱፡፡ †ሕዝ፡ ፴፱፡ ፱፡፡

፫፡ አሁንም፡ አስብ፡ እንዲት፡ ተቀበልህ፡ እንዲት ስ፡ ሰማህ፡ ጠብቅም፡ ንስሐም፡ ግባ። ባተጋም፡ እኔ፡ *እመጣብሃለሁ፡ እንደ፡ ሌባ። የምመጣብህንም፡ ሰዓት፡ አታውቅም። ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፪፡፡

፬፡ ነገር፡ ግን፡ ጥቂት፡ ስሞች፡ አሉህ፡በሰርዲስ፡ደግሞ፡ ልብሳቸውን፡ ያላረከሱ። ከኔ፡ ጋራም፡ ነጭ፡ ለብሰው፡ ይሔዳሉ፡ ይገባቸዋልና። ይሁዳ፡ ፳፫፡፡

፭፡ ድል፡የነሣ፡ይህ፡ *ነጭ፡ልብስ፡ይለብሳል። ስሙንም፡ ተከሕይወት፡ መጽሐፍ፡ አላጠፈውም፡ ስሙንም፡ **አምንበታለሁ፡ ባባቴ፡ ፊት፡በመላእክቱም።

*ም፡ ፱፡ ፱፡፡ ና፡ ፯፡ ፲፭፡፡ ፶፡ ፹፡፡ †ፈል፡ ፱፡ ፫፡፡

**ማቴ፡ ፲፡ ፴፪፡፡

፮፡ ጆሮ፡ ያለው፡ ይስማ፡ መንፈስ፡ ለአብያተ፡ ክርስቲያናት፡ የሚለውን።

፯፡ በፊላድልፊያም፡ ላለችው፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ መልአክ፡ ጻፍ። ይህ፡ ነው፡ የሚለው፡ ቅዱሱ፡ እውነተኛው፡ *የኢዊት፡መክፈቻ፡ያለው። የሚከፍት፡ማንም፡የማይዘጋ። የሚዘጋም፡ማንም፡የማይከፍት።

*ኢሳ፡ ፮፪፡ ፳፪፡፡

፰፡ ስራህን፡ አወቅሁ። እነሆ፡ *የተከፈተ፡ደጅ፡ በፊትህ፡ አደረግሁ፡ ማንም፡ ይቊልፈው፡ ዘንድ፡ አይችልም፡ ኀይል፡ አለህና፡ ቃሌንም፡ ጠበቅህ፡ ስሚንም፡ አልካህደህም። *፭፡ ቀሮ፡ ፲፯፡ ፱፡፡

፱፡ እነሆ፡እሰጥሃለሁ፡ ከሰይጣን፡ ማኅበር፡ ያሉት ን፡ *አይሁድ፡ ነኝ፡ የሚሉን፡ እርሳቸውም፡ ያይደሉ። ነገር፡ ግን፡ አሰት፡ደነገፉ። እነሆ፡ †አደርጋቸዋለሁ፡ መጥተው፡ ከግርህ፡ በታች፡ ደሰግኢ፡ዘንድ። እኔም፡ እንደ፡ ወደድሁህ፡ ያውቃሉ። †ም፡ ፱፡ ፱፡፡

ኢሳ፡ ፵፱፡ ፮፰፡ ና፡ ፮፡ ፲፱፡፡

፲፡ የትዕግሥቴን፡ *ቃል፡ ጠብቀሃልና፡ እኔም፡ ከፈተኖ፡ ጊዜ፡ የጠብቅሃለሁ፡ በዓለሙ፡ ሁሉ፡ ትመጣ፡ ዘንድ፡ ካላት፡ በምድር፡ ላይ፡ የሚኖሩት፡ ደፈትኑ፡ ዘንድ።

*ም፡ ፲፫፡ ፲፡፡ ዕብ፡ ፲፡ ፴፱፡፡

፲፩፡ እነሆ፡ፈጥኜ፡እመጣለሁ። የያዝህውን፡ጠብቅ። ማንም፡ም፡ አክሊልህን፡ እንደደወሰድብህ።

ም፡ ፭፡ ፫፡፡ ፪፡ ፭፡ ፲፡፡

፲፪፡ ድል፡ የነሣውን፡ *ዓምድ፡ አደርገዋለሁ፡ ባም ላኬ፡ መቅደስ። ወደ፡ ሚደም፡ ደግሞ፡ አይወጣም። ያባቴንም፡ †ስም፡ አጽፌበታለሁ፡ ያም፡ላኬንም፡አገር፡ስም። አርስዋም፡ አደ፡ሲቱ፡ የረሳሌም፡ከሰማይ፡ የምትወርድ፡ **ከአምላኬ፡ ዘንድ። አደ፡ሱንም፡ ስሜን፡ አጽፌበታለሁ። *ገላ፡ ፪፡ ፱፡፡

†ም፡ ፲፱፡ ፭፡፡ ፷፪፡ ፶፡፡ **ም፡ ፲፪፡ ፲፪፡፡ ና፡ ፷፭፡ ፪፡፡

፲፫፡ ጆሮ፡ያለው፡ ይስማ፡መንፈስ፡ ለአብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ምን፡ አለ።

፲፬፡ ለላኢቅያም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ መልአክ፡ ጻፍ። ይህ፡ነው፡ያለው፡*አሜን፡የሚሆን። የታመነው፡ ምስክር፡ አውነተኛውም። የእግዚአብሔር፡ ፍጥረት፡ †መጀመርያ። *ም፡ ፭፡ ፭፡፡ †ዮሐ፡ ፭፡ ፫፡፡

ቀለ፡ ፭፡ ፲፭፡፡

፲፭፡ ስራህን፡ አወቅሁ፡ ብርድ፡ ትኩስም፡ አንደ ደለህ፡ምነው፡ ብርድ፡ በሆንህ፡ ወደስ፡ ትኩስ።

ም፡ ፪፡ ፪፡ ፱፡፡

፲፮፡ ነገር፡ግን፡ለብ፡ ያልህ፡ነህና፡ የበረድህ፡ ያደደለ ህ፡ የተኩስህም። እኔ፡ ካፈ፡ አተፈህ፡ ዘንድ፡ አለኝ።

፲፯፡ ትላለህና፡ ባለ፡ ጠጋ፡ ነኝ፡ አጀግም፡ *መልቻለሁ፡ከማንም፡ አልሻም። ከተም፡ አታውቅም! ጕስቁላ፡አንደሆንህ፡ምስኪንም፡ድኃም፡ ዕውርም፡ ዕራቁ ትህም፡ አንደሆንህ። *፭፡ ቀሮ፡ ፫፡ ፲፮፡፡ ና፡ ፱፡ ፳፡፡

፲፰፡ እኔ፡ እመክርሃለሁ፡ በአሳት፡ የተፈተነውን፡ *ወርቅ፡ ከኔ፡ ትገዛ፡ ዘንድ፡ ባለ፡ ጠጋ፡ ትሆን፡ ዘንድ። ነጭ፡ልብስም፡ ትለብሳት፡ዘንድ፡ †የራቁትህም፡ ኀፍረት፡አንደትገለጥ።ዓይንህንም፡በኩል፡ ተኳል፡ አንድታይ። *ኢሳ፡ ፶፭፡ ፭፡፡ መልክ፡ ፫፡ ፫፡፡

†ራእ፡ ፲፭፡ ፲፭፡፡

፲፱፡ እኔ፡የምወደውን፡ሁሉ፡አዘልፈዋለሁ፡እገሥጸው፡ማለሁ። አሁንም፡ ቅና፡ ንስሐም፡ ግባ።

ምሳ፡ ፫፡ ፲፪፡፡ ፭፡ ቀሮ፡ ፲፭፡ ፴፪፡፡ ዕብ፡ ፲፪፡ ፯፡፡

፳፡ እነሆ፡እኔ፡ *በደጅ፡ ቁሚያለሁ፡ ያጅም፡ አመ ታለሁ። ማንም፡ድምጼን፡ ቢከፍትልኝም፡ ወደርሱ፡ †እገባለሁ። ከርሱም፡ ጋራ፡ አራቴን፡ እበላለሁ፡ እርሱም፡ከኔ፡ጋራ። *ሉቃ፡ ፲፪፡ ፴፯፡፡ †ዮሐ፡ ፲፬፡ ፳፫፡፡

፳፩፡ ድል፡ለነሣው፡እሰጠዋለሁ፡ከኔ፡ጋራ፡ ይቀመጥ፡ዘንድ፡ በዙፋኔ፡ላይ። እኔ፡ ደግሞ፡ ድል፡አንደ፡ነሣሁ፡ባባቴም፡ ጋራ፡ አንደ፡ ተቀመጥሁ፡ በዙፋኑ፡ላይ።

ማቴ፡ ፲፱፡ ፳፰፡፡

፳፪፡ ጆሮ፡ያለው፡ ይስማ፡ መንፈስ፡ ለአብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ምን፡አለ።

ምዕራፍ፡ ፱፡

፩፡ ከዚያ፡ወጀያም፡ አየሁ፡ በሰማይም፡ አነሆ፡ ደጅ፡ ተከፈተ። የፊተኛውም፡ ድምጽ፡ እንደ፡ መለከት፡ ድምጽ፡ የሰማሁት፡ ተናገረኝ፡ እንደህ፡ ሲል። ወደዚህ፡ውጣ፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ደሆን፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ አሳይሃለሁ። ም፡ ፩፡ ፲፡፡

፪፡ የዚያን፡ ጊዜውም፡ በመንፈስ፡ ነበርሁ። አነሆ ም፡ *ዙፋን፡ በሰማይ፡ ቁም፡ዋል። *ሕዝ፡ ፩፡ ፹፮፡፡ ሕዝ፡ ፲፡ ፭፡፡ ኢሳ፡ ፮፡ ፩፡፡

፫፡ በዙፋኑም፡ላይ፡ተቀማጭ፡የተቀመጠበትም፡ በማየት፡የኢያስጲድን፡ ደንጊያ፡ መሰለ፡ ሰርደዮስን ም፡የጀመኖ፡ ቀስትም፡ በዙፋኑ፡ ዙርያ፡ ነበረ፡ በማየት፡የመረግድን፡ደንጊያ፡የሚመስል። ሕዝ፡ ፩፡ ፳፮፡፡

፬፡ በዙፋን፡ዙርያም፡ሀያ፡አራት፡ ዙፋኖች፡ ነበረ። በዙፋኖችም፡ ላይ፡ ሀያ፡አራት፡*ሸማግሌች፡ ተቀመጠው፡ ነው፡ ልብስንም፡ ለብሰው፡ አየሁ። በራሳቸውም፡ላይ፡የወርቅ፡ አክሊል፡ ነበረ። *ኢሳ፡ ፷፱፡ ፷፫፡፡ ም፡ ፫፡ ፱፡፡ ና፡ ፭፡ ፲፡፡

፭፡ ከዙፋኑም፡ ወጣ፡*መብረቅ፡ ነጐድጓድም፡ድምጽም። ሰባትም፡የሳት፡መብራቶች፡ በዙፋኑ፡ ፊት፡ የተቃጠሉ። እርሳቸውም፡ የእግዚአብሔር፡ ሰባት፡ መናፍስት፡ናቸው። *ም፡ ፳፡ ፭፡፡ ፲፭፡ ፲፱፡፡ ፲፯፡ ፲፳፡፡ †ዘካ፡ ፱፡ ፩፡ ፲፡፡

፮፡ በዙፋኑም፡ፊት፡ *የብርጭቆ፡ ባሕር፡ ቢረሌን፡ የሚሚሰል፡ ነበረ። በዙፋኑም፡ውሥጥ፡ በዙፋኑም፡ ዙርያ፡አራት፡ እንስሶች፡ ነበረ፡ ዓይን፡ የመላባቸው፡ በፊትና፡በኋላ። *ዘፀአ፡ ፳፱፡ ፲፡፡ ሕዝ፡ ፩፡ ፭፡ ፶፪፡፡

፯፡ የፊተኛውም፡ እንስሳ፡ አንበሳውን፡ መሰለ። ሁለተኛውም፡ እንስሳ፡ ጥጀውን፡ መሰለ። ሶስተኛ ውም፡እንስሳ፡ፊት፡ ነበረለት፡እንደ፡ ሰው። አራተኛ ውም፡እንስሳ፡የሚበረውን፡ ንስር፡ መሰለ።

ሕዝ፡ ፩፡ ፲፡ ና፡ ፲፡ ፲፱፡፡

፰፡ አራት፡ እንስሶችም፡ ለያንዳንዱ፡ በዙርያቸው፡ ስድስት፡ ክንፎች፡ ነበረላቸው። በውሥጣቸው ም፡ዓይን፡መልተባቸዋል፡ዕረፍትም፡አልነበረላቸው ም፡ሌት፡ቀን፡እንደህ፡ሲሉ።ቅዱስ፡ቅዱስ፡ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡አምላክ፡ሁሉን፡የያዘ። የነበረና፡ያለ፡ የሚመጣም። ኢሳ፡ ፮፡ ፫፡፡

፱፡ እንስሶችም፡ ክብር፡ ና፡ንዝነትም፡ ምስጋናም፡ በሰጡ፡ጊዜ፡በዙፋን፡ላይ፡ ለተቀመጠ፡ ለዘላለሙ፡ሕያው፡ ሁኖ፡ለሚኖር።

፲፡ ሀያ፡አራቱ፡ሸማግሌች፡በዙፋን፡ላይ፡ በተቀመጠው፡ፊት፡ደወድቃሉ፡ ለዘላለሙም፡ ሕያው፡ ሁኖ፡ ለሚኖር፡ ደሰግደሉ፡ አክሊላቸውንም፡ በዙፋኑ፡ ፊት፡ ደጥላሉ፡እንደህ፡ ሲሉ። ም፡ ፭፡ ፲፬፡፡

፲፩፡ ላንት፡ ደገባል፡ ጌታ፡ ሆይ፡ምስጋና፡ ክብርም፡ ችሎትም፡ትቀበል፡ዘንድ።አንተ፡ ሁሉን፡ፈጥረሃልና፡ ሁሉም፡ በፈቃድህ፡ ሁንዋልና፡ ተፈጠረም።

ምዕራፍ፡ ፭፡

፩፡ *በዙፋን፡ላይ፡ በተቀመጠውም፡ በቀኙ፡ መጽሐፍ፡አየሁ፡ በውሥጥና፡በሚሂ፡ †የተጻፈበት፡ በሰባት፡ ማሕተም፡ የታተመ። *ም፡ ፱፡ ፪፡፡ †ሕዝ፡ ፪፡ ፱፡ ፲፡፡

፪፡ ብርቱም፡ መልአክ፡ አየሁ፡ በታላቅ፡ ቃል፡ ሲጸራ። ማነው፡ የሚገባው፡ መጽሐፉን፡ ደከፍት፡ ዘንድ፡ማሕተሙንስ፡ ደፈታ፡ ዘንድ።

፫፡ ለማንም፡አልተቻለውም፡በሰማይ፡ ላለ፡ በም ድርም፡ላለ፡ ከምድር፡ በታችም፡ ላለ፡ መጽሐፉን፡ደ ከፍት፡ ዘንድ፡ ያየውም፡ ዘንድ።

፬፡ እኔም፡እጅግ፡ አለቅሰ፡ ነበርሁ፡ አንድ፡ የሚገባው፡አልተገኘምና፡ መጽሐፉን፡ ገልጦ፡ የሚያነበው፡ የሚያየውም።

፭፡ ከሸማግሌቹም፡ አንዱ፡ አለኝ። አታልቅስ። እነሆ፡ አንበሳው፡ *ከይሁዳ፡ ወገን፡ ተየጂቂት፡ ሥር፡ አሸነፈ፡መጽሐፉን፡ ደከፍት፡ ዘንድ፡ ሰባቱንም፡ ማሕተም፡ደፈታ፡ ዘንድ። *ዘፍጥ፡ ፵፱፡ ፱፡ ፲፡፡

†ኢሳ፡ ፲፩፡ ፩፡፡ ራእ፡ ፭፪፡ ፮፡፡

፮፡ በዙፋኑና፡ ባራቱ፡ አንስሶች፡ መካከልም፡ በሀያ፡ አራቱም፡ ሸማግሌች፡ መካከል፡*በግ፡ አየሁ፡ አንደ፡ታረደ፡ ሰባት፡ ቀንደችም፡ ነበረት፡ ሰባት፡ ዓይኖችም። እርሳቸውም፡ †ሰባቱ፡ የእግዚአብሔር፡ መናፍስት፡ናቸው፡በምድር፡ሁሉ፡የተላኩ። *ኢሳ፡ ፶፫፡ ፯፡፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፶፱፡ ፴፮፡፡ ዘካ፡ ፬፡ ፩፡ ፲፡፡

፯፡ መጣም፡ መጽሐፈንም፡ ወሰደው፡ ብዙፋን፡ ላይ፡ከተቀመጠው፡ከቀኙ።

፰፡ መጽሐፈንም፡በተቀበለ፡ጊዜ፡ አራቱ፡ እንስሶች፡ሀያ፡አራቱም፡ ሸማግሌች፡ በበጉ፡ፊት፡ወደቁ። ከ ሁሉ፡ጋራም፡ አያንደንዲ፡*መሰንቅ፡ ነበራቸው። የ ወርቅም፡ ጽና፡ ዕጣን፡ የመላባት። እርሱዋም፡ †የቅ ደሳን፡ ጸሎት። *ም፡ ፲፱፡ ፪፡፡ ና፡ ፲፭፡ ፪፡፡ **ም፡ ፳፡ ፫፡ ፱፡፡

፱፡ አደስ፡ ምስጋናም፡ ደመሰግኑ፡ ነበር፡ እንደህ፡ ሲሉ። ላንት፡ ደገባል፡ መጽሐፈን፡ ትወስድ፡ ዘንድ ማሕተሙንም፡ ትፈታ፡ ዘንድ። ታርደሃልና፡ በደምህም፡ ለእግዚአብሔር፡ ገዝተሀያልና፡ ከዘመድ፡ ሁሉ፡ ከቋንቋንም፡ ከወገንም፡ ከሕዝብም።

፲፡ ነገሥታትና፡ ካህናትም፡ ለአምላካችን፡ አድርገሀያልና፡ በምድርም፡ላይ፡እንነግሣለን። ም፡ ፩፡ ፮፡፡ ና፡ ፳፡ ፮፡፡ ና፡ ፳፪፡ ፭፡፡

፲፩፡ አየሁም፡ የብዙም፡ መላእክት፡ ድምጽ፡ ሰማሁ፡ በዙፋኑና፡ በእንስሶች፡ ዙርያ፡ በሸማግሌች ም። ቁጥራቸውም፡ የብዙ፡ ብዙ፡ *አልፋ፡ አእላፋ ትም፡ ነበር። *ዳን፡ ፯፡ ፲፡፡

፲፪፡ በታላቅ፡ቃል፡እንደህ፡ ሲሉ። የታረደው፡ በግ፡ ደገባዋል፡ *ኃይል፡ ባለጠግነትም፡ ደወሰድ፡ ዘንድ፡ጥበብም፡ችሎትም፡ክብር፡ም፡ምስጋናም፡ በረከትም። *ዕ፡ ዜና፡ ፴፡ ፲፩፡፡ ፊል፡ ፪፡ ፱፡ ፲፡

፲፫፡ በሰማይና፡ በምድርም፡ ያሉ፡ ፍጥረት፡ ሁሉ፡ በምድርም፡ታች፡ በባሕርም፡ በርስዋም፡ ያሉ፡ ሁሉ። ሁሉን፡ሰማኋቸው፡ ሲሉ። በረከትና፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ምሎትም፡ በዙፋን፡ላይ፡ ለተቀመጠው፡ ደግሞ ል፡ ለበጉም፡ ለዘላለሙ።

፲፬፡ አራቱም፡ እንስሶች፡ ይሉ፡ ነበር። አሜን። ሀ ያ፡አራቱም፡ ሽማግሌች፡ ወደቁ፡ ለዘላለሙም፡ ሕያ ው፡ ሁና፡ ለሚኖረው፡ ሰገዱ።

ም፡ ፲፬፡ ፬፡፡

ምዕራፍ፡ ፮፡

፩፡ አየሁም፡በጉ፡ አንዷን፡ ከሰባቱ፡ ማሕተም፡ በ ከፈተ፡ ጊዜ፡ ካራቱ፡ እንስሶችም፡ አንዷን፡ ሰማሁ፡ እንደሀ፡ሲል፡እንደ፡ ነጐድጓድ፡ ድምጽ። ና፡እይም።

ም፡ ፬፡ ፮፡፡ ና፡ ፭፡ ፮፡ ፳፡፡

፪፡ አየሁም፡እነሆ፡ነጭ፡ፈረስ፡ከተቀመጠበትም፡ ጋራ፡ቀስት፡ነበረ፡ አክሊልም፡ ተሰጠው፡ አሸንፎም፡ ወጣ፡ያሸንፍም፡ ዘንድ።

ዘካ፡ ፩፡ ፳፡—፲፯፡፡

ዘካ፡ ፮፡ ፩፡—፳፡፡

፫፡ ሁለተኛውንም፡ ማሕተም፡በከፈተ፡ጊዜ፡ሁለ ተኛው፡እንስሳ፡ሲል፡ሰማሁ። ና፡እይም።ም፡ ፬፡ ፯፡፡

፬፡ ሌላ፡ቀይ፡ ፈረስም፡ ወጣ፡ ለተቀመጠበትም፡ ተሰጠው፡ ሰላም፡ ከምድር፡ ያስወግድ፡ ዘንድ፡ እር ሱ፡በርሳቸውም፡ እንዲጋደሉ፡ ታላቅ፡ሰይፍም፡ተሰ ጠው።

፭፡ ሶስተኛውንም፡ ማሕተም፡ በከፈተ፡ጊዜ፡ ሶስ ተኛው፡እንስሳ፡ሲል፡ሰማሁ። ና፡እይም። አየሁም፡ እነሆ፡ ጥቁር፡ ፈረስ፡ በላዩ፡ በተቀመጠበትም፡ እጁ፡ ሚዛን፡ነበረ።

ም፡ ፬፡ ፯፡፡

፮፡ ድምጽም፡ ሰማሁ፡ ባራቱ፡ እንስሳ፡ መካከል፡ እንደሀ፡ ሲል። አንድ፡ መስፈርያ፡ ስንዴ፡ በድሪም። ሶስት፡ መስፈርያ፡ ገብስም፡ በድሪም። ቅባኑግንና፡ጸ ጅንም፡አትጕደቸው።

፯፡ አራተኛውንም ፡ ማሕተም፡ በከፈተ፡ ጊዜ፡ ያ ራተኛውን፡እንስሳ፡ ድምጽ፡ ሰማሁ፡ እንደሀ፡ ሲል። ና፡እይም።

፰፡ አየሁም፡እነሆ፡ቡላ፡ ፈረስ፡ በላዩም፡ የተቀመ ጠበት፡ ስሙ፡ ሞት፡ነው። ሲኦልም፡ ተከተለው፡ከ ምድርም፡ ባራተኛው፡ ክፍል፡ ላይ፡ ሠልጣን፡ተሰጣ ቸው፡ በሰይፍ፡ ሊገልዋቸው፡ በራብም፡ በሞትም፡በ ምድርም፡አራዊት። ኤር፡ ፲፭፡ ፫፡፡ ሕዝ፡ ፲፬፡ ፳፩፡፡

፱፡ አምስተኛውም፡ ማሕተምን፡ በከፈተ፡ ጊዜ፡ ከመሠውያው፡ በታች፡ አየሁ፡ ሰለ፡ እግዚአብሔር፡ ቃል፡የሞቱትን፡ነፍሳት፡ ከርሳቸውም፡ ዘንድ፡ ሰለ፡ ነበረችው፡ምሰክር።

ም፡ ፳፡ ፭፡፡ ፲፱፡ ፲፳፡፡ ፲፮፡ ፯፡፡

፲፡ በታላቅ፡*ቃልም፡ይጮሁ፡ነበረ፡ እንደሀ፡ ሲሉ። ጌታ፡ ሆይ፡ ቅዱሱ፡ እውነተኛውም፡ ተእስከ፡ መቸ፡ አትፈርድም፡ለደማችንስ፡ አስከ፡ መቸ፡ አትበቀል ም፡ በምድር፡ ላይ፡ ከሚኖረ።

*ዘፈጥ፡ ፱፡ ፲፡፡

ተም፡ ፲፳፡ ፲፡፡

፲፩፡ *ነጭም፡ልብስ፡ ለያንዳንዲ፡ ተሰጣቸው፡ ተባ ለላቸውም፡ ጥቂት፡ሌላ፡ ዘመን፡ያርፈ፡ ዘንድ፡ እንደ ርሳቸው፡ ያሉት፡ ባርኮች፡ ወንድሞቻቸውም፡ እስኪ ፈጸሙ፡ ድረስ፡ እንደርሳቸው፡ ይሞቱ፡ ዘንድ፡ ያላ ቸው።

*ም፡ ፫፡ ፭፡፡ ፯፡ ፱፡፡ ፲፫፡ ፲፱፡፡

፲፪፡ ስድስተኛውንም፡ ማሕተም፡ በከፈተ፡ ጊዜ፡ አየሁ፡እነሆ፡ታላቅ፡መናወጥ።*ጸሐይም፡ጠቁረች፡ እንደ፡ጸጕር፡ ማቅ። ጨረቃም፡ እንደ፡ ደም፡ ሆነ።

*ኢሳ፡ ፲፫፡ ፲፡፡ ኢዮ፡ ፫፡ ፫፡ ፱፡፡ ሉቃ፡ ፳፩፡ ፳፭፡፡

፲፫፡ የሰማይም፡ ከዋክብት፡ በምድር፡ ላይ፡ ወደ ቁ፡ በለስ፡ ያልበሰለውን፡ ፍሬ፡ እንድትጥል፡ ጽኑ፡ነፋ ስ፡ በወዘወዛት፡ ጊዜ።

ኢሳ፡ ፴፬፡ ፬፡፡

፲፬፡ ሰማይም፡ተመለሰች፡ መጽሐፍ፡እንደሚታ ጸፍ። ተራራም፡ ደሴትም፡ ሁሉ፡ ከስፍራቸው፡ ተን ቀሳቀሱ።

፲፭፡ የምድርም፡ ነገሥታት፡ ታላላቆችም፡ ባለጠጎ ችም፡ የሻለቆችም፡ ብርተችም፡ ባርያም፡ ሁሉ፡ የሰ ው፡ ልጅም፡ ሁሉ፡ በዋሻና፡ በተራሮች፡ ሕንጻች፡ ራሳ ቸውን፡ሰወረ።

ኢሳ፡ ፪፡ ፲፡ ፲፱፡፡

፲፮፡ ተራሮችንም፡ሕንጻችንም፡በላያችን፡ውደቁ፡ አሉ። ሰውረኑም፡በዙፋን፡ላይ፡ከተቀመጠው፡ፊት፡ ከበጉም፡ ቍጣ።

ሉቃ፡ ፳፫፡ ፴፡፡

፲፯፡ የታላቁ፡ የቍጣው፡ቀን፡ደርሶዋልና። ማንስ፡ ይችላል፡ ይጸና፡ዘንድ።

ሮሜ፡ ፪፡ ፭፡፡

ምዕራፍ፡ ፯፡

፩፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ አራት፡መላእክት፡ አየሁ። *ባ ራቱ፡ ምድር፡ ማዝን፡ ቁመው፡ አራቱን፡ የምድርን፡ ንፈስ፡ ይዘው፡ ንፈስ፡ አንደይነፍስ፡በምድር፡ላይ፡ በ ባሕርም፡ ላይ፡ በዛፍም፡ ሁሉ፡ላይ።

*ደን፡ ፯፡ ፪፡፡

ዘካ፡ ፮፡ ፭፡፡ ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፩፡፡

፪፡ ሌላውንም፡ መልአክ፡ አየሁ፡ ከጸሐይ፡ መው ጫ፡ ሲወጣ፡ ለርሱም፡ የሕያው፡ እግዚአብሔር፡ ማ ሕተም፡ ነበረለት። በታላቅ፡ ቃልም፡ ምድርንና፡ ባሕ ርን፡ ደጉዲ፡ ዘንድ፡ የተሰጣቸውን፡ አራቱን፡ መላእ ክት፡ጸራ፡እንደሀ፡ሲል።

፫፡ ምድርን፡እስኪጐዲ፡ባሕርንም፡ ዛፎችንም፡ የአ ምላካችን፡ን፡ ባሮች፡ በማሕተም፡ በግምባራቸው፡ ላ ይ፡*እስክናመለክት፡ድረስ።

*ሕዝ፡ ፱፡ ፬፡ ፮፡፡

፬፡ የታተሙትንም፡ቍጥር፡ ሰማሁ። መቶ፡ አርባ፡ አራት፡ ሽህ፡ ከእሥራኤል፡ ልጆች፡ ወገን፡ ሁሉ፡ የታ ተመ።

ም፡ ፲፱፡ ፩፡ ፫፡፡

፭፡ ከይሁዳ፡ወገን፡አሠራ፡ሁለት፡ሽህ፡የታተሙ። ከሮቤል፡ ወገንም፡ አሠራ፡ሁለት፡ ሽህ፡ የታተሙ። ከ ጋድ፡ ወገንመ፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታተሙ።

፮፡ ከአሴር፡ ወገንም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታተ ሙ። ከንፍታሌም፡ ወገንም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የ ታተሙ። ከምናሴ፡ ወገንም፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የ ታተሙ።

፯፡ ከስምዖን፡ ወገንም፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታ
ተሙ። ከሌዊ፡ ወገንም፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታተ
ሙ። ከይሳኮር፡ ወገንም፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታ
ተሙ።

፰፡ ከዛብሎን፡ ወገንም፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታ
ተሙ። ከዮሴፍ፡ ወገንም፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የታ
ተሙ። ከብንያም፡ ወገንም፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሽህ፡ የ
ታተሙ።

፱፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ አየሁ፡ እነሆም፡ ታላቅ፡ ሕዝ
ብ፡ ለማንም፡ ይቈጥራቸው፡ ዘንድ፡ የማይቻለው። ከአሕዛብ፡ ሁሉ፡ ከወገንም፡ ከነገድም፡ ከቋንቀች
ም፡በዙፋኑ፡ፊት፡ ቁመው፡ በበጉም፡ ፊት፡ ነጭ፡ ልብ
ስ፡ ለብሰው፡ የሰሌንም፡ ዝንጣፊች፡ በጀቸው፡ ይዘ
ው።
ም፡ ፯፡ ፲፭፡፡

፲፡ በታላቅ፡ ቃልም፡ ጮሁ፡ እንጂህ፡ ሲሉ። መድኃ
ኒት፡በዙፋን፡ላይ፡ለተቀመጠ፡ለም፡ላካችንና፡ለበጉ።
ም፡ ፲፪፡ ፲፡፡

፲፩፡ *መላእክትም፡ሁሉ፡በዙፋኑና፡በሽማግሌች፡
ባራቱ፡ እንስሶችም፡ ዙርያ፡ ቀሙ ፡ ተበዙፋኑም፡ ፊ
ት፡ በግምባራቸው፡ ወደቁ፡ ለእግዚአብሔርም፡ ሰገ
ዱ፡እንጂህ፡ሲሉ።
*ም፡ ፭፡ ፲፩፡፡ ተም፡ ፲፩፡ ፲፯፡፡

፲፪፡ አሜን። በረከት፡ ክብርም፡ ጥበብም ፡ ምስጋ
ናም፡ ገና፡ነትም፡ ኃይልም፡ ችሎትም፡ ላምላካችን፡
ይሁን፡ለዘላለም።አሜን።
ም፡ ፭፡ ፲፪፡፡

፲፫፡ አንደ.ም፡ ከሽማግሌቹ፡ መለሰ፡ እንጂህ፡ ሲ
ለኝ። አሌህ፡ ነጭ፡ ልብሰ፡ የለበሱት፡ እለማን፡ ናቸ
ው። ከወዴትስ፡ መጡ።

፲፬፡ እኔም፡ አልሁት። ጌታዬ፡ ሆይ፡ አንተ፡ ታውቃ
ለህ።እርሱም፡ አለኝ። *ከታላቅ፡መከራ፡ የመጡ፡አ
ሌህ፡ ናቸው። ልብሳቸውንም፡ አጸቡ፡አነጽዋትም፡
በበጉ፡ደም።
*ም፡ ፫፡ ፲፡፡ ማቴ፡ ፳፬፡ ፳፭፡—፴፩፡፡

፲፭፡ ስለዚህም፡ እርሳቸው፡ በእግዚአብሔር፡ ዙ
ፋን፡ ፊት፡ ናቸው፡ በቀንና፡ በሌትም፡ ያመልኩታል፡
*በመቅደሱ፡ በዙፋን፡ላይ፡ የተቀመጠውም፡ ያድር
ባቸዋል።
*ም፡ ፲፩፡ ፲፪፡፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡ ፲፫፡ ፳፩፡ ፫፡ ፲፯፡፡
ም፡ ፲፯፡ ፭፡፡ ፳፭፡ ፫፡ ፳፪፡፡

፲፯፡ ደግሞም፡ አይራቡም፡ ደግሞም፡ አይጸሙ
ም፡ጸሓይም፡ አትወርድባቸውም፡ ትኩሳትም፡ ሁ
ሉ፡ አይወርድባቸውም።
ኢሳ፡ ፵፱፡ ፲፡፡

፲፯፡ በዙፋኑ፡ መካከል፡ ያለው፡ *በግ፡ ያሰማራቸ
ዋልና፡ ፣ወደ፡ ሕይወት፡ ውኃ፡ ምንጭም፡ ይመራቸ
ዋልና፡ **እግዚአብሔርም፡ እንብን፡ ሁሉ፡ ካይናቸ
ው፡ ያብሳል
*ም፡ ፭፡ ፯፡፡ ፣መዝ፡ ፳፫፡ ፪፡፡
**ም፡ ፴፭፡ ፭፡፡ ኢሳ፡ ፴፭፡ ፲፡፡

ምዕራፍ፡ ፰፡

፩፡ ሰባተኛውንም፡ ማሕተም፡ በከፈተ፡ ጊዜ፡ በሰ
ማይ፡ ዝምታ፡ ሆነ፡ እኩል፡ ሰዓት፡ የሚሆን።
ዘካ፡ ፪፡ ፲፫፡፡ አንባ፡ ፪፡ ፳፡፡

፪፡ ሰባቱንም፡ መላእክት፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡
የቀሙት፡ አየሁ። ሰባት፡ መለከትም፡ ተሰጣቸው።
ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፩፡፡

፫፡ ሌላም፡ መልአክ፡ መጣ፡ በመሠውያውም፡ ላ
ይ፡ ቀመ፡ ከርቡ፡ ጋራም፡ የወርቅ፡ ማዕጠንት፡ ነበረ፡ ብ
ዙ፡ ዕጣንም፡ተሰጠው፡ደጨምረው፡ዘንድ፡ከቅዱሳ
ን፡ ሁሉ፡ ጸሎት፡ ጋራ፡ በዙፋኑ፡ ፊት፡ ባለው፡ በወር
ቁ፡ መሠውያ፡ ላይ።
ም፡ ፭፡ ፰፡፡

፬፡ የዕጣኑም፡ጢስ፡ ወጣ፡ ከቅዱሳን፡ጸሎት፡ጋራ፡
ከመልአኩ፡ እጅ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት።
መዝ፡ ፻፵፩፡ ፪፡፡

፭፡ መልአኩም፡ ማዕጠንቱን፡ወሰደ፡ የመሠውያ
ውንም፡ እሳት፡ መላበት፡ በምድር፡ ላደም፡ ጣለው፡
ድምጽም፡ ሆነ፡ ነጐድጓድም፡ መብረቅችም፡ መናወ
ጥም።
ሕዝ፡ ፲፡ ፪፡፡

፮፡ ሰባት፡ መለከትም፡ ያላቸው፡ ሰባቱ፡ መላእክ
ት፡ ሊነፉ፡ ተዘጋጁ።

፯፡ የፈተኛው፡ መልአክም፡ ነፋ፡ በረደያ፡ እሳት
ም፡ ሆነ፡ በደም፡ ተቀላቅሎ፡ በም.ድርም፡ ወደቀ። የ
ዛፈም፡ ሲሶ፡ ተቃጠለ፡ *የለመለመውም፡ ሣዕር፡ ሁ
ሉ፡ ተቃጠለ።
*ዘፀአ፡ ፱፡ ፳፫፡፡

፰፡ ሁለተኛውም፡ መልአክ፡ ነፋ፡ እንጂ፡ *ታላቅ፡
ተራራም፡ ያለ፡ በእሳት፡ እንጂ፡ ተቃጠለ፡ በባሕር፡
ወደቀ፡ የባሕረም፡ ሲሶ፡ ተደም፡ ሆነ።
*ኤር፡ ፶፩፡ ፷፭፡፡ ተዘፀአ፡ ፯፡ ፳፡ ፳፭፡፡

፱፡ በባሕርም፡ ያለው፡ ነፍሰ፡ ያለው፡ ፈጥረት፡ ሲ
ሶው፡ ሞተ። ሲሶውም፡ መርከብ፡ ጠፋ።

፲፡ ሶስተኛውም፡ መልአክ፡ነፋ፡ *ታላቅ፡ኮከብም፡
ከሰማያ፡ ወደቀ፡ እንጂ፡ መብራት፡ ሲያበራ፡ በፈሳ
ሹም፡ሲሶ፡ላይ፡ወደቀ፡ በውኃውም፡ምንጮች፡ላይ።
*ኢሳ፡ ፲፬፡ ፲፪፡፡ ደኃ፡ ፭፡ ፲፡፡

፲፩፡ ኮከቡም፡ አፈሰንቴን፡ይባላል። የውኃውም፡
ሲሶ፡ አፈሰንቴን፡ ሆነ፡ ብዙ፡ ሰዎችም፡ ሞቱ፡ ከውኃ
ው፡ የተነሣ፡ መራራ፡ ሁኖአቸዋ።

፲፪፡ አራተኛውም፡ መልአክ፡ ነፋ፡ *የጸሐይ፡ቱም፡
ሲሶ፡ ተመታ፡ የጨረቃውም፡ ሲሶ፡ የከዋክብቱም፡
ሲሶ፡ሲሰዋቸው፡ ተይጨለም፡ ዘንድ፡ቀኑም፡ሲሶው፡
እንደያበራ፡ ሌቱም፡ እንደሁ።
*ም፡ ፯፡ ፲፪፡፡
ተዘፀአ፡ ፲፡ ፳፭፡፡

፲፫፡ አየሁም፡ ሰማሁም፡ *አንድ፡ መላእክት፡ በሰ
ማይ፡ መካከል፡ የሚበር፡ በታላቅ፡ቃል፡ ኢያለ። ተወ
ዮ፡ ወዮ፡ወዮ፡ በም.ድር፡ ለሚኖሩ፡ ከቀረት፡ከሶስቱ፡
መላእክት፡መለከት፡ድምጽ፡ደነፋ፡ዘንድ፡ያላቸው።
*ም፡ ፲፬፡ ፯፡፡ ም፡ ፬፡ ፲፪፡፡ ና፡ ፲፩፡ ፲፱፡፡ ና፡ ፲፪፡ ፲፪፡፡

ምዕራፍ፡ ፱፡

፩፡ አምስተኛውም፡መልአክ፡ነፋ፡ *ኮከብም፡ከሰ
ማይ፡ በም.ድር፡ላይ፡ ሲወድቅ፡አየሁ፡ የጠለቀም፡ጕ
ድጓድ፡ተመክፈቻ፡ተሰጠው።*ም፡፳፡፲፡፡ ተም፡ ፳፡፭፡፡

፪፡ የጠለቀውንም፡ ጕድጓድ፡ ከፈተው፡ ከጕድጓ
ዱም፡ ጢስ፡ ወጣ፡ እንደ፡ ታላቅ፡ እንደ፡እተን፡ጢስ፡
ጸሐይም፡ *ጠቁረች፡ አየርም፡ ከጕድጓዱ፡ ጢስ፡ የ
ተነሣ። ኢዮ፡ ፪፡ ፪፡ ፲፡፡

፫፡ ከጢሱም፡ አንበጣ፡ ወጣ፡ በምድር፡ ላይ፡ ሥል
ጣንም፡ ተሰጣቸው፡ እንደ፡ ምድር፡ ጊንጦች፡ ሥል
ጣን።

፬፡ ተባለላቸውም፡የምድሪን፡ሣር፡እንደይጕዱ፡
ማናቸውንም፡ የለመለመውን፡ ሁሉ፡ ዛፊንም፡ ሁ
ሉ። ከሰዉች፡ በቀር፡ የእግዚአብሔር፡ *ማሕተም፡
በግምባራቸው፡ የሌለባቸውን። *ም፡ ፯፡ ፫፡፡

፭፡ እንደይገልዋቸውም፡ ተሰጣቸው፡ አምስት፡
ወር፡ ሊሣቅይዋቸው፡ እንጅ። ሠቃያቸውም፡ እን
ደ፡ ጊንጥ፡ ሠቃይ፡ ነው፡ ሰውን፡ በነደፈች፡ ጊዜ።

፮፡ በዚያም፡ ወራት፡ሰዉች፡ ሞት፡ ይሻሉ፡ አያገኙ
ትምም። ይሞቱ፡ ዘንድም፡ ይወደዱ፡ ሞትም፡ ከር
ሳቸው፡ ይሸሻል። ሉቃ፡ ፳፫፡ ፴፡—፴፩፡፡

፯፡ *ያንበጣውም፡ ምሳሌ፡ ለሰልፍ፡ እንደ፡ ተዘጋ
ጀ፡ ፈረሰ፡ ይመስላል፡ በራሰዋም፡ ላይ፡ ወርቅ፡ እንደ
ሚመሰል፡አክሊል፡ አለ። ፊትዋም፡እንደ፡ ሰው፡ ፊ
ት፡ ነው። *ኢዮ፡ ፴፱፡ ፴፡፡

፰፡ ጸጕርም፡ አላት፡ እንደ፡ ሴት፡ ጸጕር። ጥርስዋ
ም፡ እንደ፡ አንበሳ፡ ጥርስ፡ ነው።

፱፡ ጥሬርም፡ አላት፡ እንደ፡ብረት፡ ያለ። የክንፎች
ዋም፡ ድምጽ፡ እንደ፡ ብዙ፡ እንደ፡ ፈረስ፡ ሠረገላ፡
ድምጽ፡ነው፡ ወደ፡ ሰልፍ፡ እንደምትሮጥ።

፲፡ ጅራትም፡አላት፡የጊንጥ፡ *ጅራት፡የሚመስል።
በጅራትዋም፡ ሾህ፡ አለበት። ሠልጣንዋም፡ አምስ
ት፡ ወር፡ ሰውን፡ ትጣቅይ፡ ዘንድ፡ ነው። *ቊ፡ ፲፬፡፡

፲፩፡ ለርሳቸውም፡ ንጉሥ፡ አላቸው፡ የጥልቅ፡መላ
ክ። ስሙም፡ ብዕብራይስጥ፡ አባዶን፡ ነው፡ በፅርዕ
ም፡ ስሙ፡ አጰልዮን፡ ይባላል። ቊ፡ ፭፡፡

፲፪፡ አንደ፡ ወዮ፡ ሔደ፡ እነሆ፡ ደግሞ፡ *ሁለት፡ ወ
ዮ፡ይመጣል፡ከዚህ፡በኋላ። *ም፡ ፳፡፡ ር፡፡ ፲፭፡፲፱፡፡

፲፫፡ ስድስተኛውም፡መልአክ፡ ነፋ፡አንድ፡ ድምጽ
ም፡ ሰማሁ፡ ከወርቁ፡ መሠውያ፡ ካራቱ፡ ቀንዶች፡ በ
እግዚአብሔር፡ *ፊት፡ ካለው። *ም፡ ፳፡፡ ር፡፡
ዘፀአ፡ ፴፡ ፭፡፡

፲፬፡ እንደህ፡ ሲል፡ለስድስተኛው፡ መልአክ፡ መለ
ከት፡ ለያዘው። *በታላቁ፡ ወንዝ፡ በኤፍራጥስ፡ የታ
ሠሩትን፡ አራቱን፡ መላእክት፡ ፍታ። ም፡ ፲፯፡ ፲፪፡፡

፲፭፡ አራቱ፡ መላእክትም፡ ተፈቱ፡ የተዘጋጁት፡ ለ
ሰዓት፡ ለቀንም፡ ለወርም፡ ላመትም፡ *ሲሶውን፡ ሰ
ው፡ ይገሉ፡ ዘንድ። *ም፡ ፳፡ ፯፡፡

፲፮፡ ያርበኞችም፡ ጭፍራ፡ ቊጥር፡ ሁለት፡ አልፍ፡
አአላፊት፡ ናቸው። ቊጥራቸውንም፡ ሰማሁ።

፲፯፡ እንደሁም፡በራእይ፡ ፈረሶን፡አየሁ፡ በርሳቸ
ውም፡ የተቀመጡባቸውን። በርሳቸውም፡የእሳት፡
ጥሩር፡ አለባቸው፡ ያሰማንጉንም፡ የጂንም። የፈረ
ሱም፡ ራስ፡ እንደ፡ አንበሳ፡ራስ፡ነበር፡ካፋቸውም፡ደ
ወጣል፡ እሳት፡ ጢስም፡ ዲንም።

፲፰፡ ከዚህም፡ ከሶስቱ፡ የሰው፡ሲሶው፡ሞተ፡ከእ
ሳት፡ ከጢስም፡ ከጂንም፡ ካፋቸው፡ ከሚወጣው።

፲፱፡ የፈረሶች፡ ሠልጣን፡ ባፋቸው፡ ነውና፡ በጅራ
ታቸውም። ጅራታቸውም፡ እባብ፡ ይመስላል፡ ራስ
ም፡ አለው፡በርሱም፡ ይጕዳሉ።

፳፡ የቀረትም፡ ሰዉች፡ በዚህ፡ መቅሠፍት፡ያልሞ
ቱ፡ ከጀቻው፡ ስራ፡ *ነሰሐ፡ አይገቡም፡ ነበር፡ ለሰይ
ጣናት፡ †እንደይሰግዱ፡ለወርቅም፡ጣዖት፡ለብርም፡
ለናስም፡ለደንጊያም፡ለንጨትም። የማትችል፡ታይ፡
ዘንድ፡ትሰማ፡ትሔድም፡ዘንድ። *ም፡ ፲፮፡ ፲፭፡ ፳፭፡፡
†ዳ፡ ቀር፡ ፲፡ ፳፡፡

፳፩፡ ደም፡ ከማፈሰሳቸውም፡ እይመለሱም፡ ነበ
ረ። አስማትም፡ከማድረጋቸው፡ከዝሙታቸውም፡
ከመሰረቃቸውም።

ምዕራፍ፡ ፲፡

፩፡ ሌላ፡ *ብርቱ፡ መልአክም፡ አየሁ፡ ከሰማይ፡ ሲ
ወርድ፡ በደመና፡ ተጐናጽፎ፡ በራሱ፡ ላይም፡ *የደመ
ና፡ ቀስት፡ ነበረ፡ ፊቱም፡ እንደ፡ ጸሓይ፡ ነው፡ እግሮቹ
ም፡ እንደ፡ እሳት፡ ዓምድ፡ ናቸው። *ም፡ ፭፡ ፪፡፡
†ም፡ ፱፡ ር፡፡

፪፡ *በጂም፡ታናሽ፡መጽሐፉ፡የተዘረጋ፡ነበረ፡ቀኝ፡
እግሩንም፡ በባሐር፡ ላይ፡ አደረገ፡ ግራውንም፡ በም
ድር፡ ላይ። *ም፡ ፭፡ ፩፡፡

፫፡ በታላቅ፡ ቃልም፡ ጮኸ፡ እንደሚጮህ፡ *አንበ
ሳ። በጮኸም፡ ጊዜ፡ ሰባቱ፡ ነጐድጓዶች፡ በቃላቸው፡
ተናገሩ። *ኤር፡ ፶፭፡ ፴፡፡ ሆሴ፡ ፲፩፡ ፲፡፡ አሞ፡ ፭፡ ፪፡፡

፬፡ ሰባቱ፡ ነጐድጓዶችም፡ በቃላቸው፡ በተናገሩ፡ ጊ
ዜ፡ እጽፍ፡ ብዬ፡ ነበርሁ። ከሰማይም፡ ድምጽ፡ ሰማ
ሁ፡ እንደህ፡ የሚለኝ። ተወው፡ ሰባቱ፡ ነጐድጓድ፡ የ
ተናገሩትን፡ አጻፈውም። ዳን፡ ፰፡ ፳፯፡፡
ም፡ ፲፪፡ ፱፡ ፴፡፡

፭፡ በምድርና፡ በባሕር፡ ላይም፡ ቁሞ፡ያየሁት፡ መ
ልአክ፡ እጁን፡ ወደ፡ሰማይ፡አነሣ። ዘፍጥ፡ ፲፬፡ ፳፪፡፡
ኀ፡ በዘላለሙ፡ ሕያውም፡ *ማለ፡ሰማይን፡ በፈጠ
ረ፡ በርስዋም፡ ያሉትን፡ ባሕርንም፡ በርሱም፡ ያሉት
ን። †እንጊህ፡ ዘመን፡ እንደይሆን።
*ዳን፡ ፲፪፡ ፯፡፡ †ም፡ ፮፡ ፲፭፡፡

፯፡ ነገር፡ ግን፡ *በሰባተኛው፡ መልአክ፡ ድምጽ፡ ወ
ራት፡ ደነፋ፡ ዘንድ፡ ባለው፡ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር፡
†ምሥጢር፡ ይጨረሳል፡ ለባሮቹ፡ ለነቢያት፡ እንደ፡ተ
ናገረ። *ም፡ ፲፩፡ ፲፭፡፡ †፩፡ ቀር፡ ፲፭፡ ፶፩፡፡

፰፡ ከሰማይም፡ ሰምተው፡ የነበርሁ፡ቃል፡ ደግሞ፡
ከኔ፡ ጋራ፡ ተናገረ፡ አለም። ሒድና፡ ታናሽን፡ መጽሐ
ፍ፡ የተከፈተውን፡ ውሰድ፡በምድር፡ላይና፡ በባሕር፡
ላይ፡ በቀመው፡ በመልአኩ፡ እጅ፡ ያለውን።

፱፡ ወደ፡ መልአኩም፡ ሔድሁ፡ አልሁትም። ታና

ኹን፡ መጽሐፌ፡ ስጠኝ። አለኝም። *ውሰደው፡ ብላ ውም፡ ሆድህንም፡ ያመረረው፡ ባፌህ፡ ግን፡ ጸፈጭ፡ ደሁን፡ እንጂ፡ ማር። ሕዝ፡ ፫፡ ፭፡—፫፡፡

፲፡ ታናኩንም፡ መጽሐፌ፡ ወሰድሁ፡ ከመልአኩ፡ እጅ፡ በላሁትም፡ ባፈም፡ እንጂ፡ ማር፡ ጸፈጭ፡ ሆነ። በበላሁትም፡ ጊዜ፡ ሆደን፡ አመረረው።

፲፭፡ አለኝም። ደገባሃል፡ ትንቢት፡ ትናገር፡ ዘንድ፡ ደግሞ፡ በሕዝብና፡ በአሕዛብ፡ ላይ፡ በቋንቋችም፡ በ ብዙም፡ ነገሥታት፡ ላይ።

ምዕራፌ፡ ፲፭፡

፩፡ *ዘንግም፡ ተሰጠኝ፡ እንጂ፡ በትር፡ ያለ። መልአ ኩም፡ ቀመ፡ እንጂህ፡ ሲለኝ። ተነሣ፡ የእግዚአብሔ ርንም፡ መቅደስ፡ ሰፈር፡ መሠውያውንም፡ በርሱ፡ የ ሚሰግዱትንም። *ሕዝ፡ ፵፡ ፫፡፡ ዘካ፡ ፪፡ ፩፡ ፪፡፡

፪፡ ከመቅደሱ፡ በሚያ፡ያለውን፡ ወለሉን፡ ግን፡ ተ ወው፡ አትለካውም፡ *ለአሕዛብ፡ ተሰጥተዋልና፡ የ ተቀደሰችውንም፡ አገር፡ ደረግጥዋታል፡ ፲አርባ፡ ሁለ ት፡ ወር። *ሉቃ፡ ፳፩፡ ፳፬፡፡ ተም፡ ፲፩፡ ፫፡፡ ና፡ ፲፪፡ ፯፡ ፲፬፡፡ ና፡ ፲፫፡ ፭፡፡

፫፡ ሥልጣንም፡ እሰጣለሁ፡ ለሁለቱ፡ ሰማዕታቴ፡ ሸህ፡ ከሁለት፡ መቶ፡ ሰድሳ፡ ቀንም፡ ትንቢት፡ ይናገሬ ሉ፡ ማቅ፡ ለብሰው። ቁ፡፡ ፪፡፡

፬፡ እሌህ፡ ሁለቱ፡ ዘይቶች፡ ሁለቱም፡ መቅረዞች፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ በምድር፡ጌታ፡ ፊት፡ የቆሙ፡ ና ቸው። ዘካ፡ ፬፡ ፫፡ ፲፭፡ ፲፬፡፡

፭፡ ማንም፡ ይጐዷቸው፡ዘንድ፡ቢወድ፡ ካፋቸው፡ እሳት፡ትወጣለች፡ጸላቶቻቸውንም፡*ታቃጥላቸዋለ ች። ማንም፡ ደግሞ፡ ሊበድላቸው፡ቢወድ፡ እንጂሁ፡ ይሞት፡ ዘንድ፡ ይገባል። *፪፡ ነገሥ፡ ፩፡ ፲፡፡

፮፡ እሌህ፡ ሥልጣን፡ አላቸው፡ *ሰማይን፡ ይዘጉ፡ ዘንድ፡ ዝናም፡ እንደታዘንም፡ ትንቢት፡ በሚናገሩበ ት፡ ወራት። ለርሳቸውም፡ ሥልጣን፡ አላቸው፡ በው ኖች፡ላይ፡ለደም፡ሊመልስዋቸው፡ ምድርንም፡ደቀ ሠፈ፡ ዘንድ፡ በመቅሠፌቱ፡ ሁሉ፡ በሚሹት፡ ጊዜ፡ ሁሉ። *፩፡ ነገሥ፡ ፲፯፡ ፩፡፡ ተዘፀእ፡ ፯፡ ፲፱፡ ፳፡፡

፯፡ ሰማዕትነታቸውንም፡በፈጸሙ፡ጊዜ፡ ከቀላይ፡ የወጣው፡ አርዌ፡ ከርሳቸው፡ ጋራ፡ ሰልፌ፡ ያደርጋል፡ ያሸነፌቸውማል፡ ይገላቸውማል። ም፡ ፲፫፡ ፩፡ ፯፡፡ ና፡ ፲፯፡ ፳፡፡

፰፡ ፈሳቸውም፡ ትቀመጣለች፡ *በታላቂቱ፡አገር፡ አደባባይ፡ በመንፈሳዊ፡ ነገር፡ ሶደምና፡ ምሥር፡ የም ትባል፡ ጌታችን፡ ወደ፡ ተሰቀለባት። *ም፡ ፲፯፡ ፲፱፡፡ ሉቃ፡ ፲፫፡ ፴፱፡፡

፱፡ ፈሳቸውንም፡ ያዩታል፡ ሕዝብና፡ አሕዛብ፡ ቋ ንቀችም፡ ወገኖችም፡ ሶስት፡ ቀንና፡ እኩል፡ ፈሳቸው ንም፡ ወደ፡ መቃብር፡ ትገባ፡ ዘንድ፡ አደተውም።

፲፡ በምድርም፡ የሚኖሩ፡ በርሳቸው፡ ላይ፡ ደስ፡ ይ ላቸዋል፡ ገጸ፡ በረከትም፡ ይቀባበላሉ፡ እርሱ፡በርሳቸ ው። እሌህ፡ ሁለቱ፡ ነቢያት፡ በምድር፡ የሚኖሩን፡ ደ ሟቅዩ፡ ነበሩና።

፲፩፡ ከሶስት፡ ቀንና፡ እኩል፡ በኋላም፡ በእግዚአብ ሔር፡ የሕይወት፡ መንፈስ፡ገባባቸው፡ በግራቸውም፡ ቀሙ፡ ባይዋቸውም፡ ላይ፡ ታላቅ፡ ፈርሃት፡ ወደቀባ ቸው።

፲፪፡ ታላቅ፡ ቃልም፡ ሰሙ፡ ከሰማይ፡እንጂህ፡ ሲላ ቸው። ወደዚህ፡ ውጡ። *ወደ፡ሰማይም፡ በደመና፡ ወጡ፡ጸላተቻቸውም፡እይዋቸው።*፪፡ ነገሥ፡፪፡፲፩፡፡

፲፫፡ በዚያችም፡ ሰዓት፡ታላቅ፡ መናወጥ፡ሆነ። የከ ተማዪቱም፡አሠረኛ፡ ወደቀ። በመናወጥም፡ሰባት፡ ሸህ፡ የሰው፡ ሰም፡ሞተ። የቀረትም፡ ፈሩ፡ለሰማይ፡ አምላክም፡ ምስጋና፡ ሰጡ።

፲፬፡ *ሁለተኛው፡ ወዮ፡ ሔደ። ፲ሶስተኛውም፡ ወ ዮ፡ እነሆ፡ ፈጥኖ፡ይመጣል። *ም፡ ፱፡ ፲፪፡፡ ፲ቀ፡ ፲፭፡፡ ም፡ ፲፪፡ ፲፪፡፡

፲፭፡ ሰባተኛውም፡ መልአክ፡ ነፋ። በሰማይም፡ ታ ላቅ፡ ድምጽ፡ ሆነ፡ እንጂህ፡ ሲል። *የዓለሙ፡ መንግ ሥት፡ለጌታችንና፡ለመሢሑ፡ ሆነች፡ፕለዘላለሙም፡ ይነግሣል። *ኢኑ፡ ፪፡፵፬፡፡ ና፡ ፯፡ ፵፯፡፡ ፲ዝካ፡ ፲፬፡ ፱፡፡

፲፯፡ ህያ፡ አፌቱም፡ *ሸማግሎች፡ በእግዚአብሔ ር፡ ፊት፡ ተቀምጠው፡የነበረት፡ በወንበራቸው፡ላይ፡ በግምባራቸው፡ ፲ወደቁ፡ለእግዚአብሔርም፡ሰገደ፡ እንጂህ፡ ሲሉ። *ም፡ ፱፡ ፱፡ ፲፡፡ ፲ም፡ ፯፡ ፲፭፡፡

፲፯፡ እናመሰግንሃለን፡እግዚአብሔር፡አምላክ፡ሆ ይ፡ ሁሉን፡ የሚደዝ፡ የነበረ፡ያለም፡የሚመጣም፡ታ ላቂቱን፡ ኃይልህን፡ ወሰደህ፡ ነግሠሃልና። ም፡ ፱፡ ፮፡፡

፲፰፡ አሕዛብም፡ ተቈጡ፡ ቍጣህም፡መጣ፡የሙ ታንም፡ ዘመን፡ ሊኩሉ፡ ለባሮችህም፡ ዋጋቸውን፡ ት ሰጥ፡ዘንድ፡ለነቢያት፡ለቅዷሳንም፡ስምህንም፡ለሚ ፈሩ፡ ለታናሾች፡ ለታላቆችም፡ ምድርንም፡ የሚያጠ ፋን፡ታጠፋለህ። ም፡ ፲፭፡ ፩፡፡ መዝ፡ ፪፡ ፩፡፡ ና፡ ፭፡ ፲፪፡፡

፲፱፡ የእግዚአብሔርም፡ *መቅደስ፡በሰማይ፡ተከ ፈተ፡ በመቅደሱም፡የኪደኑ፡ ታቦት፡ተገለጠ፡መብረ ቅም፡ ሆነ፡ ድምጽም፡ ነጐድጓድም፡ መናወጥም፡ ታ ላቅም፡ በረደ። *ም፡ ፲፭፡ ፭፡፡

ምዕራፌ፡ ፲፱፡

፩፡ ታላቅም፡ መልክት፡ በሰማይ፡ ታየ። ሴት፡ ጸሓ ይ፡ ተጐናጽፋ፡ ጨረቃም፡ ከግርዋ፡ በታች። በራስዋ ም፡ ላይ፡ ያሠራ፡ ሁለት፡ ከዋክብት፡ ዘውድ።

፪፡ እርስዋም፡ የጸነሰች፡ ነበረች፡ ትጮኽማለች፡ ምፅም፡ ተይዛለች፡ *ተጨንቃማለች፡ ትወልድ፡ ዘን ድ። *ሚካ፡ ፬፡ ፲፡፡

፫፡ ሌላም፡ ምልክት፡ በሰማይ፡ ተገለጠ። እነሆት፡ ታላቅ፡ ቀይ፡ ዘንጂ፡ለርሱም፡ ሰባት፡ራሶች፡ አሉት፡ አ ፔርም፡ ቀንጂች፡ በራሶቹም፡ ላይ፡ ሰባት፡ ዛውጂች። ቀ፡፡ ፴፡፡

፱፤ ጅራቱም፡ የሰማያን፡ *ከዋክብት፡ ሲሶውን፡ ጐተተ፡ በምድርም፡ ጣላቸው። ዘንዶውም፡ ቀመ፡ ትወልድ፡ ዘንድ፡ ባሉችው፡ በቤቲቱ፡ ፊት፡ በወለደች፡ ጊዜ፡ ልጅዋን፡ ይውጠው፡ ዘንድ። *ደን፡ ፹፤ ፲፡፡

፭፤ ወንድ፡ ልጅም፡ ወለደች፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ *በ ብረት፡ በትር፡ ይጠብቅ፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ ልጅዋም፡ ወ ደ፡ እግዚአብሔር፡ ወደ፡ ዙፋኑም፡ ተነጠቀ።

*መዝ፡ ፪፡ ፹፡፡ ራእ፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

፮፤ ሴቲቱም፡ ወደ፡ በረሃ፡ *ኰበለለች፡ ከእግዚአ ብሔር፡ ዘንድ፡ ተዘጋጅተላት፡ ወደለው፡ ስፍራ፡ ከዚ ያ፡ ይመግብዋት፡ ዘንድ፡ ፲፫ሀ፡ ከሁለት፡ መተ፡ ሰድሳ፡ ቀን። *መቴ፡ ፪፡ ፲፫፡፡ ፣ራእ፡ ፲፭፡ ፫፡፡

፯፤ በሰማይም፡ ሰልፍ፡ ሆነ። *ሚካኤልና፡ መላእ ክቱ፡ ዘንዶውን፡ ተዋጉ። ዘንዶውም፡ ተዋጋው፡ ከመ ላእክቱ፡ ጋራ። *ደን፡ ፲፡ ፲፫፡ ፷፭፡፡ ና፡ ፲፱፡ ፭፡፡

፰፤ አላሸነፈምም።ከዚያ፡ ወዲያም፡ በሰማይ፡ ስ ፍራ፡ አልተገኘላቸውም።

፱፤ ታላቁም፡ ዘንዶ፡ *ተጣለ፡ አርሱም፡ ተየቀደመ ው፡ አባብ፡ ዲያብሎስ፡ የሚባል፡ ሰይጣንም፡ ዓለሙ ን፡ ሁሉ፡ የሚያስት። በምድር፡ ላይም፡ ተጣለ፡ መላ እክቱም፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ተጣሉ። *ሉቃ፡ ፲፡ ፲፰፡፡ ዮሐ፡ ፲፪፡ ፴፭፡፡ †ዘፍጥ፡ ፫፡ ፭፡ ፲፱፡፡

፲፡ በሰማይም፡ ታላቅ፡ ቃልን፡ ሰማሁ፡ እንዲህ፡ ሲ ል። *አሁን፡ ያመላካችን፡ መድኃኒት፡ ኾሎቱም፡ መ ንግሥቱም፡ የመሢሑ፡ ሥልጣንም፡ ሆነች። ወንድ ሞቻችንን፡ የሚያሳጣቸው፡ ወድቋልና፡ ባመላካች ን፡ ፊት፡ ተያሳጣቸው፡ የነበረ፡ ሌትና፡ ቀን።

*ም፡ ፲፭፡ ፲፰፡፡ †ኢዮብ፡ ፩፡ ፲፭፡፡ ዘካ፡ ፫፡ ፭፡፡ ሉቃ፡ ፳፪፡ ፴፩፡፡

፲፩፤ እርሳቸውም፡ *ድል፡ ነሡበት፡ በበጉ፡ ተደም፡ በ ምሰክርነታቸውም፡ **ቃል፡ ነፍሳቸውንም፡ አልወደ ዷም፡ እስከ፡ ሞት፡ ድረስ። *ሮሚ፡ ፰፡ ፴፯፡፡

†ም፡ ፯፡ ፲፱፡፡ **ሮሜ፡ ፲፮፡፡

፲፪፤ ሰለዚህ፡ ደስ፡ ይበላቸሁ፡ አላጎት፡ ሰማዮች፡ በርሳቸውም፡ ያላቸሁ። በምድርና፡ በባሕር፡ ለምት ናፈ፡ግን፡ ወዮላችሁ። ዲያብሎስ፡ ወርዶባችኋልና፡ በ ርሱም፡ታላቅ፡ሞጣ፡ አለበት፡ ጥቂት፡ ዘመን፡ አንድ፡ ቀረላት፡ያውቃልና።

፲፫፤ ዘንዶውም፡ ወደ፡ ምድር፡ አንደ፡ ተጣለ፡ ባዮ፡ ጊዜ፡ ወንድ፡ ልጅ፡ የወለደቸውን፡ ሴት፡ አሳደደ።

፲፬፤ ለሴቲቱም፡ የታላቅ፡ ንስር፡ ሁለት፡ ክንፍ፡ ተ ሰጣት፡ወደ፡ በረሃ፡ ትበር፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ስፍራዋ፡ ከዚ ያ፡ወደምትመገብበት፡ ሰፍራ፡*አንድ፡ ዘመን፡ሁለት ም፡ዘመን፡ የዘመን፡ አኩሌታም፡ ከእባቡ፡ፊት።

*ደን፡ ፯፡ ፷፭፡፡ ና፡ ፲፱፡ ፲፡፡

፲፭፤ አባቢቱም፡ ካፍዋ፡ ውኃ፡ ተፈች፡ እንደ፡ ፈሳ ሽ፡ወንዝ፡ከሴቲቱ፡ በኋላ፡ከውኃ፡ አንደ፡ ተወሰደች፡ ሊታደርጋት።

፲፮፤ ምድሪቱም፡ ሴቲቱን፡ ረደቻት፡ ምድሪቱም፡ አፈዋን፡ ከፈተች፡ ዘንደው፡ ካፈ፡ የተፈውንም፡ ፈሳ ሽ፡ወንዝ፡ ዋጠችው።

፲፯፤ ዘንደውም፡ በሴቲቱ፡ ላደ፡ ተቈጣ፡ ከቀሩት ም፡ ዘርዋ፡ጋራ፡ ሰልፍ፡ያደርግ፡ ዘንድ፡ ሔደ፡*የእግዚ አብሔሮን፡ ትእዛዝ፡ ከሚጠብቁ፡ የዖሱስ፡ ክርስቶስ ም፡ ምሰክር፡ ካላቸው። *ም፡ ፲፱፡ ፲፪፡፡ ና፡ ፲፱፡ ፲፡፡

፭፡ዮሐ፡፭፡፲፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፫፡

፩፤ በባሕርም፡ አሻቀ፡ ላደ፡ ቀመሁ። *አርቄም፡ ከ ባሕር፡ ሲወጣ፡ አየሁ፡ ለርሱም፡ አሥር፡ ቀንደች፡ አሉ ት፡ ሰባትም፡ ራሶች፡ በቀንደቹም፡ ላደ፡ አሥር፡ አክ ሊሎች፡ በራሶቹም፡ ላደ፡ የሰድብ፡ ሰም።

*ም፡ ፲፭፡ ፯፡፡ ና፡ ፲፯፡ ፫፡፡ ደን፡ ፯፡ ፯፡ ፷፡፡

፪፤ ያየሁትም፡ አርቄ፡ነምር፡ ይመስላል፡ አግረምፉ አንደ፡ ድብ፡ አግር፡ ነው፡ አፈም፡ አንደ፡ አንበሳ፡ አፍ፡ ነው። *ዘንዶውም፡ ኃይሉን፡ ሰጠው፡ ዙፋኑንም፡ ታላ ቅም፡ ሥልጣን።

*ም፡ ፲፪፡ ፫፡፡

፫፡ አንድ፡ ራሱንም፡ አየሁ፡ ለሞት፡ አንደ፡ ታረደ፡ የሞቱም፡ ቍስል፡ ሻረ፡ *ምድር፡ ሁሉም፡ ተደነቀች፡ ከአርቄው፡ በኋላ።

*ም፡ ፲፯፡ ፷፡፡

፬፤ ለአርቄው፡ ሥልጣን፡ ለሰጠውም፡ ለዘንደው፡ ሰገዱ፡ ለአርቄውም፡ ሰገዱ፡ እንደህ፡ ሲሉ። አርቄ ውን፡ማን፡ ደመሰለዋል። ማን፡ ደቅላል፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ደዋጋ፡ ዘንድ።

፭፤ *አፈም፡ተሰጠው፡ በታላቅ፡ ነገር፡ በስድብ፡ የ ሚያገር። ሥልጣንም፡ ተሰጠው፡ ደደርግ፡ ዘንድ፡ ተአ ርባ፡ሁለት፡ወር። *ደን፡ ፯፡ ፷፡ ፲፭፡፡ ፪፡ ተሰ፡ ፪፡ ፱፡፡ †ራእ፡ ፲፭፡ ፪፡፡

፮፤ አፈንም፡ከፈተ፡ አግዚአብሔርን፡ ለመስደብ፡ ሰሙንስ፡ ደሰድባል፡ ማደርደውንም፡ በሰማደም፡ የ ሚኖሩትን።

፯፤ ከቅዱሳን፡ጋራም፡ ሰልፍ፡ደደርግ፡ ዘንድ፡ *ተሰ ጠው፡ደሸንፈቸውም፡ዘንድ፡ሥልጣንም፡ተሰጠው፡ በዘመድ፡ሁሉ፡በቋንቋም፡በወገንም። *ም፡ ፲፭፡ ፯፡፡ ደን፡ ፯፡ ፷፭፡፡

፰፤ በምድር፡ *ላደም፡ ደሉ፡ ሁሉ፡ ደሰግዱለታል፡ ስሟቸው፡ ተደለተጻፈ፡ ዓለም፡ **ሳደፈጠር፡ በታረደ ው፡ በበጉ፡ ሕደወት፡ መጽሐፍ። *ም፡ ፲፪፡ ፲፪፡፡ †ም፡ ፫፡ ፭፡፡ **ም፡ ፲፯፡ ፷፡፡

፱፤ ማንም፡ ጀሮ፡ ደለው፡ እንደሆን፡ ደስማ።

፲፡ ማንም፡ ወደ፡ እሥር፡ የሚደግዝ፡ ወደ፡ እሥር፡ ደገባል። *ማንም፡ በሰይፍ፡ ገድሎ፡ እንደሆን፡ ደገበ ዋል፡በሰደፍ፡ደሞት፡ ዘንድ። †ከዚህ፡ ነው፡ የቅዱሳ ን፡ትዕግሡት፡ሃደማናታቸውም። *ዘፍጥ፡ ፱፡ ፮፡፡ ኢሳ፡ ፴፫፡ ፭፡ ማቴ፡ ፷፯፡ ፶፱፡፡ †ራእ፡ ፲፱፡ ፲፪፡፡

፲፩፤ ሌላም፡አርዌ፡ከምድር፡ሲወጣ፡ አየሁ። ሁለ ት፡ ቀንደችም፡ ነበረት፡ አንደ፡ *በግ፡ ቀንደች፡ አንደ፡ ዘንደውም፡ ደናገር፡ ነበር። *ም፡ ፲፯፡ ፲፫፡፡ ማቴ፡ ፯፡ ፲፭፡፡ ና፡ ፷፱፡ ፭፡፡

፲፭፡ የፈተኖውንም፡አርዌ፡ሠልጣን፡ሁሉ፡በፊቱ፡ ያደርጋል። ምድርንም፡ በርስዋም፡ የሚያረጓ፡ ለፈ ተኖው፡ አርዌ፡ እንጂ፡ሰግጂ፡ ያደርጋል፡ የሞቱ፡ ቍስ ል፡ለተፈወሰችው። ቁ፡ ፪፡ ፱፡ ፭፡ ፺፡፡

፲፫፡ ታላቅ፡ *ተአምራትም፡ ያደርጋል፡ ከሰማይ፡ በምድር፡ላይ፡አሳት፡ አስኪያወርድ፡ ድረስ፡ በሰው፡ ፊት። *ማቴ፡ ፳፬፤ ፳፬፡፡ ፪፡ ተሰ፡ ፪፡ ፱፡፡ ፭፡ ነገሥ፡ ፲፰፡ ፴፱፡፡

፲፱፡ በምድር፡የሚያረትንም፡ ያታላል፡ በተሰጠች ው፡*ተአምራት፡ በአርዌው፡ ፊት፡ ያደርጋት፡ ዘንድ። በምድር፡ ላይ፡ የሚያረትን፡ ሲል፡ የአርዌውን፡ መል ክ፡ ያደርጉ፡ዘንድ፡ የሰይፍ፡ ቍስል፡ ያለበቱ፡ የደነው ም። *ዘያግ፡ ፲፫፡ ፭፡፡

፲፰፡ ለአርዌውም፡መልክ፡ ነፍስ፡ያገባለት፡ ዘንድ፡ ተሰጠው፡የአርዌው፡ መልክ፡ ደግሞ፡ አንጂ፡ናገር። ያ ደርግም፡ዘንድ፡ ለአርዌው፡ መልክ፡ የማይሰግጅ፡ ሁ ሉ፡ እንጂ፡ሞት።

፲፯፡ ሁሉንም፡ አደረገ፡ ታላቁን፡ ታናሹንም፡ ባለጠ ጎችንም፡ድኆችንም፡ የሰው፡ ልጆችንም፡ ባሮችንም፡ *ምልክት፡ አስኪሰጣቸው፡ ድረስ፡ በቀኛ፡ አጀቸው፡ ወይም፡ በግምባራቸው።። *ም፡ ፲፱፡ ፷፡፡

፲፯፡ ማንም፡መግዛትና፡መሸጥ፡ አስኪሳነው፡ ድረ ስ፡ምልክት፡ ከሌለበት፡ ወይም፡ የአርዌው፡ ስም፡ወ ይም፡የስሙ፡ቍጥር።

፲፰፡ ከዚህ፡*ጥበብ፡ናት። አውቀት፡ ያለው፡ የአር ዌውን፡ ተቍጥር፡ ይቍጠር፡ የሰው። ቍጥር፡ ነውና። ቍጥሩም፡ ሰድስት፡ መቶ፡ ስድሳ፡ ስድስት፡ ነው።

*ም፡ ፲፯፡ ፱፡፡ †ም፡ ፲፭፡ ፪፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፬፡

፩፡ አየሁም፡ እነሆም፡ በግ፡ በጽዮን፡ ተራራ፡ ላይ፡ *ቁሞ፡ከርሱም፡ጋራ፡ መቶ፡ አርባ፡ አራት፡ ሺህ፡ ያባቱ ም፡ †ስም፡ በግምባራቸው፡ ተጽፎ፡ዋል።

*ም፡ ፯፡ ፱፡ ፱፡፡ †ም፡ ፫፡ ፲፪፡፡

፪፡ ከሰማይም፡ድምጽን፡ ሰማሁ፡እንጂ፡ብዙ፡ ው ኆች፡ ድምጽ፡ እንጂ፡ ታላቅ፡ ነጐድጓድም፡ ድምጽ። መሰንቅ፡የሚመቱትንም፡ድምጽ፡ ሰማሁ። በመሰን ቋቸው፡ ሲደረድሩ። ም፡ ፭፡ ፲፭፡፡

፫፡ እንጂ፡ሰ፡ምስጋናም፡ያለውን፡በዙፋኑ፡ፊት፡ ባራቱ፡ እንሰሶችና፡ በቀሳውስቱም፡ ፊት፡ አዘመረ። ማንም፡ያችን፡ዝማሬ፡ይማር፡ዘንድ፡አይቻለውም፡ ከምድር፡ዘንድ፡ከተዋጀ፡ከመቶ፡አርባ፡አራት፡ ሺህ፡ በቀር። ም፡ ፭፡ ፱፡፡

፬፡ እሌሁ፡ናቸው፡ ከሴቶች፡ ጋራ፡ ያልረከሱ፡*ድን ግሎች፡ ናቸውና፡ በጉንም፡ ወደሚሔድበት፡ ሁሉ፡ የ ሚከተሉት፡ እሌሁ፡ ናቸው። እሌሁ፡ ከሰዎች፡ †ተዋ ጀ፡ ቀደማያት፡ ሁነው፡ ለእግዚአብሔር፡ ለበጉም። *፪፡ ቀር፡ ፲፩፡ ፪፡፡ ኤፈ፡ ፭፡ ፶፯፡፡ †ም፡ ፭፡ ፱፡፡

፭፡ ባፋቸውም፡አሰት፡ አልተገኘም። በእግዚአብ ሔር፡ ዙፋን፡ፊት፡ያለ፡ ነውር፡ ናቸውና።

፮፡ ሌላም፡ *መልአክ፡ አየሁ፡ በሰማይ፡ መካከል፡ ሲበር፡ የዘላለሙንም፡ ወንጌል፡ ይዝዋል፡ በምድር፡ ለሚያረት፡ ይሰብክ፡ ዘንድ፡ ለሕዝብና፡ ለአሕዛብ ም፡ለቋንቋንም፡ ለወገንም፡ ሁሉ። *ም፡ ፷፤ ፲፫፡፡

፯፡ በታላቅ፡ቃል፡እንጂህ፡ሲል። እግዚአብሔርን፡ ፈሩ፡*ምስጋናም፡ ስጡት፡የሚፈርድባት፡ ጊዜ፡ መጥ ታለችና። ሰማይንና፡ ምድሪንም፡ †ለፈጠረ፡ ስገጂ፡ ባሕሪንም፡ የውኃውንም፡ ምንጮች።

*ዘያግ፡ ፴፱፡ ፫፡፡ †የሐዋ፡ ፲፬፡ ፲፭፡፡

፰፡ ሌላውም፡ መልአክ፡ ተከተለው፡ እንጂህ፡ ሲ ል።*ወደቀች፡ ወደቀች፡ታላቂቱ፡ አገር፡ባቢሎን። የዝ ሙትዋን፡ ቍጣ፡ ጸጅ፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ አጠጥታለ ችና። *ም፡ ፲፰፡ ፪፡፡ ኢሳ፡ ፳፩፡ ፱፡፡ ኤር፡ ፶፩፡ ፰፡፡

፱፡ ሶስተኛውም፡ መልአክ፡ ተከተላቸው፡ በታላ ቅ፡ቃል፡ እንጂህ፡ሲል። ማንም፡ ለአርዌው፡ ቢሰግጅ፡ ለሥአሉም፡ ምልክቱንም፡ የሚወሰድ፡ በግምባሩ፡ ወይም፡ *በጀ። ም፡ ፲፫፡ ፲፪፡—፲፯፡፡

፲፡ ያህ፡ ከእግዚአብሔር፡ ቍጣ፡ ጸጅ፡ ይጠጣል፡ ሰይጀበለቅ፡በቍጣው፡ጽዋ፡*የተቀደውን። በሳትና፡ በጂገም፡በቅጂሳን፡መላእክት፡ፊት፡በበጉም፡ ፊት፡ †ይሣቀያል። *ም፡ ፲፯፡ ፲፰፡፡ ኤር፡ ፶፭፡ ፲፭፡፡ *ም፡ ፲፱፡ ፷፡፡

፲፩፡ የሠቃያቸውም፡ ጢስ፡ ለዘላለምና፡ ዘላለም ና፡ይወጣል።ዕረፍትም፡ የላቸውም፡ በቀንና፡ በሌት፡ ለአርዌው፡ለሚሰግጂ፡ለሥአሉም፡ ማንም፡ የሰሙ ን፡ ምልክት፡ ቢወሰድ። ም፡ ፲፱፡ ፫፡፡

፲፪፡ ከዚህ፡ነው፡ የቅጂሳን፡*ትዕግሥት፡ የእግዚአ ብሔርን፡ ትእዛዝ፡ †የሚጠብቁ፡ የየሱስንም፡ ሃይ ማኖት። *ም፡ ፲፫፡ ፲፡፡ †ም፡ ፲፪፡ ፲፯፡፡

፲፫፡ ከሰማይም፡ ቃልን፡ ሰማሁ፡ እንጂህ፡ የሚለ ኛን። ጻፏ። በጌታ፡ የሚሞቱ፡ ብፁዓን፡ ናቸው፡ ካሁ ን፡ ጀምረው። አዎን። መንፈስ፡ ይላል። ከድካማቸ ው፡ *ያርፉ፡ ዘንድ፡ †ምግባራቸውም፡ ትከተላቸዋ ለች። *ኢሳ፡ ፶፯፡ ፩፡፡ †ዕብ፡ ፬፡፡ ፲፡ ፲፡፡

፲፬፡ አየሁም፡ እነሆም፡ *ነጭ፡ደመና፡ በደመናው፡ ላይም፡ ተቀመጥዋል፡ የሰው፡ ልጅ፡ የሚመስል። በ ራሱ፡ላይም፡ የወርቅ፡አክሊል፡ ነበረበት፡ በጂም፡ †የ ተሳለ፡ ማጭድ፡ ይዞ፡ ነበረ። *ዳን፡ ፯፡ ፲፫፡፡ †ማቴ፡ ፲፫፡ ፴፱፡ ፵፭፡፡

፲፭፡ ሌላም፡ መልአክ፡ ከመቅደስ፡ ወጣ፡ በታላቅ፡ ቃል፡ *ሲጮህ፡ በደመና፡ ላይ፡ ለተቀመጠው። ማጭ ድህን፡ ስደድና፡ አጭድ፡ የመከር፡ ጊዜ፡ ደርሳልሃለች ና፡የምድሪ፡አህል፡ደርቋልና። *ኢዮ፡ ፫፡ ፲፯፡፡

፲፮፡ በደመና፡ ላይ፡ የተቀመጠውም፡ ማጭዱን፡ በምድር፡ ላይ፡ አደረገ፡ ምድሪቱም፡ ታጨደች።

፲፯፡ ሌላውም፡ መልአክ፡ ከሰማይ፡ ካለው፡ መቅ

ደስ፡ ወጣ፡ ከርሱ፡ ጋራም፡ ደግሞ፡ የተሳለ፡ ማጭድ፡ አለ።

፲፰፡ ሌላውም፡ መልአክ፡ ከመሠውያው፡ ወጣ፡ እርሱም፡ በእሳት፡ ታዝዋል፡ በታላቅ፡ ጩኸትም፡ጮኸ፡የተሳለ፡ ማጭድ፡ ለያዘው፡ እንጂህ፡ ሲል። የተሳለውን፡ማጭድህን፡ ስደድ፡ የምድረንም፡ ዘለላ፡ ቍረጥ፡ወይኑ፡ በስልዋልና።

፲፱፡ መልአኩም፡ ማጭዱን፡ በምድር፡ አደረገ፡ የምድረንም፡ወይን፡ ቍረጠ፡ በታላቁም፡ በእግዚአብሔር፡*ቍጣ፡መጥመቂያ፡ጣለው። *ም፡ ፲፱፡ ፲፭፡፡

፳፡ *መጥመቂያውም ፡ ተረገጠ ፡ ካገር ፡ በሚደ፡ ከመጥመቂያውም፡ደም፡ ወጣ፡ወደ፡ፈረሱ፡ልጓም፡ አስኪደርስ፡ ወደ፡ ስህ፡ ከስድስት፡ መቶ፡ ምዕራፍ።

*ኢሳ፡ ፷፫፡ ፫፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፭፡

፩፡ *ሌላ፡ምልክትም፡ በሰማይ፡አየሁ፡ የበለጠች፡ የተደነቀችም።ሰባት፡መላእክት፡ከርሳቸውም፡ጋራ፡ የኋለኛዪቱ፡ ሰባት፡ መቅሠፍት። በለዚህ፡ የእግዚአብሔር፡ተቀጣ፡ ደፈጸመልና። *ም፡ ፲፪፡ ፭፡ ፫፡፡ *ም፡ ፲፭፡ ፲፷፡፡

፪፡ *አየሁ፡ እንጂ፡ብርጭቀ፡ ባሕርም፡ በእሳት፡ ተቀላቅሎ። አርዌውንም፡ ድል፡ ተየነሡ፡ ምሳሌውንም፡ መልኩንም፡ የስሙንም፡ ቍጥር፡ በብርጭቀ፡ ባሕር፡ ላይ፡ ቁመው። ከርሳቸውም፡ ጋራ፡ የእግዚአብሔር፡**መሰንቆች፡ ነበሩ። *ም፡ ፱፡ ፯፡፡ †ም፡ ፲፫፡ ፲፭፡ ፲፷፡፡ **ም፡ ፭፡ ፮፡፡

፫፡ የእግዚአብሔርንም፡ባርያ፡ *የሙሴን፡ ምስጋን፡ያመሰግናሉ፡†የበጉንም፡ ምስጋን፡ እንጂህ፡ ሲሉ። ስራህ፡ታላቅ፡ናት፡ድንቅም፡ናት፡አምላክ፡ሆይ፡ጌታ፡ ሁሉን፡ የምቲዝ። መንገድህ፡ የቅናች፡ እውነተኛም፡ ናት፡ የቅዱሳን፡ ንጉሥ፡ ሆይ። *ዘፀአ፡ ፲፭፡፭፡ ፲፩፡፡ መዝ፡ ፻፵፭፡ ፲፯፡፡ †ም፡ ፭፡ ፱፡ ፲፪፡፡

፬፡ ማነው፡ የማይፈራህ፡ አቤቱ፡ ስምህንስ፡ የማያመሰግን። አንተ፡ ብቻ፡ ቅዱስ፡ ነህና። *አሕዛብ፡ሁሉ፡መጥተው፡ በፊትህ፡ይሰግዱሥ፡ ፍርድህ፡ ስለ፡ተገለጠ። *መዝ፡ ፹፮፡ ፱፡፡

፭፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ አየሁ፡*እነሆም፡ የደብተራ፡ ስምዕ፡መቅደስ፡በሰማይ፡ተከፈተ። *ም፡ ፲፩፡ ፲፱፡፡

፮፡ ሰባቱ፡መላእክትም፡ሰባት፡መቅሠፍት፡ የያዙት፡ከመቅደስ፡ ወጡ፡ *ነጭ፡ የተልባግር፡ ለብሰው፡ የሚያበራ። በወርቅ፡ መታጠቂያም፡ በደረታቸው፡ ታጥቀው።

ም፡ ፭፡ ፲፫፡፡

፯፡ ካራቱ፡ እንስሶችም፡ *እንጂ፡ ለሰባቱ፡ መላእክት፡ ሰባት፡ የወርቅ፡ጥና፡ሰጠ፡ የዘላለሙን፡ ሕያው፡ የእግዚአብሔርን፡ ተቀጣ፡ የመላች።

*ም፡ ፱፡ ፯፡—፲፡፡ †ም፡ ፲፱፡ ፲፡፡

፰፡ በመቅደሱም፡ ጢስ፡መላበት፡ ከእግዚአብሔር፡ *ክብር፡ የተነሣ፡ ከችሎቱም፡ ማንም፡ወደ፡ መቅደስ፡ደገባ፡ ዘንድ፡ አልቻለም፡ የሰባቱ፡ መላእክት፡ ሰባቲቱ፡ መቅሠፍት፡ አስክትፈጸም፡ ድረስ።

*ዘፀአ፡ ፵፡ ፴፬፡፡ ነገሥ፡ ፰፡ ፲፡፡ ኢሳ፡ ፮፡ ፬፡፡ ሕዝ፡ ፵፬፡ ፬፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፮፡

፩፡ ታላቅ፡ድምጽም፡ከመቅደስ፡ ሰማሁ፡ሰባቱን፡ መላእክት፡ እንጂህ፡ ሲል። ሒዲና፡ የእግዚአብሔርን፡የቍጣውን፡*ጥና፡ በምድር፡ ላይ፡ አፍሱ።

*ም፡ ፲፭፡ ፯፡፡

፪፡ የፊተኛውም፡ ሔደ፡ ጥናውንም ፡ አፈሰሰ፡ በ ምድር፡ላይ።*ክፈም፡ቍስል፡ሆነ፡ርኩስም፡በሰዎች፡ ላይ፡ የአርዌው፡ ምልክት፡ ባለችባቸው፡ ለምሳሌው ም፡በሚሰግዱ። *ዘፀአ፡ ፱፡ ፲፡ ፲፩፡፡

፫፡ ሁለተኛውም፡መልአክ፡ ጥናውን፡አፈሰሰ፡ በባ ሕር፡ላይ፡ ደምም፡ ሆነ፡ እንጂ፡ ሞተ፡ ደም፡ ሕይወት ም፡ያለው፡ነፍስ፡ሁሉ፡በባሕር፡ሞተ። ዘፀአ፡ ፯፡፲፯፡፡

፬፡ ሶስተኛውም፡ መልአክ፡ ጥናውን፡ አፈሰሰ፡ በ ፈሳሽ፡ ውኃ፡ በውኃውም፡ ምንጭ፡ ሁሉ፡ ላይ፡ *ደም ም፡ሁነ። *ዘፀአ፡ ፯፡ ፲፱፡—፳፬፡፡

፭፡ የውኖችንም፡ መልአክ፡ ሲል፡ ሰማሁ። አንተ፡ ጻድቅ፡ነህ፡አቤቱ፡ የምትኖር፡ የነበርህም፡ የምትቀደስም፡ በዚህ፡ ፈርደሃልና።

፮፡ የቅዱሳንንና፡ የነቢያትን፡ ደም፡ አፈሰሰዋልና፡ ደምንም፡ሰጠሳቸው፡ደጠጡ፡ ዘንድ፡ይገባቸዋልና።

፯፡ ሌላውንም፡*ከመሠዊያው፡ ሰማሁ፡እንጂህ፡ ሲል። አዎን፡አቤቱ፡አምላክ፡ሆይ፡ሁሉን፡ የምቲዝ። ፍርድህ፡ †እውነትና፡ ቅን፡ ናት። *ም፡ ፱፡ ፲፫፡፡ †ም፡ ፲፱፡ ፱፡፡

፰፡ አራተኛውም፡ መልአክ፡ ጥናውን፡ አፈሰሰ፡ በ ጸሓይ፡ ላይ። ሰውንም፡ በሳት፡ ታቃጥል፡ ዘንድ፡ ተሰጣት።

፱፡ ሰዎችም፡ ታላቅ፡ መቃጠል፡ ተቃጠሉ፡ በዚህ፡ መቅሠፍትም፡ ሥልጣን፡ ያለውን፡ የእግዚአብሔርን፡ስም፡*ሰደቡ፡ ንስሐም፡ †አልገቡም፡ ምስጋን፡ ለር ሱ፡ደሰጡ፡ዘንድ። *ቍ፡ ፶፭፡፡ †ም፡ ፱፡ ፲፡ ፲፭፡፡

፲፡ አምስተኛውም፡ መልአክ፡ ጥናውን፡ አፈሰሰ፡ በአርዌው፡ ዙፋን፡ ላይ ፡ መንግሥትም፡ *ጨለመች፡ መላሳቸውንም ፡ ቀረጠሙ፡ ከማመመሙ ፡ የተነሣ።

*ዘፀአ፡ ፲፡ ፲፭፡፡ ኢሳ፡ ፲፡ ፲፭፡ ፲፪፡፡

፲፩፡ የሰማይንም፡ አምላክ፡ ሰደቡ፡ ከመታመማቸው፡ የተነሣ፡ከቍስላቸውም፡ከስራቸውም፡ *አልተመለሱም።

*ም፡ ፱፡ ፲፡፡

፲፪፡ ስድስተኛውም፡መልአክ፡ ጥናውን፡ አፈሰሰ፡ በታላቁ፡በኤፍራጥስ፡ ወንዝ፡ ላይ፡ *ውኃውም፡ደረቀ፡ መንገድ፡ ደጸረግላቸው፡ ዘንድ፡ ከጸሓይ፡ መውጫ፡ላሉት፡ነገሥታት። *ኢሳ፡ ፲፩፡ ፲፭፡ ፲፯፡፡

፲፫፡ *ከዘንዶውም፡ አፍ፡ †ከአርዌውም፡ አፍ፡ **ካሰተኛውም፡ ነቢያ፡ አፍ፡ ሶስት፡ **ርኩሳን፡ መ

ናፍሰት፡ ሲወጡ፡ አየሁ፡ እንቧጉሮር፡ የሚመስሉ።
*ም፡ ፲፪፡ ፲፡፡ ተም፡ ፲፫፡ ፭፡፡ **ም፡ ፲፫፡ ፲፭፡፡
††ዘፀአ፡ ፳፡ ፯፡ ፫፡ ፭፡ ነገሥ፡ ፷፪፡ ፷፭፡፡
፲፱፡ የሰይጣናት፡ መናፍስት፡ ናቸውና፡ *ተአምራት፡ የሚያደርጉ፡ በምድር፡ ነገሥታት፡ ያልፈ፡ ዘንድ፡ በዓለምም፡ ሁሉ፡ ይሰበስብዋቸው፡ ዘንድ፡ ወደዚያ፡ ወደ፡ ታላቁ፡ ቀን፡ ሰልፍ፡ ሁሉን፡ የሚደዝ፡ ††የእግዚአብሔር፡ ቀን።
*ም፡ ፲፫፡ ፲፫፡፡ ተም፡ ፲፱፡ ፲፱፡፡
፲፭፡ እነሆ፡ እኔ፡ እንደ፡ሌባ፡ *እመጣለሁ። የሚተ ጋ፡ብፁዕ፡ነው፡ ልብሱንም፡ የሚጠብቅ፡ †ራቁቱን፡ እንደ፡ሔድ፡ ኃፍረቱንም፡ እንደ፡ያዩ።
*፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፪፡፡ ተም፡ ፫፡ ፲፮፡፡
፲፯፡ በዕብራይስጥ፡ ቋንቋ፡ *አርማጌዶን፡ ወደሚ ባል፡ ስፍራም፡ ሰበሰባቸው።
*መሳ፡ ፭፡ ፲፱፡ ፴፭፡፡
፪፡ ነገሥ፡ ፱፡ ፷፯፡፡ ና፡ ፷፫፡ ፷፱፡፡ ዘካ፡ ፲፪፡ ፲፩፡፡
፲፯፡ ሰባተኛውም፡ መልአክ፡ጥናውን፡ አፈሰሰ፡ በ አየር፡ ላይ፡ ታላቅ፡ ድምጽም፡ ከሰማያዊ፡ መቅደስ፡ ወጣ፡ ከዙፋኑ፡ እንደሆ፡ ሲል። ፈጽሞ፡ ሆነ።
፲፰፡ ድምጽም፡ ነጐድጓድም፡ መብረቅም፡ ሆነ፡ ታላቅ፡ መናወጥም፡ ነበረ። ሰውም፡ በምድር፡ ላይ፡ ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡ መናወጥ፡ አልሆነም፡ እንደሆ፡ ታ ላቅ፡ እንደርሱ።
ም፡ ፱፡ ፭፡፡ ና፡ ፮፡ ፭፡ ፲፩፡ ፲፱፡፡
፲፱፡ ታላቂቱም፡ *አገር፡ ለሶስት፡ክፍል፡ ሆነች፡ የአ ሕዛብም፡ ከተሞች፡ ወደቁ፡ ታላቂቱም፡ ባቢሎን፡ በ እግዚአብሔር፡ ፊት፡ ታሰበች፡ የመቅሠፈቱን፡ ቍ ጣ፡ ወደን፡ †ጽ ፡ይሰጣት፡ ዘንድ።
*ም፡ ፲፩፡ ፮፡፡ ተም፡ ፲፱፡ ፲፡፡
፳፡ ደሴትም፡ ሁሉ፡ ሸሸች፡ ተራሮችም፡ አልተገኙ ም።
ም፡ ፮፡ ፲፱፡፡ ና፡ ፮፡ ፲፩፡፡
፷፩፡ ታላቅ፡ *በረዶም፡ እንደ፡ ሚዛን፡ አዋቂ፡ያለ፡ ከሰማይ፡ ወረደ፡ በሰዎች፡ ላይ። ሰውም፡ እግዚአብ ሔርን፡ ††ሰደበ፡ ከበረደው፡ መቅሠፈት፡ የተነሣ፡ መ ቅሠፈቱ፡ እጅግ፡ ታላቅ፡ ነበረና።
*ዘፀአ፡ ፱፡ ፮፫፡፡ ††ቍ፡ ፱፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፯፡

፩፡ ከሰባቱም፡ መላእክት፡ ሰባት፡ ጥና፡ ይዘው፡ ከ ነበረት፡ አንዱ፡ መጣ፡ ከኔ፡ ጋራም፡ ተናገረ፡ እንደሆ፡ ሲለኝ። ና፡ የታላቂቱን፡ ጋለሞታ፡ ኩነኔ፡ አሳይሆ፡ በብ ዙ፡ ውኆች፡ ላይ፡ የተቀመጠችውን።
ም፡ ፲፭፡ ፩፡፡
፪፡ ከርስዋ፡ ጋራ፡ ያመነዘረ፡ የምድር፡ ነገሥታት፡ በ ምድርም፡ የሚኖሩ፡ ከወንዝነርዋ፡ ወይን፡ *የሰከረ።
*ም፡ ፲፱፡ ፷፡፡ ኤር፡ ፶፩፡ ፯፡፡
፫፡ በመንፈስም፡ ወደ፡ ምድረ፡ በደ፡ ወሰኝ፡ ሔደ፡ ሴትም፡ አየሁ፡ በቀይ፡አርዌ፡ ተቀምጣ፡ የስድብ፡ ስ ም፡ በመላበት። ለርሱም፡ *ሰባት፡ ራስ፡አሥር፡ቀንደ ኞም፡ አሉት።
*ም፡ ፲፫፡ ፭፡፡
፬፡ *ሴቲቱም፡ በቀይ፡ ሐርና፡ በነጭ፡ ሐር፡ ተጐናጽ ፈ፡ ነበረች፡ በወርቅና፡ በዕንቍ፡ በከበረም፡ ደንጊያ፡ በተሰራ። በጅዋም፡ የወርቅ፡ *ጽዋ፡ ይዘ፡ ነበረች፡ አ ድፋ፡ የዓመንዝርዋም፡ ርኵሰት፡ የመላበት።
*ሕዝ፡ ፳፫፡ ፲፫፡ ፲፯፡፡ ††ኤር፡ ፶፩፡ ፯፡፡
፭፡ በግምባርዋም፡ ስም፡ ተጽፈዋል። *ምሥጢ ር። †ታላቂቱ፡ ባቢሎን። የጋለሞቶች፡ እናት፡ የምድ ርም፡ርኩሰት፡ሁሉ።
*፪፡ ተሰ፡ ፪፡ ፯፡፡ †ራእ፡ ፲፱፡ ፳፡፡
፮፡ ና፡ ፲፯፡ ፲፱፡፡ ደን፡ ፱፡ ፳፯፡፡
፮፡ ሴቲቱንም፡ ሰክራ፡ አየሁ፡ ከቅዱሳን፡ደም፡ ከ የሱሰም፡ ሰማዕታት፡ደም። ባየኋትም፡ ጊዜ፡ ታላቅ፡ ድንቅ፡ ተደነቅሁ።
ም፡ ፲፰፡ ፶፱፡፡
፯፡ መልአኩም፡አለኝ። ለመን፡ ትደነቃለህ። እኔ፡ የሴቲቱን፡ ምሥጢር፡ እነግርሃለሁ፡ የተሸከማትን ም፡አርዌ፡ ሰባት፡ ራስ፡ አሥር፡ቀንዷቸው፡ ያሉትን።
፰፡ ያየኸው፡ አርዌ፡ አርሱ፡ *ነበረ፡ አርሱም፡ተአ ደደለም፡ ከቀላይም፡ ይወጣ፡ ዘንድ፡ ጊዜ፡ አለው፡ ወደ፡ ጥፋትም፡ ይሔድ፡ ዘንድ። በምድር፡ የሚያረ ም፡ ይደነቃሉ፡ ሰማቸው፡ †በሕይወት፡ መጽሐፍ፡ ያ ልተጻፈ፡ ዓለም፡ ሳይፈጠር። አርዌውን፡ አይተው፡ የነበረውን፡ ያይደለውንም፡ ምንስ፡ አርሱ፡ ቢሆን።
*ም፡ ፲፫፡ ፭፡ ፰፡፡ ተም፡ ፲፫፡ ፫፡፡ **ም፡ ፫፡ ፭፡፡
፱፡ ከዚህ፡ *ጥበብ፡ ያለው፡ አእምሮ፡ አለ። †ሰባ ቱ፡ ራሶች፡ ሰባት፡ ተራሮች፡ ናቸው፡ ሴቲቱ፡ ተቀምጣ ባቸው፡ ያሉኞ።
*ም፡ ፲፫፡ ፶፡፡ †ም፡ ፲፫፡ ፭፡፡
፲፡ አርሳቸውም፡ ሰባት፡ ነገሥታት፡ ናቸው። አም ስቱ፡ወደቁ፡አንዷም፡አለ። ሌላውም፡ገና፡አልመጣ ም። ቢመጣም፡ ጥቂት፡ ይቀመጥ፡ ዘንድ፡ይገባዋል።
፲፩፡ የነበረውም፡ አርዌ፡ አርሱም፡ያይደለውም። አርሱ፡ ስምንተኛ፡ ነው፡ ከሰባቱም፡ ነው፡ ወደ፡ *ጥፋ ትም፡ ይሔዷል።
*ቍ፡ ፶፡፡ ም፡ ፲፬፡ ፳፡፡
፲፪፡ *አሥሩም፡ ቀንዷች፡ ያየሃቸው፡ አርሳቸው፡ አሥር፡ ነገሥታት፡ ናቸው፡ ገና፡ መንግሥት፡ ያልወሰ ዷ። ነገር፡ግን፡ሠልጣን፡ ይወስዷሉ፡እንደ፡ነገሥታት፡ አንዷት፡ ሰዓት፡ ከአርዌው፡ ጋራ።
*ም፡ ፲፫፡ ፭፡፡
ደን፡ ፯፡ ፳፡ ፳፱፡፡
፲፫፡ ለለዚህ፡ አንድ፡ ምክር፡ አላቸው፡ ኃይላቸው ንም፡ ሥልጣናቸውንም፡ የአርዌው፡ ይሰጣሉ።
፲፬፡ አሌህ፡ ከበጉ፡ ጋራ፡ ይዋጋሉ፡ በጉም፡ ያሸንፋ ቸዋል፡ *የጌቶች፡ ጌታ፡ ነውና፡ የነገሥታትም፡ ንጉሥ፡ ከርሱም፡ ጋራ፡ ያሉት፡ †የተጸሩ፡ ናቸው፡ የተመረጡ ም፡ያመኑም።
*ም፡ ፲፱፡ ፲፯፡፡ †ም፡ ፲፱፡ ፲፱፡፡
፲፭፡ አለኝም፡ ገለሞቱ፡ተቀምጣባቸው፡ ያየሃቸ ው፡ *ውኖች፡ ፣ሕዝብና፡ አሕዛብ፡ ናቸው፡ ወገኖች ም፡ ቋንቀቸውም።
*ቍ፡ ፭፡፡ †ኢሳ፡ ፰፡ ፯፡፡
ኤር፡ ፶፯፡ ፱፡፡
፲፯፡ አሠረም፡ ቀንዷች፡ በአርዌው፡ ላይ፡ ያየሃቸ ው፡ አርሳቸው፡ ገለሞቱን፡ *ይጸላሉ፡ ፈቅም፡ራቁት ዋንም፡ የሚያደርጊት፡ ጊዜ፡ አላቸው፡ ሥጋዋንም፡ ይበልዋታል፡ †በእሳትም፡ ያቃጥልዋታል።
*ቍ፡ ፲፩፡ ፲፫፡፡ †ም፡ ፲፰፡ ፰፡፡

፲፯፡ እግዚአብሔር፡ በልባቸው፡ አድርጓልና፡ ምክሬን፡ ያደርጉ፡ ዘንድ፡ አንድ፡ ምክርም፡ ያደርጋሉ፡ መንግሥታቸውንም፡ ለአራዊቱ፡ ይሰጣሉ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ። ም፡ ፲፡ ፮፡፡

፲፰፡ ያየሳትም፡ ሴት፡ አርሰዋ፡ *ታላቂቱ፡ አገር፡ ናት፡ መንግሥት፡ ያላት፡ በምድር፡ ነገሥታት፡ ላይ።

*ም፡ ፲፰፡ ፲፡፡

ምዕራፍ፡ ፲፰፡

፩፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ሌላ፡ መልአክ፡ አየሁ፡ ከሰማይ፡ *ሲወርድ፡ ለርሱም፡ ታላቅ፡ ሥልጣን፡ አለው፡ ተምድርም፡ አበራት፡ ከብርሃኑ፡ የተነሣ።

*ም፡ ፲፡ ፭፡፡ †ሕዝ፡ ፵፫፡፡

፪፡አበርትተም፡ሥኽ፡በታላቅ፡ቃል፡እንደሀ፡ሲል።
*ወደቀች፡ ወደቀች፡ ታላቂቱ፡ ባቢሎን፡ ለሰይጣናት፡ ም፡ ተማደርያ፡ ሆነች። ለርኩስ፡ መንፈስ፡ ሁሉም፡ መጠበቂያ፡ ሆነች፡ ርኩስ፡ ወፍም፡ ሁሉ፡ የተጸላም፡ የሚያድርባት፡ ሆነች። *ም፡ ፲፰፡ ፳፡፡ ኢሳ፡ ፳፩፡ ፱፡፡ ኤር፡ ፶፩፡ ፰፡፡ †ኢሳ፡ ፲፫፡ ፳፩፡፡ ና፡ ፴፱፡ ፲፩፡ ፲፫፡፡ ኤር፡ ፶፡ ፫፡ ፴፱፡ ፵፡፡

፫፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ከምንዝርዋ፡ ቍጣ፡ *ወይን፡ ጠጥተዋልና፡ የምድርም፡ ነገሥታት፡ ከርስዋ፡ ጋራ፡ አመነዘረ፡ የምድርም፡ ነጋዶች፡ ከተድላዋ፡ ብዛት፡ ባለጠጎች፡ ሆኑ። *ኤር፡ ፶፩፡፮፡፡ ናሆ፡ ፫፡ ፬፡፡

፬፡ ሌላ፡ ቃልም፡ ሰማሁ፡ ከሰማይ፡ እንደሀ፡ሲል። ከርስዋ፡ *ውጡ፡ ወገኖቼ፡ ሆይ፡ በኃጢአትዋ፡ እንደ ትገኙ፡ ከመቅሠፍትዋም፡ እንደትወሰዱ።

*ኢሳ፡ ፵፰፡ ፳፡፡ ና፡ ፶፱፡ ፲፩፡፡ ኤር፡ ፶፡ ፰፡፡ ና፡ ፶፩፡ ፮፡ ፵፭፡፡

፭፡ ኃጢአትዋ፡ እስከ፡ *ሰማይ፡ ተከትልዋታልና፡ እግዚአብሔርም፡ ግፍዋን፡ አሰበው።

*ዘፍጥ፡ ፲፰፡ ፳፡፡ ኤር፡ ፶፩፡ ፱፡፡

፮፡ *ተበቀልዋት፡ እርስዋ፡ ደግሞ፡ እንደ፡ ተበቀለ ቻችሁ፡ ደግማችሁም፡ ጨምሩላት፡ እንደ፡ሰራዋ። በ መላችው፡ጽዋ፡ አላጎትም፡ አብልጣችሁ፡ምሉላት።

*መዝ፡ ፻፴፯፡ ፰፡፡ ኤር፡ ፶፡ ፲፭፡ ፵፱፡፡

፯፡ ራስዋን፡ *እንደከበረች፡ ደስም፡ እንደሳት፡ በዚያ፡ ልክ፡ ሥቃይ፡ ልቅሶም፡ ስጥዋት። በልብዋ፡ ትላለችኖ። †ንግሥት፡ ሁኜ፡ እቀመጣለሁ፡ ድኃም፡ አል ሆንም፡ ልቅሶም፡ አላይም።

*ኤር፡ ፶፡ ፵፱፡፡

†ኢሳ፡ ፵፯፡ ፯፡ ፰፡፡

፰፡ ስለዚህም፡ *ባንድ፡ ቀን፡ መቅሠፍትዋ፡ ይመጣል፡ ሞት፡ ልቅሶም፡ ራብም፡ ተበእሳትም፡ ትቃጠላለች። እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ የሚፈርድባት፡ ብርቱ፡ ነውና።

*ኢሳ፡ ፵፯፡ ፱፡፡ ኤር፡ ፶፡ ፴፭፡፡

†ራእ፡ ፲፯፡ ፲፯፡፡

፱፡ የምድርም፡ ነገሥታት፡ ያለቅሱላታልና፡ ወይ፡ ደሉለታል፡ ከርስዋ፡ ጋራ፡ *ያመነዘረ፡ ደስታም፡ ያደረጉ፡ የመቃጠልዋን፡ ጢስ፡ ባዩ፡ ጊዜ። *ም፡ ፲፯፡ ፱፡፡

፲፡ ከሥቃይዋ፡ ፍርሃት፡ የተነሣ፡ በረቅ፡ ቁመው፡ እንደሀ፡ ሲሉ። *ወዮላት፡ ወዮላት፡ ለታላቂቱ፡ አገር፡ ለባቢሎን፡ ለብርቱዪቱ፡ አገር፡ ባንድ፡ት፡ሰዓት፡ ኩነኔሽ፡ መጥትዋልና። *ም፡ ፲፱፡ ፫፡፡ ኢሳ፡ ፵፯፡ ፱፡፡ ኤር፡ ፶፩፡ ፰፡፡

፲፩፡ የምድርም፡ ነጋደች፡ ሰለርስዋ፡ ያለቅሳሉና፡ ወደ፡ ደላሉ፡ ሸያጫትዋን፡ ከዚያ፡ ወዲያ፡ የሚገዛት፡ የለምና። ቍ፡ ፲፰፡፡ ሕዝ፡ ፳፯፡ ፴፮፡፡

፲፪፡ የወርቅ፡ አቃ፡ የብርም፡ የዕንቍም፡ የሉልም፡ የቢሰም፡ ቀይ፡ ሐርም፡ ነጭ፡ ሐርም፡ ብጫ፡ ሐርም፡ የሽቱ፡ እንጨትም፡ ሁሉ፡ የዝሆን፡ ጥርስም፡ አቃ፡ ሁሉ፡ የከበረም፡ እንጨት፡ሁሉ፡ ናስም፡ ብረትም፡እብነ፡ በርድም። ሕዝ፡ ፳፯፡ ፲፪፡ ፲፫፡ ፳፪፡፡

፲፫፡ቀረፋም፡ዕጣንም፡ቅቤንም፡ምስክም፡የወይን፡ ጸጅም፡ ዘይትም። የከበረም፡ ደቂት፡ ሰንጂም፡ ላምም፡ በግም፡ ፈረስም፡ መንኰራኵርም፡ ባሮች ም፡ የሰው፡ ነፍሳትም።

፲፬፡ የነፍስሽም፡ ፈቃድ፡ ፍረ፡ ካንች፡ ተቍረጠ። ያመረም፡ የተወደደም፡ ሁሉ፡ካንች፡ ጠፋ። እንጊዲህም፡ አታገኟውም።

፲፭፡ የዚህ፡ ሁሉ፡ ነጋደች፡ከርስዋ፡ የከበረ፡ርቀው፡ ደቀማሉ፡ ሰለ፡ ሥቃይዋ፡ ፍርሃት፡ ኢያለቀሱና፡ ውይ፡ ኢያሉ፡ እንደሀም፡ ኢያሉ።

ሕዝ፡ ፳፯፡ ፳፯፡ ወ፡ ፴፮፡፡

፲፮፡ ወዮ፡ ወዮ፡ ለታላቂቱ፡ አገር፡ በብጫ፡ ሐር፡ የ ምትጐናጸፍ፡ በቀይ፡ ሐርም፡ በነጭ፡ ሐርም። በወር ቅም፡የተለቀለቀች፡ *በዕንቍም፡በሉልም። ተባንጂ ት፡ ሰዓት፡ ደሀ፡ ታላቅ፡ ባለጠግነት፡ ጠፋትዋልና።

*ም፡ ፲፯፡ ፬፡፡ †ኢሳ፡ ፳፫፡ ፲፬፡፡

፲፯፡ የመርከቡ፡ *መሪም፡ ሁሉ፡ *በመርከብም፡ የሚሔድ፡ ሰዉች፡ ሁሉ፡ መርከበኞችም፡ በባሕርም፡ የሚዘረፉ፡ ሁሉ፡ በረቅ፡ ቀሙ።

*ሕዝ፡ ፳፯ ፳፯፡—፴፭፡፡

፲፰፡ የመቃጠልዋንም፡ ጢስ፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ ሙሁ፡ እንደሀ፡ ሲሉ። ምን፡ አገር፡ ደሀቺን፡ ታላቅ፡ አገር፡ ደመ ሰላታል። ኢሳ፡ ፴፱፡ ፲፡፡

፲፱፡ በራሳቸውም፡ላደ፡ *አፈር፡ነሰነሱ፡ ኢያዘኑና፡ ኢያለቀሱ፡ ሙሁ፡ እንደሀ፡ ሲሉ። ወዮ፡ ወዮ፡ ለታላቂቱ፡ አገር፡ መርከብ፡ በባሕር፡ ያላቸው፡ ሁሉ፡ከክብርዋ፡ የከበረባት። ባንጂት፡ ሰዓት፡ ተፈትታለችና።

*ሕዝ፡ ፳፯፡ ፴፡ ፴፡፡

፳፡ ሰማይ፡ ሆይ፡ *ደስ፡ ይበልሽ፡ አላንትም፡ ቅዱሳን፡ ሆይ፡ ሐዋርያት፡ነቢያትም፡ እግዚአብሔር፡ፍርድችሁን፡ በርስዋ፡ ላይ፡ ፈርዷላችኋልና።

*ኢሳ፡ ፵፱፡ ፲፫፡፡ ኤር፡ ፶፩፡ ፵፰፡፡

፳፩፡ ብርቱ፡ መልአክም፡ *ደንጊያ፡ አነሣ፡ እንደ፡ ታላቅ፡ወፍጮ፡ያለ፡ በባሕርም፡ ጣለው፡ እንደሀ፡ ሲል። እንደሀ፡ ተገፍታ፡ትወድቃለች፡ ታላቂቱ፡ አገር፡ ባቢሎን፡ደግማም፡አትገኝም። *ኤር፡ ፶፩፡ ፷፫፡፮፱፡፡

፲፱፡ *መሰንቆ፡የሚመቱም፡ድምጽ፡ያዝማሮች ም፡ መለከትም፡ የሚነፉ፡ ዝማሪም፡ የሚዘምሩ፡ እንኒ፲ህ፡ አይሰማብሽም። ሰራን፡ ሁሉ፡ የሚሰራ ም፡እንኒ፲ህ፡ አይነኝብሽም። የወፈጨም፡ድምጽ፡ እንኒ፲ህ፡ አይሰማብሽም። *ኢሳ፡ ፮፱፡ ፮። ሕዝ፡ ፮፯፡ ፲፫። ፲፫፡ የመብራትም፡ ብርሃን፡ እንኒ፲ህ፡አይበራብ ሽም። የሙሽራ፡ *የሙሽራዪቱም፡ ድምጽ፡ እንኒ ፲ህ፡አይሰማብሽም። ፣ነጋጆችሽ፡የም፡ድር፡ታላቅች፡ ነበረ፡ን። ባሰማትሽ፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ስተዋልና። *ኤር፡ ፶፡ ፴፱። ና፡ ፲፯፡ ፱። ና፡ ፺፭፡ ፲። †ኢሳ፡ ፮፫፡ ፮። ፺፱፡ አርሰዋም፡ ተገኘ፡ የነቢያትና፡ የቅዺሳን፡ *ደ ም፡ በም፡ድር፡ ላይም፡ ተዋግተው፡ የሞቱ፡ ሁሉ። *ም፡ ፯፡ ፲። ም፡ ፲፯። ፯። ና፡ ፲፱፡ ፰። ማቴ፡ ፮፫፡ ፴፭፡ ፴፯። ም፡ዕራፊ፡ ፲፱፡ ፭፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ታላቅ፡ *ድምጽ፡ ሰማሁ፡የብ ዙ፡ ጉባዔ፡ በሰማይ፡ የሚል። ሃሌሉ፫። መድኃኒት፡ ምስጋናም፡ ክብርም፡ ኃይልም፡ ለእግዚአብሔር፡ ላ ም፡ለላችን። *ም፡ ፲፩፡ ፲፭። ፱፡ ፍርዲ፡ *እውነት፡ ቅንም፡ ነውና። ምድርን፡ በ ምንዝርዋ፡ ባጠፋች፡ በታላቂቱ፡ ጋለሞታ፡ ላይ፡ ፍር ድዋልና። ለባሮቹም፡ተደም፡ ከጅዋ፡ተበቀለ። *ም፡ ፲፯፡ ፯። ተም፡ ፯፡ ፲። ዘያግ፡ ፴፱፡ ፵፫። ፫፡ ሁለተኛም፡ አሉ። ሃሌሉያ። *ጢሰዋም፡ ለዘላ ለም፡ ይወጣል። *ኢሳ፡ ፴፱፡ ፲። ፱፡ ህያ፡ አራቱም፡ ሸማግሌች፡ አራቱም፡ እንሰ ሶች፡ ወደቁ፡በዙፋኑ፡ላይም፡ለተቀመጠው፡ለእግዚ አብሔር፡ ሰገዱ። እንኒህ፡ሲሉ። *አሜን። ሃሌሉያ። *ም፡ ፭፡ ፲፱። መዝ፡ ፻፯፡ ፶፳። ፭፡ ከዙፋኑም፡ ድምጽ፡ ወጣ፡ እንኒህ፡ ሲል። አ ምላካችነን፡ አመሰግኑ፡ አላንት፡ባሮች፡ ሁላችሁ። አ ርሱንም፡ የምትፈሩ፡ ታናናሾችም፡ ታላላቆችም። ፮፡ እንኒ፡ ብዙ፡ ጉባዔም፡ ድምጽ፡ሰማሁ፡ እንኒ፡ ብዙም፡ ውኖች፡ እንኒ፡ ብርቱም፡ ነጐድጓድ፡ ድም ጽ፡ ሲሉ። ሃሌሉያ። ሁሉን፡ የሚይዝ፡ እግዚአብሔ ር፡ አምላካችን፡ ነግሥዋልና። ም፡ ፲፩፡ ፲፭፡ ፲፯። ፯፡ *ደስ፡ ይበለን፡ በብዙ፡ ደስታ፡ ምስጋናም፡እንሰ ጠው። የበጉ፡ ተሰርግ፡ ደርሰዋልና፡ ምሽቱም፡ ራስዋ ን፡ አዘጋጅታለች። *መዝ፡ ፻፲፰፡ ፲፱። ተም፡ ፶፭፡ ፱። ፲፡ ቢሰም፡ *ትለብስ፡ ዘንድ፡ተሰጣት፡የጸራ፡የሚ ያበራም። ይህም፡ ቢስ፡ የቅዺሳን፡ ንጽሕና፡ ነው። *መዝ፡ ፵፭፡ ፲፱፡ ፲፭። ኢሳ፡ ፷፭፡ ፲። ፱፡ አለኝም። ጻፏ። *ብፁአን፡ ናቸው፡ ወደ፡ በጉ፡ ሰርግ፡ ምሳ፡ የተጸረ። አለኝም፡ ደህ፡ የእግዚአብሔ ር፡የእውነት፡ነገር፡ነው። *ሉቃ፡ ፲፱፡ ፲፭። ፲፡ በግሩ፡ ፊትም፡ *ወደቅሁ፡ እሰግድላት፡ ዘንድ። አለኝም። እደ፡ አታድርገው። እኔ፡ እንኒንተ፡ አገል ጋይ፡ ነኝ፡ የየሱስንም፡ ተመስክር፡ እንደ፡ ያዙ፡ እንደ፡ ወንድሞችህ፡ ነኝ። ለእግዚአብሔር፡ ስገድ። የየሱ ስ፡ ምስክር፡ የትንቢት፡ መንፈስ፡ ናትና። *ም፡ ፷፪፡ ፷። የሐዋ፡ ፲፡ ፶፭፡ ፷፯። ተም፡ ፲፪፡ ፲፯። ፲፭፡ ሰማያንም፡ተከፈታ፡አየሁ። እነሆም፡ *አም በላይ፡ ፈረስ። በርሱም፡ የተቀመጠ፡ ተየታመነ፡እው ነተኛም፡ ደባላል። በጽድቅም፡ **ይፈርደል፡ ይጸላ ማል። *ም፡ ፯፡ ፪። ተም፡ ፭፡ ፭። ና፡ ፫፡ ፲፱። **ኢሳ፡ ፲፭፡ ፱፡ ፭። ፲፪፡ *ዓይናቸም፡ እንደ፡ እሳት፡ ነበልባል፡ ናቸው። በራሱ፡ ላይም፡ ብዙ፡ አክሊሎች፡ ነበረ። የተጻፈም፡ ተስም፡ ነበረው፡ ማንም፡ የማያውቀው፡ ከርሱ፡ በ ቀር። *ም፡ ፭፡ ፲፱። ና፡ ፱፡ ፲፮። ተም፡ ፫፡ ፲፪። ፲፫፡ በደም፡ የታለለም፡ *ልብስ፡ ተጐናጽፎ፡ ነበር። ተስሙም፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ይባላል። *ኢሳ፡ ፮፫፡ ፭። †ዮሐ፡ ፭፡ ፭። ፲፱፡ በሰማይም፡ያሉ፡*ጭፍሮች፡ደከተሉት፡ነበረ፡ ባም፡በላይ፡ ፈረስ፡ ተቀምጠው፡ የነጻ፡ የጸራም፡ልብ ስ፡ ለብሰው። *ም፡ ፲፯፡ ፲፱። ፲፭፡ ካፈም፡ የተሳለ፡ሰይፍ፡ይወጣል፡ አሕዛብን፡ ይመታበት፡ ዘንድ። እርሱም፡ ያሰማራቸዋል፡ *በብ ረት፡ በትር። እርሱም፡ ሁሉን፡ የሚይዝ፡የእግዚአብ ሔርን፡ የመቅሠፈቱን፡ የቍጣውንም፡ ወይን፡ መጥ መቂያ፡ ተደረግላል። *ም፡ ፲፱፡፭፡፡መዝ፡፰፡፱፣—፲፱፡፡ ተም፡ ፲፱፡ ፲፱፡ ፷፡፡ ኢሳ፡ ፮፫፡ ፫፡፡ ፲፯፡ በልብሱም፡ በጭኑም፡ የተጻፈ፡ ስም፡ ነበረ ት። †የነገሥታት፡ ንጉሥ፡ የጌቶችም፡ ጌታ። *ም፡ ፲፯፡ ፲፱። ፭፡ ጢሞ፡ ፮፡ ፲፭። ፲፯፡ አንድ፡ መልአክም፡ በጸሐይ፡ ቁሞ፡ አየሁ፡ በ ታላቅ፡ ቃልም፡ ጮኸ፡ እንደህ፡ ሲል፡ በሰማይ፡ መካ ከል፡ ለሚበረ፡ ወፎች፡ *ኑ፡ ወደ፡ ታላቁ፡ ወደ፡ እግዚ አብሔር፡ ምሳ፡ ተከማቹ። *ሕዝ፡ ፴፱፡ ፬፡ ፲፯። ፲፰፡ የነገሥታትን፡ሥጋ፡ ትበሉ፡ዘንድ። የአምበሎ ችንም፡ ሥጋ። የኃያላኑንም፡ ሥጋ። የፈረሶችንም፡ ሥጋ፡ በላያውቸም፡ የተቀመጡባቸውን። የሰው፡ ል ጆችንም፡ ሁሉ፡ ሥጋ፡ የባሮችንም፡የታናናሾችንም፡የታ ላቆችንም። ፲፱፡ አርዊውንም፡*የም፡ድርንም፡ ነገሥታት፡ ጭፍ ሮቻቸውንም፡ተከማችተው፡አየሁ፡ከሰልፈ፡ያደርጉ፡ ዘንድ፡ በፈረስ፡ ከተቀመጠው፡ ጋራ፡ ከጭፍሮቹም፡ ጋራ። *ም፡ ፲፯፡ ፲፪፡—፲፱። ተም፡ ፲፯፡ ፲፱፡ ፲፯። ፳፡ *አርዊውም፡ ተያዘ፡ ከርሱም፡ ጋራ፡ አሰተኛ ው፡ ነቢ፡ በፊቱ፡ ተተአምራት፡ ያደረገው። የአርዊ ውን፡ምሳሌ፡ የወሰደ፯፡ያሳተባት፡ለመልኩም፡ የሰ ገደ፯። እሌህ፡ ሁለቱ፡ በሕይወታቸው፡ በደ፯፡ በም ትቃጠል። **በእሳት፡ ፈሳሽ፡ ወንዝ፡ ተጣሉ። *ም፡ ፲፫፡ ፭፡ ፲፭። ተም፡ ፲፫፡ ፲፭፡—፲፱። **ም፡ ፶፡ ፲። ደን፡ ፭፡ ፲፭፡ ፶፯።

፲፭፡ የቀረትም፡ ተገደሉ፡ በፈረስ፡ ላይ፡ በተቀመጠው፡ ሰይፍ፡ ካፈ፡ በሚወጣው፡ ፊፏም፡ ሁሉ፡ ሥጋ ቸውን፡ አገበ።

ምዕራፍ፡ ፳፩

፩፡ መልአክም፡ ከሰማይ፡ ሲወርድ፡ አየሁ፡ ከርሱ ም፡ገራ፡ የቀላይ፡ *መክፈቻ፡ ነበር፡ ታላቅም፡ ሰንሰለ ት፡ተ፬ጀ፡ነበር።። *ም፡ ፬፡ ፭፡፡ ተ፪፡ጰዋ፡ ፪፡ ፬፡፡ ይሁያ፡ ቀ፡ ፯፡፡

፪፡ ዘንደውንም፡*ያዘው፡ ያን፡ የቀደመውን፡ አባ ብ። እርሱም፡ ደ.ያብሉስ፡ ሰይጣንም፡ ሸህ፡ አመት ም፡አሠረው።። *ም፡ ፲፪፡ ፬፡፡

፫፡ በጠለቀም፡ ጕድጓድ፡ አያረው፡ ቍለፈውም፡ አተመበትም፡ ደግሞ፡ አሕዛብን፡ *እንደያስት፡ ሸህ ው፡አመት፡አስኪፈጸም፡ ድረስ፡ከዚያ፡ በኃላም፡ ጥ ቂት፡ወራት፡ደፈታ፡ዘንድ፡ደገባል።። *፪፡ተሰ፡ ፪፡ ፬፡፲፡፡

፬፡ *ዙፈያችም፡ አየሁ። በርሳቸውም፡ ተቀመጡ ባቸው፡ ፍርድም፡ ተሰጣቸው። ሰለ፡ የሱስ፡ ምስክር ም፡ የሞቱትን፡ ነፍሳት፡ አየሁ፡ ሰለ፡ እግዚአብሔር ም፡ቃል፡ ለአርዌውም፡ ያልሰገዱ፡ ለመልኩም፡ ጽፈ ቱንም፡ ያልወሰዱ፡ በግምባራቸው፡ በጀቸውም። በ ሕይወትም፡ ተቀመጡ፡ ከክርስቶስ፡ ጋራም፡ ነገሡ፡ ሸህ፡አመት።። *ያን፡ ፯፡ ፬፡ ፳፪፡ ፳፯፡፡

ሉቃ፡ ፳፪፡ ፴፡፡ ፭፡ ቀር፡ ፯፡ ፪፡፡

፭፡ የቀረት፡ሙታን፡ ግን፡አልደኑም፡ ሸህው፡አመት፡አስኪፈጸም፡ድረስ።ደህች፡ናት፡መጀመርያዪቱ፡ ትንሣኤ።። ፭፡ ቀር፡ ፲፭፡ ፳፫፡፡ ፭፡ተሰ፡ ፬፡ ፲፯፡፡

፮፡ ከመጀመርያዪቱ፡ ትንሣኤ፡እድል፡ያለው፡ ብ ፁዕ፡ቅዱስም፡ ነው። በእሌሀ፡ ላይ፡ ሁለተኛዪቱ፡ ሞ ት፡ ሥልጣን፡ የላትም፡ የእግዚአብሔርና፡ የክርስተ ስ፡*ካህናት፡ደሆናሉ፡እንጅ፡ከርሱም፡ጋራ፡ሸህ፡ አመ ት፡ ደነግሣሉ። *ም፡ ፭፡ ፲፡፡

፯፡ ሸህ፡አመትም፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡ሰይጣኑ፡ ከሠ ራቱ፡ ደፈታል።

፰፡ ባራቱ፡ ምድር፡ ማዝንም፡ ያሉትን፡ አሕዛብ፡ ለማሳት፡ደወጣል፡*ጎግንና፡ማጎግን፡ለሰልፍ፡ ደሰበሰ ባቸው፡ ዘንድ፡ቍጥራቸው፡ እንደ፡ ተባሕር፡ አሻዋ፡የ ሚሆን።። *ሕዝ፡ ፴፰፡ ፪፡፡ ተሕዝ፡፴፰፡ ፱፡ ፲፭፡፡

፱፡ በሰፈ፡ምድር፡ ላይም፡ ወጡ፡ የቅዲሳንንም፡ ጭፍሮች፡ ከበቡ፡ የተወደደችውንም፡ አገር፡ *አሳት ም፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ከሰማይ፡ወርዶ፡ በላቻ ቸው።። *ሕዝ፡ ፴፰፡ ፳፱፡፡ ና፡ ፴፱፡ ፮፡፡ ዘካ፡ ፲፪፡ ፱፡፡

፲፡ ዲያብሉስም፡ያሳታቸው፡ በዲንና፡በአሳት፡ፈ ሳበ፡ወንዝ፡ተጣለ።*አርዌውና፡ አሰተኛው፡ነቢይ፡ወ ደሉበት። ቀንና፡ ሌትም፡ ተደሣቀያሉ፡ ለዘላለም።። *ም፡ ፲፱፡ ፳፡፡ ተም፡ ፲፱፡ ፲፡ ፲፭፡፡

፲፭፡ ታላቅ፡ነጭ፡ ዙፈንም፡ አየሁ።። የተቀመጠበት ንም፡ከፈ.ት።*ምድር፡የሸሸት፡ሰማይም፡ ቦታም፡አል ተገኘላቸውም።። *ማቴ፡ ፳፭፡ ፴፩፡—፴፡፡ ፪፡ ጴጥ፡ ፫፡ ፯፡—፲፪፡፡

፲፪፡ ሙታንንም፡ አየሁ፡ ታናሾችን፡ ታላቅቾንም፡ *በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ቁመው። መጻሕፍትም፡ ተ ከፈቱ።። ሌላውም፡ ተመጽሐፍ፡ ተከፈተ፡ እርሱም፡ የሕይወት፡ መጽሐፍ።። ሙታንም፡ ተፈረዷ፡ በመጻ ሕፍት፡ተጽፎ፡እንደ፡ነበረ፡ እንደ፡**ሰሪት፡ መጠን።። *ያን፡ ፯፡ ፲፡ ፳፪፡፡ ተም፡ ፫፡ ፭፡፡ ፊል፡ ፬፡ ፫፡፡ **ሮሚ፡ ፪፡ ፮፡፡

፲፫፡ ባሕርም፡በርሱ፡ያሉትን፡ሙታን፡ሰጠ።። ሞት ና፡ሲኦልም፡ በርሳቸው፡ ያሉትን፡ ሙታን፡ ሰጡ።። ከር ሳቸውም፡ሁሉ፡ኢያንደንዷ፡እንደ፡ ሰራው፡ መጠን። ተፈረደበት።

፲፬፡ *ሞትና፡ ሲኦልም፡ በእሳት፡ ባሕር፡ ተጣሉ። ደህች፡ ናት፡ሁለተኛዪቱ፡ ሞት።

*፭፡ ቀሮ፡ ፲፭፡ ፳፯፡ ፶፱፡ ፶፰፡፡

፲፭፡ ማንም፡ በሕይወት፡ መጽሐፈ፡ ተጽፎ፡ ባይገ ኝ፡በእሳት፡ ባሕር፡ ተጣለ።። *ም፡ ፲፱፡ ፳፡፡ ማቴ፡ ፳፭፡ ፴፭፡፡

ምዕራፍ፡ ፳፩፡

፩፡ *አዲስ፡ ሰማይም፡ አዲስ፡ ምድርም፡ አየሁ። የፊተኛዪቱ፡ ሰማይ፡ተየፊተኛዪቱም፡ ምድር፡አልፈ ለችና። ባሕርም፡ አንጊደህ፡ አይገኝም።።

*ኢሳ፡ ፷፭፡ ፲፯፡ ፪፡ ጴጥ፡ ፫፡ ፲፫፡፡ ተም፡ ፳፡ ፲፭፡፡

፪፡ አኔም፡ዮሐንስ፡ የተቀደሰችውን፡አገር፡ አየሁ፡ አዲሲቱን፡*የረሳሌምን፡ከሰማይ፡ስትወርድ፡ተከአ ግዚአብሔር፡ዘንድ፡ተዘጋጅታ፡ለባልዋ፡ አንደጌጸች፡ **ሙሽራ።። *ዕብ፡ ፲፩፡ ፲፡ ፲፮፡፡ ተዕብ፡ ፲፪፡ ፳፪፡፡ ገላት፡ ፬፡ ፳፯፡፡ **ም፡ ፲፱፡ ፯፡ ፳፡፡

፫፡ ከሰማይም፡ ታላቅ፡ ድምጽ፡ ሰማሁ፡ አንደህ፡ ሲል። እነኋት፡ የእግዚአብሔር፡ ድንኳን፡ ከሰዎች፡ ጋራ።ከርሳቸውም፡ ጋራ፡ *ያድራል። እርሳቸውም፡ ወ ገኖቹ፡ደሆናሉ።ተእግዚአብሔርም፡ እርሱ፡ አምላካ ቸው፡ከርሳቸው፡ጋራ፡ ደሆናል።። *ሕዝ፡ ፴፯፡ ፳፯፡፡ ተም፡ ፯፡ ፲፯፡፡ ኢሳ፡ ፳፭፡ ፳፡፡

፬፡ *እግዚአብሔርም፡ እንብን፡ ሁሉ፡ ካደናቸው፡ ያብሳል። ሞትም፡ አንጊደህ፡ አደሆንም፡ ልቅሶም፡ ጩኸትም፡መጣጣርም፡ እንጊደህ፡ አደሆንም።። የቀ ደመው፡ ሒድዋልና።። ኢሳ፡ ፴፭፡ ፲፡፡

፭፡ *በዙፈን፡ላይ፡ የተቀመጠውም፡ አለ። እነሆ፡ ሁሉን፡ተአደስ፡አደርጋለሁ። አለኝም። ጸፏ። ደህ፡ነገ ር፡አውነት፡ የታመነም፡ ሁንዋልና።። *ም፡ ፬፡ ፪፡ ፬፡፡ ና፡ ፭፡ ፭፡፡ ተ፪፡ ቀሮ፡ ፭፡ ፲፯፡—፳፭፡፡

፮፡ አለኝም።ፈጽሞ፡ሆነ። *እኔ፡ነኝ፡አልፈ፡ ፀሚጋ ም። መጀመርያ፡ መጨረሻም። እኔ፡ ለተጸማ፡ ከሕ ደወት፡ ውኃ፡ ምንጭ፡ነከንጉ፡ እሰጣለሁ።

*ም፡ ፭፡ ፶፡፡

፯፡ *ድል፡ የነሣ፡ ሁሉን፡ ደወርሳል። ተእኔም፡ አም ላክ፡ እሆነዋለሁ፡ እርሱም፡ ልጀ፡ ደሆናል።

*ም፡ ፪፡ ፶፡፡ ተዘካ፡ ፰፡ ፰፡፡

፳፡ *የሚፈሩ፡ግን፡የማያምኑም፡ የተጸሉም። ተየ
ሚገድሉም። አመንዝሮችም። አስማተኞችም። ጣ
ዖት፡ የሚያመልኩም ። አሰተኞችም፡ ሁሉ። እድ
ላቸው፡ በደ.ንና፡ **በእሳት፡ ወደምትቃጠል፡ ባሕር፡
ነው።እርስዋ፡ ሁለተኛ፡ሞት፡ የምትሆን።
*ዕብ፡ ፲፡ ፴፳፡ ፴፱፡፡ ተም፡ ፳፪፡ ፲፭፡፡ **ም፡ ፳፡ ፲፱፡፡

፴፡ አንደ.ም፡ ከሰባቱ፡ *መላእክት፡ ወደኔ፡ መጣ፡
የኋለኛዪቱን፡ ሰባት፡ መቅሠፍት፡ የመላች፡ ሰባት፡
ጽና፡ ከያዙት፡ ከኔም፡ ጋራ፡ተናገረ፡ እንደህ፡ሲል። ና፡
ተሙሽራዪቱን፡ አሳይህ፡ የበጉን፡ ምስት።
*ም፡ ፲፭፡ ፩፡ ፮፡ ፯፡፡ ተም፡ ፲፱፡ ፯፡፡

፲፡ በመንፈስም፡ ወደ፡ *ታላቅ፡ ወደ፡ ረጅም፡ ተራ
ራ፡ወሰደኝ፡ ታላቂቱንም፡ አገር፡ አሳየኝ፡ የተቀደሰች
ውን፡የፈሳሌምን፡ከሰማደ፡ ሰትወርድ፡ ከእግዚአብ
ሔር፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔርም፡ ክብር፡ አለባት።
*ሕዝ፡ ፴፡ ፪፡፡

፲፭፡ *ብርሃንዋም፡ እጅግ፡ እንደ፡ ከበረ፡ ደንጊያ፡
ነው። እንደ፡ ጸራ፡እንደ፡ ኢያስጲሰ፡ደንጊያ።
*ቀ። ፳፫፡፡ ሕዝ፡ ፶፳፡ ፶፭፡፡

፲፪፡ ለርስዋም ፡ ታላቅ፡ ረጅም፡ ቅጥር፡ አለባት።
*አሥራ፡ ሁለትም፡ ደጀች፡ አልዋት። በደጀችዋም፡
ላይ፡አሠራ፡ሁለት፡መላእክት፡አሉ፡ ሰሞችም፡ ተጽ
ፈውባቸዋል። ያሠራ፡ ሁለቱ፡ የአሥራኤል፡ ልጀች፡
ወገን፡ ሰሞች። *ሕዝ፡ ፶፰፡ ፶፭፡፡

፲፫፡ በምሥራቅ፡ ሶስት፡ ደጀች። በሰሜን፡ ሶስት፡
ደጀች። በደቡብ፡ ሳስት፡ ደጀች። በምዕራብ። ሶስት፡
ደጀች።

፲፬፡ ያገሪቱም፡ቅጽር፡ አሠራ፡ሁለት፡ መሠረቶች፡
አልዋቸው። በርሳቸውም፡ ላይ፡ ያሠራ፡ ሁለቱ፡ የበ
ጉ፡ ሐዋርያት፡ ሰሞች፡ አሉባቸው።

፲፭፡ ከኔም፡ጋራ፡ይናገር፡*የነበረው፡የወርቅ፡ ዘንግ፡
ይዞ፡ ነበረ፡ አገሪቱን፡ ይለካ፡ ዘንድ፡ ደጀችዋንም፡ ቅ
ጽርዋንም። *ሕዝ፡ ፵፡ ፫፡፡

፲፮፡ አገሪቱም፡ *አራት፡ማዝን፡ ነበረች። ርዝመት
ዋም፡በወርድዋ፡ እኩል፡ ነው። አገሪቱንም፡ በዘንግ፡
ለካት፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ሸህ፡ ምዕራፍ፡ የሚሆን፡ ርዝ
መትዋ፡ ወርድዋም፡ ከፍታዋም፡ የተካከለ፡ ነው።
*ሕዝ፡ ፵፰፡ ፲፯፡ ፲፯፡፡

፲፯፡ ቅጽርዋንም፡ለካ፡መቶ፡ አርባ፡አራት፡ ክንድ፡
በሰው፡ ልክ፡ እርሱም፡ በመልአክ፡ ልክ።

፲፰፡ የቅጽርዋም፡ ሰራ፡ በኢያስጲሰ፡ ደንጊያ፡ ነበ
ረ። አገሪቱም፡ ከጽረ፡ ወርቅ፡ ና፡ት፡ ጽረ፡ ብርጭቅ፡ የ
ሚመስል።

፲፱፡ ያገሪቱም፡ ቅጽር፡ መሠረቶች፡ በከበረ፡ ደንጊ
ያ፡ሁሉ፡ *ተጌጽዋል። መጀመርያው፡ መሠረት፡ ኢያ
ስጲስ፡ ነው። ሁለተኛው፡ ሰፈርስ። ሶስተኛው፡ ከል
ቄያን።አራተኛው፡መረግድ። ኢሳ፡ ፶፱፡ ፲፭፡ ፲፪፡፡

፳፡ አምስተኛው፡ ሰርደንክሶስ ። ስድስተኛው፡
ሰርድዮን።ሰባተኛው፡ ክሪሶሊት። ስምንተኛው፡ በሪ
ሉ። ዘጠነኛው፡ ተጳዚዮን። አሥረኛው፡ክሪሶጵራሰ።
አሠራ ፡ አንደኛው ፡ ሀያክንተስ ። አሠራ ፡ ሁለተኛ
ው፡ አሜቲስጦስ።

፳፩፡ አሠራ፡ሁለቱም፡ ደጀች፡ አሠራ፡ ሁለት፡ ሉ
ል፡ናቸው። ደጂ፡ኢያንደንደ፡ አንድ፡አንድ፡ ሉል፡ ነበ
ረ።*ያገሪቱም፡አደባባይ፡ በጽረ፡ ወርቅ፡ ነበረ፡ እንደ፡
ጽረ፡ ብርጭቅ።
ም፡ ፳፪፡ ፪፡፡

፳፪፡ መቅደስም፡አላየሁባትም።እግዚአብሔር፡አ
ምላክ፡ሁሉን፡ የሚደዝ፡መቅደሰዋ፡ ነው፡ና፡ በጉም።

፳፫፡ አገሪቱም፡ ጸሐይ፡ ጨረቃም፡ ያበረሳት፡ ዘን
ድ፡አትሻም። የእግዚአብሔር፡ ክብር፡ አብርተላታል
ና፡ መብራትዋም፡ በጉ፡ ነውና።
ም፡ ፳፪፡ ፭፡፡

ኢሳ፡ ፷፡ ፲፱፡፡ ና፡ ፮፡ ፲፱፡ ፳፡፡

፳፬፡ የደኑም፡ አሕዛብ፡ በብርሃንዋ፡ ይሔደሉ። የ
ምድርም፡ነገሥታት፡ክብራቸውን፡ ባለጠግነታቸው
ንም፡ ወደርስዋ፡ ያመጣሉ።
ኢሳ፡ ፮፡ ፫፡ ፭፡፡

፳፭፡ ደጀችዋም፡በቀን፡አደዘንም። ሌት፡ ከዚያ፡
የለምና። ኢሳ፡ ፮፡ ፲፩፡፡ ዘካ፡ ፲፬፡ ፯፡፡ ራእ፡ ፳፪፡ ፭፡፡

፳፮፡ የአሕዛብንም፡ ክብር፡ ምስጋናቸውንም፡ ወ
ደርስዋ፡ ያመጣሉ።

፳፯፡ ርኩስም፡ሁሉ፡ አይገባባትም፡ ጽድፈኖ፡ሐጎ
ት፡ የሚያደርግም፡ በበጉ፡ ሕይወት፡ መጽሐፍ፡ ከተ
ጻፈት፡በቀር።
ም፡ ፮፡ ፲፭፡፡ ፊል፡ ፱፡ ፫—፬፡፡

ምዕራፍ፡ ፳፪፡

፩፡ *ጽረ፡ ፈሳሽም፡ አሳየኝ፡ከሕይወት፡ ውኃ፡እን
ደ፡ባሎር፡ የሚያበራ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዙፋን፡ ከበ
ጉም፡ ሲወጣ። *ሕዝ፡ ፶፯፡ ፲፪፡፡ ዘካ፡ ፲፬፡ ፰፡፡

፪፡ *ባደባባይዋም፡ መካከል፡ በፈሳሽ፡ ወንዝም፡
ደር፡ ወደ.ሀና፡ወደ.ያ፡ የሕይወት፡ ዛፍ፡ አለች። አሠ
ራ፡ ሁለት፡ ፍሬም፡ ትሰጣለች፡ በወር፡ በወርም፡ ታፈ
ራለች።የዛፈቱም፡ተቅጠል፡የአሕዛብ፡ፈውስ፡ነው።
*ም፡ ፳፭፡ ፶፭፡፡ †ሕዝ፡ ፵፯፡ ፲፪፡፡

፫፡ *መርገምም፡ ሁሉ፡ ከዚያ፡በኋላ፡ አደሆንም።
የእግዚአብሔርና፡ የበጉም፡ ዙፋን፡ በርሰዋ፡ ደያ
ል፡ባሮቹም፡ያመልኩታል።
*ዘካ፡ ፲፬፡ ፲፭፡፡

፬፡ ፊቱንም፡*ደዩታል፡ ተስሙም፡በግምባራቸው፡
ተጽፏዋል።
*ም፡ ፳፭፡ ፫፡፡ †ም፡ ፫፡ ፲፪፡፡

፭፡ *ሌትም፡ ከዚያ፡አደሆንም። መብራትም፡ አ
ደቸም፡ የጸሓይንም፡ ብርሃን። እግዚአብሔር፡አም
ላክ፡ ያበራላቸዋልና። ለዘላለሙም፡ †ደነግሣሉ።
*ም፡ ፳፭፡ ፲፭፡፡ †ም፡ ፭፡ ፲፡፡ ደን፡ ፯፡ ፲፳፡ ፳፯፡፡

፮፡ አለኝም። ደህ፡ ነገር፡ እውነተኛ፡ የታመነም፡
ነው፡ እግዚአብሔርም፡የቅዱሳን፡ነቢያት፡ አምላክ፡
*መልአኩን፡ ሰደደ፡ ፈጥና፡ ይሆን፡ ዘንድ፡የሚገባው
ን፡ለባሮቹ፡ ያገልጥ፡ ዘንድ።
*ም፡ ፭፡ ፩፡፡

፯፡ አነሆኝ፡አኔ፡ ፈጥኜ፡ እመጣለሁ። የዚህን፡ መ
ጽሐፍ፡ ትንቢት፡ ነገር፡ የሚጠብቅ፡ ብፁዕ፡ነው።
ቀ። ፲፱፡ ፳፡፡ ም፡ ፫፡ ፲፭፡፡ ና፡ ፭፡ ፫፡፡

፹፤ እኔ፡ዮሐንስ፡ ነኝ፡ የሀችን፡ ያየሁ፡ የሰማኋት ም። ባየሁም፡ በሰማሁም፡ ጊዜ፡ ይህችን፡ ይገልጥል ኝ፡በነበረው፡በመልአኩ፡ *እግር፡ ፊት፡ እሰግድ፡ዘን ድ፡ወደቅሁ። *ም፡ ፲፪፤ ፲፡፡

፪፤ አለኝም። ተመልከት፡ አታድርገው። እኔ፡ አን ደንተ፡ ባርያ፡ ነኝና፡ እንደ፡ ወንድሞችህም፡ እንደ፡ ነቢያት። የዚህንም፡ መጽሐፍ፡ ነገር፡ እንደሚጠብ ቁ። ለእግዚአብሔር፡ ስገድ።

፲፡ አለኝም። የዚህን፡ መጽሐፍ፡ ትንቢት፡ ነገር፡ አትቍልፈ። ዘመኑ፡ ቀርብዋልና።

፲፩፤ ግፈ፡ የሚሰራ፡ግፈ፡ይሰራ፡ደግሞ። ርኩስም፡ የሚሆን፡ርኩስ፡ይሁን፡ደግሞ። ጻድቁም፡ይጸድቅ፡ ደግሞ። ቅዱሱም፡ ይቀደስ፡ ደግሞ።

፲፪፤ *እነሆኝም፡ ፈጥኜ፡እመጣለሁ፡ ዋጋዬም፡ ከ እኔ፡ጋራ፡ ነው፡ ለሁሉ፡ ኢያንጃንጂ፡ እንደ፡ስራው፡ ተአ ስጠው። ዘንድ። *ቍ፡ ፲፯፡፡ ም፡ ር፡ ፲፭፡፡ †ሮሚ፡ ፪፡ ፮፤—፲፭፡፡

፲፫፤ እኔ፡ ነኝ፡ አልፋ፡ ዖሜጋም፡ መጀመርያ፡ መጨ ረሻም። የፈተኖው፡ የኋለኛውም። ም፡ ፭፡ ፱፤ ፳፡፡

፲፬፤ ትእዛዙን፡የሚያደርጉ፡ብፁዓን፡ ናቸው። ሥ ልጣናቸው፡ በሕይወት፡ ዛፍ፡ ላይ፡ ይሆን፡ ዘንድ። በ ደጅም፡ ወደ፡ ከተማ፡ ይገባሉ። ም፡ ፲፫፡ ፲፡፡

፲፭፤ በሚደዋ፡ ግን፡ ናቸው፡ ውሾች፡ አስማተኞች ም፡ አመንዝሮችም፡ ነፍሰ፡ ገደሎችም፡ ጣዖት፡ የሚ ያመልኩም፡ አሰትም፡ የሚወድ፡ ሁሉ፡ የሚያደርገ ውም። ም፡ ፳፭፤ ፳፡ ፳፯፡፡ ፭፤ ቀር፡ ፮፤ ፱፤ ፲፡፡

፲፯፤ እኔ፡ የሱስ፡ *መልአኬን፡ ላክሁ፡ ይህችን፡ ተደ መሰክርላችሁ፡ዘንድ፡በአብያተ፡ክርስቲያናት። እኔ፡ የደዊት፡ **ሥር፡ ዘረም፡ ነኝ፡ የሚያበራ፡ የንጋት፡ ተተኰከብ። *ም፡ ፭፤ ፭፡፡ ተም፡ ፭፤ ፱፡፡ **ኢሳ፡ ፲፩፤ ፲፡፡ ራእ፡ ፭፤ ፭፡፡ ††ሉቃ፡ ፭፤ ፫፳፡፡

፲፯፤ *መንፈስም፡ ሙሽራዪቱም፡ ይላሉ። ና። የ ሚሰማም፡ ይበል። ና። ተየተጸማም፡ ይምጣ። የወ ደደም፡ የሕይወት፡ ውኃ፡ በነጻቱ፡ ይውሰድ።

*ሮሚ፡ ፳፤ ፳፫፡፡ ተም፡ ፸፭፤ ፯፡፡ ኢሳ፡ ፶፭፤ ፭፡፡ ዮሐ፡ ፯፤ ፴፯፡፡

፲፰፤ የዚህን፡ መጽሐፍ፡ ትንቢት፡ነገር፡ ለሚሰማ ሁሉ፡ እመሰክራለሁና። ማንም፡ በዚህ፡ ላይ፡ አንደ ች፡ ቢጨምር፡አግዚአብሔር፡ *በዚህ፡ መጽሐፍ፡የተ ጻፈውን፡ መቅሠፍት፡ ይጨምርበታል።

*ም፡ ፲፭፤ ፭፤ ፯፤—፳፡፡

፲፱፤ ደግም፡ *ማንም፡አንደች፡ከዚህ፡ትንቢት፡መ ጽሐፍ፡ነገር፡ቢያጐድል፡ እግዚአብሔር፡ ከሕይወት፡ መጽሐፍ፡ ከተቀደሰችውም፡ አገር፡ ተመክፈልትን፡ ያጐድልበታል፡ በዚህ፡ መጽሐፍም፡ ከተጻፈው።

*ዘጸግ፡ ፬፤ ፪፡፡ ና፡ ፲፪፡ ፹፪፡፡ †ፊል፡ ፬፤ ር፡፡

፳፡ በዚህ፡ የሚመሰክረው፡ ይላል። አዎን፡ ፈጥ ኜ፡እመጣለሁ።አሜን። አዎን፡ጌታ፡ሆይ፡ የሱስ፡ና።

፳፩፤ የጌታ፡ የየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጸጋ፡ ከሁላችሁ፡ ጋ ራ፡ትሁን። አሜን።

ተፈጸመች ፡ የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ አጸቃሊጵሲስ።

220.46
B 777
24904
BRITISH & FOREIGN BIBLE SOCIETY
AUTHOR
Bible (Complete) in Ethiopian
TITLE

DATE DUE	BORROWER'S NAME
	[redacted]
MAR 31 1976	CCSC MAY 13 1976
JUN 2 - 1981	AUG 10 1981 PUTS Bob Zahl 12989
JUL 3 1 1984	Pat Toby Leibert SFTS
SEP 10 1984	JAN 3 1985 RENEWED

220.46
B 777

24904

GRADUATE THEOLOGICAL UNION LIBRARY
BERKELEY, CA 94709